# የግጭት መንስኤዎችና መፍትሔዎቻቸው በጋብቻ ውስጥ!
# Causes of Conflict and Suggested Solutions in Marriage!

ፓስተር ዶ/ር ሙላቱ በላይነህ
(ላይሰንስድ ክሊኒካል ፓስቶራል ካውንስለር)
ካሊፎርንያ ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ
ግንቦት 5, 2007 ዓ.ም

Pastor Dr. Mulatu Belayneh, Licensed Clinical Pastoral Counselor- Advanced Certified (LCPC)
California, United States of America
May 13, 2015

# ቅጽ.1፡ - " በመጀመሪያዎቹ አስርተ ዓመታት የጋብቻ ዘመናት ላይ ሊፈጠሩ የሚችሉ ግጭቶች፣ የግጭት መንስኤዎችና መፍትሔዎቻቸው!"


ፓስተር ዶ/ር ሙላቱ በላይነህ
(ላይሰንስድ ክሊኒካል ፓስቶራል ካውንስለር)
ካሊፎርንያ ዩናይትድ ስቴትስ አፍ አሜሪካ


ግንቦት 5, 2007 ዓ.ም

# The Most Common Areas of Conflicts in the First Ten Years of Marriage and Suggested Solutions!"


Pastor Dr. Mulatu Belayneh, Licensed Clinical Pastoral Counselor- Advanced Certified (LCPC)
California, United States of America


May 13, 2015


Printed in California, United States of America
Bang printing
28210 N. Avenu Stanford
Valencia, CA 91355



Copyright
All rights reserved. No part of this book may be reproduced in any form or by any electronic or mechanical means, including information storage and retrieval systems, without permission in writing from the publisher, except by a reviewer who may quote brief passages in a review.
አሳታሚው የጽሑፍ ፈቃድ ካልሰጠ በስተቀር ከዚህ መጽሐፍ ውስጥ በከፊልም ሆነ በሙሉ ማባዛት፣ በኤሌክትሮኒክስ ውጤቶች መቅረጽና ማራባት የተከለከለ ነው፡፡



Editing:-Desyibelew Demmissie
Texting Formating: Yared Gezai
Cover Design: Asfaw Berhe


## መታሰቢያነቱ

1. የእግዚአብሔር ድንቅ ስጦታና የትዳር አጋር ለሆነች ለባለቤቴ ለእመቤት ታደሰ( እሙ) በእኔ አጠራር " እናት" የትዳርንን ምንነት፣ በረከትነት፣ በሕይወትና በአገልግሎት በሚገጥሙ በከፍታም ሆነ በዝቅታ፣ በጤንነትም ሆነ በሕመም፣ በማግኘትና በማጣት፣ በስኬትና ባልተሳካ ወቅት፣ በሕይወት በሚገጥሙና በሚፈራረቁ የተለያዩ ገጽታዎች ሁሉ ታማኝ ሚስት፣ እናት፣ እህት፣ ጓደኛና በእውነተኛ ልብና አመለካከት መካሪና ገሳጻጭ ለሆነችና እንዲሁም እውነተኛ የትዳርን ምንነት፣ አስፈላጊነትና ተግዳሮት በጋራ እንድለማመድ ዕድል ለሰጠችኝ ለሚስቴ ይሁን!!
2. የአምላክ ዕጹብ ድንቅ ፍጡርና ስጦታ ለሆኑ ለሁለት ወንድ ልጆችችን ለናታንና ለኖህ ሙላቱ ( To Nathan & Noah Mulatu) የአባትነት ወግ፣ ሚናና ኃላፊነት እንድለማመድ፤ ደግሞም የእግዚአብሔርን አባትነት ለእኛም ሆነ ለልጆቻችን እንዴት እንደሆነ ይበልጥ እንድረዳና በአባትነቱ እንድደነቅ ዕድል ለሰጡኝ ለልጆቻችን ይሁልንኝ!

## ስጦታ

ከ፡_______________________

ለ፡_______________________

ቀን፡_______________________

ፊርማ፡_______________________

## የአንባቢያን አስተያየት

ጋብቻ ባልና ሚስት ጨርሰው የማይመረቁበት ትምህርት ቤት ነው:: በተለይ ተጋቢዎች በመጀመሪያዎቹ የጋብቻ ዕድሜያቸው ብዙ የማያውቁትና ያልተለማመዱት ነገር ስለሚኖር፣ በቀላሉ ሊፈቱ የሚችሉ ግጭቶች ግንኙነታቸውን አደጋ ላይ ሊጥሉ ይችላሉ። ይህ መጽሐፍ በዚህ ወቅት የሚከሰቱ ግጭቶችንና መንስኤዎቻቸውን በመተንተን የመፍትሔ አቅጣጫዎችን ይጠቁማል። ስለዚህ ባለማወቅ ምክንያት የሚከሰተውን የጋብቻ ችግሮችንና አሉታዊ ውጤቶቹን ለመቅረፍና ለማስወገድ የሚያግዛችሁን ይህን መጽሐፍ እንድታነቡ እመክራለሁ::

**ከበደ በከሬ**
**የሥነልቦና አማካሪና ፀሐፊ**

የዚህች መጽሐፍ ዋና ዓላማ በትዳር ውስጥ የሚያጋጥሙ ግጭቶች ምንነትን፣ መንስኤዎቻቸውንና መፍትሔዎቻቸውን በዝርዝር በማለጥ ክርስቲያን ትዳራቸውን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድና ምሪት በማስተዳደር የተባረከ ሕይወት ለመኖር እንዲችሉ ነው። ዶ/ር ሙላቱ ይህንን ትምህርት ዋና ዋና መመሪያ የሆኑትን ነጥቦች በአራት ዓበይት ክፍሎች የግጭት ዓይነቶች፣ መንስኤዎቻቸውንና ከነመፍትሔቻቸው አንባቢው ሊረዳውና ሊጠቀምበት በሚችልበት መንገድ በዝርዝር አቅርቧል። ግጭት በመላው ጋብቻ ዘመን ሁሉ የሚከሰት ስለሆነ በጋብቻ ዘመናት ሁሉ ለሚገኙትም የሚጠቅም ነው። አብያተ ክርስቲያናት የአባላቶቻቸውን የትዳር ሕይወት ለማሳደግና ጽኑ ቤተሰብን ለማፍራት ሲያስተምሩ ይህችን መጽሐፍ እንደ ማስተማሪያ መጽሐፍ ቢጠቀሙባት በጣም ትረዳለች።

**ሥዩም ገብረየሱስ**
**የቤተሰብ ኅብረት አገልግሎት ክፍል የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ባፕትስት ቤተ ክርስቲያን ዳላስ ቴክሳስ**

ይህን መጽሐፍ ትዳራችንን እንደ እግዚአብሔር ሰው በመንፈሳዊ እንደ ባለ አእምሮ በጥበብ ለመምራት ጠቃሚ ነው።

**ዶ/ር ብሩክ ታፈሰ አማረ (M.D)**
**የማህጸን ስፔሻሊስትና አሁን ደግሞ በሰሜን አሜሪካ የውስጥ ደዌ ሐኪም**

ክርስቲያናዊ ትዳር ለመመሥረት ለምታስቡ ሰዎች፣ ከጋብቻ በኋላ በተለያዩ ትዳር ነክ ችግሮች ውስጥ በማለፍ ላላችሁ ባለትዳሮች፣ እንዲሁም በትዳርና በቤተሰብ ዙሪያ የማስተማርና የማማከር ሸክም ለተቀበላችሁ አገልጋዮች ሰፋ ያለና ጠቃሚ እውቀት የያዘች መጽሐፍ በመሆንዋን ስለተገነዘብሁ በእጃችሁ ውስጥ እንድትገባ አሳስባለሁ።

**ኢንጅነር ተካ ገብሩ የጋብቻና ቤተሰብ አማካሪ**

የትዳር ሕይወት ምን መሆን እንደሚገባና ሚዛኑን በጠበቀ ደረጃ የተሰናዳ የሚያስተምር መጽሐፍ እንደሆነ አንብቤዋለሁ እንዲሁም ሁሉም በጋብቻ ውስጥ ያሉ ሁሉ ቢያነቡት ተጠቃሚ ይሆናሉ እላለሁ።

**ፓስተር አሸብር በላይነህ**

**መ/ቅ/ዓ/አ/ቤ.ክ የትምህርት ክፍል ዋና ኃላፊና በአመራር የድህረ ምረቃ ዲግሪ ተማሪ**

ዶ/ር ሙላቱ በትዳር ውስጥ የሚነሱትን ግጭቶች በፍች ከማሳረግ ይልቅ እንደመረማመጃ ድንጋዮች በመጠቀም ወደፊት ለመስፈንጠር የሚረዱ እጅግ ጠቃሚ ትምህርቶችንና ምክሮችን አብርክቶልናል። አንኳር የሚባሉ ጉዳዮችን አንስቶ የግጭቶችን ውል እያስጨበጠና ውስብስቡን መፍቻ መንገድ እየጠቆመ ሩጫ አቋርጦ ከመሸነፍ ማሸነፍ የሚቻልበትን ቀና ጎዳና እንድንይዝ በጥበብና በእውቀት አቅጣጫዎችን አመላክቶናል። በማንበቤ ልብ ብያለሁ አንብቡና ልብ በሉ!

**ወንድም ዮናስ አረፋይኔ የኢትዮጵያ ጉባኤ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ዋና ጸሐፊ**

በተለያየ የዕድሜ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ክርስቲያኖች ከትዳር ሕይወት ጋር በተያያዘ ሁለንተናዊ የሆነ እይታ የሚሰጥና ችግሮችንም ሆነ መፍትሔዎቻቸውን በጥልቀት የሚያሳይ ጥናትን መሠረት አድርጎ በአማርኛ የተጻፈ መጽሐፍ ማግኘት አስቸጋሪ ሆኖ ይታያል፡፡ ከዚህ አኳያ ይህ የዶ/ር ሙላቱ በላይነህ መጽሐፍ ያለውን ክፍተት ለመሙላት አንድ እርምጃ ነው፡፡ መጽሐፉ በተለይ የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጆችና ት/ቤቶች፣ ሰባኪዎች፣ አስተማሪዎችና የጋብቻ አማካሪዎች ለማስተማሪያ ቢጠቀሙበት የሚረዳቸው በርካታ መረጃዎችንና ትምህርቶችን የያዘ ጠቃሚ መጽሐፍ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡

**ዶ/ር ንጉሤ ተፈራ(PhD)**

ይህ መጽሐፍ የአሳብ ፍሰቱ፣ የአጻጻፉና የአቀራረቡ ብስለትና ጥራት ያለው ከመሆኑም በላይ የእግዚአብሔርን ቃል ማዕከል ያደረገ ስለሆነ በጋብቻ ውስጥ ግጭትን እየፈቱ ደስተኛና ጤነኛ የትዳሩ ግንኙነት እንዲኖራቸው ለሚሹ ጥንዶች ሁሉ መሠረታዊ እውቀትን የሚያስጨብጥና ወቅታዊ መጽሐፍ ነው። የመጽሐፉ ዝግጅት ጥንዶች በግል በጥሞና ጊዜያቸው፣ በቤተ ክርስቲያን ያሉ ባለትዳሮች በቡድን በመሆን ሊያጠኑትና ሊወያዩበት የሚችሉበትና የቤተ ክርስቲያን መጋቢዎች፣ አስተማሪዎች፣ የጋብቻና የቤተሰብ አማካሪዎች እንዲጠቀሙበት ሆኖ የተዘጋጀ ብዙ ቁም ነገሮችን ያዘለ መጽሐፍ መሆኑን ተመልክቻለሁ።

**እህት ደብረወርቅ መኮንን የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ኅብረት ቤተ ክርስቲያን የቤተሰብና የማማከር አገልግሎት ክፍል ሎስ አንጀለስ**

ፓስተር ሙላቱ በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረተ፣ በብዙ ትክክለኛ ሳይንሳዊ መረጃዎችም የተደገፈ ፣ለትዳር ስለልጆች አስተዳደግና ልጅ ከመውለድ በኃላ በእናቶች ጤና ላይ ሊከሰቱ የሚችሉትን የጤና እክሎች፥ መንስሔዎችና መፍትሔዎቻቸውን በቀላሉ ለመረዳትና አሳቡን ለመከተል በሚያስችል መልኩ ይህን መጽሐፍ አቅርቦልና። ይህን መጽሐፍ ወደ ትዳር ሊገቡ በዝግጅት ላይ ያሉና በማንኛውም የጋብቻ ዘመን ያለን ሁላችን ይህንን መጽሐፍ አንብበን ተጠቃሚዎች እንድንሆን አበረታታለሁ።

**ዶ/ር ደረጀ ሳህለ አዮ( M.D)**

**Pulimonary Disease, Critical Care and sleep Disorder Fort Worth lung Clinic**

ይህ መጽሐፍ አብዛኛውን ቤተሰብ ነክ የሆኑ ጉዳዮችን ሰፋ ባለ ሁኔታ የሚዳስስ ፣ የጋብቻና የቤተሰብ ጉዳዮች ላይ ጠቃሚ እውነቶችንና ተግባራዊ የሆነ ግንዛቤዎችን የሚያስጨብጥ ሁኖ አግቸዋለሁ። በዚህ መጽሐፍ የተነሱት ዋና ዋን ርዕሶች መካከል ጥቂቱን በመጥቀስ ይበልጥ አስፈላጊነቱን ለማጉላት እፈልጋለሁ። የባለትዳሮች የአልጋ ጉዳይ ግልጥነትና ጨዋነት በተላበሰ ሁኔታ መቅረቡ፣ በጋብቻና በቤተሰብ ሕይወት ተግዳሮት የሆነዉን የዘመኑ ፈተና ስለፖርኖግራፊ በሰፊው መዳሰሱ፣ በሁሉም የግንኙነት መስመሮች ተግዳሮት የሚሆኑበትን የግጭት ምክንያቶችን ለመፍታት የሰመረ ተግባቦት አስፈላጊነትና በጋብቻና በቤተሰብ ሕይወት ትምህርት ፍችን በተመለከተ ከማውገዝና እግዚአብሔር የሚጠላው መሆኑን አበክሮ ከመናገር ያለፈ ብዙ አይባልም ነገር ግን በዚህ መጽሐፍ ዉስጥ ስለ ፍች የቀረበው መሠረታዊ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶች፣ የሚያስከትለው መጠነ ሰፊ ቀውስ፣ የተሰጡት የመፍትሔዎች አሳቦችና በተለይ ስለ ይቅርታ በተሰጠው ትምህርት ይቅርታን መለማመድ አማራጭ የሌለውን ክርስቲያናዊ ግዴታችንን መሆኑን በአጽንዎት የሚያሳስብ ሆኖ አግቸዋለሁ። ይህ መጽሐፍ ትዳር ለሚያስቡ፣ ትዳር ለጀመሩ፣ በትዳርም የቆየነውንና በማማከር አገልግሎት ላይ ያለነው ሁላችን ልናነበውና እንደ ማጣቀሻ ልንጠቀምበት የሚገባ መጽሐፍ ነው እላለሁ።

**ወ/ሮ ስንቅነሽ አዘነ**

**የቤተሰብ ሕይወትና የጋብቻ የማማከር አገልግሎት በኢ.ሙ.ወ.ማ.ቤ/ክ መካከለኛው ቀጠና አዲስ አበባ**

## ማውጫ

ገጽ


ክፍል አንድ(1):- የጋብቻ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረቶች ............ 1

ምዕራፍ አንድ(1):- የጋብቻ ትርጉምና መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረቱ ........ 2

I. የጋብቻ ምንነት ........ 2
II. ጋብቻ ለሰው ልጆች የተሰጠበት ዓላማ ........ 5
III. መጽሐፍ ቅዱሳዊ የጋብቻ መርህ ........ 6
IV. ጋብቻ የሚጠይቀው የየግል ኃላፊነትና ተጠያቂነት ........ 8
V. የጋብቻ አጠቃላይ ባህርይ /ተፈጥሮ/ ........ 9
VI. የጋብቻ የላቀ ምሳሌነት ........ 10

ክፍል ሁለት(2):- የግጭት መንስኤዎችና መፍትሔዎቻቸው 14

ምዕራፍ ሁለት(2):- የግጭት ምንነትና አይቀሬነት ........ 15

I. የግጭት ምንነት ........ 15
II. በባለትዳሮች መካከል የግጭት አይቀሬነት ........ 20

ምዕራፍ ሶስት(3):- ግጭትን በወቅቱ በጋራ ያለመፍታት የሚፈጥረው ተጽዕኖ ........ 34

I. በጥንዶች የፍቅር ግንኙነት ላይ ........ 34
II. በጥንዶች ሁለንተናዊ ማንነት ላይ ........ 37

ምዕራፍ አራት(4):- የተለያዩ የለውጥና የሽግግር ደረጃዎች ........ 42

I. የተለያዩ የለውጥ ደረጃዎች ምንነት ........ 42
II. በጥንዶች መካከል ሊፈጠሩ የሚችሉ የተለያዩ ለውጦች ........ 42
III. የተለያዩ ወቅታዊ የለውጥ ደረጃዎችና ባህሪያቸው ........ 46

ምዕራፍ አምስት(5):- በጋራ መወሰን /ውሳኔ አሰጣጥ/ ........ 53

I. በጋራ የመወሰን ምንነት ........ 53
II. በጋራ የመወሰን አስፈላጊነት ........ 53
III. በጋራ በመወሰን ሂደት ላይ ሊፈጠሩ የሚችሉ የግጭት መንስኤዎች ... 55
IV. በጋራ በመወሰን ሂደት ላይ ለሚፈጠሩ ግጭቶች መፍትሔዎች ........ 59

ምዕራፍ ስድስት(6):- የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ........ 64

I. ቤተሰብና የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ምንነት ........ 64
II. አባትንና እናትን መተው ........ 64
III. በቤተ ዘመድ ጣልቃ ገብነት ለግጭት ሊያጋልጡ የሚችሉ መንስኤዎች ........ 67
IV. በቤተ ዘመድ ጣልቃ ገብነት ለሚፈጠሩ ግጭቶች መፍትሔዎች ........ 71

**ምዕራፍ ሰባት(7)፡- ተግባቦት /ኮሙኒኬሽን/** ..... 76
I. የተግባቦት /የኮሙኒኬሽን/ ምንነት ..... 76
II. ከተግባቦት /ኮሙኒኬሽን/ ጋር ተያይዘው ሊፈጠሩ የሚችሉ የግጭት መንስኤዎች ..... 78
III. በተግባቦት /በኮሙኒኬሽን/ ላይ ለሚፈጠሩ ግጭቶች መንስኤዎች መፍትሔዎች ..... 85
**ምዕራፍ ስምንት(8)፡- ገንዘብና ንብረት** ..... 93
I. የገንዘብና ንብረት ምንነት ..... 93
II. ከገንዘብና ከንብረት ጋር የተያያዙ የግጭት መንስኤዎች ..... 93
III. በገንዘብና በንብረት ምክንያት ለሚፈጠሩ ግጭቶች መፍትሔዎች ..... 103
**ምዕራፍ ዘጠኝ(9)፡- የግብረ ስጋ ግንኙነት** ..... 109
I. የግብረ ስጋ ግንኙነት ምንነት በትዳር ውስጥ ..... 109
II. በክርስቲያን ትዳር ሕይወት የግብረ ስጋ ግንኙነት /ሩካቤ ስጋ/ ዓላማ ..... 110
III. ከግብረ ስጋ ግንኙነት ጋር የተያያዙ የግጭት መንስኤዎች ..... 113
IV. በግብረ ስጋ ግንኙነት ምክንያት ለሚፈጠሩት ግጭቶች መፍትሔዎች ... 122
**ምዕራፍ አስር(10)፡- የእምነትና የመንፈሳዊ መረዳት ልዩነት** ..... 131
I. የእምነትና የመንፈሳዊ መረዳት ልዩነት ምንነት ..... 131
II. በመንፈሳዊ ሕይወትና መረዳት ልዩነት መሠረት የግጭት መንስኤዎች ..... 131
III. በመንፈሳዊ ልዩነት ለሚፈጠሩ ግጭቶች መፍትሔዎች ..... 136
**ምዕራፍ አስራ አንድ(11)፡- የባልና የሚስት ኃላፊነትና የተለያየ ሚና** ... 143
I. የክርስቲያን ባልና ሚስት ሚና ምንነት ..... 143
II. ከባልና ሚስት ኃላፊነትና ሚና ጋር የተያያዙ የግጭት መንስኤዎች ..... 143
III. ከባልና ሚስት ኃላፊነትና ሚና ጋር በተያየዘ ለሚፈጠሩ ግጭቶች መፍትሔዎች ..... 148
**ምዕራፍ አስራ ሁለት(12)፡- ፖርኖግራፊ** ..... 156
I. የፖርኖግራፊ ምንነት ..... 156
II. የፖርኖግራፊ መስፋፋት ..... 156
III. የተጠቃሚዎች አመለካከት ..... 157
IV. ፖርኖግራፊ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ እይታ ..... 159
V. ባለትዳሮችን ለፖርኖግራፊ ሱስ ተጋላጭ የሚያደርጉ ምክንያቶች ..... 161



VI. የፖሮኖግራፊ ሱስ አሉታዊ ተጽዕኖ ..... 164
VII. በፖርኖግራፊ ሱስ ለሚፈጠሩ ግጭቶች መፍትሔዎች ..... 167
**ክፍል ሶስት(3)፡- ቅድመ ወሊድ፣ ወሊድና ድህረ ወሊድ** ..... 177
**ምዕራፍ አስራ ሶስት (13)፡- መውለድ አለመፈለግና አለመቻል** ..... 178
I. መውለድ አለመፈለግና አለመቻል ..... 178
II. ባለመውለድ ምክንያት ሊፈጠሩ ለሚችሉ ግጭቶች መፍትሔዎች ..... 181
**ምዕራፍ አስራ አራት(14)፡- ወሊድን መቆጣጠር** ..... 193
I. ወሊድን የመቆጣጠር ምንነት ..... 193
II. በወንጌላዊያን ክርስቲያኖች መካከል ያሉ የተለያዩ አመለካከቶች ..... 193
III. የተለመዱ የቤተሰብን ቁጥር የመመጠን ምክንያቶች ..... 194
IV. የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴ ዓይነቶች ..... 195
V. የወሊድ መቆጣጠሪያ ተጠቃሚ በመሆን ወቅት ..... 198
**ምዕራፍ አስራ አምስት (15)፡- እርግዝናና ከእርግዝና ጋር የተያያዙ ክስተቶች** ..... 202
I. የእርግዝና ምንነት ..... 202
II. በእርግዝና ወቅት የሚፈጠሩ ለውጦች ..... 203
III. በእርግዝና ወቅት ለሚፈጠሩ ችግሮች መፍትሔዎች ..... 205
**ምዕራፍ አስራ ስድስት(16)፡- ያልተፈለገና ያልታሰበ እርግዝና** ..... 212
I. ያልተፈለገና ያልታሰበ እርግዝና ምንነት ..... 212
II. ያልተፈለገና ያልታሰበ እርግዝናና ወሊድ ወቅት ሊወሰዱ የሚገባቸው መፍትሔዎች ..... 213
**ምዕራፍ አስራ ሰባት(17)፡- ከወሊድ በኋላ ሊፈጠር የሚችል ትኩረት የሚያሻው ለውጥ** ..... 218
I. ድህረ ወሊድ ድብርት ..... 218
II. የድህረ ወሊድ ድብርት መንስኤዎች ..... 218
III. ድህረ ወሊድ ድብርት የሚያመጣው ተጽዕኖ ..... 219
IV. ድህረ ወሊድ ድብርትን ተቋቁሞ ደስተኛ ባለትዳር ለመሆን ..... 219
**ምዕራፍ አስራ ስምንት(18)፡- የመጀመሪያና ልጅና ተከታትለው የተወለዱ ልጆችን ማሳደግ** ..... 227
I. የመጀመሪያ ልጅና ተከታትለው የተወለዱ ልጆችን የማሳደግ ምንነት ..... 227

I. የመጀመሪያና ልጅንና ተከታትለው የተወለዱ ልጆችን በማሳደግ ሂደት ሊፈጠሩ የሚችሉ የግጭት መንስኤዎች ........ 228
II. የመጀመሪያ ልጅንና ተከታትለው የተወለዱ ልጆችን በማሳደግ ለሚፈጠሩ ግጭቶች መፍትሔዎች ........ 234
**ምዕራፍ አስራ ዘጠኝ (19)፡- የእንጀራ ልጅን ማሳደግ** ........ 244
I. የእንጀራ ልጅ ምንነት ........ 244
II. የእንጀራ ልጅን በማሳደግ ሂደት ሊፈጠሩ የሚችሉ የግጭት መንስኤዎች 245
III. የእንጀራ ልጅን በማሳደግ ሂደት ለሚፈጠሩ ግጭቶች መፍትሔዎች ........ 249
**ምዕራፍ ሃያ (20)፡- ልጆችን በአግባቡ በመቅጣት ማሳደግ** ........ 254
I. ልጆችን በአግባቡ በመቅጣት የማሳደግ ምንነት ........ 254
II. ልጆች በመቅጣት ሊፈጠሩ የሚችሉ የግጭት መንስኤዎች ........ 255
III. ልጆችን እየቀጡ በማሳደግ ሂደት ለሚፈጠሩ ግጭቶች መፍትሔዎች ........ 260
**ምዕራፍ ሃያ አንድ (21) በቂ እንቅልፍ ማጣት** ........ 265
I. የበቂ እንቅልፍ ምንነት ........ 265
II. የእንቅልፍ አስፈላጊነት ........ 266
III. በቂ እንቅልፍ ማጣት የሚያስከትለው ተጽዕኖ ........ 267
IV. በቂ የሆነ እንቅልፍ በማግኘት የትዳርና የቤተሰብን ጤንነት ለመጠበቅ የሚረዱ መፍትሔዎች ........ 270
**ክፍል አራት፡- እርቅ፣ የፍች ሂደትና ከፍች በኋላ አዲስ ቀጣይ ኑሮ** ........ 275
**ምዕራፍ ሃያ ሁለት (22)፡- ፍችና የፍች ሂደት** ........ 276
I. የፍች ምንነት ........ 276
II. ፍች በመጽሐፍ ቅዱስ እይታ ........ 276
III. ስለፍች የተለያዩ አመለካከቶች ........ 277
IV. የፍች ደረጃዎች ........ 278
V. በፍች ሂደት በሚያልፉ ጥንዶች ላይ ሌሎች ሰዎች ሊፈጠሩባቸው የሚችሉ የተለያዩ ስሜቶች ........ 283
VI. ይቅርታና እርቅ ........ 286
VII. በባለትዳሮች መካከል እርቅ ያስፈለገበት ምክንያት ........ 291
VIII. እውነተኛ እርቅ የሚጠይቀው ........ 294
IX. ለእውነተኛ እርቅ መዘጋጀት ........ 296
**ምዕራፍ ሃያ ሶስት (23)፡- ከፍች በኋላ አዲስ ቀጣይ ኑሮ** ........ 300
I. ከፍች በኋላ የአዲስ ቀጣይ ኑሮ ምንነት ........ 300



II. ከፍች በኋላ አዲስ ቀጣይ ኑሮ ለመለማመድ ጥረት የማድረግ አስፈላጊነት ........ 301
III. በፍች ሂደት እያለፉ ያሉትን ወደ ፊት መጓዝ እንዲችሉ የማገዝ አገልግሎት ........ 303
**ማጠቃለያ** ........ 312
**ዋቤ መጽሐፍት** ........ 313
**ስለጸሐፊው** ........ 316

## ምስጋና

1. ከሁሉ አስቀድሜ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ከዘላለም ሞት ለአዳነኝ፣ ለአገልግሎቱ ታማኝ አድርጎ ለጠራኝና ለቆጠረኝ ብሎም ይህን መጽሐፍ እንድጽፍ በብዙ መንገድ የረዳኝን እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ።
2. የእግዚአብሔር ድንቅና ውብ ስጦታ የሆነችውን ውድ ባለቤቴን ወ/ሮ እመቤት ታደሰን ( እሙ) እንደ እኔ አጠራር "እናት" የትዳር ምንነት፣ በረከት፣ ኃላፊነት ለማጣጣምና መመረቅ በሌለበት የትዳር ሕይወት ትምህርት ቤት በመማር ሂደት ውስጥ እንድሆን በብዙ ነገርና መንገድ ከጎኔ ለማትለየው ባለቤቴን ከልቤ ላመሰግን፣ ለእርሷ ያለኝን ፍቅርና አክብሮት ልገልጽ እወዳለሁ!
3. የትዳርና የቤተሰብን በረከት፣ ደስታ፣ ኃላፊነት እንድለማመድ ብሎም መጽሐፉን ስጽፍ ይበልጥ የግል የትዳርና የቤተሰብ ሕይወቴን እንድቃኝና እንደ ልጆች ከአባታቸው ከሚያገኙት ጊዜ በመስጠት እንድጽፍ ዕድል ለሰጡኝ የአምላክ ስጦታችን ለሆኑት ናታንና ኖህ ሙላቱ በአባትነት ፍቅር ላመሰግን እወዳለሁ።
4. ለተወሰኑ ወራት ከእኛ ጋር በመሆን ልጆችንና እኛን በመንከባከብ ጊዜና ምቹ ሁኔታዎችን በማግኘት እንድጽፍ ለተባበረችኝ ወላጅ እናቴ ለወ/ሮ የሽጥላ ካ (ማማየ) እንዲሁም ለመምጣቷና ከእኛ ጋር ለመቆየቷ በደስታ በመፍቀደ ለተባበረን ለአባቴ ዋና ሳጅን በላይነህ በለጠ (ባባ) ሳላመሰግን አላልፍም።
5. የመጽሐፉን ንድፍ በማንበብ የተለያዩ እርማቶችንና ማስተካከያ ሥራ ለአከናወነል ወንድም ደስይበለው ደምሴ፣ የመጽሐፉን ሽፋን ዲዛይን በማድረግ ለተባበረ ወንድም አስፋው በርሔ እንዲሁም ጊዜ በመወሰድ ጽሑፍን የመጽሐፍ መል እንዲይዝ ጽሑፉን በማቀናጀት የተባበረኝን ወንድሜን ያሬድ ገዛኢን ከል አመሰግናለሁ።
6. የመጽሐፉን ንድፍ በማንበብ ጠቃሚና አበረታታች አሳብና ሙያዊ ምክር ለለገሱ የእግዚአብሔር ሰዎች፦ ወንድም ጋሽ ተካ ገብሩ (ኢንጅኔር) ፣ ዶ/ር ንጉሴ ተፈራ ፣ ወንድም ጋሽ ሰዩም ገብረየስ፣ ወንድም ከበደ በከሬ ፣ እህት ደብረወርቅ መኮነን ፣ ፓ/ር አሸብር በላይነህ፣ ዶ/ር ብሩክ ታፈሰ፣ ወንድም ዮናስ አረፋይኔ፣ ወ/ዊ ዳዊት ቆጢሶ፣ እህት ስንቄ አዘነ እና ዶ/ር ደረጀ ሳህለ ከልብ ላመሰግን እወዳለሁ።
7. የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ኅብረት ሎስ አንጀለስ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ አገልጋዮች፣ ምዕመናንና በሰሜን አሜሪካ ባለች ኢትዮጵያንና ኤርትራዊያን አብያተ ክርስቲያናት በራቸውን በመክፈት እና በአካል፣ በስልክና በስካይፕ በማማከር አገልግሎቴ ተጠቃሚ ለነበራቹህ ለመጽሐፉ ከብዙ አቅጣጫ እንድመለከትና እይታየ እንዲሰፋ እድል ስለሰጣችሁኝ እናንተንም ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን ላቀርብ እወዳለሁ።



8. በተለያየ መንገድ የመጽሐፉ ረቂቅ ተጠናቆ ለአንባቢ እንዲተዋወቅ ባለው ሂደት በብዙ አቅጣጫ የተባበሩኝ ወንድም አልዓዛር ጌታቸው እና ወንድም ነብዩ ኢያሱን እንዲሁም በተለያየ አቅጣጫ ድጋፋቹህ ላልተለየኝ የእግዚአብሔር ሰዎች በሙሉ ከልብ አመሰግናለሁ።
9. በኢትዮጵያና በአፍሪካዊያን ሕብረተሰብ መካከል የተሻለ ሁለንተናዊ የሆነ ጤንነት እንዲኖር ለማበረታታት፣ ለማስተማርና አስፈላጊውን የሕክምና አገልግሎት ከመንግሥትና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ሕብረተሰቡ ማግኘት እንዲቻል ታስቦ ለተቋቋመና እየሠራ ላለ መንግሥታዊ ላልሆነ ድርጅት " ***African communities public Health Collation (ACPHC)"*** ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ስለሰጠን የተለያዩ ትምህርትና ስልጠናዎች ዕድል ለመጽሐፌ ይበልጥ እይታየን ስላሰፋልኝ ከልብ ላመሰግንና ድርጅቱም ይበልጥ ይስፋ፣ ይጠንክርና ሕብረተሰቡን እንደሚገባ ማገልገሉን ይቀጥል በማለት ልባዊ ምኞቴን ልገልጽ እወዳለሁ።
10. በዙሪያችን ላሉ ቤተሰቦች፣ ወንድሞች፣ እህቶችና ወዳጆች የእናንተ የተለያዩ ድጋፋቹህ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በትዳራችን፣ በቤተሰባችን፣ በሕይወታችንና በአገልግሎታችን ያላችሁ አስተዋጾ ቀላል አይደለምና እግዚአብሔር ይባርካችሁ ለማለት እወዳለሁ።


### Special Thanks

I would like to give a very special thanks to the West Angeles Church of God in Christ counseling Center, Administrative and Clinical staffs. I can't forget your generosity for granted me a scholarship to continue my education and license. I am so great full for the opportunity each one of you gave me to learn from your experience. God Bless you all.

## ስለመጽሐፉ አጻጻፍና አቀራረብ ስልት አጭር መግለጫ

**የመጽሐፉ አቀራረብ**

1. መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት በአደረገ
2. በተግባራዊ ልምምድ የተጠናከረና
3. በክሊኒካል እና ክርስቲያናዊ ስነ ልቦና ላይ የተደገፈ

**የመጽሐፍ አጻጻፍ ስልት**

1. ምንነትን በማስረዳት
2. ችግሮችን ለይቶ በማስቀመጥና
3. ለችግሮቹ መፍትሔ ሊሆኑ የሚችሉትን በመዘርዘር ግጭትን እየፈቱ ደስተኛ የሆነ ትዳርና ጤነኛ የሆነ ግንኙነት በመፍጠር መልካም ቤተሰብ መመሥረት እንዲቻል ታስቦ የተጻፈ መጽሐፍ ነው።
4. ለጥንዶችና ለቡድን የሚሆን የውይይት ጥያቄዎችን የያዘ

**የመጽሐፉ ተደራሲያን**

1. በዚህ የጋብቻ ዘመን ክልል ያሉ ባለትዳሮች
2. በቅርብ ሊጋቡ በዝግጅት ላይ ላሉ እጮኛሞች
3. ለቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አገልጋዮች
4. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በማማከር አገልግሎት እያገለገሉና ሊያገለግሉ ለሚያስቡ
5. በተለያየ የትዳር ዘመን ላይ ላሉ ነገር ግን ራሳቸውን ለመመርመርና ለመማር ብሎም የሚቀጥለው በሌሎች የጋብቻ ዘመናት ላይ ያሉ የግጭት መንስኤዎችና መፍትሔዎች ታትመው እስኪወጡ ድረስ ትክክለኛ አንድ ወጥ የሆነ መረጃና ማስረጃ እንዲኖራቸው የሚረዳ መጽሐፍ ነው።



## መቅድም

ፓስተር ዶ/ር ሙላቱ ከዚህ ቀደም የአገልግሎት ተግዳሮቶች እና መፍትሔዎቻቸው በሚል ርዕስ መጽሐፍ ማሳተሙና ለአንባቢ ማቅረቡ ይታወቃል። ይህም መጽሐፍ ለብዙዎች መታነጽ ምክንያት እንደሆነ የአነበብነው ሰዎች ምስክሮች ነን። አሁን ደግሞ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሁላችንንም የትዳር ሕይወት የሚቃኝ ጠንከር ያለ ትምህርትና ምክር የያዘ ወቅታዊ መጽሐፍ በጋብቻ ዙሪያ አበርክቶልናል። ያገቡ ሰዎችንም ሆነ ያላገቡ ሰዎችን ነቃ የሚያደርግ ርዕሰ ጉዳይ ነው። ያገቡ ጥንዶች ተዳራቸውን እንዴት እንደሚመሩ ብቃት የሚጨምርላቸው እውቀትና ክህሎት ለማግኘት ያላገቡ ደግሞ ማንን ላግባ ከሚለው መሠረታዊ ጥያቄያቸው በመነሳትና ለሌሎችም ጥያቄዎች ምላሽ ለማግኘት ባላቸው መሠረታዊ ፍላጎት ምክንያት የተጻፈን ለማንበብና የሚያወያይም ከተገኘ በድፍረት በውይይቶች ለመሳተፍ ይጓጓሉ።

የሰው ልጅ ምላሹን ለማወቅ ለሚጓጓለት ጥያቄ መሠረታዊ ምላሽ ለመስጠት ዶ/ር ሙላቱ በላይነህ ያበረከተው መጽሐፍ ጠቀሜታው የጎላ ነው። ይህ መጽሐፍ ቅዱሳት መጽሐፍትን መሠረት ያደረገ፣ በክሊኒካል እና ክርስቲያናዊ ስነ ልቦና እውቀት፣ ክህሎትና ሳይንሳዊ መርሆዎች የበለጸገ፣ በጸሐፊው የማማከር አገልግሎትና የትዳር ሕይወት ልምድና ምስክርነት የታገዘ መሆኑ እንዲሁም የስነ ጽሑፍ ጥራቱ፣ የሃሳብ ፍሰቱና ግልጽነቱ መጽሐፉን ለየት የሚያደርጉት የመጽሐፉ ጥራቶች ናቸው:: እነዚህ ጥራቶች መጽሐፉ ለአንባቢያን የሚሰጠውን ጠቀሜታም ከፍተኛና ላቅ ያለ እንዲሆን ያደርጉታል::

የትዳር እንቅቅልሽ አካባቢን፣ ዘርን፣ ጥቁርና ነጭ፣ ሀብታምና ድሃ፣ የተማሩና ያልተማሩ፣ መንፈሳዊና ዓለማዊ ... በማለት የሃይማኖት ክፍል ሳይለይ የሰውን ልጆች ሁሉ የሚዳስስ እንቆቅልሽ ነው። እንደሚታወቀው በየትኛውም ማሕበረሰብ ውስጥ አንዱና ዋናው ቀውስ ትዳርና ቤተሰብ ላይ የሚከሰት ከሆነ ሰነባብቷል። በአሁኑ ዘመን ትዳር ለዘለቄታ ሳይሆን የኮንትራት ዓይነት ስምምነት እየሆነ ለመምጣቱ የዓይን ምስክሮች ነን! ትዳርን ለዘለቄታ ብለው በእግዚአብሔርና በቅዱሳን ጉባኤ ወደ ትዳር ዓለም ከገቡበት በኋላ በጥቃቅንና ምናልባትም ለሰው ትልቅ በሚመስሉ ችግሮች ወይንም አለመግባባቶች ምክንያት ክቡር የሆነውን የትዳር ሕይወት እንደቀላል ንደው ሲያፈርሱት መስማትና ማየት የተለመደ ሆኗል። የትዳር መፈራረስ በቤተሰብ፣ በማሕበረሰብና በአገር ላይ የሚያሳድረው አሉታዊ ተጽዕኖ ቀላል የሚባል አይደለም:: በተለይም በእግዚአብሔር ሕዝብ ማሕበር መካከል የሚያመጣው መንፈሳዊ ዝቅጠት ከፍተኛ ነው። ዶ/ር ሙላቱ በላይነህ እየሞገተን ያለውም ይህንን ቀውስ ለማስቀረት ልንኖርባቸው የሚገቡንን መርሆዎች እንድንረዳቸው እና እንድንጠቀምባቸው ነው። በየምዕራፉ ያነሳቸው ቁም ነገሮችም በአግባብ ካልተያዙና መፍትሔ ካልተበጀላቸው ሊያመጡ የሚችሉትን አስከፊ ተጽዕኖ በስፋትና በጥልቀት ከመፍትሔዎቻቸው ጋር በመጽሐፉ አሳይቶናል።

ከፓስተር ሙላቱ በላይነህ ጋር ካለን የረዥም ጊዜ (ከ21 አመት በላይ) ትውውቅና የአብሮነት አገልግሎት በውስጡ ያለውን መንፈሳዊ ቅንዓት ጠንቅቄ እንዳውቀው ዕድል

የትምህርትና የምክር አገልግሎት መጽሐፍ ቅዱሳዊውን መርህ መሠረት በማድረ ግለሰቦች፣ ባለትዳሮች፣ ቤተሰብና ቤተ ክርስቲያን የዘመኑን ተግዳሮቶችን በጽድ መርህ እንዲያሸንፉ መርዳት ላይ ያነጣጠረ መሆን አለበት፡፡ ተግባራዊ የሆነ የጋብ ትምህርትና የምክር አገልግሎት በዚህ ዘመን ከመቼውም ዘመን በበለጠ በቂ ጊ ሊሰጠው ይገባል፡፡ ለተጋቢዎችና ለባለትዳሮች የሚያስፈልግና የሚመጥን ትምህርት ምክር በትክክለኛ አገልጋዮች እንዲሰጥ በማድረግ ግጭትን፣ መለያየትንና ፍች ለመቀነስ ጥረት የማድረጉ ሥራም ከመቼውም ጊዜ በላይ አጽንዖት ተሰጥቶት መተግበ ያለበት ባለንበት ዘመን ነው።

**ፓስተር ዶ/ር ሙላቱ በላይነህ**
**ግንቦት 05, 2007 ዓ.ም**
**Pastor Dr. Mulatu Belayneh, licensed Clinical Pastorlal Counselour-Advanced Certified (LCPC)**
**May 13, 2015**

# ክፍል አንድ(1)፡- የጋብቻ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት

# ክፍል ሁለት(2)፡- የግጭት መንስኤዎችና መፍትሔዎቻቸው





## ምዕራፍ ሁለት(2)
## ግጭትና የግጭት ተጽዕኖ

### 1. የግጭት ምንነት

በባለትዳሮች መካከል ስለሚፈጠሩ ልዩ ልዩ የግጭት ዓይነቶች፣ የግጭት መንስኤዎችና መፍትሔዎቻቸው ከማሰባችን በፊት በባለትዳሮች መካከል የሚፈጠረውን አለመግባባትና ግጭት ምንነት ከመረዳት መጀመር መልካም ነው። የግጭትን ምንነት መረዳት ትክክለኛ፣ የተለመደ እና አይቀሬ የሆነውን ግጭት፣ የግጭት መንስኤና የግጭትን ተጽዕኖ ለመለየትና በፍጥነት መፍትሔ ለማፈላለግ ይጠቅማል። ግጭት በሁለትና ከዚያም በላይ በሆኑ ሰዎችና አሳቦቻቸው መካከል የሚፈጠር የስምምነት መጥፋት ወይም የአለመግባባት ሂደት ነው። በትዳር ውስጥ የሚፈጠረውን ግጭት ምንነት በሚከተሉት ሃሳቦች አጠቃልለን መዳሰስ እንችላለን፡፡ በትዳር ውስጥ የሚፈጠር ግጭት ማለት፡-

### 1. አንዱ ሌላውን ለማሸነፍ የሚደረግ ትግል

ግጭት በተለያዩ ጉዳዮች ላይ መስማማት ከመጥፋቱ የተነሳ በባለትዳሮች መካከል የሚከሰት ለማሸነፍ የሚደረግ ትግል ነው። በተለይ ከተጋቡ ብዙ ያልቆዩ ጥንዶች በአንደኛው ወይም በሁለቱም ወገን ማሸነፍ የሚል መንፈስ ብቻ ሲኖራቸው አሸናፊ የመሆን ትግልና አፍራሽ ፍክክር ይጀመራል፡፡ ይህ ሁኔታ በጊዜ የማይቃና ከሆነ ክስተቱ የትግሉን ማብቂያ ጊዜ የሚያራዝመው ሲሆን ግጭቱ የሚፈጥረውን ጉዳትና የሚያመጣውን አሉታዊ ተጽዕኖም እንዲጨምር ያደርገዋል።

### 2. ተስማምተውና ተጣምረው እንዳይሄዱ ሊያደርግ የሚችል ክስተት

ግጭት ባለትዳሮች ተስማምተውና ተጣምረው እንዳይሄዱ በመካከላቸው የሚፈጠር ክስተት ነው። ግጭት የሃሳብን ልዩነት በአግባቡ ማስተናገድ ባለመቻል ምክንያት በአሳብ የአለመስማማትና የአለመግባባት ውጥረት የመፈጠር ሂደት ነው፡፡ የተፈጠረው ውጥረት ሁለቱ (ጥንዶቹ) ተስማምተውና ተግባብተው በትዳራቸው ጠንካራ ግንኙነት እንዳይኖራቸው፣ ጥምረታቸው እንዲላላና ብሎም ፍች ላይ እንዲደርስ ሊያደርግ የሚችል ክስተት ሊሆን ይችላል። ክስተቱ እንዲሁ በጋራ ሲኖሩ ሳይታሰብ በባለትዳሮች መካከል የሚፈጠርና ደግሞም ታቅዶና ተቀነባብሮ ሊፈጠር የሚችልም ክስተት ነው።

### 3. ልዩነቶች የሚገለጡበትና የሚፈልጉትን ለማግኘት እርስ በእርስ እንዳይግባቡ የሚያደረግ ሂደት

ግጭት በባለትዳሮች መካከል ያሉ ልዩነቶች የሚገለጡበትና የሚፈልጉትን ለማግኘት እርስ በርሳቸው የማይግባቡበት ሂደት ነው። በአንድ ሰው ጾታ፣ አስተዳደግ፣ ልምምድ፣ ባህሪይና እሴቶች የተነሳ ከሌላ ሰው ጋር ሲነፃፀር ልዩነት ሊኖረው የግድ

ነው። ይህ ልዩነት ይበልጥ ሊገለጥና ሊታወቅ የሚችለው ደግሞ ብዙ ጊዜ አብረው በሚኖሩ ሰዎች መካከል ነው። በባለትዳሮች መካከል ያለው ቅርበትና መተዋወቅ ከሌሎች ግንኙነቶች የበለጠና የጠነከረ ነው። በዚህ የጠነከረ ግንኙነት ውስጥ ለጊዜው ተደብቆ የነበረው ልዩነት መገለጥ ሲጀምር ግጭት ይፈጠራል። የሁለቱ ጥንዶች የየግልና የተለያዩ ፍላጎቶቻቸውን ለማግኘት መፈለግና ጥረት ማድረግ ደግሞ ይበልጥ ግጭቱን ጠንካራ ሊያደርገው ይችላል።

## 4. በማናቸውም የጋብቻ ዘመን ክልል ሊፈጠር የሚችል ክስተት

ግጭት በማናቸውም ጥንዶችና በየትኛውም የጋብቻ ዘመን ክልል ውስጥ ባሉ ባለ ትዳሮች መካከል ሊፈጠር የሚችል ክስተት ነው። በትዳር ዘመናችን በቀናት፣ በሳምንታት፣ በወራት፣ በዓመታትም ይሁን በደረስንበት የጋብቻ ዘመን የግጭት ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ልዩነቶችና ፍላጎቶች መኖራቸው የማይቀር ነው። ተጋቢዎች በመካከላችን ግጭት ተፈጥሮ አያውቅም ሊፈጠርም አይችልም ብለው የሚያስቡ ከሆነ እስከ አሁን አብረው በትዳር ብዙ አልቆዩም ወይም እውነተኛውን የትዳር ሕይወት እስከዛሬ አልኖሩትም ማለት ነው። ለዚህን ያክል ዓመታት አብረን ቆይተናል ካሉም ደግሞ አብረው እየኖሩ አይተዋወቁም እንዲሁም አይነጋገሩም ነበር ለማለት ያስደፍራል። አብረን እየተነጋገርን ነው የምንኖረው ብለው የሚያስቡ ከሆነ እውነትን በመናገር ሳይሆን በግብዝነት ወይም ከሰው ጋር ሳይሆን ከሮቦት ጋር ነው እንዴ

> **ባለትዳሮች ሆይ አለመግባባትና ግጭት በትዳራችን የለም ብንል ራሳችንን እናስታለን እውነትም በእኛ ውስጥ የለም!!**

የሚኖሩት? ሊያስብልባቸው ይችላል። ሰው ሁለትና ከዚያም በላይ ሁኖ አብሮ መኖር ሲጀምር አለመግባባትና ግጭት....አይቀሬነቱ የታወቀ ነው!!

## 5. በአግባብ ካልተቆጣጠሩት በየጊዜው እያደገ ሊመጣ የሚችል ባህርይ አለው

ግጭት መጠኑና ዓይነቱ በየጊዜው እያደገ ሊመጣና ሊለዋወጥ ይችላል። ከዚህ አኳያ በጥንቃቄና በብስለት ካልተያዙ ማንኛቸውም የሚያነጋግሩ ርዕሰ ጉዳዮች ወደ አለመግባባትና አለመስማማት ያድጋሉ ግልጥ የሆነ የአሳብ ልዩነትም ይፈጠራል፡፡ የተፈጠረው የአሳብ ልዩነት ደግሞ ወደ መሸናነፍ ትግል ይለወጣል። ጥንዶቹ በትግሉ ሂደት ውስጥ ለማሸነፍ ተግቶ መዋጋት አሊያም መሸሽ እንዲመርጡ ይገደዳሉ። ይህም ሁኔታ የግጭቱ መጠን እንዲያድግ ወይም የተለያየ ገጽታ እንዲኖረው ያደርገዋል፡፡[3]

[3] ከበደ በከሬ, <u>የትዳር ግጭት መፍቻ ስልቶች</u> : መካነ ኢየሱስ የምስራች ድምፅ ኅትመት መገናኛ ዘዴ ክፍል፡ አዲስ አበባ, ኢትዮጵያ 1999 ዓ.ም ገጽ 78-83





## 6. ግጭት አሉታዊና አዎንታዊ ተጽዕኖ ያለው መሆኑ

በማንኛውም መንገድ ሰዎች ሁለት ወይም ከሁለት በላይ ሁነው የሚኖሩ ከሆነ በተለይም ደግሞ በትዳር ግንኙነት አብረው በሚኖሩ ሰዎች መካከል ግጭት የማይቀር ነው። አለመግባባት ብሎም ግጭት በግንኙነታችን መካከል ሲፈጠር ደግሞ አሉታዊ አሊያም አዎንታዊ ተጽዕኖ አምጥቶ ማለፉ አይቀሬ ነው። የግጭቱ ተጽዕኖ እንደ ጥንዶቹ ግጭት አፈታት ብስለት ይወሰናል። አሉታዊ የሆነ ተጽዕኖ ስንል ምን ማለት ነው? ምንስ ሲፈጠር ነው አሉታዊ (ክፉ፣ መጥፎና አፍራሽ የሆነ) ተጽዕኖ ነው የምንለው? የሚለውን በማወቅ አፍራሽ የሆነው የግጭት ተጽዕኖ እየተፈጠረ ከሆነ ከጉዳቱ ለማምለጥና ወደ ፊትም በትዳራችን ቋሚ ቀውስ ፈጥሮ እንዳያልፍ ለመጠንቀቅ ይረዳን ዘንድ የሚከተሉትን ሁለት ሃሳቦች በማስተዋል ማየት ጠቃሚ ነው፡-

**አሉታዊ ተጽዕኖ (አፍራሽ የሆነ)** ግጭት በተለያየ ጊዜና በተለያየ መንስኤ በባለትዳሮች መካከል የሚፈጠር ሐቅ ነው። ግጭት ከተከሰተ በኋላ ባግባቡ ካልተፈታ ብዙ ጊዜ በባለትዳሮች ግንኙነት ላይ እርስ በርሳቸው እንዳይቀራረቡ የጥላቻን ተጽዕኖ ፈጥሮ የመሄድ አስተዋጾ አለው። መጽሐፍ ቅዱስ እንኳን የትዳር አጋሮቻችንን ሌሎችን ሰዎች መጥላት እንደሌለብን እንዲህ ሲል ያዘናል፡- *"... ወንድሙን የሚጠላ ግን በጨለማ አለ በጨለማም ይመላለሳል"፣ "ወንድሙን የሚጠላ ሁሉ ነፍሰ ገዳይ ነው" እና "እግዚአብሔርን እወዳለሁ እያለ ወንድሙን ቢጠላ ሐሰተኛ ነው..."* በማለት ሰውን የመጥላት ስሜት ካለን በምን አይነት ሕይወት እንዳለንና ውጤቱም ምን እንደ ሆነ በማሳየት ያስጠንቅቀናል /1ኛዮሐ 2: 11፣ 3: 15፣ 4: 20/።

ግጭት የፈጠረው ክፉ የጥላቻ ተጽዕኖ ጥንዶችን አንዱ በሌላው ላይ ለበቀል እንዲነሳሱና ይበልጥ እንዲጎዳዱ ሊያደርግ ይችላል። በግጭት ወቅት ያልተግባባንበትና ለግጭት ምክንያት የሆነውን ጉዳይ በመለየት በይቅርታ ነገሮቻችንን ለማስተካከል ከፍተኛ ጥረት ካላደረግን የይቅርታ ተቃራኒ የሆነውን በቀልን እንድንለማመድ ያደፋፍረናል። እንደ ክርስቲያን ባልና ሚስት ከመበቀል ይልቅ ክርስቶስ እኛን ይቅር ብሎ እንደ ተቀበለን እርስ በርሳችን ልንቀባበል እንደሚገባ ቃሉ ያዘናል /ኤፌ 4: 32፣ቆላ 3: 13/።

ሌላው የግጭት አሉታዊ ተጽዕኖ ሁልጊዜ የእኔ አሳብ ካልሆነ በሚልና የግል ፍላጎታችንን ለማስፈጸም ባለን ፍላጎት በግጭቱ ለማሸነፍ እንድንታገል በማድረግ በመሸነፍ የማሸነፍ ሚስጥር እንዲጠፋብን አይናችንን ሊጋርድ የሚችል መሆኑ ነው። "ተሳስቻለሁ" እና "አጥፍቻለሁ" የሚሉ ቃላትን እንዳንጠቀምና ዝቅ ብለን በመሸነፍ ግጭቱ በሰላምና በእርቅ እንዲደመደም ጥረት እንዳናደርግ ልባችን በትዕቢትና በእልከኛነት እንዲሞላ ሊያደርግ ይችላል። የማሸነፍ መንፈስ የተጠናወታቸው ጥንዶች

አጋጣሚውን እየፈለጉና እየተጠቀሙ በቃላት ጦርነት ቤታቸውን ያተራምሱታል፡፡ ልባቸው በጉዳት ይሰበራል፡፡ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ወድቀው ለእርቅና ግንኙነታቸውን ለማደስ ጥረት ከማድረግ ይልቅ በሰላም ተቀምጠው እንዳይነጋገሩና ችግራቸውን እንዳይፈቱ ልባቸው የከበደባቸው ባለትዳሮች የግጭት አሉታዊ ተጽዕኖ ሰለባዎች ናቸው። ለትዳራችን ሰላም እንዲመጣ የትዳር አጋሮቻችንን ገንዘብ በማድረግ ግንኙነታችን ጤናማ እንዲሆን ከፈለግን *"እንግዲህ ፈጽሞ የእርስ በርስ ሙግት እንዳለባችሁ በእናንተ ጉድለት ነው። ብትበደሉ አይሻልምን? ብትታለሉስ አይሻልምን"* /1ኛቆሮ 6: 7/ የሚለውን የሐዋሪያው ጳውሎስን ምክር ልንሰማ ይገባል፡፡

በባለትዳሮች መካከል የሚፈጠሩ የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ወደ አለመግባባትና ግጭት በማደግ ጥንዶችን በስሜት ተጎዳድተው እንዲራራቁ ያደርጓቸዋል፡፡ በአካል እንዲለያዩ ብሎም ግንኙነታቸው በፍች እንዲደመደም በማድረግ ከፍተኛ ተጽዕኖ እያመጡም ይገኛሉ። ትንሽ አለመግባባት እያደገ በመሄዱ ምክንያት በሚፈጠር ግጭት የክርስቲያን ባለትዳሮች መለያየትና ብሎም ወደ ፍች መድረስ በየቤተ እምነታችንና በየአጥቢያችን እየተለመደ የመጣና በየዕለቱ የምንሰማው ከፍተኛ የሆነ የትዳር፣ የቤተሰብ፣ የቤተ ክርስቲያንና የሕብረተሰብ ተግዳሮት ሆኗል። እግዚአብሔር በነብዩ በኩል እንዲህ ሲል ፍችን እንደሚጠላ ይናገራል፦ *"መፋታትን እጠላለሁ ይላል የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር፥..."* /ሚል 2: 16/፡፡ ነገር ግን ብዙዎቻችን ለራሳችን ፍላጎት እንጅ ለመለኮት ፈቃድ ሕይወታችንን ባለማስገዛታችን የአሳብ ልዩነት ወደ አለመግባባት፤ አለመግባባት ደግሞ ወደ ግጭት፤ ግጭት ደግሞ ወደ ፍች እያደገ እግዚአብሔር የሚጠላውን የሚወዱና የሚያደርጉ ጥንዶች በዝተው እንዲታዩ አድርጓል፡፡

በግጭት ምክንያት በባለትዳሮች መካከል የሚፈጠረው ተጽዕኖ አሉታዊ ብቻ አይደለም፡፡ ግጭት መልካም የሆነ አዎንታዊ ተጽዕኖ እንዳለውም ማየት ይበልጥ ተጠቅመንበትና ተምረንበት ለማለፍ እንድንችል የሚሰጠው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው። ለባለትዳሮች በመካከላቸው የሚፈጠረው አለመግባባትና ግጭት ከግል ሕይወታቸው፣ አስተሳሰባቸው፣ ባህሪያቸው፣ ልምምዳቸው ጀምሮ በግንኙነታቸው ውስጥ ለውጥ የሚያሻው ጉዳይ እንዳለ አመላካችና የማንቂያ ደወል ሊሆን ይችላል። በትዳር ውስጥ ባለው ግንኙነት ከብዙ አቅጣጫ ብዙ ነገሮች እየተለወጡ፣ እርምጃ እየተወሰደባቸው ባለትዳሮች ተስማምተው ያቋረጧቸው፣ ያስወገዷቸውና ሌላ ጊዜ እንዲህ አይቀጥልም የተባባሉባቸው ነገሮች እንዳሉ ሁሉ እንዲሁም ወደ ፊት ለውጥ የሚፈልጉ ብዙ ጉዳዮች አሏቸው፡፡ ግጭት መፈጠሩ በጥንዶቹ መካከል ለውጥ የሚያስፈልጋቸውን ጉዳዮች የሚጠቁም ስለሚሆን ለውጥ የሚያስፈልጋቸውን አካባቢወች ለመለወጥ ትኩረት ማድረግ ተገቢ ነው። የተበላሹ የመኪና መንገዶችን ለማስተካከል ሌላ የተሻሉ አማራጭ መንገዶች መሥራት ሲጀመር ***"በሥራ ላይ"*** ፤ ***"በግንባታ ላይ"*** ና ***"በጥገና ላይ"*** የሚሉ ምልክቶች ይቀመጣሉ፡፡ ያኔ ቀስ ብለን በዝግታ ወደ ምንሄድበት ቦታ ሊያደርሱን





የሚችሉ ሌሎች አማራጭ መንገዶች ካሉ እነርሱን በመጠቀም የአሁኑ መንገድ እንዲህ ሁኖ መቆፋፈሩን እያየን ለተሻለ ለውጥ ነው በማለት በትዕግስት እናሽከረክራለን። በማንኛውም የትዳር ዘመን ያሉ ጥንዶች በሙሉ የትዳር ሕይወታችን በግንባታ፣ በሥራና በለውጥ ሂደት ላይ እንዳለ አምነን ልንቀበል ይገባል። ይህ ከገባን የትዳራችን ግንኙነት ይበልጥ እንዲጠነከር ለለውጥ አጥብቀን እንድንሠራ ያደፋፍረናል።

ሌላው የግጭት አዎንታዊ ገጽታ በግጭቱ መፈጠር ያለፍንባቸውና የምናልፍባቸው ተሞክሮዎች የሚሰጡን ትምህርት ነው። የትዳር ሕይወት አንዱ መመረቅ የሌለበት ትምህርት ቤት ነው። በትዳራችን መካከል የሚፈጠሩት ግጭቶች አስመርረውን ሳይሆን አስተምረውን እንዲያልፉ ተማሪ የመሆን ፈቃደኝነት በማሳየት ግንኙነታችንን መጠበቅ አስፈላጊ ነው።

**ግጭት አሉታዊ የሆነ ተጽዕኖ እንዳይፈጥርብን ከግጭቱ ሂደት ተማሪ እንጅ ተመራሪ እንሁን!!**

ብዙ ጊዜ የምንጋጨውና በግጭቱ ወቅትም ለማሸነፍ ከፍተኛ ጥረት የምናደርገው የግል ፍላጎታችንን ለማስፈጸም በሚደረግ ጥረት ነው። ራስ ተኮር የሆነው ማንነታችን ዋና የግጭት መንስኤ ነው። ነገር ግን የትዳር ግንኙነት የራሳችንን ግለ ፍላጎት የምናስጠብቅበት ሳይሆን ለሌላው ማለትም ለትዳር አጋሮቻችን ፍላጎት ለመኖር ራሳችንን የምንሰጥበት ነው፡፡ ለዚህም ነው መጽሐፍ ቅዱስ በ1ቆሮ 7 *"ባል ለሚስቱ የሚገባትን ያድርግላት፥ እንደዚሁም ደግሞ ሚስቲቱ ለባልዋ።"* ቁ 3 *" ሚስት በገዛ ሥጋዋ ላይ ሥልጣን የላትም፥ ሥልጣን ለባልዋ ነው እንጂ፤ እንዲሁም ደግሞ ባል በገዛ ሥጋው ላይ ሥልጣን የለውም፥ ሥልጣን ለሚስቱ ነው እንጂ።"* ቁ 4 እና *"... እርስ በርሳችሁ አትከላከሉ"* ቁ 5 በማለት የሚያስተምረን፡፡ የክርስቲያን ትዳር መሠረት አጋፔያዊ ፍቅር ነው፡፡ አጋፔ ፍቅር ደግሞ ራሱን አሳልፎ ለሌላው በመስጠት መሥዋዕት የሚሆንና በራስ ወዳድነት የማይጠመድ ፍቅር ነው። *"ፍቅር ...የራሱንም አይፈልግም..."* /1ኛቆሮ 13: 4-7/፡፡ ጋብቻ ባለትዳሮች በዚህ ፍቅር ላይ ተመሥርተው የየራሳቸውን የግል ፍላጎት በመተው ለትዳራቸው ጤናማነትና ሰላም አንዱ የሌላውን ፍላጎት ለማርካት የሚጥሩበት ተቋም ነው። የእግዚአብሔር ቃል ሁልጊዜ የራሳችንን ኃላፊነትና ግዴታ ያሳየናል እንጅ ሌላው አካል ለእኛ እንዲያደርግልን የምንሟገትበት ምንም ዓይነት ድጋፍ አይሰጠንም።

ሌላው የግጭት አዎንታዊ ተጽዕኖ ግጭትን በጋራ እየፈቱ በሚጓዙበት ወቅት ባልና ሚስት የሚያገኙት ከፍተኛ የሆነ ልምድ ነው። ለዚህም ነው በቅርብ ያገባን ሰዎች ከቆዩ ባለትዳሮች ለመማር መዘጋጀት ያለብን። ያሳለፍናቸው የተለያዩ የትዳራችን ተግዳሮቶች እንድንለወጥ ተገዳድረውን፣ እንደ ጎበዝ ተማሪ መልካም አሠራርንና አኗኗርን ተምረንባቸውና ነገ ለሚፈጠሩ ግጭቶች ልምድ አግኝተንባቸው ካለፍን ጥበበኞች ነን። ግጭቶች እርስ በርሳችንም ይበልጥ እንድንተዋወቅ እድል ስለሚሰጡን በብዙ ነገሮች

ከቀድሞ በበለጠ እየተረጋጋንና ስጋት እየቀነሰን እንድንመጣ ያግዙናል። አንድ ጊዜ ባለቤቴ በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ባልተግባባንና በተጋጨን ወቅት ከተወሰኑ ሰዓታት በኋላ ተነጋግረንና ይቅርታ ተጠያይቀን ይበልጥ ከትናትናው በበለጠ መፈላለጋችን ሲጨምርና ግንኙነታችን ሲጠንክር ስትመለከት:- "እንዲህ መጋጨት ፍቅርን የሚጭምርና ግንኙነትን የሚያጠናክር ከሆነ ለግጭት ፕሮግራም እናውጣ!" አለችኝ:: ይህ ተሞክሮ የሚያሳየን ግጭትን ፈልገን እናምጣው ወይም እንውደደው የሚል ሳይሆን ባጋጠመንና በትክክል መፍታት በቻልን ጊዜ በእኛ ግንኙነት ውስጥ ያመጣውን መልካምና ገንቢ የሆነውን ተጽዕኖ ነው።

ግጭትን በአግባቡ፣ ብስለትና ጥበብ በተሞላው መንገድ መፍታት ከተቻለ በየጊዜው ለሚፈጠሩብን ግጭቶች እውነተኛ መንስኤዎችን ለይቶ በመረዳት ከምንጩ ለማድረቅና ለማሸነፍ በጋራ ተስማምቶ ለመሥራት መነሳትን ይፈጥራል። የመጣው ችግር ትዳራችንንና ግንኙነታችንን ለማፈራረስ የሚገዳደረን ነውና የማፍረስ ተጽዕኖውን እምቢ ለማለት መንቃት አለብን:: እንዲህ አይነት ንቃትና አስተዋይነት ካለን ሊያፈርስን የመጣው ተግዳሮት በጋራ አንዱ ሌላውን እያሸፈነና እየረዳ እንድንመላለስ ያስተምረናል። የትዳራችንን ጉዳይ በምንም ሁኔታ አንዳችን ከሌላችን ጋር ***"የራስህ (የራስሽ) ጉዳይ ነው!"*** በሚል እልከኝነት የምንገፋፋበትና የምንጣጣልበት አይደለም:: እንዲህ አይነቱ የመጣጣል ችግር ሰይጣን ጥንዶችን በየግል ለይቶ የሚመታበትና አንድነታቸውን ለማፈራረስ የሚጠቀምበት ዘዴ ነውና ነቅተን ግንኙነታችንን መጠበቅ ኃላፊነታችን መሆኑን አንዘንጋ! በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የትዳር አጋሮቻችን ጉዳይ ሕይወታችንና ጉዳያችን ነውና!!

## II. በባለትዳሮች መካከል የግጭት አይቀሬነት

### 1. ተፈጥሯዊ ልዩነታችን

ስለ ሰው ተፈጥሯዊ ማንነት የእግዚአብሔር ቃል ሲናገር *"እግዚአብሔር አምላክም ሰውን በመልኩ እንደ አምሳሉ ፈጠረው ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው"* **/ዘፍ 1: 26-27/** ይላል። ይህ አፈጣጠራችን በወንድ እና በሴት መካከል ያለውን አንድነታችንና ልዩነታችንን ያመለክተናል። አንድነታችን ከሌሎች ፍጥረታት ተለይተን በእግዚአብሔር መልክና አምሳል መፈጠራችን፣ ሕያው ነፍስ ያለን መሆናችንና ለአዳም እንደ እርሱ ዓይነት ረዳት አልተገኘለትም በሚሉ የተለያዩ መግለጫዎች ተብራርቷል። ወንድና ሴት ሆነን መፈጠራችን ደግሞ ልዩነታችንን የሚያሳይ ነው:: በዚህ ክፍል ማንሳት የፈለኩት በትዳር መካከል አለመግባባትና ግጭት አይቀሬ እንዲሆን ያደረገው አንደኛው ምክንያት ተፈጥሯዊ ልዩነታችን መሆኑን ነው። ተፈጥሯዊ ልዩነት በውስጡ የተለያዩ ዝርዝር ልዩነቶችን እንደሚያካትት መረዳት አስፈላጊ ነው።

#### 1) ጾታዊ ልዩነት





እግዚአብሔር ሰዎችን ወንድና ሴት አድርጎ ሲፈጥር በዓላማ፣ ተመሳሳይነትና ልዩነት እንዲኖራቸው አድርጎ ፈጥሯቸዋል። በትዳር ውስጥ ስንኖር የወንድና የሴትን ተፈጥሯዊ ተመሳሳይነትና ልዩነት መረዳት ካልቻልን ለማያቋርጥ ግጭት ተጋላጭ እንሆናለን። የመጀመሪያው ልዩነት ስነ ልቦናዊ ነው። የፔኒሲሊፌናያ ዩኒቨርስቲ ጥናት *"ሴቶች አእምሮቸው ከብዙ ነገር ጋር የተገናኘ እንደሆነና በአንድ ጊዜ ብዙ ቦታ ማሰብ፣ መገናኘትና መሥራት እንደሚችሉ ይገልጻል"*::[4] አብዛኛው የወንድ ልጅ አእምሮ አንድ ነገር ሲያስብ ወይም አንድ ነገር ላይ ብቻ ሲያተኩር ብሎም በውጥረት ወቅት ብዙ ማሰብና መናገር የማይፈልግ ሲሆን አብዛኛዎቹ ሴቶች በተቃራኒው አእምሮቸው በአንድ ጊዜ ብዙ ቦታ መሄድ፣ ማሰብ፣ መሥራትና በውጥረት ወቅት በማውራት ስሜታቸውን መግለጽና መፍትሔ ለማግኘት ጥረት ማድረግ ይችላሉ። ለምሳሌ ሴቶች ብዙ የኮምፒዩተር ዊንዶ ከፍተው በአንድ ጊዜ መሥራት ሲችሉ ወንድ ልጅ ግን አንድ ዊንዶ ከፍቶ ከዚያ ሲጨርስ ሌላ ዊንዶ በመከፈት መጠቀም እንደሚመርጠው ማለት ነው። ሚስቶች በቤት ውስጥ በአንድ ጊዜ ብዙ ሥራ መሥራት ሲችሉ ባሎች አንዱን ስራ ስንጨርስ ወደ ሌላው እንቀጥላለን እንጅ ብዙ የተለያዩ ሥራዎችን በአንድ ጊዜ የመስራት ተፈጥሮ የለንም።

ባለትዳሮች ወንድና ሴት ሁነው መፈጠራቸው ሊያመጣ የሚችለውን ልዩነት፣ ለውጦችና ተጽዕኖዎች መረዳት መቻል አለባቸው። ጾታዊ ልዩነት በባለትዳሮች አካላዊ አቋም፣ ስሜት፣ አስተሳሰብ፣ ማሕበራዊ ግንኙነት፣ የግብረ ስጋ ግንኙነትና አካላዊ ንጥረ ነገሮች (ሆርሞን) ይታያል:: ይህም ደካማና ጠንካራ ጎናቸው ላይ ልዩነት መፍጠሩ የግድ ነው። ጾታዊ ልዩነት የሚፈጥረውን አሉታዊ ተጽዕኖ በመረዳት፣ በመተሳሰብና በልበ ሰፊነት ግጭትን በትክክለኛ መንገድ ለመቆጣጠር ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው። ልዩነቱን አስቀድሞ መረዳት የተፈጠረና ሊፈጠር የሚችል ግጭት በባለትዳሮች ግንኙነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ፈጥሮ እንዳያልፍ ከወዲሁ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ለማድረግ ይጠቅማል።

#### 2) የዕድሜ ልዩነት

በባለትዳሮች መካከል ግጭት አይቀሬ እንዲሆን ከሚያደርጉት ሌሎች ምክንያቶች አንዱ በጥንዶች መካከል ሊኖር የሚችል የዕድሜ ልዩነት ነው። በባለትዳሮች መካከል ያለው የዕድሜ ልዩነት በጥንዶች መሰረታዊና አስፈላጊ በሆኑ ፍላጎቶቻቸው፣ ዋጋ በሚሰጧቸው እሴቶች፣ በችሎታቸውና በአስተሳሰባቸው (እይታቸው) ላይ ግልጥ የሆነ

[4] Jason Howerton, The Difference Between Men and Women's Brains Revealed? http://www.theblaze.com/stories/2013/12/02/the-difference-between-men-and-womens-brains-revealed Dec. 2, 2013 accessed March. 26, 2014

ተጽዕኖ ሊያመጣ ይችላል። አንዳንድ ሰዎች በኑሮ ላይ ያለባቸውን ጫና ለማቃለልና ችግራቸውን ለማስወገድ የአባትና የልጅን፣ የእናትና የልጅን የሚያክል የዕድሜ ልዩነት እንዳላቸው እያወቁ ወደ ትዳር ይገባሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ ወደ ትዳር የገቡ ጥንዶች የእድሜ ልዩነት በመካከላቸው አለመግባባትና ግጭት ሲፈጥርባቸው ይታያል። አንዳንዶች በዓላማ ለተወሰነ ጊዜ በትዳር በመቆየትና ሰበብ ፈልገው በመለያየት ንብረት ተካፍለው ኑሯቸውን በመቀየር ቃል ኪዳናዊ የሆነውን ትዳር ወደ ኮንትራት ጋብቻ ይቀይሩታል። የዕድሜ ልዩነት የሚያመጣውን ግጭትና አሉታዊ ተጽዕኖ በመረዳት ልዩነትን ማጥበብና የትዳርን ግንኙነት በማጠናከር ግጭትን መቀነስ፣ እንዲሁም በትክክለኛ መንገድና በብስለት ግጭትን መፍታት አስፈላጊ ነው።

3) **ቴምፕራመንት (ስብዕና)**

አንድ ሰው ሲወለድ የራሱ ተፈጥሯዊ ማንነት አለው። ከአንድ እናትና አባት የተወለዱ ልጆች የተለያየ ተፈጥሮ ይታይባቸዋል። *"የእናት ሆድ ዥንጉርጉር"* እንዲሉ ከአንድ ወላጅ የተወለዱ ልጆች የተለያየ ስብዕና ካላቸው ከተለያየ ቤተሰብ የመጡ ሁለት ጥንዶች የስብዕና ልዩነት ሊኖራቸው እንደሚችል መገመት ከባድ አይደለም። እያንዳንዱ ሰው ራሱን የቻለ ብርታትና ደካማ ጎን አለው። **የመጀመሪያው** የስብዕና ልዩነት አንድ ሰው ከሌሎች ሰዎች፣ ከአካባቢውና ከሁኔታዎች ጋር ራሱን በቀላሉ የማስለመድና አብሮ የመኖር ዝንባሌ ሲኖረው ሌላኛው ሰው ደግሞ ቁጥብና በቀላሉ ከአካባቢውም ሆነ ከሌላ ሰው ጋር ለመዋሃድ የሚቸገር ሰው ይሆናል፡፡ ይህም ማሕበራዊ ግንኙነታቸው የተለያየ ለመሆኑ አንዱ ምስክር ነው። **ሁለተኛው** ልዩነት አንድ ሰው ሌላውን ሰው ለመቆጣጠር ወይም በሌላ ሰው ቁጥጥር ሥር ለመሆን የመፈለግ ዝንባሌ ሊኖረው የሚችል መሆኑ ነው። **የመጨረሻው** ልዩነት አንድ ሰው ፍቅርን ከሌላው የሚፈልግበትና ፍቅርን ለሌላው የሚገልጽበት ስሜት የተለያየ መሆኑ ነው፡፡[5] እነዚህን የመሳሰሉ ልዩነቶችን መገንዘብ ከሌላ ሰው ጋር በሰላም አብሮ ለመኖር አስፈላጊ ነው።

እነዚህን የመሳሰሉ ልዩነቶች ምክንያት ሆነው ከተለያየ ቤተሰብና አስተዳደግ የመጡ ጥንዶች የመጋጨት እድላቸው ሰፊ እንዲሆን ያደርጉታል። ጥንዶች ከአካባቢያቸው ጋር ለመመሳሰልና ማሕበራዊ ግንኙነት ለመፍጠር በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ልዩነት ሊኖራቸው እንደሚችል መገንዘብ መቻልም አስፈላጊ ነው። ምሳሌ ለመጥቀስ ያክል፡- ባል በማሕበራዊ እንቅስቃሴ ሂደት ሰዎች ወደ እርሱ እንዲመጡ የሚፈልግ እንጂ እርሱ ወደ ሰዎች መሄድ የማይፈልግ ሊሆን ይችላል። ሚስት በተቃራኒው በአብዛኛው ማሕበራዊ ግንኙነት ላይ የምትገኝ ብቻ ሳትሆን በብዙ ነገር

[5] Arno, Richard G. Temperament Theory. National Christian Counselour Assosation (NCCA) Sarasota: Fl, 1994. Page3.





የማሕበሩን ትኩረት የምትስብ ቶሎ የምትቀላቀል ልትሆን ትችላለች። ባንድ ወቅት የውጭ አገር ዜጋ የሆኑ ባልና ሚስቶችን በማማከርበት ጊዜ ባል ከጠቀሰው ችግር አንዱ ሚስቴ ከእኔ ይልቅ ማሕበራዊ ነገር ታበዛለች፡፡ በማሕበራዊ ስበሰባ ላይ ብቻየን በመቀመጥ ባይተዋር እሆናለሁ፡፡ ከሚስቴ ይልቅ ሌሎች በደንብ ይንከባከቡኛል የሚል ነበር፡፡ እኔም ሚስት የሞላችውን ፎርም በመመልከትና በግል በመጠየቅ ከባህርይዋ ማሕበራዊ ነገር እንደምትወድ አረጋገጥኩ። ከዚያም የሌላውን ተፈጥሯዊ ባህርይ ለመረዳትና ነገሮችን ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ለማየት አንዱ በሌላው ላይ ትኩረት እንዲያደርጉና ግንኙነታቸውን እንዲያጠናክሩ በማሳየትና የቤት ስራ በመስጠት ለሌላ ጊዜ ቀጠሮ መያዝ እንደሚፈልጉ ተነጋግረን ተለያየን። አንዳንድ የትዳር አጋሮች ቤት ውስጥ ብቻቸውን ሲሆኑ አቅም ሲያገኙና ሲደሰቱ ሌላው አካል ደግሞ በሰዎች መካከል ሲሆንና በሰዎች ሲከበብ ደስተኛ ይሆናል።

ከዚህም ባሻገር አንዱ ሌላውን የመቆጣጠር ዝንባሌ ሲኖረውና በሌላ ሰው ቁጥጥር ስር መሆንን የማይፈልግ ሲሆን የመቆጣጠር ሙከራ ከተደረገበት ሊቆጣ፣ ሊጋጭና ዐመጽ ሊያስነሳ ይችላል። እንዲህ አይነት የስብዕና ልዩነት ባለበት ቦታ "ሚስት ለባሏ ትገዛ" የሚለው ጥቅስ ባለትዳሮችን ሲያጋጭ ይታያል። አንዳንዶች ደግሞ ማንንም የመቆጣጠር ስብዕናና ፍላጎት የላቸውም፤ ከዚህ የተነሳ ብዙ ነገር ሲበላሽ ዝም ማለትን ይመርጣሉ፡፡ በትዳራቸው የሚኖራቸው ኃላፊነትና ሚናም የተገላቢጦሽ ሊሆን ይችላል። አንዳንዶች ማንንም መቆጣጠር አይፈልጉም ነገር ግን ራሳቸው በአንድ ስልጣን ቁጥጥር ስር ሆነው መታዘዝና መገዛት ይፈልጋሉ። ሌላውን የመቆጣጠር ፍላጎት ያላቸውና በሌሎች ቁጥጥር ስር መሆን የመፈለግ ተፈጥራዊ ስብዕና ያላቸው ሰዎች መኖራቸውን መረዳት ካልቻልን በትዳር ላይ ግጭት መፈጠሩ የማይቀር ነው፡፡ ግጭቱም ኃይለኛና ቶሎ የማይበርድ በመሆን ግንኙነቱን ወደ ማይፈለግ አቅጣጫ ሊቀይረው ይችላል።

ጥንዶቹ አንዱ ከሌላው ፍቅር በሚፈልጉበት ጊዜ ፍላጎታቸውን ለመግለጽ ሁኔታዎች ካልተመቿቸውና እርስ በርሳቸው ካልተረዳዱ የሚፈልጉትን በማጣት የማይፈልጉት ሲፈጠርባቸው ሊበሳጩ ደግሞም እንዳልተወደዱና ተቀባይነት እንደሌላቸው ሊያስቡ ይችላሉ። በተቃራኒ ጾታ ፍቅር ከትዳር አጋሮቻቸው የሚፈልጉትና የሚሰጡት አለመመጣጠን ከተፈጠረና ፍቅራቸውን የሚገልጹበት ቋንቋ የተለያየ ሆኖ አለመግባባት ካለ ግጭት እንዲፈጠር ሁኔታዎች ምቹ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ይህ ችግር ያጋጠማቸው ባለትዳሮች የትዳር አጋሮቻቸውን ከሌሎች የትዳር አጋሮች ጋር በማወዳደር ይበልጥ ሊጎዱና ሊጋጩ ይችላሉ፤ ይህም ለመለያየት ጠንቅ ሊሆን ይችላል። ወደ ትዳር ዓለም የገባናው ከትዳር አጋሮቻችን ጋር አንድ ዓይነት ሰው እንድንሆን ሳይሆን ልዩነታችንን፣ ጠንካራና ደካማ ጎናችንን በመረዳት ተዋደን፣

ተቀባብለን፣ ተሳስበንና በጋራ ግጭቶቻችንን እየፈታን አንዳችን ሌላችንን በመጥቀም ለመኖር ነው።

## 2. የተለያዩ የግል ፍላጎቶች

በጥንዶች መካከል ግጭት እንዳይጠፋ ከሚያደርጉ ምክንያቶች አንዱ ጥንዶች የየግል የሆነ የተለያየ ፍላጎት ያላቸው ሰዎች መሆናቸው ነው። የፍላጎት ልዩነት እንዳይግባቡ፣ እንዲጋጩና እንዲለያዩ ሊያደረግ ይችላል። የፍላጎት ልዩነት ብቻ ሳይሆን በጥንዶች መካከል ተመሳሳይ የሆነ ፍላጎት መኖሩም ሌላው የግጭት መንስኤ ሊሆን የሚችል ጉዳይ ነው። ከተመሳሳይነቱ የተነሳ ለእኔ ይሁንና የእኔ ይቅደም በሚሉ ጥያቄዎች፣ የጥንዶችን ተመሳሳይ የሆነ የየግል ፍላጎት ለማሟላት የገንዘብ፣ የጊዜና የጉልበት አቅም ሊኖር ስለማይችል ግጭት ይፈጠራል ግጭቱም ሊባባስ ይችላል።

በቅርብ የተጋቡ ባለትዳሮች አብረው ያሳለፉት ጊዜ አጭር ከመሆኑ የተነሳ፣ የሰው ልጅ ፍላጎት ከጊዜ ወደ ጊዜ ስለሚለዋወጥና እርስ በእርስ ሙሉ በሙሉ ተዋውቀው ስለማይጨርሱ አንዱ የሌላውን ትክክለኛ የሆነ የግል ፍላጎት ለማወቅ መቸገራቸው ጭምር ችግሩ አይቀሬ እንዲሆን ያደርገዋል። አንዱ የሌላውን ፍላጎት አለማወቅ ብቻ ሳይሆን ፍላጎትን ለማሟላት የሚደረገው ጥረትም በቂ ካልሆነ አንዱ የሌላውን ፍላጎት ለማሟላት፣ ለማርካትና ለማስደሰት የሚያደርገው ጥረት ተመጣጣኝ አለመሆን ወደ ግጭት ያመራል:: እንዲሁም በነገሮች ያለመርካት ችግር መታየት በየጊዜው በመካከላቸው ግጭት እንዲነሳ፣ ግጭቱ እንዲሰፋና እንዳይጠፋ ሊያደርገው ይችላል።

*"ባል ለሚስቱ የሚገባትን ያድርግላት፤ እንደዚሁም ደግሞ ሚስቲቱ ለባልዋ።" /1ኛ ቆሮ 7፡ 3/*

## 3. የእሴቶች ልዩነት

እያንዳንዱ ሰው የራሱ የሆነ ዋጋ የሚሰጠው ጉዳይ አለው። እሴቶች ለልዩ ልዩ ጉዳዮች የምንሰጣቸው ዋጋዎች ናቸው:: እያንዳንዳችን ለሰው፣ ለቤተሰብ፣ ለግንኙነት፣ ለጊዜ፣ ለገንዘብና ለንብረት፣ ለሥራ፣ ለትምህርት፣ ለመንፈሳዊ ሕይወትና ለአገልግሎት፣ ለወዳጅነትና ለራሳችን የምንሰጠው ዋጋ የተለያየ መሆኑ በዚህ ልዩነት ምክንያት አለመግባባትና ግጭት መፈጠሩ አይቀሬ እንዲሆን ያደርገዋል። እሴቶቻችን በአስተዳደጋችን፣ በምንማረው፣ በልምምዳችን፣ በእምነታችንና ምናልባትም በዙሪያችን ባሉ ሰዎች ሊወሰኑ፣ ሊቀረጹ፣ ሊያድጉና ሊሻሻሉ ይችላሉ። አንዳንድ ጊዜ "ግድ አይሰጥህም/ሽም/"፣ "ይኸኔ እንዲህ እናድርግ ቢባል ኖሮ"፣ "ምንድን ነው የሚያስደንቅህ/ሽ/"፣ "ለምንድን ነው ለዚህስ ጉዳይ ስፍራ የማትሰጠው /ጭው/?" ... የሚሉ ንግግሮች በግንኙነታችን መካከል እየተንጸባረቁ አለመግባባቶችን ወደ ከፋ ግጭት እንዲደርሱ ሲያደርጉ የሚታዩት በእሴቶቻችን ላይ ባሉን ልዩነቶች ምክንያት ነው::





## 4. ወደ ትዳር ሕይወት የገቡበት የተሳሳተ ምክንያት

ሌላው በባለትዳሮች መካከል አለመግባባትና ግጭት እንዳይጠፋ ብሎም መለያየት እንዲፈጠር ከሚያደረጉ ምክንያቶች አንዱ ሰዎች ስለትዳር ያላቸው የተሳሳተ መረዳት ነው። ፍቅርን ለትዳር መሠረት አድርጎ ወደትዳር ከመግባት ይልቅ በሌሎች በተለያዩ ነገሮች ላይ መመሥረት ወይም ወደ ትዳር ዓለም የሚገቡባቸው የተለያዩ የተሳሳቱ ምክንያቶች መኖራቸው ማለትም የግብረ- ስጋ ግንኙነት ፍላጎትን ለማርካት ብቻ፣ ልጅ ለመውለድ ካላቸው ብርቱ ፍላጎት በመነሳት፣ የኢኮኖሚ ችግሮቻቸውን ለማስወገድ፣ በውጭ አገር የሚኖሩ የኢሚግሬሽን ጉዳይ ለማስፈጸምና አገር ቤት ያሉ ወደ ውጭ አገር ለመውጣት፣ በተለይ በእህቶች ላይ የሚታይ የዕድሜን ፍርሃት ለማምለጥ፣ የቤተሰብንና የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ማህበራዊና ስነልቦናዊ ግፊትና ጫናን ለመግታትና ምላሽ ለመስጠት በማሰብ ወደ ትዳር መግባት በትዳር ውስጥ ግጭት እንዳይጠፋ ሊያደርግ የሚችል ምክንያት ነው።

ወደ ትዳር ዓለም ለመግባት የሚያስቡ ወገኖች ስለጋብቻ ትክክለኛ የሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረዳት በማግኘት ወደ ትዳር ለመግባት በእውነተኛ ፍቅር መዋደድን በማረጋገጥ እንዲሁም ትክክለኛ የሆነ በጋራ ለመረዳዳት የሚያስችል ኅብረት መኖሩን በመገንዘብ እንጂ በአንዱ አካል ብቻ ለመረዳት በሚያስብ ፍላጎትና ምክንያት ወደ ትዳር ላለመግባት ቆም ብሎ ማሰብና መጠየቅ፣ መጸለይና ማማከር አስፈላጊ ነው። ወደ ትዳር ዓለም ያልገቡ ወጣቶች ለምን ማግባት እንደፈለጉ ትክክለኛ ምክንያት እንዲኖራቸው ብቻ ሳይሆን ሊያገቡት የሚያስቡትን ግለሰብ ለትዳር የመረጡት ለምን እንደሆነ መነሻ ሃሳባቸውንና ምክንያታቸውን በመፈተሽ ትክክለኛ ምላሽ ሊያገኙ ይገባል። ይህንን ማድረጋቸው ወደ ትዳር በሚገቡበት ወቅት የግጭትን መንስኤዎችን መቀነስ እንዲቻልና በትዳር ውስጥ ደስተኛ የትዳር ሕይወትና ጤነኛ ግንኙነት እንዲኖር ከፍተኛ አስተዋጾ ይሰጣል።

## 5. ከትዳር ተጠብቆ የሚገባው ተስፋ (ግምት)

በግንኙነት ላይ የሚፈጠሩ ግጭቶችን በሚገባ ተቆጣጥረን ገንቢ በሆነ መንገድ ተምረንበትና ተለውጠንበት የማለፍ ስኬታማነታችንን ጥበቃችን ይወስነዋል። አንዳንዶች ከትዳርና ከትዳር አጋራቸው ጠብቀው የሚገቡት ነገር ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ እንደጠበቁት ሳይሆን ሲቀር ይጎዳሉ:: ስለትዳር አጋሮቻቸው "የእግዚአብሔር ፈቃድ ነውን? " ፣ "አብረን መሄድ የማንችል ሰዎች ነበርን እንዴ? " እና "ምንድን ነው የተሳሳትኩት?"... በማለት መጠየቅ ይጀምራሉ። አንዳንዶቹ በትዳር ውስጥ ሁልጊዜ ደስታ፣ ጤነኛነት፣ የግብረ ስጋ ግንኙነት... እንደሚኖር እየሰሙና እያሰቡ ማደጋቸው፤ ጥበቃቸው ከፍተኛ እንዲሆን አድርጎት ሊሆን ይችላል። ሳይሟላ ሲቀርም ከፉኛ ይጎዳሉ::

ሕጻናት ልጆችን እወዳለሁ፣ በተቻለ መጠን ላቀርባቸውና ላጫውታቸው እሞክራለሁ እነርሱም ደስ ይላቸዋል፡፡ ነገር ግን እንዲህ የማጫውታቸው ሕጻናት የሽንት ጨርቃቸው /ዳይፐራቸው/ በወላጆቻቸው የተቀየረላቸው፣ የታጠቡና የተመገቡ ናቸው። ሰዎች ልጆችን ስታጫውት ጎበዝ ነህ ሲሉኝ እንዲህ እላቸው ነበር ዳይፐሩ የተቀየረለትና ንጹህ የሆነ ሕጻን ማጫወት እወዳለሁ እላቸዋለሁ። የሚያምር እያያዝ የተያዘን ሕጻን ልጅ ሌላ ሰው አዘጋጅቶ ሰጥቷቹህ ማጫወትና ራሳችሁ አጥባቹህ፣ ልብሳቸውን ቀይራችሁና መግባችሁ ማጫወት ፈጽሞ የተለያዩ ልምምዶች ናቸው። ትዳር እንዲህ ዓይነት ሥራና ድካም እንዳለው ካላሰብንና ካልጠበቅን በስተቀር ልጆችን እንደ ስጦታ ሳይሆን እንደ መከራ ልናያቸው እንችላለን። አንዳንዶች ትዳር የእያንዳንዳችንን ሥራ የሚጠይቅ ግንኙነት እንደሆነ አስበው ወደ ትዳር አለመግባት መሠረታዊ ችግራቸው ነው፡፡ ትዳር ተብሎ ሲታሰብ ሁልጊዜ እየተሠራን የምንሠራበት ተቋም እንደሆነ ጠብቀን ወደ ትዳር አለመግባት በሚፈጠረው ግጭት እጅግ በጣም ተጎጅዎች እንድንሆን ያደርገናል።

አንዳንዶችን ለእንዲህ ዓይነቱ ከፍተኛ የሆነ ተስፈኝነት ተጋላጭ ሊያደርግ የሚችለው መልካሙን የትዳር የሕይወት ገጽታ ብቻ በሚመሰከሩ ባለትዳሮችና በሚያስተምሩ የጋብቻ አስተማሪዎች የሚፈጠረው ሚዛናዊ ያልሆነ ተጽዕኖ ነው፡፡ በጓዳቸው ውስጥ ቀውስ በቀውስ ሆነው በሰው ፊት ግን ትዳርን ምንም ችግር የሌለበት ዓለም የሚያስመስሉ ጥንዶችና ኑሯቸውና የሚሠሩት ፊልም ፈጽሞ የተለያየ የሆነባቸው የፊልም ተዋናያንኖች መካከል ከፍተኛ መመሳሰል አለ፡፡ ሁለቱም ከእውነታው ዓለም ጋር የሚመሳሰል ነገር ግን ከገሃዱ ዓለም ፈጽሞ የራቀ ተውኔት ያሳዩናል፡፡ በዚህም ሥራቸው በምናየው ፊልም ተጽዕኖ ስለትዳር የተዛባ ግምት እንዲኖረንና ግምታችን እንዲበላሽብን ያደርጋሉ፡፡ የጠበቅነው ተስፋ እውነት አለመሆኑን ስናውቅም ከፍተኛ ጉዳት ውስጥ እንወድቃለን።

ሌላው ችግር ከትዳር ዝቅተኛ የሆነ ጥበቃና ተስፋ ይዞ ወደ ጋብቻ መግባት ነው። ስለትዳር ከቤተሰቦቻቸው እያዩ ካደጉት በመነሳት፤ በሌሎች የታወቁ በሚባሉ መንፈሳዊ ሰዎች ትዳር ከሚፈጠረው ግጭት፣ መለያየትና ፍች፤ አንዳንድ የጋብቻ አስተማሪዎችና አማካሪዎች ይበልጥ የጥንዶችን ኃላፊነት ለማሳየት በሚያደርጉት የማስጠንቀቂያና የማስፈራሪያ ትምህርትና ምክር ምክንያት ትዳርን ፈጽመው አጨልመው የሚያዩ ብዙ ሰዎች አሉ፡፡ እንዲሁም በዓለም ላይ ከጋብቻ ጋር በተያያዘ የሚታየው ከፉ የሆነ አፍራሽ ተጽዕኖ አንዳንዶች ስለትዳር ያላቸው ግምትና ተስፋ እንዲደበዝዝ ብሎም እንዲጠፋ ያደርጋል።

ስለትዳር ያለን የተሳሳተ ጨለምተኝነት በዚህ ዘመን ቢጋብቻ ጸንቶ መቆየት አይቻልም የሚል የተሳሳተ ድምዳሜ ላይ እንድንደርስ ያደርገናል! የሰማናቸው አሉታዊ አስተሳሰቦች ትዳርን እንደ እስር ቤት እንድንቆጥርና ትዳር መልካም ነገር የሌለበት





የውጥረት ዓለም ነው የሚል ከንቱ አስተሳሰብ እንዲኖረን ተጽዕኖ ያሳድሩብናል፡፡ በላጤነት የነበሩ ብዙ ጊዜያዊ ነጻነቶችንም እንድንናፍቅ ይቀሰቅሱናል፡፡ እነዚህን በመሳሰሉ ከንቱ ምክንያቶች በትዳር ውስጥ ያለው በረከት ተካፋይ ሳንሆን እንዳንቀር በጋራ ተዋድደን፣ ተቀባብለንና ተረዳድተን በመኖር በትዳራችን በታማኝነት ለመዝለቅ ሚዛናዊ የሆነ ግንዛቤ፣ ጥበቃና ግምት ሊኖረን ይገባል። በከፍተኛ ጥበቃ በአየር ላይ እንዳንንሳፈፍ ደግሞም በዝቅተኛ ግምት ፈጽሞ ነገር ሁሉ ተገላቢጦሽ ሆኖብን በትዳር ቀውስ እንዳንሰቃይ ሚዛናችንን ጠብቀን መሬት መርገጥ ይሻለናል።

## 6. የችሎታና ልምድ አለመኖር

እያንዳንዱ ሰው የተለያየ ችሎታና ልምምድ አለው። ሁሉም ሰው አንድ ዓይነት ችሎታና ልምምድ ሊኖረው አይችልም። የትዳር ግንኙነት አስፈላጊ ከሚሆንባቸው ምክንያቶች አንዱ ባለን የተለያየ ችሎታና ልምምድ እርስ በርስ ለመረዳዳት እንድንች ነው። በትዳር ግንኙነት ውስጥ ጥንዶች እርስ በርሳቸው አንዱ የሌላውን ችሎታና ልምድ መለየትና መረዳት ካልቻሉ አንዱ ሌላውን እንዲመስል፣ እንደሌላው እንዲሰራና እንዲለማመድ የሚያደርጉት ጥረት ግጭት እንዲፈጠርና አብሯቸው እንዲሰነብት ሊያደርግ ይችላል።

ጥንዶቹ በጋብቻ የቆዩበት ዘመን አጭር ከመሆኑ የተነሳ አንዱ የሌላውን ችሎታና የግል ልምምድ ለመረዳት ሊቸገሩ ይችላሉ። ምናልባት ይህ ደረጃ አንዱ የሌላውን ማንነት፣ ችሎታና ልምምድ ለማወቅና ለመረዳት ጥረት የሚያደርጉበት ወቅት ሊሆን ይችላል። በጋብቻ ውስጥ የትዳር አጋር ችሎታዎችና ልምዶች በተለያዩ ደረጃዎችና ራሳቸውን በቻሉ ወቅቶች የመታየት ባህርይ እንዳላቸው መረዳት ያስፈልጋል። በቅርብ በተጋቡ ጥንዶች ሕብረት ውስጥ ግጭት እንዳይጠፋ ከሚያደርገው ምክንያት አንዱ ያሉበት ደረጃ አንዳቸው የሌላቸውን ችሎታ፣ ክህሎትና ልምድ ለማወቅ ጥረት የሚያደርጉበት ወቅት መሆኑን መገንዘብ አለመቻላቸው ነው።

ችሎታዎችና የተለያዩ ልምዶች ልንማራቸው የምንችላቸው ናቸው፡፡ ስለዚህ ለማወቅ፣ ለመማርና ለመለወጥ ዝግጁ መሆን ተገቢ ነው። ሁሉን ለማወቅ መማርና መልመድ አለብህ/ሽ/ በሚል ግትርነት እንዳንጋጭ አንዱ የሌላውን ጉድለት በመሙላትና በመረዳዳት በልዩነት ያለውን ውበት አድምቀን ለማሳየት ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብናል። እዚህ ላይ አንድ የራሴን ልምድ ላካፍላችሁ:- እኔ ለብዙ አመታት በቤተሰብ ቤትና በምግብ ቤት እየፈረመና እየገዛ ይመገብ የነበረ እንዲሁም በትምህርት ቤት ውስጥ ዶርም ይዞ በመማር እዚያው እየተመገበ ያሳለፍኩ ከዚያም በጋብቻ ውስጥ ለተወሰነ ዓመት ምግብ ማብሰል የማይችልና ምግብ የማብሰል ፍላጎትም ያልነበረው ሰው ነበርኩኝ፡፡ አንድ ቀን በየወሩ በመገናኘት የምንማርበትና የምንመካከርበት የባለትዳሮች ፕሮግራም ላይ በተነሳ አንድ ጥያቄና በአንዲት እህት ማበረታቻ ቀላል ነገር ማለትም

ቁርስ ከዚያም ሌሎችን ነገሮች በተለይ ሚስቴ የምትወደውን ጥቂት ነገር ማብሰልና ማቅረብ ጀመርኩ።

በዚህ ምግብ የማብሰል መልመድ ሂደት ከፍተኛ እገዛ ያደረገልኝ አንደኛው ምክንያት የመጀመሪያዋ እህት ማበረታቻ ነው:: ነገር ግን በተለይ የምሰራው ሁሉ ለሚስቴ የሚጥማትና የምትወደው መሆኑ ትልቅ የሞራልና የጽናት ስንቅ ሆኖኛል። በዚህ ወቅት ምግብ ማብሰል መልመድ መቻሌ ባለቤቴ ባረገዘችና በወለደች ወቅት እንዳንቸገር ጠቅሞናል። የማልችለውን ለመልመድ እኔ እንዲህ መለወጥ ከቻልኩ እንደ እኔ ልምድ የሌላችሁ ልትለምዱና ልትማሩ የምትችሉት ብዙ ነገር አለ ማለት ነው! ችሎታውና በቂ ልምድ ያለው የትዳር አጋር ሌላውን ሰው ለማስተማርና ለማሰልጠን በልበ ሰፊነት እድል ሊሰጥና ደግሞም አንድ ሰው ተሳስቶና አበላሽቶ የሚማርና የሚሻሻል ፍጡር መሆኑን ሊያስተውል ይገባል።

## 7. ግልጥ ኃላፊነትና ሚና አለመኖሩና ካለም ደግሞ እንደሚገባ አለመወጣት

ጋብቻ የተለያየ የሥራ ኃላፊነትና ሚና ያለበት ተቋም ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ግልጥ አድርጎ እንደሚያስቀምጠው በጋብቻ ውስጥ ባልና ሚስት የየራሳቸው ሚና አላቸው:: እርሱ ባል (ወንድ)እርሷ ደግሞ ሚስት (ሴት)ናቸው:: ለልጆቻቸው የአባትነትና የእናትነት ኃላፊነት አለባቸው /ኤፌ 5፡ 21-31 እና 6፡ 1-4/። መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ ኃላፊነትና ሚናን አለመረዳትና መወጣት አለመቻል በዚህ የተነሳ የሚፈጠሩ ችግሮች (ግጭቶች) እንዳይበርዱ ያደርጋል። ግልጥ ባልሆነው ሚናቸው ምክንያትም ባልና ሚስት ያለአግባብ ጥቅስ እየተማዘዙ የሌላውን አካል ሚና ለማሳወቅ፣ ለማሳመንና ለማዘዝ በሚያደርጉት ጥረት ጠብ ውስጥ ይገባሉ። የተፈጠረው ጠብና ንትርክም ልጆች ሲወለዱ ልጆችን ተንከባክቦ በማሳደግ የአባትነትና የእናትነት ሚናን በመወጣት ሂደት ውስጥ የባሰ ግጭት እንዲፈጠር ሊያደረግ ይችላል።

ጥንዶች በጋብቻ ሕብረት ውስጥ ገና መኖር የጀመሩ ከመሆናቸው የተነሳ በቤት ውስጥ ያላቸው የሥራ ኃላፊነት ብዙም ግልጥ ላይሆን ይችላል። ምናልባትም ከባህል አንጻር የሴቶችና የወንዶች የሥራ ድርሻ በማለት ሥራን ሊከፋፈሉ ይችሉ ይሆናል። በእርግጥ የወንድና የሴት የሥራ ድርሻ የሚለውን ልምዳችንን እንድንለውጥ ተጽዕኖ የሚያደርጉብን የአመለካከትና የሁኔታ ግፊቶች በየጊዜው መፈጠራቸው አይቀሬ ነው:: በተለይ ከአገር ውጭ የምንኖር ወገኖችን የዘመን መለዋወጥ፣ የምንኖርበትን አገር ውጥረትና ኑሮን የማሸነፍ ትግልና የምንሠራቸው ልዩ ልዩ ሥራዎች ጫናዎች በጾታ ሳይሆን በችሎታ፣ በልምድና ጊዜ ያለው ሰው ሥራዎችን እንዲሠራና በጋራ የሥራ ኃላፊነታችንን እንድንወጣ እያስገደዱን ናቸው:: ቢሆንም ግን ሁሉም ሰው ወደ ለውጥ መጥቷል ማለት አይደለም። ከልጅነቴ ጀምሮ ሥራ አይወድም እየተባልኩ ያደግሁና ሌላ ሰው በሚሠራው ሥራ በማትረካ ባለሙያ እናት እጅ ያደገ ሰው ከመሆኔ የተነሳ ከቤት





ውስጥ ሥራዎች እጅግ በጣም የራቅሁ ሰው ነበርኩ:: ነገር ግን በትዳር ዓለም እንዲሁ መቀጠል የሚቻል ሆኖ አላገኘሁትም።

የግድ ባለቤቴን ማገዝ፣ ልጆቼን ማሳደግና የጋራ ቤታችን ውስጥ በጋራ መንቀሳቀስ አለብን! ነገር ግን አሁንም የተለያዩ ቢሎችን እንድከፍል ኃላፊነት በተደጋጋሚ ሲሰጠኝ ኃላፊነቱን እሺ ብዬ ብቀበልም እንኳ እስካሁን ምክንያቱን በገልጥ ባላውቅም ቢሎችን የመክፈሉን ሥራ ተሳክቶልኝ ተወጥቸው አላውቅም። በዚህ ጉዳይ ላይ አንዳንድ ጊዜ ባለቤቴ እኔ ምን አገባኝ መብራቱንና ስልኩን፣ ኢንተርኔቱን፣ የቴሌቪዥኑን መስመር ይቁረጡት በማለት ትዝተብኛለች:: በኋላ ግን ልሠራው ያልቻልኩትን ሥራ እርሷ አቀላጥፋ ትፈጽመዋለች። እስካሁን በቤታችን ጉዳይ ከውጭ ሥራዎች ጋር የምታገናኝን እርሷ ናት:: ነገር ግን **"የቤታችን የውጭ ጉዳይ ከብርት ሚኒስቴር"** እንድትሆን የቀረበላትን የእኔን የባሏን ሹመት መቀበል አልፈለገችም:: ምክንያቱም ሹመቱን የሰጠሁበትን መነሻ አሳብ አሳምራ ታውቀዋለች!!

ለምሳሌ ለመጥቀስ ያክል እንደ አጋጣሚ ሆኖ በቤት ውስጥ ቤትን መጥረግ፣ ማጽዳትና ልብስ ላውንደሪ ማድረግ በመጠኑም ቢሆን ደስ የሚለኝና በአብዛኛው እኔ የምሠራው ሥራ ሲሆን እርሷ ደግሞ እነዚህን ሁለት ነገሮች በመጠኑም ቢሆን ትጠላለች። የባለቤቴን የሥራ ዩኒፎርም ይበልጥ እንዲነጻ በሚል በጎ ሃሳብ ለነጭ ልብስ ማንጫ በማይሆን ባለቀለም የሆኑ ልብሶች ላውንደሪ ላይ በመጠቀም ብዙ ዩኒፎርሞቿን ዝንጉርጉር በማድረግ ያበላሸሁባት ቀናትም ትዝ ይሉኛል። ለእርሷ ደግሞ ምግባችንን በማብሰል፣ ፍላጎታችንን በማወቅና ወደ ገበያ ወጥታ አስፈላጊ የሆኑ የቤት ወጭዎችን በማድረግ አስቤዛ፣ ፍጆታና ዕቃዎችን መገዛዛትና ማቅረብ ተጠቃሽ ኃላፊነቶቿ ናቸው።

## 8. በየጊዜው የተለያዩ ለውጦች በባለትዳሮች መካከል መፈጠር

ጥንዶች ተፈጥሯዊ የሆኑ አካላዊ ለውጦች አሏቸው። በዚህ ሂደት ውስጥ ለውጦች ለግጭት ምክንያት ግጭቶችም ለለውጥ ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ። በጥንዶች ሕይወት በተፈጥሯዊ የሰውነት ንጥረ ነገር (ሆርሞን) በተለይ ደግሞ በሴቶች ላይ በየወሩ የሚከሰት በወር አበባ ምክንያት የስሜት፣ የጸባይና ሌሎች ከወር አበባ ጋር ተያይዘው የሚፈጠሩ ሁኔታዎችን ጥንዶቹ በጋራ መረዳት ካልቻሉ ወቅታዊና ቀጣይነት ያለው ግጭት መፈጠር ምክንያት ሊሆን ይችላል።

ሌላው ከሆርሞን ጋር በተያያዘና በዕድሜ መጨመር ምክንያት፣ በክብደት መጨመርና መቀነስ፣ በእርግዝና፣ በልጆች መወለድ፣ ከስራ በመቀነስ የመሳሰሉ ምክንያቶች ለውጦች ድንገት ሳይታሰቡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ታቅደው ሊፈጠሩ ይችላሉ። ጥንዶች የተለያዩ ለውጦችን ለማስተናገድ እንዲችሉ ቅድመ እውቀቱ፣ ዝግጅቱ እንዲሁም ለውጡን ለማስተናገድ ፈቃደኛነቱ ከሌላቸው ግጭት መፈጠር ብቻ ሳይሆን ግጭቱ ተባብሶ ወደማይፈለግ ሌላ አቅጣጫ ሊለወጥ ይችላል።

ሌላው አስቸጋሪ የሆነውና ለሌሎች ችግሮች አሳልፎ ሊሰጥ የሚችለው ለውጥ የባሕርይ ለውጥ ችግር ነው። ባለትዳሮች በየጊዜው የሚቆጡ፣ የማይግባቡ፣ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ ቁጣቸውን መቆጣጠር የማይችሉ፣ ትንሹን ነገር ትልቅ በማድረግ የሚናደዱና ሲናደዱ የሚያደረጉትን የማያውቁ ሰዎች መሆን ሲጀምሩ በቤተሰብ ውስጥ ያልታሰቡ ቀውሶች ይፈጠራሉ። ሌላው ከፉ ቀውስ የሚፈጠረው ራስ ወዳድነት የሚባለው የተደበቀና የተገለጠ ባሕርይ ሲኖር ነው። ከትዳር አጋር ይልቅ ለራስ፣ ከእኔ፣ ለእኔ፣ በእኔ በኩል ብቻ የሚሉ ግለኝነትን ማዕከል ያደረጉ ባሕርያት ትዳርን ከፉኛ የሚያቃውሱ ጠንቆች ናቸው። በራስ ወዳድነት የተጠመደ ማንነት ያለው የትዳር አጋር ቀናተኛ፣ ነገሮችን ሁሉ ልቆጣጠር የሚል፣ እኔ ያልኩት ብቻ ይሁን ባይና አምባገነንነት የሚያጠቃው ነው። ይህ ዓይነት ባሕርይ ያላቸው ባለትዳሮች *"በአንድ አሳብ ተስማሙ፥ አንድ ፍቅር አንድም ልብ አንድም አሳብ ይሁንላችሁ፤"* /ፊል 1፡ 2/ የሚለውን የጳውሎስ ምክር በመዘንጋት በእኔነት ታውረው መስማማት ሲያቅታቸውና ሲጋጩ ይታያሉ።

በከፉ እኔነት የተጠመዱ ባለትዳር የሆኑ ሰዎች ለሌላው አካል የሚያደርጉትን ሁሉ በከንቱ ውዳሴ የሚያደርጉ ናቸው:: ነገር ግን ከትዳር አጋራቸው ይልቅ እንደሚሻሉ የሚያስቡና የሚቆጥሩ፣ ከትዳር አጋራቸው ይልቅ ለግል ጥቅማቸውና ፍላጎታቸው ትኩረት የሚሰጡና የክርስቶስን ምሳሌነት ከመከተል ይልቅ የሚያስነቅፉ ሁነው ይታያሉ /ፊል 2፡ 1-5/። በትዳራችን መካከል የተፈጠሩ አለመግባባቶችና ግጭቶች እንዲሁም ለመስማማት በሚደረገው ሂደት ይቅርታ ማድረግን ለመለማመድ እንድንቸገር ያደረጉንን ምክንያቶች በፐርሰንት እናስቀምጥ ብንል ሊያመዝን የሚችለው የእኔነታችን ጉዳይ መሆኑ አጠያያቂ አይሆንም።

## 9. የመንፈሳዊ ብስለት ልዩነት

በጥንዶች መካከል አንድነትና ልዩነት ከሚንጸባረቅበት ጉዳይ አንዱ መንፈሳዊ ማንነታችን ነው። መንፈሳዊ ብስለታችን እንደ ክርስትና ዕድሜያችን ወይም በክርስትና ሕይወት በቆየንበት ዘመን መጠን ለመማር፣ ለማደግና ለመለወጥ እንዳለፍንባቸው ሂደቶች የተለያዩ ናቸው:: በዙሪያችን ያሉ ሰዎችና ሌሎችም ሁኔታዎች ሁሉ ተጨማምረው ብስለታችን ላይ ከፍተኛ የሆነ ተጽዕኖ ማምጣታቸው አይቀሬ ነው። በእነዚህ ምክንያቶች ባልና ሚስት በተመሳሳይ የመንፈሳዊ ብስለት ደረጃ ላይ ላይሆኑ ይችላሉ:: ይህም ልዩነት እይታቸው፣ እሴቶቻቸውና ራዕዮቻቸው ላይ ተጽዕኖ ሊፈጥር ይችላል። ልዩነቶችን በመቻቻልና አንዱ ከሌላው ለመማር በተዘጋጀ ማንነት ማራመድ ካልቻሉ ግጭት መኖሩ የማይቀር ነው::

በቆሮንጦስ ቤተ ክርስቲያን ለነበረው አለመግባባትና መከፋፋል ምክንያቱ በወቅቱ የነበራቸው መንፈሳዊ ሕጻንነት ወይም አለማደግ ነበር። *"እኔም፥ ወንድሞች ሆይ፥ የሥጋ እንደ መሆናችሁ፥ በክርስቶስም ሕፃናት እንደ መሆናችሁ እንጂ መንፈሳውያን እንደ መሆናችሁ ልናገራችሁ አልቻልሁም። ገና ጽኑ መብል ለመብላት አትችሉም ነበርና ወተት ጋትኋችሁ፤ ገና ሥጋውያን ናችሁና እስከ አሁን ድረስ ገና አትችሉም። ቅናትና ክርክር ስለሚገኝባችሁ ሥጋውያን መሆናችሁ አይደላችሁምን? እንደ ሰው ልማድስ አትመላለሱምን?"* /1ኛቆሮ 3፡ 1-3/:: መርሳት የሌለብን ነገር ቢኖር ጠብ የበዛበት ትዳር ጠብን ልምምድ ያደረገ ቤተሰብን እንደሚያፈራና በብዙ ጥላቻና መከፋፈል የተሞላች ቤተ ክርስቲያን እንድትኖር አስተዋጽዖ ሊያደረግ እንደሚችል መገንዘብ አስፈላጊ መሆኑን ነው:: የመልካም ቤተ ክርስቲያን መሠረት የሚጣለው መልካም ትዳር ባላቸው ጥንዶችና ባፈሯቸው መልካም የቤተሰብ አባላት ላይ ነው።





## 10. ሚዛኑን ባልጠበቀ ሁኔታ ከትዳርና ከቤተሰብ ይልቅ በሌሎች ጉዳዮች መጠመድ

በሕይወት፣ በኑሮና በማሕበራዊ ጉዳይ አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮች ኖረው ነገር ግን ቅድሚያ መሰጠት ያለበትን ነገር እንደሚገባ ባለመረዳትና ሚዛኑን ባልጠበቀ ሁኔታ አንዱ የትዳር አጋር ጽንፈኛ ሲሆን፣ በጥብቅ ቁጥጥር ሥር ሲሆን ወይም በትዳሩና በቤተሰቡ የሚተካው እንቅስቃሴ ወይም ልምምድ ሲኖር ግጭት ሊፈጠር ይችላል። ሥራ መሥራት አስፈላጊ ነው። ቃሉም እንደሚናገረውና እንደሚያዘው *"ሊሠራ የማይወድ አይብላ..."* /2ኛተሰ 3፡10/:: ነገር ግን በዚህ ክፍል ለግጭት ምክንያት ሊሆን የሚችለው አንዱ የትዳር አጋር ከመጠን ባለፈ በሥራ ላይ ጊዜውን ሲሰጥ፣ ትኩረት ሲያደርግ፣ በሥራ የመጠመድ ሱሰኛ ሲሆን፣ ለእርሱ ሥራ ማለት ሁለንተናውና የራሱ ዓለም ሲሆንበት ነው።

አንዳንዶች ደግሞ እግዚአብሔር ለጥንዶቹ የጋራ ልጆች ይሆኑ ዘንድ ስጦታ አድርጎ ልጆችን ሰጥቷቸው ሳለ አንዱ የትዳር አጋር የግል ልጆች እስኪመስሉ ድረስ በልጆች ላይ ልዩ ትኩረት ሲያደርግና ለልጆች ብቻ ጊዜውን፣ ትኩረቱንና ሁለንተናውን ሲሰጥና የትዳር አጋሩን ችላ ማለት ሲጀምር ግጭት መፈጠሩ አይቀሬ ነው። ማገልገል እንደ ክርስቲያን አስፈላጊና እግዚአብሔርም ሆነ ቤተ ክርስቲያን የሚጠብቁብን ኃላፊነት ነው። ነገር ግን አንዳንዶች ደግሞ ከመጠን በማለፍና ሚዛኑን ባልጠበቀ ሁኔታ በአገልግሎትና በቤተ ክርስቲያን በተለያዩ ፕሮግራሞች መጠመዳቸውና ትዳርንና ቤተሰብን ችላ ማለታቸው ግጭት ሊፈጠር ይችላል። በአጠቃላይ ከትዳር አጋርና ከቤተሰብ ይልቅ ሚዛናዊ ባልሆነና ጽንፈኝነት በተሞላው መንገድ በሌሎች እንቅስቃሴዎች፣ ነገሮች፣ ልምምዶች፣ ግንኙነቶችና ፕሮግራሞች ላይ መጠመድ ወይም መወሰድ ጥንዶችን ለግጭት ሊያጋልጣቸው ይችላል።

**መልካም ምስክርነት ላላት ቤተ ክርስቲያን መሠረት የሚጣለው መልካም ትዳር ባላቸው ጥንዶችና ባፈሯቸው መልካም የቤተሰብ አባላት መሆኑን አንዘንጋ!!**

## 11. የሰይጣን ውጊያ

በትዳር ሕይወት ውስጥ የምንኖረው የሰይጣንን አሳብ በመሳትና የእርሱን ተጽዕኖ ዝቅተኛ አድርገን በማየት መሆን እንደሌለበት እንድትገነዘቡ እወዳለሁ። ከፍጥረት መጀመሪያ ባለትዳሮችን በኃጢአት ያሳሳተ፣ እርስ በርሳቸው አንዱ ሌላውን እንዲወቅሱና እንዲያመካኙ በማድረግ ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸውን መልካም ግንኙነት ያበላሸ የአሳቹ ሰይጣን ተጽዕኖ ነው። አሁን ባለንበት ዘመን ዓለም በክፉ እንድትሞላ፣ በብዙ ክፉ ተጽዕኖ ምክንያት የብዙዎች ትዳር እንዲፈርስ፣ ቤተሰብ እንዲበተንና ቤተ ክርስቲያን እንድትዳከም ከፍተኛ እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል።

አሁንም በባለትዳሮች መካከል ጠብን በመዝራት፣ አንዱ ሌላውን እንዳይረዳ በማድረግ፣ በብዙ የኃጢአት ፈተና እንዲወድቁ ወጥመድ በማዘጋጀት፣ የይቅርታ ልብ እንዳይኖራቸው በእኔነት በመሙላት፣ መለያየትና መፋታት በማንኛውም ሁኔታ የሚፈቀድና ቀላል እንደሆነ አድርጎ በማቅረብ ቅዱሳንን እየተፈታተነ ይገኛል። ብዙ ሁኔታዎችን በመጠቀም ባለትዳሮች ለትዳር አጋሮቻቸው ታማኝ እንዳይሆኑ፣ የከበረው የሁለት ተቃራኒ ጾታ ያላቸው ሰዎች አንድነት የሆነውን ትዳር በከፍተኛ ሁኔታ በተመሳሳይ ጾታ ትዳር እንዲለወጥ ዘመናዊነትንና ሰብአዊነትን እየተጠቀመ ያለበት ዘመን ነው። በአጠቃላይ የተዋረደውን እንደ ክቡር፣ አመጹን እንደ ጽድቅ፣ የሚያሳዝነውን እንደሚያስደስት እያደረገ ትዳርን፣ ቤተሰብንና ቤተ ክርስቲያንን እየተገዳደረ ይታያል /1ኛጴጥ 5፡ 8-9/





## ለጥንዶች በግላቸውና በቡድን ለማጥናት የሚረዷቸው የውይይት ጥያቄዎች

## የምዕራፍ ሁለት (2)

## የውይይት ጥያቄዎች

1. መጽሐፍ ቅዱስንና የግል የትዳር ግንኙነት መርሆዎችን መሠረት በማደርግ የግጭትን ምንነት በመተርጎምና በማብራራት ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲኖራችሁ ተወያዩ::
2. ከአጠቃላይ የግጭት ተጽዕኖ ምንነትና በግል የትዳር ሕይወታችሁ የተፈጠሩትን የተለያዩ ተጽዕኖዎች በመጥቀስ የግጭትን አዎንታዊና አሉታዊ ተጽዕኖዎች ለእውነተኛ ለውጥ ለመጠቀም በግልጥነት ውይይት አድርጉ::
3. በባለትዳሮች መካከል አለመግባባትንና ግጭትን አይቀሬ ያደረጉ ምክንያቶች ምንድን ናቸው? በእናንተ የትዳር ግንኙነት ውስጥ ግጭት እንዳይቀር ያደረገው ምክንያት ምንድን ነው? እንዴትስ ልዩነቶችን በመረዳት ግጭትን በአግባቡ መፍታት ይቻላል ትላላችሁ?
4. በእናንተ የትዳር ሕይወት በአብዛኛው ጎልቶ ለግጭት ምክንያት የሚሆነውን ጉዳይ ለይታችሁ በማውጣትና የመፍትሔ እርምጃው ምን መሆን እንዳለበት በመፈለግ ግልጥና ሰፊ ውይይት አድርጉ::
5. በዚህ ዘመን ሰይጣን ትዳርን፣ ቤተሰብንና ቤተ ክርስቲያንን እየተዋጋ ያለበትን የተለያየ ዘዴ በመጥቀስ እንደ ክርስቲያን ባለትዳርና ቤተሰብ ከግል ትዳራችሁ ጀምሮ በቤተ ክርስቲያን ምን ሊደረግ ይገባል ትላላችሁ?

# ምዕራፍ ሶስት(3)

## ግጭትን በወቅቱ በጋራ ያለመፍታት የሚፈጥረው ተጽዕኖ

በማንኛውም የጋብቻ የዕድሜ ክልል ያሉ ባለትዳሮች መካከል አለመግባባትና ግጭት መፈጠሩ አይቀሬ መሆኑ የምንስማማበት ጉዳይ ነው። ግጭቶች አሉታዊና አዎንታዊ ገጽታዎችን ይፈጥራሉ። አለመግባባቶችንና ግጭቶችን በአግባብ ካልፈታናቸውና ካልተቆጣጠርናቸው ደግሞ በጥንዶች ላይ ፈጥረዋቸው ሊያልፉ የሚችሉ አሉታዊ ተጽዕኖዎች በቀላሉ የሚታዩ አይደሉም። ይህ ምዕራፍ ግጭቶች በማስተዋልና በብስለት በጋራ መፍትሔ ካለተፈለገላቸው በጥንዶች የተለያዩ የሕይወት አቅጣጫዎች ላይ ሊፈጥሯቸው የሚችሏቸውን ተጽዕኖዎች የመረዳትና የመጠንቀቅ አስፈላጊነት ላይ ትኩረት ያደርጋል:: ባለትዳሮች የግጭቶችን ተጽዕኖዎች ቀንሰው ጤነኛ ትዳርና በመልካም ግንኙነት ላይ የተገነባ ቤተሰብ እንዲኖራቸው የሚያስችል ግንዛቤን ማስጨበጥ የዚህ ምዕራፍ አብይ ዓላማ ነው።

### 1. በጥንዶች የፍቅር ግንኙነት ላይ

በየጊዜው በባለትዳሮች መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶችና ግጭቶች ከሚፈጥሩት አሉታዊ የሆነ ተጽዕኖ መካከል አንዱ በጥንዶች መካከል በነበረ፣ ባለና ሊኖር በሚገባው የፍቅር ግንኙነት ላይ ከፍተኛ የሆነ ተጽዕኖ ማምጣት ነው። ግጭት በአግባቡ ካልተፈታ የጋብቻ መሠረት የሆነውን እውነተኛ ፍቅር እያደገ፣ እየበሰለና እየጨመረ እንዳይሄድ፣ ባለበት እንዲቀጥልና ፈጽሞ እንዲጠፋ ሊያደረግ ይችላል። ጥንዶች በጋራ ተሳስበው እንዲኖሩ አንቀሳቃሽና ዘላቂነት ያለው መልካም ግንኙነት እንዲኖራቸው የሚያደርገውን ፍቅር ጥያቄ ውስጥ እንዲገባ አፍራሽ ተጽዕኖ ያሳርፍበታል። ባለትዳሮች አውቀዋቸው ትዳራቸውን ከእነዚህ ችግሮች ለመጠበቅ ይችሉ ዘንድ የግጭት በጊዜ አለመፈታት በባለትዳሮች ሕይወትና የትዳር ግንኙነት ላይ ከሚያሳድራቸው አፍራሽ ተጽዕኖዎች ጥቂቶቹን እንደሚከተለው እንቃኛለን:-

#### 1. ፍቅርን የማቀዝቀዝ

ፍቅር በጋብቻ ውስጥ እንደ ከትባት አንዴ ወስደነው ከዚያ እንዲሁ የምንኖረው አይደለም:: ፍቅር በጋብቻ ውስጥ በየጊዜው አንዱ ለሌላው በመጠንቀቅ፣ በራስ ወዳድነት ሳይሆን ለሌላው በማሰብና በመኖር፣ በተለያዩ ጉዳቶች ላይ በመነጋገርና በይቅርታ፣ አብሮ ጊዜ በማሳለፍና አንዱ የሌላውን ፍላጎት በመረዳትና በማሟላት የምንጠብቀው፣ የምናሳድገውና የምንንከባከበው ኑሮ ነው። በየጊዜው ተመሳሳይና የማያቋርጥ አለመግባባትና ግጭት የሚበዛበት ትዳር በጥንዶቹ ሕይወት ፍቅርን የማቀዝቀዝ ተጽዕኖ አለው። *"ከዓመፃም ብዛት የተነሣ የብዙ ሰዎች ፍቅር ትቀዘቅዛለች።"* /ማቴ 24፡ 12/ ግጭት በባለትዳሮች መካከል ፍቅርን የማቀዝቀዝ አቅም እንዳለው በመረዳት ፈጥኖ ከዚህ ችግር ለመውጣትና ፍቅርን ለማደስ የጋራ ጥረት ማደረግ ተገቢ ነው። *"ዳሩ ግን የምነቅፍብህ ነገር አለኝ የቀደመውን ፍቅርህን ትተሃልና። እንግዲህ ከወዴት እንደ ወደቅህ አስብ ንስሐም ግባ የቀደመውንም ሥራህን አድርግ፤ አለዚያ እመጣብሃለሁ ንስሐም ባትገባ መቅረዝህን ከስፍራው አወስዳለሁ።"* /ራዕይ 2፡ 4-5/ በዚህ ክፍል ውስጥ ያለው ሃሳብ ለጌታ ያላቸውን ፍቅር ቢገልጡም ነገር ግን በተለያዩ ግጭቶች ምክንያት በጥንዶች መካከል የቅርብ ግንኙነት መጥፋት ከጀመረና ፍቅር ከቀዘቀዘ ለጌታ እውነተኛ ፍቅር የሌላቸው መሆኑን እንዲሁም እወድሃለሁ ያሉትን ጌታ የማስደስት ሕይወት በመምራት ላይ እንደማይገኙ የሚጠቁም ነው:: በእርግጥ የተጠቀሰው ክፍል በቀጥታ በትዳር ውስጥ ስላለ ፍቅር የሚናገር ሳይሆን በአማኞች መካከል ስላለ ፍቅር የሚናገር ነው። ነገር ግን ማስተዋል ያለብን የመጀመሪያዎቹ በቅርባችን ያሉ አማኞች የትዳር አጋሮቻችን መሆናቸውን ነው። ይህንን ክፍልም የጠቀስኩት አንድ ሰው ለትዳር ጓደኛው ፍቅር የሌለው ከሆነ ለሌሎች ወገኖች ብሎም ለክርስቶስ ኢየሱስ ያለው ፍቅር ቀዝቃዛ መሆኑንና የበለጠ የመቀዝቀዝ እድል እንደሚኖረውም ለማስጨበጥ ነው። በቅርቡ ያለውን የትዳር አጋሩን የማይወድድ ሰው በርቀት ያሉ ወገኖች እና ክርስቶስን እወድዳለሁ ሊል እንዴት ይችላል!

#### 2. አለመተማመንን የመፍጠር

ግጭት በአግባቡ ካልተፈታ ጥንዶቹ በፍቅርና እርስ በርስ በመተማመን ይኖሩበት የነበረው የትዳር መርሆ እንዲቀየር የማድረግ ተጽዕኖ አለው። እውነተኛ ፍቅር በጥንዶቹ መካከል ሲኖር አንዱ ሌላውን በማመን የመቀባበል ሕይወት ጎልቶ ይታይባቸዋል። እውነተኛ ፍቅር ሲኖር ባለመተማመን የሚፈጠርን ፍርሃት አውጥቶ ይጥላል። በማማከር አገልግሎት ከገጠሙኝና ካደመጥኳቸው ንግግሮች መካከል *"ከእንግዲህ ማመን ይከብደኛል" "እንዳላምነው/ናት/ አደረገኝ"፣ "አምኖ አብሮ መኖር ከበደኝ"* እና *"አመኔታ የምትጥልበት አይደለም"* የሚሉ የተለያዩ ቃላቶች ይገኙበታል:: *"ፍጹም ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል እንጂ በፍቅር ፍርሃት የለም፥ ፍርሃት ቅጣት አለውና፤ የሚፈራም ሰው ፍቅሩ ፍጹም አይደለም።"* /1ኛዮሐ 4፡ 18/ *"ፍቅር ሁሉን ያምናል፣ ሁሉን ተስፋ ያደረጋል"* ይላልና /1ኛቆሮ 13፡ 7/ አለመግባባትና ግጭት በባለትዳሮች መካከል የነበራቸውን የእውነተኛ ፍቅር ባሕርይ መገለጫ የሆነውን መተማመንን ወደ ፍርሃትና አለመተማመን ይለውጣል።

#### 3. ግንኙነትን የማሻከር

ሌላው የግጭት አሉታዊ ተጽዕኖ በባለትዳሮች መካከል ያለውን መልካም ግንኙነት ማሻከርና መልካም ተግባቦት እንዳይኖራቸው ማድረግ ነው። ግጭት በፍቅር ተሸፍኖና ተቻችሎ የመኖር መርህ ተለውጦ በጠብና በጥላቻ ለከፍተኛ ጠብ ለመፈላለግ ተጋላጭ ሊያደረጋቸው ይችላል። በባለትዳሮች መካከል በቀላል ግንኙነት፣ በነፃነት፣ በበጎ ህሊና፣ በቀጥተኛነትና የውስጥን ስሜት በግልጥነት በማቅረብ ተገንብቶ የነበረው ተግባቦታቸው ወደሻከረ ግንኙነት በመሻገር ፍቅርን በማጥፋት ጠብን የሚያባብስ ሁኔታ ሊፈጥር ይችላል። ግጭት የሚፈጥረው አሉታዊ ተጽዕኖ በቸልታ የሚታይ ሳይሆን በማስተዋልና በብስለት ልንቆጣጠረውና ልንፈታው የሚገባ ነው።


የግጭት መንስኤዎችና መፍትሔዎቻቸው በጋብቻ ውስጥ!

## 4. ከትዳር አጋር ይልቅ የግጭቱ መንስኤ ላይ እንዲያተኩሩ የማድረግ

በባለትዳሮች መካከል የሚጋጩበት ርዕሰ ጉዳይ ዋና ምንጩ ከራስ ወዳድነት ጋር የተያያዘ በሆነ ወቅት ግጭቱን በጋራ ከመፍታትና ለትዳር አጋር ቅድሚያ ትኩረት ከመስጠት ይልቅ ችግሩ ላይና የግጭቱ መንስኤ ላይ በማተኮር ይበልጥ ግጭቱ እየጨመረ እንዲመጣ ያደርጉታል:: እርስ በእርስም ሊጎዳዱ ይችላሉ። በተለይ ተድላን ከመውደድ የሚመነጭ ግጭት ቶሎ ላያባራና ጥንዶቹ ከትዳር አጋራቸው ይልቅ ራሳቸውን፣ ገንዘብን፣ ንብረታቸውን እንዲሁም ድሎትን የበለጠ በመውደድ ላይ ብቻ ሊያተኩሩ ይችላሉ:: ለትዳር አጋራቸው ግድ የማይሰጣቸው፣ መለያየትን የሚመርጡና ቤተሰባቸውን መበተን ምንም የማይመስላቸው እንዲሆኑ ሊያደርጋቸው ይችላል። *"ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ ይሆናሉና፥ ገንዘብን የሚወዱ፥ ትምክህተኞች፥ ትዕቢተኞች፥ ተሳዳቢዎች፥ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፥ የማያመሰግኑ፥ቅድስና የሌላቸው፥ ፍቅር የሌላቸው፥ ዕርቅን የማይሰሙ፥ ሐሜተኞች፥ ራሳቸውን የማይገዙ፥ ጨካኞች፥ መልካም የሆነውን የማይወዱ፥ ከዳተኞች፥ ችኩሎች፥ በትዕቢት የተነፉ፥ ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ ይሆናሉ፤ "* /2ኛጢ.ሞ 3፡ 2-4/

## 5. መተሳሰብና መፈላለግ እንዲቀንስ የማድረግ

ትዳር ጥንዶች በጋራ እየተሳሰቡና በፍቅር እየተፈላለጉ የሚኖሩት ኪዳን ነው። የአለመግባባትና የግጭት ምክንያት የሆኑ ችግሮች በጊዜው እልባት ካላገኙና በይቅርታ መስማማት ካልተቻለ በስተቀር ባለትዳሮች ያላቸውን የእርስ በርስ መተሳሰብና መፈላለግ እንዲቀንሱ ብሎም መተሳሰብ ከመካከላቸው እንዲጠፋ የሚያደርግ ሁኔታ ውስጥ ይገባሉ። እንደ ባለትዳር አንዱ ለሌላው ማሰብ ቀንሰው ግለኝነትን የሕይወት መርህ ያደርጋሉ:: ግለኝነትን የሕይወት መርህ ማድረግ ደግሞ በተገኘው አጋጣሚ እንደ ባልና ሚስት የመፈላለግ ጥረት እንዲጠፋ የማድረግ አቅም አለው። *"ፍቅር ይታገሣል፥ ቸርነትንም ያደርጋል፤ ፍቅር አይቀናም፤ ፍቅር አይመካም፥ አይታበይም፤ የማይገባውን አያደርግም፥ የራሱንም አይፈልግም፥ አይበሳጭም፥ በደልን አይቆጥርም፤ ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ ዓመፃ ደስ አይለውም፤ ሁሉን ይታገሣል፥ ሁሉን ያምናል፥ ሁሉን ተስፋ ያደርጋል፥ በሁሉ ይጸናል።"* /1ኛቆሮ 13፡ 4-7/

## 6. አብሮ የመቀመጥና የማውራት ልምድ እንዲጠፋ የማድረግ

የጋራ የሆነ ጊዜ መመደብና አጋጣሚዎችን እየፈለጉ መገናኘት እንዲሁም ተቀምጦ በመልካም ግንኙነት ማውራት የጤናማና የደስተኛ ባለትዳሮች መለያ ነው። አለመግባባትና ግጭት ሲበዛና በየጊዜው በአግባብ ሳይፈታ ሲቀር በጋራ ትዳራቸውን ለመገንባት ሲነጋገሩ የነበሩት ጥንዶች መራራቅ ይመርጣሉ:: አብረው ከተቀመጡ የሚያወሩት የሌላቸው ይሆናሉ:: ማውራት ከጀመሩ ደግሞ ለከፋ ግጭት ተጋላጭ ይሆናሉ። ችግሩ የተከሰተው አብረው እንዲቀመጡና እንዲያወሩ ሊያደርጋቸው የሚችለው ፍቅር መቀነስ ወይም መጥፋት ስለጀመረ ነው። በተደጋጋሚ በማማከር አገልግሎቴ ከሰማሁዋቸው ንግግሮች መካከል *"አብረን መቀመጥ የምንችል ሰዎች አይደለንም"* ፣ *"ተቀምጠን ካወራን አያሌ ቀናት፣ ሳምንታትና ወራት አስቆጥረናል"*፣ *"በስንት ጊዜያችን ያውም በእኔ ተነሳሽነትና ግፊት መነጋገር ጀምረን ወዲያውኑ ስንጣላ አቆምን"*፣ *"ከእኔ ይልቅ በስልክ የሚያወራው /የምታወራው/ ይበልጣል"* የሚሉት ገጠመኞች የችግሩ ማሳያ በመሆን በምሳሌነት ሊጠቀሱ ይችላሉ።





## II. በጥንዶች ሁለንተናዊ ማንነት ላይ

የሰው ሁለንተና መንፈስ፣ ነፍስና ስጋ ያለው መሆኑን ከእግዚአብሔር ቃል ማየት እንችላለን /1ኛተሰ 5፡ 23፤ ዕብ4፡ 12/። እዚህ ላይ የምፈልገው ስለሰው ሁለንተና ለመጻፍ ሳይሆን አለመግባባትና ግጭት በባለትዳሮች ሁለንተናዊ ማንነት ላይ የሚፈጥረውን አሉታዊ ተጽዕኖ በተመለከተ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ነው። የሰው ማንነት አንዱ በሌላው ላይ ተጽዕኖ ሊያደርግ ይችላል። ከዚህም የተነሳ ግጭት በጥንዶች ሁለንተናዊ ማንነት ላይ ሊፈጥር የሚችለውን አሉታዊ ተጽዕኖ በዝርዝር መመልከት እንችላለን።

### 1. መንፈሳዊ

ግጭት በባለትዳሮች መንፈሳዊ ሕይወት ላይ የሚያመጣው አሉታዊ ተጽዕኖ ቀላል አይደለም። በጥንዶቹ መንፈሳዊ ሕይወት ላይ የሚፈጠረው ተጽዕኖ ብለን ስናስብ፡- **በመጀመሪያ** ባልና ሚስት በግልና በሕብረት ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውና ሊኖራቸው የሚገባ ሕብረት ላይ የሚፈጠረው አሉታዊ ተጽዕኖ ማለታችን ነው። በአለመግባባት ምክንያት ቅሬታ ሲፈጠር፣ እርስ በርስ ይቅር መባባል ሲያቅታቸውና በውስጣቸው የበደለኝነት ስሜት ሲፈጠርባቸው ወደ እግዚአብሔር በመቅረብ እግዚአብሔርን በቃሉና በጸሎት ከመፈለግ ይልቅ ከእግዚአብሔር ጋር ከሚደረግ ሕብረት መራቅ ግጭት የሚያስከትለው የባለትዳሮች የመንፈሳዊ ሕይወት ችግር ነው። በዚህ ምክንያት ቀድሞ የነበራቸው መንፈሳዊ ግለትና መነቃቃት ሊጠፋባቸው ይችላል። *"እንግዲህ መባህን በመሠዊያው ላይ ብታቀርብ፥ በዚያም ወንድምህ አንዳች በአንተ ላይ እንዳለው ብታስብ፥ በዚያ በመሠዊያው ፊት መባህን ትተህ ሂድ፥ አስቀድመህም ከወንድምህ ጋር ታረቅ፥ በኋላም መጥተህ መባህን አቅርብ። አብረኸው በመንገድ ሳለህ ከባላጋራህ ጋር ፈጥነህ ተስማማ፤ ባላጋራ ለዳኛ እንዳይሰጥህ ዳኛም ለሎሌው፥ ወደ ወህኒም ትጣላለህ፤"* /ማቴ 5፡ 23-25/

**በሁለተኛ ደረጃ** በጊዜ ያልተፈታ ግጭት በጥንዶቹ መንፈሳዊ ሕይወት ላይ የሚፈጥረው አሉታዊ ተጽዕኖ ከቅዱሳን ጋር የሚኖራቸው ኅብረት እንዲቀንስና እንዲጠፋ ሊያደርግ መቻሉ ነው። የግል መንፈሳዊ ሕይወታቸው መድከም ሲጀምር ከቅዱሳን ጋር ኅብረት በማድረግ በቅዱሳን የተዘጋጀውን በረከትና ጸጋ የመካፈል ትጋታቸውና ፍላጎታቸው ይቀንሳል ወይም ይጠፋል:: በሌሎች አገልግሎት ከመጠቀምና ሌሎችን ከመጥቀም ወደ ኋላ እንዲሉና ይህ ዓይነቱ መተናነጽ ግድ የማይሰጣቸው እንዲሆኑ ሊያደርጋቸው ይችላል።

**ሶስተኛውና** የመጨረሻው የግጭት አለመፈታት በመንፈሳዊ ሕይወት ላይ የሚያመጣው አሉታዊ ተጽዕኖ የነበራቸውንና ሊኖራቸው የሚችለውን የአገልግሎት መልካም ተጽዕኖ ዝቅተኛ እንዲሆን ማድረጉ ነው። በጠብና በግጭት የተሞላ ማንነትና

የትዳር ሕይወት ያላቸው ጥንዶች በግል ሕይወታቸውና በየጊዜው በቅዱሳን ሕብረት ለመልካም ሥራ የነበራቸው መነቃቃት የጠፋባቸውና ምሳሌነት የሌለው ማንነት ባለቤት ሆነው አገልግሎት ለመስጠት የሚታገሉ ይሆናሉ:: ሚስጥሩ በደንብ ባይገባውም እንኳን ተገልጋዩም ለመገልገልና አገልግሎታቸውን ለመቀበል ሊቸገር ይችላል። *"ልጆቹን በጭምትነት ሁሉ እየገዛ የራሱን ቤት በመልካም የሚያስተዳድር፤ ሰው ግን የራሱን ቤት እንዲያስተዳድር ባያውቅ፥ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን እንዴት ይጠብቃታል?"* ፩ኛጢሞ 3፡4-5

## 2. አካላዊ

በጊዜው እልባት ያላገኘ አለመግባባትና ግጭት በባለትዳሮች የሰውነት (የአካል) የጤና መታወክ ሊያስከትል ይችላል። ግጭት የጥንዶችን የውስጥ ስሜት በመጉዳት ለውጫዊ አካላዊ መጎዳት ተጋላጭ ያደርጋቸዋል። በውስጣቸው ሰላምና ደስታ የራቃቸው ጥንዶች ለሌሎች በሽታዎች ተጋላጭ ይሆናሉ:: ከአሁን በፊት የተለያዩ በሽታዎች ያሉባቸው ከሆኑ በሽታዎቻቸውን ሊያባብሱ ይችላሉ። ካለመግባባትና ከመጋጨት የተነሳ ሊከሰቱ ወይም ሊባባሱ ከሚችሉ በሽታዎች መካከል:- የጨጓራ፣ የደም ግፊት፣ የስኳር ሕመም፣ ፊት ላይ የሚወጣ ማድያትና የፊት መጨማደድ የመሳሰሉት ተጠቃሾች ናቸው። በአንዳንድ ባለትዳሮች መካከል ከቃላት ባለፈ ቁጣን መቆጣጠር አቅቷቸው የሚደባደቡና የሚጎዳዱም አይጠፉም።

በመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ ውስጥ በዲፕሎማ የክርስቲያን ሳይኮሎጅ ኮርስ በምንወስደበት ወቅት ከተማሪዎች መካከል አንዱ በወቅቱ ለሚያስተምሩን ዶክተር ጥያቄ አቀረበ። ለጥያቄው መልስ የሚሆን ማብራሪያ በማግኘት ፋንታ "አንድ የጋብቻ አስተማሪ እንዲህ ብሎ አስተማረን" በማለት ከአስተማሪው የተማረውን ትምህርት የግል እምነቱ አድረጎ ያቀረበውን አሳብ ፈጽሞ አልረሳውም! ያ ወንድም *"ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ።"* /ኤፌ 5፡ 31/ የሚለውን ጥቅስ ከጠቀሰ በኋላ ከጥቅሱ "አንድ ስጋ" የሚለውን ሀረግ በመውሰድና *"ነገር ግን ለሌሎች ከሰበክሁ በኋላ ራሴ የተጣልሁ እንዳልሆን ሥጋዬን እየጎሰምሁ አስገዛዋለሁ።"* /፩ኛቆሮ 9፡ 27/ ከሚለው ቃል ጋር በማቀናጀት መተርጎም ጀመረ። ያቀረበው የትርጉሙ አሳብ "ባል ሚስቱን ሊቀጣትና ሊመታት ወይም ሊደበድባት ይችላል" የሚል ሲሆን ከሌሎች ተግባራዊ ምስክርነቶች ጋር እያይዘ በማቅረብ ለማሳመን ጥረት አደረገ። በወቅቱ ከዚህ ወንድም ጋር እርሱ ያጣቀሰውን የጋብቻ ትምህርት የተማሩ ጥንዶች ወይም የሰሙ አገልጋዮች እርሱ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ውስጥ ሊያቀርበው የሞከረውን ይህን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ መረዳትና ልምምድ የተጋሩ ከሆነ ወደ ተለያዩ አማኞች አባዝተውት ሊሆን እንደሚችል ወይም ሊያባዙት እንደሚችሉ መገመት አያስቸግርም። እንደዚህ አይነት ትምህርት፣ ልምምድና ተግባር ቁጣን መቆጣጠር አቅቧቸው አካላዊ ጉዳት ለሚያደርሱ ግለሰቦችና ባለትዳሮች አበረታችና አጽናኝ የሆነ ነገር ግን አፍራሽ እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ ልምምድ ነው።





## 3. ስነ ልቦናዊ

በወቅቱ በጋራ ውይይትና በይቅርታ ያልተፈታ አለመግባባትና ግጭት በባለትዳሮች ስነ ልቦና ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ፈጣሪ ነው። በግጭት ምክንያት በባለትዳሮች መካከል ከሚፈጠሩ ስነ ልቦናዊ ጉዳቶች መካከል የተሰበረ ልብና የተራራረቀ ስሜት እንዲኖር ማድረጉ ተጠቃሽ ነው። ጥንዶችን በቁጣ፣ በንዴትና በምሬት እንዲሞሉና ለአጭር ጊዜም ቢሆን አዕምሮቸውን መቆጣጠር እንዲያስቸግራቸው ሊያደርግ ይችላል። ይህ ችግር ያጋጠማቸው ባለትዳሮች ብዙ ጊዜ በፍርሃት በመሞላት ለተስፋ መቁረጥና ላለመተማመን ተጋላጭ ይሆናሉ:: ብሎም በብዙ ነገር ድፍረት የሌላቸው እንዲሆኑ የማድረግ አቅምም አለው።

## 4. ማሕበራዊ ሕይወት

መልካም ትዳር ለመልካም ቤተሰብ፣ መልካም ቤተሰብ ለመልካም ቤተ ክርስቲያንና ለመልካም ሕብረተሰብ መሠረት ነው። የሰው ማሕበራዊ ሕይወት የሚጀምረው ከቤተሰቡ ነው። መልካም ግንኙነት የሌላቸውና ግጭት የበዛባቸው ባለትዳሮች ፈጥነው በይቅርታ መስማማትና ችግሮቻቸውን መፍታት ካልቻሉ ችግሩ ከእነርሱ አልፎ ቤተሰብን፣ ቤተ ዘመድን፣ ወዳጆችን፣ ጎረቤትንና ቤተ ክርስቲያንን የተጽዕኖው ሰለባ ማድረጉ አይቀሬ ነው።

በባለትዳሮች መካከል የሚፈጠረው አለመግባባትና ግጭት ጥንዶችን ከማሕበራዊ ሕይወትና ግንኙነት እንዲርቁ፣ ራሳቸውን እንዲያገልሉ፣ ከሌሎች ማለትም ከቤተሰብ፣ ከቤተ ዘመድ፣ ከወዳጆቻቸውና ከቤተ ክርስቲያን ሰዎች ጋር ያላቸው ግንኙነት እንዲበላሽና እንዲቋረጥ ያደርጋል። በተለያዩ ሚዲያዎች እየተጠቀሙ ይከውኑት የነበሩትን ማሕበራዊ ግንኙነት ማለትም የነበራቸውን የስልክ፣ የኢሜል፣ የፌስ ቡክና ሌሎችን ማሕበራዊ ድረ ገጾችን መጠቀምን እንዲተውት ያስገድዳቸዋል። ሰዎችን የመዝጋት፣ ስልክ ቁጥርና አድራሻ ማጥፋትና ቀድሞ ሲያዘወትሩባቸው ከነበሩ ቦታዎች ሁሉ የመጥፋት ባሕርይ ሊታይባቸው ይችላል ።

በጊዜው ፈጥኖ በመወያየትና በይቅርታ እልባት ያላገኘ የባለትዳሮች ግጭት አሉታዊ ተጽዕኖው ከፍተኛ ነው። ያልተፈታ ግጭት ትንሽ የነበረው ትልቅ፣ ጥቂት የነበረው ብዙ፣ ቶሎ ሊፈታ ለሚችለው አላስፈላጊ የሆነ ጊዜ በመስጠቱ ችግሩ ያልተፈለገ አቅጣጫ እንዲይዝ ሊያደርግ ይችላል:: በጥንዶች ሁለንተናዊ ማንነት ላይም አሉታዊ፣ ውስብስብና አስቸጋሪ የሆነ ገጽታ እንዲፈጠር የማስገደድ አስተዋፅጾው ከፍተኛ ነው:: አለመግባባትና ግጭት በማንኛውም ትዳር ውስጥ የማይጠፋ ልምምድ ቢሆንም ግጭቱን ፈጥኖ በመፍታት ሁኔታውን ወደ ሰላማዊ ግንኙነት ለመለወጥ ፈቃደኛ መሆን የእያንዳንዱ ባለትዳር የግል ኃላፊነት ነው:: ስለዚህ ክርስቲያን ባለትዳሮች ለዚህ ሊተጉ ይገባል:: ይህን ለማድረግና ኃላፊነትን ለመወጣት ከአቅም

በላይ የሆነ ችግር ካጋጠመ የሌሎችን ሰዎች አስፈላጊ የሆነ እርዳታ በማግኘት ችግሩን መፍታት በጣም አስፈላጊ ነው።

**መልካም ትዳር ለመልካም ቤተሰብ፣ መልካም ቤተሰብ ለመልካም ቤተ ክርስቲያንና ለመልካም ሕብረተሰብ መሠረት ነው!!**





## ለጥንዶች በግላቸውና በቡድን ለማጥናት የሚረዷቸው የውይይት ጥያቄዎች

## የምዕራፍ ሶስት (3)

## የውይይት ጥያቄዎች

1. ግጭትን በጊዜው መፍታትን እንዴት ትገልጡታላችሁ?
2. ግጭት በጊዜው በአግባብ ካልተፈታ ሊፈጥራቸው የሚችላቸው አሉታዊ ተጽዕኖዎችን በመዘርዘር በሰፋት ተወያዩባቸው::
3. በትዳር ግንኙነታችሁ የሚፈጠሩ ግጭቶችን በጊዜው በጋራ እንዳትፈቱ የሚያደርጓችሁን ምክንያቶችና በግልና በትዳር ሕይወታችሁ ያመጡባችሁን አሉታዊ ተጽዕኖዎች በመዘርዘር በፍጹም ግልጥነት ተነጋገሩ::
4. በጊዜው ያልተፈታ ግጭት በመንፈሳዊ ሕይወት ላይ የሚያመጣውን አሉታዊ ተጽዕኖ በመዘርዘርና የተለያዩ ምሳሌዎችና ምስክርነቶችን በመጨመር ውይይት አድርጉ::
5. በጊዜው መፈታት ያለባቸውን የግል የትዳር ግጭቶቻችሁን ቆም ብላችሁ በማሰብ ራሳችሁን መርምሩ:- ፈጥናችሁ እርምጃ ልትወስዱባቸው የሚገቡ የግጭት ምክንያቶች ምንድን ናቸው? ጊዜ በመበጀትና ምቹ ሁኔታን በመፍጠር ፈጣን የሆነ ተግባራዊ እርምጃ ለመውሰድ በግልና በጋራ አቅዱ::

# ምዕራፍ አራት (4)
# የተለያዩ የለውጥና የሽግግር ደረጃዎች

## I. የተለያዩ የለውጥ ደረጃዎች ምንነት

ብዙ የግንኙነት ባለሙያዎች እንደሚስማሙበት በባለትዳሮችም ሆነ ረጅም ጊዜ የቆየ ግንኙነት ባላቸው ሰዎች መካከል የተለያዩ ወቅቶችን መሠረት አድርገው የሚከሰቱ ለውጦች አሉ። እነዚህ የተለያዩ ወቅቶች የሚፈጥሯቸውን የለውጥ ሂደቶች ተከትለው ከሚፈጠሩ ግጭቶች ትዳርን የመጠበቁ ስኬት እንደ ባለትዳሮች ማንነት፣ የትዳራቸው ግንኙነት እንደተመሠረተበት መሠረት፣ ወደ ትዳር ሲገቡ ከትዳር ለማግኘት እንደሚጠብቁት ጉዳይ፣ እርስ በእርስ ይበልጥ እንደመተዋወቃቸው፣ ለተለያዩ የግንኙነት ደረጃዎች እንዳላቸው መረዳትና እንደ ጥንዶች ብስለት ሊወሰን ይችላል። በተለያየ ጊዜ የሚፈጠሩ የተለያዩ ወቅታዊ የሆኑ የሽግግር ደረጃዎች መኖራቸውን መረዳትና እንደ አመጣጣቸው ለማስተናገድ ዝግጁ መሆን፣ የለውጥ ሂደቶቹን ለመቆጣጠርና የሚያስከትሉትን አሉታዊ የሆኑ ተጽዕኖዎች አስቀድሞ ቢቻል ለማስቀረት ቢያንስ ደግሞ ጎጅ ተጽዕኖቻቸውን ለመቀነስና ተመርሮ ሳይሆን ተምሮ ለማለፍ መዘጋጀት ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው። ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በትዳር የተጣመሩ ጥንዶች ሊረዷቸው የሚገቡ በባለ ትዳሮች መካከል የሚፈጠሩ የለውጥና የሽግግር ደረጃዎች ምንድን ናቸው? የሚከተሉት ነጥቦች ይህንን የሚያስዳስሱን ይሆናሉ:-

## II. በጥንዶች መካከል ሊፈጠሩ የሚችሉ የተለያዩ ለውጦች

### 1. ሆርሞናል ለውጥ

ሆርሞናል ለውጥ በወንድና በሴት አካል ውስጥ የሚገኝ ተፈጥሯዊ የሆነ ሆርሞን በመባል በሚጠራ የተፈጥሮ ንጥረ ቅመም አማካኝነት የሚመጣ ለውጥ ነው:: በወንድ ልጅ አካል ውስጥ ቴስቶስተሮን የተባለው ንጥረ ነገር ከፍና ዝቅ ማለት የሚያመጣውና ሊፈጥረው የሚችለው አሉታዊና አዎንታዊ ተጽዕኖና የለውጥ ሂደት በትዳር ሕይወት ውስጥ ግጭት እንዲፈጠር ምክንያት ሊሆን ይችላል:: ኢስትሮጅን እየተባለ የሚጠራው በሴቶች አካል ውስጥ የሚገኝ ተፈጥሯዊ የሆነ ንጥረ ቅመም ደግሞ በሴቶች ላይ በወር አበባ ጊዜ፣ በእርግዝና፣ በወሊድና በዕድሜ ምክንያት መጨመሩና መቀነሱ የሚያመጣው ለውጥና ተጽዕኖም በትዳር ውስጥ ለሚፈጠር ግጭት አንዱ ሊጠቀስ የሚችል ምክንያት ነው:: ይህን ርዕስ ጉዳይ ማንሳት አስፈላጊ የሆነው ጥንዶች አንዱ ሌላውን እንዲረዱና እርስ በርሳቸው እንዲረዳዱ ለመጠቆም ነው። የሆርሞን ለውጥ የሚያመጣውን ተፅዕኖ በመረዳት አንዱ ለሌላው አስፈላጊ የሆነ እንክብካቤ በመስጠት ግጭትን ለመቀነስና መልካም እና ሁለተናዊ የሆነ ግንኙነት ለመፍጠር እንደሚቻል ጥንዶቹ ሊገነዘቡ ይገባል። በወንዶችም ሆነ በሴቶች ውስጥ ያለው ሆርሞን (በሰውነት





ውስጥ ያለ ንጥረ ቅመም) በጥንዶቹ ግንኙነት፣ ወሲባዊ መነሳሳትና መጣጣም፣ ስነ ልቦናዊ የባህሪ መለዋወጥ፣ የፍላጎትና የስሜት ለውጥ ብሎም ማሕበራዊ ኑሯቸው ላይ የሚፈጥረውን ተጽዕኖ በመገንዘብ ለትዳር ግንኙነት ጥንቃቄ ማድረግ  አስተዋይነት ነው::

### 2. አካላዊ ለውጥ

አንድ ሰው በመወለድ ይጀምርና በየጊዜው ሁለንተናዊ እድገት እያሳየ በመቀጠል በመጨረሻም በሞት ምድራዊ ኑሮው ይገደባል። የሰው ልጅ በራሱ ላይ የሚያስተናግደው አካላዊ እድገት፣ የሰውነት መጠን፣ የክብደት መጠንና የውበት ለውጥ በየጊዜው በዕድሜ መጨመርና በሌሎች የተለያዩ ጉዳዮች ምክንያት ለውጡ ሊፈጥንና ሊዘገይ ይችላል። ዕድሜ ሲጨምር፣ በእርግዝና፣ በወሊድና ልጅ በማሳደግ ሂደት ብሎም በአኗኗር ዘይቤና በምንኖርበት አካባቢ ተጽዕኖዎች የተነሳ በጥንዶቹ በተለይ ደግሞ በሴቶች አካል ላይ ለውጥ መኖሩ አይቀሬ ነው። ቀድሞ ከጋብቻ በፊት የነበረ ውበት፣ የሰውነት አቋም፣ ቅርጽ፣ ክብደት... በሚለወጥበት ወቅት ተፈቃቅሮና ተቀባብሎ በመኖር የትዳርን ግንኙነት መጠበቅ አስፈላጊ ነው። ከዚህ ለውጥ አንጻር ነው ያላገቡ ወጣቶች ትዳርን በውጫዊ ውበት ላይ ብቻ መመሠረት የሌለባቸው። ከውጭ የጀመሩት አድናቆት ግርዶሽ ሳይሆንባቸው ውጭውን አልፈው የውስጥን ውበት በመመልከትና በማድነቅ የትዳር ውሳኔ ላይ ሊደርሱ እንደሚገባ መመከር የሚገባቸውም ለዚህ ነው!!

### 3. ስነ ልቦናዊ ለውጥ

ሰው በየጊዜው በሚያድግበትና በተለያየ ሁኔታ ውስጥ በሚያልፍበት ሂደት ከሚያጋጥሙት ለውጦች መካከል አይቀሬ ከሆኑት አንዱ በስነ ልቦና ላይ የሚፈጠር ለውጥ ነው። ከአካባቢ ጋር የስሜት ሕዋሳትን ተጠቅሞ ግንኙነት በማድረግ፣ በማንበብ፣ በመማር፣ አካበቢ በመቀየር ለተለያዩ ነገሮች ተጋላጭ በመሆን፣ በሕይወት የሚገጥሙ የኑሮ ምርጫዎች፣ ውሳኔዎችና ተግዳሮቶች ጥለዋቸው የሚያልፉ ልምምዶች፣ ስሜቶች፣ አስተሳሰቦችና እሴቶች ስነ ልቦናዊ ለውጥ እንዲኖር ያስገድዳሉ። አንዳንድ ለውጦች ማለትም የሆርሞን (የንጥረ ቅመም)፣ አካላዊና ስሜታዊ ... ለውጦች በስነ ልቦና ላይም ተጽዕኖ ማድረጋቸው አይቀሬ ነው። ለውጦችን ከተለያዩ አዎንታዊና አሉታዊ ተጽዕኖዎች ጋር እንደሚገባ ለመረዳት ጥረት ማድረግ በጥንዶች መካከል በየጊዜው የሚፈጠርን ግጭት የመቀነስ አስተዋጽዖ ብቻ ሳይሆን አንዱ ሌላውን በመረዳት እርስ በርሳቸው እንዲረዳዱ ለማስቻል የሚሰጠው ጠቀሜታ  የጎላ ነው።

### 4. ስሜታዊ ለውጥ

የሰው ልጅ እውቀት፣ ፈቃድና ስሜት ያለው ፍጡር ነው። በሰው ሕይወት ውስጥ መደሰት እንዳለ ሁሉ የሐዘን ጊዜና ስሜት የሚቀየርባቸው አጋጣሚዎች ብዙ ናቸው። ጥንዶች ለመጋባት የቃል ኪዳን ውል ስንዋዋል በማግኘት በማጣት፣ በሕመም፣

በጤንነት፣ በደስታና በሐዘን በማለት በተለያዩ የሕይወት ገጠመኞች ሁሉ የማይሰበር ቃል ኪዳን ገብተናል፡፡ ለዚህም ነው በምንም ዓይነት የስሜት መለዋወጥ ውስጥ ስናልፍ አንዳችን ለሌላችን ታማኝ ባልና ሚስት እንድንሆን የምንጠየቀውና ቃል ኪዳናችንን በመጠበቅ አፍቃሪ ባልና ሚስት እንድንሆን ፍላጎትና ጥረት ልናሳይ የሚገባን።

በጥንዶች መካከል በየጊዜው የሚፈጠሩ አለመግባባቶች፣ ግጭቶች፣ የተለያዩ ያልታሰቡና ያልታቀዱ የሕይወትና የኑሮ ቀውሶች፣ የሕመም ስሜቶች፣ እርግዝና፣ በወሊድ ወቅትና ከወሊድ በኋላ የሚፈጠሩ የስሜት መለዋወጦች፣ ድብርቶችና ልጅ የአለመውለድ ችግሮች በትዳር ውስጥ ያጋጥማሉ፡፡ በተጨማሪም ነገሮች እንደታሰቡት ሳይሄዱ በመቅረታቸው ስሜታችን ላይ ሊፈጠሩ የሚችሉ አሉታዊ ተጽዕኖዎች፣ የስሜት ለውጦች ማለትም ደስታ፣ ለቅሶ፣ መቆዘም፣ ቁጡና ንዴታማ መሆን የመሳሰሉ የሕይወት ገጽታዎች አይቀሬ መሆናቸውን መረዳት ተገቢ ነው። የስሜት ለውጥ በሥራ፣ በግንኙነት፣ በቤተሰብ፣ በግብረ ስጋ ግንኙነት፣ በንግግር፣ በስነ ልቦና፣ በእርግዝናና በጤንነት ላይ የሚፈጥረው አሉታዊ ተጽዕኖ በቀላሉ የሚታይ አይደለምና ችላ ማለትን አስወግደን ጥንዶች እርስ በርስ በመተሳሰብ አንዳችን ለሌላችን የደስታ፣ የሳቅ፣ የጤነኛ ስሜት ምክንያት ለመሆን ጥረት ማድረግ ይጠበቅብናል። ጥንዶች ጉዳዩ ከቁጥጥራችንና ከአቅማችን ውጭ ካልሆነብን በስተቀር ለትዳር አጋሮቻችን የመጥፎ ስሜት መፈጠር ምክንያት እንዳንሆን ለስሜታቸው በመጠንቀቅ የእውነተኛ አፍቃሪ ባልና ሚስት ባህርይ መገኛዎች ልንሆን ይገባናል።

## 5. የባሕርይ ለውጥ

የሰው ባሕርይ አብሮት በሚኖረው ሰው፣ በቤተሰብ፣ በጓደኛ፣ በሚኖርበት አካባቢና ሁኔታ ሊቀረጽና ሊለወጥ ይችላል። እውነተኛው ባህሪያችን ሊገለጥ የሚችልበት ቦታ ትዳራችንና ቤተሰባችን ውስጥ ነው። በተለያዩ ነገሮች ተሸፍኖ የነበረው ማንነታችን የምንፈልገውን ስናገኝ ወይም ስናጣ፣ እምነታችንና ዋጋ የምንሰጠው ነገር ዋጋ ሲሰጠው ወይም ዋጋ ሲያጣ እና በተለያዩ ነገሮች ምክንያት ስሜታችን በደስታ ወይም በሐዘን ሲነካ እየተገለጠ መምጣቱ አይቀሬ ነው። አንዳንድ ያልታሰቡ ጉዳዮችና ለውጦችም በባህሪይ ላይ ለውጥ ሊያስከትሉ  ይችላሉ። ወደ ትዳር ከገቡ በኋላ የሚፈጠሩ የባህሪይ ለውጦች ምናልባት ከማግባት በፊት የነበሩ ነገር ግን አንደኛው አካል ራሱን ሁኖ ባለመቅረቡ ምክንያት ተደብቀው የነበሩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ሌላው ደግሞ ስሜታዊ አፍቃሪ በመሆናቸው ምክንያት የትዳር ጓደኛቸው ባሕርይ አልታይ ብሏቸው ከቆየ በኋላ ወደ ተለያዩ የሕይወት ገጠመኞች በሚገቡ ወቅት የትዳር አጋራቸውን ባሕርይ አስተውለውት ሊሆን ይችላል።

በወንዶች (ባሎች) ላይ ከሥራ ድካምና ውጥረት የተነሳ፣ የጠበቁት እንዳሰቡት ሳይሆን ሲቀር፣ ወሲባዊ ግንኙነት ሲነፈጉና ሌሎች የተለያዩ ጫናዎች ሲፈጠሩባቸው ወቅታዊ የሆነ የባሕርይ ለውጥ ሊታይባቸው ይችላል። በሴቶች (በሚስቶች) ላይ ደግሞ





በወር አበባ፣ በእርግዝና ወቅትና ከወሊድ በኋላ በሚፈጠር ድብርትና ልጆችን በማሳደግ ሂደት ከባል ምንም ዓይነት እርዳታ የማያገኙ ከሆነ በሚፈጠርባቸው የተለየ መጥፎ ስሜት የተለየ የባሕርይ ለውጥ  ሊታይባቸው ይችላል።

## 6. መንፈሳዊ ለውጥ

በጥንዶቹ ሕይወት ከሚፈጠሩ ለውጦች መካከል መጠቀስ ያለበት ሌላው ለውጥ መንፈሳዊ ለውጥ ነው። የእግዚአብሔር ቃል እንደሚያስተምረን መንፈሳዊ እድገት የማያቋርጥ ማለትም ክርስቶስ በአካል ዳግም እስኪመጣ ወይም ግለሰቡ በግል ወደ ጌታ በስጋው ሞት በማንቀላፋት እስኪጠራ ድረስ የሚቀጥል ሂደት ነው። የመንፈሳዊ ሕይወት እድገት ልኩ ክርስቶስን መምሰል መሆኑ እድገቱ የማያቋርጥ እንዲሆን ያደርገዋል። በዚህ የመንፈሳዊ ብስለትና እድገት ሂደት ውስጥ የጥንዶቹ ሕይወት በተለያዩ ምክንያቶች እድገት ሊያቆም፣ የመንፈሳዊ ሕይወታቸውና አገልግሎታቸው ግለት እንዲሁም ለጌታና ለቅዱሳን ያላቸው ፍቅር እየቀዘቀዘ ሊመጣ ይችላል።

ከላይ የተጠቀሱ የተለያዩ ለውጦች በጥንዶች በግልና በጋራ የመንፈሳዊ ሕይወትና አገልግሎት እድገትና ብስለት ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተጽዕኖ ሊፈጥሩባቸው ይችላሉ። መንፈሳዊ ለውጥም ሌሎች የተለያዩ ለውጦች እንዲከሰቱ ከፍተኛ የሆነ ተጽዕኖ መፍጠሩ አጠያያቂ አይደለም። በጥንዶች መካከል የሚፈጠር አለመግባባትና ግጭት በእርግዝናና ልጅ ወልዶ በማሳደግ ሂደት ወቅት ከአሁን በፊት የነበሩ መንፈሳዊ እንቅስቃሴዎች እየቀነሱ ብሎም እየጠፉ በመምጣታቸው ምክንያት ሊከሰት ይችላል። በእንደዚህ ዓይነት ወቅት አንዱ የሌላውን መንፈሳዊ እድገት በመረዳት የተለየ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች፣ መጋቢዎች፣ መሪዎች፣ የበሰሉ ሰዎች አገልግሎት የሚያገኙበትን መንገድ ማመቻቸትና መንፈሳዊ አቅም ሊያገኙ የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠር ተገቢ ነው። ምናልባት በአንዱ አካል ላይ ብቻ የሥራ ጫና በዝቶ ለመንፈሳዊ ሕይወት ጊዜና ፍላጎት ማጣት ሊፈጠር ስለሚችል በቤት ውስጥ ያሉ ሥራዎችን ኃላፊነት መከፋፈል፣ መረዳዳት ብሎም በተራ የቤተ ክርስቲያን ፕሮግራሞችንና አገልግሎቶችን ለመካፈል ሁኔታዎችን በግልጥነት በመነጋገር ማመቻቸት የጤናማ ባልና ሚስት ብስለት መለያ ነው፡፡

## 7. ማሕበራዊ ለውጥ

በጥንዶች መካከል አለመግባባትና ግጭት እንዲፈጠር ሊያደርጉ ከሚችሉ ለውጦች መካከል መጠቀስ ካለባቸው አንዱ ማሕበራዊ ለውጥ ነው። በተፈጥሮ የሚከሰቱ የተለያዩ ለውጦችና በጥንዶች መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶችና ግጭቶች በማሕበራዊ ግንኙነታቸው ላይ አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ተፅዕኖ ማምጣታቸው አይቀሬ ነው። የንጥረ ቅመም፣ አካላዊ፣ ስሜታዊና ስነ ልቦናዊ የባህሪይ ለውጦች በማሕበራዊ ሕይወት ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚፈጥሩት ተጽዕኖ በቀላሉ የሚታይ አይደለም።

ለምሳሌ የሳሙኤል እናት ሀና ልጅ ከመወለዷ በፊት ብቸኛ፣ በትዳሯ ደስተኛ ያልነበረች፣ በጣውንቷ የምትነቀፍ፣ በሊቀ ካህኑ በኤሊ ሰካራም ተብላ የተሰደበች ሴት ነበረች። ከነበረባት አሉታዊ ማሕበራዊ ግንኙነት ነፃ በመውጣትና ከድብርት በመላቀቅ ቀና ብላ ከሌሎች ሰዎች ጋር በነፃነት ኅብረት ማድረግ የጀመረችው ሳሙኤልን ከጸነሰችና ከወለደች በኋላ ነበር /1ኛሳሙ 1፥ 6-2፥ 7/። ይህ ዓይነቱ የማሕበራዊ ለውጥ ሂደት ደግሞ በአንደኛ ሳሙዔል ምዕራፍ አንድ እንደተገለጠው ከባለቤቷ ከህልቃና ጋር በነበራት ግንኙነት ላይም ተጽዕኖውን አሳርፏል፡፡

በሌላው አቅጣጫ ደግሞ ልጅ መውለድና ማሳደግ የሚጠይቀው ኃላፊነት በቤተ ክርስቲያን ከሚደረጉ ኅብረቶችና ከሌሎች ማሕበራዊ ግንኙነቶች በመለየት ብቸኝነት እንዲፈጠር ሊያደርግና ይህ ማሕበራዊ ለውጥ ደግሞ የተለያዩ ተጽዕኖዎች እንዲፈጥሩ ምክንያት ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ባልና ሚስት ማሕበራዊ ለውጦችን ሊያስከትሉ የሚችሉትን ተጽዕኖዎች በመረዳትና ችግሩ ጊዜያዊ መሆኑን በማስተዋል እርስ በርስ መተጋገዝና ነገሮችን ሚዛናዊነትን በጠበቀ ሁኔታ የማስኬድ ኃላፊነታቸውን ለመወጣት ዝግጁ መሆን አለባቸው፡፡ ይህን ማድረጋቸው ለትዳራቸው ጤናማነትም ሆነ ለጠንካራ ቤተሰብ መፈጠር ዓይነተኛ መፍትሔ ነው።

## III. የተለያዩ ወቅታዊ የለውጥ ደረጃዎችና ባሕርያቸው

አንዳንድ የትዳርና የሌሎች ግንኙነት አማካሪዎችና አስተማሪዎች በግንኙነት ሂደት የተለያዩ ደረጃዎች እንዳሉ ይገልጻሉ። እነዚህ የተለያዩ ደረጃዎች ራሱን የቻለ ወቅት፣ ሂደት፣ ባሕርይና ትኩረት እንዳላቸው ይጠቁማሉ። እነዚህን የተለያዩ የግንኙነት ደረጃዎች መረዳት አስቀድሞ ለዝግጅት፣ ወቅቱ ሲመጣ ግጭትን ለመቀነስ፣ ለመቆጣጠርና ከወቅቱ እንድንማር እንጂ እንዳንመረር የሚሰጠው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው። ከዚህ የተነሳ እኔም እነዚህን አምስት የግንኙነት ደረጃዎችን በቅደም ተከተል በማስቀመጥ የትኛው ደረጃ ላይ እንዳለንና እንዴትስ ወደ ሌላው ደረጃ በመልካም ግንኙነት መሸጋገር እንደምንችል አቅጣጫ ለማሳየት በማሰብ ከዚህ በታች ለመዘርዘር እሞክራለሁ፡፡[6]

### 1. የጫጉላ ቤት ጊዜ (የሃኒሙን ወቅት)

የጫጉላ ጊዜ (የሃኒሙን ወቅት) የሚባለው ብዙ አዲስ ተጋቢዎች ጋብቻ ከፈጸሙበት ቀን አንስቶ ለተወሰኑ ቀናት፣ ወራትና ዓመታት የሚያልፉበት ወቅታዊ የመዝናናትና የመደሰት ሂደት ነው። ከላይ ለመግለጥ እንደ ሞከርኩት ይህ የጫጉላ

[6] Gregory A. Kuhlman. Marriage facts. Stages of marriage: http://www.stayhitched.com/stages.htm accessed March 25, 2014.





ወቅት እንደ ባለትዳሮች ሁኔታ ሊወሰን ይችላል። በዚህ የጫጉላ ወቅት ጥንዶች አንዳቸው ለአንዳቸውና በአጠቃላይም ለትዳር ባላቸው ከፍተኛ የሆነ ግምት የሚኖሩበት፣ አብዛኛውን ጊዜ ሰላምና ደስታ የሚታይበት፣ ጠንካራ የሆነ የግብረ ስጋ ግንኙነት የሚኖርበት፣ ተከታታይነቱ የሚበዛበትና ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጥበት ወቅት ነው።

የጫጉላ ቤት ወቅት ጥንዶቹ በጋራ የሚያሳልፉበት፣ አቅማቸው በፈቀደና ከዚያም ባለፈ በብድር የሚዝናኑበት፣ የተለያዩ ቦታዎችን ማለትም ከተሞችን፣ ምግብ ቤቶችን፣ ታላላቅ ሆቴሎችን፣ መዝናኛ ቦታዎችን በመዘዋወር የሚጎበኙበትና በመዝናኛ ስፍራዎች የሚያሳልፉበት ወቅት ነው። በዚህ ወቅት አንዱ ሌላውን ለማወቅ ጥረት የሚያደርጉበትና ያላቸውን አንዱ ለሌላው የሚያካፉሉበት ወቅት ነው። ይህን ወቅት አቅምና ጊዜ በፈቀደ መጠን በጋራ በመደሰትና ግንኙነትን በማጠናከር ማሳለፍ ተገቢ ነው። ነገር ግን የጫጉላ ሽርሽር መደበኛ የተጋቢዎች ኑሮ አይደለም፡፡ ስለዚህ ጥንዶች እውነታውን በመረዳት ትዳር ሁልጊዜ እንዲህ ሁኖ ሊቀጥል እንደማይችል፣ ሌላ ወቅት እንደሚመጣና ይህ የሽግግር ወቅት በግንኙነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ በማምጣት የነበሩትን መልካም ቀናት ሁሉ አስረስቶ ድንጋጤ እንዳይፈጥር እንዲሁም ለግጭትና ከትዳር ሕይወት ለመውጣት ሰበብ እንዳይሆን ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

### 2. ከእውነታ ጋር የሚጋፈጡበት ወቅት

ይህ የጋብቻ ወቅት አዲስ ባለትዳሮች ከአሁን በፊት በእጮኝነትና በተጋቡ በተወሰኑ ወራት ወይም ዓመታት ገጥሟቸው የማያውቅ ሁኔታ ጋር ሊጋፈጡ የሚችሉበት ወቅት ነው። አስቀድሞ በእጮኝነት ጊዜ የነበረው ግንኙነት አጭርና ገደብ ባለው ሁኔታ የተያዘ ስለነበር ይበልጥ በጥንቃቄና አንዱ ሌላውን ላለማጣት በሚፈጠር የውስጥ ፍርሃት የማስመሰልና የማመቻመች አዝማሚያ የሚታይበት ሆኖ አልፎ ሊሆን ይችላል። እውነታው ግን ጥንዶቹ በዚህ ሁኔታ ለረጅም ጊዜ የሚቀጥሉ አለመሆናቸው ነው፡፡ እንዲህ ታፍኖ የቆየውና ነፃ ባልሆነ ግንኙነት ላይ የተመሠረተው የማስመሰል፣ የማመቻመችና በፍርሃት የመጠባበቅ መሠረት ላይ በጋራ ዓለምን የመቅጨቱ የወረት ጊዜ ያልፋል፡፡

ጥንዶቹ በሕይወታቸው ከተለያዩ ተፈጥሯዊና የተጠበቁም ሆነ ያልተጠበቁ የሕይወት ገጠመኞችና ችግሮች ጋር በሚጋፈጡበት ወቅት የማስመሰል ጭምብላቸው ተገፍፎ ራሳቸውን መሆን ይጀምራሉ፡፡ በዚህ ጊዜ በሕይወታቸው በሚገጥሟቸው ተግዳሮቶችና በሚጋፈጧቸው የተለያዩ እውነታዎች ሰበብ ያልለመዱት አለመስማማት ከዚያም አልፎ ብዙ ግጭቶች በግንኙነታቸው ሊፈጠሩባቸው ይችላሉ። በተፈጠረው ግጭት ምክንያት የተለያዩ አንዳንድ ባዕድ የሆኑ ስሜቶች ይፈራረቁባቸዋል። በሚፈጠሩ ያለመግባባትና የግጭት መንስኤዎችና ባሕርያት አንዱ በሌላው የመደናገጥ፣ የማዘን፣

ከፍተኛ የሆነ ተስፋ የመቁረጥና የወደ ፊት የትዳራቸውን ጉዞ ሲያስቡም የፍርሃት ስሜት ሊሰማቸው ይችላል።

በተፈራረቀባቸው የተለያዩ የለውጥ ስሜቶች ምክንያት በትዳር ጓደኛ ምርጫ ውሳኔያቸው እንደተሳሳቱና ትክክል እንዳልነበሩ ሊሰማቸውና ሊጸጸቱ ይችላሉ። ከትዳር አጋራቸው ጋርም አብረው ሊሄዱ የማይችሉ እንደሆኑ ያስባሉ። በብዙ ፀፀትና ምሬት ውስጥ በመሆን ደስታ ሊርቃቸው፣ ምሬትና ማጉረምረም ብሎም አንዱ በሌላው ላይ በማሳበብ መነጫነጭና መቆጣት፣ የትዳር ጓደኛቸውን ወይም ራሳቸውን ያለአግባብ ጥፋተኛ የማድረግ ስሜት ሊፈራረቅባቸውና ይበልጥ ግጭታቸውን ሊያባብስባቸው ይችላል።

በመካከላቸው በተከሰቱ አዳዲስ ሁኔታዎች የተፈጠሩ አለመግባባቶችና ግጭቶች አይቀሬነት ተፈጥሯዊና በማንኛውም ባለትዳር መካከል ሊፈጠር የሚችል ስለማይመስላቸው ራሳቸውን ብቻ እየኰነኑና በእነርሱ ላይ ብቻ የተፈጠረ አድርገው በመቁጠር ይበልጥ ተስፋ ይቆርጣሉ። በሚያልፉበት ግጭትና ጥፋትም የሚሸማቀቁበትና የሚያፍሩበት ጊዜ ይኖራል። በመካከላቸው የተፈጠረው አለመግባባትና ግጭትም ሊፈታ የማይችልና መፍትሔ የሌለው እንደሆነ እያሰቡ ብቻቸውን ይሰቃያሉ።

ባለትዳሮች በዚህ ወቅት እንዲህ ዓይነቱን እውነታ በብስለትና በተዘጋጀ ማንነት ለመጋፈጥ እንዲሁም የማይፈልጓቸው የተለያዩ ስሜቶች ሲፈራረቁባቸውና በውሳኔ እንደተሳሳቱ የመቁጠር ስሜት ሲሰማቸው የትዳር ግንኙነታቸው እንዳይሻክር ወቅቱን በማስተዋል፣ በመረዳዳትና በመግባባት ለማለፍ ነገሮችን በሰከነ መንፈስ የሚመዝን ጠቢብነትና ሁኔታን ታግሶ የሚያልፍ የፍቅር ሕብረት ያስፈልጋቸዋል። ግጭት በማንኛውም የጋብቻ ዘመን አይቀሬ እንደ ሆነ መገንዘብ አስፈላጊ ነው። በእንዲህ ዓይነቱ ወቅት ሌሎች እንዴት እንዳለፉ በመማርና ልምድ በመውሰድ ተደጋግፎ ለማለፍ እንጂ በዛሬው ችግር አሉታዊ ተጽዕኖ ነገን አብረው እንዳያዩ በሚከለክል መጋረጃ ተሸፍነው ተስፋ እንደሌለ እንዳያስቡ ጨለምተኝነትም እንዳይሰማቸው ከወዲሁ በእውቀት መዘጋጀት ተገቢ ነው።

## 3. በልጆች ላይ ትኩረት የሚወሰዱበት ወቅት

ይህ ሶስተኛው የትዳር ደረጃ ጥንዶች ልጅ በመውለድ የቤተሰብ አባላትን የሚጨምሩበትና አዲስ ልምምድ ውስጥ የሚገቡበት ወቅት ነው። ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታዎች ናቸው ነገር ግን ልጆች ስጦታዎች ብቻ ሳይሆኑ ኃላፊነትም ጭምር መሆናቸው መዘንጋት የለበትም። ልጆችን ማሳደግ ራሱን የቻለ የተለየ ልምምድ ነው። ልጅ የመውለድና የማሳደግ ልምምድ ጥንዶች ቀድሞ የነበራቸውን የትኩረት አቅጣጫ ሊቀይርና በመካከላቸው የኑሮና የግንኙነት ውጥረት እንዲጨምር ምክንያት ሊሆን የሚችል ልምምድ ነው።





ይህ ደረጃ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲያጋጥም ባለትዳሮች ቀድሞ ከነበሯቸው ኃላፊነቶች በተጨማሪ የተለያየ ሥራ፣ ጊዜና ጉልበት የሚጠይቅ በመሆኑ ኃላፊነቱን በተግባር ለመወጣትና ልጅን ለማሳደግ ጥንዶቹ ልምድ ከሌላቸው በመካከላቸው ውጥረት እንዲፈጠርና ግጭት እንዲባባስ ሊያደርግ ይችላል። ይህ ሂደት ካለፈው በመማርና ብስለትን በማሳደግ ካልተያዘ ሁለተኛና ሶስተኛ ልጅ በሚወለድበት ወቅት ውጥረቱ ይበልጥ ይጨምራል። ጥንዶች የራሳቸው ጊዜ እንዳይኖራቸው፣ ግንኙነታቸው ላይ ትኩረት እንዳያደርጉና ወደ ልጆቻቸው እንዲያዘነብሉም ያስገድዳቸዋል። ይህን በመረዳት በዚህ ወቅት ትዳር ላይ ችግር እንዳይፈጠር ለየት ያለ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባዋል።

ልጆች በሚወለዱበት ወቅት የወላጆች ትኩረት ልጆች ላይ መሆኑ ፍቅር እንደቀዘቀዘ ወይም እንደጠፋና የትዳር ግንኙነት እንደ ተቋረጠ አድረጎ በማሰብ ባል ወይም ሚስት ፍርሃትና ድንጋጤ ውስጥ እንዳይገቡ ከወዲሁ ጉዳዩ ሊከሰት የሚችል መሆኑን ሊረዱ ይገባል። የእግዚአብሔር ስጦታ የሆኑት ልጆች በባለትዳሮች መካከል ገብተው የትዳር ግንኙነት መሠረት የሆነው ፍቅር ለመቀዝቀዙና ለመጥፋቱ ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ። ይህ እንዳይፈጠር ጥንዶች ሁኔታዎችን በማመቻቸት አብረው ጊዜ በማሳለፍ ግንኙነትን ለማጠናከር ከፍተኛ ጥረት ሊያደረጉ ይገባል። ነገ ልጆች አድገውና ለቁም ነገር ደርሰው ቤታችንን ለቀው የሚወጡበትና ራሳቸውን የሚችሉበት ወቅት እንደሚመጣ በማሰብ ወላጆች ለግንኙነታችን ለየት ያለ ትኩረት መስጠት ያሻናል። በእርግጥ ልጆችን ማሳደግ ኃላፊነት ቢሆንም ከትዳር አጋር ግን ልናስበልጣቸውና ልናስቀድማቸው አይገባም። ለልጆች መገኘት ምክንያት የሆነው የጋብቻ ተቋምም በልጆች መወለድ ምክንያት ቀውስ ውስጥ መግባትም ይሁን መፍረስ የለበትም። ልጆች የወላጆች ኃላፊነትና ደስታ ናቸውና የልጆች መወለድ የባልና የሚስትን ግንኙነት የበለጠ የሚያጠናክርና ወደ ከፍተኛ ደረጃ እንዲያድግ የሚያግዝ ጠቃሚ ግብዓት በመሆን እንዲያገለግል ወላጆች በብስለት፣ በእውቀትና በተረጋጋ ማንነት ሊጠቀሙበት ይገባል።

**የሚሰጡን ማንኛውም ስጦዎች ሁሉ ይብዛም ይነስም ኃላፊነት እንዳላቸው መዘንጋት የለብንም!!**

## 4. የትዳርን ግንኙነት ለማደስ ጥረት የሚደረግበት ወቅት

የትዳር ግንኙነትን የማደስ ጥረት የጫጉላ ዘመንን በማስታወስ፣ የኑሮ እውነታዎችን በመጋፈጥና ትኩረታቸውን በልጆች ላይ በማድረግ የተለያዩ ደረጃዎችን ያሳለፉ ጥንዶች የጋራ የትዳር ግንኙነታቸውን ለማደስ የሚነሱበትና የሚንቀሳቀሱበት ወቅት ነው። በዚህ ወቅት አንዱ ሌላውን እንደሚገባ የሚያወቁበት፣ ምን እንደሚያስፈልጋቸው የሚረዱበት፣ ልዩነታቸውን የሚያጠቡበት፣ አለመግባባትንና

ግጭትን የሚቆጣጠሩበት እንዲሁም የሚያስተካክሉበት ወቅት ነው። ይህ ደረጃ ካለፈው ስህተታቸው በመማር ለዛሬና ለወደፊት ትዳራቸው የሚያስቡበት፣ በጋራ በመረዳዳት እንዲሁም አንዱ የሌላውን ፍላጎት ለማሟላት ከፍተኛ ጥረት በማድረግ በግንኙነታቸው ይበልጥ ደስ እየተሰኙ የሚኖሩበት ደረጃ ነው። ይህ ደረጃ ብዙ ያስጨነቋቸውን፣ ያሳዘኗቸውንና ፍርሃትና ተስፋ መቁረጥ እንዲፈራረቅባቸው ያደረጓቸውን ሁኔታዎች ጥሩ ትምህርት ቤት አድርገው በማየት ባለፈው አስቸጋሪ ዘመን ተምረውበት ግንኙነታቸውን የሚያጠናከሩበት ለአዲስ ኅብረት፣ ፍቅርና አብሮነት የሚታደሱበት ደረጃ ነው። ጥንዶች ነገሮች ሁሉ እንዲህ እንደሚያልፉና ዛሬን መድረስ ብሎም ነገን በተሻለ መንገድ መገናኘት እንደሚቻል አምነውና ተቀብለው እንዲቀጥሉ ሊበረታቱ የሚችሉበት አድርገው ከተጠቀሙበት ከዚህ ወርቃማ ሂደት ብዙ ያተርፉበታል።

## 5. በትዳር ግንኙነት ውጤታማ የሚሆኑበት ወቅት

የመጨረሻው የትዳር የግንኙነት ደረጃ የጋብቻን ዓላማና ጥቅም በመረዳትና አንዱ የሌላውን ፍላጎት ይበልጥ በማሟላት በግንኙነታቸው በጣም ደስተኛ የሚሆኑበት ወቅት ነው። ይህ ደረጃ ለብዙ ዓመታት ካሳለፉት የሕይወት ውጣ ውረድ የተማሩትን፣ በብዙ ሁኔታዎች የተፈተነ ማንነታቸውንና ግንኙነታቸውን ይበልጥ እያደነቁና እያከበሩ የሚይዙበት የትዳር ደረጃ ነው። ይህ ደረጃ ባልና ሚስት እርስ በርስ እየተዋደዱ፣ እየተከባበሩና እየተረዳዱ ለመኖር ከፍተኛ ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉበት ደረጃ ከመሆኑ የተነሳ ወደ ፊት ስጋት ሳይሆን ተስፋ፣ ሽንፈት ሳይሆን ድል፣ በግጭት መደናገጥ ሳይሆን ተረጋግቶ ችግርን መፍታት ይታያቸዋል:: ይህ ወቅት በሚያልፉት አስቸጋሪ ሁኔታ ተመራሪነትን ሳይሆን ተማሪነትን፣ ግለኝነትን ሳይሆን አብሮነትን እንዲሁም ተጠቃሚነትን ብቻ ሳይሆን ጠቃሚነትን ለመምረጥ ዝግጁ የሚሆኑበት ወቅት ነው።

ይህ ማለት በዚህ ወቅት አለመግባባትና ግጭት የለም ማለት አይደለም። ነገር ግን ለግጭት መነሻ የሚሆኑ ምክንያቶችንና ግጭቶችን የሚፈቱበትን መንገድ ከቀደሞው በተለየና በበሰለ ማንነት የሚይዙበት ወይም የሚያስተናግዱበት ጊዜ ነው። በዚህ የጋብቻ ደረጃ ላይ ያሉ ጥንዶች ሌላው አስቸጋሪ ጊዜ የሚሆንባቸው ልጆቻቸው 16 ዓመት ላይ የሚደርሱበት ወቅት ነው። ይህ ራሱን የቻለ ለትዳርና ለቤተሰብ ግንኙነት አስቸጋሪና ፈታኝ ሊሆን የሚችልበት ጊዜ ሲሆን የትዳር ሕይወት መመረቅ የሌለበት ትምህርት ቤት መሆኑንም ያሳያል። ለቤተ ክርስቲያን መሪነት የሚታጭ አማኝ እንኳን ቤቱን በመልካም የሚያስተዳድር መሆኑ የሚጠየቀውና በዚህ መርህ የማስተዳደር ማንነቱ በቤቱ መፈተን አለበት የሚባለው እንደዚህ ዓይነቱን ተግዳሮት በአግባቡ መወጣት የሚያስችል በሳል የቤት አስተዳደር ጥበብ ወይም ክህሎት ያለው መሆኑን ይህ ወቅት ስለሚያሳይ ነው። *"ልጆቹን በጭምትነት ሁሉ እየገዛ የራሱን ቤት በመልካም የሚያስተዳድር፤ ሰው ግን የራሱን ቤት እንዲያስተዳድር ባያውቅ፥ የእግዚአብሔርን ቤት ክርስቲያን እንዴት*





*ይጠብቃታል?"* /1ኛጢሞ 3: 5-6/:: እዚህ ደረጃ ላይ በመልካም ሁኔታ የደረሱ ባለትዳሮች በአመታት የትዳር የአብሮነት ጉዞ በተገኘው የተሳካ የግንኙነት ብዙ ውጤትና ፍሬያማነት መደሰትና መርካት ይችላሉ:: ነገር ግን በዚህ ወቅትም እንኳን በትዳር ሕይወት ውስጥ ተማሪዎችና ኃላፊነት ያለባቸው ሰዎች መሆናቸውን በመረዳት የተገነባው የጋብቻ ሕይወት ስኬት የበለጠ እየታነፀ እንዲቀጥል የሚያግዝ ገንቢ አስተዋፅኦቸውን ማበርከት አለባቸው::

**ባለትዳሮች ሆይ በምናልፉበት አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ተመራሪነትን ሳይሆን ተማሪነትን፣ ግለኝነትን ሳይሆን አብሮነትን እንዲሁም ተጠቃሚነትን ብቻ ሳይሆን ጠቃሚነትን ለመምረጥ ዝግጁ ልሆን ይገባል።**

## ለጥንዶች በግላቸውና በቡድን ለማጥናት የሚረዷቸው የውይይት ጥያቄዎች

## የምዕራፍ አራት (4)

## የውይይት ጥያቄዎች

1. የለውጥና የግንኙነት ደረጃዎችን ምንነት ከዚህ መጽሐፍ ሐሳብ በመነሳት አብራሩ::
2. በመጽሐፉ የተጠቀሱና ከዚያም ባሻገር በባለትዳሮች መካከል ሊፈጠሩ የሚችሉ ለውጦችን በመጥቀስ በስፋትና በግልጥነት ተወያዩ::
3. በመጀመሪያ በአንተ/ች/ ከዚያም በትዳር አጋርህ/ሽ/ ያስተዋላችሁት ለውጥ ምንድን ነው? ለውጡ በእያንዳንዳችሁ ላይ የፈጠረው አዎንታዊና አሉታዊ ተጽዕኖ አለን? ካለስ ምንድን ነው?
4. የአምስቱን የግንኙነት ደረጃዎች ባሕርያትን በመዘርዘር የትዳር ግንኙነታችሁ በየትኛው ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለማወቅ የሚያስችል ግልጽና በቂ ውይይት አካሂዱ፡- ለአንድ አፍታ ወደ ኋላ ዘወር በማለት የጫጉላ ቤት ጊዜያችሁን እንዴት እንዳሳለፋችሁና ዛሬ ላይ የደረሳችሁበትን የግንኙነት ሂደት በቅኝት መልክ በመዳሰስ ተነጋገሩበት::
5. እውነታን በምትጋፈጡበት ደረጃና ልጆች ትኩረታችሁን በሚወስዱበት ወቅት እንዴት የትዳር ግንኙነትን ሚዛን መጠበቅ እንደቻላችሁ ምክክር አድርጉ::
6. ዛሬ ላይ በመቆም በትዳር ሕይወታችሁ ከገጠሟችሁ የተለያዩ ግጭቶች በመነሳት በምርጫችሁና በውሳኔያችሁ ላይ የተፈጠረውን የተለያየ ስሜትና ድባብ በመግለጽ ልምምዳችሁን ተከፋፈሉ::





# ምዕራፍ አምስት(5)

# በጋራ መወሰን (ውሳኔ አሰጣጥ)

## I. በጋራ የመወሰን ምንነት

ጥንዶቹ በትዳር ሕይወታቸው፣ በኑሯቸውና በቤተሰባቸው የተለያዩ ምርጫዎችንና ውሳኔዎችን ጠያቂ የሆኑ የጋራ ጉዳዮች ላይ የመነጋገር፣ የመመካከር፣ አንዱ ለሌላው ጥቅም፣ ስሜት፣ ፍላጎትና ማንነት የመጠንቀቅ ልምድ ሊኖራቸው ይገባል። በጥንዶች የትዳር ሕይወት በጋራ መወሰን ማለት የጋራ ውሳኔ የሚያሻቸው ጉዳዮችን፣ ችግሮችን ለመፍታት የሚወሰዱ እርምጃዎችን እንዲሁም የቤተሰቡን የዛሬና የወደፊት ሁኔታ የሚመለከቱ የምርጫና የውሳኔ ሂደቶችን የእግዚአብሔርን ቃል መርህ መሠረት ባደረገ እንዲሁም ለቤተሰቡ መታነጽ በሚያመጣ መንገድ በመምራት በጋራ ከመወሰን ጋር ተያይዘው ሊፈጠሩ የሚችሉ የግጭት መንስኤዎችንና የመፍትሔ አሳቦችን አስቀድመው የማሰብና ትዳራቸውን አብረው የመገንባት የሁለትዮሽ ኃላፊነታቸውን የመወጣት ሂደት ነው::

በዚህ ርዕስ ላይ ትኩረት ማድረግ ያስፈለገው ጥንዶች በመከራከር ሳይሆን በጋራ በመመካከር፣ በመደፋፈር ሳይሆን እርስ በእርስ በመከባበር እና በግጭት ሳይሆን በስምምነት አብረው መወሰንን እንዲለማመዱና የትዳር ግንኙነታቸውና የቤተሰባቸው ጤንነት እንዲጠበቅ ለመጠቆምና ለመርዳት በማሰብ ነው። በጥንዶች ሕይወት ትዳር የጋራ ውሳኔ በሚጠይቁ ምርጫዎችና ገጠመኞች የተገነባ ኑሮ ነው። ይህ እውነት የጥንዶችን በትዳር ሕይወታቸው በገጠማቸውና ሊገጥማቸው ባለ የጋራ ጉዳይ ላይ አስፈላጊነቱን፣ አንገብጋቢነቱንና አስቸኳይነቱን በሚመለከት እርስ በርስ በመነጋገር፣ በመመካከርና በመስማማት ወደ አንድ ውሳኔ የመምጣትን አስፈላጊነት የሚያመለክት ነው። ጥንዶች ለጋራ ጉዳይ በጋራ ለመወሰን አብረው ቢቀመጡና ቢነጋገሩ በሁሉ ነገር ይስማማሉ ወይም መስማማት አለባቸው ማለት ሳይሆን አንዳንድ ጊዜ ግጭት አልባ በሆነ አለመስማማት ተስማምተው ልዩነትን በሰላም እያስተናዱ የትዳርን ግንኙነት ጤናማነትና የጋራ ደስታን ግን ለመጠበቅ መትጋት ይኖርባቸዋል።

> **የጋራ ውሳኔዎችን በመከራከር ሳይሆን በመመካከር፣ በመደፋፈር ሳይሆን በመከባበር እንዲሁም በግጭት ሳይሆን በስምምነት ለመወሰን ጥረት እናድርግ።**

## II. በጋራ የመወሰን አስፈላጊነት

ሕይወት ምርጫና ውሳኔ የበዛባት ጉዞ ናት። በምርጫችንና በውሳኔያችንም ተጠያቂዎች እኛው ሰዎች ራሳችን ነን! እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር ነጻ ፈቃድ ያለው፣ የወደደውን የመምረጥ ችሎታ ያለውና ደግሞም በመረጠው ምርጫ ሊጠየቅ የሚችል

አድርጎ እንደፈጠረው ገና ከፍጥረት ጅማሬ መመልከት እንችላለን። መጽሐፍ ቅዱስ **በዘፍ 2፡ 16-17** *"እግዚአብሔር አምላክም ሰውን እንዲህ ብሎ አዘዘው፡- ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና።"* ብሎ በመናገር በምርጫውና በውሳኔው ተጠያቂ ፍጡር እንደሆነ ግልጥ ያደርግልናል፡፡ በዘፍጥረት ምዕራፍ ሦስት ላይ አዳምና ሔዋን በእባብ የሐሰት ቃል በመታለል የእግዚአብሔርን ፈቃድ ትተው የራሳቸውን ምርጫና ውሳኔ በመከተላቸው በውጤቱ ተጠያቂ ሆነዋል፡፡

ምርጫና ውሳኔ በግለሰቦች የግል ሕይወት የሚከሰት ጉዳይ ብቻ ሳይሆን በትዳር በተጣመሩ ባለትዳሮች መካከልም የሚፈጠር የትዳር ጉዞ ቋሚ ገጽታ ነው። ጋብቻ በየግል የራሳቸውን ኑሮ ሲመሩና በየግላቸው ሲመርጡና ሲወስኑ የነበሩ ሁለት ተቃራኒ ጾታ ያላቸው ሰዎች በፍቅር ተዋደው በጋራ ለጋራ የትዳር ሕይወታቸው በመስማማት የሚወስኑበት ተቋም ነው። ሰው አባትና እናቱን በመተው ከሚስቱ ጋር የሚተባበር መሆኑ የብሉይ ኪዳንም ሆነ የአዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጽሐፈት ትምህርት ነው። **በዘፍ 2፡ 24** የተነገረው *"...ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ በሚስቱም ይጣበቃል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ።"* የሚለው የእግዚአብሔር ንግግር **በማቴ 19፡ 15** የተገለጠው *"... ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል፥ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ የሚለውን ቃል አላነበባችሁምን?"* የሚለው ኢየሱስ ክርስቶስ ለጠያቂዎቹ የሰጠው መልስ እና የጥንቷ ቤተክርስቲያን አገልጋዮች የነሐዋሪያው ጳውሎስ ጋብቻን በሚመለከት *"ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ።"* /**ኤፌ 5፡ 31**/ በማለት የሰጧቸው መመሪያዎች ባል እና ሚስት ግላዊ ምርጫወቻቸውንና ውሳኔዎቻቸውን በመተው በጋራ ለመኖር የሚበጃቸውን ጉዳይ አብረው ለመምረጥና ውሳኔ ለመወሰን ጋብቻ የሚባለውን ተቋም የመሠረቱ ወይም የሚመሠርቱ መሆኑን በግልጥ የሚያረጋግጡ መርሆዎች ናቸው፡፡

ከጫጉላ ጊዜ እስከ መጀመሪያው አስር ዓመት የጋብቻ ዘመን የሚገኙ ባለትዳሮች ባብዛኛው የጋራ የትዳርና የቤተሰብ ማሕበራዊ ሕይወት ጉዳዮችን አብረው መምረጥና መወሰን ሲገባቸው በግል ወደ መወሰን የሚያዘነብሉ በመሆናቸው በትዳር ላይ አለመግባባት፣ ግጭትና መለያየት ይፈጠራል። ጊዜያቸውን በአግባቡ ለሚጠቀሙ ተጋቢዎች ዕድሜና ቆይታ ለእድገታቸውና ለብስለታቸው ገንቢ አስተዋጾ አለው። ይህ እውነታ ግን እንደ ባለትዳሮች የጋብቻ ዘመን እንዲሁም ከገጠመኞቻቸው የመማርና የመለወጥ አቅምና ችሎታ መጠን የተለያየ ይሆናል፡፡ ይህንን ባለመረዳትም በቅርብ የተጋቡ ባለትዳሮች በጋራ መወሰንን አይለማመዱም፡፡ በዚህም ምክንያት ትዳራቸው ግጭት የበዛበት ይሆናል፡፡ ጥንዶች ግራ ተጋብተውም፡- " ምክንያቱ ምንድን ነው? ችግሩ የግል (የአንድ ሰው) ትዳር ብቻ ነው ወይስ የሌሎችም ሰዎች? በእኛ ቤት የትኛው ችግር ጎልቶ ይታያል? ችግሩስ እያመጣ ያለው ተጽዕኖ ምንድን ነው? ምንስ ብናደርግ ጤነኛ ግንኙነት ያለን ደስተኛ ጥንዶች ልንሆን እንችላለን?..." የሚሉ መሠረታዊ





ጥያቄዎችን በተደጋጋሚ ይጠይቃሉ፡፡ ለእነዚህ ጥያቄዎቻቸውም ምላሽ ማግኘት ይገባቸዋል። የችግሮቻቸው መሠረታዊ መነሻ በጋብቻ ሕይወት ውስጥ ማንኛውንም ጉዳይ በመመካከር፣ በመግባባትና ስምምነት ላይ በመድረስ አብረው መወሰን አለመቻላቸው ነው፡፡

በአንድ ቤት ውስጥ በየግል መኖርን በመቀነስ በጋራ ማሰብን፣ መመካከርንና ማንኛውንም የትዳር ጉዳይ በጋራ የመወሰንን አስፈላጊነት ተረድተው የመተግበር ልምድ በቤታቸው ውስጥ እንዲኖር ማድረግና ራሳቸውን ለዚህ መርህ በቋሚነት ማስገዛት ይገባቸዋል፡፡ በብስለት በዚህ መርህ መሠረት መኖርን ሲለማመዱ ችግሮቻቸውን በሰላማዊ መንገድ ይፈታሉ፡፡ ጥያቄዎቻቸውንም በአግባቡ ይመልሳሉ፡፡ በሚቀጥለው ርዕስ ውስጥ የሚዳሰሱ አሳቦች በዚህ ሁኔታ ላይ ባልና ሚስት የበለጠ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያግዟቸዋል።

## III. በጋራ በመወሰን ሂደት ላይ ሊፈጠሩ የሚችሉ የግጭት መንስኤዎች

### 1. ሳይነጋገሩ በየግል መወሰን

በቅርብ በተጋቡ ባለትዳሮች መካከል ከውሳኔ ጋር ተያይዞ የሚፈጠር አንደኛው ችግር ጥንዶቹ በትዳራቸውና ከትዳራቸው ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ሳይወያዩ ብቻቸውን መወሰናቸው ነው። እንግዳ መጋበዝ፣ ከፍተኛ ገንዘብ ወጭ ማድረግ፣ ቤተሰብንና ሌሎችን ሰዎች መርዳት፣ ወደ ሌላ አገር መሄድ የመሳሰሉ የጋራ ውሳኔን የሚጠይቁ ጉዳዮችን በግል ተነሳሽነትና ውሳኔ ብቻ የመፈጸም ዝንባሌ ከጥንዶቹ አንደኛው ያላቸው ከሆነና ይህንንም ወደ መተግበር የሚያመሩ ከሆነ በጋራ የመወሰን ሂደት ላይ ችግር ይፈጠራል።

እንዲህ ዓይነቱ በግል የመወሰን ዝንባሌና ተግባር ሊፈጠር ከሚችልባቸው ምክንያቶች መካከል **አንደኛው** ከማግባታችን በፊት ራሳችንን በራሳችን ስናስተዳድርና ውሳኔወቻችንንም በግላችን ስንወስን የነበረ መሆኑ ነው። ይህ ቅድመ ጋብቻ ላይ የነበረ የግል ልምምድ አሁንም በትዳር ላይ መቀጠሉ የችግሩ ዋነኛ መንስኤ ነው። ብዙ ዓመት አብሮን የቆየና የእኛ የሆነን ልምምድ በአንድ ጊዜ ለመተው መሞከር አስቸጋሪ ነው፡፡ ይህ የግለኝነት ልምምድ አብሮን ከቀጠለ ደግሞ በትዳራችን ውስጥ ችግር ይፈጥራል። ስለዚህ በእርጋታ አሰበንበት መለወጥ በምንችልበት መንገድ ላይ በትጋት ለውጡን በሕይወታችን እስከናይ ድረስ ራሳችንን ለማሻሻል መሥራት ይጠበቅብናል፡፡

ሌላው **ሁለተኛው** ምክንያት ደግሞ የባልና የሚስት እይታ ልዩነት ነው፡፡ ሰው በሕይወቱ ውስጥ ዋጋ የሚሰጠው እሴትና ነገሮችን የሚያይበት አስተሳሰብ የተለያየ ነው። አንዱ ምናለበት ሲል ሌላው ችግር አለበት ይላል፡፡ አንዱ ነገር ሲያቃልል ሌላው ያካብዳል፡፡ አንዱ ውጤቱ ላይ ሲያተኩር ሌላው ሂደቱ ላይ በማተኮር በግልና በጋራ መወሰን አለብን የሚሉ ትግሎች በባለትዳሮች መካከል ይፈጠራሉ። በጋራ ለመወሰን የግድ አንድ ዓይነት ሰዎች ልንሆን ወይም አንድ ዓይነት እይታና ባሕርይ ሊኖረን

አይገባም፡፡ ሊኖረንም አይችልም!! ነገር ግን በትዳር ሕይወታችን ጉዳዮችን ከተለያየ እይታ አንጻር በማየት፣ በጋራ በመወያየት፣ በጋራ በመተማመን፣ እንዲሁም ባለመስማማትና በመስማማት በጋራ እየወሰንን መተግበር ወደ ትዳር ስንገባ ልንኖርበት የተቀበልነው የጋብቻ ሕይወት መርህ ነው። በዚህ መርህ ደግሞ ልንኖርበትም ይገባል።

## 2. በግል ተወስኖ ሊፈጸም ያለን ጉዳይ ትክክለኛ በሆነ ጊዜ አለማሳወቅ

ሌላው ከሚፈጠሩት ችግሮች መካከል አንዱ በግል ተወስኖ ሊፈጸም ያለን ጉዳይ በጊዜው አለማሳወቅ ነው። በአንዳንድ ሁኔታዎች ውስጥ ስናል በሕይወታችን ጊዜ የማይሰጥ ምርጫና ውሳኔ ሊያጋጥመንና ፈጣን ውሳኔ እንድንወስን ልንገደድ እንችላለን። ነገር ግን ውሳኔውን ከወሰንን በኋላ ጊዜ ስናገኝ ለምንና እንዴት ውሳኔውን እንደወሰንን በእርጋታ በማብራራት ወቅቱን በጠበቀ መልኩ ለትዳር አጋራችን መግለጥ ይኖርብናል። ይህንን በጊዜው ሳናደርግ ከቀረን ወይም ደግሞ ጉዳዩ ጊዜ ሰጭና የትዳር አጋርን ምክር፣ አስተያየት፣ ስምምነትና ውሳኔ የሚጠይቅ ጉዳይ ሆኖ ሳለ እንዲሁ በማን አለብኝነት በግል ወስነንና አከናውነን ጊዜው ካለፈ በኋላ ወይም ሌላ ሁኔታን በመጠቀምና በእግረ መንገድ አጋጣሚወች እንዲሰሙና እንዲያውቁ ማድረግ የግጭት ምክንያት መሆኑ አይቀሬ ነው። እንዲህ ዓይነቱ ችግር አንዳንድ ጊዜ ሊፈጠር የሚችለው ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ከሆነ አለማወቅ፣ አለመልመድ፣ መርሳትና ለነገሩ ክብደት አለመስጠት የችግሩ ምክንያቶች ሊሆኑ ይችላሉ። እንዲህ ዓይነቱን ስህተት በእርጋታ ከተነጋገሩ በግል የወሰነው አካል በመደንገጥና ስህተቱን በመረዳት ወደ ፊት በውሳኔው የትዳር አጋርን የማካተት እርምጃ እንዲወስድ ይገደዳል።ከዚህ ውጭ የሆነ ሃሳብና እንቅስቃሴ ለግጭት መንስኤና ማባባሻ ሊሆን ስለሚችል ጉዳዩ በጥንቃቄና በብስለት ሊያዝ ይገባል።

ሌላው መጠቀስ ያለበት ከባህላችን አንጻር የሴት ልጅን ሃሳብ ዝቅ አድርጎ በማየት ሚስቶችን በውሳኔ ላይ የአለማሳተፍ ችግር ነው፡፡ በውሳኔ ሰጭነት እንዲሳተፉ እድል አለማግኘት ብቻ ሳይሆን ስለተወሰነው ነገር ምንም የማያውቁ የትዳር አጋሮች የተደረጉ ሚስቶች ቁጥር ጥቂት አይደለም። ይህ ችግር ኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩ የአንዳንድ ወንድሞች አመለካከት ብቻ ሳይሆን ከኢትዮጵያ ውጭና የሰለጠኑ በሚባሉ አገሮች የሚኖሩ የአንዳንድ ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊ ወንዶችም የሚጋሩት ችግር ነው።

ለሴት ልጅ ያለንን ዝቅተኛ አመለካከት አስወግደን በትዳራችን ያለእነርሱ ተሳትፎ ትዳርንና ቤተሰብን በጠንካራና ጤናማ መሠረት ላይ ማቆም ፈጽሞ የማይቻል መሆኑን በመገንዘብ በውሳኔ ሰጭነት ተግባር ላይ በእኩልነት ማሳተፍ መጀመርና አብሮ ወደ መወሰን መምጣት ተገቢ ነው። እንዲያውም ለሚፈጠሩ ችግሮች ሴቶች ከወንዶች የተሻለ የመፍትሔ ሃሳብ የማፍለቅ ተፈጥሮ እንዳላቸው በመገንዘብ በውሳኔ ሰጭነትና በመፍትሄ አምጭነት ለትዳራቸው ምትክ የለሹን ሚናቸውን እንዲያበረክቱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት የባሎች ኃላፊነትና ግዴታ ነው።





ሌላው ከጾታና ከባህል በዘለለ በትዳር የተጣመርን ጥንዶች አንዳችን ከሌላችን እንበልጣለን ብለን የምናስብባቸው ልምምዶች፣ እውቀቶች፣ ችሎታዎችና ጠንካራ ጎኖች በትዳር ሕይወት ውሳኔዎች ላይ አንዱ ሌላውን እንዳያሳትፍ የሚያደርጉ እንቅፋቶች ናቸው፡፡ በየትኛውም ደረጃ ከትዳር አጋራችን የምንሻልባቸው ጠንካራ ጎኖች ቢኖሩንም ሁል ጊዜም የትዳር አጋሮቻችን ደግሞ ከእኛ የሚሻሉባቸው ጠንካራ ጎኖች ይኖሯቸዋል፡ ፡ እነዚህን ቁም ነገሮች አለማወቅና ለማወቅም ዕድል የማይሰጡ መሆን ሌላኛው በትዳር ውስጥ የሚከሰት አደገኛ ችግር ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ *"በአንድ አሳብ ተስማሙ፥ አንድ ፍቅር አንድም ልብ አንድም አሳብ ይሁንላችሁ፤ ለወገኔ ይጠቅማል በማለት ወይም በከንቱ ውዳሴ ምክንያት አንድ እንኳ አታድርጉ፥ ነገር ግን እያንዳንዱ ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትሕትና ይቍጠር፤"* /ፊል 2፡ 2-3/ በማለትና የኢየሱስ ክርስቶስን የሕይወት ምሳሌ በመጥቀስ ትህትና እንድንማር ይመክረናል። ከትዳር አጋሮቻችን የምንበልጥበትና የምንሻልበት

> **ከትዳር አጋሮቻችን የምንሻልበትና የምንበልጥበት ጉዳይ እንዳለ ቢሰማንና ብናምንም የተሻለና የሚበልጥ ጉዳይ ከትዳር አጋሮቻችንም ዘንድም እንዳለ ማሰብ፣ ማወቅና ማመን ያስፈልገናል።**

ጉዳይ እንዳለ ቢሰማንና ብናምንም እንኳን ሐቁ ግን የተሻለና የሚበልጥ ጉዳይ ከትዳር አጋሮቻችንም ዘንድ እንዳለ ማሰብ፣ ማወቅና ማመን አስፈላጊ መሆኑ ነው።

## 3. የራስ ፍላጎትና አሳብ ብቻ እንዲፈጸም ጥረት ማድረግ

በጋብቻ ውስጥ የትዳር አጋርን ሳያሳትፉ በግል ከመወሰን ጋር በተያያዘ በቅርብ በተጋቡ ባለትዳሮች መካከል የሚታይ ሌላው ችግር የራስ ፍላጎትና አሳብ ብቻ እንዲፈጸም ጥረት ማድረግ ነው። እንዲህ ዓይነቱ ችግር ሊፈጠር የሚችለው እንዲፈጸም በምንፈልገው ጉዳይ ይበልጥ ተጠቃሚ እንሆናለን ብለን ስናስብ ነው፡፡ ከመሸነፍ ይልቅ ማሸነፍ፣ ከመታዘዝ ይልቅ ማዘዝና ሌሎች ተኮር ከመሆን ይልቅ ራስ ወዳድ መሆን በአስተዳደጋችን ሁልጊዜ ትክክል ናችሁ እየተባልንና ሁልጊዜ በማሸነፍ ብቻ የምንታወቅ ሁነን በማደጋችን የሚመጣ ችግርም ሊሆን ይችላል፡፡ በየትኛውም መንገድ የመጣ ይሁን ችግሩ በሕይወታችን ካለ ለዛሬው የትዳር ሕይወት ትግል ምክንያት ይሆናል። ሌላው አንዳንዶቻችን የየግላችንን ፍላጎት፣ ሃሳብ፣ ምርጫና ውሳኔ መተው ወይም መልቀቅ የሚባል ጽንሰ አሳብ የሌለን ሁነን ማደጋችንና መኖራችን ለችግሩ መከሰት ከፍተኛ አስተዋጾ አለው።

ወደ ትዳር ከመግባታቸው በፊት አንዳንድ ሰዎች እኔ ብቻ ትክክልና አዋቂ ነኝ ወይም የሌሎች ሰዎች ምንም አስተዋጽኦ የማያስፈልገኝ ብቻየን በቂ ነኝ የሚል ከፉ የእኔነት በሽታ የተጠናወታቸው ናቸው፡፡ እንደዚህ ዓይነት ሰዎች ለእኔ በቂ የሚሆን የትዳር አጋር የለም እያሉ የራሳቸውን ዋጋ ከፍ የሚያደርጉና ሌሎችን የሚያጣጥሉ ናቸው፡፡ ምናልባትም በእጮኝነት ጊዜያቸው በዚህ አስቸጋሪ ባህሪያቸው ምክንያት ብዙ

ጊዜ በግጭት ውስጥ የሚያልፉና በጓደኞቻቸው ወደፊት ይለወጣሉ በሚል ሰበብና ተስፋ የታለፉ ሊሆኑ ይችላሉ። በአገልግሎት ቢሮዬ ውስጥ ባለትዳሮችን በማማከርበት ወቅት ወደ ኋላ ያለፈ የልጅነት አስተዳደጋቸውንና የእጮኝነት ጊዜያቸውን በመጠየቅ ችግሩ የቆየ መሆኑን ለማወቅ በጥያቄና መልስ ለመረዳት ጥረት አደርጋለሁ። አንዳንዶችም ይለወጣል (ትለወጣለች) በሚል ተስፋ ተቀባይነት ያገኙ ስለሆኑ እንጂ ከበፊትም ችግር የነበረባቸው ናቸው፡፡ በዚህ ችግር ምክንያት እጮኝነታችን ፈርሶ ነበር ሌሎች ሰዎች ታገሳት (ታገሺው) በማለት ገፋፍተው ለዚህ ከፍተኛ ችግር ዳረጉኝ እንጅ የሚሉ ጥንዶች ቁጥር ጥቂት አይደለም።

ትዳር ማለት የራሣችንን ፍላጎትና ጥቅም የምናስጠብቅበት መድረክ ሳይሆን ለትዳር አጋራችን መልካም ፍላጎት ሙላት ሆነን የምንኖርበት ተቋም ነው። የኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወትና የጳውሎስ ትምህርት እንዲህ የሚል ነው፡- *"እያንዳንዱ ለራሱ የሚጠቅመውን አይመልከት፥ ለባልንጀራው ደግሞ እንጂ። በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ አሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን። እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቈጠረውም፥" /ፊል 2፡ 4-6/*፡፡ ይህን እውነት መሰረት ባደረገ የሕይወት መሰጠት ለራሳችን ፍላጎት ሳይሆን ለሌላው ጥቅም የመኖርን ክርስቶስ መሰል ሕይወት

> **ትዳር ማለት የራሳችንን ፍላጎትና ጥቅም የምናስጠብቅበት መድረክ ሳይሆን ለትዳር አጋራችን መልካም ፍላጎት ሙላት ሆነን የምንኖርበት ተቋም ነው!**

የምንኖርበት የመጀመሪያው መኖሪያችን ትዳር (ቤተሰብ) ነው፡፡ ይህን የሕይወት መርህ መመሪያችን ካደረግን ቤታችን በመግባባትና በሰላም ይሞላል፡፡ የዚህን ሕይወት ተቃራኒ በመምረጥ ራስ ተኮር ከሆንን ግን ከትዳር ጓደኛችን ጋር ያለን ሕብረት የጦርነት መደ መሆን ይቀየራል፡፡ ራስ ወዳድነት ባለበት የትዳር ግንኙነት ውስጥ ሁልጊዜም አለመግባባት፣ ግጭትና መለያየት መኖሩ ደግሞ አይቀሬ ነው።

## 4. ከጋብቻ በፊት በውሳኔ ሲረዷቸው የነበሩ ሰዎችን ጣልቃ ማስገባት

በቅርብ በተጋቡ ባለትዳሮች መካከል በውሳኔ ሂደት ላይ ለሚፈጠሩ ችግሮች ሌላው ተጠቃሽ ምክንያት ከተጋቢዎቹ አንዱ ወይም ሁለቱም ወደ ጋብቻ ሕይወት ከመግባታቸው በፊት በተለያዩ የኑሮ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ሲወስኑ ይረዷቸው የነበሩ ሰዎችን በትዳር ውስጥ ጣልቃ ማስገባታቸው ነው። ከአሁን በፊት ይረዷቸው በነበሩ ሰዎች ላይ ያላቸው ከፍተኛ የሆነ አመኔታ አሁንም ያለእነርሱ መወሰን የማይችሉ ጥገኛ ሰዎች እንዲሆኑ ስላደረጋቸው በየጊዜው ምርጫና ውሳኔ በሚፈልጉ ጉዳዮች ጣልቃ እንዲገቡ ዕድል መስጠት ይጀምራሉ። እነዚህ ውሳኔ በመወሰን ሂደት ድጋፍ ይሰጡ የነበሩ ሰዎች የቤተሰብና የቤተ ክርስቲያን አባላት፣ ወዳጆች፣ አገልጋዮችና አማካሪዎች ሊሆኑ ይችላሉ።





በውሳኔ የሚረዱ ሰዎችን መፈለግ ብልህነት ቢሆንም የምናማክራቸው ሰዎች እንዲመርጡልንና እንዲወስኑልን መፍቀድ ግን ሰው መሆንን ትተን ስብእናችንን ሌሎች ሰዎች የሚያንቀሳቅሱን ሮቦቶች ለመሆን አሳልፈን መስጠት ነው። እኛ የሚያውቁ፣ የሚያስቡ፣ የሚያመዛዝኑና ውሳኔ ማሳለፍ የሚችል በቃት ያላቸው በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ የተፈጠሩ ሰዎች ነን፡፡ ስለዚህ ያለ አማካሪዎቻችን የማንተነፍስ እስከንሆን ድረስ በእነርሱ መተማመንና መደገፍ የለብንም። አማካሪዎችና ድጋፍ ሰጭዎች በአስፈላጊ ጊዜ ለውሳኔ የሚረዳ አሳብ በማፍለቅ በጋራ የመፍትሔ አሳብ የሚያፈላልጉና ውሳኔውን ለእኛ የሚተውሉን መሆን መቻል አለባቸው። አማካሪዎችም የምናማክራቸውን ሰዎች ያለእኛ የማይንቀሳቀሱ ሁልጊዜ በእኛ ተረጅና ጥገኛ ሰዎች ልናደርጋቸው አይገባም። አንድ ወቅት ላይ የማማከር አገልግሎታችን ሊያቆም ይገባል። ባለትዳሮች በራሳቸው እንዲቆሙና ለችግሮቻቸው ራሳቸው እንደ ባለትዳር ተነጋግረው መፍትሔ እንዲያፈላልጉ መፍቀድና መንገዱን ማሳየት መቻል አለብን።

ከጋብቻ በፊትና በትዳር ሕይወት ውስጥ ሁነው በየጊዜው ስልክ እየደወሉ፣ በአካል እየተገናኙ ምክር መጠየቅ አስፈላጊ ቢሆንም የሚያማክሩንን ሰዎች ምስክርነት፣ ማረጋገጫ፣ ተቀባይነትና አስተያየት ሳንሰማ አለመወሰን ሌላ አደገኛ ችግር ነው። እንደ ባለትዳር በአንድ ጉዳይ ላይ ስንነጋገር ስለዚህ ጉዳይ እነርሱ ምን ይላሉ? እነርሱ ምንም ካላሉ ምንም እርምጃ መውሰድ የለብንም፣ እነርሱ አልተስማሙበትም... የሚሉ የተለያዩ ባሎችና ሚስቶች በጋራ ተነጋግረው ውሳኔ መወሰን እንዳይችሉ ድፍረታቸውን የሚያስጥሉና ግንኙነትን ሊያሻክሩ የሚችሉ ልምዶች በተለይ በቅርብ የተጋቡ ባለትዳሮች የሚያጋጥሟቸው ተግዳሮቶች ናቸው። እነዚህን ተግዳሮቶች በመቀነስ ለችግሮች በመረዳዳትና በጋራ መፍትሔ እያፈላለጉ ጤነኛ ግንኙነት ያለውና ደስተኛ የሆነ የትዳር ሕይወት ለመኖር መትጋት ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው፡፡

# IV. በጋራ በመወሰን ላይ ለሚፈጠሩ ግጭቶች መፍትሔዎች

## 1. መቀመጥ፡- በጋራ ለመወያየትና ለመጸለይ መቀመጥ

በትዳር ውስጥ የሚያጋጥሙ ውሳኔ የሚፈልጉ ጉዳዮች ባልና ሚስት ተገቢ ውይይት አድርገውባቸው በስምምነት ሊወሰኑ ይገባል፡፡ ወደ ትክክለኛ ውሳኔ የሚያደርስ ገንቢ ውይይት ማካሄድ የሚቻለው ደግሞ ጥንዶቹ የጋራ ጊዜ ኖሯቸው አብረው መቆየት ሲችሉ ነው፡፡ ስለዚህ ባለትዳሮች የትዳራቸውን ሰላም፣ መልካም ኅብረትና የሕይወት ዘመን እግዚአብሔርን አክባሪ ስኬታማ ጉዞ እንዲኖራቸው አብረው ለመጸለይና ለመወያየት በመቀመጥ የጋራ ጊዜ መውሰድ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ባለትዳሮች በጋራ በምንቀመጥበት ወይም የጋራ ጊዜ በምንወስድበት ወቅት መጠንቀቅና ራሳችንን መፈተሽ ያለብን የውስጥ መነሻ አሳባችን ላይ ነው። በጋራ በምንቀመጥበት ጊዜ በጉዳዮቻችን ላይ ትኩረት አድርገን ያሰብነውን ለመፈጸም እንዳንችል ነጻነት የሚነፍጉ ጉዳዮችን ማስወገድ አስፈላጊ ነው። ለመወያየትና ለመመካከር የምንቀመጠው

በማሸነፍና በመሸነፍ፣ በፍርሃትና በጭንቀት፣ በከርክር፣ በጠብና በቁጣ መንፈስ እንዳይሆን መጠንቀቅ ያስፈልጋል:: ላለመስማማት ራስን አዘጋጅቶና ዝግ አድርጎ ከመምጣትና ከመቅረብ ራስን ማጽዳት በጋራ ተቀምጦ ለመወያየት፣ ለመጸለይና የተለያዩ አማራጭ የመፍትሔ ሃሳቦችን በነጻነት ለማንሸራሸር ጠቀሜታው የጎላ ነው።

## 2. መግለጥ፡- ውሳኔ የሚጠይቀውን ጉዳይ መግለጥ

ግልጥነቱ ይበልጥ እንዲታወቅና እንዲጎላ ውሳኔ የሚፈልገው ርዕሰ ጉዳይ አስፈላጊነት ላይ ተወያይቶ መተማመን የሚኖረው ገንቢ ስተዋጽኦ አጠያያቂ አይደለም። አሳቡን ወይም ችግሩን በግልጥነት ማስቀመጥ ለመግባባትና ወደ አንድ ውሳኔ ለመድረስ የሚሰጠው እገዛ ቀላል አይደለም። ለትዳር ግንኙነታችን የሚሰጠውን ጠቀሜታ ማንሳት ብቻ ሳይሆን አስቸኳይነቱንና አንገብጋቢነቱን ጭምር መግለጽ ይበልጥ በጋራ የመወሰን እድሉን ከፍ ያደርገዋል። ነገሮችን ከብዙ አቅጣጫ በመመዘንና በመመልከት ለትዳራችንና ለቤተሰባችን የትኛው ይበልጥ ይጠቅማል? ጥቅሙ ወይስ ጉዳቱ ያመዝናል? የትኛውስ ቢቀድም መልካም ነው? በማለት የተለያዩ አማራጭ የመፍትሔ አሳቦችን በማቅረብ ለትዳር ግንኙነታችን የሚበልጠውን በጋራ ተስማምቶ ለመወሰን የምንችለውን ሁሉ ጥረት ማድረግ ቤተሰባችንን በመተማመንና በነፃነት ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ያስችለዋል።

## 3. መመከር፡- ለትክክለኛና ጽድቅ ለተሞላው ውሳኔ በእግዚአብሔር ቃል መመከር

ስለእያንዳንዱ ርዕሰ ጉዳዮቻችን ከእግዚአብሔር ቃል ቀጥተኛ ጥቅስ ልናገኝላቸው አንችልም! ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል በዚህ ጉዳይ ላይ ምን ይላል? እየተጓዝን ያለነው ጽድቅ በሞላበት አካሄድ ነው ወይስ በአመጽ? ይህ ጉዳይ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኛል ወይስ ያሳዝናል? ያሰብነው ሃሳብ ትዳራችንን የሚደግፍ ነው ወይስ የሚያፈርስ? ውሳኔያችን የእኛ የግል ፍላጎት ብቻ ነው ወይስ በእግዚአብሔር ቃልም የተደገፈ ነው? የሚሉ የተለያዩ መሠረታዊ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር መመካከር አስፈላጊ ነው። ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ስንመካከር ለቃሉ ለመሸነፍና ለመታዘዝ እንጂ ቃሉን ወደ ምንፈልገው ወደ ራሳችን የግል ፍላጎት ማስፈጸሚያነት ለመጠምዘዝ እንዳይሆን ከፍተኛ ጥንቃቄ ያስፈልገናል /2ኛጢሞ 3፡16/።

## 4. መውሰድ፡- በቁጣና በስሜት ውሳኔ እንዳንወስን አስቀድሞ በቂ ጊዜ መውሰድ

በቁጣና የእኔ አሳብ ብቻ ይፈጸም በሚል ጭፍን ስሜት ውሳኔ እንዳንወስን ውጥረቶችን በማለዘብና የእኛን የውስጠኛ መነሻ አሳብ ለመፈትሸና ለመመዘን በቂ ጊዜ በመውሰድ ውሳኔን ለመወሰን ዝግጁ መሆን በትዳር ውስጥ በጣም አስፈላጊ ከሆኑት ግብዓቶች አንዱ ነው:: ይህን ማድረጋችን ተጸጽተን ነገሮችን በመተው፣ በይቅርታና በሰላም ለትዳር አጋሮቻችንና ለቤተሰቦቻችን እንድናስብ ዕድል ይሰጠናል። በጊዜው





በርዕሰ ጉዳዮቻችን ላይ መስማማት ካቃተን የግድ ዛሬ ካልሆነ ሞቼ እገኛለሁ የሚለውን የሞኞች ችኩልነት በመተው በጥሩ ልብና በተረጋጋ ስሜት የተሻለ የውሳኔ አሳብ መፍለቅ እንዲችል እስኪ በሌላ ጊዜ፣ በሚቀጥለው ቀን፣ ሳምንት… በዚህ ጉዳይ ላይ እንመለስበት በሚል ስምምነት ቀጠሮ ሰጥተነው በሂደት ነገሮችን መቃኘቱ ብልህነት እንጂ ተሸናፊነት አይደለም!! ከብዙ አቅጣጫ ነገሩን ለማየት ማለትም ለማሰብ፣ ለመጸለይ፣ ሌሎችን ሰዎች ለማማከርና የሌሎችን ልምምድ ለመጠየቅ ጊዜ መስጠቱ አስፈላጊ ነው። ጊዜ መስጠት ዛሬ በጭፍን የወሰንነው ጉዳያችን ነገ እንዳይጸጽተን፣ ቀላሉ ነገር ውስብስብ እንዳይሆን፣ ለትዳራችን ጥቅምና ሰላም የፈለግነው ጉዳይ ሰላም የሚነሳንና ልብ የሚያሳዝን ብሎም ለመለያየት በር ከፋች እንዳይሆን ከወዲሁ ተረጋግቶ በሰከነ ስሜትና በትዕግስት ውሳኔ ላይ ለመድረስ የሚረዳን አስፈላጊ እርምጃ ነው።

## 5. መፈለግ፡- በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ድጋፍ የሚያደርጉልን አማካሪዎችን በጋራ መፈለግ

ለውሳኔ ያቀረብነው ወይም እየተነጋገርንበት ያለው ጉዳይ ከፍተኛ ትኩረት የሚጠይቅ በሚሆንበት ጊዜ የሌሎች ሰዎች ምክር፣ ተሞክሮና ድጋፍ የሚያስፈልግ ሊሆን ይችላል። ምናልባት የምንነጋገርባቸውና ውሳኔ የምንፈልግባቸው ጉዳዮች ልጅ መውለድና ማሳደግ፣ የለመድነውን አገር ወይም አካባቢ መልቀቅና ወደ ሌላ አገር መሄድ፣ ሥራ መቀየር፣ የጤንነትና የሕክምና ጉዳይ ላይ መፍትሄ መሻት፣ አገልግሎት፣ ከፍተኛ የገንዘብ ወጭ የሚጠይቅ ፕሮጀክት… ሊሆኑ ይችላሉ። እንደነዚህ ዓይነት ታላላቅ ውሳኔ የሚጠይቁ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ከመወሰናችን በፊት ከትምህርት፣ ከመንፈሳዊነት፣ ከሙያና ከልምድ አንጻር የሚመክሩንና አቅጣጫ የሚያሳዩን ባለሙያ ሰዎች ያስፈልጉናል።

ሌሎችን ሰዎች ማማከር ማለት ሽንፈት፣ አላዋቂነት፣ ገመናን አውጥቶ ማሳየት፣ እንዲሁ በከንቱ ጊዜ ማጥፋት እና ሌሎች ሰዎች ውሳኔውን እንዲወስኑልን ማድረግ አይደለም ነገር ግን እኛ ያላየነውን፣ የማናውቀውን እና የሌለንን የተለያየ ሃሳብና መረጃ ከሌሎች በመቀበል ለውሳኔ እንድንደረስ በአማካሪዎች መረዳት ነው:: እንዲህ ዓይነት እርዳታ በሚያስፈልገን ጊዜ ወደ ትክክለኛ አማካሪዎች በመሄድ ድጋፋቸውን መጠየቅ ጠቃሚና ምትክ የማይገኝለት ትልቅ አስተዋጾ እንደሆነ ልንገነዘብ ይገባል። ይህ ሲሆን በጋራ በመስማማት ካልሆነ በስተቀር አማካሪ መፈለግ አንድ ጉዳይ ሆኖ እያለ እነማን ይሁኑ፣ ምን ዓይነት ሙያና ልምድ ያላቸው፣ መቼና እንዴት የሚሉ ሌሎች አነጋጋሪና ስምምነት ጠያቂ ጉዳዮች መሆናቸውን መዘንጋት የለበትም። በተቻለ መጠን ለጋራ የትዳር ሕይወት በጋራ ማሰብ፣ መወያየትና የጋራ ስምምነት ላይ መድረስ ተግቢ ነው።

በባለትዳሮች መካከል የተለያዩ ቀውሶች መፈጠራቸው አይቀሬ ነው። እነዚህን በትዳር ውስጥ የሚያጋጥሙ የተለያዩ ለግጭት ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ክስተቶች በሁለት ልንከፍላቸው እንችላለን። ***የመጀመሪያዎቹ*** ያልተጠበቁ የሕይወት ክስተቶች

(ገጠመኞች) ናቸው። ገጠመኞቻችን በሰው ሕይወት ሲከሰቱ የነበሩና አሁንም የሚከሰቱ ቢሆኑም ያልተጠበቁ ገጠመኞች ያልናቸው ያልጠበቅናቸው ክስተቶች ስለሆኑ ነው። እነዚህ ክስተቶች ውርጃ (ጭንገፋ)፣ ሕመም፣ ድብርት፣ የተለያዩ አደጋዎች፣ የሚወዱት የቤተሰብ አባል በድንገተኛ ሞት መለየት፣ ኢኮኖሚያዊ ክስረትና ሌሎችም ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮችን ሊያጠቃልሉ ይችላሉ።

**ሁለተኛዎቹ** የሚጠበቁ ክስተቶች ናቸው። የሰው ልጅ ይወለዳል፣ ያድጋል፣ ይሞታል። በወሊድና በእድገት ወቅት ደግሞ የሚከናወኑ ብዙ የሕይወት ውጣ ውረዶች መኖራቸው ይታወቃል። በባለትዳሮች መካከል ራሳቸው ጥንዶችም ሆኑ ቤተሰብና ሌላው ሰው የሚጠብቋቸው ነገሮች አሉ፡፡ ልጅ መውለድ፣ የልጆች እድገትና ትምህርት ቤት መግባት እና ቀጣይ እድገታቸው የሚያመጣቸው ለውጦች ከሚጠበቁ ክስተቶች መካከል ተጠቃሽ ናቸው። እነዚህን ለውጦች ተከትሎ በትዳር ግንኙነት ውስጥ ችግሮች ይፈጠራሉ፡፡ እንደ ችግሮችና እንደሚያሻቸው ውሳኔ የሌሎችን ሰዎች ወይም የአማካሪዎችን እርዳታ አጥብቆ መፈለግ ብልህነት ነው። መልካም መካሪ የሆነው የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ሲል ይመክራልና፡- *"መልካም ምክር ከሌለ ዘንድ ሕዝብ ይወድቃል በመካሮች ብዛት ግን ደኅንነት ይሆናል።"* /ምሳሌ 11፡ 14/





## ለጥንዶች በግላቸውና በቡድን ለማጥናት የሚረዷቸው የውይይት ጥያቄዎች

## የምዕራፍ አምስት (5)

## የውይይት ጥያቄዎች

1. በጋራ መወሰንን እንዴት ትገልጡታላችሁ? ባልና ሚስት ሆነን ስንኖር በሁሉ ነገር መስማማት አለብን ወይ? ካልሆነስ ምን ማድረግ አለብን ትላላችሁ?
2. የባለትዳሮች በጋራ መወሰን የሚሰጠውን ጥቅም በማንሳትና ከትዳር ሕይወታችሁ ጋር በማያያዝ ተወያዩበት።
3. ባልና ሚስት እንደ ባለትዳር በጋራ መወሰን እንዳይችሉ የሚያደርጓቸው የተለያዩ ምክንያቶች ምንድን ናቸው? ምክንያቶችን በመዘርዘርና በእናንተ ትዳር የግጭት ምክንያት የሆኑባችሁን ሰበቦች በማንሳት በፍጹም ግልጥነት ተወያዩባቸው፡፡
4. እንደ ባለትዳር ለጋራ የትዳር ሕይወት በጋራ እየተመካከሩ መወሰን እንዲቻል ምን መደረግ አለበት ትላላችሁ?
5. ዛሬ በእናንተ የትዳር ሕይወት በግልና በጋራ ልትወስዷቸው የሚገቡ ተግባራዊ የመፍትሔ እርምጃዎች ምንድን ናቸው? በጋራ ለውጥ ለማምጣትና በጋራ ለመረዳዳት ቃል በመግባት እርምጃውን ተግባራዊ ለማድረግ እቅዱ።

# ምዕራፍ ስድስት(6)
# የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት

በባለትዳሮች መካከል ከሚፈጠሩ ችግሮች መካከል አብይ ከሚባሉት አንዱ የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ነው። ይህ ምዕራፍ የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ችግር ላይ ትኩረት በማድረግ ከባህላችን አንጻር የቤተሰብ አባላት እነማን እንደሆኑና የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ማለት ምን እንደሆነ በመዳሰስ በቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ሊፈጠሩ የሚችሉ ችግሮችንና *"ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል በሚስቱም ይጣበቃል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ።"* /**ዘፍ 2፡ 24**/ የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርህ መሰረት ያደረጉ መፍትሔዎቻቸውን ይጠቁማል።

## I. ቤተሰብና የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ምንነት

ቤተሰብ ማለት በመወለድ፣ አብሮ በማደግ እንዲሁም በጠበቀ ወዳጅነት በተፈጠረ ማሕበራዊነት የተጣመረ ግንኙነት ያለው ቤተ-ዘመዳዊ ትስስር ነው። በአብዛኛው የቤተሰብ አባላት በመባል የሚታወቁት አባትና እናት፣ ወንድምና እህት፣ እንጀራ ልጆች.፣ አያትና ቅደመ አያት፣ አክስትና አጎት፣ የአክስትና የአጎት ልጆች ሲሆኑ እንደ ሰዎች ቅርበት የልጆች አሳዳጊዎች፣ የቅርብ ወዳጆችና ጓደኞችን እንደ ቤተሰብ የመቁጠርና የማጠጋጋት ባህልም አለን። ባልም ሆነ ሚስት የሚያድጉትና የሚቀረጹት በዚህ ሕብረት ውስጥ በመሆኑ ካደጉና ወደ ራሳቸው ትዳር ከገቡ በኋላ እንኳን የዚህ ማሕበራዊ መረብ ጥልፍልፎሽ በአእምሮአቸው፣ በአይታቸው፣ በልምዶቻቸው፣ በፍላጎታቸውና በአጠቃላይ በሁለንተናቸው ውስጥ ሊረዱት ከሚችሉት በላይ ማረፊያ ቦታና ዋጋ አለው።።

የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ስልን አንድ ሰው ከቤተሰብ ኅብረት ወጥቶ ትዳር ከመሠረተ በኋላ በሚኖረው የትዳር ሕይወት ላይ የቀድሞው ቤተሰብ አባላት አዲስ ቤተሰብ የመሠረተውን የቀድሞ የቤተሰባቸው አባል እንደ ቀድሞው ለማስተዳደር የመፈለግና ጥረት የማድረግ ሂደት ነው። ይህ ሁኔታ በተለያየ መንገድ ሊገለጥ ይችላል። ከአዲሶቹ ተጋቢዎች መካከል የአንዳቸው ወይም የሁለቱም የቤተሰብ አባላት እንደ ቀድሞው የልጅነት ኑሮ በጥንዶች ሕይወት ላይ ለመወሰን ፍላጎት ማሳየታቸውና ሙከራ ማድረጋቸው እንዲሁም የጥንዶችን የፍቅር ግንኙነት በተለያየ መንገድ መሻማት መፈለጋቸውና ለመሻማት መታገላቸው ዋናው የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት መገለጫ ነው።

## II. አባትንና እናትን መተው

**በዘፍጥረት 2፡ 24** የተጻፈውን ክፍል በማጣቀስ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር አገልግሎቱ ለፈርሳዊያን ጥያቄ **በማቴ 19፡ 5** በሰጠው ምላሽ *"… ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል፥ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ የሚለውን ቃል አላነበባችሁምን?"* /**ማቴ 19፡ 5**/ በማለት ሰው ወደ ጋብቻ ሕይወት ሲገባ አስቀድሞ ከቤተሰቡ ጋር የነበረውን ጥብቅ ቁርኝት በማላላት ራሱን ችሎ የተገነባ አዲስ ቤተሰብ የመሰረተ መሆኑን አሻሚ





ባልሆነ መንገድ ግልጥ አድርጎታል። ሐዋሪያው ጳውሎስም **በኤፌ 5፡ 31** ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን በጻፈው መልዕክት ይህንኑ መርህ ሲያረጋግጥና ሲያጠናክር መመልከት እንችላለን።

በእርግጥ *"ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱ ጋር ይጣበቃል"* የሚለውን ቃል ሚዛኑን ያልጠበቀ ትርጓሜ በመስጠት ትክክለኛ ባልሆነ መንገድ የተረዱትን አንዳንቹን ጥንዶች ከወላጆች ጋር ፈጽሞ ቤተሰባዊ ግንኙነት እንዳይኖር የመፈለግ ዝንባሌ እንዲያንጸባርቁ ዳርጓቸዋል። ከዚህ በተቃራኒ ሌሎች ጥንዶች ደግሞ ሊተገበር የማይችል መርህ እንደሆነ ቆጥረውት ይህንን እውነት ወደ ጎን በመተው ድንበር የለሽ በሆነ መቀላቀል ትዳራቸውን ከቤተሰቦቻቸው ጋር በመጋራት ባልተፈለገ የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ምክንያት ትዳራቸውን በቀውስ አደጋ ላይ ሲጥሉት ይታያል። ስለዚህ ባልም ሆነ ሚስት ወደ ትዳር በሚገቡበት ወቅት ከብሉይ ኪዳን እስከ አዲስ ኪዳን ያሉት ቅዱሳት መጽሐፍት በስምምነት የመሰከሩለትንና የገለጡትን እውነት ከጽንፈኝነት በጸዳ እንዲሁም ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ሊረዱት ይገባል። ለዚህ እውነት ራስን ለማስገዛት በተዘጋጀ ማንነትና በቆረጠ ፈቃደኝነትም አዲሱን ቤተሰብ መመሥረት ኃላፊነታቸው ነው። ኃላፊነታቸውን በሚገባ ይወጡት ዘንድ ደግሞ ከሚከተሉት አሳቦች ጋር መግባባት አለባቸው፡-

### 1. አባትና እናትን የመተውን መርህ በትክክል መረዳት

አስቀድሞ እንደተገለጠው ትዳር የመሠረቱ ጥንዶች *"ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱ ጋር ይጣበቃል"* የሚለውን አምላካዊ ቃል ትክክለኛ በሆነ፣ ትዳርን ሊያንጽ እና ሊተገበር በሚችል መንገድ ሊረዱት ይገባል። አንደኛው መገንዘብ ያለባቸው እውነት አባትና እናትን መተው ማለት ከቤተሰብ ጋር ፈጽሞ ቤተሰባዊ ግንኙነት አለማድረግ ወይም ከቤተሰብ ጋር ያለን ግንኙነት ሙሉ በሙሉ ማቋረጥ ማለት አይደለም። ተጋቢዎች ማስተዋል ያለባቸው ጉዳይ የእኛ ወይም የትዳር አጋራችን ቤተሰቦች ቤተሰቦቻችን መሆናቸውን ነው። የትዳር አጋራችን ቤተሰብ አባላት የባል ወይም የሚስት ወላጆች (አባትና እናት)፣ እህት፣ ወንድም… መሆናቸው መዘንጋት የለበትም። ወደን ያገባናቸው የትዳር አጋሮች የተገኙበትና አቅማቸው በፈቀደ መጠን የትዳር ጓደኞችንን አሳድገው ለቁም ነገር ያበቁ እነዚህ የቤተሰብ አባላት ናቸው። ስለዚህ የአክብሮት፣ የፍቅር፣ የወዳጅነትና የበጎ አመለካከት ምላሽ ሊሰጣቸው ይገባል። ይህን ሐቅ በመቀበል በተቻለ መጠን ጤናማ ቤተሰባዊ ግንኙነት እንዲኖር መጣር መልካም ነው።

ሌላው ***"መተው"*** ማለት ፈጽሞ ቤተሰብ ለባለትዳሮች፡ ባለትዳሮች ደግሞ ለቤተሰብ የተለያየ ድጋፍ ማድረግ አያስፈልገንም ማለት አይደለም። የትዳርን ጤንነትና ደስታ በማያደፈርስ መንገድ፣ በሚያስፈልግ ጊዜና ሁኔታ በተለያዩ መንገዶች መመካከር፣ መረዳዳትና መደጋገፍ ተገቢ ነው። ለወላጆቻችን እንደ ልጅና እንደ ትዳር አጋሮቻችን

ቤተሰብ በሚያስፈልጋቸው ነገር አቅማችን በፈቀደ መጠን በመመካከር ልንረዳቸው፣ አብረናቸው ልንቆምና የልጅነት ኃላፊነትና ግዴታችንን ልንወጣ የግድ ነው። ነገር ግን በትዳር የተጣመርነውና አዲሱን የባልነትና የሚስትነት ዝምድና የፈጠርነው እኛ (ባልና ሚስት) በመሆናችን ጥንዶች በሚኖረን ግንኙነትና የትዳር ኃላፊነት ውስጥ ቤተሰብ እኩል ድርሻ ኖሮት አብሮን በጉዳዮቻችን ላይ ይወያያል፣ ውሳኔ ይወስናል ወይም መመሪያ ይሰጣል ማለት አይደለም፡፡ ወደ ትዳር ስንገባ ከቤተሰብ ጋር ያለን ጥብቅ ትስስር መላላትና ከትዳር አጋራችን ጋር ያለን ትስስር ግን የሌላ ሰው ጣልቃ ገብነትን ንፋስ በማያስገባ መንገድ ጠበቅ ማለት ይኖርበታል፡፡ ይህ መርህ ሁል ጊዜ መጣስ የሌለበት መጽሐፍ ቅዱሳዊ የጋብቻ ሕግ ስለሆነ በተጋቡ ጥንዶች ሁሉ መከበር አለበት፡፡

## 2. የቤተ- ዘመድ ጣልቃ ገብነትን ምንነት መረዳት

የቤተሰብ ጣልቃ ገብነትን ምንነት፣ መቼ፣ በምንመልኩና እንዴት እንደሚከሰት መረዳት ድንበር ዘለል የሆነው ቤተሰባዊ ግንኙነት የተመሠረተውን የትዳር ሕይወት እንዳይጎዳ አስቀድሞ ለመጠንቀቅ ይረዳል። ለመሆኑ የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ማለት ምን ማለት ነው።

**አንደኛ፡-** የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ማለት፡ የቤተሰብ አባል የሆኑ ቤተ- ዘመዶች በሙሉ ወይም በከፊል በጥንዶች የትዳር ሕይወት ውስጥ ቅድሚያ እንዲሰጣቸው የመፈለግና ጥንዶቹም በጋራ ወይም በተናጠል ከትዳር አጋሮቻቸው በፊት ለቤተ-ዘመድ በማንኛውም ጉዳይ ቅድሚያ መስጠት የመጀመር ሂደት ነው።

**ሁለተኛ፡-** የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ማለት፡ የቤተ-ዘመድ አባል የሆኑ ሰዎች የጥንዶችን የትዳር ፍቅር በመጋራት ወይም በመሻማት ጥንዶቹ ከትዳር አጋራቸው ጋር ሰፊና የተመረጠን ጊዜ ለማግኘት የሚያደርጉትን ጥረት፣ ከትዳር አጋራቸው እንዲሰጣቸው የሚፈልጉትን ትኩረት እንዲሁም ማግኘት የሚፈልጉትን ፍቅርና እንክብካቤ በአግባቡ እንዳያገኙ እንቅፋት የመሆን ሂደት ነው፡፡ ወይም የተወደዱ እናት፣ አባት፣ ልጅ፣ ወንድም፣ እህት... ለትዳር ጓደኛ የሚሰጥን ፍቅርና እንክብካቤ ለራሳቸው ለመውሰድ ሲንቀሳቀሱ ከዚያም አልፎ ባለትዳሮችም ሲፈቅዱላቸው የሚጠቁም ወይም የሚያሳይ ሁኔታ ነው።

**ሦስተኛ፡-** የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ማለት የቤተ- ዘመድ አባል በተለይ ወላጆች፣ እህትና ወንድም ወይም ሌሎች ቤተ-ዘመዶችና ከጥንዶቹ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ያላቸው ሰዎች በጥንዶች የትዳር ሕይወት ጣልቃ በመግባትና የባልና የሚስትን ሚና በመጋፋት ወይም በመንጠቅ አዲስ የተመሰረተውን ቤተሰብ መምራትና ማስተዳደር ሲጀምሩና በተለያየ ምክንያት ጥንዶችም የቤተሰብ አባል የሆነ ሰው ይህን እንዲያደረግ እድል ሲሰጡ የሚያሳይ ሂደት ነው።





**አራተኛ፡-** የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ማለት የቤተሰብ አባት በባለትዳሮች ሕይወት፣ ምርጫና ውሳኔ ላይ ለመሳተፍና ለመወሰን ዕድል እንዲሰጣቸው ሲጥሩና ጥንዶችም በጋራ ወይም በግል ፈቅደው በውሳኔዎች ሁሉ እንዲሳተፉ በር የመክፈት ሂደት ነው።

**አምስተኛውና የመጨረሻው፡-** የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ማለት የቤተ-ዘመድ አባል የሆነ ግለሰብም ይሁን በአጠቃላይ የቤተሰብ አባላት ከጥንዶቹ ጋር እኩል በሆነና ከእነርሱ ባልተናነሰ መልኩ በማንኛውም ጉዳይ ላይ ከጥንዶቹ የትዳር ሕይወት ተጠቃሚ መሆን ሲፈልጉ፣ ሲጀምሩና እንዲጠቀሙ ባለትዳሮች ሲፈቅዱላቸውና ዕድል ሲሰጧቸው የሚያሳይ ሂደትና ሁኔታ መሆኑ መዘንጋት የለበትም።

በአጠቃላይ እንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች በባለ ትዳሮች ኅብረት ውስጥ የሚፈጠሩ ከሆነ በጥንዶቹ የተመሠረተው ትዳር ከፍተኛ ቀውስ ውስጥ ይገባል፡፡ ጉዳዩ በጊዜ ካልተስተካከለም ወደ ፍች ሊያደረስ ይችላል፡፡ ይህንን እውነታ በመረዳት ጥንዶች የትዳራቸው ጤንነት ጠላት ከሆነው ከዚህ በሽታ አስቀድመው ትዳራቸውን መጠበቅ ይኖርባቸዋል፡፡ ችግሩ ከተከሰተ በኋላ ካወቁት ደግሞ ግልጥ በሆነ ውይይትና በማያወላውል ውሳኔ አግባብነት ያለው እርምጃ በመውሰድ ትዳራቸውን ከቀውስ ማዳን ይጠበቅባቸዋል፡፡

## III. በቤተ-ዘመድ ጣልቃ ገብነት ለግጭት ሊያጋልጡ የሚችሉ የግጭት መንስኤዎች

በቅርብ በተጋቡ ባለትዳሮች መካከል ከቤተ-ዘመድ ጋር ተያይዘው ሊፈጠሩ የሚችሉ ችግሮች ምንድን እንደሆኑ መረዳት ብዙ አመት ሳንጓዝና የትዳር ግንኙነታችንን ሳያበላሽ በጊዜ ለመንቃት፣ ለመመካከር፣ ለመወሰንና እርምጃ ለመውሰድ ጠቃሚ ነው። ለቤተሰብ ድንበር ዘለል የሆነ ጣልቃ ገብነት ተጋላጭ የሚያደረጉንን ምክንያቶች በማወቅ ሚዛኑን በጠበቀ ግንኙነት፣ ከቤተሰብ ጋር መቀራረብና ሰላማዊ በሆነ መንገድ ቤተሰባዊነትን መጠበቅ እንችላለን። በሐበሻው ሕብረተሰብ መካከል ለቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ተጋላጭ ከሚያደረጉን ምክንያቶች መካከል ጥቂቶቹ እያንዳንዳችን ለቤተሰብ ያለን ቤተሰባዊ የሆነ ፍቅር፣ የቤተሰብ ባህሎቻችን የፈጠሯቸው እሴቶችና ልምዶች፣ የኢኮኖሚ ችግሮቻችን፣ አንዱ የሌላው ጥገኛ መሆንና የሥራን ጫና ለመጋራት (ለመደጋገፍ) በተለይ በወሊድ፣ በሕመም፣ ልጆችን በማሳደግና ለመማርና የተሻለ ሥራ አግኝቶ ለመሥራት መፈለግ የመሳሰሉት በዋናነት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በእነዚህ ሰበቦች ምክንያት ባለትዳሮች ይበልጥ ከቤተሰብ ጋር ይቀራረቡና ለችግሩ የበለጠ ተጋላጭ ይሆናሉ፡፡ የሚከተሉት ለችግሩ ተጋላጭ የሚያደርጉን ነጥቦች ይህንን አሳብ የበለጠ ለማብራራት ያስችሉናል፡፡

### 1. አባትንና እናትን አለመተው

አስቀድሞ በሚገባ እንደተገለጠው መጽሐፍ ቅዱስ *"ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል፥ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ የሚለውን ቃል አላነበባችሁምን?"*

/ማቴ 19: 5፣ ኤፌ 5: 31/ የሚል ግልፀ መመሪያ መጽሐፍ ቅዱስ የሰጠ ቢሆንም በቅርብ የተጋቡ እንዲሁም ጥቂት ለማይባሉ አመታት በጋብቻ ውስጥ የቆዩ ባለ ትዳሮች ይህንን እውነት በመረዳት በዚህ መርህ ትዳራቸውን ሲመሩ አይታዩም፡፡ ይህ ችግርም በተለይ በአዲስ ተጋቢዎች የጋብቻ ሕብረት መካከል የቤተ-ዘመድ ጣልቃ ገብነት እንዲከሰት ሰበብ ከሚሆኑ ምክንያቶች መካከል እናትና አባትን አለመተው ከዋናዎቹ አንዱ እንዲሆን አድርጎታል።

ብዙዎቹ አዲስ ተጋቢዎች ቀድሞ ከቤተሰባቸው ጋር የነበራቸው የብዙ አመት ግንኙነት፣ አስተዳደግ፣ ቅርበትና ባሕርይ ተደማምሮ የተቀረጹበትን የቀድሞ ዓለም ለመተው ይቸገራሉ። አባትንና እናትን ባለመተው ከትዳራቸው በፊት እነርሱን በማስቀደምና ለትዳር ጓደኛቸው መስጠት ያለባቸውን ፍቅር እንዲሻሙ በመፍቀድ ከትዳራቸው ይልቅ ቤተሰብን ማስበለጣቸው ለሌላ ተያያዥ ችግር የሚያጋልጣቸው ሆኗል። ይህ ሁኔታ በትዳር ውስጥ በሚደረግ ምርጫና ውሳኔ ጣልቃ እንዲገቡና አዲሱን ቤተሰብ እንዲያስተዳድሩ ለወላጆች ወይም ለዘመዶች የማይገባቸውን ፍቃድና መብትም ይሰጣቸዋል፡፡

በማንኛውም ሁኔታ ከትዳር ሕይወታቸው ተገቢ ባልሆነ መንገድ ቤተሰብ ተጠቃሚ እንዲሆን ካደረጉ ከመጠን ላለፈ የቤተሰብ አስተዳደር ጣልቃ ገብነት አዲሱ ትዳር ተጋላጭ ይሆናል። ችግሩ የሚያስከትለው አፍራሽ ተጽዕኖ ሀሉቱም ተጋቢዎች ወይም ከሁለቱ አንዱ ከጋብቻ በፊት ይኖሩት የነበረውን የአኗኗር ዘይቤ ካገቡ በኋላ እንዳይተውትና አብሯቸው እንዲቀጥል በማነሳሳት ባለትዳሮች ሆነው ሳለ ትቸዋለሁ ወዳሉት የብቸኝነት ኑሮ የኋሊት እንዲመለሱ ያደርጋቸዋል፡፡ ይህም ከስተት በባለትዳሮች መካከል የአስከፊ አለመግባባትና ግጭት ምክንያት ይሆናል፡፡ ነገሩ ከከፋም ለፍች ሊዳርጋቸው የሚችል ቀውስ ይሆናል።

## 2. ከቤተሰብ አባል የለመዱትን ከትዳር አጋሮቻቸው ማጣትና የለመዱትን መፈለግ መጀመር

ለቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ችግር አዲስ ተጋቢዎች ተጋላጭ እንዲሆኑ የሚያደርጋቸው ሌላው ምክንያት ከጋብቻ በፊት በቤተሰብ አባሎቻቸው መካከል ሲሆኑላቸው የነበሩትን ልዩ ልዩ ጥቅሞችና እንክብካቤዎች ከትዳር አጋሮቻቸው መጠበቅ መጀመራቸው ነው። ሚስቶች ከአባታቸውና ከወንድሞቻቸው የለመዱትን ባሎቻቸው እንደ አባትና እንደ ወንድም በመሆን እንዲያሟሉላቸው ይጠብቃሉ፡፡ የጠበቁትን ሳያገኙ ሲቀሩ ደግሞ ሊናደዱ፣ ሊያጉረመርሙ፣ ሊያማርሩና በትዳር ግንኙነታቸው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊመጣ ይችላል። እንዲሁም ባሎች የእናታቸውንና የእህቶቻቸውን ባሕርይ፣ ልምምድና እንክብካቤ ... ከሚስቶቻቸው ማግኘት ጠብቀው ሳያገኙ ሲቀሩ ይጎዳሉ፡፡ ጉዳዩም ላለመግባባትና ለግጭት መንስኤ ሊሆን ይችላል።





ይህ ችግር ባጋጠማቸው ጊዜ ከትዳር አጋሮቻቸው ማግኘት ያልቻሉትን ነገር ፍለጋ ወደ ቤተሰቦቻቸው ይመለሳሉ፡፡ ከትዳር ጓደኛቸውም ይልቅ ከቤተሰቦቻቸው ጋር ቅርበታቸውን ያጠናክራሉ፡፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ችግሩ አድጎ ትልቅ የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ቀውስ በትዳር ውስጥ ይፈጥራል፡፡ ለዚህም ነው አዲስ ተጋቢዎች ከጋብቻ በፊት ስለቤተሰባቸውና ስለአስተዳደጋቸው መነጋገር፣ መተዋወቅ ብሎም አንዳንድ ነገሮችን አስቀድሞ ማስተካከል የሚያስፈልጋቸው። አስቀድመው ያወቁት ነገር አያስደነግጥም፣ ግራ አያጋባም፣ ደግሞም ራስን አስቀድሞ ለማዘጋጀት ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው።

## 3. ቤተሰብን ለመርዳትና ከቤተሰብ እርዳታ በመፈለግ መካከል የሚፈጠር ውጥረት

በቅርብ በተጋቡ ባለትዳሮች መካከል እንዲህ ዓይነቱ ችግር እንዲፈጠር የሚያደርገው ምክንያት ወቅቱ የሽግግር ጊዜ መሆኑ ነው። በቤተሰብ ሲተዳደሩ የነበሩ ወይም በግል ራስን በራስ ሲያስተዳድሩ የነበሩ ላጤዎች ወደ ጋብቻ በሚገቡበት ወቅት የቤተሰብ አስተዳደር ጥገኝነት ዝንባሌ ወይም የራስን በራስ ለመምራት የመምረጥና የመወሰን ችግር ሊታይባቸው ይችላል። በዚህ ሁኔታ ውስጥ የሚፈጠሩ ችግሮች በሁለት አቅጣጫ ሊከሰቱ ይችላሉ። የመጀመሪያው የመጡበት የቤተሰብ የኑሮ አቅም ደካማ ሆኖ ራሳቸውን በራሳቸው ማስተዳደር የማይችሉ ሲሆንና ለወላጆቻቸው የገንዘብና የተለያዩ ነገሮች እርዳታ ማቅረብ የሚያስፈልጋቸው ሲሆን የሚፈጠር ችግር ነው። ቤተሰብን ለመርዳት የሚደረገው ጥረት ሂደት ከትዳር አጋር ጋር ሊያጋጫቸውና ለትዳራቸው ችግር ሊሆን ይችላል። የተረጂው ቤተሰብ አባላትም የሚያገኙት ጥቅማ ጥቅምና ድጋፍ እንዳይቋረጥባቸው በልጆቻቸው ትዳር ውስጥ ጣልቃ ይገባሉ፡፡

ሌላው በትዳር ላይ ያሉ ልጆች በወላጆች እርዳታ ሥር የወደቁና አግብተውም የቤተሰብ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ወይም ጥገኛ ከሆኑ ለቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ተጋላጭ ይሆናሉ፡፡ ክስተቱም በባለትዳሮች መካከል ሰላም እንዲጠፋ፣ እንዳይግባቡና እንዲጋጩ ያዳርጋል። ብዙ ጊዜ በገንዘብ ጥገኛ የሆኑ ሰዎች በራሳቸው የመምረጥና የመወሰን ብቃታቸው ላይ ጥገኝነታቸው አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያመጣባቸው ይችላል። አንዳንድ በገንዘብ የሚረዱ ሰዎች በተጋቢዎች መካከል ጣልቃ በመግባት በሚረዷቸው ሰዎች ኑሮ ላይ የመምረጥ፣ የመወሰንና የማስተዳደር የባለስልጣንነት አዝማሚያ ይታይባቸዋል። እነዚህ ሁለት ውጥረቶች በጥንዶች ትዳር ውስጥ መልካም የሆነ ግንኙነት እንዲጠፋ፣ በመካከላቸው ሰላምና ደስታ እንዳይኖርና እንደ ባለትዳር በጋራ እየወሰኑ የመኖር ዋስትናቸው ጥርጣሬ ውስጥ እንዲገባ በማስገደድ ከፍተኛ የሆነ እንቅፋትን ይፈጥሩባቸዋል።

## 4. የአንዱ የትዳር አጋር ቤተሰብ ላይ ብቻ ያተኮረ እርዳታና ቅርብ ግንኙነት መፍጠር

ሌላው ችግር ሊሆን የሚችለው ባል ወይም ሚስት ከአንዳቸው ቤተሰብ ላይ ብቻ ትኩረት ማድረጋቸው ነው። ወደራስ ቤተሰብ ብቻ ያጋደለ የገንዘብና የቁሳቁስ... እርዳታ በማድረግ የሌላውን የትዳር አጋር ቤተሰብ መርሳት፣ መተውና ችላ ማለት ሲጀመር በትዳራቸው መካከል አለመግባባትና ግጭት እንዲፈጠር ምክንያት ሊሆን ይችላል። አድሏዊነት በተሞላ መንገድ አንዱ የትዳር አጋር ሳይፈቅድና ደስተኛ ሳይሆን ከአንደኛው ቤተሰብ ጋር ብቻ የተለየ ቅርበት፣ ግንኙነት እና ኅብረት ማድረግ በትዳር ውስጥ ችግር እንዲፈጠር ከማድረጉ ባሻገር ለሌሎች የተባባሱ ግጭቶች አሳልፎ ሊሰጥ ይችላል።

## 5. የትዳርና የትዳር ጓደኛ በቤተ-ዘመድ ዘንድ ተቀባይነት ማጣት

ስለቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ባለን የባህል ተጽዕኖና አሉታዊ አስተሳሰብ ምክንያት ስለትዳር አጋሮቻችን ቤተሰብ መልካም አለማሰብ ሊፈጠር ይችላል። መልካም የሆነ አስተሳሰብ ካለመኖሩ የተነሳም በትዳር ጓደኞችን ቤተሰብ ዘንድ ጥሩ ተቀባይነት እያለን እንዳልተቀበሉን ሊሰማን ይችላል። በዚህ ወቅት የምናስባቸው ሃሳቦች፣ የምናሳያቸውና የምናደርጋቸው እንቅሳቃሴዎች ለትዳር አጋሮች በትዳራቸውና በቤተሰብ መካከል የመሆን ውጥረት ውስጥ እንዲገቡ ያደርጋቸዋል። ባላረጋገጥነው ጉዳይ የራሳችንን የተሳሳተ ግምት በመውሰድ ለትዳራችንና ለቤተሰብ ሰላምና ደስታ መደፍረስ ምክንያት ልንሆን እንችላለን፡፡ ስለዚህ በማስተዋል ነገሮችን በመያዝ ከተሳሳተ ግምት የጸዳ አስተሳሰብ እንዲኖረን ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

ነገር ግን ሁልጊዜ ችግር የሚፈጠረው በተሳሳቱ ግምቶች ምክንያት ነው ማለት አይደለም፡፡ ስለትዳር ጓደኞቻቸው ቤተሰቦቻቸው ዘንድ መልካም አስተሳሰብ ያላቸው ተጋቢዎችም የችግሩ ሰለባዎች የሚሆኑባቸው አጋጣሚዎች ብዙ ናቸው፡፡ በተለይ በቅርብ የተጋቡ ባለትዳሮች ከቤተሰቦቻቸውና ከአማቾቻቸው ጋር ያላቸው መልካም ግንኙነት የመፍጠር ተስፋ እንደ ጠበቁትና በቀና ስሜት እንደ አሰቡት ሳይሆን ሲቀር ሁኔታው ወደ ግጭትና አለመግባባት ያመራል። ሲያገቡ ከቤተሰቦቻቸውና ከትዳር አጋሮቻቸው ቤተሰብ ጋር እንዲኖራቸው የሚፈልጉት መልካም ግንኙነት፣ ቅርበትና መረዳዳት እንደፈለጉት ሳይሆን በመቅረቱ ያዘኑ የትዳር አጋሮች በንግግርና በድርጊት ተቃውሞቸውን ማሰማትና ማሳየት ይጀምራሉ። በዚህ ወቅት በባለትዳሮች መካከል የቃላት ጦርነት፣ የመኮራረፍና በከፍተኛ ሁኔታ የመጋጨት ዕድሎች ይበዛሉ።

የባለትዳር ቤተሰቦችም ልጃቸው በማግባቱ ምክንያት የግል ጥቅማቸው ሊቀር እንደሚችል ወይም እንደ ቀረባቸው ማሰብና ማየት ከጀመሩ የሚያሳዩትና የሚያንጸባርቁት የተለየ ጸባይ በባለትዳሮች መካከል ስምምነት እንዳይኖርና ችግር እንዲፈጠር ያደርጋል። ይህ ሲከሰት የተሳሰተ ግምትን በመልካም ድርጊትና ፍቅርን በሕይወት በማሳየት በመልካምነት ማሸነፍ ተገቢ ነው። ቀድሞ ይደርግላቸው የነበረ





የግል ጥቅም ለምን እንደ ቀረ ማሳየትና የታሰበ ልዩ የሆነ ዕቅድ ካለ በመልካም ግንኙነት በመነጋገር ማሳወቅ፣ ማስረዳትና ነገሮችን ግልጥ ማድረግ ችግሩን ለመከላከልና ለመቀነስ ጠቃሚ ነው፡፡

አንዳንድ ጊዜ ለትዳርና ለትዳር ጓደኞች ቤተሰብ እንግዳ ከሆነ አዲስ ልምምድ፣ የሌላውን አካል ቤተሰብ ባህል ካለማወቅ፣ እንዴት መቀራረብና መነጋገር እንደሚቻል ካለመገንዘብ፣ የሚወዱትንና የሚጠሉትን እንዲሁም ዋጋ የሚሰጡትን ነገር ካለማወቅና ካለመረዳት የተነሳ ከትዳር አጋር ቤተሰብ ጋር የሚፈጠር አለመግባባትና ጥላቻ ወደ ትዳር ዘልቆ በመግባት ጥንዶችን እንዳይግባቡና እንዲጋጩ ሊያደርግ ይችላል። በተቻለ መጠን ለምን እንደ ተጋጨን፣ ግጭቱን የፈጠረውን ወይም ያባባሰውን ችግርና ሊደረግ የሚገባውን ነገር ጠንቅቆ በማወቅና መፍትሔ እንዲያገኝ በመጣር እንደ ቤተሰብ ችግሮችን በሰላም ለመፍታት ጥረት ማድረግ ተገቢ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ *"ቢቻላችሁስ በእናንተ በኩል ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ።"* /ሮሜ 12፥ 18/ በማለት እንደሚናገር ለመኖር ራስን መስጠት የትዳር ብቻ ሳይሆን በማንኛውም ጊዜ ልንከተለው የሚገባ የክርስቲያናዊ ሕይወት ኃላፊነት ነው፡፡ ይህን ኃላፊነት በቅድሚያ የምንወጣበትና ለመተግበር የምንለማመድበት የመጀመሪያው ቦታ ግን የጋብቻ ሕይወታችን ነው፡፡

## 6. ከቤተሰብ ጋር በአንድ አካባቢ በመኖር የትዳር ግንኙነት ለቤተሰብ ግልጥ መሆን

አንዳንድ ጊዜ ካለን ቅርበትና ከቤተሰብ ጋር ለመለያየት ከመቸገር የተነሳ፣ በጊዜው አዲስ ተጋቢዎችና ቤተሰብ ካላቸው ኢኮኖሚያዊ ጥገኝነትና ለጊዜውም ሆነ በቋሚነት በአንድ አገር፣ ከተማ፣ ሰፈር፣ ግቢ ወይም ቤት ውስጥ አብረው በመኖር የሁለቱም ወገኖች ሕይወት፣ መውጣትና መግባት፣ ስሜትና ኑሮ ... በጣም የሚታወቅ ወይም ግልጥ ይሆናል። በተቻለ መጠን አብሮ ከጋብቻ በኋላ ከቤተሰብ ጋር አንድ ሰፈር፣ ግቢና ቤት መኖርን በማስወገድ የግል ኑሮን ከቤተሰብ ፈቀቅ ብሎ መምራት ለተጋቢዎች የትዳር ግንኙነት ጠቀሜታው ላቅ ያለ ነው። አብሮ የመኖር ግዴታ ከተፈጠረ ደግሞ በገደብ፣ በመከባበር፣ አንዱ በሌላው ኑሮ አላስፈላጊ የሆነ ጣልቃ ገብነት በሌለበትና ሁሉን የትዳር ሕይወት ግልጥ ባለማድረግ ለመኖር ጥረት ማድረግ ተገቢ ነው።

# IV. በቤተ-ዘመድ ጣልቃ ገብነት ለሚፈጠሩ ግጭቶች መፍትሔዎች

## 1. ማስተካከል፡- ትክክለኛ ባልሆነ ግምት የተበላሸ አእምሮን ማስተካከል

አስቀድሞ በተለያዩ ምክንያቶች፣ ትክክለኛ ባልሆነ መረጃና ባልተፈጸመ ተስፋ የተበላሸ አእምሮን ማስተካከል ተገቢ ነው። እንዲሁ በደፈናው ከሌሎች ሰዎች በሰማነው ወሬ ብቻ ምንም ማስረጃ ሳይኖረን የተበላሸን ህሊና ማስተካከል ችግሮችን የመፍታት የመጀመሪያው እርምጃ ሊሆን ይገባል። ይህን ማድረጋችን ነገሮች እንደ ጠበቅናቸው ሳይሆኑ በመቅረታቸው ከማፈርና ከመልካም የትዳር አጋሮቻችንና አማቾቻችን ጋር መልካም ግንኙነት ሳይኖረን በመቅረቱ ጸጸት ውስጥ ከመግባት ራሳችንን

ለመጠበቅ ይረዳናል። በመልካም አእምሮ በተቻለ መጠን ከትዳር ጓደኛችን ብሎም ከአማቾች ጋር መልካም ግንኙነት እንዲኖረን የበኩላችንን ጥረት ማድረግ አስፈላጊ ነው። እንደ ሙሴ አማት ዓይነት መልካም ምክር የሚመክሩ አማቾች እንዳሉ መዘንጋት የለብንም። *"የሙሴም አማት አለው። አንተ የምታደርገው ይህ ነገር መልካም አይደለም። ይህ ነገር ይከብድብሃልና አንተ ከአንተም ጋር ያለው ሕዝብ ትደክማላችሁ አንተ ብቻህን ልታደርገው አትችልም። አሁንም አመክርሃለሁና ቃሌን ስማ፥ እግዚአብሔርም ከአንተ ጋር ይሆናል አንተ በእግዚአብሔር ፊት ለሕዝቡ ሁን፥ ነገራቸውንም ወደ እግዚአብሔር አድርስ ሥርዓቱንም ሕጉንም አስተምራቸው፥ የሚሄዱበትን መንገድ የሚያደርጉትንም ሥራ ሁሉ አሳያቸው።"* /ዘጸ 18: 17-20/።

## 2. ማሳየት፡- የትዳር አጋርና የትዳር ግንኙነት ቀዳሚ ኃላፊነታችን እንደሆነ ማሳየት

የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ማለት ቤተሰቦቻችን ከትዳር አጋሮቻችን በበለጠና ቀዳሚ በሆነ ሁኔታ ጊዜ፣ ትኩረት፣ ዋጋና ቅድሚያ እንዲሰጣቸው የመፈለግና እኛም እድሉን የመስጠት ሂደት ነው። ስለዚህ እንዲህ ዓይነት ጥያቄ፣ ፍላጎትና እንቅስቃሴ በቤተሰብ አካባቢ ከመጀመሩ በፊትና ሲጀመር ትዳራችን ቁጥር አንድ ኃላፊነታችን መሆኑን ለሁሉም ቡድኖች በግልጥ ማሳየት አስፈላጊ ነው። ይህም ምናልባት ውሳኔ በሚጠይቁ ሁኔታዎች በጋራ በመመካከር፣ በአማቾች ፊት በእውነተኛ ፍቅር የትዳር አጋሮቻችን በማክበርና በተለያየ ጊዜ ከቃል ባለፈ በድርጊት አስፈላጊውን ነገር በአስፈላጊ ጊዜና ቦታ በማቅረብ፣ ቅድሚያ በመስጠትና በመንከባከብ አጋርነታችንን የምናሳይበት መልካም አጋጣሚ ይሆንልናል። በዚህ መንገድም መጽሐፍ ቅዱስ *"ፍቅራችሁ ያለ ግብዝነት ይሁን። ክፉውን ነገር ተጸየፉት፤ ከበጎ ነገር ጋር ተባበሩ፤ በወንድማማች መዋደድ እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ፤ እርስ በርሳችሁ ተከባበሩ፤"* /ሮሜ 12፡ 9-10/ በማለት በሚሰጠን ምክር በመኖር የትዳራችንን ጤንነትና ደስታ እንድንጠብቅ ያስችለናል።

## 3. ማስለመድ፡- ቤተሰቦቻችንን ማክበርን እንጂ በሁሉም ነገር መታዘዝ የሌለብን መሆኑን ማሳየትና ማስለመድ

ወላጆቻችን መሆናቸውንና የትዳር አጋሮቻችንን ወልደውና አሳድገው እንደ ሰጡን በመረዳት ቤተሰቦቻችንን በልባችንና በተግባር ልናከብራቸው ይገባል። *"እግዚአብሔር አምላክህ እንዳዘዘህ አባትህንና እናትህን አክብር እግዚአብሔር አምላክህ በሚሰጥህ ምድር ላይ ዕድሜህ እንዲረዝም፥ መልካምም እንዲሆንልህ።"* /ዘዳ 5፡ 16፤ ማቴ 15፡ 4/ የሚለው የእግዚአብሔር ቃል እውነትም የሚያሳየን ይህንን ነው። ወላጅን ማክበር ማለት ግን በሁሉም ነገር ወይም የሚሉንን ሁሉ ለእነርሱ በመታዘዝ የመፈጸም ግዴታ አለብን ማለት አይደለም። በወላጅና ባለትዳር በሆኑ ልጆች እንዲሁም በአማቾች መካከል የጋራ ሁለትዮሽ የሆነ መከባበር መፈጠርና መጠበቅ ይኖርበታል። ነገር ግን በሰው ፊት የግል ሚስጥሮቻችንንና መረጃዎቻችንን ሲያወጡ፣ መብቶቻችንንና ኃላፊነቶቻችንን ሲጋፉ፣ በሌሎች ሰዎች ፊት ሲያሸማቅቁን፣ ሲዘልፉንና ሲያቃልሉን ያደረጉትን በማሳየትና ያለፈውን ችግር በማስተካከል ቀጣይ ግንኙነታችን በመከባበር ላይ የተመሠረተ





እንዲሆን መጠየቅ ተገቢ ነው። በተለይ ልጅ የሆነው አካል ለቤተሰቡ በትዳር አጋሩ ላይ የሚባለውን፣ የሚደረገውንና እየተፈጠረ ያለውን አሉታዊ ተጽዕኖ በጥበብ ቃል፣ በትዕግስትና አክብሮት በተሞላው ማንነት በማሳየት ገደብ እንዲኖራቸው ማስለመድ ተገቢ ነው። ይህንን ማድረግ ስንችል ነው *"ጥበብን ማግኘት ምንኛ ከወርቅ ይሻላል! ማስተዋልን ማግኘት ከብር ይልቅ የሚመረጥ ነው።"* /ምሳሌ 16: 16/ የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥበብ አግኝተናል ማለት የሚቻለው።

## 4. ማቆም፡- በትዳር የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን ወደ ቤተሰብ አባላት ይዞ መሄድን ማቆም

በትዳር መካከል አለመግባባትና ግጭት መኖሩ አይቀሬ ነው። በግጭት ወቅት የሚፈጠረው አሉታዊ ስሜት ቀላል ላይሆን ይችላል። ነገር ግን የትዳርን ችግር ወደ ቤተሰብ አባላት ይዞ መሄድ ይበልጥ ችግሩን ሊያባብስ ይችላል። የትዳርን ችግር ይዞ መሄድ ችግሩን ሊያባብስ የሚችልበት ምክንያት ቤተሰቦቻችን ከመሆናቸው የተነሳ አድሎ ማድረጋቸው አይቀሬ ስለሚሆን ነው። አልያም አድሎ አደረጉ እንዳይባሉ በሚያደርጉት ጥረት ችግሩ የበለጠ ሌላ አቅጣጫ ሊይዝና ሊባባስ ይችላል።

አንድ የእግዚአብሔር ሰው ባንድ ወቅት በዚህ ጉዳይ ላይ ሲናገር "ቤተሰብን ስለችግሮቻችን ማማከር ቆይቶ የሚያዳልጥ ዳገት (አቀበት) ሊሆን ይችላል"[7] በማለት አስገንዝቧል። ስለዚህ ባለ ትዳሮች ራሳችንን ችለን በተረጋጋ፣ በሰከነና ትዕግስት በሞላበት ስሜት መወያየት፣ አብረን መወሰንና ችግሮቻችንን ለመፍታት ጥረት ማድረግ ተገቢ ነው። ይህ ማለት ግን ከእኛ አስቀድመው ረጅም ዘመን በትዳር የሕይወት ልምድ ውስጥ ያለፉት ወላጆቻችን ከልምምዳቸው የሚጠቅም፣ የሚያስተምር፣ የሚያስጠነቅቅና የሚመክር ነገር የላቸውም በዚያም አንጠቀምበትም ማለት አይደለም። ነገር ግን ይህንን ጠቃሚ አስተዋጾ ፍሊጋ በስሜታዊነት፣ እውቀትና ብስለት በሌለበት ሁኔታ ወደ ወላጆች ሄደን መፍትሔ ለማምጣት ጥረት ስናደርግ ችግሩን የሚያባብስና የሚያወሳስብ ሌላ ችግር ወደ ትዳራችን እንዳንጎትት በእውቀትና በጥንቃቄ ልናደርገው ይገባል። ይህንንም ማድረግ ያለብን በጣም አስገዳጅ ሁኔታ በሚፈጠርበት ጊዜ ቢሆን ይመረጣል።

## 5. ማስወገድ፡- ሚዛናዊነቱን ያልጠበቀ እርዳታና እንክብካቤን ለአንደኛው ቤተሰብ ብቻ ማድረግን ማስወገድ

በጋራ ተነጋግሮና ተስማምቶ በተገቢው መንገድ ቤተሰብን መርዳት ትዳርን ከቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ለመከላከል ይጥቅማል። ከትዳር አጋር ተደብቆ ቤተሰብን

---

[7] Focus on The Family, The first Five Years of Marriage: Tyndale House publishing Inc Carol Stream: Illinois, 2006. page 316

የመርዳት ልምድ በመጀመሪያ በትዳር ውስጥ በመሳቀቅና በድብብቆሽ የሚከናወን ተገቢ ያልሆነ የስረቆት ተግባር ሲሆን በኋላም በታወቀ ወቅት በትዳር ውስጥና በቤተሰባዊ ግንኙነት ላይ የሚያመጣው አሉታዊ ተጽዕኖ ቀላል አይደለም። የሚጠይቁትንና የሚያስፈልጋቸውን እርዳታ ከትዳር አጋሮቻችን ጋር በጋራ ተወያይተን እንደምንወስን ማሳየትና የትዳርን ግንኙነት ጤንነት መጠበቅ ይኖርብናል። ሁልጊዜ ልጆች እንደሆንን ብቻ በማሰብ አለመግባባትና አለመረዳዳት እንዳይፈጠር በግላችንና በጋራ እንደ ባለትዳር መምረጥና መወሰን እንደምንችል ማስገንዘብ ተገቢ ነው። *"ጥበብን ማግኘት ምንኛ ከወርቅ ይሻላል! ማስተዋልን ማግኘት ከብር ይልቅ የሚመረጥ ነው።"* /ምሳሌ 16: 16/።

## 6. ማጠናከር፡- ለመልካም ቤተሰባዊ ግንኙነት የሚጠይቀውን ዋጋ በመክፈል ሕብረትን ማጠናከር

ከወላጆቻችንና ከትዳር አጋሮቻችን ወላጆች ጋር እንደ ወላጅና እንደ ቤተሰብ መልካም ግንኙነት ሊኖረን ይገባል። በትዳር የተሳሰረ ቤተሰባዊነትን መፍጠርና መጠበቅ የጋራ ብርቱ ጥረትን ይጠይቃል። መልካም ቤተሰባዊነት እንዲፈጠርና መልካሙ ግንኙነት ለረጅም ዘመን ዘላቂ እንዲሆን በደስታና በሐዘን ጊዜ ፈጥኖ ምላሽ መስጠት፣ ክፉን በክፉ አለመመለስ፣ መልካም የሆነውን ማሰብ፣ በሰላም ለመኖር ጥረት ማድረግና ክፉውን በመልካም ማሸነፍ በጣም አስፈላጊ ነው። *"ደስ ከሚላቸው ጋር ደስ ይበላችሁ፥ ከሚያለቅሱም ጋር አልቅሱ። ... ለማንም ስለ ክፉ ፈንታ ክፉን አትመልሱ፤ በሰው ሁሉ ፊት መልካም የሆነውን አስቡ። ቢቻላችሁስ በእናንተ በኩል ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ። ... ክፉውን በመልካም አሸንፍ እንጂ በክፉ አትሸነፍ።"* /ሮሜ 12: 15-21/

እንደ ቤተሰብ እርስ በእርስ በመጠያየቅ፣ በበዓል ጊዜ በመገባበዝ፣ የቤተሰብ የመገናኛ ፕሮግራም በመፍጠር፣ ለእርፍት ወደ ቤተሰብ በመሄድና ቤተሰብን እኛ ወዳለንበት በማምጣት፣ በስልክ በመደዋወል፣ በጋራ በመጸለይና መንፈሳዊ ፕሮግራሞችን በመካፈል ከቤተሰብ ጋር ግንኙነትን ማጠናከር መልካም ነው። *"ለፍቅርና ለመልካምም ሥራ እንድንነቃቃ እርስ በርሳችን እንተያይ፤ በአንዳንዶችም ዘንድ ልማድ እንደ ሆነው፥ መሰብሰባችንን አንተው እርስ በርሳችን እንመካከር እንጂ፤ ይልቁንም ቀኑ ሲቀርብ እያያችሁ አብልጣችሁ ይህን አድርጉ።"* /ዕብ 10: 24-25/





## ለጥንዶች በግላቸውና በቡድን ለማጥናት የሚረዷቸው የውይይት ጥያቄዎች

## የምዕራፍ ስድስት (6)

## የውይይት ጥያቄዎች

1. ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱ ጋር ይጣበቃል የሚለው ቃል እንዴት ትረዱታላችሁ?
2. በባለትዳሮች መካከል የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ተፈጠረ የምንለው መቼና ምን ሲፈጠር ነው?
3. በባለትዳሮች መካከል በቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ምክንያት ለግጭት የሚዳርጉ መንስኤዎች ምንድን ናቸው?
4. በእናንተ የትዳር ሕይወት የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ችግር ተከስቶ ያውቃልን? ከተከሰተስ በምን መልኩ ነበር የተከሰተው? በአግባቡ ተወያዩበት፡፡
5. በእናንተ የትዳር ግንኙነት የተፈጠረ የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት የግጭት ምክንያት በሄነ ጊዜ ግጭታችሁን ባግባቡ መፍታት ቻላችሁን? ከፈታችሁት ግጭታችሁን የፈታችሁት እንዴት ነበር? ችግሩ እስካሁን ካልተፈታ ምን ማድረግ አለብን ትላላችሁ?
6. በጋራ ለጋራ ለሆነው የትዳር ግንኙነታችሁ በተረጋጋ መንፈስ፣ የትዳርን ግንኙነት ለማደስና መልካም ቤተሰብ ለመመሥረት ዛሬ ልትወስዱት የሚገባ የመፍትሔ እርምጃ ምንድን ነው? እንደሚገባ በሰፊው በመነጋገር በነገሩ ላይ ለመጸለይ በጋራ አቅዱ።

# ምዕራፍ ሰባት(7)
# ተግባቦት (ኮሙኒኬሽን)

በባለትዳሮች መካከል በጣም አስፈላጊ ከሆኑትና ልዩ ትኩረት ከሚያሻቸው ጉዳዮች አንዱ በመካከላቸው ያለው የተግባቦት ሂደት ነው:: የባለትዳሮች መግባባት፣ የተግባቦት ደረጃ፣ የተግባቦት እንቅፋቶችና አለመግባባትን ለመፍታት የሚጠቀሙበት መንገድና ዘዴ በትዳር ጉዞ ላይ ከፍተኛ ሚና አለው። በቅርብ አመታት በተጋቡ ባለትዳሮች መካከል የሚፈጠሩና ሊፈጠሩ የሚችሉ የተግባቦት ችግሮችንና መፍትሔዎችን በመጠቆም፣ በማስጠንቀቅ፣ በማስተማርና በማበረታታት የተግባቦት ደረጃዎቻቸውን ከፍ እንዲያደርጉ መርዳት የዚህ ምዕራፍ ዋና ዓላማ ነው

## 1. የተግባቦት (ኮሙኒኬሽን) ምንነት

### 1. ተግባቦት በሰዎች መካከል ግንኙነታዊ ትስስር የሚፈጥር ነው

ተግባቦት በንግግር ወይም በቃላትም ሆነ ያለቃላት በሚደረግ የሰውነት እንቅስቃሴ ራስን ለሌሎች የመግለጽ ሂደት ነው። በትዳር ውስጥ ከትዳር ጓደኛ ጋር እንዲሁም ከሌሎች ሰዎች ጋር በሰላም አብሮ ለመኖር፣ አብሮ ተግባብቶ ለመስራትና ተስማምቶ ለመጓዝ ተግባቦት (ኮሙኒኬሽን) አስፈላጊ ነው:: ተግባቦት በአጠቃላይ በሕይወት ጉዞ ውስጥ ምትክ የለሽ ሚና ይጫወታል። መጽሐፍ ቅዱስም *"በውኑ ሁለት ሰዎች ሳይስማሙ በአንድነት ይሄዳሉን?"* /አሞ 3፡ 3/ በማለት ከሰው ጋር ብቻ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ጋር እንኳን ስርዓት ያለው ሕብረት ለማድረግ ተግባቦት አስፈላጊ መሆኑን ይጠቁመናል። ያለመልካም ተግባቦት በሰዎች መካከል ግንኙነትና ትሥሥር ሊኖር አይችልም። መልካም ግንኙነት መልካም ተግባቦትን ይጠይቃል።

### 2. ተግባቦት ግልጽነትና እውነተኝነትን የሚፈልግ ነው

ተግባቦት በተሳካ መልኩ እንዲከናወን ግልጥነት በጣም ጠቃሚ ግብዓት ነው:: ግልጽ የሆነ ተግባቦት ወደ መረዳዳት ይመራል። ግልጥነትና እውነተኝነት በሌለበት መግባባት ሳይሆን ግራ መጋባት ይፈጠራል። ወደ ትዳር ዓለም ስንመጣ ጥንዶቹ የራሳችን የሆነ የቃላት ምርጫ፣ ትርጉም፣ አገላለጽና ዘይቤ ሊኖረን ይችላል። የተለያየ ዘይቤ ያለን ከመሆናችን የተነሳ ለመግባባት ሲባል ግልጽ ያልሆኑ ቃላቶችን፣ ትርጉሞችን፣ አባባሎችንና የምንጠቀምባቸውን ምሳሌዎች ለማብራራት እንገደዳለን:: *"በዚያን ጊዜ ኢየሱስ መልሶ እንዲህ አለ፦ አባት ሆይ፥ የሰማይና የምድር ጌታ፥ ይህን ከጥበበኞችና ከአስተዋዮች ሰውረህ ለሕፃናት ስለ ገለጥህላቸው አመሰግንሃለሁ፤ "* /ማቴ 11፡ 25/:: በዚህ ክፍል ውስጥ የኢየሱስ ክርስቶስ ምስጋና ምክንያቱ ጥበበኞችና አስተዋይ የሚባሉ እያሉ ነገር ግን ሰማያዊና መንፈሳዊ የሆነው የእግዚአብሔር ሃሳብ ለሕጻናት መገለጡ፣ እነርሱም አሳቡን ተረድተው ምላሽ በመስጠት መግባባት መቻላቸው ነው።





ንግግራችንን እንደሚገባ ማቅረብ አለመቻልና አድማጫችንን እንደሚገባ አለማድመጥ ይህን ባለማድረግ ምክንያት የሚፈጠር አለመግባባት እንዲያጋጥመን ያደርጋል:: እንዲህ ዓይነት ችግር ሲያጋጥመን እንደገና በተሻለ ግልጥነት ለማስረዳት ጥረት በማድረግ ወደ መግባባት ለመድረስ ተግባቦት ግልጥነትንና እውነተኝነትን የሚፈልግ ሂደት መሆኑን ማሳየት አለብን:: ተግባቦትን በዚህ መልኩ ማካሄድ ካልቻልን የምንፈልገው ጤናማ ግንኙነት ሊከናወን ካለመቻሉም ባሻገር በዚያው ልክ መግባባት አቅቶን ወደ መጋጨት እንገባለን።

### 3. ተግባቦት በሁለት ወይም ከሁለት በላይ በሆኑ ወገኖች መካከል የሚከናወን ነው

ተግባቦት በሁለትና ከሁለት በላይ በሆኑ ግለሰቦች፣ ቡድኖች ወይም ተቋማት መካከል የሚከናወን ሂደት ነው:: ተግባቦት መልዕክት ሰጭ ወይም ላኪ እና መልዕክት ተቀባይ አለው:: በትዳር ሕይወት ውስጥም ተግባቦት ሁለቱን በጋብቻ የተጣመሩ ግለሰቦች እንዲሁም ባለትዳሮችና ቤተሰቦች በነፃነት የሚያሳትፍ ሊሆን ይገባል። ተግባቦት ተካሄደ ማለት የሚቻለው በሁለቱም በኩል ግልጥ የሆነ ንግግር፣ ማስተዋል፣ ትኩረት የተሞላው መልዕክት የመለዋወጥ ሂደት ሲኖርና መልዕክቱን በተመለከተ የጋራ ግንዛቤ መፍጠር ሲቻል ነው። ተግባቦትን ሁለትዮሽ ካደረጉት ምክንያቶች መካከል አንዱ ተናጋሪ አድማጭን ማሳተፍ መቻሉ ነው። ተግባቦት ሁለትዮሽ የሆነ ያልተከፋፈለ ሙሉ ትኩረትንና ሌላው ሰው የተናገረውን ማድመጥ፣ ማሰብና መረዳትን የሚጠይቅ ነው።

**የኢየሱስ ንግግር ምሳሌ፡-** ኢየሱስ ክርስቶስ ለሕዝቡ ስለሞቱና ስለትንሳኤው በተናገረ ጊዜ እነርሱ ግን ንግግሩን በተሳሳተ መንገድ በመተርጎም ስለሕንጻ እንደተናገረ አስበው ከአርባ ስድስት ዓመት ጀምሮ ይሠራ የነበረውን ሕንጻ እንዴት በሶስት ቀን ውስጥ መልሶ ሊሠራው ይችላል? በማለት ግራ ሲገባቸው ታይቷል:: ደቀ መዛሙርቱም እንኳ ከሞት ከተነሳ በኋላ ነበር ትክክለኛ ትርጉሙ ገብቷቸው ቃሉን አምነው የተቀበሉት። *"ኢየሱስም መልሶ፦ ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት፥ በሦስት ቀንም አነሣዋለሁ አላቸው። ስለዚህ አይሁድ፦ ይህ ቤተ መቅደስ ከአርባ ስድስት ዓመት ጀምሮ ይሠራ ነበር፥ አንተስ በሦስት ቀን ታነሣዋለህን? አሉት። እርሱ ግን ስለ ሰውነቱ ቤተ መቅደስ ይል ነበር። ስለዚህ ከሙታን ከተነሣ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ይህን እንደ ተናገረ አሰቡና መጽሐፍንና ኢየሱስ የተናገረውን ቃል አመኑ።"* /ዮሐ 2፡ 19/

ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ በወንጌላት ውስጥ የሰጣቸውን ማስጠንቀቂያም ደቀ መዛሙርቱ ሊረዱት አልቻሉም ነበር:: *"እርሱም፦ ተጠንቀቁ፤ ከፈሪሳውያንና ከሄሮድስ እርሾ ተጠበቁ ብሎ አዘዛቸው። እርስ በርሳቸውም። እንጀራ ስለሌለን ይሆናል ብለው ተነጋገሩ። ኢየሱስም አውቆ እንዲህ አላቸው፦ እንጀራ ስለሌላችሁ ስለ ምን ትነጋገራላችሁ? ገና አልተመለከታችሁምን? አላስተዋላችሁምን? ልባችሁስ ደንዝዞአልን? ዓይን ሳላችሁ አታዩምን? ጆሮስ ሳላችሁ አትሰሙምን? ትዝስ አይላችሁምን?"* /ማር 8፡ 15 -18/:: ኢየሱስ ክርስቶስ የሕይወት እንጀራ ስለመሆኑ በተናገረ ጊዜም ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በትርጉም መግባባት አቅቷቸው

እንደነበር እንዲያውም ንግግሩ አስጨናቂ እንደሆነ እርስ በእርሳቸው ሲንሾከሾኩ የነበረ መሆኑን *"... ከደቀ መዛሙርቱም ብዙዎች በሰሙ ጊዜ። ይህ የሚያስጨንቅ ንግግር ነው፤ ማን ሊሰማው ይችላል?።" /ዮሐ 6፥ 51-60/* ከሚለው ክፍል መገንዘብ እንችላለን።።

## II. ከተግባቦት (ኮሙኒኬሽን) ጋር ተያይዘው ሊፈጠሩ የሚችሉ የግጭት መንስኤዎች

ጤነኛና ደስተኛ ትዳር ያላቸው ባለትዳሮች ከሌሎች የሚለዩበት አንዱ ምክንያት ደስተኝነታቸው ከመልካም ተግባቦት የተገኘ መሆኑ ነው። የተግባቦት ጠንቆችን በመረዳት የተግባቦት ደረጃችንን ከፍ ማድረግ የትዳራችንን ጤንነትና ደስታ ለመጠበቅ ይረዳናል። ብዙ ጊዜ በባለትዳሮች መካከል ሊፈጠሩ የሚችሉ የተግባቦት ችግሮች ከትዳር ዘመናችን ጋር ይያያዛሉ። በቅርብ በተጋቡ ባለትዳሮች መካከል ሊፈጠሩ የሚችሉ የተግባቦት ችግሮችን መመልከት በተግባቦት ውስጥ እንቅፋት ከሚሆኑ ነገሮች ለመጠንቀቅ፣ የተግባቦትን ሂደት ለማሻሻልና የተግባቦት ደረጃን ከፍ ለማድረግ ይጠቅማል። የተግባቦትን ጥራትና ስኬታማነት ለማሳደግ በመጀመሪያዎቹ አስር የጋብቻ አመታት ክልል ውስጥ የሚገኙ ባለትዳሮች የሚከተሉትን ከተግባቦት ጋር በተያያዘ ለግጭት ምክንያት የሚሆኑ ነገሮች መረዳት ይጠቅማቸዋል፡-

### 1. የተግባቦት መልዕክት የተዋቀረባቸውን ሶስት ነገሮችን እንደሚገባ አለማወቅ

አንድ እንዲተላለፍ የምንፈልገው መልዕክት ከሶስት ነገሮች መሠራቱን መረዳት አስፈላጊ ነው። ይህን ባለመረዳት መልዕክታችን እንደሚገባ ተላለፈ ሲባል ሳይተላለፍ፣ ያልተፈለገ ትርጉም ሲይዝና ከሌሎች ሰዎች ጋር ሲያጋጨን ይታያል። የምናስተላልፈው የመልዕክት ይዘት /Content/ **7%** ነው። መልዕክቱን ለማስተላለፍ የምንጠቀመው የድምጽ ከፍና ዝቅ ማለት እንዲሁም መወፈርና መቅጠን /Tone/ **38%** መሆኑን መረዳት ጠቃሚ ነው። ሌላው በንግግር የማይገለጽ፣ የሰውነት እንቅስቃሴ /Non-Verbal/ **55%** በመሆን ከፍተኛውን ቁጥር እንደያዘ መረዳት እንችላለን።[8]

ድምጽ የሚያስተላልፈው መልዕክት ያላሰብነውን ወይም ያልተናገርነውን መልዕክት ሊሆንና ከሰዎች ጋር ወደ አልተፈለገ ግጭት ሊያስገባን ይችላል። ዝቅ ባለ ድምጽ ሊነገር የሚገባው ሞቅ ባለ ድምፅ ሲነገር የሚሰጠው መልዕክት ምናልባት የቁጣና የንዴት ወይም ነገሩ አሳሳቢነት ያለው መሆኑን የሚያሳይና ሌላ ያልታሰበን መልዕክት የሚያስተላልፍ ሊሆን ይችላል። አንዳንድ ጊዜ ከባለቤቴ ጋር ስንነጋገር ድምጼን ከፍ አድርጌ በምናገርበት ወቅት ይታወቅሃል ድምጽህ እኮ ከተለመደው ለየት ይላል ትለኛለች፡፡ አንዳንዴም ትንሽ ጊዜ ቆይቼ እኔው እራሴ የድምጼ ከፍ ማለት የሰጣትን ትርጉም በማሰብ "ድምጼ ትክክል አልነበረም!" በማለት ይቅርታ እጠይቃለሁ።

[8] Wright H. Norman: communication key to your marriage page 99, 100





ይህን ለምሳሌ ለማንሳት የሞከርኩት ከንግግራችን ይዘት ይልቅ ድምጻችን ከፍተኛ የሆነ መልዕክትን የማስተላለፍ አቅም እንዳለው ለማስገንዘብና ድምጻችንን ባለመቆጣጠር የተዛቡ መልዕክቶችንና የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን ለመቀነስ እንዲቻል ለማሳየት ነው።

ከፍተኛውን ቁጥር የያዘ መልዕክት የሚፈጠርበት ሌላው የመልዕክት ቅብብሎሽ ሂደት የአካል ወይም የሰውነት እንቅስቃሴ ነው። ከመልዕክታችን ይዘትና ድምጽ ጋር ተደምሮ የሰውነታችን እንቅስቃሴ የሚያስተላልፈው መልዕክት ከፍተኛውን ቦታ እንደሚይዝ መረዳት ይቻላል። የፊት መኮሳተርና ሳቅ፣ መወራጨትና አለመንቀሳቀስ፣ የደስታና የሐዘን ፊት፣ እጅን ኪስ ውስጥ ከቶና ሳይከቱ መናገር፣ ተቀምጦና ቁሞ መናገርና ሌሎችም የሰውነት እንቅስቃሴዎች እያንዳንዳቸው እንደ አካባቢው፣ እንደ ቤተሰብ ልምድና እንደ ባለትዳሮች ሁኔታ የተለያዩ መልዕክቶች ሊኖራቸውና ሊያስተላልፉ እንደሚችሉ መገንዘብ ይኖርብናል። የሰውነት እንቅስቃሴያችን ላለመግባባት መንስኤ ሊሆን፣ አለመግባትን ሊያባብስና ከፍተኛ ግጭት ሊፈጥር ሚችል እንደሆነ ማጤን ተገቢ ነው።

### 2. ምቹ ጊዜ፣ ቦታና ሁኔታን አለመምረጥ

በባለትዳሮች መካከል ከኮሙኒኬሽን ጋር በተያየዘ ከሚፈጠረው ችግር አንዱ ምቹ ጊዜን አለመምረጥ ነው። የትኛው ጊዜ ምቹ ነው? በየትኛው ጊዜ ማለትም በማለዳ፣ በቀን፣ በማታ... መወያየት አለብን የሚለውን ጥያቄ በመመለስ አመች የሆነውን ምቹ የተግባቦት ጊዜ መምረጥ ለተሳካ የተግባቦት ሂደት የሚኖረው አስተዋጾ ከፍተኛ ነው፡፡ እንደ አርስተ ጉዳዩ አስፈላጊነት፣ አንገብጋቢነትና በጊዜው የትዳር አጋር እያከናወነው ያለውን ሁኔታ በመቃኘት ምቹ የሆነ የተግባቦት ጊዜ መምረጥ አስፈላጊ ነው። **90%** በተግባቦት መካከል የሚፈጠሩ ችግሮች ዋና ምክንያት ትክክለኛ ያልሆነን ጊዜ፣ ቦታና ሁኔታ ለተግባቦት ክንውን ከመምረጥ ጋር የተያያዘ እንደሆነ ጥናቶች ይጠቁማሉ።[9]

ትክክለኛ ጊዜ አለመምረጥ ችግር እንደሚፈጥር ሁሉ ምቹ የሆነ ቦታ አለመምረጥም ሌላው ችግር ፈጣሪ ጉዳይ ነው። በልጆችና በሰዎች ፊት፣ መኝታ ቤትና አልጋ ላይ፣ በሥራ ቦታ፣ ከቤት ውጭ ወጣ ብሎ የርዕስ ጉዳዩን አስፈላጊነትና አንገብጋቢነት በመለየት ለተግባቦት ምቹ ቦታ መምረጥ አስፈላጊ ነው። ምቾትና ነጻነት የሚሰጥ ቦታ ባለመምረጣቸው በቀላሉ መግባባት የሚችሉበት ጉዳይ ግጭትና የከፋ ግንኙነትን የሚያሻክር ሁኔታ በጥንዶቹ መካከል እንዲፈጠር ያደርጋል።

ለመልካም ተግባቦት አስተዋጾ ከሚያደርጉ ጉዳዮች መካከል ሌላው ትክክለኛና ምቹ ሁኔታዎችን መምረጥ ነው። ባለትዳሮች መልካም ግንኙነት እንዲኖራቸው ለሚነጋገሩበት ርዕሰ ጉዳይ ምቹ ሁኔታን የመምረጥን አስፈላጊነት መረዳት አለባቸው። ያሉበትን ሁኔታ፣ በሐዘን፣ በደስታና በንዴት ስሜት፣ በውጥረትና በመረጋጋት፣ በሞትና

[9] Chapman, Gary. Marriage Works helping couples God's way, publishing light university: Forest, Virginia, 2011.

በወሊድ፣ በሴቶች የወር አበባ መምጣት ወቅት፣ በተለያዩ አደጋ ጊዜዎች፣ የተለያዩ እንግዳ ስሜቶች በተፈጠሩ ጊዜ ሁኔታዎችን አለመቃኘትና እንደ ሁኔታው ርዕሰ ጉዳዮችን መርጦ አለማንሳት ላለመግባባትና ለግጭት ሊዳርግ ይችላል። እንደ ባለትዳር ባል የሚስትን ሚስት ደግሞ የባልን ሁኔታ መረዳት አለመግባባትንና ግጭትን ይቀንሳል።

**እርስ በእርስ መረዳዳት ይጠብቃል ከተለያየ ጉዳት !**

## 3. ስሜትን በነፃነት መግለጽ የማይቻልበት የተግባቦት ደረጃ ላይ መሆን

በትዳር ግንኙነታችን ያለ የተግባቦት ደረጃ ዝቅተኛና ነፃነት የሌለው ግንኙነት መሆን በቅርብ ወደ ትዳር በገቡ ተጋቢዎች መካከል ከሚፈጠሩ ችግሮች መካከል አንዱ ነው። በእርግጥ የተግባቦት ደረጃ በየጊዜው እያደገ የሚሄድ ቢሆንም የእድገቱ ፍጥነት ግን በጥንዶቹ ማንነት፣ ትውውቅ፣ ግንኙነት፣ ብስለትና ግልጥነት ይወሰናል። በቅርብ የተጋቡ ባለትዳሮች በመካከላቸው ሊኖራቸውና ሊያሳድጉት የሚገባ የተግባቦት ደረጃን መለየትና መረዳት መቻላቸው ተገቢና አስፈላጊ ነው።

የተግባቦትን ሂደት ለማሳደግ የሚጠቅሙ አምስት የተለያዩ የተግባቦት ደረጃዎች እንዳሉ ይታመናል እነርሱንም እንደሚከተለው እንቃኛቸዋለን:-[10]

***የመጀመሪያው ደረጃ እጅግ በጣም ዝቅተኛ የሆነን ቅርበት*** የሚያሳይ የተግባቦት ደረጃ ነው። ይህ የተግባቦት ደረጃ አንዳንድ ሐቆችን፣ ታሪኮችን፣ መረጃዎችን በማብራራት፣ ሰላምታን፣ ዜናን፣ የጋዜጣን፣ የመጽሔትን...አሳብና መረጃን በመለዋወጥ የሚገለጽ የተግባቦትደረጃ ነው። ከዚህ ያለፈ በግልጽ መነጋገርና መግባባት የማይችሉ ባለትዳሮች እጅግ በጣም ዝቅተኛ የሆነ ቅርበት ያላቸው ባለትዳሮች ናቸው። ዝቅተኛ ቅርበት ያላቸው ባለትዳሮች ከዚህ እጅግ በጣም ዝቅተኛ ከሆነ የተግባቦት ደረጃ ወደሚቀጥለው ደረጃ ተግባቦታቸውን ለማሳደግ ከፍተኛ ጥረት ሊያደርጉ ያስፈልጋል።

ሌላው ***ሁለተኛው ደረጃ ዝቅተኛ የሆነን ቅርበት*** የሚያሳይ የተግባቦት ደረጃ ነው። ይህ የተግባቦት ደረጃ በባለትዳሮች መካከል ስለሌሎች ሰዎች ሃሳብንና አስተያየቶችን በመለዋወጥ የሚደረግ የተግባቦት ደረጃ ነው። ሁለተኛው ደረጃ ዝቅተኛ የሆነ ቅርበት ያላቸውና ስለሌሎች ሰዎች እንጂ ስለራሳቸው ለመነጋገር ግልጥነትና ነጻነት የሌላቸው ጥንዶች ያሉበትን የተግባቦት ሂደት የሚያሳይ ነው። በዚህ ደረጃ ላይ ያሉ ጥንዶች እርስ በርሳቸው ስለራሳቸው መነጋገር የማይችሉ፣ ከተነጋገሩ የማይግባቡና የሚጋጩ ሊሆኑ ይችላሉ። በትዳር የተጣመሩ ጥንዶች ይህን ደረጃ የዘለለ ተግባቦት ሊኖራቸው ግድ ይላል።

***ሶስተኛው ደረጃ መካከለኛ የሆነ መቀራረብ*** ያለበት የተግባቦት ደረጃ ነው። በዚህ ወቅት ባለትዳሮች በሌሎች ነገሮች ላይ የራሳቸውን ሃሳብ፣ አስተያየት፣ እምነት፣ እይታ በማቅረብ የሚነጋገሩበትና መረጃ የሚከፋፈሉበት ደረጃ ነው። ከሁለተኛው ደረጃ የሚሻለው ጥንዶቹ ስለሌሎች ሰዎችና ጉዳዮች ከመናገር ባለፈ የራሳቸውን አሳብ፣ አስተያየትና እምነት የሚገልጹበት ሁኔታ ላይ መድረሳቸው ነው። ጥንዶች እንደ ባለትዳር ግንኙነታቸውን ወደ ጠለቀ የተግባቦት ደረጃ በመቀራረብና በመግባባት ሊያሳድጉት ይገባቸዋል።

***አራተኛው ደረጃ ከፍተኛ የሆነ መቀራረብ*** ያለበት የተግባቦት ደረጃ ነው። ባለትዳሮች በተወሰነ መጠን ስለራሳቸው ግልጽ የሚሆኑበትና ስለእያንዳንዳቸው የግል ያለፈና የአሁን ታሪክ በመወያየት የሚቀራረቡበት የተግባቦት ደረጃ ነው። ካሁን በፊት የነበራቸውና ያላቸው ልምምድ ምን ይመስል እንደ ነበር የራሳቸውን የግል መረጃና ስሜት አንዱ ለሌላው ማካፈል የሚጀምሩበት ወቅት ነው። ይህ ደረጃ ከፍተኛ የሆነ መቀራረብ ያለበት የተግባቦት ደረጃ ቢሆንም ባልና ሚስት እንደ ባለትዳር በመካከላቸው ያለው የተግባቦት ሂደት ወደ ሚቀጥለው ደረጃ እንዲያድግ ጥረት ሊያደርጉ ይገባል።

***አምስተኛውና የመጨረሻው ደረጃ እጅግ ከፍተኛ የሆነ መቀራረብ*** የሚታይበት የተግባቦት ደረጃ ነው። በዚህ የተግባቦት ደረጃ ባለትዳሮች ማንነታቸውን በነፃነት የሚገልጹበትና በግል ስለሚሰማቸው የውስጥ አሳብ ያለምንም ፍርሃት መናገር የሚችሉበት ነፃነት የሚንጸባረቅበት ደረጃ ነው። በዚህ ደረጃ ጥንዶቹ ከአእምሮአቸው ከመናገር የውስጥ ስሜታቸውን ወደ መናገር የሚሸጋገሩበትና የልብ ሰዎች የሚሆኑበት ደረጃ ነው። ባለትዳሮች ለግልም ሆነ ለትዳራቸው ያሰቡትንና ያቀዱትን እንዲሁ በነፃነትና በግልጥነት ወደ መነጋገር የሚደርሱበት ደረጃ ነው። ይህን በመገንዘብ በየጊዜው የተግባቦት ክህሎት ከፍ እንዲል የሚቻለውን ዋጋ በመክፈል መቀራረብ አስፈላጊ ነው ።

በቅርብ የተጋባን ጥንዶች የተግባቦት ደረጃችን የት ላይ እንዳለ:- ምን ያክል በግልጥነትና በነፃነት እየተግባባን ነው? የተግባቦት ደረጃችን ወደ ከፍተኛና ወደ ላቀ ደረጃ እንዳይደረስ እንቅፋት የሆነብን ምንድን ነው? ለመልካም ተግባቦትና የበለጠ ለመቀራረብ ምን ጥረት እያደርግን ነው? የመሳሰሉ ጥያቄዎችን በመጠየቅና እርስ በእርስ ያለምንም ፍርሃት የውስጥ ስሜትን በመግለጥ የልብ ሰው ወደ መሆን ለማደግ ማሰብ፣ ለመሻሻል ጥረት ማድረግና በየጊዜው የተግባቦት ክህሎታችንን ከፍ ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡ ይህ ለጤነኛና ደስተኛ ትዳርና ቤተሰብ መፈጠር መሠረታዊ ምክንያት ነውና!!

[10] David M. Ephraim. http://www.touchoffaith.org/family_ministry/communication/five_levels.Htm: The Five Levels of Communications accessed Feb.12, 2014.

## 4. ጥሩ አድማጭ አለመሆን

ለመልካም ተግባቦት አንደኛው ምትክ የለሽ አስፈላጊ ነገር ጥሩ አድማጭ መሆን ነው። ያዕቆብ በመልክቱ እንዲህ ይላል፡-*"ስለዚህ፥ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፥ ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ ለመናገርም የዘገየ ለቍጣም የዘገየ ይሁን፤"* /ያዕ 1፡ 19/፡፡ ነገር ግን ብዙ ሰዎች ጥሩ አድማጭ ለመሆን ትኩረት ሲሰጡ አይታዩም፡፡ ጥሩ አድማጭ እንዳንሆን ያደረጉን የተለያዩ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ። እነዚህን የጥሩ አድማጭነት እነቅፋቶች ራሳችንን በመመዘን ለይተን ማግኘትና ለማስወገድ ጥረት ማድረግ ይኖርብናል፡፡

ከጥሩ አድማጭነት እንቅፋቶች መካከል አንዱ ሳይሰሙ ለመናገር መዘጋጀትና አስደንጋጭ ቃላትን መጠቀም ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ሳይሰማ መልስ የሚሰጥን ሰው *"ሳይሰማ ነገርን በሚመልስ ስንፍናና እፍረት ይሆንበታል።"* /ምሳሌ 18፡ 13/ በሚለው የጥበብ ምክሩ ሳይሰሙ መናገር ወይም መልስ መስጠት የጥሩ አድማጭነት እንቅፋት ብቻ ሳይሆን ስንፍናና በኋላ የሚያሳፍር መሆኑንም ግልጥ ያደርጋል፡፡ ሌላው በግል ያለን አስተሳሰብና የንግግር ዘይቤ ላይ ብቻ በመመርኮዝ ለሌላው አካል ንግግር እድል ፈንታ አለመስጠት ጥሩ አድማጭ ያለመሆን መገለጫ ነው። ከእነዚህም በተጨማሪ የተናጋሪው ወይም የአድማጩ ሰው ጾታ፣ ዘር፣ ዕድሜ፣ ያለፈ ታሪክና ልምምድ ጥሩ አድማጭ ለመሆን እንቅፋትና ምቾት የማይሰጥ ሊሆንበት ይችላል።[11]

በባልና በሚስት የተግባቦት ሂደት ውስጥ የጾታ ልዩነት አንዱ የጥሩ አድማጭነት እንቅፋት ሊሆን ይችላል፡፡ሴቶች በክፉና በመልካም ቃላት በንግግር መካከል መልስ የመስጠት፣ ወንዶች አንገት በመነቅነቅ ተቃውሞን ወይም ምላሽን የማሳየትና ብዙ ጊዜ በንግግር መካከል አቋርጦ እርማት የመስጠት አጉል ልማዳቸው የጥሩ አድማጭነት ጠንቅ ሊሆንባቸው ይችላል። ሌላው በባለትዳሮች መካከል የሚፈጠሩ ውስጣዊ የሆኑ የስሜት ትግሎች ማለትም ፍርሃት ሲኖርብን፣ ጭንቀት ሲበዛ፣ ስጋት ሲጨምርና በውስጣችን በሆነ ምክንያት ጥርጣሬ ሲሞላ የማዳመጥ ፍላጎታችንና ችሎታችን ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያመጣል።[12]

መጥፎ ጊዜ ማለትም ትክክለኛ ጊዜን አለመምረጥ ለምሳሌ አካላዊ ድካም፣ የሐዘን ወይም ከፍተኛ የሆነ የደስታ ስሜት በሚፈጠርበት ወቅት የጥሩ አድማጭነት ትኩረት እንዳይኖር ሊያደርግ ይችላል። ሌላው ሳይጠቀስ የማይቀረው ከራሳቸው ፍላጎት፣ እይታ፣ እሴትና እምነት አንጻር ብቻ የሚሰሙትን ነገር በመምረጥ የሌላውን አካል ፍላጎት፣ እይታና አስተያየት ለመስማት አለመፈለግ የጥሩ አድማጭነት እንቅፋት ሊሆን ይችላል።[13]

---

[11] Wright H. Norman: communication key to your marriage page 103-110

[12] Wright H. Norman: communication key to your marriage page 103-110

[13] Wright H. Norman: communication key to your marriage page 103-110



የግጭት መንስኤዎችና መፍትሔዎቻቸው በጋብቻ ውስጥ!

## 5. እውነትን በፍቅር አለመናገር

በኮሙኒኬሽን እረገድ በቅርብ በተጋቡ ጥንዶች መካከል ከሚፈጠረውና ሊፈጠር ከሚችለው ችግር አንዱ እውነትን አለመናገር ነው። እውነትን ብናገርና እውነቱ ቢገለጥ በትዳር ጓደኛየ ላይ ጥሩ ያልሆነ ስሜት ሊፈጠር ይችላል የሚል አሳብ በሚኖርበት ጊዜ እውነትን የመደበቅ ተግባር በባለ ትዳሮች መካከል ይከሰታል፡፡ ነገር ግን ይህ ዓይነቱ ተግባር ትክክለኛነቱ ባልተረጋገጠ ግምት እውነትን በመሰወር የግብዝነት ተግባቦት የማድረግ ጥረት ነው።

ሌላው በአንዳንድ ጥንዶች ዘንድ የሚታየው እንደሚገባ ከመተዋወቅ የተነሳ እውነቱ ቢገለጥ ሊፈጠር የሚችልን አለመግባባትና ግጭት በመፍራት እውነትን ደብቆ በማመቻመች ለመግባባት መሞከር ነው። ሁለቱም ጤንነት የጎደላቸውና እውነተኛ ያልሆኑ የባለትዳሮች የመልካም ግንኙነት እንቅፋቶች ናቸው። ውሎ አድሮ እውነቱ በተለያየ መንገድ ገሃድ ሲወጣ እውነትን በመደበቅ ይመጣል ተብሎ የታሰበው መግባባት በመረረ አለመግባባት ይተካል፡፡ ከዚህም ባለፈ ከስተቱ ወደፊት ለሚደረገው የተግባቦት ሂደት መሠረታዊ እንቅፋት ይሆናል፡፡ ስለዚህ እንደዚህ ዓይነት ልምድ፣ ባሕርይና አስተሳሰብ ያላቸው ባለትዳሮች በጊዜ ራሳቸውን የማሻሻል ጥረት ሊያደርጉ ይገባል፡፡

እውነትን መናገር ዋጋ ሊያስከፍል ይችላል። እውነትን መናገር ለጊዜው አመኔታ ሊያሳጣ ይችላል። ኢየሱስ ክርስቶስ ስለራሱ እውነትን መናገሩ በአድማጮቹ ዘንድ ሊፈጥርበት የሚችለውን ችግር እንዲህ ሲል ገልጿል፡- *"እኔ ግን እውነትን የምናገር ስለ ሆንሁ አታምኑኝም።"* /ዮሐ 8፡ 45/ *"ስለዚህ ውሸትን አስወግዳችሁ፥ እርስ በርሳችን ብልቶች ሆነናልና እያንዳንዳችሁ ከባልንጀሮቻችሁ ጋር እውነትን ተነጋገሩ።"* /ኤፌ 4፡ 25/፡፡ በባህላችን እውነትን በግልጥነት ከመናገር ይልቅ ሰላም ሳይሆን ሰላም ነው፣ ትክክል ሳይሆን ትክክል ነው ማለትና ተቃራኒውን ምላሽ ግን ጉዳዩ ለማይመለከተው ሌላ ወገን መናገር ወይንም ወደ ሐሜት መግባት የተለመደ ነው። እንዲህ ዓይነቱን ልምምድ ባህል በማድረግ ሰዎች በሚኖሩበት በዚህ ዘመን እውነትን መናገርና መስማት ከባድና አስቸጋሪ ቢሆን ምንም የሚያስገርም ነገር አይደለም።

እውነትን በመነጋገር በአጭር ሊቀጭ የሚችል ችግር ሰነባብቶ ለቤተሰብ መበተን ምክንያት የሚሆን ከፍተኛ የትዳር ችግርን ያስከትላል። የተሰወረ እውነት አንድ ቀን መገለጡ አይቀሬ ነው። እውነት በተገለጠ ጊዜ አንዱን አካል ነፃ ሲያወጣ ሌላውን አካል ሊያጋልጥና ሊያዳልጥ ይችላል። እውነትን ባለመነጋገር ከትዳር ጓደኛችን ጋር የሚኖረንን የተግባቦት እድገት ዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንዲቆም ማድረግ የለብንም፡፡ ይህ እንዲሆን ከፈቀድን በትዳር ውስጥ ለሚፈጠር ከፍተኛ አለመግባባትና ግጭት መንስኤ ሊሆን ስለሚችል ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው። *"እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል አላቸው"* /ዮሐ 8፡ 32/

እውነትን አለመነጋገር ብቻ ሳይሆን እውነትን የምንናገርበት መንፈስ ሌላው የአለመግባባትና የግጭት መንስኤ ነው። እውነት ብቻውን በአንዳንድ ሰዎች ዘንድ ሕመም ሊፈጥር ይችላል፡፡ ነገር ግን ፍቅርና ምህረት ቢታከልበት የሚፈጠረውን ሕመም ይቀንሰዋል። እውነትን በፍቅር፣ በምህረትና በትዕግስት መነጋገር፣ መያዝና መግባባት አስፈላጊ ነው። ሐዋሪያው ጳውሎስ ለኤፌሶን ክርስቲያኖች *"ነገር ግን እውነትን በፍቅር እየያዝን በነገር ሁሉ ወደ እርሱ ራስ ወደሚሆን ወደ ክርስቶስ እንደግ፤"* /ኤፌ 4፡ 15/ በማለት የመከራቸው እውነትን በፍቅር የመግለጥን አስፈላጊነት እንዲረዱ በመፈለጉ ነበር፡፡

## 6. ቴክኖሎጅን ተጠቅሞ ለመግባባት ጥረት በሚደረግበት ወቅት እንደታሰበው ሳይሆን ሲቀር

በአሁኑ ዘመን የመረጃና የኮሙኒኬሽን መንገዶች በብዛት መገኘታቸውና የመለወጥ ፍጥነታቸው ከመቼውም ዘመን በበለጠ የጎላ ነው፡፡ እንደዚህ ዘመን ብዙ ሰዎች የቴክኖሎጅ ተጠቃሚ የሆኑበት ጊዜ የለም። ቴክኖሎጅ ፈጣን በሆነ መንገድ ለመገናኘት፣ መረጃና መልዕክት ለመለዋወጥ ከፍተኛ ጠቀሜታ እየሰጠ ይገኛል። ቴክኖሎጅ አፈራሽ የሆነውን የመገናኛ ዘዴ ተጠቅሞ አሳብን መለዋወጥ ጠቀሜታው አጠያያቂ አይደለም ነገር ግን ማንኛውንም ዘዴ ተጠቅመው ለመገናኘትና ለመግባባት የሚሞክሩ ጥንዶች በልባቸው ውስጥ ያለውን የልብን ቅንነት መግለጽ ባለመቻል የሚፈጠር አለመግባባት በለውጡ ሂደት ውስጥም በመታየት ላይ ያለ ችግር ነው።

ቴክኖሎጅ አፈራሽ የሆኑ የመገናኛ ዘዴዎችንና ማሕበራዊ ድረ ገጾችን ተጠቅሞ ግንኙነት ለመፍጠርና ለመግባባት በሚደረገው ሙከራ ቴክኖሎጅው የሚጠቀመውን የተለየ ቋንቋ ለምሳሌ የእንጊሊዘኛን የቋንቋ ተጠቃሚው በሚገባ ባለማወቁ ምክንያት የሚገጥመው የቋንቋ ውስንነት በባልና ሚስት መካከል የተግባቦት እንቅፋት ይሆናል፡፡ ይህ የቴክኖሎጂውን ቋንቋ ያለማወቅ የቋንቋ ውስንነት የሚፈጥረው የትርጉምና የመረዳት ልዩነት ባለትዳሮች እንዳይግባቡ ምክንያት ሊሆን ብሎም ከፍተኛ ለሆነ

> **ግምታችን ሊሳሳት ይችላልና ምክንያቱን ጠይቀን ባልተረዳነው ሁኔታ ላይ ሌላውን አካል ፈጥኖ ከማኩረፍ፣ ከመቆጣትና ከመፍረድ እንጠበቅ!**

ግጭት መንስኤ ሊሆን ይችላል። በስልክ በመነጋገር፣ በስልክ የጽሁፍ መልዕክት በመጻጻፍ፣ ኢሜል በመደራረግና ማሕበራዊ ድረ ገጽ በመጠቀም አሳብን ለመግለጥና መልዕክት ለመለዋወጥ በሚደረገው ሂደት አንዳንድ ጊዜ የሰው ሥራ ፍጹም አይደለምና በኔት-ዎርክ ላይ በሚፈጠሩ የመልዕክት ቅብብሎሽ እንቅፋቶች፣ በቂ የሆነ አገልግሎት የአለማግኘት ወይም ፈጽሞ አገልግሎት ባለመኖሩ ምክንያት የተላከው ፈጽሞ ላይደርስ ወይም መልእክቱ በከፊል ሊሸራረፍ ይችላል፡፡ ይህ ሁኔታ ተከስቶ የተላከው ፈጽሞ



የግጭት መንስኤዎችና መፍትሔዎቻቸው በጋብቻ ውስጥ!

ሳይደርስ ሲቀር ወይም ከተፈለገው ወቅት ዘግይቶ ሲደርስ፣ የተላከ መስሎን ሳይላክ ሲቀር ወይም ስልክ የጠራ እየመሰለን ሌላው አካል ላይ ጥሪው ሳይደርስ ሲቀር እንዲሁም በተፈጠረ ስህተት ምክንያት ወዳልተፈለገ ቦታ መልዕክቱ ሲላክ በባልና በሚስት መካከል የተዛባ ግንዛቤ፣ ጥርጣሬ፣ አለመተማመን፣ አለመግባባትና ግጭት ሊፈጠር ይችላል።

ሌላው ደግሞ በተለያዩ ምክንያቶች የምንጠቀምባቸው የስልክና የማሕበራዊ ድረ ገጾች በየጊዜው ተጠቃሚ አለመሆን ሌላው ተጠቃሽ የግጭት መንስኤ ነው። የሚጠቀሙበትን ስልክ ድምጽ በመቀነሳቸውና በማጥፋታቸው ከዚያም ለረጅም ሰዓት ስልክና ኢሜል መመልከት ባለመቻላቸው ምክንያት አንዱ የትዳር አካል ግጭት ሊፈጠር ይችላል። በሥራ፣ በስብሰባ፣ ከሌሎች ሰዎች ጋር በመሆንና በማይመች ሁኔታ ውስጥ በመገኘት የስልክ ጥሪና መልዕክት አለመመለስ በሌላው አካል ላይ ቁጣ፣ የስሜት መለወጥና የማኩረፍ ሁኔታ ሊፈጠርና ከዚያም ለግጭት ምክንያት ሊሆን ይችላል። እነዚህን የግጭት መንስኤዎችን ለመረዳት ጥረት ማድረግ ያለብን የግጭት ምክንያቶችን ለመቀነስና እርስ በርስ ለመረዳዳት እንድንችል እንጂ ለግጭት ፈቃድ ለመስጠት አይደለም። ይህ ክስተት ሲያጋጥመን ቶሎ ብለን በቁጣና በብስጭት የትዳር አጋርን ከማነጋገር ይልቅ በእርጋታ ለምን ሁኔታው እንደተፈጠረ በመጠየቅ ምክንያቱን ለማወቅ ጥረት ማድረግ ተገቢ ነው። ከመቆጣትና ከመፍረድ በፊት ምክንያቱን ማወቅ ከፍርድና ከግጭት ይጠብቃል። ካልተመለሰው የስልክ ጥሪና መልዕክት ይልቅ የትዳር አጋር ይበልጣልና አንዱ ለሌላው በማሰብ ደህንነትን በፍቅር መጠያየቅና ቁጣን ማብረድ ብስለትና መንፈሳዊነትም ነው።

## III. በተግባቦት (ኮሙኒኬሽን) ላይ ለሚፈጠሩ የግጭት መንስኤዎች መፍትሔዎች

ለጤነኛና ለደስተኛ ትዳር መልካም ተግባቦት የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው። መልካም ተግባቦት በሌለበት አብሮ መኖር፣ መስራት፣ መቀመጥ፣ ረጅም ጉዞ መጓዝና ሰላምና ነፃነት የተሞላው ስሜት ሊኖር አይችልም። በመልካም ተግባቦት ጠንካራ፣ ቀጥተኛና ግልጥነት የሞላበት ግንኙነት እንዲኖረን ማድረግ እንችላለን፡፡ በየጊዜው የተግባቦትን ክህሎት በማሳደግና አለመግባባትንና ግጭትን በመቀነስ በጋራ መኖር አስፈላጊ ነው። ከዚህ በመቀጠል የምንዳስሳቸው እውነቶች የተግባቦትን ክህሎት ለማሳደግና የተሳካ ግንኙነት በትዳር ውስጥ እንዲኖረን ለማድረግ ከፍተኛ ገንቢ ሚና ይኖራቸዋል፡-

### 1. *መገንዘብ፡- መልካም ተግባቦት የጤነኛና የደስተኛ ባለትዳሮች መለያ እንደሆነ መገንዘብ*

መልካም ተግባቦት እንዲኖር የመጀመሪያው ሊስተካከል የሚገባው አስተሳሰባችን ነው። መልካም ተግባቦት የጤነኛና የደስተኛ ባለትዳሮች መለያ እንደሆነ መገንዘብና

በቀጣይ የተግባቦት ክህሎትን ለማሻሻል ራስን ማዘጋጀት ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው። የጤነኛና ደስተኛ ትዳር መለያው ጥንዶቹ እርስ በርሳቸው በነፃነት ሰፋ ላለ ጊዜ መወያየትና መነጋገር የሚችል አቅም ያላቸው መሆኑ ነው። ይህም አስፈላጊ የሚሆነው ባለትዳሮች እንዲወያዩ የሚያደርጓቸው ሰፊና ብዙ የመነጋገሪያ ርዕሶች ስላሏቸውና ስለሚኖሯቸው ነው።

ከፍተኛ የሆነ የተግባቦት ደረጃ ላይ የደረሰ ውጤታማ የተግባቦት ሂደት እንዲኖራቸው ጥረት የሚያደርጉ ባለትዳሮች በጋራ በሚነጋገሩ ወቅት አንዱ የሌላውን የጠለቀ ስሜት መረዳት ይጀምራሉ። የተለያዩ የመግባቢያ መንገዶችን በመጠቀም የመግባባት ክህሎታቸውን ያሻሽላሉ:: አንዱ የሌላውን ቋንቋና ስሜት በመገንዘብ እርስ በእርስ ስለሚረዳዱ፣ ጥንቃቄ ስለሚያሳዩና ስለሚጠባበቁ በመካከላቸው የሚካሄደው ተግባቦት ወደ ላቀ ደረጃ ያድጋል። ይህ የጤነኛና የደስተኛ ትዳር መለያ የሆነው ቁም ነገር በትዳራችን እንዲገለጽ ግንዛቤያችን ከፍ ሊል ይገባል። ግንዛቤያችን ከፍ እንዲልም በትዳር ውስጥ ያለን ጥንዶች አስበንበት በጋራ መትጋት ይጠበቅብናል::

## 2. መረዳት:- የተግባቦት መሠረታዊ እውነቶችን መረዳት

ለመልካም ተግባቦት ክህሎት መኖር በማዳመጥና በመስማት መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት መረዳት ጠቃሚ የተግባቦት መሠረታዊ እውነት ነው። መስማት የምንፈልገውን አሳብ ይዘት ወይም መረጃ የያዘ ሲሆን ማድመጥ ግን ስለሚናገረው ሰው ማሰብንና መጨነቅን ያካተተ ነው። መስማት ማለት በንግግር ወቅት በውስጣችን ምን እንደሚከናወን ማሰብ ላይ ያተኮረ ሲሆን ማዳመጥ ግን የተናጋሪውን ሰው ስሜት ለመረዳት መጣርና ለሚናገረው ሰው ሙሉ ትኩረት መስጠትን ያካትታል።

**የማዳመጥ ምንነት:-** የትዳር አጋር በሚናገርበት ወቅት ምን መናገር እንዳለብን ማሰብንና ጣልቃ ገብተን መናገርን በማቆም ተናጋሪውን ለመስማት ሙሉ ትኩረትን መስጠት የማዳመጥ ሂደት ነው::[14] ባግባቡ ሳይሰሙ መናገር መጽሐፍ ቅዱስ በ**ምሳ 18፡ 13** *"ሳይሰማ ነገርን በሚመልስ ስንፍናና እፍረት ይሆንበታል።"* ብሎ እንደተናገረው ውጤቱ ስንፍናና እፍረት ይሆናል። ማዳመጥ ተናጋሪ የሆነው የትዳር አጋር ምን፣ ለምንና እንዴት እንደተናገረ ሳይፈርዱ ሙሉ በሙሉ በመረዳት መቀበል ነው። ይህ ሲባል በሁሉ ነገር ተስማምተናል ማለት አይደለም! በሃሳብ፣ በድምጽ፣ በአገላለጽ የምንሰማው ነገር አንዳንድ ጊዜ ላይመቸን ይችላል:: ነገር ግን ማዳመጥ ይህን ሁሉ ከፈራጅነት በጸዳ ልቦና መስማትን ይጠይቃል። ማዳመጥ የመላ ሰውነት እንቅስቃሴን፣ በቃላት የማይገለጹ አገላለጾችንና የአይን ምልከታን ሁሉ በመከታተል እውነተኛውን መልዕክት ለማግኘት የማድረግ ጥረት ነው::[15]

[14] Wright H. Norman: communication key to your marriage page 96, 97
[15] Wright H. Norman: communication key to your marriage page 96, 97





**ማዳመጥ**:- የተናጋሪውን የመልዕክት ይዘት፣ እውነተኝነትና ስሜት በተናጋሪው ስሜት ውስጥ ሁኖ መስማት፣ የሌላውን ስሜት፣ ፍላጎትና አስተያየት ለመረዳት በመጣር ሙሉ የሆነ ትኩረትን የሚጠይቅና በየጊዜው እየተማርነው የምንሄደው ችሎታ ነው::[16] **ሳይኮሎጂስቶች:-** የሰዎች የማዳመጥ ችሎታ ከመናገር ችሎታቸው ጋር ሲነጻጸር አምስት እጥፍ እንደ ሆነ ይናገራሉ። አንድ ሰው **ሁለት መቶ** ቃላት ቢናገር **አምስት እጥፍ** ማለትም **አንድ ሺ** ቃላት መስማት ይችላል **(200 ቃላት መናገር X 5= 1000 ቃላትን መስማት)**::[17] የእግዚአብሔር ቃል ከመናገር ይልቅ ለመስማት ቅድሚያ መስጠት አስፈላጊ እንደሆነ እንዲህ ሲል ያረጋግጣል:- *"ስለዚህ፥ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፥ ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ ለመናገርም የዘገየ ለቍጣም የዘገየ ይሁን፤..."* /**ያዕ 1፡ 19**/::

በመስማትና በማዳመጥ መካከል ልዩነት አለ:: በሁለቱ መካከል ያለውን ልዩነት መረዳት ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው። እየሰማን እያለ እያዳመጥን እንዳይመስለን ወይም እያዳመጥከኝ/ሽኝ/ አይደለም በሚል እሰጣገባ እንዳይፈጠር ኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎችን ማለትም ስልክ፣ አይፓድ፣ ኮምፒዩተርና ሌሎች ተቀራራቢ የሆኑ ትኩረት የሚሰቡ መሳሪዎችን በውይይት ጊዜ ከአካባቢያችን ማስወገድ ተገቢ ነው:: ይህንን ማድረግ መሳሪያዎችን እየነካኩና እየተጠቀሙ ትኩረት ባለመስጠት ምክንያት አለመግባባት እንዳይፈጠርና ይበልጥ ግጭቱ እንዳይባባስ ይረዳል። *"ጆሮህ ጥበብን እንዲያደምጥ ታደርጋለህ፥ ልብህንም ወደ ማስተዋል ታዘነብላለህ"* /**ምሳሌ 2፡ 2**/:: መግባባት ለሚፈልጉ ባለትዳሮች ጥሩ አድማጭ መሆን ምርጫ ሳይሆን ግዴታ ነው።

**መግባባት ለሚፈልጉ ባለትዳሮች ጥሩ አድማጭ መሆን ምርጫ ሳይሆን ግዴታ ነው!!**

መጽሐፍ ቅዱስም አስቀድሞ እንደተገለጠው በ**ያዕ** 1፡ 19 ላይ ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ መሆን እንዳለበት ግልጥ መመሪያ ሰጥቶናል:: ለዚህ አምላካዊ መርህ ራስን በማስገዛትና በመታዘዝ መኖር በትዳር ውስጥ ለሚኖሩ ጥንዶች የጋብቻ ኃላፊነት ብቻ ሳይሆን ክርስቲያናዊ ኃላፊነታቸውም ነው:: ለእግዚአብሔር ቃል በመታዘዝ ይህንን ኃላፊነት የመወጣቱን ተግባራዊ ሕይወት የሚለማመዱበት የመጀመሪያው የመታዘዝ መሠረት መጣል ያለበት ደግሞ በቤታቸው ውስጥ ነው:: *"... እነሆ፥ መታዘዝ ከመሥዋዕት፥ ማዳመጥም የአውራ በግ ስብ ከማቅረብ ይበልጣል።"* /**1ኛሳሙ 15፡ 22**/

[16] Wright H. Norman: communication key to your marriage page 96, 97
[17] Chapman, Gary. Marriage Works helping couples God's way, publishing light university: Forest, Virginia, 2011.

## 3. መምረጥ:- ትክክለኛ ጊዜ፣ ቦታና ሁኔታን መምረጥ

ለተሳካ ተግባቦት ሂደት ትክክለኛ ጊዜ፣ ቦታና ምቹ ሁኔታን ባለመቃኘት የሚፈጠሩ አለመግባባቶች በቀላሉ ሊፈቱ የነበሩ ግጭቶች ያልተፈለገ አቅጣጫ እንዲይዙ የማድረግ ተጽዕኖ ስላላቸው ሊታሰብባቸው ይገባል። *"ለመቅደድ ጊዜ አለው፥ ለመስፋትም ጊዜ አለው ዝም ለማለት ጊዜ አለው፥ ለመናገርም ጊዜ አለው"* /መክ 3፡ 7/ የሚለው የእግዚአብሔር ቃል እንደሚናገረው ለመግባባት የምንናገረውንና ልንደመጥበት የምንችልበትን ጊዜ፣ ቦታና ምቹ ሁኔታን መምረጥ ብልህነት ነው። *"የወርቅ እንኮይ በብር ፃሕል ላይ የጊዜው ቃል እንዲሁ ነው።"* /ምሳሌ 25፡ 11/ የሚለው የመጽሐፈ ምሳሌ ምክር ግልጽ እንደሚያደርገው የጊዜው ቃል ወይም መልዕክት መልካም ነው። *"ሰው በአፉ መልስ ደስ ይለዋል ቃልም በጊዜው ምንኛ መልካም ነው!"* /ምሳሌ 15፡23/

ትክክለኛ ጊዜና ቦታ እንዳንመርጥ ከሚያደርጉን ምክንያቶች መካከል የቁጣ ስሜት፣ ያለመረጋጋት መንፈስ፣ ለነገሮችና በነገሮች ላይ ትዕግስት ማጣት፣ ከኋላ በመሆን የሚገፋፉን ሶስተኛ ወገን ሰዎች መኖራቸውና የነገሩ አስቸኳይነትና አንገብጋቢነት ወ.ዘ.ተ. የሚጠቀሱ ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህ ሁሉ ግፊቶች ቢኖሩም ግንኙነታችንን በመልካም ተግባቦት ለማስቀጠል ግን ትክክለኛ ጊዜ፣ ቦታና ሁኔታን መምረጥ የአድማጭን ሁኔታ መረዳትና አንዱ የሌላውን ስሜት መጠበቅ የግድ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ፣ ለሕዝቡ፣ ለካህናት... ምቹ የሆነ ጊዜ፣ ቦታና ሁኔታ በመጠቀም ሊገባቸው በሚችል ምሳሌና ማብራሪያ መልዕክቱን ያስተላልፍ ነበር። *"መስማትም በሚችሉበት መጠን እነዚህን በሚመስል በብዙ ምሳሌ ቃሉን ይነግራቸው ነበር፤ ..."* ማ4፡33

## 4. መለወጥ:- በየጊዜው የተግባቦት ደረጃዎችን ከፍ ለማድረግ መለወጥ

ሌላው የተግባቦት ደረጃዎች በባለትዳሮች መካከል እንዲኖሩና በየጊዜውም እያደጉ እንዲመጡ ለለውጥ መዘጋጀት አስፈላጊ ነው። ይህ የተግባቦት እድገት ወደ ሕብረታችን እንዲመጣ ለውጥ የሚያሻቸው ጉዳዮችን ማለትም ሌላው ሲናገር የማዳመጥ እንቅፋቶችን ለማስወገድና የትዳር አጋሮች ምን እንደሚሰማቸው የመረዳት አቅምንና በሁለንተናዊ አካል ለማድመጥ ራስን የመስጠት ሂደትን ለይቶ በማወቅ ለለውጥ የመሥራት ፍላጎት ያለንና የምንተጋ ሰዎች መሆን አለብን፡፡ ነገሮችን ግልጥ በማድረግ ማስተዋል፣ በትክክል ማዳመጣችንን በማንጸባረቅና ደግሞ ለማዳመጥ ፍላጎትን በማሳየት ለውጣችንን ማሳየትና ለውጥ በሚያሻው ጉዳይ ላይ ለመለወጥ ፈቃደኛ መሆንም ተገቢ ነው።

ትዕግስት በማጣት ከሚፈጠሩ አለመግባባቶች ለመጠበቅና ወደ ተባባሰ ግጭት ላለመግባት ታጋሽ መሆን አስፈላጊ ነው። በመታገስ መግባባት ላይ ለመድረስ:- ፈጥኖ ፍርድን ከማስተላለፍ፣ ያልታሰበበትን ተጨማሪ አሳብ ድንገት በውይይት መሃል ከማቅረብ፣ ለግላችን የተስማማን አሳብ ብቻ ትክክለኛ እንደ ሆነ አድርጎ ከመቁጠር፣ ምን አገባኝ በማለት ከነገሮች ትኩረትን ፈጥኖ ከማውጣት፣ አዕምሮን ከመዘጋት፣





የምኞት መግለጫን ፈጥኖ ለመስማትና ለማሰማት ከመጣደፍ፣ የተለያዩ ትርጉሞችን ባልገባን ነገር ላይ ከመስጠት፣ ቸኩሎ ሳይሰሙ ለመመለስና ለማመጣጠን ብሎ ፈጥኖ ከመሸሽ ራሳችንን ነፃ ለማውጣትና ለመለወጥ ጥረት ማድረግ በጣም ወሳኝ እርምጃ ነው፡፡

እንዴት ንግግራችን መጀመርና በመልካም ንግግር መልካም ተጽዕኖ በማምጣት መግባባት እንችላለን? የሚል አግባብነት ያለው ጥያቄ በማንሳት ምላሽ ማግኘት መቻል ለተሳካ ተግባቦት መኖር አጋዥ ለውጥ ልናመጣ በምንችልበት መስመር ላይ እንድንሠራ ወደሚያስችል አቅጣጫ ይመራናል። ለመልካም ንግግር:- ልንነጋገርበት የምንፈልገውን ርዕሰ ጉዳይ መለየት፣ የትኛው ትክክለኛ ጊዜ እንደሆነ መምረጥ፣ የትዳር አጋርን በአግባቡ ማናገር፣ አሳባችንን በጥሩ መልኩ ማጠቃለል፣ ምላሽ ለመስማት ጊዜ መስጠት፣ ለትዳር ጓደኛ አክብሮትን ማሳየት፣ ሃሳብን ለመግለጥ የሰውነት እንቅስቃሴን በአግባብ መጠቀም፣ የትዳር አጋርን የመግባቢያ መንገድ ግምት ውስጥ ማስገባትን አለመርሳት፣ የትዳር አጋርን ፍላጎቶች መጠበቅ፣ በተቻለ መጠን ንግግራችን ተደማጭነት ያለው እንዲሆን በሚስብ መልኩ ማቅረብ፣ እውነተኛ ሁኖ መቅረብ፣ ለመቀባበልና ለመደሰት አጥብቆ መፈለግ፣ ንግግርን በአድናቆትና ተስፋ ጫሪ በሆነ አቀራረብ መጀመርና መግባባት መቻል የንግግር ግብዓቶች ሆነው በበሰለ መንገድና በተሟላ ሁኔታ መቅረብ አለባቸው፡፡[18]

## 5. መለማመድ:- የተግባቦት መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶችን በመረዳት መለማመድ

በትዳር ውስጥ ግጭትን ቀናሽ መልካም ተግባቦት እንዲኖር ስለመልካም ተግባቦት መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል? መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶችና መርሆችስ ምንድን ናቸው? ... የሚሉ መሠረታዊ ጥያቄዎችን መመለስና ያሉትን እውነቶች በተግባር መለማመድ ተገቢ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከምናገኛቸው የተግባቦት መርሆዎች አንዱ አንደበትን መግራት ነው፡፡ አንደበትን ያለመግራት ችግር ብዙ ጊዜ ኃይለኛነት በሞላበት ንግግር ይገለጣል፡፡የቃላት (የንግግር) ኃይለኛነት በተለያዩ ምሳሌዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተገልጧል። ለሌሎች ሰዎች የምንናገረውን ቃል ጉልበት ለማሳየት ሌሎች ጉልበት ያላቸውን ምሳሌዎች መሠረት በማድረግ **ያዕ.3፡ 3-10** የምላስን ጉልበት ***"ከጉልበታም ፈረስ"*** ና ***"ከግዙፍ መረከብ"*** ጋር ያነጻጽረዋል፡፡

የጉልበታም ፈረስ ጉልበተኝነት በልጓም የሚገራ ሲሆን የግዙፍ መርከቦች እንቅስቃሴ ደግሞ ምንም ያክል ትልቅ ቢሆኑና ማዕበልም ቢያናውጣቸው እንኳን በመቅዘፊያ ይመራል፡፡ ያዕቆብ በመልክቱ እንደገለጠው አንደበት ግን ከሁለቱም ምሳሌዎች ይለያል፡፡ ምክንያቱም አንደበት ለመግራት የሚያስቸግር በብልቶቻችን

[18] Focus on the family, <u>the first five years of your marriage,</u> PP.216-218

መካከል አመጸኛ ዓለም በመሆን ስጋን ከማሳደፉም በላይ የፍጥረትን ሩጫ ያቃጥላል፡፡ ይህንን እውነታ በማሳየት ያዕቆብ አንደበትን ጫካን ሁሉ በሚያቃጥል ትንሽ እሳት በመመሰል *"የሚገድል መርዝ የሞላበት ወላዋይ ክፉት"* ይለዋል፡፡ አስፈሪ የሆኑ እንስሶችና መርከቦች ሰዎች በሠሯቸው የመቆጣጠሪያ መሳሪያዎችና ሰዎች በሚሰጧቸው ስልጠናዎች ይገራሉ፡፡ ነገር ግን ሌሎችን አስቸጋሪዎች የሚገራበት መሳሪያ መፍጠር የቻለው ሰው ምላሱን ለመግራት እንደሚቸገር ያዕቆብ በመልዕክቱ ያሳየናል።

የአንደበት አስቸጋሪነት የገባው ሌላው ሰው ሐዋርያው ጴጥሮስ በ1ኛጴጥ 3፡ 10 *"ሕይወትን ሊወድ መልካሞችንም ቀኖች ሊያይ የሚፈልግ ሰው ምላሱን ከክፉ ከንፈሮችንም ተንኮልን ከመናገር ይከልከል..."* ሲል ይመክራል፡፡ በየጊዜው ስለራሳችን የምንናገረው ቃል ለቁጣ፣ ለጭንቀት፣ ለበደለኝነት ስሜትና ለድብርት ተጋላጭ እንድንሆን ሊጋብዘን ይችላል። በተደጋጋሚ ስለራሳችን የምንናገረው የሕይወታችን አስተሳሰብ፣ እሴትና እምነት ወደ መሆን ሊለወጥ ይችላል።

ከመናገር በፊት ማሰብና አንደበታችንን መግራት በንግግር የትዳር አጋርን እንዳንጎዳ ይጠብቀናል፡፡ የአንደበትን ቃል መጠበቅን ለመለማመድ *"አቤቱ፥ ለአፌ ጠባቂ አኑር፥ የከንፈሮቼንም መዝጊያ ጠብቅ።"* /መዝ 141፡ 3/ ብሎ ዘማሪው እንደጸለየው ብርቱ ጸሎት ያስፈልገናል። ምክንያቱም *"እንደሚዋጋ ሰይፍ የሚለፈልፍ ሰው አለ የጠቢባን ምላስ ግን ጤና ነው። "* /ምሳ 12፡ 18/ እንደሚለው የእግዚአብሔር ቃል በልፍለፋችን የምንዋጋ ሰዎች ሳይሆን በጠቢብ ምላሳችን ለትዳር ጓደኛችንና ለቤተሰባችን ጤና ምክንያት እንድንሆን የሚያስችለን የእግዚአብሔር ፀጋ ያስፈልገናል፡፡ አንዴ ከአንደበታችን የወጣ ቃል አይመለስምና በምናወጣቸው ቃላት የምንጸጸት እንዳንሆን እንጠንቀቅ። ከአንደበታችን ያወጣነውን ቃል ምናልባት ልናብራራ፣ ልናስተባብል ወይም ይቅርታ ልንጠይቅበት እንችላለን እንጂ መመለስ አንችልም። ቃላት ግን አንድ ጊዜ ከአንደበታችን ከወጡ የፈጠሩትን ችግር ያስተካከልን ቢመስለንም እንኳን በአድማጩ አዕምሮ ውስጥ በመቆየት ጊዜ እየጠበቁ ቆስቋሽ አጋጣሚ ሲያገኙ የሚፈነዱ በትዳር ውስጥ መልካም ተግባቦትን የሚያቃውሱ ግጭት ፈጣሪ ፈንጅዎች ይሆናሉ፡፡ *"አፉንና ምላሱን የሚጠብቅ ነፍሱን ከመከራ ይጠብቃል።"* /ምሳሌ 21፡ 23/

ከዚህም በተጨማሪ ሐሰትን መለማመድን ከሕይወታችን ማስወገድና እውነተኛነትን የዘወትር ልምዳችን ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡ እግዚአብሔር የሚጠላውን በመጥላት የሚወደውን በመውደድ ቃሉን መታዘዝን መለማመድ ያስፈልጋል። መጽሐፈ ምሳሌ እንደሚናገረው እግዚአብሔር ከሚጠላቸው ሰባት ነገሮች መካከል አንዱ ሐሰተኛ ምስክር ነው /ምሳ 6፡ 16-19፤ 12፡ 17፤ 28፡ 23፣ ኤፌ 4፡ 15፣25ና ቆላ 3፡ 9/፡፡ ሌላው ልንለማመደው ከሚገባን ነገር አንዱ ጠብን ማስወገድ ነው /ያዕ 4፡ 1-3፣ ምሳ 11፡ 12፣ ምሳ 17፣ 14፣ 20፡ 3፣ 26፡ 21፣ ሮሜ 12፡ 18፣ ኤፌ 4፡ 31፣ ዕብ 12፡ 14/፡፡ *"ሕይወትን ሊወድ መልካሞችንም ቀኖች ሊያይ የሚፈልግ ሰው፥ መላሱን ከክፉ ከንፈሮቹንም ተንኰልን ከመናገር ይከልከል"* /1ኛ ጴጥ 3፡ 10/፡፡





ለማነጽ የማይጠቅም አሉታዊ የሆነ ትችት ለተግባቦት እንቅፋት ነውና ፈጽሞ አለመሞከርና ለማስወገድ መልመድ ተገቢ ነው /ሮሜ 14፡ 13፣ ማቴ 7፡ 3-4/። ለማነጽ ከማይጠቅሙ አሉታዊ የሆኑ ትችት አይነቶች መካከል በቀልድ መንፈስ በመሆን ሁልጊዜ መቀለድ አንዱ ነው፤ *"ትንታግንና ፍላጻን ምትንም እንደሚወረውር እንደ ዕብድ ሰው፤ ባልንጀራውን የሚያታልል። በጨዋታ አደረግሁት የሚል ሰውም እንዲሁ ነው።"* /ምሳ 26፡ 18-19/፡፡ ሌላው ጠቀሜታ የሌለው ሁልጊዜ ስህተት በመፈልግ መተቸት ነው *"እንደሚዋጋ ሰይፍ የሚለፈልፍ ሰው አለ የጠቢባን ምላስ ግን ጤና ነው።"* /ምሳ 12፡ 18/፡፡ የመጨርሻው የሚነገሩ ቃላትን በማጣጣል ወይም ዋጋ በማሳጣት መተቸት ናቸው። እንደ ክርስቲያን ባለትዳር መልካም ተግባቦት እንዲኖር ከተፈለገ እነዚህን የተግባቦት እንቅፋቶች በማስወገድ አንደበትን መጠበቅ፣ አንደበትን አጥብቆ መግራትና መልካም መናገርን መለማመድ በጣም አስፈላጊ ነው።

## 6. መቃኘት፡- በጥንቃቄ ሁኔታዎችን መቃኘት

*"ጥንቃቄ ይጠብቅሃል ማስተዋልም ይጋርድሃል፥"* /ምሳሌ 2፡ 11/ እንደሚለው የእግዚአብሔር ቃል መልካም ተግባቦት በትዳር መካከል እንዲኖረንና ግንኙነታችንን ያለምንም ፍርሃትና በነፃነት ማከናወን እንድንችል አስተዋይ መሆን ይገባናል፡፡ በግድ የለሽነት ሳይሆን ጥንቃቄ በተሞላ አካሄድ ለጋብቻ ሕይወታችን ጥበቃ የምናደርግ ባለትዳሮች ልንሆን ያስፈልጋል። ለመልካም ተግባቦት ጥንቃቄ የሚያሻው፡- ለምንናገረው ቃል፣ ለምንናገርበት መንፈስና ሁኔታ፣ ልንጠብቀው ለምንፈልገው ወዳጅነትና ለልባችን ሃሳብ ነው፡፡ እነዚህን ሁሉ በጥንቃቄ መቃኘትና በጤናማው መንገድ ላይ እንዲቀጥሉ በመቆጣጠር የተሳካ ተግባቦት ከትዳር ጓደኛችን ጋር እንዲኖረን ኃላፊነታችንን መወጣት ተገቢ ነው ምክንያቱም ብዙ ጉዳት የሚፈጠረው ጥንቃቄ ከጎደለው ንግግር ባጠቃላይም የተግባቦት ሂደት ነውና። *"አቤቱ፥ ረድኤቴ መድኃኒቴም፥ የአፌ ቃልና የልቤ አሳብ በፊትህ ያማረ ይሁን።"* /መዝ 19፡ 14/

በተግባቦት ሂደት ውስጥ በአእምሮችን የሚወጡና የሚወርዱ የተለያዩ አሳቦችን የመምረጥ፣ ደግሞ ደጋግሞ የማሰብ፣ የማሰላሰልና በማስተዋል የመቃኘት ኃላፊነት አለብን፤ አለበለዚያ ለክፉ ድርጊት አልፈን ልንሰጥ እንችላለን። *"ነገር ግን እባብ በተንኮሉ ሔዋንን እንዳሳታት፥ አሳባችሁ ተበላሽቶ ለክርስቶስ ከሚሆን ቅንነትና ንጽሕና ምናልባት እንዳይለወጥ ብዬ እፈራለሁ።"* /2ኛቆሮ 11፡ 3/ አጥብቀን ልባችንን እንጠብቅ የሕይወት መውጫ ነውና!! ስለዚህ እንደ ንጉስ ዳዊት *"አንተን እንዳልበድል፥ ቃልህን በልቤ ሰወርሁ።"* /መዝ 119፡ 11/ ብለን በመጸለይ ለቃሉ ለመታዘዝ በልባችንና በኑሯችን ስፍራ እንስጥ፡፡

## ለጥንዶች በግላቸውና በቡድን ለማጥናት የሚረዷቸው የውይይት ጥያቄዎች

## የምዕራፍ ሰባት (7)

## የውይይት ጥያቄዎች

1. የተግባቦት (ኮሙኒኬሽን) ምንነት በማብራራት ግለጡ::
2. በባለትዳሮች መካከል ትክክለኛ የሆነ ተግባቦት አለ የምንልለው መቼና ምን ሲፈጠር ነው?
3. ባለትዳሮች እንደሚገባ እንዳይግባቡ ሊያደርጓቸው የሚችሉ ምክንያቶች ምንድን ናቸው ትላላችሁ?
4. የእናንተን የትዳር ግንኙነት ደረጃ ስትገመግሙት የት ላይ ነው ያላችሁት? እንደሚገባስ እንዳትግባቡ ያደረጋችሁና ለግጭት የዳረጋችሁ ምክንያትስ ምንድን ነው?
5. ጥንዶች በትዳር ሕይወታቸው መልካም ተግባቦት እንዲኖር ምን ማድረግ አለባቸው? በሰፊው ተወያዩበት::
6. የእናንተን ተግባቦት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ለማድረስ ምን ማድረግ አለብን ትላላችሁ? የተግባቦት ደርጃችሁን ከፍ ለማድረግ ዛሬ አብራችሁ አቅዱ።





# ምዕራፍ ስምንት(8)

# ገንዘብና ንብረት

## I. የገንዘብና የንብረት ምንነት

ገንዘብና ንብረት የምንለው ጥንዶቹ በግልም ሆነ በጋራ በሥራ፣ በንግድ፣ በውርስ፣ ያገኙትንና የሚያገኙትን ለጋራ ትዳራቸው የሚጠቀሙበትን ጥሬ ገንዘብ፣ የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት፣ ብር፣ ወርቅና ገቢ ሊያመጣ የሚችል ማንኛውንም ዓይነት ንብረት ሁሉ ያጠቃለለ ነው። ክርስቲያን ባልና ሚስት አንድነታቸው የሚገለጥበት አንዱ ጉዳይ የጋራ ገንዘብና ንብረት ባለቤት መሆናቸው ነው። ይህ ርዕሰ ጉዳይ በዚህ የጋብቻ ዘመን ከገንዘብና ከንብረት ጋር ተያይዘው ሊፈጠሩ የሚችሉ የተለያዩ የግጭት ምክንያቶችንና መፍትሔዎቻቸውን በማሳየት የጥንዶችን ግንኙነት ይበልጥ ለማጠናከር የሚረዳና አቅጣጫ የሚጠቁም ነው።

እንደ ክርስቲያን ባለትዳር አንዳችን ለአንዳችን ራሳችንን የመስጠት ኃላፊነትን የመተግበርን አስፈላጊነት መረዳት ብቻ ሳይሆን ያለን ሁሉ የጋራ እንደሆነ ልናውቅና ልናምን ይገባል። በትዳር ውስጥ አንድነት ከሚገለጥባቸው መንገዶች አንዱ ገንዘባችንና ንብረታችን ነው። ክርስቲያን ባለትዳሮች ያለንን ሁሉ በመካፈልና በጋራ በመጠቀም ለመኖር የጀመርነው የአብሮነት ጉዞ ሁለንተናዊ መሰጠትን የሚጠይቅ ነው። ክርስቲያን ባለትዳሮች ይህንን ሕይወት መግለጥ የሚችሉት ገንዘባቸውን ያለ አድሎና ከፍፍል ለእኔ ብቻ ከሚል ገንዘብን የመውደድ ግለኝነት በጸዳ መልኩ አብረው መጠቀም ሲችሉ ነው *"አካሄዳችሁ ገንዘብን ያለ መውደድ ይሁን፥ ያላችሁም ይብቃችሁ፤ እርሱ ራሱ። አልለቅህም ከቶም አልተውህም ብሎአልና፤..."* /ዕብ.13:5/::

## II. ከገንዘብና ከንብረት ጋር የተያያዙ የግጭት መንስኤዎች

በባለትዳሮች መካከል ላለመግባባትና ለግጭት ቀዳሚ ከሚሆኑት ምክንያት መካከል አንዱ ገንዘብ ነው። በቅርብ አመታት በተጋቡ ባለትዳሮች መካከል ሆነ በቆዩት ከገንዘብና ከንብረት ጋር በተያያዘ የሚፈጠሩና ሊፈጠሩ የሚችሉ ችግሮችን መለየትና ማወቅ መፍትሔ ለማፈላለግ አገዛው ከፍተኛ ነው። እነዚህን በገንዘብና በንብረት ላይ ባለትዳሮች እንዳይግባቡ የሚያደርጉ የግጭት ምክንያቶች እንደሚከተለው እንቃኛለን:-

### 1. ለሰርግና ከሰርግ ጋር ተያይዘው በወጡ የተለያዩ ወጭዎች

ጥንዶች ከእጮኝነት ወደ ባለትዳርነት መሸጋገር በሚያስቡና በሚወስኑበት ወቅት ከፍተኛ ባጀት የሚጠይቁ የሰርግና ከሰርግ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ወጭዎች አሉ። የሰርግ ድግስ ማድረግ አለብን ወይስ የለብንም? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የሚወሰነውን ውሳኔ ለጥንዶች መተው የግድ ነው። የሰርግ ድግስ መተው ማለት ግን ጋብቻችንን በቤተ ክርስቲያን በኩል ማድረግን፣ በቤተክርስቲያን የሚጠየቁትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላትንና በጽድቅ በእግዚአብሔርና በምስክሮች ፊት በይፋ ቃልኪዳን በመግባት መጋባትን መርሳት እንዳይደለ መረዳት በጣም አስፈላጊ ነው።

ሰርግ ሲታሰብ ከሌሎች ሰዎች ወይም ከጓደኞች ጋር ለመወዳደርና የእኔ ወይም የእኛ ሰርግ ለየት ያለ ነበር የሚል ዝና ፍለጋ ወደ ሰርግ ውሳኔ ከመምጣት ራስን መጠበቅ ተገቢ ነው። ዛሬ በሰርግ ከሌሎች ጋር መወዳደር ከጀመርን ይህ የውድድር ስሜት ከእኛ ጋር አብሮን በመቀጠል ሁልጊዜ ባለን ነገር እንዳንረካና ሌሎች የእኛ የቅርብ ሰዎች ባላቸውና በሚኖራቸው ንብረት፣ ገንዘብና ሐብት በመቅናት ደስታ የራቀንና የሰዎችን የማግኘት ሳይሆን የማጣት ዜና መስማት እንድንናፍቅ ሊያደርገን ይችላል። ሌሎች ሰዎች የሆነ ነገር ባገኙ ጊዜ ሁሉ ደስታ የራቀን ከመሆናችንም ባሻገር ከሌሎች ሰዎች በልጦ ለመገኘት የምናደርገው አቅምን ያላማከለ የተለያየ ወጭ ከትዳር አጋራችን ጋር ያጋጨናል፡፡ ይህ ክስተት ባግባቡ ካልተስተካከለ የመለያየት ምክንያት ሊሆንም ይችላል።

ስለዚህ ይህን እውነታ በመረዳት ሰርግ ለመደገስ የሚያስቡ እጮኞሞች አቅማቸውን ማገናዘብና ያሉበትን ሁኔታ በማስተዋል ማየት ቢችሉ መልካም ነው። ሰርግ መደገስ መቼ፣ እንዴትና ምን ያክል ወጭ ይጠይቀናል ብለን ስናስብ በቀጣይ ኑሯችን ላይ አሉታዊ የሆነ ተጽዕኖ ሳያሳድር ልንወጣው መቻላችንን ማረጋገጥ አለብን፡፡ ትዳር ለመመሥረት ብለን የምናደርጋቸው ነገሮች የትዳራችን እንቅፋት ሊሆኑ አይገባም። ለሰርግና ከሰርግ ጋር ተያይዘው ልናወጣቸው የሚታሰቡ ወጭዎችን በሚመለከት በጋራ በመወያየት አስፈላጊነታቸውንና አቅማችንን መቃኘትና ስምምነት ላይ መድረስ ተገቢ ነው። ትናንት እንዴት ባለ መልኩ ገንዘቡን ለማግኘት ዋጋ እንደከፈልን ማሰብ፣ ዛሬ ያለንን አቅም መመልከትና ነገ በትዳራችን ላይ ሊፈጥር የሚችለውን ተጽዕኖ መቃኘት እንደገና ለሌላ ችግር አልፈን እንዳንሰጥ ይጠብቀናል፡፡ የትዳር ግንኙነታችንም በጤንነትና ደስታ በተሞላ ሁኔታ እንድንመራ ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወት መዘንጋት የለብንም።

ሰርግን ከአቅም በላይ በሆነና በብድር ደግሰው የተጋቡ የቅርብ ተጋቢ ባለትዳሮች ወደ ኋላ ተመልሰው መጸጸትና አንዱ በሌላው ማሳበብ ከሰርግ ማግስት የሚያጋጥማቸው ተግዳሮት ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ሲያጋጥማቸው መካሰስንና መወቃቀስን አስወግደው በጋራ ካሉበት ዕዳ ለመውጣት ማቀድ መቻል አለባቸው። ጥንዶቹ በጋራ በመስማማት ከትናንቱ አባካኝ የሆነ ውሳኔ በመማር ዛሬ ብድር ውስጥ የሚያስገቡ ሁኔታዎችን ማቆምና ማስወገድ መቻል ይኖርባቸዋል። ከሌሎች ጋር ተወዳድሮ በልጦ መገኘት ከሚባለው መጥፎ የውድድር መንፈስ ራስን ነጻ በማድረግና በመጠበቅ የራስን ኑሮ መኖር ተገቢ ነው፡፡ ይህን መርህ የሚከተሉ ጥንዶች ነገ ልጆች ሲወለዱ፣ ሲያድጉና ትምህርት ቤት ሲገቡ የሚጠብቃቸውን ወጭና ሌሎች ያልታሰቡ ወጭዎችን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በአቅማቸው በመኖር የቤተሰባቸውን የሰላምና የደህንነት መሠረት ዛሬ መጣል ተገቢ ነው፡፡ በሚወስዱት መልካም እርምጃም ቤታቸውን ነገ ከሚያጋጥም





ግጭት አስቀድመው ይጠብቃሉ፡፡ ይህ ዓይነቱ የጠቢብ ሰው ተግባር ትዳርንና ቤተሰብን ለመጠበቅ አንዱ ብስለት የተሞላ እርምጃ ነው።

## 2. ጥንዶች በገንዘብ ላይ ያላቸው የአመለካከት (የእይታ) ልዩነት

ባልና ሚስት በገንዝብ ላይ ያላቸው የአመለካከት ልዩነት አለመግባባትና ግጭት በትዳራቸው እንዲፈጠር ምክንያት ይሆናል። **የመጀመሪያው** በአመለካከት ልዩነት ቀውስ የሚፈጠርበት ምክንያት ባልና ሚስት ገንዘብን በተለያየ አመለካከት በማየታቸው ነው። አንዱ የትዳር አጋር ገንዘብ እጅግ በጣም አስፈላጊና ዋና ነገር እንደሆነ ሲያስብና ሲያምን ሌላው አካል ደግሞ ገንዘብ ዋና ነገር እንደሆነ ሳያስብ ወይም ምንም እንዳልሆነ ሲያስብ በመካከላቸው አለመግባባት የሚፈጠርበት ሰበብ አለ ማለት ይቻላል። በሁለቱ መካከል ያለው የእይታ ልዩነት ገንዘብን ለማግኘትና ለመጠቀም ተነሳሽነታቸው እንዲለያይ በማድረግ አንዱ አካል ሌላውን ወደ ራሱ አመለካከት ለማስገባት የሚያካሂደው ትግል ውጥረት ያስከትላል፡፡ ጥንዶችንም ለግጭት ይዳርጋል።

**ሁለተኛው** በአመለካከት ልዩነት ምክንያት ቀውስ የሚፈጠረው ገንዘብን ሠርቶ ለማግኘት አንደኛው አካል ደሞዝና ክፍያ ላይ ሲያተኩር ሌላው አካል ደግሞ ከክፍያ ይልቅ ከሥራው ዓይነትና ቦታ፣ ከቤተሰብ፣ ከቤተ ክርስቲያን፣ ከወዳጆችና ከልጆች ትምህርት ቤት ጋር በተያያዘ ለማሰብ ቅድሚያ በሚሰጥበት ጊዜ ነው፡፡ በእይታቸው መለያየት መነሻነት ልዩ ልዩ ጉዳዮችን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባትና የሚኖሩበትንና የሚሠሩበትን አገር ወይም አካባቢ ጫና እና የሚጠብቃቸውን ወጭ በመመልከት ፍላጎታቸውን ለማሟላት በሚያራምዱት አስተሳሰብ መለያየት ጥንዶች ወደ ግጭት ሊገቡ ይችላሉ።

**ሶስተኛው** ከጥንዶች የእይታ ልዩነት ጋር የተያያዘ ችግር በጋብቻ ውስጥ የሚፈጠረው አንዱ አካል ዛሬ ላይ ብቻ በማተኮር ገንዘብን ለዛሬ እንጠቀም ነገን በእግዚአብሔር እንታመን የሚል አመለካከት ሲኖረውና ሌላው ደግሞ ከዛሬ ይልቅ ብዙ ነገዎችን በማሰብ ለወደፊት ወይም ለአደጋ ጊዜ የሚሆን የኢኮኖሚ መሠረት እንጣል የሚል አቋም ሲይዝ ነው፡፡ እይታቸው መለያየቱ ሁለቱ ተጋቢዎች ለዛሬ ብቻ ደስ ብሎን እንኑር ወይንስ ለቀጣዩ ሕይወታችንና ኑሯችን እናስብ በሚል መንታ ሃሳብ እንዲሟገቱና እንዲጨቃጨቁ ያስገድዳቸዋል፡፡ በዛሬና በነገ መካከል ባላቸው የአመለካከት ልዩነት ሰበብም በጥንዶቹ የትዳር ሕይወት ውስጥ ገንዘብ ያለመግባባትና የግጭት አብይ ምክንያት ይሆናል።

**አራተኛው** በአመለካከት ልዩነት ምክንያት ቀውስ የሚፈጠረው አንዱ የትዳር አካል ለቤተ ክርስቲያን፣ ለችግረኞች፣ ለቤተሰብ፣ ለወዳጅና ለሌሎች ጉዳዮች ገንዘብ መስጠት አስፈላጊና ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ እንደሆነ በሚያምንበትና ሌላው አካል ደግሞ የራስ የወደፊት ኑሮና አስፈላጊ ወጭ ላይ ብቻ እናተኩር በሚልበት ጊዜ ነው፡፡ አንደኛው አካል ለሌሎች የገንዘብ ድጋፍ ካላደረግን ሲል ሌላኛው አካል ደግሞ

መስጠትን ሲከለክልና መስጠት ሲያመጣ ይችላል ብሎ የሚያስበውን ከስረት በየምክንያቱ እያነሳ ማስጠንቀቅ ሲጀምር ገንዘብን ለሌሎች የመስጠት አስፈላጊነት ላይ ተጋቢዎች ያላቸው የአመለካከት መለያየት ግጭት እንዲፈጠር ዋና ምክንያት ሊሆን ይችላል።

**አምስተኛው** የእይታ ልዩነት በትዳር ውስጥ ለቀውስ ምክንያት የሚሆንበት ጊዜ የአንዱ አካል ብቻ በቤት ውስጥ ላሉ ለተለያዩ ወጭዎች በቂ ገቢ ለማግኘት፣ ኑሮን ለመሸፈን፣ እዳን ለመከፈልና ለወደፊት ለታቀዱ ታላላቅ ወጭዎች ለመዘጋጀት ሲባል መደበኛ የገቢ ምንጭ ከሆነው ስራ በተጨማሪ ሌላ ስራ በመስራት ገቢን ለመጨመር ማሰብና መጣር ነው። ሌላው አካል ደግሞ ለተጨማሪ ገቢ ተጨማሪ ሰዓታትን መስራትን በመቃወም እንደ ባለትዳር የጋራ ጊዜን አብሮ በማሳለፍ የትዳርን ግንኙነት መገንባት ላይ ሲያተኩር በመካከላቸው ላለመግባባትና ለግጭት አልፈው ሊሰጡ ይችላሉ።

**ስድስተኛው** በጥንዶች መካከል በእይታ ልዩነት ሰበብ ችግር የሚፈጠረው አንዱ የትዳር አካል የገቢንና የወጭን ሂደት መከታተልና መቆጣጠር የሚፈልግ ሲሆንና ይህንንም ፍላጎቱን በሁሉም የወጭና የገቢ እንቅስቃሴ ላይ በቁጣና በተቆጣጣሪነት መንፈስ በመናገር ለማሟላት ሲሞክር ነው:: ሌላው አካል ደግሞ በተቃራኒው እርሱ ራሱ ሠርቶ የሚያስገባውን ገቢ እንዲሁም በልዩ ልዩ እንቅስቃሴዎች የሚገባውንና የሚወጣውን ገንዘብ የማወቅም ይሁን የማሳወቅ አስፈላጊነት ላይ ግድ የማይሰጠው ምን እንደተደርገና እንደሚደረግ የማያውቅ ሊያውቅም የማይፈልግ ይሆናል:: ወይንም አስቦበት የተደበቀ ዓላማ ያለው ሰው ይሆንና ወጭና ገቢ ላይ ድብብቆሽ ይጫወታል:: እነዚህ ተቃራናዊ መስመር ያላቸው የዕይታ ልዩነቶች፣ ፍላጎቶችና ድርጊቶች በጥንዶቹ መካከል በየጊዜው ያለመግባባትና የግጭት መነሻና ማደጊያ የውጥረት አካባቢዎች ሆነው ይቀጥላሉ ።

**የመጨረሻው** ጥንዶቹ በገንዘብ ላይ ባላቸው የተለያየ አመለካከት መነሻነት ላለመግባባትና ለግጭት የሚዳረጉት ወጭ በሚያወጡበት ወቅት ቅድሚያ በሚሰጧቸው ነገሮች ላይ ልዩነት ሲኖራቸው ነው። አንዱ አካል ለልጆች አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮች ላይ፣ ሌላው አካል ለወላጆች አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮች ላይ ወይም የቅንጦት እና የመዝናኛዎች እቃዎች ላይ ሲያተኩር በመካከላቸው ጭቅጭቅና የውድድር መንፈስ ይፈጠራል:: ይህ በውድድር መንፈስ ጥንዶቹ ወደ ፉክክር መግባታቸው በእልህ በሌላኛው አካል አሳብ አቅራቢነት ከወጣው ወጭ ጋር የሚመጣጠን አቻ የወጭ በጀት ለእርሱም እንዲበጀትለት ከፍተኛ ወጭ የሚጠይቁ ንብረቶች፣ ያልታሰበባቸው አዳዲስ እቃዎች እንዲገዙ ወይም የግል መብቱ እንዲከበርለት ከጥንዶቹ አንደኛው ግትር አቋም እንዲይዝ ያደርገዋል:: በዚህም ምክንያት ላይግባቡና ግጭትም ሊፈጠር ይችላል።





## 3. ዕዳ ውስጥ በመግባትና ለመውጣት በሚደረግ ውጥረት

ወደ ትዳር ዓለም ከመግባታቸው በፊት ለትምህርት፣ ለንግድ፣ አንዳንድ ከፍተኛ ወጭን የሚጠይቁ ንብረቶችን ለመግዛት ሲባል፣ ለሚደግሱት የሰርግ ወጭና ለሚያዘጋጁት አዲስ ቤትና የቤት ዕቃ ግዥ ከመንግሥትም ሆነ ከግለሰብ በተበደሩት እዳ ምክንያት ጥንዶች ላለመግባባትና ለግጭት ሊዳረጉ ይችላሉ። ወይም ለግላቸው፣ ለትዳራቸው፣ ለቤተሰባቸውና ለንግድ እንቅስቃሴያቸው የተበደሩት ብድር ባጀትን ባገናዘበ መንገድ በግልጥና በጋራ በመስማማት የተፈጸመ ካልሆን ከጋብቻ በፊትና በኋላ በሚፈጠረው ግጭት ላይ የሚያመጣው አሉታዊ ተጽዕኖ ቀላል ላይሆን ይችላል።

ቤተሰብን የሚመሩ ጥንዶች ቀውስን በቀነሰ ሂደት ብድር ለመበደርና እዳቸውን ከፍለው ከብድር ተጽዕኖ ለመውጣት ከፈለጉ በቅድሚያ የራሳቸውን አቅም ያገናዘበና ምክንያታዊ የሆነ ባጀት በመበጀት በፕሮግራም ትዳራቸውን ሊመሩት ይገባል:: ነገር ግን ብዙዎቹ ባለትዳሮች ገቢን ያገናዘበ በጀትን በምክክር ወስኖ በፕሮግራም መመራትን በተመለከተ ያላቸው አመለካከት አሉታዊ ቅድመ እሳቤ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ በዚህ መንገድ ቤተሰብን የማስተዳደሩንና የመምራቱን ጉዳይ ችላ ሲሉት ይታያሉ::

ባጀትን መሠረት ባደረገ የታሰበበት መንገድ መኖርንና ቤተሰብን መምራትን ነፃነትን እንደሚነፍግና የማያምን ክርስቲያን የኑሮ ዘይቤ እንደሆነ በማሰብ የሚፈጠረው ሽሽት ለግዴለሽነታቸው ዋናው ምክንያት ነው። በትዳር ውስጥ ለሚያስፈልገው ገቢና ወጭ በቂ የሆነ የታሰበበት፣ በግልጥ ምክክር ውሳኔ ላይ የተደረሰበትና አቅምን ያገናዘበ በጀት አለመኖር ባለትዳሮችን ያለአግባብ ለብድር ተጋላጭ ሊያደርጋቸው ይችላል።

በእርግጥ ባጀት በጀትን ማለት በዚህ ብዙ ነገሮች በቅጽበት በሚለዋወጡበት ዓለም ውስጥ ዛሬ ላይ የወሰንነው ባጀት በየቀኑ የሚያጋጥሙንን ያላወቅናቸውን ገጠመኞችና ለውጦች ተከትሎ የሚፈጠሩ ወጭዎችን ሁሉ ፍጹማዊ በሆነ መንገድ ያሟላል ማለት አይደለም:: ባለትዳሮች በሳሎችና በገሃዱ ዓለም ላይ ያሉ እውነታዎችን በማገናዘብ ሕይወታቸውን፣ ትዳራቸውን፣ ቤተሰባቸውንና በአጠቃላይ እንቅስቃሴያቸውን ሁሉ የሚመሩ ኢጋሮች መሆን አለባቸው::

በትዳር ውስጥ ያለው የሕይወት ጉዞ ደግሞ በግትርነት ሳይሆን በተገቢው ጊዜ ተገቢውን ወጭ በማውጣት መሆን ያለበትን ነገር የማድረግንም ብስለትና ውሳኔ ሰጭነትን የሚጠይቅ ኃላፊነት ነው:: የታሰበበት ባጀት መኖር የምናወጣውን ወጭ በዘፈቀደ ሳይሆን በዕቅድ እንድናወጣ ይረዳናል:: ቅድመ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ከአላስፈላጊ ብድር እንድንቆጥብ ያበረታታናል:: በገቢና በወጭ አለመመጣጠን የሚፈጠርን ውጥረት ይቀንሳል:: ላልተጠበቀ ወጭ ዝግጅት እንድናደርግ ያነቃናል:: ንፉግነትን ሳይሆን የታሰበበትን የመስጠት ሕይወት እንድንለማመድ ያበረታታናል:: በትዳራችን መካከል ግልጥነትና መተማመን ይበልጥ እየዳበረና እያደገ የትዳራችን ደህንነት እንዲጠበቅ ሰላም በቤታችን እንዲበዛ ገንቢ አስተዋጾ ያበረከትልናል::

ጥንዶችን አንዱ ለሌላው እንዲታዘዙ ያበረታታል፡፡ ደግሞም አስገዳጅ ሁኔታ ሲፈጠር ወይንም ስናምንበት ዕቅዳችንን እንደ ሁኔታውና እንደ አስፈላጊነቱ እንድንለውጥ ግልጥ መነሻ መሠረት በመሆን ይረዳናል። ቤተሰባችንንም ግልጥ በሆነ ሁለንተናዊ የእድገት ጎዳና ካለንበት የመንፈሳዊ፣ የኢኮኖሚያዊ፣ የማሕበራዊ፣ የትምህርትና የአኗኗር ደረጃ ወደ ቀጣይ ከፍተኛ ደረጃ የምናሳድግበት ሂደት እንዲኖር እድል ይሰጠናል።

በተለይ በውጭ አገር ለምንኖር ሐበሾች በግድሌሽነትና በውድድር መንፈስ የክሬድት ካርድ ተጠቃሚ በመሆን ብድራችን ጨምሮ መውጫ እንዳይቸግረንና ለትዳራችን ግንኙነት ችግር እንዳይሆንብን ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ነው። ከገቢያችን ጋር በማይመጣጠን መንገድ ኑሯችን በብድር ይሸፈናል ብለን በማሰብ በግዴለሽነት ዕዳ ውስጥ መዘፈቅ ቆይቶ ለማንወጣው ከፍተኛ የሆነ የኢኮኖሚ ችግር ተጋላጭ ያደርገናል፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን በሁለንተናዊ ጤንነታችን ላይ የሚፈጥረው ችግርና በትዳራችን ውስጥ የሚፈጥረው የቀውስ በሽታም በቀላሉ የሚፈወስ አይሆንም።

## 4. አንዱ የትዳር አጋር የበለጠ ገንዘብ አባካኝ መሆን

በቅርብ በተጋቡ ባለትዳሮች መካከል ከገንዘብ ጋር ተያይዞ ችግር እንዲፈጠር ከሚያደርጉ ምክንያቶች መካከል በዚህ ርእስ ውስጥ የምንዳስሰው አንዱ አካል በተለያየ ምክንያት የበለጠ ገንዘብ አባካኝ የመሆኑን ጉዳይ ነው። አንዳንድ ጊዜ ከጥንዶቹ አንዳቸው ዋጋቸው ውድ የሆኑ እቃዎችን በመግዛት ማለትም ዕቃው ከሚሰጠው አገልግሎት ይልቅ የእቃው ብራንድ፣ ስምና ዋጋ ውድነት ላይ በማተኮር ከፍተኛ ወጭ የማውጣት ችግር ያለባቸው ይሆናሉ። በአንዳንድ ቤተሰቦችም ዘንድ በየጊዜው ገበያ በመውጣት ውድ ነገር የመግዛት፣ ያዩትንና ያላሰቡበትን ድንገት ወጥተው ገዝተው የመግባት ችግርና ሱስ ያለባቸው ጥንዶች መኖራቸውም የአደባባይ ሚስጥር ነው ቢባል ግነት አይሆንም።

በሌሎች ባለትዳሮች ዘንድ ደግሞ ከማባከን ችግር ጋር በተያያዘ ሊጠቀስ የሚችለው ጉዳይ ምናልባትም ሰዎችን በችግራቸው ለመርዳት ያላቸውን የሚያካፍሉ (የሚሰጡ) የትዳር አጋሮች መኖራቸው ሊሆን ይችላል። ያለንን ለችግረኞች ማካፈል በመልካም ክርስቲያናዊ ስነ-ምግባር በመኖር ክርስቲያናዊ ኃላፊነትን የመወጣት ተግባር ነው፡፡ ነገር ግን ያለንን ለችግረኞች የማካፈል ተግባር መልካም ክርስቲያናዊ ስነ-ምግባር መሆን የሚችለው በእግዚአብሔር ቃል መርህ መሠረት በትክክለኛው መንገድ ሲከናወን ነው፡፡ አንዳንድ ባለ ትዳሮች እንደዚህ ዓይነቱን መልካም ስነምግባር የሚፈጽሙት አቅምን ባላገናዘበና ገደብ የለሽ በሆነ መንገድ ከትዳር ጓደኛቸው ጋር ድብብቆሽ በመጫወትና ከትዳር ጓኛቸው እውቅና ውጭ ለሌሎች ተቸግረዋል ብለው ለሚያስቧቸው ሰዎች በመስጠት ነው፡፡ ይህንን የሚያደርጉት ትዳርን በሚመለከት መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን መርህ በመጣስ የትዳር አጋራቸውን ዋሽተውና አታልለው እንዲሁም ሰርቀው ነው፡፡ ይህን ዓይነት ድርጊት የሚፈጽሙ ባለትዳሮች





ተደራራቢ ጥፋትና ኃጢአት ከመፈጸማቸውም በላይ በትዳር ሕይወታቸው ውስጥ በቀላሉ ሊስተካከል የማይችል ችግር ይፈጥራሉ፡፡

ሰዎችን ለመርዳት የሚፈልጉ በትዳር ውስጥ ያሉ ሰዎች ለእርዳታ ወጭ ማድረግ ባለባቸው ገንዘብ ላይ ከትዳር አጋራቸው ጋር በአንድነት መወሰን ያለባቸው መሆኑን በግዴለሽነት ማለፍ ወይም መርሳትና በግላቸው የሚፈልጉትን ወደ ማድረግ መግባትን ፈጽሞ ማስወገድ አለባቸው፡፡ አባካኝ የሆነውን የትዳር አጋር ለመረዳትና ለመርዳት ጥረት በማድረግ ማለትም ለሌላ ሰው ገንዘብ በመስጠት ሂደትም ውስጥ ሆነ በግዥ ወቅት ስንት እንደምናወጣና በየስንት ጊዜው ግዥ ማከናወን እንዳለብን በመመካከር ከገቢያችን በታች መኖር መቻል ችግሩን ለመቀነስ ያስችላል፡፡ ችግሩ ያለበት የትዳር ጓደኛም እውነታውን በመገንዘብ ራሱን ለማሻሻልና ቤተሰቡን የሚጠቅም አቅጣጫን ተከትሎ ለመኖር ፈቃደኝነት ሊኖረው ይገባል፡፡ የማያቋርጥ ጥረት ማድረግም ይጠበቅበታል፡፡

## 5. ሚዛኑን ባልጠበቀና ታማኝነት በጎደለው መንገድ ቤተሰብን መርዳት

በቅርብ ተጋቢዎች መካከል አንዱ ያለመግባባትና የግጭት ምክንያት የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ነው። ባለትዳሮች ወላጆቻቸውን ባለመተው ወይም በትዳራቸው ውስጥ የቤተሰብን አስተዳደር ምርጫና ውሳኔ በማሳተፍ ለቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ተጋላጭ ይሆናሉ። ይህ ተጋላጭነት ባለትዳሮች የጋራ ውሳኔ በሌለበት፣ ሚዛኑን ባልጠበቀ፣ ግልጥነትና ታማኝነት በጎደለው መንገድ ለቤተሰቦቻቸው በድብቅ የገንዘብና የቁሳቁስ ... ድጋፍ በማድረጋቸው ይፈጠራል፡፡ አስቀድሞ የተፈጠረ ከሆነ ደግሞ ይባባሳል። በድብቅ እርዳታ መቀበላቸውን የሚያውቁ ቤተሰቦችም ይበልጥ በድብቅ መረዳታቸው እንዲቀጥል ዕድሉን የመጠቀም ፍላጎትና ጥረት ሊያሳዩ ይችላሉ። በአድሎና በድብቅ ይደረግ የነበረው እርዳታ በተገለጠ ወቅት የሚፈነዳው የግጭት ደማሚት የሚያካልለው የጥንዶችን ትዳር ብቻ ሳይሆን ወላጆችን ጭምር ሲሆን መተማመን እንዳይኖርም ፈጥሮ ሊያልፍ የሚችለው ችግር በቀላሉ የሚፈታ አይደለም።

## 6. የሚስት በገቢ ባሏን መብለጥና እርሷ ብቻ የቤተሰቡ የገቢ ምንጭ መሆን

ሚስት ከባሏ በገቢ በምትበልጥበት ወይንም ብቸኛዋ የቤተሰቡ የገቢ ምንጭ በምትሆንበት ወቅት ለዘመናት በነገሰው የባህል ተጽዕኖ፣ በቤተሰብና በሌሎች ሰዎች ተጽዕኖ፣ በአመለካከት መዛባት ወይንም ገንዘብ ለሰዎች በሚሰጠው የኃይል የበላይነት ምክንያት በባልና በሚስት መካከል ያለመግባባትና ግጭት ይፈጠራል፡፡ ከባህላችን አንጻር ወንድ ልጅ (ባል) የገቢ ምንጭ በመሆን ቤተሰቡን በማስተዳደር አብዛኛውን የቤተሰቡን አቅርቦት እንዲያሟላና ቤተሰቡን እንዲመግብ ይጠበቅበታል። ነገር ግን ጊዜያዊ ወይም ቋሚ በሆነ ምክንያት የባል ከሥራ መቀነስ፣ ወደ ሌላ ስራ ለመዘዋወር በሽግግር ወቅት ላይ መገኘት፣ በተማረበትና በሰለጠነበት ሙያ ሥራ አለማግኘት፣ የቤተ

ክርስቲያን አገልጋይ በመሆን አነስተኛ በሆነ የቤተ ክርስቲያን ክፍያ ማገልገል፣ ይሠራበት የነበረው መሥሪያ ቤት (ድርጅት) ፈጽሞ መዘጋትና ከሚስት ጋር በትምህርትም ሆነ በደሞዝ አለመመጣጠን በመሳሰሉት ምክንያቶች ባል በሚስቱ በገቢ መበለጥ ወይም የሚስት ብቻ የገቢ ምንጭ የመሆን ክስተት ፈጠራል:: ባልም የሚጠበቅበትን ቤተሰቡን ዋና የገቢ ምንጭ በመሆን የመመገብ ኃላፊነቱን የማይወጣበት ሁኔታ ያጋጥመዋል። በዚህ ወቅት ባል ኃላፊነቴን መወጣት አልቻልኩም በሚል ስሜት የስነ ልቦና ተጽዕኖ ይፈጠርበታል። ጭንቀትና የበታችነት ስሜትም ሊረብሸው ይችላል:: ሚስትም ካደገችበት የባህል ተጽዕኖና ዋና የገንዘብ ምንጭ መሆኗ በውስጧ ከፈጠረው የኩራት ስሜት በመነሳት ባሏን ዝቅ አድርጋ የመመልከት ዝንባሌ ሊኖራት ይችላል::

በተፈጠረው ሁኔታ ምክንያት በቤተሰብ፣ በጓደኞችና ቅርበት ባላቸው ሰዎች ዘንድም ባል አስቀድሞ ይሰጠው የነበረው ክበሬታ እየቀነሰ የሚመጣበት አጋጣሚ ይፈጠራል:: እነዚህ ተደማምረው በሚያስከትሉት አሉታዊ ተጽዕኖ ባል ነጭናጫ፣ ስሜቱ በቶሎ የሚነካ፣ ትካዜ የሚያበዛ፣ ቁጣ የሚቀድመውና መረጋጋት የራቀው ሊሆን ይችላል:: በተቃራኒው ሚስት ደግሞ የቀድሞ ትህትናዋ እየቀነሰ ወደ አዛዢነት፣ ወደ ባለስልጣንነት፣ ከውይይትና የባሏን አሳብ በማድመጥና በማክበር ነገሮችን ከማድረግ ይልቅ ልክ ነው ብላ ያሰበችውን ነገር በራሷ ውሳኔ ወደ መፈጸም ትገባለች:: እነዚህን ነገሮች በተረጋጋና ጤናማ በሆነ አስተዋይነት ማስተካከል ካልቻሉ በጥንዶቹ መካከል የከፋና መራራ አለመግባባትና ግጭት ሊከሰት ይችላል::

በእርግጥ በአሁኑ ወቅት በዘመናዊው ባህል እየተቀረጸ ያለው ትውልድና ከአገር ቤት ውጭ የምንኖር ኢትዮጵያዊያን በዚህ ጉዳይ ላይ ከቀድሞው ትውልድ የተሻለ አመለካከትና አቋም ያለን መሆኑ የማይታበል ሃቅ ነው። የሴቶችም ከወንዶች ባላነሰና በበለጠ ሁኔታ የመማር፣ የመሰልጠንና በሙያቸው በደህና ክፍያ ተቀጥሮ ወይም ሥራ ፈጥሮ የመኖር ባህል እየተለመደ ለመምጣቱ የአይን ምስክሮች ነን። ነገር ግን እንዲህ ዓይነቱን ለውጥ ለመቀበልና ተዋዶና ተቀባብሎ ለመኖር በቂ ዝግጅት አድርገናል ማለት የምንችልበት ደረጃ ላይ ለመድረስ ገና ብዙ ረጅም መንገድ ይጠብቀናል:: ይህ ጉዳይ በየቤታችን በአግባቡ ሊታሰብበት ካልቻለ ግጭት መፈጠሩ አይቀሬ ይሆናል። ይህ ጉዳይ ለባለትዳሮቹ ችግር ባይሆንም እንኳን ሕብረተሰባችን ማለትም የባለትዳሮች ቤተሰብና ጓደኞች የሴቶችን (የሚስቶችን) በገቢ ምንጭ መብለጥና እነርሱ ብቻ የቤተሰቡ የገቢ ምንጭ መሆን መነሻ በማድረግ የተለያዩ ጤናማና ጤናማ ያልሆኑ አስተያየቶችና ቃላቶች እየሰነዘሩ ጥንዶችን በነገር ሊሸነቁጡአቸው ይችላሉ::

ሰዎች የሚናገሯቸው አሽሙሮችና ቀጥተኛ ስድቦች የጥንዶችን ህሊናና ስሜት በመጉዳት፣ ያላሰቡትን ነገር እንዲያስቡ በማንቃትና ለጠብ በሚያነሳሳ መንገድ ስሜታቸውን በመቀስቀስ ለግጭት ሊዳርጓቸው ይችላሉ። በሕበረተሰባችን ዘንድ አንዱ ስለሌላው ትዳር በመልካምም ሆነ በመጥፎ ስሜት መነጋገር፣ ጣልቃ መግባትና





አስተያየት መስጠት የተለመደ ነው። በዚህ ልምምድ ሂደት ውስጥ አፍራሽ ተጽእኖዎችን በመቀነስና በማስወገድ ራስንና የትዳርን ግንኙነት በሰላም ጠብቆ መኖር በሳልነት ነው። እንኳን በብዙ ነገር ተበልጠው ያለዚያም ተሽለው ተገኝተውና እንዲሁ ከባህርያቸው ነገር የሚተርጉሙና እንዲተረጎም በማድረግ የሚናገሩ፣ ነገር የሚያካብዱና የሚያቃልሉ፣ ስሜታቸው ቶሎ የሚነካና የሌላውን ስሜት የሚነኩ፣ ያላቸውን ንብረት በመቆጣጠር ራስ ተኮር የባለቤትነት ስሜት የሚገዛቸውና የባለቤትነት ስሜት የማይሰማቸው፣ በነገሮች ሁሉ የሚያሽማቅቁና በሁኔታዎች የሚሽማቀቁ ... ሁለት ተቃራኒ ገጽታዎች በጥንዶቹ የትዳር ሕይወት መፈራረቃቸው የተለመደ ነው:: ሁኔታውም የትዳር ግንኙነታቸውን ደስታ የራቀውና ውጥረት የበዛበት እንዲሆን ሊያደርገው ይችላል።

በተፈጠሩት ውጥረቶች ምክንያትም ጥንዶቹ የጋራ ከሆነው የባንክ አካውንት በተጨማሪ በግል ድብቅ የባንክ አካውንት በመክፈት ገንዘብን የማስተዳደር መንገዶችን መከተል ሊጀምሩ ይቻላሉ። አንዱ የሌላውን ገቢና ወጭ አለማወቅ፣ የማያገባው ሆኖ መቆጠርና ተጠያቂነት የሌለበት የገንዘብ አወጣጥ ሂደት ይከተላል። እንዲህ ዓይነት ኑሮ የሚኖሩ ጥንዶች በመብዛታቸው በሌሎች ነገሮች ብቻ አንድነታቸውን እየገለጡ በገንዘባቸው ላይ አንድ ያልሆኑ ባለትዳሮች ቁጥራቸው እየጨመረ ነው። በተለይ አሁን ስልጣኔንና እድገትን በአግባብ ባለመያዝ፣ ባልና ሚስትም እኩል ሠርተው የገቢ ምንጭ ባለቤት መሆናቸውን በአግባቡ ለማስተናገድ ባለመዘጋጀታቸውና ከበፊቱ ይልቅ በዓለም ላይ ብዙ ምርጫና ውሳኔ እየበዛ መምጣቱ በቤተ ክርስቲያን እንኳን ፍች እየበዛ እንዲመጣ አፍራሽ ተጽዕኖ በማሳደሩ ችግሩ እየተባባሰ ይገኛል። የችግሩ መባባስም የጋራ የባንክ አካውንት በመክፈት በጋራ ገቢንና ወጭን በመቆጣጠር ለጋራ ጥቅም አብሮ መትጋት እየጠፋ እንደ እድር፣ እቁብና በመዋጮ አንድን ወጭ እንደሚሸፍኑ ጓደኞች በመዋጮ በመኖር የክርስቲያኖች ትዳር የአንድነት መገለጫ የሆነውን ገንዘብን በመለያየት ኑሮን ለማሸነፍ ጥረት የማድረጉ ሂደት ቤተሰብን የሚያመሰቃቅል የግጭት ምክንያት እየሆነ ነው::

## 7. ከጋብቻ በፊት የነበራቸውን ወይም ያፈሩትን ንብረት የጋራ እንዳይደለ በማሳወቅ መፈራረም

ወደ ጋብቻ ውሳኔ በሚመጡበትና በሚያገቡበት ወቅት ሌላው የግጭት ምክንያት በአንዳንድ ባለትዳሮች መካከል የጋብቻ ውል ሲፈረም ቀደም ብሎ ያፈሩት ወይም በውርስ ያገኙት ንብረት የጋራ እንዳይደለ ነገር ግን ከተጋቡበት ጊዜ አንስቶ በጋራ ያፈሩት ገንዘብና ንብረት ብቻ የጋራ እንደሚሆን በመተማመን መፈራረም ነው። ከጋብቻ በፊት በአጭር ጊዜ በሥራና በንግድ ውጤታማ በመሆን ያፈሩት፣ ከቤተሰብና ከሌሎች ቅርብ ከሆኑ ግለሰቦች በውርስ ያገኙት ንብረት ሲኖር፣ ከጥንዶቹ አንዱ ወይም ሁለቱም አስቀድመው ሌላ ጋብቻ የነበራቸውና ከቀድሞ የትዳር አጋሮቻቸው ጋር በመሆን ያፈሩት ሀብት ሲኖርና ከቀድሞው ትዳራቸው የተወለዱ ልጆች በውርሱ

የተካተቱ ሲሆን ወ.ዘ.ተ የልጆችን መብት ለመጠበቅ ወይም 'ንብረት'ን ለመጠበቅ ሲባል እንዲህ ዓይነቱን እርምጃ ለመውሰድ ይገደዳሉ።

እንዲህ ዓይነቱን አስቀድሞ መፈራረም የሚፈልጉበት ምክንያት አላቸው፡፡ የመጀመሪያው ምክንያታቸው ባላቸው የግል የንግድ ድርጅት ክስረት እንዳይገጥማቸውና በክስ ወደ ሌላ ክስረት እንዳይገቡ በማሰብ ነው። ሌላው ወደ ትዳር የሚገቡ ሰዎች ይህን የሚያደርጉበት ምክንያት በትዳር ውስጥ ለትዳር አጋር ታማኝ ባለመሆን በዝሙትና እንዲሁ የትዳርን አጋር ትቶ በመሄድ ወቅት ከሚፈጠር ችግር ንብረትን ለመከላከልና ለመጠበቅ ይረዳል ብለው ስለሚያስቡ ነው። አንዳንድ ሰዎች ከሚያገቡት ሰው ይልቅ ያላቸውን ንብረት በማየት ከእነርሱ ዕድሜና ስብዕና ጋርና ሌሎች ከየራሳቸው መለኪያ ጋር የማይመጣጠን ሁኔታ እንዳለ እያወቁና እየታወቀ እንዲሁ በጊዜው በገንዘብ በታወረ አእምሯቸው ወደ ትዳር የሚገቡና ከፉ ምኞታቸውን ለመፈጸም የሚፈልጉ ሰዎች ከሚፈጥሯቸው ችግሮች ራሳቸውን ለመከላከል በማሰብ ይህን ያደርጋሉ።

ከእንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ጋር የተያያዘውን ችግር በሁለት አቅጣጫ ልንተረጉመው እንችላለን። የመጀመሪያው ባለሃብት የሆነው አካል በገንዘቡ የፈለገውን ማድረግ እንደሚችልና የትዳር አጋር መግዛትና መቆጣጠር እንደሚችል በማሰብና ለእርሱ ጥሩ አጋር የምትሆን አቻ ሚስት በማግባት ፋንታ ሚስትን ባለሃብቷ ሴት ከሆነች ደግሞ ባልን ከብዙ ሰዎች መካከል መርጠው ለማግባትና የግል ንብረታቸው ለማድረግ በማሰብ የትዳር ጓደኛ ግዥ መፈጸማቸው ነው። ለእንዲህ ዓይነቱ ችግር አንዳንድ በውጭ ሃገራት የሚኖሩ ሀበሻ አገር ቤት በመሄድ ባጭር ጊዜ የትዳር ጓደኛ ፈልጎ ወይም አስፈልጎ ጋብቻ በመፈጸም ትዳርን ለመመስረት የሚደረጉ ጥረቶች በምሳሌነት ሊጠቀሱ ከሚችሉት መካከል ዋነኛዎቹ ናቸው። ተፈልጎ የተገኘው ወገን ደግሞ ገንዘብና ንብረትን ወይም በትዳር ሰበብ ወደ ውጭ አገር መውጣትን ብቻ በማየትና ሁኔታዎችን በማመቻቸት ራሱን ለሽያጭ ያቀርባል፡፡ በዚህ መንገድ የሚደረጉ ትዳሮች በአብዛኛው ስጋት የሞላባቸው የትዳር ስምምነቶች በመሆን መቀጠላቸውና ስጋቶቹም የተመሠረተውን ትዳር በአጭር ጊዜ እንዲፈርስ የሚያደርጉ የጤነኛ ትዳር እንቅፋቶች መሆናቸውን ለአንባቢ ለማስረዳት መሞከር ለቀባሪ እንደማርዳት የሚቆጠር ይመስለኛል።

ሌላው ባለጠጋ ወይም ባለንብረት የሆኑ ሰዎች በሚያገቡበት ወቅት ለትዳር የሚያስቧቸውን ወገኖች ለትዳር የሚያነሣሣቸው ፍቅር እንጅ ገንዘብ እንዳይሆን ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ ሂደቱ በትክክለኛው መንገድ ካልተፈጸመ እንዲህ ዓይነቱ ድርጊት በአብዛኛው ውሎ አድሮ ጥንዶችን ለፍች የሚያነሳሳና የሚያዘጋጅ ነው። በሌላ በኩል ባለሃብት የሆነው የትዳር ጓደኛ ደግሞ በአብዛኛው የገንዘብ አቅም ለሌለው የትዳር አጋር የማያስብ እንዲሁም የማይጠነቀቅ እንዳይሆንና ራስ ወዳድነት የተሞላው





አካሄድ በመሄድ በትዳር ውስጥ ለሚፈጠር ስምምነት እንቅፋት እንዳያስቀምጥ ኢኮኖሚያዊ ለውጥን ለማስተናገድ የማይፈቅድ፣ መበለጥን የሚፈራና ግትር አቋም ያለው መሆንና አለመሆኑ ላይ ራሱን መመርመርና ማስተካከል ይጠበቅበታል። ክርስቲያናዊ ትዳር ሁለንተናዊ መስጠት ያለበት የዕድሜ ልክ ቃል-ኪዳናዊ ትሥሥር መሆኑን ከማሳየትና ከማስለመድ ይልቅ ጊዜያዊ የሆኑ ጥቅሞችና መብቶች ላይ በማተኮር ጊዜያዊ ኮንትራትና ስምምነት እንዳናደርገው በትዳር ውስጥ ያለን ክርስቲያኖች ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል በተገራና በሰለጠነ አስተሳሰብና ስብዕና የተለወጠ ማንነት ሊኖረን ይገባል።

## III. በገንዘብና በንብረት ምክንያት ለሚፈጠሩ ግጭቶች መፍትሔዎች

### 1. መቀየር፡-በገንዘብ ላይ ያለንን ትክክለኛ ያልሆነ አስተሳሰብና እምነትን መቀየር

በክርስቲያን ባለትዳሮች መካከል ገንዘብን በጋራ ማስተዳደርና መጠቀም ጥንዶቹ አንድነታቸውን ከሚገልጹበት መንገድ አንዱ ነው። ገንዘብ የምንጠቀምበት መሣሪያ እንጂ በመኖሩ ብቻ ደስታ የሚፈጥር የደስታ ምንጭ እንደሆነ አድርጎ ማሰብንና ገንዘብን አግባብ በአልሆነ መንገድ መውደድን ማስወገድ ተገቢ ነው። ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ስር መሆኑን በመገንዘብ አእምሮንና ልብን መጠበቅ ከተለያየ ክፉ አደጋ ሕይወታችንና ትዳራችንን ይጠብቃል። መጽሐፍ ቅዱስ *"ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነውና፥ አንዳንዶች ይህን ሲመኙ፥ ከሃይማኖት ተሳስተው በብዙ ሥቃይ ራሳቸውን ወጉ።"* /1ኛጢሞ 6፡ 10/ እያለ እንደሚመሰክረውም ሕይወታችንንና ትዳራችንንም ብዙ ዓይነት ስቃይ ውስጥ ይጥለዋል፡፡ የእግዚአብሔር ቃል በዕብ 13፡5 *"አካሄዳችሁ ገንዘብን ያለ መውደድ ይሁን፥ ያላችሁም ይብቃችሁ፤ እርሱ ራሱ። አልለቅህም ከቶም አልተውህም ብሎአልና፤"* በማለት የሚሰጠውን ምክር በመስማትና በመታዘዝ ክርስቲያን ባለትዳሮች ትዳራቸውንና አካሄዳቸውን ገንዘብን ባለመውደድ ሊመሩትና ሊያስተዳድሩት ይገባል፡፡

ገንዘብን መውደድና ለገንዘብ ባሪያ መሆን የክርስቲያን ባለትዳር ባህርይ ሊሆን እንደማይገባ መጽሐፍ ቅዱስ በሌሎች የቅዱሳት መጽሐፍት ክፍሎችም አስረግጦ ይመክረናል /ማቴ. 6፡24/። በመጨረሻው ዘመን ሰዎች ስለሚወዱት ነገር ሲናገር *"... ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ ... ገንዘብን የሚወዱ..."* እንደሚሆኑ ሐዋሪያው ጳውሎስ ሁላችንን ያስጠነቅቃል /2ኛጢሞ. 3፡ 2/። ደግሞም እንዲሁ ሳይሠሩ በሰው ትከሻ ለመኖር መፈልግና ጥረት ማድረግም ሌላው ለውጥ የሚያሻው ክርስቲያናዊ ያልሆነ አመለካከት መሆኑን *"ደግሞ ከእናንተ ጋር ሳለን። ሊሠራ የማይወድ አይብላ ብለን አዘናችሁ ነበርና። ሥራ ከቶ ሳይሠሩ፥ በሰው ነገር እየገቡ፥ ያለ ሥርዓት ከእናንተ ዘንድ ስለሚሄዱ ስለ አንዳንዶች ሰምተናልና። እንደነዚህ ያሉትንም በጸጥታ እየሠሩ የገዛ እንጀራቸውን ይበሉ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እናዛቸዋለን እንመክራቸውማለን። እናንተ ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ መልካም ሥራን ለመሥራት አትታክቱ።"* /2ኛተሰ.3፡ 10-13/ የሚለው እውነት ያረጋግጥልናል፡፡

## 5. መኖር፡- በጋራ በመነጋገርና በመግባባት መኖር

አለመግባባትንና ግጭትን ለመቀነስ በጋራ ለኑሯችን ስንት ማውጣት እንደሚኖርብን በመነጋገር ገቢና ወጭን መቆጣጠር ተገቢ ነው። ሥርተን ከምናስገባው ያነሰ የወጭ ባጀትን ማቀድና ለወጭአችን ገቢያችንን መሠረት ያደረገ ገደብ (ልክ) ማስቀመጥ ባቀድነው ለመኖርና በዕቅዳች ለመቀጠል በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ በጋራ ራሳችንን በዚህ መርህ ለመኖር በማስለመድ መግባባትን የትዳራችን ጣዕም ልናደርገው ይገባል፡፡ ለተለየ ለውጥ ከፍት በመሆን ወጭን በመቆጣጠር ሊፈጠር ያለን ውጥረትና ግጭት መቀነስ ተገቢ ነው። በጋራ በመነጋገር ባጀትን መበጀትን መለማመድ፣ ብድርን ለማቆም ዝርዝር ማውጣት፣ ስልቶችን መቀየስና በቀላሉ ወይም አባካኝ በሆነ መንገድ ወጭን ማውጣትን ለማስወገድ የጋራ ስምምነት ላይ መድረስ የእርስ በርሳችንን ደስታና የትዳራችንን መልካም ግንኙነት ለመጠበቅ ይረዳል።

እንደገና በፈተና ላለመውደቅ ገንዘብን እንደ አስፈላጊ መሳሪያ እንጅ እንደ ደስታ ፈጣሪ አለመመልከት፣ ወጭን በመቀነስ ሂደት እድገትን መጠበቅ /ሮሜ 5፡ 3-4/፣ በፈተና ለሚወድቀው የትዳር አጋር ይቅርታን እየሰጠን መተማመንን ማዳበር፣ አስፈላጊ የሆኑ ወጭዎቻችንን መጻፍ፣ ያለ ዓላማ ማውጣትን ማስወገድ፣ ገቢያችንን ከወጭአችን ጋር ትክክለኛ በሆነ መንገድ ማወዳደር፣ አቅማችንን ግምት ውስጥ ያስገባ የዕቃ ግዥ ማካሄድና ውጥረትንና ግጭትን በመቀነስ የትዳርን ደስታ መጨመር አስፈላጊ ነው።

## 6. መሥራት፡- ሥራን ያለመውደድና የመናቅ ልማድን ማስቀረት

እንደ ክርስቲያን ባለትዳር እርስ በእርስ በኑሮ መደጋገፍ አንዱ የባለትዳሮች ኃላፊነት ነው። አንደኛው የትዳር አጋር ሥራ ባይኖረውና ሥራን የሚጠላ ሳይሆን መሥራት የማይችልበት ሁኔታ ላይ የሚገኝ ቢሆን ሌላው የትዳር አካል አእምሮውን በበጎ አመለካከት በማነጽ የተፈጠረውን ክፍተት በትህትናና በኃላፊነት ስሜት መሸፈን ይጠበቅበታል፡፡ ሥራ መሥራት ባለመቻልና ሥራ ባለመውደድ መካከል ከፍተኛ የትርጉም ልዩነት አለ። ሥራ መሥራት አለመቻል በጤንነት ችግር፣ ለጊዜው ሥራ ባለማግኘትና ከሥራ በመውጣት ምክንያት ሊፈጠር የሚችል አንዱ የግለሰቦች፣ የባለትዳሮች፣ የቤተሰብና የማሕበረሰብ ችግር ነው። እንዲህ ዓይነት ችግር በሚፈጠርበት ጊዜ ግለሰቦች፣ ባለ ትዳሮችና በአጠቃላይ ክርስቲያኑ ማሕበረሰብ ወይም በአጠቃላይ ማሕበረሰቡ ጭምር አንዱ የሌላውን ሸክም የመጋራትና የመደጋገፍን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርህ መተግበርን መለማመድ ይኖርብናል፡፡ ነገር ግን ብዙ የሥራ አማራጮች እያሉ ሥራ መሥራትን ባለመውደድ ብዙ ሰበቦችን እየደረደሩ ራስን ሥራ ከመሥራት ተፈጥሯዊ፣ ክርስቲያናዊ፣ ግላዊ፣ ቤተሰባዊና ማሕበራዊ ኃላፊነት ማራቅ በየትኛውም መለኪያ ሊበረታታ የማይችል መለወጥ ያለበት ችግር ነው፡፡ ይህ ችግር በትዳር ውስጥ የከፋ አለመግባባትና ግጭት ከሚፈጥሩ ዋና ምክንያቶች መካከል አንዱ ነው፡፡





ብዙ የሥራ ዕድሎች እያሉ ለመሥራት ፈቃደኛ አለመሆንና ሥራን አለመውደድ በትዳር ውስጥ የቀውስ መፈጠር መንስኤ ከመሆኑም ባሻገር መጽሐፍ ቅዱስ የሚቃወመው ተግባርም ነው። *"ደግሞ ከእናንተ ጋር ሳለን። ሊሠራ የማይወድ አይብላ ብለን እዘዛችሁ ነበርና።ሥራ ከቶ ሳይሠሩ፥ በሰው ነገር እየገቡ፥ ያለ ሥርዓት ከእናንተ ዘንድ ስለሚሄዱ ስለ አንዳንዶች ሰምተናልና። እንደነዚህ ያሉትንም በጸጥታ እየሠሩ የገዛ እንጀራቸውን ይበሉ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እናዛቸዋለን እንመክራቸውማለን። እናንተ ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ መልካም ሥራን ለመሥራት አትታክቱ።"* /2ኛተሰ 3፡ 10-13/፡፡ ስለዚህ ሥራን አለመውደድ ሊወገዝና ከማናችንም በተለይም የትዳርን ኃላፊነት ከተሸከምን ወገኖች ሕይወት ፈጽሞ ሊወገድ የሚገባው ልምምድ ነው።

## 7. መጣር፡- ለቁሳቁስ መጨነቅን ለማስወገድ መጣር

ከሌሎች ሰዎች ጋር መወዳደርና እኩል ለመሆን ከተቻለም በልጦ ለመገኘት የባልጀራን ገንዘብና ንብረት መመኘት የተከለከለ መሆኑን *"የባልጀራህን ሚስት አትመኝ የባልንጀራህንም ቤት እርሻውንም ሎሌውንም ገረዱንም በሬውንም አህያውንም፥ ከባልንጀራህ ገንዘብ ሁሉ ማናቸውንም አትመኝ።"* /ዘዳ 5፡ 21/ በማለት ቃለ እግዚአብሔር ይነግረናል። ከፉ ምኞት፣ ጣዖትንም ማምለክ የሆነ መጎምጀት ከሕይወታችን ሊወገድ የሚገባው ነው /ቆላ 3፡ 5/፡፡ አረማመዳችንን ገንዘብን ባለመውደድ ማድረግ አለብን /ዕብ 13፡ 5/፡፡ የሰው ሕይወት በገንዘቡ ብዛት አይደለምና ከመጎምጀትም ሁሉ በመራቅ ራስን ከኃጢአት በመጠበቅ /ሉቃ 12፡ 15/ ስለሚበላና ስለሚለበስ እንዳንጨነቅ ቃሉ ይመከረናል /ማቴ 6፡ 25፣ 31፣ 34/፡፡ በዚህ እውነት ላይ በመመሥረት ለቁሳቁስ ከመጨነቅ ይልቅ ትዳር ከገንዘብ የሚበልጥ ኃላፊነት መሆኑን መረዳት አስፈላጊ ነው፡፡ በከፉ ምኞት ላለመጠመድ ያለኝ ይበቃኛል የሚል መርህን መከተል ደግሞም በክፉ ምርጫና ውሳኔ እንዳንወሰድ የከበረውን ከተዋረደው በመለየት መምረጥ አስተዋይነት ነው፡፡ የገንዘብ ፍቅር ለሌሎች ከፉ አመጾች እልፎ የመስጠት መንገድ መሆኑን በመገንዘብ ከዚህ መራቅ ጠቢብነት ነው፡፡ በአጠቃላይ ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብፁህ ነው ለሚለው አምላካዊ መርህ በመገዛት መስጠትና ማካፈልን መልመድ፣ለጌታና ለትዳር አጋር ፍቅር መጠንቀቅ ላይ በማተኮር በማግኘትና በማጣት ውስጥም ታማኝ ልንሆንለት የገነባነውን የጋብቻ ቃል ኪዳን ማሰብና መጠበቅ የክርስቲያን ባለትዳሮች የሕይወት ዘመን ኃላፊነት ነው።

## ለጥንዶች በግላቸውና በቡድን ለማጥናት የሚረዷቸው የውይይት ጥያቄዎች

## የምዕራፍ ስምንት (8)

## የውይይት ጥያቄዎች

1. በገንዘብና በንብረት ላይ ያላችሁን የአይታ ልዩነትና አንድነት በመዘርዘር ተወያዩበት::
2. በገንዘብና በንብረት ላይ ያላችሁን ልዩነት ለማጥበብና አንድነታቹህ ላይ በጋራ አጠናክሮ ለመቀጠል ምን ማድረግ አለብን ትላላችሁ?
3. የጋራ የሆነ ገንዘብና ንብረት በፍጹም ግልጥነትና ነፃነት እየተጠቀማችሁ ነውን? ካልሆነ ችግሩ ምንድን ነው?
4. መጽሐፍ ቅዱስ ከገንዘብና ከንብረት ይልቅ ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጣቸውን የከበሩ ነገሮች በመዘርዘር ተወያዩባቸው::
5. እንደ ክርስቲያን ባለትዳር ገንዘብን በጋራ እንዴት እንደምታስተዳድሩና እንደምትጠቀሙበት በፍጹም ግልጥነት፣ ነፃነት በተሞላውና የለውጥ እርምጃ ለመውሰድ በተዘጋጀ አቋም ተወያዩ::
6. በእናንተ ቤት ከገንዘብና ከንብረት ጋር ተያይዞ የተፈጠረና ሊፈጠር የሚችል ግጭት አለን? ካለ በምን ምክንያት ተፈጠረ? ግጭቱን ለመፍታትስ ምን እርምጃ መውሰድ አለብን ትላላችሁ?
7. በገንዘብና በንብረት ምክንያት በትዳራችሁ ግጭት እንዳይፈጠር አስቀድሞ የመከላከያ እርምጃ ለመውሰድ ከወዲሁ በመመካከር ተግባራዊ እርምጃ ለመውሰድ አቅዱ::





# ምዕራፍ ዘጠኝ(9)

# የግብረ ስጋ ግንኙነት

## I. የግብረ ስጋ ግንኙነት ምንነት በትዳር ውስጥ

የግብረ ስጋ ግንኙነት ወይም ሩካቤ ስጋ ማለት ባለትዳር በሆኑ ጥንዶች መካከል ማለትም በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል ለጠለቀ ግንኙነት፣ ለስሜት እርካታና ልጅን ለመውለድ የሚደረግ አካላዊ ወይም ወሲባዊ ግንኙነት ነው:: የግብረ ስጋ ፍላጎትን በማሟላት ፍቅርን የመሥራት ወይም የመገንባት ሂደት ነው። በትዳር በኩል የሚደረግ የግብረ ስጋ ግንኙነት የከበረ፣ ንጹህ፣ አርኪና ለባለትዳሮች የተፈቀደ ነው። (ዕብ13፡4) በክርስቲያን ባለትዳሮ መካከል ችግሮችና አለመግባባቶች እንዲፈጠሩ ከሚያደርጉ ምክንያት አንዱ በግብረ ስጋ ግንኙነት አለመጣጣምና አለመርካት ወይም መልካም የሆነ ግንኙነት አለመኖር ነው። በግብረ ስጋ ግንኙነት አለመጣጣም ራሱን የቻለ ያለመግባባት መንስኤ መሆኑ ብቻ ሳይሆን በትዳር መካከል የሚፈጠሩ የተለያዩ ችግሮችን የሚያባብስ አቀጣጣይ የመሆን ሚናም ይጫወታል:: በግብረ ስጋ ግንኙነት አለመጣጣም የሚፈጠሩ ችግሮች ግለት ቶሎ እንዳይበርድ የሚያደርግና ቀስ በቀስም የትዳርን ህልውና የሚያጠፉ የተዳፈነ እሳት ሊሆን ይችላል።

ከባህላችን ተጽዕኖ የተነሳ በትዳር ውስጥ ፍላጎታችንና ችግራችንን በፍጹም ግልጥነት የማናወራበትና የማንወያይበት ጉዳይ ቢኖር የግብረ ስጋ ግንኙነት ነው። የጋብቻ አስተማሪዎችም ሆንን አማካሪዎች እንደ ሌሎች ችግሮች በድፍረት የማናስተምርበትና የማናማክርበት ርዕሰ ጉዳይ ከመሆኑ የተነሳ ችግሩ ከመቼውም በበለጠ እየጨመረና እየተባባሰ በመምጣቱ ብዙዎች ለአለመግባባት፣ ለመለያየትና ለፍች ተጋላጭ እንዲሆኑ እያደረገ ይገኛል።

በትዳር ላይ የሚፈጠር የግብረ ስጋ ግንኙነት አለመጣጣም ችግር ጥንዶቹ ሊያስተካክሉት ፍላጎት ካላቸውና ተገቢ ጥረት ካደረጉ በሂደት ሊቀንስ ይችላል:: እንደገናም በተለያዩ እርዳታዎችና ሕክምናዎች የመሻሻልና የመስተካከል ሁኔታዎች ሊፈጠሩ እንደሚችሉ ልንገነዘብ ይገባል። ያላገቡና ሊያገቡ እየተዘጋጁ ያሉ እንዲህ ዓይነቱን ችግር በመፍራት ከጋብቻ በፊት መሞካከርና ወሲብ መፈጸም ዝሙት የሆነ ኃጢአት እንደሆነ ሊያውቁት ይገባል። በትዳር ውስጥ የግብረ ስጋ ግንኙነት ፍላጎትና ድርጊት አንዱ የጋብቻ ክፍል እንጂ የትዳር ሁሉ ነገር አድርገን ከማሰብ መቆጠብና ሌላው የትዳር ገጽታ የሚጠይቀውን የሁለትዮሽ መሰጠት፣ መተሳሰብና መረዳዳት መዘንጋት አይገባንም። በሌሎች ጉዳዮች ላይ ስንተሳሰብና ስንረዳዳ በግብረስጋ ግንኙነት ጊዜ ወደ መጣጣም መምጣት የሚያስችለንን መልካም ስሜት መፍጠርና ማሳደግ እንችላለን::

ከችግሩ ጥልቀት፣ አሳሳቢነትና በክርስቲያኖች ትዳር ላይ ከሚፈጥረው አሉታዊ ተጽዕኖ የተነሳ እንደ ባለትዳር በግልጥነት ልንነጋገርበት ይገባል። በርዕሰ ጉዳዩ ላይ

## ለጥንዶች በግላቸውና በቡድን ለማጥናት የሚረዷቸው የውይይት ጥያቄዎች

## የምዕራፍ ስምንት (8)

## የውይይት ጥያቄዎች

1. በገንዘብና በንብረት ላይ ያላችሁን የእይታ ልዩነትና አንድነት በመዘርዘር ተወያዩበት::
2. በገንዘብና በንብረት ላይ ያላችሁን ልዩነት ለማጥበብና አንድነታቹህ ላይ በጋራ አጠናክሮ ለመቀጠል ምን ማድረግ አለብን ትላላችሁ?
3. የጋራ የሆነ ገንዘብና ንብረት በፍጹም ግልጥነትና ነፃነት እየተጠቀማችሁ ነውን? ካልሆነ ችግሩ ምንድን ነው?
4. መጽሐፍ ቅዱስ ከገንዘብና ከንብረት ይልቅ ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጣቸውን የከበሩ ነገሮች በመዘርዘር ተወያዩባቸው::
5. እንደ ክርስቲያን ባለትዳር ገንዘብን በጋራ እንዴት እንደምታስተዳድሩና እንደምትጠቀሙበት በፍጹም ግልጥነት፣ ነፃነት በተሞላውና የለውጥ እርምጃ ለመውሰድ በተዘጋጀ አቋም ተወያዩ::
6. በእናንተ ቤት ከገንዘብና ከንብረት ጋር ተያይዞ የተፈጠረና ሊፈጠር የሚችል ግጭት አለን? ካለ በምን ምክንያት ተፈጠረ? ግጭቱን ለመፍታትስ ምን እርምጃ መውሰድ አለብን ትላላችሁ?
7. በገንዘብና በንብረት ምክንያት በትዳራችሁ ግጭት እንዳይፈጠር አስቀድሞ የመከላከያ እርምጃ ለመውሰድ ከወዲሁ በመመካከር ተግባራዊ እርምጃ ለመውሰድ አቅዱ::





# ምዕራፍ ዘጠኝ(9)

# የግብረ ስጋ ግንኙነት

## 1. የግብረ ስጋ ግንኙነት ምንነት በትዳር ውስጥ

የግብረ ስጋ ግንኙነት ወይም ሩካቤ ስጋ ማለት ባለትዳር በሆኑ ጥንዶች መካከል ማለትም በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል ለጠለቀ ግንኙነት፣ ለስሜት እርካታና ልጅን ለመውለድ የሚደረግ አካላዊ ወይም ወሲባዊ ግንኙነት ነው:: የግብረ ስጋ ፍላጎትን በማሟላት ፍቅርን የመሥራት ወይም የመገንባት ሂደት ነው። በትዳር በኩል የሚደረግ የግብረ ስጋ ግንኙነት የከበረ፣ ንጹህ፣ አርኪና ለባለትዳሮች የተፈቀደ ነው። (ዕብ13:4) በክርስቲያን ባለትዳሮ መካከል ችግሮችና አለመግባባቶች እንዲፈጠሩ ከሚያደርጉ ምክንያት አንዱ በግብረ ስጋ ግንኙነት አለመጣጣምና አለመርካት ወይም መልካም የሆነ ግንኙነት አለመኖር ነው። በግብረ ስጋ ግንኙነት አለመጣጣም ራሱን የቻለ ያለመግባባት መንስኤ መሆኑ ብቻ ሳይሆን በትዳር መካከል የሚፈጠሩ የተለያዩ ችግሮችን የሚያባብስ አቀጣጣይ የመሆን ሚናም ይጫወታል:: በግብረ ስጋ ግንኙነት አለመጣጣም የሚፈጠሩ ችግሮች ግለት ቶሎ እንዳይበርድ የሚያደርግና ቀስ በቀስም የትዳርን ህልውና የሚያጠፋ የተዳፈነ እሳት ሊሆን ይችላል።

ከባህላችን ተጽዕኖ የተነሳ በትዳር ውስጥ ፍላጎታችንና ችግራችንን በፍጹም ግልጥነት የማናወራበትና የማንወያይበት ጉዳይ ቢኖር የግብረ ስጋ ግንኙነት ነው። የጋብቻ አስተማሪዎችም ሆንን አማካሪዎች እንደ ሌሎች ችግሮች በድፍረት የማናስተምርበትና የማናማክርበት ርዕስ ጉዳይ ከመሆኑ የተነሳ ችግሩ ከመቼውም በበለጠ እየጨመረና እየተባባሰ በመምጣቱ ብዙዎች ለአለመግባባት፣ ለመለያየትና ለፍች ተጋላጭ እንዲሆኑ እያደረገ ይገኛል።

በትዳር ላይ የሚፈጠር የግብረ ስጋ ግንኙነት አለመጣጣም ችግር ጥንዶቹ ሊያስተካከሉት ፍላጎት ካላቸውና ተገቢ ጥረት ካደረጉ በሂደት ሊቀንስ ይችላል:: እንደገናም በተለያዩ እርዳታዎችና ሕክምናዎች የመሻሻልና የመስተካከል ሁኔታዎች ሊፈጠሩ እንደሚችሉ ልንገነዘብ ይገባል። ያላገቡና ሊያገቡ እየተዘጋጁ ያሉ እንዲህ ዓይነቱን ችግር በመፍራት ከጋብቻ በፊት መሞካከርና ወሲብ መፈጸም ዝሙት የሆነ ኃጢአት እንደሆነ ሊያውቁት ይገባል። በትዳር ውስጥ የግብረ ስጋ ግንኙነት ፍላጎትና ድርጊት አንዱ የጋብቻ ክፍል እንጂ የትዳር ሁሉ ነገር አድርገን ከማሰብ መቆጠብና ሌላው የትዳር ገጽታ የሚጠይቀውን የሁለትዮሽ መስጠት፣ መተሳሰብና መረዳዳት መዘንጋት አይገባንም። በሌሎች ጉዳዮች ላይ ስንተሳሰብና ስንረዳዳ በግብረስጋ ግንኙነት ጊዜ ወደ መጣጣም መምጣት የሚያስችለንን መልካም ስሜት መፍጠርና ማሳደግ እንችላለን::

ከችግሩ ጥልቀት፣ አሳሳቢነትና በክርስቲያኖች ትዳር ላይ ከሚፈጥረው አሉታዊ ተጽዕኖ የተነሳ እንደ ባለትዳር በግልጥነት ልንነጋገርበት ይገባል። በርዕሰ ጉዳዩ ላይ

ትምህርትና ምክር ሊሰጥበትና ባለትዳሮች የሆንን አንዱ ሌላውን በመረዳት፣ በመተሳሰብና በመጣጣም አንድነታችንና የጠለቀ ግንኙነታችንን እያጠናከርን ልንኖር ይጠበቅብናል። በቅርብ የተጋቡ ተጋቢዎች መካከል በግብረ ስጋ ግንኙነት ጋር በተያያዘ የሚፈጠሩ ችግሮችንና መፍትሔዎቻቸውን መዳሰስ በትዳር ውስጥ በዚህ ሰበብ የሚፈጠሩ ችግሮችን መቀነስ የሚያስችሉ መርሆዎችን መዳሰስ የዚህ ምዕራፍ ዋና ትኩረት ነው።

## II. በክርስቲያን የትዳር ሕይወት የግብረ ስጋ ግንኙነት (ሩካቤ ስጋ) ዓላማ

### 1. በትዳር ውስጥ ያለውን ግንኙነት ጥልቀቱንና አንድነቱን ለመገንባት /ዘፍ 2፡ 24-25፣ መዝ 7፡6-12/

ከእግዚአብሔር ቃል እንደምንረዳው በትዳር ውስጥ ያለው የግብረ ስጋ ግንኙነት አንደኛው ዓላማው በባልና በሚስት መካከል ያለው ግንኙነት ጥልቀት እንዲኖረውና አንድነታቸው ይበልጥ እንዲጠናከር ማድረግ ነው። በትዳር መካከል ያለውን ግንኙነት ምን ያክል የጠነከረ ግንኙነት እንደሆነና ሊሆን እንደሚገባው ሲገልጥ መጽሐፍ ቅዱስ *"ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ በሚስቱም ይጣበቃል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ።"* /ዘፍጥ 2፡ 24/ በማለት ያስረዳል። *"አዳምና ሚስቱ ሁለቱም ዕራቁታቸውን ነበሩ አይተፋፈሩም ነበር"* /ዘፍ2፡ 25/ በሚለው መርህም ቅዱሱ መጽሐፍ በባለትዳሮች መካከል ግልጥነትና ነፃነት ያለው የግብረ ስጋ ግንኙነት ሊኖር የሚገባ መሆኑን አጽንኦት ሰጥቶ ያስረዳል:: ይህንን መረዳታችን የግብረ ስጋ ግንኙነት የተሰጠበትን ዓላማ ለመጠበቅና በግንኙነታችን መካከል ለሚፈጠረው ችግር በጋራ መፍትሔ ለማፈላለግ ጥረት እንድናደርግ ያግዘናል። በትዳር ውስጥ ያለውን አንድነት የሚያሳይና ጥልቅ የሆነ ግንኙነት መሆኑ በግንኙነቱ ሂደት ባለው ግልጥነት፣ መተፋፈር የሌለበት በመሆኑ፣ ራቁትነትን የሚጠይቅ በመሆኑ፣ መከላከል የሌለበትና አንድ ስጋ የመሆን ሚስጥር ያለበት ግንኙነት በመሆኑ ተገልጧል።

### 2. ለደስታና ለእርካታ /ምሳ 5፡ 18-19፣ 1ኛቆሮ 7፡ 2-5/

ሐዋሪያው ጳውሎስ የቆሮንጦስ ክርስቲያኖች ለጻፉለት በትዳር ውስጥ ላሉ ጥያቄዎች መልስ መስጠት የሚጀምረው በትዳር መካከል ስላለው የግብረ ስጋ ግንኙነት *"ባል ለሚስቱ የሚገባትን ያድረግላት እንደዚህም ደግሞ ሚስቲቱ ለባልዋ"* /ቆሮ 7፡ 3/ የሚል ግልጥ መመሪያ ለባልና ለሚስት በመስጠት ነው:: ጋብቻ በትዳር ውስጥ ባለው ግንኙነት ባል የሚስትን ሚስት ደግሞ የባልን ፍላጎት በማስቀደም አንዱ አካል ሌላውን ለማስደስትና ለሌላው የእርካታ ምክንያት በመሆን ለመኖር ጥረት የሚደረግበት ተቋም ነው። እያንዳንዳችን ባለትዳሮች ልንገነዘበው የሚገባን በራሳችን ስጋ ላይ ስልጣን እንደሌለንና ስልጣኑ የትዳር አጋሮቻችን እንደሆነ ነው:: ይህንን በመገንዘብ ለሌላው ስሜትና እርካታ ራሳችንን መስጠት እንዳለብን የእግዚአብሔር ቃል ያስረግጥልናል። በራሳችን አካል ላይ ስልጣን እንደሌለን ብቻ ሳይሆን አንዱ ሌላውን መከልከል እንደሌለበት ሲያስረዳም ሐዋርያው ጳውሎስ *"አትከላከሉ"* በማለት ያሳስባል። መታቀብ ካስፈለገም





ዓላማው ለጸሎት ብቻ ሊሆን ይገባል:: ይህ ዓይነቱ መታቀብ እንኳን የጋራ ስምምነትን የሚጠይቅና ለአጭር ጊዜ ብቻ መቆየት ያለበት ነው። እርስ በርሳችን በመስማማት ለጸሎት ጉዳይ ከግብረ ስጋ ግንኙነት መታቀብ የምንችል ሲሆን ይህ እርምጃ ለረጅም ጊዜ መታቀብን በማስወገድና አብሮ መኖርን በማበረታታት ራስን ባለመግዛት ለሰይጣን ፈተና አልፈን እንዳንሰጥና እንዳንጋለጥ ያደርገናል።

የእግዚአብሔር ቃል በምሳ 5፡ 18-20 *"ምንጭህ ቡሩክ ይሁን ከጉብዝናህም ሚስት ጋር ደስ ይበልህ። እንደ ተወደደች ዋላ እንደ ተዋበችም ሚዳቋ ጡትዋ ሁልጊዜ ታርካህ በፍቅርዋም ሁልጊዜ ተጋገብ"* ይላል። በባለትዳሮች መካከል አንዱ ሌላውን እንዲያረካና በትዳር የተጣመረ ሰው ከትዳር አጋሩ ጋር ባለው የግብረ ስጋ ግንኙነት ብቻ በመወሰን ደስተኛ እንዲሆን ይመክራል። ማንኛውም ከትዳር ውጭ ያለ ግንኙነት ዝሙት ነው። በግብረ ስጋ ግንኙነት እኛም ለሌላ የትዳር አጋሮቻችንም ለሌላ እንዲሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ አይፈቅድም! ይልቁንም ከጉብዝና የትዳር ጓደኛችን ወይም ከመጀመሪያ የትዳር አጋራችን ጋር ብቻ ደስ ይበለን ይለናል /ምሳ 5፡ 18/:: ከትዳር አጋሮቻችን ጋር በሩካቤ ስጋ ግንኙነት እርስ በርሳችን እንረካ ዘንድ ከእግዚአብሔር የተሰጠን ስጦታ ነው። አንዱ ለሌላው ፍላጎትና እርካታ መጠንቀቅ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትዕዛዝ ነው። ምንም ዓይነት ምክንያቶች ቢኖሩን እንኳን አንዱ የሌላውን ፍላጎት ባለመረዳትና ባለማሟላት ከሚፈጠር ግጭትና መለያየት የትዳርን ግንኙነት እየጠበቁ መተሳሰብ እንጅ ማሳበብ አያዋጣንም!!

### 3. ልጅ ለመውለድ (ለመዋለድ) /ዘፍ 2፡ 27-28/

ሌላውና የመጨረሻው የግብረ ስጋ ግንኙነት በትዳር ውስጥ ያለው ዓላማ ልጆችን በመውለድ የመባዛትን ሂደት ማስቀጠል ነው:: ጋብቻ እግዚአብሔር ለባለትዳሮች ልጆችን ስጦታ አድርጎ የሚሰጥበት መንገድ ነው *"እናንተም ብዙ፥ ተባዙ በምድር ላይ ተዋለዱ፥ እርቡባትም።"* /ዘፍ 9፡ 7/:: ይህ ሲባል ከጋብቻ ውጭ ባለ የግብረ ስጋ ግንኙነት ልጆች አይወለዱም ማለት አይደለም። ደግሞም ክርስቲያን ባለትዳሮች ሆነው ልጆች የሌሏቸው ጥንዶች የሉም ለማለትም አይደለም። ልጆች ሳይኖሯቸው በደስታ የሚኖሩ ጥንዶች እንዳሉ ሁሉ እንዲሁ በሐዘን፣ በግጭት... የሚኖሩ ቁጥራቸው ጥቂት አይደሉም! ትዳር ልጆች ባይኖሩም ተዋደን፣ ተቀባብለንና ተረዳድተን የምንኖረው ቃል ኪዳናዊ ትሥሥር ነው::

ለትዳር ግንኙነታችን የልጆች አለመኖርም ሆነ መኖር ለግጭትና ላለመግባባት ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ። ነገር ግን በዚህ ርዕስ ውስጥ በዋናነት ለመናገር የምፈልገው እግዚአብሔር ሰዎችን ወንድና ሴት አድረጎ የፈጠረበትና ወንድና ሴት ብቻ በትዳር እንዲጣመሩ የፈለገበት አንደኛው የትዳር ዋና ዓላማ ልጆችን መውለድና የማሕበረሰብን ሂደት ማስቀጠል መሆኑን ነው:: በዚህም በትዳር በተጣመሩ ባልና ሚስት ወይም እናትና አባት ጥበቃና እንክብካቤ ልጆች ደህንነታቸው ተጠብቆ እንዲያድጉ ቤተሰብ የሚባለውን ተቋም እግዚአብሔር ሰውን በፈጠረበት ወቅት እንዲመሠረት አድርጓል::

ስለዚህ እግዚአብሔር የሰጠንን ልጆች ለሰጪው ምስጋና እያቀረብን በአግባብ የማሳደግ ኃላፊነት አለብን፡፡ ይህንን ኃላፊነት ተገንዝበን ልጆቻችን ባንድ በኩል ከመለኮት የተቀበልናቸው የደስታችን ምክንያቶች በሌላ በኩል ደግሞ ጠብቀንና ተንከባክበን ማሳደግ ያለብን የመለኮት አደራዎች ናቸውና ኃላፊነታችንን በአግባቡ በመወጣት የትዳር ዓላማ በትክክል ግቡን እንዲመታ የድርሻችንን አስተዋጾ ማበርከት አለብን፡፡ ከዚህ በተቃራኒ ግብረ ሰዶማዊነት የዘመኑ ሰይጣናዊና ስልጣኔ አመጣሽ የትዳር፣ የቤተሰብና የማሕበረሰብ ብሎም የትውልድ ቀጣይነት እንቅፋት በመሆን የመገለጡን ሃቅ ልብ ማለት ይኖርብናል፡፡ ይህ የተመሳሳይ ጾታ ሰዶማዊ ግንኙነት የእግዚአብሔርን ዓላማ በሚቃወም መልኩ ዲያብሎስ እየተጠቀመበት ያለ ሰይጣናዊ ስልት ነው። ይህንን በመረዳት ትዳርን የእግዚአብሔር መልካም ዓላማ መፈጸሚያ በሚሆን መንገድ መጠበቅ ከመቼውም ጊዜ በላይ ልንጠነቀቅለት የሚገባ ኃላፊነታችን ነው፡፡ ልጆቻችንንም በእግዚአብሔር ቃልና ሰላም በተገነባ ቤተሰብ ውስጥ ተቀርጸው እንዲያድጉ የማድረግ መለኮታዊ አደራ አለብን፡፡ ከዚህ የምንዘገይ ዳተኞች ሆነን ልጆቻችን ለትዳራችን የግጭት ምክንያት እንዳይሆኑብን ኃላፊነታችንን አውቀን የምንኖር አስተዋይ ባለ አደራዎች ልንሆን ይገባል።

ልጆች የሌሉን ባለትዳሮች ከሆንን ደግሞ መካኒቷን ሰባት እንድትወልድ ያደረገ እግዚአብሔር ዛሬም አልተለወጠምና በጸሎትና በምልጃ ከምስጋናም ጋር ልምናችንን ማሳወቅ እንጂ ተገቢ ባልሆነ ጭንቀት መሰቃየት የለብንም፡፡ ትዳር ስንመሠርት ልጆች አልነበሩም፡፡ ትዳሩን የመሠረትንበትን ቃል ኪዳን በእግዚአብሔርና በሰዎች ፊት የገባናውም ልጆችን አካትተን አይደለም፡፡ በፊቱ የዕድሜ ልክ ጋብቻ ቃል ኪዳን ስንገባ አብሮን የነበረው አምላክ ልጅን የመስጠት ችሎታና አቅም ያለው እርሱ ነው፡፡ እርሱ ደግሞ የሚያደርገውን የሚያውቅ በሥራው ጻድቅ የሆነ አምላክ ነው፡፡ እግዚአብሔር የትዳርን መርህ ባሳወቀበት በቃሉ ልጆች ካልሰጠኋችሁ ወደ ግጭትና ወደ ፍች ሂዱ ብሎም አላዘዘንም፡፡ ስለዚህ ይህንን እውነት በመረዳት በትዳር የተጣመርን ባልና ሚስቶች ልጅ ባለ መውለድ ምክንያት በእግዚአብሔር ቃል መርህ የተመሠረተውን ትዳር እንዳናፈርሰው ጥንቃቄ ልናደርግ ይገባል፡፡ ይህ ማለት ልጅ ያለመውለድ ችግር ቀላል ነው ማለት አይደለም፤ ነገር ግን ችግሩ ምንም አስቸጋሪ ቢሆንም እንኳን ሳንጋጭ ደስታችንን በጌታና ከጌታ በተሰጠን የትዳር አጋር ላይ በማድረግ ባለን ግንኙነት ማረፍን በመለማመድ ጌታን እንጠብቅ። ልጆች ሊኖሩን ባይችሉም እንኳን እግዚአብሔርን አክብሮ ማለፍ የመጀመሪያው የሕይወታችን ደስታ ሆኖ እንዲቀጥል ትዳራችንን ለዚህ ክቡር አገልግሎት ማስገዛት ዋናው የሕይወት ዓላማችን ሊሆን ይገባል፡፡





## III. ከግብረ ስጋ ግንኙነት ጋር የተያያዙ የግጭት መንስኤዎች

### i. በወንዶች ላይ የሚከሰት ፈጥኖ እርካታ ላይ የመድረስ ችግር

አንድ ወንድ በግብረ ስጋ ግንኙነት ወቅት እርካታ ላይ ደረሰ የሚባለው የዘር ፈሳሹን ወደሚያፈስስበት ደረጃ ሲደርስ ነው፡፡ በግብረ ስጋ ግንኙነት ውስጥ እርካታ ላይ ደርሷል ሲባል ባል ወይም ወንዱ የፍትዎት ፍላጎቱ ከፍተኛ ደረጃ ላይ በመድረሱ የጋለ ስሜት ላይ በመሆን የወንድ ዘር ማፍሰስ (መርጨት) ደረጃ ላይ ደርሷል ማለት ነው። ብዙ ጊዜ ባሎች (ወንዶች) ከዚህ ከቁጥጥር ውጭ የሆነ የስሜት እርካታ ደረጃ ላይ የሚደርሱት ሚስቶቻቸው (ሴቶች) ገና በአግባቡ ዝግጁ ሳይሆኑ ነው፡፡ በግብረ ስጋ ግንኙነት ወቅት ወደዚህ ከቁጥጥር ውጭ ወደሆነ የፍትዎት ስሜት እርካታና ደስታ ደረጃ ሚስት ከመድረሷ፣ ለመርካት ዝግጁ ከመሆኗና ከመርካቷ በፊት ባል በጥድፊያ እርካታ ላይ መድረሱ የሚስትን ስሜት የሚጎዳና ደስታዋን የሚከለክላት ችግር እንዲፈጠርባት ያደርጋል፡፡ ሚስት ገና እርካታ ላይ መድረስ እየፈለገች ባሏ አስቀድሞ ሲረካና ግንኙነቱን ሲጨርስ የጋራ እርካታ የሚባለው መተሳሰብ ይጠፋና ሚስት የእርሱን ስሜት ለማርካት ብቻ የተፈጠረች ስሜት አልባ ተደርጋ እንደታየች እንድታስብ ያስገድዳታል፡፡ ይህ በግብረ ስጋ ግንኙነት ውስጥ ባሎች የሚስቶችን ስሜት ሳይጠብቁ አስቀድሞ የስሜት መርካት ላይ የመድረስና የግብረ ስጋ ግንኙነትን ሂደት ቅጽበታዊ በሆነ ጥድፊያ ቀድመው የመጨርስ ችግር በሬሽዮ ሲጠና 1፡3 ሲሆን ይህ ማለት ከሶስት ወንዶች በአንድ ወንድ ላይ ሊከሰት ይችላል።[19]

እንዳቸው የሌላቸውን ስሜት ሳይጠብቁ በጥድፊያ በመርካት ችግር ምክንያት እግዚአብሔር ለሰዎች በሰጠው በትዳር ውስጥ ባለው የግብረ ስጋ ግንኙነት መልካም ስጦታ ከመደሰት ይልቅ የስሜትና የስነ ልቦና ቀውስ እንዲፈጠርባቸው ያደርጋል፡፡ የችግሩ ሰለባዎችም የማፈር፣ የመሸማቀቅ፣ ተገቢውን ክብርና ስፍራ ያለማግኘትና ራሳቸውን የመውቀስ ስሜት ይፈራረቅባቸዋል። በትዳራቸው ከመደሰት ይልቅ ሐዘንተኞች ይሆናሉ፡፡ ጉዳዩ በጊዜ ካልተስተካከለ የትዳሩ ዘላቂነትም አደጋ ላይ ይወድቃል፡፡ ችግሩ በጊዜ ይስተካከል ዘንድም የችግሩን ምክንያቶችና መፍትሔዎች

[19] Clinton, Tim & Laaser, Mark. The Quick-Reference Guide to Sexuality and Relationship Counseling, Baker books, a division of baker publishing Group: Grand Rapids, Michigan, 2009. page 82

መረዳት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ የሚከተሉት ነጥቦች የችግሩን ምክንያቶች በማስቃኘትና መፍትሔዎችን በመጠቆም የአንባቢውን ግንዘቤ የማስፋት ጥረት ያደርጋሉ፡-

**1) ፈጥኖ የወንድ ዘር ፍሬ የመፍሰስ ችግር ምክንያቶች**

**ሀ. ስነ ልቦናዊ ምክንያቶች**

**i. በልጅነታቸው (ለአቅመ-አዳም ወይም ለአቅመ-ሄዋን) ሳይደርሱ የደረሰባቸው ጥቃት (ጉዳት)**

እንዲህ ዓይነቱ ጥቃት በአስገድዶ መደፈር፣ በመጠለፍና በተለያዩ መንገዶች የጾታዊ ጥቃት ሰለባ የመሆን ገጠመኝ ነው። ጥቃቱ ስውር በሆነ መንገድ አብረው ቤት ውስጥ በሚኖሩ የቅርብ ዘመዶች፣ ወዳጆች፣ በጎረቤት ሰዎችና ቤት ውስጥ ተቀጥረው በሚሠሩ የቤት ሠራተኞች በኩል በልጅነት ወቅት የደረሰ ጉዳት ሊሆንም ይችላል፡፡ ልጆች በተለያዩ ሰዎች ተታልለው ወይም ተገድደው የጾታዊ ጥቃት ሰለባ ይሆናሉ፡፡ ራሳቸውን መጠበቅና ከጉዳት መከላከል የማይችሉ ሕጻናት ልዩ ልዩ የሰውነት ክፍላቸውን በመነካካትና የግብረ ስጋ ግንኙነት እንዲፈጽሙ ወይም በማያውቁትና ባልገባቸው መንገድ የሌሎች መጠቀሚያ እንዲሆኑ እየተገደዱ ሊያድጉ ይችላሉ፡፡ ይህ ክስተት ልጆች እያደጉ ሲመጡ በስነ ልቦናቸው ላይ የሚፈጥርባቸው አሉታዊ ተጽዕኖ የልጅነት ዘመን ጉዳት ብቻ ሳሆን የሕይወት ዘመን ቁስል በመሆን ትዳር በሚመሠርቱበት ጊዜም የግንኙነት እንቅፋት ይሆናል። የእንዲህ ዓይነቱ ስውር ጥቃት ተጋላጭ እንዳይሆኑ ወላጆች ከልጆች ጋር ያላቸው ግንኙነት የጠነከረ፣ ግልጥና መልካም ተግባቦት ያለው ሊሆን ይገባል። በእንደዚህ ዓይነት መንገድ ተጠቂ የሆኑ ልጆች ማንነታቸው ላይ ቀውስ ሊፈጥርባቸው ይችላልና ትክክለኛ የምክር፣ የጸሎትና የመንፈሳዊ ትምህርት ድጋፍ በማግኘት በክርስቶስ ማንነት ላይ ሥር የሰደደ መሠረት እንዲኖራቸው መረባረብ ያስፈልጋል። በዓለም ላይ ወጣቶችና ሕጻናት ለግብረ ሶዶማዊነት አልፈው እንዲሰጡና ግብረ ሶዶማዊነትም እንዲስፋፋ እያደረጉ ካሉ ምክንያቶች አንዱ በልጅነታቸው በልጆች ላይ የሚደርስ ወሲባዊ ጥቃት እንደሆነ ይነገራል።[20]

**ii. ቶሎ ለመርካት ያላቸው ጉጉት**

ክርስቲያን ወንዶች እንደ ማንኛውም ሰው የፍትወት ፍላጎት አላቸው። የግብረ ስጋ ግንኙነት ፍላጎትን ማርካት የሚቻለው ደግሞ ከትዳር አጋር ጋር በሚደረግ ግንኙነት ብቻ መሆኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሐቅ ነው። *"መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ይሁን፤ ሴሰኞችንና አመንዝሮችን ግን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል።"* /ዕብ 13፡ 4/ ለዚህ የክርስትና ሕይወት መርህ ራሳቸውን በማስገዛት ምክንያትም ከጋብቻ በፊት ከዝሙት ራሳቸውን ለመጠበቅ ስሜታቸውን በብዙ ትግል ውስጥ ሲቆጣጠሩት ኖረዋል፡፡ ለትዳርም ከፍተኛ ናፍቆትና ጉጉት አላቸው፡፡ እነዚህ ክርስቲያን ወንድሞች ወደ ጋብቻ ሲገቡ በጋብቻ

[20] Hunt, June. Counseling through your Bible Handbook page 211-212





ውስጥ ከትዳር አጋራቸው ጋር በሚያደርጉት የሩካቤ ስጋ ግንኙነት የመፈጸም ሂደት ለመርካት ባላቸው ከፍተኛ ጉጉት ምክንያት የሚሰትን ስሜት ሳይጠበቁና እነርሱ ራሳቸውም እንኳን ዝግጁ ሳይሆኑ የመርካት ደረጃ ላይ ይደርሳሉ።

**iii. ባል ብልቴ ይቆም ይሆን የሚል ጭንቀት ሲያጋጥመው**

አንዳንዶች ወደትዳር የሚገቡ ወንዶች (ባሎች) ካሁን በፊት አሉታዊ ተጽዕኖ ያደረሰባቸው ገጠመኝ ካለ ከደረሰባቸው ስነ ልቦናዊ ችግር የተነሳ የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈጸሚያ የሰውነት ክፍላቸው (ብልታቸው) ይቆም ይሆን የሚል ፍርሃትና ስጋት ያጋጥማቸዋል።[21] አብዛኛውን ጊዜ ፍርሃትና ስጋት በሚኖርበት ወቅት ወደ ግብረ ስጋ ግንኙነት ለመግባት ስሜታዊ ዝግጁነት ያለን መሆን ያቅተናል። ይህ ዓይነቱ የስሜት ዝግጅት አለመኖር ደግሞ የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈጸሚያ የሰውነት ክፍሎቻችንም ለግብረ ስጋ ግንኙነት ዝግጁ እንዳይሆኑ አሉታዊ ተጽዕኖ ይፈጥራል፡፡ እንደዚህ ዓይነት ጭንቀት ውስጥ ያለ ባል የትዳር አጋሩን በግብረ ስጋ ግንኙነት ለማርካት አይችልም። ራሱም በግብረ ስጋ ግንኙነት ውስጥ የሚገኘውን እርካታና ደስታ መካፈል አይችልም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ እንዲህ ዓይነት የግንኙነት ችግር ያጋጠማቸው ባለትዳሮች ለሌሎች አለመግባባቶችና ግጭቶች አልፈው የመስጠት ዕድላቸው ከፍተኛ ነው።

**ለ. ስነ ሕይወታዊ (ባዮሎጅካል) ምክንያቶች**

**i. የሆርሞን (የሰውነት ንጥረ-ቅመም) መጠን መዛባት**

የባሎች በግብረ ስጋ ግንኙነት ወቅት ፈጥኖ የዘር ፍሬን በማፍሰስ ወደ እርካታ የመድረስ ችግር በወንድ ልጅ አካል ውስጥ የሚገኝ ቴስቴስትሮን የሚባል አካላዊ ንጥረ-ቅመም (የሆርሞን) መጠን በመዛባቱ ምክንያት ሊፈጠር ይችላል። በተፈጥሯዊ ምክንያቶችና በሚወሰዱ ልዩ ልዩ መድሃኒቶች ምክንያት እንዲህ ዓይነቱ ችግር ሊፈጠርና ሊባባስ ይችላል። ከዚህም ባሻገር በአእምሮ (Neurotransmitters) ውስጥ ያለ የኬሚካል መጠን በመዛባቱ ምክንያትም ችግር ሊፈጠር ይችላል።[22] ይህ ከሆነ ደግሞ ችግሩ ያጋጠመው ሰው ጉዳዩ ሊፈታ የሚችል ከሆነ የምክር፣ የሕክምና ወይም ሌሎች ሙያዊ ድጋፎችን የመፈለግ ጥረት ማድረግ አለበት፡፡ ጥፋቱ የራሱ እንደሆነ በማሰብ ራሱን መውቀስና መኰነን አይኖርበትም፡፡ ይህንን የሚያደርግ ከሆነ ያላሰባቸው ሌሎች የስነ ልቦናና የስሜት ቀውስ ችግሮች ያጋጥሙታል፡፡ የትዳር ጓደኛ የሆነችው ሚስቱም ይህንን ችግር መረዳትና መታገስ መቻል ይጠበቅባታል፡፡

**ii. የወንድ የዘር ፍሬ መርጫ ስርዓት (ሲስተም) እንደሚገባ በትክክል አለመሥራት**

የወንድ የዘር ፍሬ መርጫ የሰውነት ስርዓት (ሲስተም) እንደሚገባ በትክክል አለመሥራት ሌላው ተጠቃሽ በግብረ ስጋ ግንኙነት ወቅት እርካታ ላይ ለመድረስም ሆነ

[21] Clinton, Tim & Laaser, Mark. The Quick-Reference Guide to Sexuality and Relationship Counseling, Baker books, a division of baker publishing Group: Grand Rapids, Michigan, 2009. page 84

[22] pp.84

የትዳር ጓደኛን የእርካታ ፍላጎት ማሟላት ያለመቻል ምክንያት ነው። የተለያዩ የሰውነት አካል ክፍሎች በበሽታ መጠቃት ይህን ችግር የሚያስከትል ተጠቃሽ መንስኤ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ያክል በሰውነት ላይ የሚፈጠር ጉዳት ወይም በእንቅርት እጢና ፕሮስቴት በመባል የሚታወቀው ከወንድ ልጅ ፊኛ በታች የሚገኝ ለወንድ ዘር የሚሆን ፈሳሽ የሚያመርት እጢ የመጎዳትና የቁስለት ችግርና ይህም ጉዳት በዘር ተላላፊ መሆኑ ተጠቃሽ ምክንያቶች ናቸው።[23]

**2) ፈጥኖ የወንድ ዘር በመፍሰስ ለሚቸገሩ ባለትዳሮች መፍትሔዎች**

***ሀ. መረዳት፡- አልፎ አልፎ ሊፈጠር የሚችል ክስተት መሆኑን መረዳት***

ይህ ችግር በአብዛኛው በወንዶች ላይ የሚታይና የሚከሰት ችግር መሆኑን መገንዘብ መቻል አስፈላጊ ነው። ይህ የሚፈጠረው ችግር ምንም ዓይነት ጥንቃቄ ብናደርግም እንኳን መከሰቱ አይቀሬ እንደሆነ መረዳትና የሚከሰተው ግን አልፎ አልፎ መሆኑ ማረጋገጥ ተገቢ ነው። ባሎች ስለችግሩ ምንም ያህል ቢያውቁና ችግሩን የማስቀረት ፍላጎት ኖሯቸው ከፍተኛ ጥረት ቢያደርጉም እንኳን ችግሩን ይቀንሱት እንደሆነ እንጂ ፈጽሞ ሊያስወግዱት አይቻላቸውም፡፡ ስለዚህ ፈጥኖ የወንድ ዘር የመፍሰስ ችግር የሚያጋጥመው አልፎ አልፎ ከሆነ መታገስና መቀበል አስፈላጊ ነው፡፡ ችግሩ አልፎ አልፎ ከሆነ መታገስና መቀበል አስፈላጊ የሚሆነውም በሚታየው ችግር ከሚፈጠረው አሉታዊ ተጽዕኖ ራስንና የትዳርን ግንኙነት ለመጠበቅ ሲባል ነው። ይህን ማድረጉ ጊዜያዊ የሆነው ችግር ዘላቂ የሆነው ትዳር ላይ የሚከብድ ጉዳት ፈጥሮ እንዳያልፍ ለመከላከል እንዲቻል በጋራ ለመረዳትና ለመረዳዳት ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው። ለቀጣይ እርዳታ የመጀመሪያው እርምጃ ችግሩ ጊዜያዊና አልፎ አልፎ ብቻ ሊከሰት የሚችል መሆኑን ማረጋገጥ መቻል ነው።[24]

***ለ. መታየት፡- በሕክምና ባለሙያ መታየት***

ፈጥኖ የወንድ ዘር የማፍሰስ ችግር በተለያዩ በሽታዎች ምክንያት ወይም ለሌሎች ሕመሞች ፈውስ ለማግኘት ሲባል በሐኪም ትዕዛዝ የሚወሰዱ መድሃኒቶች በሚያስከትሉት የጎንዮሽ ተጽዕኖ ምክንያት የተከሰተ ሊሆን ስለሚችል የችግሩን መንስኤም ሆነ መፍትሔውን ለማፈላለግ ወደ ሕክምና ባለሙያ መሄድና ማነጋገር አስፈላጊ ነው። የሕክምና ባለሙያን ማነጋገር ሊያሸማቅቅ፣ ሊያስፈራና ሌላ ስጋት ውስጥ ሊያስገባን አይገባም። እንዲህ ዓይነት እርምጃ መውሰድ ለችግሩ በፍጥነት መፍትሔ በማፈላለግና መፍትሄ በማግኘት በትዳር ውስጥ የሚገኘው እርካታና ደስታ ሁለቱንም ጥንዶች የሚያካትት እንዲሆን ለትዳር ግንኙነት ትኩረት መስጠትንና አሳቢነትን ያመላክታል።

[23] Sexuality and Relationship Counseling pp 84
[24] Sexuality and Relationship Counseling pp 83





በሰውነት ውስጥ በሚገኝ ንጥረ-ቅመም (ሆርሞን) መብዛትና ማነስ፣ የወንድ ዘር የመርጫ የሰውነት ስርዓት (ሲስተም) እንደሚገባ አለመሥራት ወይም ሌሎች በሽታዎችና በሽታዎችን ለማስወገድ የሚወሰዱት መድሃኒቶች ተደማምረው የሚያመጡት አሉታዊ ተጽዕኖ ሊታወቅና ሊረጋገጥ መፍትሔም ሊፈለግለት የሚችለው ወደ ሕክምና ባለሙያ በመሄድ ነው፡፡ ሐኪም ማነጋገርና የተለያዩ የምርመራ ዘዴዎችን በመጠቀም በምርመራ ውጤቱ የችግሩን እውነተኛ ገጽታ ማረጋገጥ በጣም አስፈላጊ ነው። በትክክለኛ ሐኪም ታይቶና ተገቢ የሕክምና ምርመራ አድርጎ የምርመራ ውጤቱ ሳይረጋገጥና ሐኪም ትዕዛዝ ሳይሰጥ ችግሩን ለመፍታት ያግዛሉ የሚባሉ መድሃኒቶችን መጠቀም አሁን ያለውን ችግር ከማባባስ በተጨማሪ ላልታሰቡ የጎንዮሽ ተጽዕኖዎች ያጋልጣል፡፡ በዚህም ምክንያት ለሌሎች ውስብስብ ለሆኑ በሽታዎችና ችግሮች አልፈን ልንሰጥ እንችላለን።

በወንድ ልጅ ላይ የሚከሰተውን ፈጥኖ የወንድ ዘር ማፍሰስ ችግር ለመቀነስ በሐኪም ከሚታዘዙ የተለያዩ መድሃኒቶች ውስጥ አንዱ በሐኪም ትዕዛዝ ለጸረ-ድብርት (ለጸረ-ድባቴ) የሚሰጥ መድሃኒት (Antidepressant medicine) ነው፡፡ ይህን መድሃኒት መውሰድ በባሎች ላይ የሚከሰተውን በግብረ ስጋ ግንኙነት ወቅት ፈጥኖ ዘርን የማፍሰስን ሂደት የማዘገየት ተፅዕኖ አለው። ይህ መፍትሔ ፈጥኖ የወንድ ዘርን የማፍሰስ ችግርን ሲያስወግድ በአንጻሩ ደግሞ ይህን መድሃኒት የሚወስዱ ሰዎች ለፍትወት ያላቸውን ተነሳሽነት እንዲቀንስ የሚያደርግ አሉታዊ ተጽዕኖም እንዳለው መረዳት አስፈላጊ ነው።[25]

ሌላው በሕክምና ባለሙያ ለወንድ ልጅ ዘር ፈጥኖ የመፍሰስ ችግር ከሚታዘዙት መድሃኒቶች መካከል የሚታዘዘው የሚቀባ ክሬም እንዲጠቀሙ ነው። ይህ የሚቀባው ክሬም (Lidocaine or Prilocaine ) በመባል የሚታወቅ ሲሆን ቅባቱ የወንድን ብልት (ስሜትን) የማደንዘዝ ባህሪይ አለው። የወንድን ብልት በማደንዘዝም በግብረ ስጋ ግንኙነት ወቅት ባሎች የዘር ፈሳሻቸው ፈጥኖ እንዳይፈስ የማዘግየት ባህሪይ አለው። ነገር ግን መድሃኒቱ የሴትን ብልት የማደንዘዝና የፍትወት ፍላጎቷን የመቀነስ ባህሪይና አሉታዊ ተጽዕኖ ሊኖረው ስለሚችል መድሃኒቱን ከመጠቀም በፊት የሐኪምን ሙያዊ ምክር መጠየቅ አስፈላጊ ነው።[26]

***ሐ. መጠቀም፡- የተለያዩ ዘዴዎችን (ቴክኒኮችን) መጠቀም***

**i. የመጭመቅ ቴክኒክ**

ፈጥኖ የወንድ ዘር መፍሰስን ችግር ለማስወገድና በባለትዳሮች መካከል የጋራ እርካታ የሚያስገኝ የግብረ ስጋ ግንኙነት እንዲኖር ከሚመከረው ምክር አንደኛው ዘዴ የመጭመቅ ቴክኒክ ነው። ይህ የመጭመቅ ዘዴ አራት ደረጃ በደረጃ ሊወሰዱ የሚገቡ

[25] Sexuality and Relationship Counseling pp 86
[26] Sexuality and Relationship Counseling pp 86

እርምጃዎችን ያካተተ ነው። የመጀመሪያው ደረጃ የወንድ ዘር የመፍሰስ ስሜት እስኪጀምር ድረስ ትክክለኛ የሆነ ግብረ ስጋ ግንኙነትን መቀጠልና በተለያዩ ስጋቶች ግንኙነትን አለማቋረጥን ይጠይቃል። ሌላው ሁለተኛ ደረጃ የመጭመቅ ቴክኒክ ዘዴ የወንዱ ዘር መፍሰስ ከመጀመሩ በፊት የወንድን ብልት ጫፍ ጨምቆ ለተውሰኑ ሴኮንዶች በመያዝ የማሳለፍ ዜዴ ነው። ሶስተኛው ደረጃ የመጭመቅ ዘዴ እንደ ገና የግብረ ስጋ ግንኙነት ከመጀመር በፊት ለ30 ሴኮንድ የወንዱን ብልት በመልቀቅ መጠበቅ መቻል ነው። የመጨረሻው ደረጃ ደጋግሞ በመጭመቅ ሚስቶች በግብረ ስጋ ግንኙነት እስኪረኩ ድረስ መጠበቅና በጋራ የግብረ ስጋ ግንኙነት እርካታን በመጋራት በግንኙነታቸው አብረው ደስታን የሚካፈሉ የሚተሳሰቡ ጥንዶች መሆን መቻል ነው።[27]

**ii. ትንፋሽንና አሳብን የመቆጣጠር ዘዴ**

ችግሩን ለመቀነስ ከሚያግዙ የተለያዩ ዘዴዎች ሌላኛው ትንፋሽንና አሳብን የመቆጣጠር ዘዴን መጠቀም ነው። አንደኛው የዚህ ዘዴ ትግበራ በግብረ ስጋ ግንኙነት ወቅት ረዘም አድርጎ ትንፋሽ በመውሰድ የተፈጠረውን ስሜት የመቆጣጠርና የማዘገየት ሂደትንና ችሎታን ማዳበር ነው። ሌላው የትግበራ ሂደት ደግሞ ባል የዘር ፈሳሹን ፈጥኖ የማፍሰስን ችግር ለማስወገድ በግብረ ስጋ ግንኙነት ወቅት የፍትዎት ፍላጎቱ የእርካታ ጫፍ ላይ ወይም ከፍተኛ ደረጃ ላይ በሚደርስበት ወቅት ከዚህ ስሜት ሊያወጡ የሚችሉ የተለያዩ አሳቦችን የማሰብ ሂደት ነው። ብዙ ጊዜ ድርጊቶች የአስተሳሰብ ውጤቶች ናቸውና ይህንን አእምሮን በተለያዩ ሃሳቦች በመሙላት ስሜትን የመቆጣጠር ዘዴ ባሎች ሊረዱትና ሊጠቀሙበት ይገባል።[28]

**iii. ጭንቀትንና ውጥረትን የመቆጣጠር ዘዴ**

በባለትዳሮች የግብረ ስጋ ግንኙነት ወቅት የወንድ ልጅ የዘር ፈሳሽ ፈጥኖ እንዲፈስስና ከትዳር ጓደኛ ጋር የጋራ የሆነ የስሜት እርካታ እንዳይፈጠር ከሚያደርጉት ችግሮች መካከል ሌላው ምክንያት ባል አስቀድሞ ከሚስቱ ጋር ባደረጋቸው የግብረ ስጋ ግንኙነት ሂደቶች ውስጥ ያጋጠሙት ተመሳሳይ ችግሮች የሚፈጥሩት አሉታዊ ተጽዕኖ ነው። ከሚፈጠሩት አሉታዊ ተጽዕኖዎች መካከል አንዱ ቶሎ ስሜቴ ይረካል፣ ሚስቴን ሳላረካ ልቀር እችላለሁና ሚስቴ ምን ትለኛለች...? የሚሉ አሳቦችና ጥያቄዎች አእምሮውን ማስጨነቃቸው ነው:: እነዚህን የመሳሰሉ አሳቦች ይበልጥ እንዲጨነቅና የስነ ልቦና ጫና ውስጥ እንዲገባ ያደርጉታል:: የግብረ ስጋ ግንኙነት በሚያደርግበት ጊዜም በውስጡ ውጥረት ይፈጥራሉ።[29] ችግሩ እንዲፈታ እነዚህን ስነ ልቦናዊ ችግሮች ማስወገድ፣ መቆጣጠር፣ አንዱ ሌላውን ማበረታታትና በነገሮች ላይ በፍቅር መነጋገር ተገቢ ነው።

[27] Sexuality and Relationship Counseling PP 85
[28] Sexuality and Relationship Counseling PP 85
[29] Sexuality and Relationship Counseling PP 85





**2. በባለትዳር ሴቶች ላይ የሚፈጠር ለፍትዎት ተነሳሽነት ያለመኖር ችግር**

የፍትዎት ተነሳሽነት ፍላጎት ብለን ስናስብ አንዳንዶቹ ዝቅተኛ የሆነ ፍላጎት መኖር ችግር ሲኖርባቸው ሌሎች ደግሞ ፈጽሞ ፍላጎት የሌላቸው በመሆን ሊቸገሩ ይችላሉ። በቅርብ ዓመታት በተጋቡ ባለትዳሮች መካከል ከሚፈጠሩ ችግሮች መካከል አንዱ በሴቶች ላይ የሚከሰት ለፍትዎት ፍላጎት ተነሳሽነት አለመኖር ነው። ይህ ችግር ከባለትዳር ሴቶች መካከል በ20% ላይ እንደሚፈጠር ይታመናል።[30] ባለትዳር ሴቶችን የፍትዎት ፍላጎት እንዳይኖራቸው ወይም እንዲጠፋባቸው ሊያደረጉ የሚችሉ የተለያዩ ምክንያቶች አሉ። ከእነርሱም ጥቂቶቹን ከዚህ ቀጥለን ባጭሩ እንቃኛለን:-

**1) ፍላጎት ሳይኖራቸው የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈጸማቸው**

ባለትዳር ሴቶች የግብረ ስጋ ግንኙነት ተነሳሽነት እንዲጠፋባቸው ከሚያደርጉ ምክንያቶች መካከል የመጀመሪያው ፍላጎት ሳይኖራቸው የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈጸማቸው ነው። ብዙ ጊዜ ሚስቶች የግብረ ስጋ ግንኙነት ፍላጎት ሳይኖራቸው እንዲሁ በባሎቻቸው ጥያቄ፣ ፍላጎትና አስገዳጅነት ብቻ የግብረ ስጋ ግንኙነት እንዲፈጽሙ ይደረጋሉ። ያለሚስቶች ፍላጎት ወይም ፈቃደኝነት እንዲሁ በተለያየ መንገድ በማስገደድ የግብረ ስጋ ግንኙነት ውስጥ እንዲገቡ ሲደረጉ እርካታ ፈጽሞ ላይኖራቸው ይችላል። በእንዲህ ዓይነት ሂደት የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈጸም ከደስታ ይልቅ ሐዘንተኛ እንዲሆኑና ከእርካታ ይልቅም የሕመም ስሜት እንዲፈራረቅባቸው ያስገድዳቸዋል። ከትዳር አጋሮቻቸው ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት በሚፈጽሙበት ወቅት እርካታ ስለማያገኙ ውስጣቸው በጥላቻና በሰቀቀን ይሞላል:: ይህም ከስተት በቀጣዮቹ ቀናት(ጊዜያት) የግብረ ስጋ ግንኙነት ፍላጎትና ናፍቆት ፈጽሞ እንዳይኖራቸው ሊያደርጋቸው ይችላል።

**2) በሕመም ምክንያት የማህጸን መሳሳት**

በተለይ የማህጸን መሳሳት የሚያመጣው አሉታዊ ተጽዕኖ ሚስቶች ለግብረ ስጋ ግንኙነት ተነሳሽነት እንዲያጡ የሚያደርግ ምክንያት ነው። በተለያዩ ምክንያቶች የማህጸን መሳሳት ሊፈጠር ይችላል። የማህጸን መሳሳት ሴቶች በግብረ ስጋ ግንኙነት ወቅት የሕመም ስሜት እንዲሰማቸውና የፍትዎት ፍላጎታቸው እንዲቀንስ፣ እንዲጠፋ ብሎም ፈጽሞ ፍላጎት እንዳይኖራቸው ሊያደርግ ስለሚችል አስፈላጊውን የሕክምና ምርመራና ድጋፍ እንዲያገኙ መርዳት ያስፈልጋል።[31]

**3) በከፍተኛ ሁኔታ በግብረ ስጋ ግንኙነት ልምምድ ውስጥ ማለፍ**

ሚስቶች ክርስቶስን እንደ አዳኝና ጌታ መከተል ከመጀመራቸው ማለትም ክርስቲያን ከመሆናቸውና ከጋብቻ በፊት በከፍተኛ ሁኔታ በግብረ ስጋ ግንኙነት ልምምድ ውስጥ ያለፉ መሆናቸው ለግብረ ስጋ ግንኙነት ተነሳሽነት እንዳይኖራቸው

[30] Sexuality and Relationship Counseling PP 70
[31] Sexuality and Relationship Counseling pp 71

የሚያደርግ ሌላው ተጠቃሽ ምክንያት ሊሆን ይችላል። የተለያዩ ነገሮችን ለምደው መቆየታቸውና ብዙ ጊዜ አዘውትረው መለማመዳቸው አሁን በትዳር ሕይወታቸው ውስጥ የግብረ ስጋ ግንኙነት ፍላጎት ሊጠፋባቸው ይላል፡፡ እንደ ቀድሞው የሆነ የፍትዎት ፍላጎት ሳይኖራቸው ነገር ግን ግንኙነታቸውን ከፍትዎት ባለፈ አብሮ በብዙ ነገር እየተረዳዱ መኖር ላይ ትኩረት በማድረግ በትዳር ውስጥ ሊቀጥሉ ይችላሉ።[32]

**4) በሴቶች ላይ የሚፈጠር የሥራ ጫና**

በሴቶች ላይ የሚፈጠር የሥራ ጫናም ሚስቶች ለግብረ ስጋ ግንኙነት ፍላጎት ወይም ተነሳሽነት እንዳይኖራቸው የሚያደርግ ምክንያት ነው። ከባህል አንጻር አብዛኛውን ጊዜ የቤት ሥራዎች፣ ልጆችን የመመገብ፣ የመንከባከብና ምግብ የማብሰል ኃላፊነቶች ለሚስቶች ብቻ ይተዋሉ፡፡ ሚስቶች የውጭ ሥራዎችን ሲሠሩ ውለው ወደ ቤት ሲመለሱ ከውጭ ሥራዎቻቸው በተጨማሪ የቤት ውስጥ ሥራዎችን ሁሉ እንዲሠሩ ይገደዳሉ፡፡ ይህ ገጠመኝ ተዳምሮ መሸከም ከሚችሉት በላይ ከፍተኛ የሥራ ጫና ይሆንባቸዋል። በቤትም ሆነ በውጭ የሚፈጠርባቸው የሥራ ጫና አካለዊ ድካም በማምጣት ሌላ ነገር እንዳያስቡ ያደርጋቸዋል፡፡ ይህ የሕይወት ሸክም የስሜትና የስነ ልቦና ጉዳት በማድረስ በፍትዎት ፍላጎታቸው ላይ የሚያመጣው አሉታዊ ተጽዕኖ ቀላል አይደለም። ባለትዳሮች በመተሳሰብ የሥራ ክፍፍል ካላደረጉ በስተቀር በሴቶች ላይ ብቻ የሥራ ጫና ማሳረፍ ሊያስመርራቸው፣ ፍላጎት ሊያሳጣቸውና እንዳልተፈቀሩ እንዲያስቡና ለትዳር አጋራቸው ያላቸውን የፍቅር ፍልቀ ስሜት ሊያጠፋባቸው ይችላል። የባለትዳር ሴቶች ከትዳር አጋራቸው ጋር ያላቸው የፍቅር ፍልቀ ስሜት መጥፋት ለፍትዎት ፍላጎት ተነሳሽነት እንዳይኖራቸው ያደርጋል።[33]

**5) ከፍተኛ የሆነ ውጥረትና ጭንቀት መኖር**

ሌላው ሚስቶች የፍትዎት ፍላጎት እንዳይኖራቸው የሚያደርግ ተጠቃሽ ምክንያት በግልም ሆነ በትዳር መካከል ከፍተኛ የሆነ ውጥረትና ጭንቀት መኖር ነው። በባለትዳሮች መካከል በብዙ ነገር አለመግባባትና መጋጨት ካለ ሚስቶች ስሜታቸው ስለሚጎዳ ለፍትዎት ያላቸው ተነሳሽነት እንዲጠፋ የማድረግ አቅም አለው። የተጎዳ ስሜት ሲኖር ባለትዳሮች እርስ በርስ እንዳይቀራረቡ፣ መልካም ተግባቦት እና የጠለቀና የጠነከረ ግንኙነት እንዳይኖራቸው ከማድረጉ ባሻገር ሴቶች በሚኖራቸው የግብረ ስጋ ግንኙነት ፍላጎት ላይ ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ ያመጣል።

**6) የወሊድ መቆጣጠሪያ መድሃኒቶች የሚያስከትሉት አሉታዊ ተጽዕኖ**

ሚስቶች ለግብረ ስጋ ግንኙነት ፍላጎት እንዲያጡ በማድረግ ከሚጠቀሱት ምክንያቶች መካከል ሌላው ምክንያት የወሊድ መቆጣጠሪያ መድሃኒቶች የሚያስከትሉት አሉታዊ ተጽዕኖ ነው። የስነ ተዋልዶን ሂደት ለማዘግየት ወይም

[32] Sexuality and Relationship Counseling pp 71

[33] Sexuality and Relationship Counseling pp 71





ለማስቀረት በማሰብ ሚስቶች የሚወስዷቸው ብዙዎቹ የወሊድ መቆጣጠሪያ መድሃኒቶች የሚያመጡት አሉታዊ የሆነ ተጽዕኖ መድሃኒቱን እንደሚወስዱት ሴቶች ስነሕይወታዊ (ተፈጥሯዊ) ልዩነትና እንደ ወሊድ መቆጣጠሪያው ዘዴ ዓይነት ቢለያይም የጎንዮሽ( ሳይድ ኢፌክት) ተጽዕኖ ማምጣታቸው ግን አይቀሬ ነው። ለአንዳንድ ሴቶች የተስማማው የወሊድ መቆጣጠሪያ ለሌሎች ሴቶች የማይስማማ ሁኖ የሚታየውና ለሁሉም ሴቶች አንድ ዓይነት የሆነ የወሊድ መቆጣጠሪያ መድሃኒት የማይታዘዝበት አንዱ ተጠቃሽ ምክኒያትም ይህ ነው።[34]

**7) በሴቶች ላይ በሕጻንነት የሚደረግ ግርዛት**

በአንዳንድ ቦታዎች የሚከሰተው በሴቶች ላይ በሕጻንነት የሚደረግ ግርዛት ሌላው ሴቶች ለግብረ ስጋ ግንኙነት ፍላጎት እንዳይኖራቸው ተጽዕኖ የሚያሳድር ምክንያት ነው። ካልተገረዙ ሴቶች ይልቅ የተገረዙ ሴቶች ለግብረ ስጋ ግንኙነት ያላቸው ተነሳሽነት ዝቅተኛ ነው። ይህ እንዲከሰት የሚያደርገው በሴት ልጅ ላይ ግርዛት በሚፈጸም ወቅት ለፍትዎት ፍላጎት ሊያነሳሷቸው የሚችሉ ነርቮች መነካታቸው ነው። ይህ ችግር በሕጻንነታቸው ያጋጠማቸው ሚስቶች በትዳር ውስጥ ከባላቸው ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት የማድረግ ፍላጎታቸው ደካማ ይሆናል፡፡ በትዳር ውስጥ በግብረ ስጋ ግንኙነት ለባላቸው ሊሰጡት የሚችሉትን ጋርዮሻዊ የደስታ ስጦታና እርካታም መስጠትና መቀበል ያቅታቸዋል፡፡ ይህን ቀውስ ፈጣሪ የሆነው ባህልም ሊወገድ ይገባል። ቀውሱን ፈጣሪ የሆነው ሴት ልጅን የመግረዝ አጉል ልማድና የሚያስከትለውን ችግርም በግልጥ በማሳየት ሕብረተሰባችንን ማስተማር የሚገባ ጉዳይ ሲሆን የሴቶችን ግርዛት ማስወገድ እንዲቻል ጥረቱ መቀጠል አለበት።[35]

**8) በግብረ ስጋ ግንኙነት ወቅት የተለያየ የሕመም ስሜት መፈጠር**

በተለያዩ ምክንያቶች በግብረ ስጋ ግንኙነት ወቅት የሕመም ስሜት ሊፈጠር ይችላል። አንዳንዶቹ ዝቅተኛ ፍላጎት ያላቸው መሆን ወይም ፈጽሞ ፍላጎት አለመኖር፣ በሴቶች ላይ ለፍትዎት ሲነሳሱ የሚመነጭ ፈሳሽ አለመኖር ብልቶታቸው የመድረቅና የመጠንከር ሁኔታ ስለሚገጥማቸው በግብረ ስጋ ግንኙነት ወቅት የሕመም ስሜት ሊፈጠርባቸውና በግብረ ስጋ ግንኙነት ከመደሰት ይልቅ ሊጠሉ፣ ሰበብ እየፈለጉ መከላከልና እንደ መከራ ሊቆጥሩት ይችላሉ። እንዲህ ዓይነቱ የሕመም ስሜት ሊፈጠርበት የሚችለበትን ምክንያት ለመረዳት በግልጥነት ማውራት፣ መመካከርና በጋራ መፍትሔ ማፈላለግ ተገቢ ነው።

[34] Sexuality and Relationship Counseling 71

[35] Women and Global HumanRights.http://www2.webster.edu/woolflm/fgm.htmlFemaleGenitalMutilation accessed 05/20/2014

### 3. በወንዶችና በሴቶች ላይ የሚከሰት የቀድሞ የከንፈር ወዳጅን የማሰብ ክስተት

በቅርብ በተጋቡ ባለትዳሮች መካከል ከግብረ ስጋ ግንኙነት ጋር በተያያዘ ከሚፈጠሩት ችግሮች መካከል ሌላው ሁለቱም ጥንዶች ወይም አንደኛቸው የቀድሞ ወዳጅን በማሰብ ከአዲሱ የትዳር አጋር ጋር በደስታ አብሮ ለመኖር መቸገራቸው ነው። እንዲህ ዓይነት ችግሮች በአብዛኛው የሚከሰትባቸው ባለትዳሮች በተለይ በጌታ ከመሆናቸው በፊት የግብረ ስጋ ግንኙነት ሲያዘወትሩ የነበሩ ናቸው። ሌላው በጌታ ሁነው በመንፈሳዊ ሕይወት በደከሙበት ወቅት የዝሙት ኃጢአት የተለማመዱ ከሆነ በእንዲህ ዓይነት ልምድ ውስጥ ያለፉ የትዳር አጋሮች ተጠቃሽ የሚሆኑ የችግሩ ሰለባዎች ናቸው። ሶስተኛው ምክንያት ከትዳር በፊትም ሆነ በኋላ ለፍትዎት ፍላጎት አነሳሽ የሆኑ ፊልሞችና ቪዲዮዎች ወይም ፖርኖግራፊ ተጠቃሚ የሆኑ ባለትዳሮች ለዚህ ችግር ተጋላጭ ይሆናሉ።

በመጨረሻ ልጠቅሰው የምፈልገው ደግሞ ከጥንዶቹ አንዱ አካል አግብቶ በተለያዩ ምክንያቶች ፍች ከፈጸመ በኋላ ሁለተኛ ጋብቻ ውስጥ በሚገባበት ወቅት ችግሩ ሊያጋጥም የሚችል መሆኑን ነው:: በተለያየ ምክንያት ማለትም የትዳር ጓደኛቸውን በሞት በማጣትም ይሁን ፍች በመፈጸም ሁለተኛ ያገቡ የትዳር አጋሮች የቀድሞ ትዳራቸውን እያሰቡ ከአሁን የትዳር አጋሮቻችው ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት ሲፈጽሙ የመርካት እንቅፋት የሚሆንባቸው የስሜትና የስነ ልቦና ተጽዕኖ ያጋጥማቸዋል:: ይህም በትዳር ውስጥ በግብረ ስጋ ግንኙነት የሚገኘውን ደስታና እርካታ እንዳይሰጡና እንዳይቀበሉ በማድረግ ለግጭት ምክንያት ሊሆንባቸው ይችላል። ለየት ያለ ጥንቃቄ ካላደረጉ ችግሩ ወደ ቀድሞ ወዳጆቻቸው እንዲመለሱ ወይም በቀላሉ ለተቃራኒ ጾታ ግንኙነት ፈተናና ለዝሙት እንዲጋለጡ ሊያደርጋቸው ይችላል። *"ከዝሙት ሽሹ"* /1ኛቆሮ.6፡ 11/

## IV. በግብረ ስጋ ግንኙነት ምክንያት ለሚፈጠሩት ግጭቶች መፍትሔዎች

### 1. መጸለይ፡- እንደ መንፈሳዊ ሰው በጋራ በእግዚአብሔር ፊት መጸለይ /ያዕ 5፡ 13-15፣ ኤር 33፡ 3/

ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱሳዊውን መርህ መሠረት ባደረገ መንገድ የግል ሕይወታቸውንም ሆነ የትዳር ኃላፊነታቸውን የሚወጡት በራሳቸው ጥረት ብቻ አይደለም:: እግዚአብሔር የሚያስፈልጋቸውን ጸጋ በመስጠት ከእነርሱ ጋር ይሆናል:: ስለዚህ ይህንን እውነት በመረዳት እንደ ክርስቲያን ባለትዳር ጥንዶቹ በጋራ ችግሮቻቸውን ይዘው በእግዚአብሔር ፊት መቅረባቸው በጣም አስፈላጊ ነው። ባለትዳሮች ችግር የሆነባቸውን፣ ከአቅማቸው በላይ ያጋጠማቸውንና ለግጭት ምክንያት በመሆን ሰላም የነሳቸውን ሸክም ይዘው ወደ እግዚአብሔር ጸጋ ዙፋን በእምነት





መቅረብ ይኖርባቸዋል። *"እንግዲህ ምሕረትን እንድንቀበል በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ።"* /ዕብ 4፡ 16/

በጋራ በመስማማት ወደ እግዚአብሔር በጸሎት መቅረባቸው ችግሩ ከአቅማቸው በላይ መሆኑን፣ ለችግራቸው መፍትሔ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንዳለ ማመናቸውን፣ በጋራ የተስማሙበት መፍትሔ ለማግኘት አብረው እየተጉ መሆኑን፣ የሚያገኙት መፍትሔ ለትዳራቸው በጋራ እንዲሠራ ፍላጎት ያላቸው መሆኑንና በጋራም ጥረት ማድረጋቸውን አመላካች ሊሆን ይችላል። እነዚህ የጤናማነትና የጤናማ ትዳር አመላካች የሆኑ መሠረታዊ እውነቶች ያሏቸውን ባለትዳሮች የሚረዳ አምላክና አባት፣ ግሩም የሆነ አማካሪ መንፈስ ቅዱስ ለልባቸው በመናገርና በጸጋው እነርሱን በመደገፍ ችግራቸውን ማወቅ እንዲችሉ፣ ለችግራቸው መፍትሔ እንዲያገኙና በሕይወታቸው የመታነጽ ለውጥ እንዲመጣ አብሯቸው ይሠራል።

### 2. መወጣት፡- ግንኙነትን ለማጠናከር ጥንዶች የየበኩላቸውን ድርሻ መወጣት

በአብዛኛው በቅርብ ጊዜ በተጋቡ ባለትዳሮች መካከል የፍትዎት መቀነስ ወይም ተነሳሽነት መጥፋት የሚታየው በሴቶች ላይ ነው። የፍትዎት ፍላጎት ለቀነሰባቸውና ለጠፋባቸው ሚስቶች ባል የሚስትን የፍትዎት ፍላጎትና ስሜት ለማነሳሳትና የግብረ ስጋ ግንኙነት ፍላጎት እንዲኖራት የሚያግዛት እንክብካቤ ማድረግ ይጠበቅበታል:: ይህንንም ማድረግ የሚችለው ከእርሷ ጋር አብሮ ጥሩ ጊዜ በማሳለፍ፣ በማድነቅ፣ በመንከባከብ እንዲሁም በጋራ የስሜት እርካታ ላይ መድረስ እንዲችሉ የሚያግዟቸውን ስሜት ቀስቃሽ ጨዋታዎች በመጫዎትና የተለያዩ ከክርስቲያን ስነ ምግባር ያልወጡ የግብረ ስጋ ግንኙነትን ቆስቋሽ ድርጊቶችን በመለማመድ ነው። ይህንን ኃላፊነቱን ባል በአግባቡ በመወጣት ሚስትም ኃላፊነቷን ተረድታ ወደ መወጣት እንድትመጣ ጉልህ ሚና መጫዎት ይችላል::

### 3. መበጀት፡- ጊዜ በመበጀት አብሮ ማሳለፍን ማዘውተር

አብሮ የመሆን አስፈላጊነቱ ላቅ ያለ በመሆኑ የትዳርን ግንኙነት ለማጠናከር የአብሮነት ጊዜን መበጀትና ያንን ጊዜም አስደሳችና ፍቅርን ገንቢ በሆነ መንገድ መጠቀም ተገቢ ነው። ለሁሉም ጊዜ አለውና!! ነገርን ጊዜን በአግባብ በመከፋፈል፣ በልክና ለጋራ ጥቅም እንዲውል ማድረግ አስፈላጊ ነው። ባለትዳሮች የጋራ ጊዜ እንዳይኖራቸውና ግንኙነታቸውን እንዳያጠናክሩ ከሚያደረጓቸው የተለያዩ ሁኔታዎች መካከል ሥራ፣ ትምህርት፣ የቤተ ክርስቲያን ፕሮግራምና አገልግሎት ተጠቃሽ ናቸው። ሌሎች ደግሞ ጊዜ እያላቸው ነገር ግን ከትዳር አጋሮቻቸው ጋር አብረው ጊዜ እንዳያሳልፉ የመገናኛ ብዙሃንና ማሕበራዊ ድረ-ገጾች ማለትም ቴሌቪዥን፣ የኢንተርኔት መረብ፣ ፌስ ቡክ፣ የቤት ሥራ፣ የቤተ ዘመድ አብሮ መኖር የመሳሰሉ ችግሮች ተጽዕኖ ያሳድሩባቸዋል። ሌሎች ባለትዳሮች ደግሞ ጊዜ እያላቸው ነገር ግን አብረው ለማሳለፍ የማይስማሙ፣

አብረው ቢሆኑ በጋራ የሚያወሩት የሌላቸው፣ ሲያወሩም የማይግባቡ፣ የተግባቦት ችግር ያለባቸውና በተቻለ መጠን አብረው ላለማሳለፍ ሰበብ የሚፈልጉ ጥንዶች ናቸው። እነዚህን ሁሉ ችግሮቻቸውን በመረዳት በተቻለ መጠን ያላቸውን ጊዜ ለትዳራቸውና ለቤተሰባቸው በመስጠትና አብሮ በማሳለፍ የትዳር ግንኙነታቸው ይበልጥ እንዲጠናከር እድል የሚሰጡና የተገኘውን አጋጣሚ ሁሉ የሚጠቀሙ ባለትዳሮች ወደመሆን ለመለወጥ መትጋት ይጠበቅባቸዋል።

ለጠበቀና እጅግ በጣም ለጠለቀ ግንኙነት አብሮ ጊዜ ማሳለፍ፣ ጊዜ መበጀት፣ ጊዜን በአግባብ መጠቀም ብልህነት ነው። ሊረሳ የማይገባው ጉዳይ ቢኖር የግብረ ስጋ ግንኙነት የማድረግ ፍላጎት ባለቤት መሆንና የግብረ ስጋ ግንኙነት በማድረግ በጋራ እርካታንና ደስታን ማግኘት አብረን በጋራ በምናሳልፈው ጣፋጭ ጊዜ ሊወሰን እንደሚችል ነው፡፡ ይህንን መረዳትና ሰበብ ፈልጎ ከትዳር አጋር ጋር አብሮ መልካም ጊዜ ማሳለፉን መለማመድ በትዳር ውስጥ የራሳችንን አስደሳችና ደስተኛ ትንሽ ዓለም በመፍጠር አርፈንና ረክተን እግዚአብሔርን በማክበርና በመተናነጽ ኅብረት የምንኖርበት መሠረት ነው።

**4. መነጋገር፡- በጋራ በመነጋገር ፍላጎትን መግለጥ**

ባለትዳሮች አብሮ ለመሆን የጋራ ጊዜ በመበጀት ያስፈለጋቸው በንግግር (በቃላት) የማይገለጡ የደስታ ጊዜያቶች ከማሳለፍ ባሻገር በጋራ መነጋገር፣ መወያየትና ፍቅርንም በቃላት መግለጥ የሚችሉበት ጊዜ እንዲኖራቸው ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ ኅብረት በባለትዳሮች መካከል በጣም አስፈላጊና አስበውበት ሊፈጥሩትና ሊጠቀሙበት የሚገባ ጉዳይ ነው። ባለትዳሮች ቢያንስ በቀን ውስጥ በአራት ክፈለ ጊዜያቶች ለአራት ደቂቃዎች ቢነጋገሩ መልካም ነው ተብሎ ይታመናል።[36]

ከእነዚህ አራት ክፍል ጊዜያት፡- **የመጀመሪያው** ማለዳ ከእንቅልፍ ሲነሱ ለአራት ደቂቃዎች የሚለዋወጡት ንግግር ነው፡፡ **ሁለተኛው** ደግሞ አብረው ቆይተው አንደኛው አካል በተለያዩ ምክንያቶች ለተወሰኑ ሰዓቶች የሚለይ ሲሆንና ስንብት ሲያደርግ ያሉት አራት ደቂቃዎች ንግግር ነው። **ሶስተኛው** ክፍለ ጊዜ ጥንዶቹ ተለያይተው ቆይተው እንደገና ሲገናኙ የሚነጋገሩባቸው የመጀመሪያዎቹ አራት ደቂቃዎች ናቸው፡፡ **የመጨረሻው** አራተኛው ክፍለ ጊዜ ደግሞ ወደ መኝታ በሚሄዱበት ሰዓት የሚደረግ የአራት ደቂቃዎች ንግግር ነው።[37] በዚህ የግንኙነት ሞዴል የክፍለ ጊዜ ክፍፍል ማሳየት የተፈለገው ለጤናማ የትዳር ግንኙነት መልካም የሆነ ተግባቦት አስፈላጊ እንደሆነ ነው። የጤናማ ባለትዳሮች አንዱ መለያ በየጊዜው የሚያወሩ፣ የሚነጋገሩና የሚግባቡ መሆናቸው ነው።

---

[36] Sexuality and Relationship Counseling

[37] Chapman, Gary. Marriage Works helping couples God's way, publishing light university: Forest, Virginia, 2011.



የጥቃት መንስኤዎችና መፍትሔዎቻቸው በጋብቻ ውስጥ!

ለግብረ ስጋ ግንኙነት መነሳሳት እንዲቻል በጋራ ማውራት ተገቢ ነው። በተለይ እንሶላ ውስጥ በመሆን ከግብረ ስጋ ግንኙነት በፊት፣ በግብረ ስጋ ግንኙነት ወቅትና ከግብረ ስጋ ግንኙነት በኋላ የሚደረጉ የጋራ ምክክሮች(ውይይቶች) ጠቀሜታቸው ላቅ ያለ ነው። ይህ መልካም የተግባቦት ሂደት የጥንዶቹ የጋራ የተግባቦት ደረጃ እጅግ በጣም ከፍተኛ መሆኑን ከማሳየቱም በተጨማሪ አንዱ ለሌላው ትኩረት፣ ዋጋና እንክብካቤ የሰጠና የሚሰጥ መሆኑን አመላካች ነው። ጥንዶቹ ባላቸው ነፃነት የተሞላው ተግባቦት እንሶላ በመጋፈፍ ወቅት እርስ በርስ መጫዋወት፣ ለሩካቤ ስጋ የሚያነሳሳ ንግግርና ወሬ በማውራትና ሁኔታዎችን በመቀየር ምቹ ኅብረቶችን የመፍጠር ጤናማነትና መንፈሳዊነትም ነው።

## 5. መደባበስ፡- አንዱ የሌላውን የሰውነት ክፍል መደባበስ /መኃ 4፡ 1 - 16፤ 8፡ 1-4/

የትዳር ጓደኛን የሰውነት ክፍል መነካካት አንዱ የፍቅር መግለጫና የግብረ ስጋ ግንኙነትን መቀስቀሻ መንገድ ነው። አንዱ የሌላውን የሰውነት አካል መነካካት ሲባል መሳሳም፣ መዳሰስ፣ መተቃቀፍ፣ እጅ ለእጅ መያያዝ፣ የተለያዩ የሰውነትን ክፍል መነካካትን ሊያጠቃልል ይችላል። የባለትዳሮች የግብረ ስጋ ግንኙነት የጋራ የሆነ መጣጣም እንዲኖርበትና የሚያስገኘውም እርካታ ከፍተኛ እንዲሆን አካላዊ መነካካት ጠቃሚ ነው። አንዲት የእግዚአብሔር ሴት የሆነች መምህርት የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ ተማሪዎችን ስለጋብቻ ትምህርት በምታስተምርበት ወቅት **"በአፍሪካውያን ባለትዳሮች ዘንድ ሶስት ጨለማዎች አሉ"** በማለት አንድ የተጠና ጥናት አካፈለቻቸው። እነርሱም በግብረ ስጋ ግንኙነት ወቅት የሚታዩ ጨለማዎች ሲሆኑ፡- የመጀመሪያው ጨለማ ከግብረ ስጋ ግንኙነት በፊት መብራት ማጥፋት ነው፡፡ ሁለተኛው ጨለማ በብርድ ልብስ ውስጥ መግባትና መሸፈን ነው፡፡ ሶስተኛው ጨለማ ደግሞ አይን በመጨፈን የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈጸም ናቸው።[38]

አንዳንድ ቦታ ላይ ምናልባት የኑሮ ሁኔታ፣ ባህልና የጥንዶቹ የጋራ የመግባባት ደረጃ አደገ ቢባል እንኳን ከሶስቱ ጨለማዎች ሁለቱ ወይም አንዱ ጨለማ መኖሩ የግድ ወይም አይቀሬ ሊሆን ይችላል። የጥናቱም ሆነ የእኔ የጽሑፌ ሃሳብ ፍጹም ግልጥ በሆነና ክርስቲያናዊ ስነምግባርን በጠበቀ መንገድ አካላዊ መነካካት ያለበት ስሜት ለስሜት የሆነ ግንኙነት አካላዊ መቀራረብንና ለግብረ ስጋ ግንኙነት ፍላጎት መነሳሳትን የመፍጠር ጠቀሜታው ከፍተኛ መሆኑን ለማሳየት ነው።

## 6. መሆን፡- በርኅራኄ የተሞላና በመልካምነት የታነጸ ማንነት ያለን መሆን

ሌላው አስፈላጊ ነገር ከትዳር አጋር ጋር አብሮ ጊዜ ከማሳለፍ፣ ከመነጋገርና ከአካላዊ መነካካት ጋር ፍቅርና ርኅራኄ በተሞላ ማንነትና በበጎነት መልካም የሆነ

---

[38] Addis Ababa Bible Collage. Marriage course class lecture 2002.

ግንኙነት መፍጠር መቻል ነው። ስሜትን የሚጎዳና ተነሳሽነትን የሚያጠፋ ከማንኛውም ክፉና ራስ ወዳድ ከሆነ ማንነት ራስን መጠበቅና ክፉ ባህርይዎችን ከሕይወት፣ ከግንኙነት ማስወገድ ክርስቲያናዊ ግዴታችንና የመልካም ባለትዳርነት መለያችን ሊሆን ይገባል። ፍቅርን በተግባርና በመልካም ባህርይ መገለጥም ይገባናል። *"ልጆቼ ሆይ፥ በሥራና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት አንዋደድ።"* /1ኛዮሐ 3፡ 18/

## 7. መራቅና መርዳት፡- ስሜትን ከሚጎዱ ነገሮች መራቅና ሌላውም የትዳር አጋር እንዲርቅ መርዳት

በማወቅም ሆነ ባለማወቅ አንዱ የሌላውን ስሜት ሊጎዳ የሚችል ወይም የሚጎዳ ድርጊት ሊፈጽም ይችላል። በማወቅ የሚደረግን ጉዳት በመጸጸትና በይቅርታ ማስተካከል አስፈላጊ ነው። ባለማወቅ አንዱ የሌላውን ስሜት በሚጎዳበት ወቅት ተጎጅው አካል ስሜቱን የሚገልጥበትና የሚያሳውቅበት መንገድ መፈጠር መቻል አለበት። በወቅቱ የሚሰማንን ስሜት በመግለጥ መፍታትና መግባባት ካልተቻለ የስሜት መራራቅ ለግብረ ስጋ ግንኙነት ያለመነሳሳት ሊያመጣና የጥንዶችን ግንኙነት በማሻከር ሊያለያይ ይችላል። የፍቺ የመጀመሪያው እርምጃ በስሜት በመራራቅ መፋታት መጀመር ነው። ጥንዶች እርስ በርሳቸው ለየት ያለ እንግዳ የሆነ መልካም ያልሆነ የስሜት ለውጥ ሲያዩ በእርጋታ ችግሩ ምንድን እንደ ሆነ በመጠየቅ ስሜታቸውን የጎዳውን ጉዳይ የማጣራትና ፈጥኖ መፍትሔ የማፈላለግ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ባለትዳሮች ይህን ማድረጋችን ለትዳራችን፣ ለአካላዊ፣ ለመንፈሳዊ፣ ለስነ ልቦናዊ ጤንነታችንና ለማሕበራዊ ግንኙነታችን ምትክ የለሽ የሆነ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው።

## 8. መመርመር፡- የሕክምና ባለሙያ በማነጋገር መመርመር

በባለትዳሮች መካከል ሚስቶችን ለግብረ ስጋ ግንኙነት ተነሳሽነት እንዳይኖራቸው ያደረገውን ችግር ለመረዳት የሐኪም ወይም የባለሙያ እርዳታ መጠየቅ አስፈላጊ የሚሆንበት ጊዜም አለ። ይህ በሚሆንበት ወቅት ወደ ሕክምና ባለሙያ በመሄድ ለግብረ ስጋ ግንኙነት ተነሳሽነት እንደጠፋባቸው በግልጥ በመናገርና ምርመራ በማድረግ የችግሩን ምንነት ሊያረጋግጡ ይገባል። በሕክምና ችግራቸውን ያረጋገጡ ሚስቶች (ጥንዶች) በሐኪም የሚታዘዝላቸውን የሕክምና ክትትል በመቀጠል መፍትሔ በጋራ እንዲያፈላልጉ ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል።

በሰለጠኑ አገሮች የተለያዩ ክርስቲያን ፕሮፌሽናልና ክሊኒካል የሆነ የማማከር አገልግሎት የሚሰጡ ባለሙያዎች አሉ። ከእነዚህ መካከል ለተጠቀሰው ችግር ከግብረ ስጋ ግንኙነት ጋር ተያዥነት ያላቸው ችግሮችን ለመፍታት የሰለጠኑ ባለሙያዎች መኖራቸው ጠቃሚ ነው። በምድራችን በተለያዩ ሙያዎችና ክህሎቶች የሰለጠኑ ባለሙያ የሆኑ ክርስቲያን አማካሪዎች ቢኖሩና ሕዝቡም የምክር አገልግሎት ተጠቃሚ በመሆን ችግሩ ባለትዳሮችን ከማጥቃቱና ፍችን ከማስከተሉ በፊት አስፈላጊውን እርዳታ





በማግኘት ችግሮቻቸውን ሊቀርፉ ቢችሉ ትልቅ ደስታን ይሰጠናል፡፡ ይህ ተከናውኖ ባለትዳሮች ችግራቸውን ሲቀርፉ ማየት የውስጥ ጩኸቴና ጸሎቴም ነው።

## 9. መቻል፡- በወንድና በሴት መካከል ያለውን የተፈጥሮ ልዩነት መረዳት መቻል

ባለትዳሮች በወንድና በሴት መካከል ያለውን የተፈጥሮ ልዩነት መረዳት መቻላቸው የግብረ ስጋ ግንኙነት በሚያደርጉበትም ወቅትም ሆነ በአጠቃላይ በትዳር ውስጥ በሚኖራቸው ኅብረት በመግባባት፣ በመቀባበል፣ በመረዳዳትና አንዱ ለሌላው የደስታና የእረፍት ምክንያት በመሆን እንዲኖሩ ከፍተኛ እገዛ ያደርግላቸዋል። ስለዚህ ወንድና ሴት ሆነን በመፈጠራችንና በፆታችን ልዩነት ምክንያት የሚመጣውን ተጽዕኖ፣ የፍላጎት፣ የጸባይ፣ የእሴትና የእይታ ልዩነታችንን በመገንዘብ ትዳራችንን ማነጽ ይኖርብናል። ይህ ዓይነቱ ግንዛቤ ልዩነታችንን ለማጥበብ፣ ለመረዳዳትና የጋራ ለሆነ ግብረ ስጋዊ ግንኙነት እርካታ የሚጫወተው ሚና ቀላል አይደለም። ክርስቲያን ባለትዳሮች ልዩነታቸውን በመረዳት በልዩነታቸው ምክንያት በመካከላቸው ሊፈጠር የሚችለውን ያለመጣጣምና ግጭት አስወግደው እርስ በእርስ በመሟላት በሚገኘው እርካታ፣ ሰላምና እረፍት ደስተኛ ሆነው እንዲኖሩ ለማገዝ በሚከተለው ስንጠረዥ በወንድና በሴት መካከል ያለውን ከግብረ ስጋ ግንኙነት ጋር የተያያዘ የተፈጥሮ ልዩነት ባጭሩ እንቃኛለን፡-

<u>በግብረ ስጋ ግንኙነት ላይ የባልና የሚስት ተፈጥሯዊ ልዩነት</u>

| ተ.ቁ | ተፈጥሯዊ ልዩነት | ወንዶች (ባሎች) | ሴቶች (ሚስቶች) |
|---|---|---|---|
| 1 | ጠባይ፣ ሁኔታ | አካላዊ | ግንኙነታዊና ሁለንተናዊ |
| 2 | መነሳሳት | አካላዊ አቋም ላይ ያተኮረ<br>እይታ<br>መዓዛ (ሽታ)<br>ተግባር | ማንነት<br>ንኪኪ<br>ጠባይ፣ ሁኔታ፣ አኳኋን<br>ቃላት/ ንግግር/ |
| 3 | ፍላጎት | መከበር<br>ሰውነት (አካላዊ የሆነ ግንኙነት) | መከበር<br>ስሜታዊ ግንኙነት<br>የቀረበ ግንኙነት |
| 4 | ለግበረ ስጋ ግንኙነት ያላቸው ምላሽ | ላይ በላይ (ግልብ የሆነ ስሜታዊነት)<br>ፈጣን የሆነ<br>አሳባቸው በሌላ ነገር ቶሎ የማይወሰድ | ውህደት<br>የዘገየ (ረጋ ያለ)<br>በተለያዩ ሁኔታዎች ቶሎ አሳባቸው ሊወሰድ የሚችል |
| 5 | ወሲባዊ እርካታ | ባጭር ጊዜ (በቶሎ) የሚጠናቀቅ የጋለ ስሜት<br>አብዛኛው አካላዊ ዝንባሌ ያላቸው መሆናቸው ነው። | ረዘም ያለ ጊዜ የሚፈልግ (በጥልቀት)<br>አብዛኛውን ጊዜ ስሜታዊ ዝንባሌ ያላቸው መሆናቸው ነው። |

ሰንጠረዥ 2[39]

## 10. መጠንቀቅ፡- የባልና ሚስት የሚፈልጉትን ለይተው ማወቅና ለጋራ ፍላጎት መጠንቀቅን መለማመድ

አብዛኛውን ጊዜ ባሎች ከሚስቶቻቸውና ሚስቶች ከባሎቻቸው ጋር ስላላቸው ግንኙነት በምክር አገልግሎት፣ በጋብቻ ትምህርትና በውይይት ወቅት ፍላጎታቸውን በስሞታ መልክ ሲናገሩ ይደመጣሉ፡፡ በእንደዚህ ዓይነት የውይይት ወቅት ስሜታቸውን ሲገልጡ ያንጸባርቋቸውን ሃሳቦች መሠረት በማድረግ በተለይ የግብረ ስጋ ግንኙነት ፍላጎትን እና ስነ ልቦናዊና አካላዊ መቀራረብን በተመለከተ ያላቸው ልዩነት በሚከተለው ሰንጠረዥ (ቻርት) ባጭሩ ቀርቧል። ይህን አሳብ በሰንጠረዡ ውስጥ ማቅረብ የተፈለገው በቻርቱ ውስጥ የቀረበው ሃሳብ በሁሉም ባለትዳሮች ዘንድ ይከሰታል ለማለት ሳይሆን በአብዛኛው ባለትዳሮች ላይ የሚታይ በመሆኑ ነው፡፡ ዓላማውም ባለትዳሮች እርስ በርስ በመረዳዳት የትዳር ጓደኛቸውን ፍላጎት በመገንዘብ አብረው

[39] Dr. Gary & Barbara Rosberg with Ginger Kolbabathe. <u>The 5 sex needs of men and women</u> Tyndale House Publishes, Inc. Carol Stream, illinois 2006.





እንዲኖሩና የትዳር ጓደኛቸው የግብረ ስጋ ግንኙነት ጥያቄ በሚያቀርብበት ወቅትም መከላከል እንዳይኖር፣ መጣጣም እንዲችሉና አንዳቸው ለሌላቸው የእረፍት ምክንያት እንዲሆኑ እገዛ የሚያደርግ ሃሳብ ለመስጠት ነው።

| ተ.ቁ | ባሎች ከሚስቶች የሚፈልጓቸው፣ የሚጠብቋቸውና ለሚስቶች የሚናገሯቸው፡- | ሚስቶች ከባሎች የሚፈልጓቸው፣ የሚጠብቋቸውና ለባሎች የሚናገሯቸው፡- |
|---|---|---|
| 1 | በግብረ ስጋ ግንኙነት ላይ ንቁ እንድትሆኑልን፣ | በፍቅር በሆነ ስሜታዊ መቀራረብ ቅረቡን |
| 2 | በተለያዩ ጉዳዮች ወንድነታችንን እወቁልን ብሎም በንግግርና በመታዘዝ አክብሮትን ስጡን፣ | ለግብረ ስጋ ግንኙነት ብቻ ሳይሆን እንዲሁ አብራችሁን ሆናችሁ እንድትደባብሱን እንፈልጋለን፣ |
| 3 | የምንፈልገውን የመጠየቅ ነፃነት ስጡን፤ በተለይም በግብረ ስጋ ግንኙነት መቀጣት ይቁምልን፣ | የጠለቀ የፍቅር ግንኙነት እንዲኖርን እንጂ የስሜታችሁ ማርኪያ ብቻ መሆን እንደማንፈልግ ተረዱን፣ |
| 4 | የግብረ ስጋ ግንኙነት ፍላጎታችንን ተረዱንና በጠየቅን ወቅት አዎንታዊ ምላሽ ስጡን እና | ሁለንተናዊ የሆነ ንጽህናን ከእናንተ እንፈልጋለን ይህን ስንል የአይን፣ የስሜት፣ የመንፈስና የአካል ንጽህና እንዲኖራችሁ እንፈልጋለን እና |
| 5 | ታማኝ ሁነን እንድንቀጥል የእናንተን ሁለንተናዊ እርዳታ እንፈልጋለን የሚሉ ናቸው:: | ታማኝ ሁኑልን የሚሉ ናቸው:: |

ሰንጠረዥ 3[40]

[40] Focus on The Family, <u>The first Five Years of Marriage</u>: Tyndale House publishing Inc Carol stream: Illinois, 2006. pp168-173

## ለጥንዶች በግላቸውና በቡድን ለማጥናት የሚረዷቸው የውይይት ጥያቄዎች
## የምዕራፍ ዘጠኝ (9)
## የውይይት ጥያቄዎች

1. የግብረ ስጋ ግንኙነትን ምንነትና መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረቱን በመጥቀስ ተወያዩበት::
2. በትዳር ውስጥ የግብረ ስጋ ግንኙነት ያለውን ዓላማና ሚና በመግለጥ በፍጹም ነፃነት ተነጋገሩበት::
3. በመካከላችሁ በግብረ ስጋ ግንኙነት መጣጣም ከሌለ ችግሩ ጎልቶ የሚታየው በማን ላይ እንደሆነና መንስኤው ምን ሊሆን እንደሚችልና ማረጋገጫዎችን በመጥቀስ በግልጥነት ተወያዩበት::
4. በጋራ በወያየት፣ የችግሩን መንስኤ በመረዳትና በጋራ የመፍትሔ ሃሳብ በመፈለግ አስፈላጊ ነው የምትሉትን ወቅታዊ የሆነ እርምጃ ላይ ተወያዩ:: መወሰድ ያለበት እርምጃ ምንድን ነው ትላላችሁ? በጋራ በመወያየት ተግባራዊ እንቅስቃሴ ለመውሰድ አቅዱ::
5. በወንዶችና በሴቶች /በባልና በሚስት/ የግብረ ስጋ ግንኙነት ላይ ሊፈጠር ስለሚችል ልዩነት በግልጥነት በመወያየት ወደ ፊት ልዩነትን በመረዳት ለማጥበብና በጋራ ለመረዳዳት ምን ማድረግ አለብን ትላላችሁ?
6. እንደ ባለትዳር አንዱ ከሌላው ምን እንደምትፈልጉ ስሜታችሁንና ፍላጎታችሁን በነፃነት የምትገልጹበት እንዲሁም የሌላውን አካል ፍላጎት ለመረዳት የምትችሉበትን ሁኔታ በማመቻቸት ለመረዳዳት ጥረት በማድረግ ተወያዩበት::





# ምዕራፍ አስር(10)
# የእምነትና የመንፈሳዊ መረዳት ልዩነት

## I. የእምነትና የመንፈሳዊ መረዳት ልዩነት ምንነት

የጥንዶች መሠረታዊ የእምነት ልዩነት የምንለው ጥንዶቹ የተለያየ ሃይማኖት ተከታይ በሚሆኑበት ጊዜ የሚያጋጥም ልዩነት ነው:: እንደዚህ ዓይነቱ ክስተት ጥንዶቹ በጌታ ከመሆናቸው በፊት የተጋቡ ሲሆንና አንዳቸው ብቻ ጌታን ሲቀበሉ ሊፈጠር ይችላል:: አንዳንድ ጊዜ አማኝ የሆኑ ወንድሞች ወይም እህቶች በሕይወታቸው ድካም ላይ በሆኑበት ወቅት ወይም በአስተሳሰብ መንጋደድ፣ ትክክለኛ ባልሆነ ፍላጎት ወይም በሌሎች ምክንያቶች አማኝ ካልሆኑ ሰዎች ጋር በትዳር በሚጣመሩበት ጊዜ የእምነት ልዩነት ሊፈጠር ይችላል:: እንደዚህ ዓይነት ጥንዶች ወደ ጽድቅ በሚወስደው የደህንነት መንገድ ላይ ከፍተኛ የሆነ ልዩነት ያላቸው ይሆናሉ::

የመንፈሳዊ መረዳት ልዩነት የምንለው ደግሞ በክርስቶስ አምኖ በመዳን ጉዳይ ላይ አንድ አቋም ኖሯቸው ነገር ግን በሌሎች የቤተ እምነቶች የዶክትሪንና የልምምድ ልዩነቶች አለመስማማትን የሚያመለክት ነው። በአንድ ቤተ እምነትና በአንድ አጥቢያ ውስጥ አባል ሆነው በመንፈሳዊ መረዳትና በሕይወት ብስለት ልዩነት ያላቸው ባልና ሚስትም የመረዳት ልዩነት ይታይባቸዋል:: መንፈሳዊ መረዳት ስንል በየጊዜው በክርስትና ሕይወት በእግዚአብሔር ቃል አብርሆት መለወጥ፣ ማደግ፣ መብሰልና መጠንከር የሚመጣ የክርስትና ሕይወት እድገት ባህርይ ነው /**1ኛጴጥ 2: 1-2**/:: ይህ ርዕስ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እንዲካተት የተደረገው በተፈጠረው የመረዳት ልዩነት ሊከሰቱ የሚችሉ አለመግባባቶችንና ግጭቶችን በመረዳት ለመቀነስና በጋራ በእርጋታ የእግዚአብሔርን ቃል በልበ ሰፊነት በመመርመር ለመማር፣ ለመለወጥና ለማደግ ራስን፣ ትዳርንና ቤተሰብን ለሕይወት ኃላፊነት ለማዘጋጀት እንዲችሉ ክርስቲያን ባለትዳሮችን ለመርዳት ነው።

## II. በመንፈሳዊ ሕይወትና መረዳት ልዩነት መሠረት የግጭት መንስኤዎች

ጥንዶች የተለያዩ ሰዎች እንደመሆናቸው በመካከላቸው የዕድሜ፣ የአካል፣ የመንፈሳዊ ሕይወት ልምምድ፣ የመንፈሳዊ ዕድገት፣ የብስለት ደረጃና አንዳንድ ጊዜም የሃይማኖት ልዩነቶች ሊኖሯቸው ይችላል። እንደዚህ ዓይነቱ በጥንዶች መካከል ያለው የእምነትና የመንፈሳዊ መረዳት ልዩነት ደግሞ በልዩ ልዩ ገጠመኞች ወቅት በመካከላቸው አለመግባባትና ግጭት እንዲፈጠር ምክንያት መሆኑ አይቀሬ ነው። በእርግጥ በመንፈሳዊ ብስለትና እንቅስቃሴ ሁሉ ባልና ሚስት አንድ ዓይነት አንሆንም:: ደግሞም በሁሉም ነገር አንድ ዓይነት መሆን የለብንም! ነገር ግን ልዩነታችን ለግጭትና ላለመግባባት ምክንያትን መስጠት የለበትም:: ለምሳሌ:- የንጉስ ዳዊትንና የሚስቱን የሜልኮልን የመንፈሳዊ ሕይወትና የመረዳት ልዩነት ልንጠቅስ እንችላለን::

ንጉስ ዳዊት እግዚአብሔርን ለማክበር በሁለንተናዊ መሰጠት አምልኮውን በእግዚአብሔር ፊት ያቀረበ ሲሆን፡፡ ለእግዚአብሔር ክብር በሚያደርገው አምልኮ ምክንያት መናቅም ቢደርስበት እንኳን ያለጸጸትና ያለማመቻመች ለንጉስነት ክብሩ ሳይጨነቅ አምልኮውን ለአምላኩ ለማቅረብ የማያወላውል አቋም ይዞ ነበር፡፡ እውነተኛው የሕይወቱ ኃላፊነትም ራሱን በመናቅና ዝቅ በማድረግ እግዚአብሔርን ማክበር መሆኑን በአግባቡ ተረድቶ ስለነበር በንግስና ስርዓት ጭምብል ውስጥ ተደብቆ ግላዊ ክብሩን መንከባከብ ላይ ያተኮረ አቋምና ኑሮ አልነበረውም፡፡ በተቃራኒው ሚስቱ ሜልኮል ደግሞ እግዚአብሔርን ለማክበር ዳዊት ያደረገውን የአምልኮ ተግባር ለንጉስ የማይገባ እንደሆነ አቋም ይዛ ነበር፡፡

ንጉሱ ዳዊት ለእግዚአብሔር የሚያቀርበው አምልኮም የንጉስነት ክብሩንና ማዕረጉን በሚመጥንና ማሕበራዊ ክብሩን በጠበቀ መልኩ ብቻ ሊደረግ ይገባል የሚል አመለካከት ታራምድ ነበር፡፡ እንዲህ ዓይነት መረዳት ላይ የተመሠረተ አቋም ስለነበራትም ዳዊት ለእግዚአብሔር ክብር ለመስጠት ግላዊና ማሕበራዊ ክብሩን በመጣል ባደረገው እንቅስቃሴ ደስ ባለመሰኘት ናቀችው፡፡ ባደረገውም ነገር መሸማቀቅና እፍረት እንዲሰማው ተጽዕኖ ልታደርግበት ሞከረች፡፡ ይህም ከስተት መጽሐፍ ቅዱስ *"የእግዚአብሔርም ታቦት ወደ ዳዊት ከተማ በደረሰ ጊዜ የሳኦል ልጅ ሜልኮል በመስኮት ሆና ተመለከተች ንጉሥም ዳዊት ሲዘፍንና ሲጫወት አይታ በልቧ ናቀችው።"* /1ኛዜና 15፡ 29፤ 2ሳሙ 6፡ 20-22/ በማለት እንደሚናገረው በግንኙነታቸው ላይ ግልጥ የሆነ ከፍተትና አሉታዊ ተጽዕኖ ፈጥሮ ነበር። ስለዚህ ክርስቲያን ባለትዳሮች ይህን እውነታ በመረዳት በመካከላቸው ያለውን የብስለትና የመረዳት ልዩነት ለማጥበብ፣ እርስ በእርስ በሚገባ ለመተዋወቅና የተሻለ የሚባለው አካል ደካማውን በመረዳት፣ በመሸከምና በመታገስ በጥሩ ኅብረትና ስምምነት አብረው ጌታን በማክበር ሊኖሩ ይገባል፡፡ እንደዚህ ማድረጋቸው በመጀመሪያው አስር አመታት የጋብቻ ዘመናቸው የመንፈሳዊ ሕይወት ብስለት ደረጃና የመረዳት ልዩነት ምክንያት ሊፈጠሩ በሚችሉ ችግሮች ሰበብ የሚነሱ ግጭቶችን ለመቀነስና በመልካም ሁኔታ ለመቆጣጠር ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው። እነዚህን በትዳር ውስጥ ለግጭትና አለመግባባት መፈጠር ምክንያት የሆኑ ከእምነትና ከመንፈሳዊ መረዳት ልዩነት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ችግሮችንና መፍትሔዎቻቸውን በሚከተሉት ነጥቦች በመቃኘት ጥንዶች ግንዛቤ እንዲያገኙና መፍትሔዎችን በመጠቀም ከችግሩ ትዳራቸውን እንዲጠብቁ የመርዳት ጥረታችንን እንቀጥላለን፡፡

## 1. አንዱ አካል በጌታ ያላመነ መሆን

ይህ ርዕሰ ጉዳይ መነሳቱ በክርስቲያናዊ ትዳር ያመነ ካላመነ ጋር ሊጋቡ ይችላሉን? የሚል ጥያቄ ሊያስነሳ ይችላል። እውነት ነው ያመነ ካላመነ ጋር መጋባት እንደሌለባቸው መጽሐፍ ቅዱስ አስረግጦ ይናገራል። በአካባቢያችንና በየአጥቢያችን ቤተ ክርስቲያናችን እንደምናየው እንዲሁም በማማከር አገልግሎት ካጋጠሙኝ ልዩ ልዩ ክስተቶች በመነሳት ለምን አማኝ ያላመነን ሊያገባ እንደሚችል በሚከተሉት አሳቦች ባጭሩ ለመጠቆም እሞክራለሁ።

ችግሩ በሁሉም ቦታ የሚታይ ቢሆንም ከአገር ቤት ውጭ የሚኖሩ አማኞች በአገር ቤት ከሚኖሩት ይልቅ ለዚህ ችግር የበለጠ ተጋላጭ ናቸው። በጌታ ሆነው ከማያምን ሰው ጋር ጋብቻ የሚፈጽሙ ወገኖች ይህን የሚያደርጉባቸው የየራሳቸው ምክንያቶች አሏቸው፡፡ **እንዳንዶች** ኑሮን ለማሸነፍ፣ ሌሎች ማግባት ያለባቸው ጊዜ ያለፈባቸው ሲመስላቸው፣ ተገቢ ባልሆነ መቀራረብ ምክንያት፣ ውጫዊ በሆነ ነገር ሲሳቡና ሲፈተኑ፣ በወቅቱ ከጌታ በመራቅ ዓለማዊነት ሲያሸንፋቸውና ከጋብቻ በኋላ ወደ ጌታ ይመጣል የሚል ተገቢ ያልሆነና የተሳሳተ ተስፋን ምክንያት በማድረግ አማኝ የሆኑ ወንድሞችና እህቶች ከማያምን ሰው ጋር ጋብቻ ይፈጽማሉ፡፡ ከዚህም ባሻገር ወደ ጌታ ከመምጣታቸው በፊት ትዳር ከመሠረቱ ባለትዳሮች መካከል አንደኛው አካል ብቻ ጌታን የግል አዳኙ አድርጎ በመቀበል ክርስቲያን በሚሆንበት ወቅት አንዱ አካል አማኝ ሌላው አካል የማያምን የሚሆኑበት አጋጣሚ ይፈጠራል።

አማኝና አላማኝ በሆኑ ጥንዶች መካከል ግጭት ቢፈጠር ምንም የሚያስደንቅ ነገር አይደለም። በሁለቱ መካከል ያለው መንፈሳዊ ልዩነት በብርሃንና በጨለማ መካከል ያለውን ልዩነት የሚያክል ክፍተት ነውና! *"ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመዱ፤ ጽድቅ ከዓመፃ ጋር ምን ተካፋይነት አለውና? ብርሃንም ከጨለማ ጋር ምን ኅብረት አለው? ክርስቶስስ ከቤልሆር ጋር ምን መስማማት አለው? ወይስ የሚያምን ከማያምን ጋር ምን ክፍል አለው?"* /2ኛቆሮ 6፡ 14-15/፡፡ አማኝ የሆነ ወንድም ወይም እህት ከማያምን ሰው ጋር መጋባት ፈጽሞ ስህተት እንደሆነ ማሰብና ትክክለኛ ውሳኔ መወሰን ያለበት በቅድመ ጋብቻ ወቅት እንጂ ከተጋቡ በኋላ አይደለም፡፡ ባላመኑና አማኝ በሆኑ የትዳር ጓደኞች መካከል በሚፈጠር የማያቋርጥ ግጭት የሚሰቃዩና ብሎም ትዳራቸውን በማፍረስ በፍች የተለያዩ ክርስቲያን ባለትዳሮች ቁጥራቸው ጥቂት አይደለም። ነገር ግን አማኞች መረዳት ያለባቸው ስቃዩና ችግሩ ምንም ቢበዛ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የቅዱሳት መጽሐፍትን መርህ ተላልፈው ከማያምን ሰው ጋር በትዳር ከተጣመሩ በኋላ በጌታ ነኝ፣ መንፈሳዊ ነገር አሁን በርቶልኛል፣ ሕይወት አግኝቻለሁ፣ እንደ በፊቱ አይደለሁምና ድሮ ሳይገባኝ የፈጸምኩት ይበቃኛል የመሳሰሉ ምክንያቶችን በማንሳት ትዳራቸውን ለማፍረስ ሰበብ የመፈለግ መብት የሌላቸው መሆኑን ነው።

## 2. የመንፈሳዊ ብስለት ልዩነት

ክርስትና ሁልጊዜ ከክርስቶስ ጋር፣ በክርስቶስና ለክርስቶስ መኖርን የሚጠይቅ የየዕለት ኑሮ ነው። የተለያዩ የቅዱሳት መጽሐፍት ክፍሎች ሥር መስደድ፣ ማደግ፣ መጠንከርና ወደ ሙላቱ ልክ ማደግ ... በሚሉ አሳቦች የመንፈሳዊ ብስለትን አስፈላጊነት ግልጥ በሆነ መንገድ ያሳያሉ፡፡ *"እንግዲህ ጌታን ክርስቶስ ኢየሱስን እንደ ተቀበላችሁት በእርሱ ተመላለሱ። ሥር ሰዳችሁ በእርሱ ታንጹ፥ እንደ ተማራችሁም በሃይማኖት ጽኑ፥ ምስጋናም ይብዛላችሁ።"* /ቆላ 2፡ 6-7/፡፡ በተቃራኒው ደግሞ በክርስቶስ ሕጻናት (ብስለት የጎደላቸው አማኞች) እና

ስጋዊያን መሆን እንደማይገባን *"ከጊዜው የተነሳ አስተማሪዎች ልትሆኑ ሲገባችሁ፥ አንድ ሰው ስለ እግዚአብሔር ቃላት መጀመሪያ ያለውን የሕፃንነትን ትምህርት እንዲያስተምራችሁ እንደ ገና ያስፈልጋችኋልና..."* /ዕብ 5፡ 11-14፤ 1ኛቆሮ 3፡ 1-3/ በማለት መጽሐፍ ቅዱስ ያስጠነቅቃል።

**አንዳንዶች** ተመስክሮላቸው ወደ ጌታ እንደመጡ ብዙ በክርስትና ሳይቆዩ ወደ ትዳር ዓለም ይገባሉ:: የተወሰነ አመት በክርስትና አስቆጥረው ነገር ግን አጠንክረው ክርስትናን ሳይዙ የፕሮግራም ደንበኛ በመሆን ብቻ አመታትን ይቆጥራሉ:: አንዳንዶች ደግሞ ከቤተሰብ ክርስትናን ወርሰዋል እንጂ በግላቸው ጌታን የግል አዳኝ አድርገው በመቀበል የተለወጠ ማንነት የሌላቸው ይሆናሉ:: የቤተ ክርስቲያን ስርዓትና ቋንቋ በመልመድ ለጊዜው የሚፈልጉትን እስኪያገኙ ድረስ በማስመሰል መቆየት የሚችሉ ሰዎችን ማየት በአሁኑ ዘመን አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ እንግዳ ክስተት አይደለም። በእነዚህ ሁሉ መንገዶች ውስጥ እየተጓዙ ያሉ ወገኖች ክርስቲያን በመባል ይታወቃሉ:: በቤተ ክርስቲያን ስርዓት መሠረትም ከክርስቲያን ወገኖች ጋር ትዳር ይመሠርታሉ:: ነገር ግን በዚህ መንገድ ወደትዳር በመግባት የባልና ሚስት ውል የፈጸሙት ክርስቲያን ወንድምና ክርስቲያን እህት ጥቂት ጊዜ አብረው እንደቆዩ በመካከላቸው ሰፊ የሆነ የመንፈሳዊ መረዳትና ብስለት ልዩነት እንዳለ ይገነዘባሉ::

ልዩነታቸውም ልዩ ልዩ ግጭቶችና አለመግባባቶች በመካከላቸው እንዲፈጠር መነሻ ምክንያት ይሆናል:: ይህ ሁኔታ የሚያሳየን በመንፈሳዊ ብስለት ደረጃችንና ለመንፈሳዊ ሕይወትና አገልግሎት በምንሰጠው እሴት ልዩነት ምክንያት በትዳራችን ግጭትና አለመግባባት የመፈጠር እድሉ ሰፊ መሆኑን ነው:: እንደዚህ ዓይነቱም ልዩነት በሕይወት ለውጥና በማያቋርጥ እድገት ክፍተቱ ካልጠበበ ለፍችም ተጋላጭ ሊያደረገን ይችላል::

## 3. ለቤተ ክርስቲያን ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች ያልተመጣጠነ ትኩረት መስጠት

ክርስቲያኖች ከጋብቻ በፊት የነበራቸው ለራስ በራስ የመወሰን፣ ጊዜን ለፈለጉት ጉዳይ የመጠቀም፣ በቤተ ክርስቲያን ባሉት ፕሮግራሞች ሁሉ የመሳተፍና የማገልገል ልምድ በቀላሉ አይለቃቸውም። ወደ ትዳር በሚገቡበትና ወላጅ በሚሆኑበት ወቅት ሁኔታዎች በላጤነትና ልጆች ባልተወለዱበት ወቅት እንደነበረው ላይቀጥሉ ይችላሉ። ቀድሞ የነበረው ልምምድ እንዲቀንስ የሚያስገድድ ሁኔታ ሲፈጠር በብስጩነት ስሜታዊ በመሆን ወደ ግጭት ለመግባት ይጋበዛሉ። ትዳርን፣ ቤተሰብን፣ የቤተ ክርስቲያን ፕሮግራምንና አገልግሎትንም ሚዛኑን በጠበቀ መንገድ ማከናወን ካልተቻለ ሌላኛው ግጭት የሚፈጠርበት ምክንያት መሆኑ የግድ ነው። ሁልጊዜ ሚዛን ያልጠበቀ ድርጊት ሲኖር ማለትም ወደ አንድ ጽንፍ የተለጠጠ አመለካከትና የሕይወት ልምምድ ሲጀመር ጉዳዩ ከተጠበቀው ውጤት የተለየ አቅጣጫ የመያዙ እድል በጣም ከፍተኛ ነው። በቤተ ክርስቲያን የሚከናወኑ የተለያዩ የጸሎት፣ የአምልኮ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ





ጥናት፣ የልዩ ልዩ የአገልግሎት ዘርፍ ፕሮግራሞችና የቤተ ክርስቲያን ትናንሽና ትላልቅ ስብሰባዎች ሁሉ ትርጉም ያለው ጊዜን የሚጠይቁ ናቸው። እነዚህን ጊዜ ጠያቂ የሆኑ ተግባሮች ከትዳርና ከቤተሰብ ሕይወት ጋር አጣጥሞ ለማስኬድ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባውን ጉዳይ መለየትና መመጠን ያስፈልጋል።

በነገሮች ላይ በግልጥነት ተወያይቶ መግባባትና መረዳዳት እንደተጠበቀ ሆኖ ለትዳርና ለቤተሰብ ቅድሚያ መስጠት እንዳለብን ግን የማያወላዳ አቋም ልንይዝ ይገባል። ለትዳራቸው ቅድሚያ በማይሰጡ፣ በጣም መንፈሳዊ የሆኑ በሚመስላቸውና በብዙ ፕሮግራሞች ላይ መገኘትና መሳተፍ አለብኝ ብለው በሚያስቡ አንዳንድ ጥንዶች ትዳር ላይ የማያቋርጥ ግጭት ይፈጠራል:: ግንኙነታቸውም ይሻክራል። መንፈሳዊ እንደሆኑ የሚነግራቸው ስሜታቸውም ሳያስቡት ይከዳቸዋል:: በስተመጨረሻም በትዳር ውስጥ በሚያጋጥማቸው ግጭትና ቀውስ ምክንያት በሚካፈሏቸው መንፈሳዊ ፕሮግራሞች ብዛትና በሃይማኖት ስርዓቶች ተጀቡኖ መንፈሳዊ ጭምብል የተላበሰው ስጋዊና ያልበሰለ ማንነታቸው በግል ሕይወታቸውና በትዳራቸው ውስጥ የሚገለጥበት ሁኔታ ይፈጠራል:: ይህንን በማስተዋልና አርቆ በማሰብ ክርስቲያን ባለትዳሮች እውነተኛውን መንፈሳዊነት በግል ሕይወታችን ከዚያም ከትዳር ጓደኛችን ጋር ባለን ጤናማ ኅብረት እንዲሁም ለቤታችንና ለትዳራችን በምንሰጠው በቂና የተመጣጠነ ጊዜ ልንኖረው ይገባል::

## 4. የራዕይ ልዩነት

የራዕይ ልዩነት ሲባል በሕይወት፣ በኑሮና በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ ጥንዶቹ የሚኖራቸው የተለያየ እይታ ነው። ለምሳሌ ያክል አንደኛው የትዳር አጋር ስለአገልግሎት ያለው መረዳትና የተሰጠው ራዕይ ከሌላው የትዳር አጋር መረዳትና ራዕይ ጋር ያለውን ልዩነት በብስለት መያዝ ካልተቻለ በመካከላቸው አለመግባባትና ግጭት ሊፈጥር ይችላል። አንዱ የትዳር አጋር ያለው የአገልግሎት ራዕይ ወደ ፍጻሜ እንዲደርስ ካስፈለገ የመጀመሪያውን ትብብር የሚያገኘው ከትዳር አጋሩ ሊሆን ይገባል። ይህ እንዲሆን ራዕይን በግልጥ የማካፈልና አስረድቶ የማሳመን ትጋቱን ተቀባይነት እስኪያገኝ ድረስ በትዕግስት በጋራ በመጸለይና በመወያየት መጠበቅ አስፈላጊ ነው። ዋጋ ከፍሎ የትዳር አጋርን የአገልግሎት ራዕይ ተካፋይ ማድረግ መንፈሳዊነትም ብስለትም ነው። ራዕይ ከሚጠይቃቸው ነገሮች መካከል አንዱ ተባባሪ ሰዎችን ማፍራት ነው። ይህ አልሳካ ብሎ የትዳር አጋር የአገልግሎት ራዕይ ተባባሪ ከመሆን ይልቅ ተከራካሪና ተቃዋሚ በሚሆንበት ወቅት ግጭት መፈጠሩ የማይቀር ነው:: ግጭቱም ተባብሶ ግንኙነትን ከማሻከር ባሻገር የአገልግሎት ተነሳሽነትንም ሊያጠፉ ይችላል።

## 5. አስራት፣ መባና ስጦታ ላይ የጎላ ልዩነት መፈጠር

በአንዳንድ ባለትዳሮች መካከል ከሚፈጠረው ችግር አንዱ ለእግዚአብሔር ቤት ሥራ አማኞች እንዲሰጡ የታዘዘውን አስራትና መባ መስጠትና አለመስጠትን

በተመለከተ ካላቸው ልዩነት ጋር የተያያዘ ነው። አንዳንድ ሰዎች የገቢያቸውን አንድ አስረኛ ማለትም የአስራታቸውን መጠን ሌሎች ጉድለቶችን ይሸፍናል ብለው በማሰብና ጉድለትን ለመድፈን በሚደረግ ውጥረት አስራትን ወደ ቤተ ክርስቲያን ለማምጣትና ለመስጠት ሲቸግራቸው ይደመጣሉ። አንዳንዶችም ስለአስራት አዲስ ኪዳን ምንም አይልም የሚል ማብራሪያ በማቅረብ አስራትን ለቤተ ክርስቲያን ከመስጠት ይልቅ ላለመስጠት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ ምክንያት ማቅረብ ይመርጣሉ። አስራት ማውጣት አንዱ ከገንዘብ በላይ እግዚአብሔር የሕይወታችን ገዥና አለቃ መሆኑን የምንመሰክርበትና ሁሉንም እርሱ እንደሰጠንና ሁሉ የእርሱ እንደሆነ እውቅና የምንሰጥበት ነው።

## III. በእምነትና በመንፈሳዊ መረዳት ልዩነት ምክንያት ለሚፈጠሩ ግጭቶች መፍትሔዎች

### 1. መሆን፡- በጌታ የሆነው አካል በክርስቲያናዊ ስነ ምግባር ምሳሌ መሆን

ዳግም ልደትን በማግኘት ክርስቲያን ያልሆኑ የትዳር ጓደኞች ክርስትናን ባለመረዳትና በሚከተሉት እምነት ተጽዕኖ ምክንያት አማኙን የትዳር ጓደኛቸውን መቃወም ጽድቅ አድርገው በመቁጠር በትዳር አጋራቸው ላይ ጎጂ ተጽዕኖ ሊያደርሱ ይችላሉ። በአንዳንዶቹ በተለያየ የሰይጣን አሠራር ተጽዕኖ ውስጥ መሆንና በተለያዩ ሱሶች በመጠመድ ምክንያት ግጭቱ ሊባባስ ይችላል። በዚህ ወቅት ክርስቲያን የሆነው አካል ክርስቲያናዊ በሆነ ሕይወት ምሳሌ መሆን ይጠበቅበታል።

ብዙ ጊዜ ክርስቲያን በሆኑ የትዳር ጓደኞች በኩል የሚታየው ችግር የክርስትናን ሕይወት የሚያስነቅፍ ኑሮ መኖራቸው ነው። በአሁኑ ወቅት ከማያምኑት ያልተሻለ አንዳንዴም የባሰ የስነ-ምግባር ዝቅጠት በኑሯቸው የሚያሳዩ ክርስቲያን የትዳር ጓደኞችን ለማየት ብዙ ጥረት አይደለም። የማናስተውላቸው ነገር ግን የሕይወትን ንጽህናና የትዳርን ግንኙነት የሚያሻክሩ እንደ ቁጣ፣ ስድብ፣ ሐሜት፣ ምሬት፣ ማኩረፍ፣ የስንፉና ንግግር፣ የትዳር ጓደኛን አለማክበርና ገንዘብን መውደድ የመሳሰሉ ኃጢአቶች በክርስቲያን ባለትዳሮች ዘንድ መዘውተራቸው ክርስቲያን የትዳር አጋሮች የክርስቲያናዊ ስነ-ምግባርን ከቡርነት ዋጋ ዝቅ ያደረገ አኗኗር መከተላቸውን የሚያሳዩ ናቸው። እንዲህ አይነት ኑሮ በክርስቲያን ሕይወት ሊታይና ሊዘወተር እንደማይገባ *"እንግዲህ በምድር ያሉቱን ብልቶቻችሁን ግደሉ፥ እነዚህም ዝሙትና ርኵሰት ፍትወትም ክፉ ምኞትም ጣኦትንም ማምለክ የሆነ መጎምጀት ነው። በእነዚህም ጠንቅ የእግዚአብሔር ቍጣ በማይታዘዙ ልጆች ላይ ይመጣል። እናንተም ደግሞ ትኖሩባቸው በነበራችሁ ጊዜ፥ በፊት በእነዚህ ተመላለሳችሁ። አሁን ግን እናንተ ደግሞ ቍጣንና ንዴትን ክፋትንም፥ ከአፋችሁም ስድብን የሚያሳፍርንም ንግግር እነዚህን ሁሉ አስወግዱ። እርስ በርሳችሁ ውሸት አትነጋገሩ፥ አሮጌውን ሰው ከሥራው ጋር ገፋችሁታልና፥የፈጠረውንም ምሳሌ እንዲመስል እውቀትን ለማግኘት የሚታደሰውን አዲሱን ሰው ለብሳችሁታል።"* /ቆላ 3፡ 5-10/ የሚለው የእግዚአብሔር ቃል መርህ አስረግጦ ይነግረናል።





በተለይም በወንጌሉ እውነት አማኝ ያልሆኑ የትዳር ጓደኞች ካሉን እንደ ክርስቲያን የላቀ፡ ምሳሌነት የተሞላ፣ ክርስቶስን የሚገልጥና የሚያሳይ ኑሮን በየዕለቱ በመኖር ክርስቶስን ያለመቀበል ፍላጎት እንዳይኖራቸው የሚያደርግን ማንኛውንም እንቅፋት የሚሆን ነገር ከቤታችንና ከኑሯችን ልናስወግድ ይገባል፡፡ ይልቁንም በሕይወት ተማርከው ክርስቶስን እንዲያምኑና እንዲከተሉ ለማገዝ መልካም ተፅዕኖ ማምጣት የሚችል መጽሐፍ ቅዱሳዊውን የሕይወት ከቡርነት የሚያሳይ ኑሮ የመኖር ኃላፊነት አለብን። ሐዋሪያው ጳውሎስ ለጢሞቲዎስ *"በቃልና በኑሮ በፍቅርም በእምነትም በንጽሕናም ለሚያምኑቱ ምሳሌ ሁን እንጂ፥ ማንም ታናሽነትህን አይናቀው።"* /1ኛጢም 4፡ 12/ በማለት የመከረውን ምክር እንደ መርህ በመውሰድ አማኝ የሆኑ የትዳር ጓደኞች ምሳሌነታቸው አማኝ ባልሆነ የትዳር አጋር ዘንድ አክብሮትን የሚያስገኝላቸውና ንቀትን የሚያርቅላቸው ሊሆን ይገባዋል።

### 2. መፍቀድ፡- ሁልጊዜ ለመማርና ለማደግ መፍቀድ

የክርስትና ሕይወት ከዳግም መወለድና መንፈሳዊ ሕጻን ከመሆን ይጀምራል። ይህንን ሕይወት የጀመሩ አማኞች ሁሉ ከሕጻንነት ሕይወት ለመውጣት ሁል ጊዜ ለመማርና ለማደግ የሚፈልጉ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት በመሆን ትጋት የሕይወት ዘመናቸውን መምራት አለባቸው፡፡ በክርስትና ሕይወት ሁሉን አውቆ እድገትን መጨረስ የሚባል ነገር የለም። ነገር ግን ሁልጊዜ በእድገትና ክርስቶስን በመምሰል የማያቋርጥ ምኞት፣ እርምጃና ግስጋሴ መስመር ላይ እየተጓዝን ዘመናችንን ለመፈጸም ዝግጁ መሆን አለብን። ከዚህ የሕይወት መርህ ጋር ከተግባባን ደግሞ *"እንግዲህ ክፋትን ሁሉ ተንኰልንም ሁሉ ግብዝነትንም ቅንዓትንም ሐሜትንም ሁሉ አስወግዳችሁ፥ጌታ ቸር መሆኑን ቀምሳችሁ እንደ ሆነ፥ ለመዳን በእርሱ እንድታድጉ አሁን እንደ ተወለዱ ሕፃናት ተንኰል የሌለበትን የቃልን ወተት ተመኙ።"* /1ኛጴጥ 2፡ 2-3/ የሚለውን የእግዚአብሔር ቃል በመረዳት እንደ ክርስቲያን ባልና ሚስት በጋራ ለማደግ መነሳትና መደጋገፍ ያስፈልገናል።

እንደ ክርስቲያን ባለትዳር በክርስትናና በመንፈሳዊ ሕይወት እድገት ጎዳና ላይ ወደፊት ለመገስገስ ቤታችን አንዱና ዋናው ለመንፈሳዊ ሕይወት እድገት አስፈላጊ የሆኑት የጸሎት፣ የቃሉ ጥናትና የአምልኮ ኅብረት የማድረግ ክርስቲያናዊ እንቅስቃሴዎችንና አገልግሎትን የምንለምድበት የመጀመሪያው ቦታ ሊሆን ይገባዋል። ተምሮ መመረቅና እድገ መጨረስ በሌለበት የክርስትና ሕይወት ትምህርት ቤት ውስጥ ሁልጊዜ ቃሉን በመማርና ስር በመስደድ እግዚአብሔርን በየዕለቱ ለማወቅና ለማምለክ ራሳችንን መስጠት ይኖርብናል፡፡ ለዚህ ሕይወት የሚከፈለውን ዋጋ በመክፈል ለማደግ ጥረት ማድረግ *"የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ። እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን።"* /ኢያሱ 24፡ 15/ ከሚለው የኢያሱ አቋም ጋር መስማማታችንን በተግባራዊ ምላሽ የምናረጋግጥበት የሕይወት አዋጅ ነው። በእንዲህ ዓይነት የሕይወት መርህ ለመኖር ከተስማማንና አቋም ከያዝን በትዳራችን ውስጥ ብስለት በማጣትና በመንፈሳዊ ቀውስ ውስጥ በመገኘት ምክንያት ሊፈጠር የሚችለውን ግጭትና አለመግባባት አስቀድመን

ይታያሉ፡፡ በእርግጥ ለትዳር ጓደኛና ለቤተሰብ ያለን ፍቅር ከጌታ ፍቅር ሲበልጥብንና ክርስቶስን እንዳንከተለው የሚከለክለን ሲሆን በሞቱ ሕይወት የሰጠንን ጌታ በማንኛውም መስዋዕትነት ውስጥ የመከተል ቅድሚያ ልንሰጥ ይገባል፡፡ ነገር ግን ይህ ዓይነት ችግር በሌለበት ለትዳርና ለቤተሰብ የሚሰጠውን ጊዜና ትኩረት በመተው በሙሉ ኃይላችንና ትኩረታችን ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ያለ አገልግሎት ላይ መሰለፍ ተገቢ አይደለም። ትክክለኛ አገልግሎት ለትዳርና ለቤተሰብ እንክብካቤንና ትኩረትን ከመስጠት ይጀምራል።

**ትክክለኛ አገልግሎት ለትዳርና ለቤተሰብ እንክብካቤንና ትኩረትን ከመስጠት እንደሚጀምር አንዘንጋ!!**

ነገር ግን በተሳሳተ ሁኔታ ጥቅስን በማጣቀስ ራስን ከትዳርና ከቤተሰብ አርቆ አገልግሎትን መደበቂያ ከማድረግ በፍጥነት መመለስ ካልተቻለ አንድ ቀን በዚህ ስህተት የመጀመሪያው ተጠቂ ትዳርና ቤተሰብ እንደሚሆን ከወዲሁ መረዳት ያስፈልጋል። ከቤት ያልተጀመረ አገልግሎት ትክክለኛ አገልግሎት ካለመሆኑም ባሻገር አገልግሎቱ ዘላቂ አይሆንም። *"ልጆቹን በጭምትነት ሁሉ እየገዛ የራሱን ቤት በመልካም የሚያስተዳድር፤ ሰው ግን የራሱን ቤት እንዲያስተዳድር ባያውቅ፥ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን እንዴት ይጠብቃታል?"* /1ኛጢሞ 3፡ 4-5/፡፡ ስለዚህ እያንዳንዱ የትዳር አጋር አንዱ የሌላውን የጸጋ ስጦታ እንዲረዳ በማገዝ በዚያው ጸጋ እርስ በእርስና ቅዱሳን እንዲገለገሉበት ምቹ ሁኔታን መፍጠር ተገቢ ነው። ለትዳርና ለቤተሰብ ቅድሚያ በመስጠት ጌታን በታማኝነት ለማገልገልና ለቅዱሳን መታነጽ መኖር የሚቻልበት ትክክለኛ የሕይወት መስመርና የልምምድ ተቋም ነው። *"እያንዳንዳችሁ የጸጋን ስጦታ እንደ ተቀበላችሁ መጠን በዚያው ጸጋ እርስ በርሳችሁ አገልግሉ፤"* /1ኛጴጥ 4፡ 10/፡፡

## 6. መጣር፡- በትክክለኛ ራዕይ ቢጋራ ለማደግ መጣር

በምድር ስንኖር ጌታ ፈጽመነው እንድናልፍ ወይም ለቀጣይ ትውልድ እንድናስተላፈው የሰጠን ራዕይ ሊኖር ይችላል። በራዕይ ለመኖርና ራዕይን ወደ ፍጻሜ ለማምጣት ባለው ሂደት ከትዳር አጋር ጋር በተለያየ መልኩ አብሮ መቆም ወሳኝ ነው። በዚህ ሂደት በሙሉ መሰጠት ከመተባበር በፊት በራዕይ ላይ ወደ ጋራ ስምምነት የመድረሱ ሂደት መቀባበልን ይጠይቃል። ይህን ሂደት በአግባቡ ለማሳካት ራዕይን ጥበብ በሞላው ብስለት ለትዳር ጓደኛ ማካፈል አስፈላጊ ነው። በተሳካ ሁኔታ ይህን ተግባር ለማከናወን ራዕይን የምናካፍለበት ትክክለኛ ጊዜ፣ ምቹ ቦታና ስልት ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። *"ራእዩ ገና እስከ ተወሰነው ጊዜ ነው፥ ወደ ፍጻሜውም ይቸኵላል፥ እርሱም አይዋሽም ቢዘገይም በእርግጥ ይመጣልና ታገሠው እርሱ አይዘገይም።"* /ዕን 2፡ 3/

እንደ ባለትዳር ከሁለት አቅጣጫ ሚዛንን መጠበቅ አስፈላጊ ነው። እንደ ባለራዕይ ደግሞ በራዕይ መኖር አስፈላጊ ነው፡፡ ነገር ግን ራዕይን የጋራ ለማድረግ ወይም





ተደጋግፎ ራዕይን ወደፍጻሜ የመውሰድ ስምምነት ላይ ለመድረስ የትዳር አጋሮች ራዕዩውን አምነው እስኪቀበሉት ድረስ ጥረት በማድረግ የመጠበቅ ባህል ቢኖር ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው። በሚደገረው ጥረት ውስጥ ከመተባበር ይልቅ መከራከር የሚያጋጥም ከሆነ በትዕግስት፣ በማስተዋልና በፍቅር ማሸነፍ የሚቻልበትን መንገድ መፍጠር ተገቢ ነው። ራይውን የሚካፈለው የትዳር አጋርም አስቀድሞ ተቃዋሚ ከመሆንና ግጭት ውስጥ ከመግባት ይልቅ ራዕዩን ለመረዳትና የትዳር ጓደኛን ለመርዳት ከመነሳት መጀመር መንፈሳዊነት ነው። በእርግጥ ትክክለኛ ራዕይ ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ስለሆነ ከባለራዕዩና ከተባባሪዎች አቅም ያለፈ ነው። ስለዚህ የትዳር ጓደኞች ከአቅም በላይ የሚመስለው ራዕይ አስፈርቶን ወይም በተሳሳተ መንገድ ተረድተነው ለራዕይው ተባባሪ ወዳለመሆን ከመግባት ይልቅ ከጥቂትና ከትንሽ የሚጀመርበትን ስልት በመቀየስ ተባባሪነታችንን ማሳየት ተገቢ ነው። በዚሁ አጋጣሚ በአገልግሎት ራዕይ ላይ በአሳብ፣ በጸሎትና በገንዘብ በመተባበር ቅዱሳንን ለማገልገል ዕድል እንዳገኝ የምትረዳኝ ባለቤቴን ላመሰግን እወዳለሁ።

ምናልባት ራዕዩ የሚጠይቀውን የጊዜና የገንዘብ እንዲሁም የሰው ኃይል መጠን ለመቀበል ቢከብድም እንኳን በራዕዩ አሳብ ላይ መቀባበል ካለ ባለመስማማት መስማማትና ውጤቱን መጠበቅ መልካም ነው። በራዕይው ላይ እርግጠኛ የሆነ መሠረታዊ ተቃውሞ ከሌለንና ነገር ግን ራዕይውን እኛ ማየት ካልቻልን ከባለ ራዕዩ ጋር መተባበር፤ መተባበር ከከበደን ደግሞ ባለራዕይው ጉዞውን እንዲቀጥል አምነን መልቀቅ ተገቢ ነው። በሚደረገው ሂደት ስህተት፣ ድካምና አለመሳካት ሊፈጠር ይችላልና መፍረድ ሳይሆን ከተፈጠረው ስህተት እንዲማሩ ብሎም እንደ ገና እንዲነሱ ማበረታታት የትዳር አጋርነት ኃላፊነት ሊሆን ይገባል። *"እኔም። እኛ ያለንበትን ጕስቍልና ኢየሩሳሌም እንደ ፈረሰች፥ በሮችዋም በእሳት እንደ ተቃጠሉ ታያላችሁ አሁንም ከእንግዲህ ወዲህ መሳለቂያ እንዳንሆን ኑና የኢየሩሳሌምን ቅጥር እንሥራ አልኋቸው። የአምላኬም እጅ በእኔ ላይ መልካም እንደሆነች፥ ንጉሡም የነገረኝን ቃል ነገርኋቸው። እርሱም፡- እንነሣና እንሥራ አሉ። እጃቸውንም ለበጎ ሥራ አበረቱ። ... የሰማይ አምላክ ያከናውንልናል፥ እኛም ባሪያዎቹ ተነሥተን እንሠራለን እናንተ ግን በኢየሩሳሌም እድል ፈንታና መብት መታሰቢያም የላችሁም አልኋቸው።"* /ነህ 2፡ 17-20/

## ለጥንዶች በግላቸውና በቡድን ለማጥናት የሚረዷቸው የውይይት ጥያቄዎች

## የምዕራፍ አሰር (10)

## የውይይት ጥያቄዎች

1. የእምነትንና የመንፈሳዊ መረዳትን ልዩነት ምንነት መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት በማድረግ ተወያዩበት።
2. በባለትዳሮች መካከል የእምነትና የመንፈሳዊ መረዳት ልዩነት ሊፈጠር የሚችልባቸውን አጋጣሚዎች በመዘርዘር ውይይት አድርጉ፡፡
3. በባለትዳሮች መካከል በእምነትና በመንፈሳዊ መረዳት ልዩነት ምክንያት ሊፈጠሩ የሚችሉ የግጭት መንስኤዎችን ዘርዝሩ፡፡ የእናንተን የግል የግጭት ምክንያት የሆነውን ለይታችሁ በማውጣት ተነጋገሩበት፡፡
4. እንደ መንፈሳዊ ሰው ያላችሁ ራዕይ ምንድን ነው? የራዕይ ስምምነት እንዲኖራችሁ ምን አደረጋችሁ ወይም ምን ማድረግ አለብን ትላላችሁ?
5. በእምነትና በመንፈሳዊ ልዩነት ለሚፈጠሩ ግጭቶች የመፍትሔ እርምጃዎች ምንድን ናቸው? በዝርዝር በመወያየት የግል የግጭት መንስኤ ለሆኑ ችግሮቻችሁ ልትወስዱት የሚገባ እርምጃ ምንድን ሊሆን ይገባል ትላላችሁ?
6. እንደ ባለትዳርና ቤተሰብ የግል የጸሎት፣ የአምልኮና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዘ እንዲኖራችሁና በጋራ በመንፈሳዊ ሕይወት ለማደግ ምን ማድረግ እንዳለባችሁ ለማቀድ ምቹ የሆነ ጊዜና ቦታ በማመቻቸት ለማቀድ ዝግጅት አድርጉ።





# ምዕራፍ አስራ አንድ(11)

# የባልና የሚስት ኃላፊነትና የተለያየ ሚና

## I. የክርስቲያን ባልና ሚስት ኃላፊነትና ሚና ምንነት

አንድ ክርስቲያን ወንድምና አንዲት ክርስቲያን እህት በእውነተኛ ፍቅር ላይ በተመሠረተ የትዳር ሕይወት በዕድሜ ልክ ቃል ኪዳን በመጣመር ቤተሰብ የሚባለውን ተቋም ይመሠርታሉ፡፡ በዚህ ተቋም ውስጥ ባልና ሚስት በየራሳቸውና በትብብር የሚሸከሟቸውና ሊወጧቸው የሚገቡ ኃላፊነቶችና ሚናዎች አሏቸው፡፡ ልጆች በሚወለዱበት ጊዜ ደግሞ የወላጅነትን ኃላፊነት በጋራ የመወጣት ግዴታ ያለባቸው ሲሆን የአባትነትና የእናትነትን ኃላፊነት ለመወጣት ደግሞ የየራሳቸው ሚና ይኖሯቸዋል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስም ይህንን እውነት በማስረገጥ ወንዱ የባልነትና የአባትነት ሴቷ ደግሞ የሚስትነትና የእናትነት ኃላፊነትና ሚና እንዳለባቸው በመረዳት እርስ በርሳቸው የበኩላቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ የሚጠበቅባቸው መሆኑን በመናገር የሚናቸውን ምንነት ግልጥ አድርጓል /ኤፌ.5:21-33/። ይህ ምዕራፍም የሚያተኩረው በዚህ አብይ ጉዳይ ላይ ነው፡፡

## II. ከባልና ሚስት ኃላፊነትና ሚና ጋር የተያያዙ የግጭት መንስኤዎች

ይህ ምዕራፍ ባልና ሚስት የየግል የጋራ ኃላፊነታቸውን እንደሚገባ ካለመረዳትና ካለመወጣት ጋር በተያያዘ በትዳር ውስጥ ግጭት የሚያመጡ ምክንያቶችን በማሳየት ጥንዶች የግጭት ሰበቦችን ለመቀነስ ሚናቸውን እንዲረዱና እንዲወጡ የማስቻል ዓላማ አለው፡፡ ባልና ሚስት ትክክለኛ የአጋርነትን ሚና የመወጣት ክርስቲያናዊ፣ ፍጥረታዊና ማሕበራዊ ግዴታ አለባቸው፡፡ ይህን ግዴታቸውን በአግባቡ መወጣት ከቻሉ በመካከላቸው ያለው ግንኙነት በጥሩ መሠረት ላይ በመታነጽ ሥር እየሰደደ ሰላምና መግባባት የሞላበት ይሆናል፡፡ ግዴታቸውን በአግባቡ ካልተወጡ ደግሞ የሕብረታቸው መሠረት ይናጋል፡፡ ግንኙነታቸውም በአለመግባባትና በግጭት የሚናወጥ የጦር ሜዳ ወደ መሆን ይሸገራል፡፡ ስለዚህ ባልና ሚስት የጋራና የየግል ኃላፊታቸውን በመረዳት ለትዳራቸው ጤናማነትና ሰላማዊነት መትጋትን ቀዳሚ ጉዳያቸው ሊያደርጉት ይገባል፡፡ ጥንዶቹ የጋራና የየግላቸው ከሆነው ኃላፊነት ባሻገር ባል የሚስትን ሚስት ደግሞ የባልን ኃላፊነት እንደሚገባ በማወቅና አንዱ ለሌላው እርዳታ፣ ትብብርና ድጋፍ በማሳየት ግጭቶችን ቀንሰው የሚፈጠሩ ችግሮችን በአግባብ በመፍታትና እርስ በእርስ በመግባባት ቤታቸውን ሊያንጹና ሊጠብቁ ይገባል።

አንዳንድ ባሎች ሚስት የሚያገቡበት ዓላማ በቤት ውስጥ የሚሠሩ የተለያዩ ሥራዎችን ማከናወን ስለሚቸገሩና ይህንን ክፍተት የምታሟላ አጋዥ እንድትኖራቸው በማሰብ ነው። የዛሬ አስራ ስድስት ዓመት ገደማ አገር ቤት እያለን ወንድሞች ሰብሰብ ብለን ስናወራ የእግር ካልሲውን ማጠብ የሰለቸው አንድ ወንድም "አሁንስ ካልሲዬን

የምታጥብ ሚስት ጌታ በሰጠኝ" አለን፡፡ እኔም ለዚህ ወንድም "አንተ ሚስት ሳይሆን የምትፈልገው የቤት ሠራተኛ ነው" በማለት እንደመለስኩለት አስታውሳለሁ። ከአደግንበትና ከተቀረጽንበት ባህል አሉታዊ ተጽዕኖ የተነሳ ስለሚስት ስናስብ እነዚህን የመሳሰሉ አስተሳሰቦች እናንጸባርቃለን። ሚስት የቤት ሠራተኛ አይደለችም! ሚስት ለባሏ አጋዢ እንድትሆን የተፈጠረችና የባሏ አቻ ወይም እኩያ የሆነች ምቹ ረዳቱ ናት። እርሱም የባልነት ኃላፊነቱን በመወጣት የሚስቱ የትዳር አጋር ነው /**ዘፍ 2፡ 23-24፤ ምሳ 18፡ 22፤ 31፡ 11-12**/፡፡ ስለዚህ ሚስት ባል አምባገነን በመሆን እንዲሁ እንደፈለገ የሚረግጣት ምንጣፍ አይደለችም! ባል እንደ ወደደና እንደ ፈለገ በሚያስበው በሁሉም አሳቡ ሚስት እንድትስማማ የሚጠበቅባትና የምትባለውን ሁሉ የምትፈጽም የራሷ የሆነ ፈቃድ የሌላት አይደለችም። ከባሏ የበታች ሁና የምትኖር ሳትሆን የራሷ የሆነ መልካም አሳብ ያላት ቤታቸውን ከእርሱ ጋር በአቻነት አብራ የምትሠራ፣ የምትገነባ፣ ትዳሯንና ቤተሰቧን የምትንከባከብ አምላካዊ ስጦታ፣ በረከትና ረዳት ናት። ከዚህ በመነሳት የሚስትነትን ኃላፊነትና ሚናን ባለመረዳት የሚፈጠሩ የግጭት ምክንያቶችን በሚከተሉት ነጥቦች በመዘርዘር ለመጠቆም እሞክራለሁ:-

## 1. ሚስት ለባሏ ትገዛ የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አሳብ በተሳሳተ *መንገድ መረዳት*

*መጽሐፍ ቅዱስ የመታዘዝንና የመገዛትን ትዕዛዝ የሚሰጠው በጋራ ለባልና* ለሚስት ነው:- *"ለእያንዳንዳችሁ በክርስቶስ ፍርሃት የተገዛችሁ ሁኑ።"* /**ኤፌ 5፡ 21**/፡፡ አንዱ ለሌላው የመገዛታቸውና የመታዘዛቸው መለኪያው ደግሞ ሌላ ሳይሆን በክርስቶስ ፍርሃት መኖር ነው። ለክርስቶስ የተገዛች ሚስት ለባሏ ለመገዛት፣ ለክርስቶስ የተገዛ ባል ደግሞ ለሚስቱ ለመገዛት አይከብደውም። መጽሐፍ ቅዱስ ሚስት ለባሏ እንድትገዛ በግልጥ ቢያዝም ነገር ግን ሁለቱንም በክርስቶስ ፍርሃት አንዳቸው ለሌላቸው እንዲገዙ ያስተማረ መሆኑን በማስተዋል የመጽሐፉን አጠቃላይ ምክር መረዳት አስፈላጊ ነው፡፡ ስለዚህ ባሎች ይህን ሃሳብ በመሰረዝ የመታዘዝን ኃላፊነት በሚስት ላይ ብቻ የተጫነ ግዴታ አድርገን በመቁጠር ሚስቶችን የምናዝዝ አለቆች መሆንና በአይነኬ የገዥነት ዙፋን ላይ ተቀምጠን ለመኖር ማለም የለብንም። በክርስትና ሕይወት ውስጥ አንዳችን ለሌላችን የመገዛት ኃላፊነት ባሎችንም የሚያጠቃልል ለክርስቲያኖች ሁሉ የተሰጠ መሆኑ የእግዚአብሔር ቃል አስረግጦ የሚያስተምረው መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርህ ነው /**ፊል 2፡3-4፤ 1ኛ ጴጥ 5፡5፤ ሮሜ 13፡1ና ዕብ 13፡7**/፡፡

*" ሚስት ለባሏ ትገዛ "* የሚለው መሠረታዊ የሆነ የትዳር ግንኙነት መርህ ሚስት ባሪያ መሆን አለባት የሚል ትርጓሜ ሊሰጠው አይገባም! ቀድሞ እንደ ነበረው የባሪያ አገዛዝ ዘመን ሚስቱን ምንም መብት የሌላት ተናገሪና ተንቀሳቃሽ የሆነች ሕይወት ያላት እቃ አድርጎ የሚያስብ ወንድ ካለ መጽሐፍ ቅዱሳዊው እውነት ያልገባውና ለጋብቻ ኃላፊነትም ፈጽሞ ያልተዘጋጀ ማንነት ያለው ሰው ነው።





*"አፉዋን በጥበብ ትከፍታለች የርኅራኄም ሕግ በምላስዋ አለ።"* /**ምሳ 31፡ 26**/ የሚለው የእግዚአብሔር ምክር ሚስት የባሏን የተሳሳተ መረዳት ልታስተካክል የምትችል ረዳት እንደሆነች ያሳየናል። *"...ማኑሄም ሚስቱን:- እግዚአብሔርን አይተናልና ምት እንሞታለን አላት። ሚስቱም:- እግዚአብሔርስ ሊገድለን ቢወድድ ኖሮ የሚቃጠለውን መሥዋዕትና የእህሉን ቍርባን ከእጃችን ባልተቀበለን፥ ይህንም ነገር ሁሉ ባላሳየን፥ እንዲህ ያለ ነገርም በዚህ ጊዜ ባላስታወቀን ነበር አለችው።"* /**መሳ 13፡ 21-23**/ ነገር ግን ምንም መናገር የሌለባቸው (የማይናገሩ) እና መልካም ሃሳብና ፈቃድ የሌላቸው አድርጎ ሚስቶችን መቁጠር በትዳር ላይ ግጭትን ማብዛትና መለያየትን የሚያስከትል አፍራሽ አመለካከትና ተግባር ነው።

በአንዳንዶቹ ትዳር ውስጥ ሚስትን በቤት ውስጥ ካሉ የተለያዩ የቤት ዕቃዎች መካከል እንደ አንዱ አድርጎ መቁጠርና የሚገባትን ዋጋ አለመስጠት በንግግር ባይገለጽም ከዚህ ባልተናነሰ አመለካከት በተግባር ሲገለጽ ይታያል። ሚስት ባል እንደፈለገ የሚያደርጋት የቤት ዕቃ ሳትሆን ከባሏ ጋር በአቻነት አብራ የሃብቷ ባለቤትና ቤታቸውንና ያላቸውን ሁሉ በመንከባከብ ሚናዋን የምትወጣ አጋር ናት። *"እርሻንም ተመልክታ ትገዛለች ከእጅዋም ፍሬ ወይን ትተክላለች። ወገብዋን በኃይል ትታጠቃለች፥ ክንድዋንም ታበረታለች። ንግድዋ መልካም እንደ ሆነ ትመለከታለች መብራትዋ በሌሊት አይጠፋም።"* /**ምሳሌ 31፡ 16-18**/፡፡

## 2. ሚስት ብቻ የገቢ ምንጭ መሆን ወይም በገቢ መጠን ከባሏ መብለጥ

ይህ ችግር በገንዝብና በንብረት ላይ እንደ አንድ ችግር አስቀድሞ የተጠቀሰ ቢሆንም እንኳን በባልና በሚስት ኃላፊነትና ሚና ላይ የሚያመጣው አሉታዊ የሆነ የሚናና የስርዓት ለውጥ ቀላል አይደለምና በድጋሚ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። የገንዘብ አቅም ያላቸው ሰዎች በቤት፣ በትዳር፣ በቤተሰብ፣ በቤተ ክርስቲያን ብሎም በአገር ላይ የሚያመጡት አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ ቀላል አይደለም። ጤነኛ ያልሆነ የገንዘብ ተጽዕኖ ከማንነት፣ ከችሎታ፣ ከጸጋ ስጦታ፣ ከልምድ፣ ከክህሎት፣ ከስልጠናና ከመልካም ልምዶች ወደ ኋላ ሊያስብልም ይችላል፡፡ በዚህ ስፍራ ላይ ይህን ርዕሰ ጉዳይ በድጋሚ ማንሳት ያስፈለገው ያለን የልማዳዊ አመለካከት ተጽዕኖ ወይም የሕይወትን ኃላፊነት ለመሸከም የምንችልበት ብስለት ሳይኖረን ገንዘብ ማግኘታችን ከትዳር ጀምሮ በተዋረድ የሰዎችን ኃላፊነትና ሚና በአፍራሽነት ሊያስቀይር ስለሚችል ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ከሚያመጣው አዎንታዊ ተጽዕኖ ይልቅ አሉታዊ ተጽዕኖው ጎልቶ ሊታይ ይችላልና ልዩ ጥንቃቄ ሊደረግበት የሚገባው መሆኑን ማሳየትም የዚህ ነጥብ መሠረታዊ ትኩረት ነው፡፡

በብዙ አገሮች ባህልና በታሪካዊው ነባራዊ ሁኔታ ውስጥ የባል የቤቱ የገቢ ምንጭ መሆን የተለመደና የሚጠበቅም ነው። እንዲህ ዓይነቱ ችግር በእኛ አገር ባህል ብቻ ሳይሆን በሌሎችም አገሮች ባህል ውስጥ የሚታይ ችግር ነው። በቅርብ ጊዜ የሌላ አገር ዜጋ የሆኑ ለ25 ዓመት በትዳር ላይ የቆዩ ባልና ሚስቶች የምክር አገልግሎት ፈልገው የምሠራበትን የካውንስሊግ ሴንተር ጎብኝተው ነበር፡፡ የትዳራቸው ችግር ምንድን

እንደሆነ በምጠይቅበት ወቅት እንደተረዳሁት አንዱ ችግራቸው ባል በጊዜው ሥራ አጥ መሆኑና ለቤተሰቡ የገቢ ምንጭ አለመሆኑ በነፃነት አሳቡን መግለጽ እንዳይችል ያሳደረበት አሉታዊ ተጽዕኖ ነው:: ያጋጠመው የሥራ አጥነትና ለቤተሰቡ የገቢ ምንጭ አለመሆን ችግር በማንነቱም ላይ የበታችነት ስሜት ፈጥሮበታል:: ስነ-ልቦናው ተጎድቷል፣ ብስጩነትና ድብርትም እንደያዘው ገለጾልኛል።

ከአሁን በፊት የገቢ ምንጭ በመሆን ሲያስተዳድር የነበረ ባል በተለያየ ምክንያት ሥራ አጥ ሲሆን ወይም የገቢው መጠን ከሚስቱ ገቢ ያነሰ በሚሆንበት ወቅት ሊፈጠርበት በሚችለው ስነ ልቦናዊ አሉታዊ ተጽዕኖና የማንነት ቀውስ ምክንያት የባህርይ ለውጥ ሊያመጣና ሰብብ ፈልጎ መጋጭት የየዕለቱ ልምዱ ሊሆን ይችላል። በአንድ ወቅት አገር ቤት ለአገልጋዮች ስለማማከር አገልግሎት ስልጠና እሰጥ ነበር:: በባህላችን በተለይ ሚስቶች ብቻ የገቢ ምንጭ የሚሆኑበት ሁኔታ በሚያጋጥምበት ጊዜ በትዳር ግንኙነት ውስጥ ችግር ሊፈጠር የሚችል መሆኑን ማብራራት ስጀምር አንድ ምስክርነት ነገሩኝ:: ታሪኩ በአንድ ወቅት ትዳር መሥርተው አብረው ይኖሩ በነበሩ ጥንዶች መካከል የተፈጠረ ታሪክ ነው:: ባልና ሚስት አብረው በሰላም ሲኖሩ ከቆዩ በኋላ አንድ ቀን በመካከላቸው ግጭት ይፈጠራል:: ባልና ሚስት በተጋጩ ወቅት ባል የአካባቢው ባህልና ወግ በቀረጸው አስተሳሰቡ በስሜታዊነት በተሞላ ንግግር ***"ከዚህ ቤት ውልቅ ብለሽ ትወጫለሽ"*** ብሎ በቁጣ ይናገራል:: ሚስትም በምላሹ የእነርሱን ቤት ነባራዊ እውነታ ባንጸባረቀ ንግግሯ ***"አንተ ነህ ወይንስ እኔ ነኝ ከዚህ ቤት መውጣት ያለብን?"*** በማለት ባል ላቀረበው የውጭልኝ ትዕዛዝ መጠይቃዊ መመሪያ ትሰጣለች::

ባል በዚህ ጊዜ ከጋረደው ባህላዊና ልማዳዊ የአስተሳሰብ ጭጋግ አዕምሮውን በማጽዳት ተጨባጩን እውነታ ለማገናዘብ ሲሞክር ለካስ ሙሉ በሆነ ቤት ውስጥ ሻንጣውን ይዞ ወደ ዚህ ቤት የገባውና በኢኮኖሚ የሚስቱ ጥገኛ የሆነው እርሱ ነበር:: ምስክርነቱን ያካፈሉኝ ሰዎች ባል ይህንን ገሃዳዊ እውነት ባስተዋለ ጊዜ "እኔ ነኝ ለካስ የምወጣው" እንዳለ አጫውተውኛል። ከታሪኩ እንደምንገነዘበው በዚህ ትዳር ውስጥ የንብረት ባለቤትነት ጋርዮሻዊ አልነበረም:: በዚህ ቤት ንብረት በባለቤትነት የተመዘገበው መጀመሪያ በገዛው ሰው ማለትም በሚስት ስም ነው:: በእርግጥ በታሪኩ እንደተገለጠው አንዳንድ ባሎች የፍጹማዊ አንባገነን ባሕርይ ባለቤት በመሆን በትዳር ውስጥ ያሉበትን ወቅታዊ ሁኔታ እንኳን ማገናዘብ አይችሉም:: በሌላ በኩል ብቸኛ የቤተሰብ የገቢ ምንጭና የኢኮኖሚ መሠረት የሆኑ ሚስቶችም የያዙትን ኢኮኖሚያዊ የኃይል የበላይነት ትዳራቸውን ለመጠበቅ ሳይሆን ግላዊ መብታቸውን ለማስጠበቅ የሚጠቀሙበት ኃይልና ጉልበት አድርገው በመውሰድ ክርስትና ስለጋብቻ ከሚያስተምረው ትምህርት በተቃራኒ ለመኖር የሚመርጡ መሆኑን ነው።

በተለይ በአሁኑ ዘመን ከአገር ቤት በእድገትና በስልጣኔ ሂደት በመንግስትና በግል ስራ ላይ የሴቶች ተሳትፎ በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ በመጣበት ወቅት የሚስቶች የግቢ





ምንጭ ከባሎች ሊበልጥ በሚችልበት አልያም ከባል ጋር በማይተናነስበት ዘመን ሚዛናዊ በሆነ መንገድ የትዳርን ግንኙነት መጠበቅ ካልተቻለ በሚፈጠሩ ክፍተቶች ትዳር ለከፋ አለመግባባትና ግጭት ሊጋለጥ ይችላል። ባለትዳሮች በየግል በሚያገኙት የገቢ መጠን የበላይና የበታችነት ስሜት እየተፈጠረባቸው የትዳር ግንኙነታቸው እንዳይሻክር ከገንዘብና ከንብረት ይልቅ ከትዳር ጓደኛ ጋር ያለው ግንኙነት ላይ ማተኮር ተገቢ ነው። በለውጥና በእድገት ዘመን እኛ በገቢና በኢኮኖሚ የምንበልጠው ሰው የተለያዩ የእድገት እድሎችን በማግኘት እኛን ሊበልጠን ይችላል። በተለይ በትዳር ውስጥ ያለን ሰዎች እንዲህ ዓይነት መልካም አጋጣሚ ሲፈጠር እድገቱ የመጣው በባልም ይሁን በሚስት በኩል ጉዳዩን ትክክለኛና ጤነኛ በሆነ መንገድ በማየት ለቤተሰቡ አባላት በሙሉ የሚጠቅም የእድገት በረከት መምጣቱን በመረዳት ሁላችንም ደስተኛና እግዚአብሔርን የምናመሰግን ልንሆን ይገባል::

በውጩ ዓለም የሚኖሩ ሀበሻዎች እንደየሚኖሩበት አገርና እንዳለው የሥራ ሁኔታ ሴቶች (ሚስቶች) የተሻለ የሥራ እድል ሊያገኙ ይችላሉ። በዚህ ጊዜ ባሎች የበታችነት ስሜት ሊሰማቸው ይችላል:: ይህ በበታችነት ስሜት የመጠቃት ሁኔታ በባሎች ላይ የባሕርይ ለውጥና የማንነት ቀውስ እንዳያስከትልና ስሜታቸውንና ፍላጎታቸውን መግለጽ ወደ ማይችሉበት የተግባቦት ደረጃ አድርሷቸው ነፃነታቸውን እንዳይነፍጋቸው መጠንቀቅ ተገቢ ነው። አገር ቤት በነበሩበት ወቅት የነበረ መተሳሰብ ብዙ ዕድል በበዛበት አገር ሊጠፋ አይገባም። እውነተኛ የሆነ መታዘዝን፣ መቀባበልንና ባለን ገንዘብ በጋራ መጠቀም መለማመድን ማቆም መንፈሳዊነት አይደለም። እውነተኛ መታዘዝና መከባበር ምንም ምርጫ በሌለበት ሁኔታ ውስጥ ብቻ ሳይሆን ብዙ ምርጫ በበዛበት ሁኔታ ውስጥ የሚገለጽ ክርስቲያናዊ የሕይወት ኃላፊነት ነው።

## 3. ጾታን ብቻ መሠረት ያደረገ የሥራ ክፍፍል

ከጾታ አንጻር አቅማችን፣ ጉልበታችን፣ እይታችን፣ ችሎታችን ሊለያይ ይችላል:: ነገር ግን በትዳር ውስጥ ያለውን የባልና የሚስት የሥራ ኃላፊነት ልማዳዊውን ወይም ባህላዊውን አስተሳሰብ በመከተል ከጾታ አንጻር ብቻ በማየት የሚደረግ የሥራ ክፍፍል በጋራ መረዳዳትን ማዕከል ያላደረገ ስለሚሆን በጥንዶቹ ተደጋግፈው መኖር ላይ እንቅፋት ሊሆን ይችላል። በአብዛኛው ሐበሻ ዘንድ ከጾታ አንጻር ብቻ ማንኛውንም የቤት ውስጥ ሥራ የሚስት ኃላፊነት ከቤት ውጭ ሠርቶ የቤት ወጭን የማምጣትንና ቤተሰብን የማስተዳደርን ኃላፊነት ደግሞ የባል ብቻ አድርጎ የመቁጠር አስተሳሰብና ተግባር ጥንታዊነት ከጥንት ጀምሮ የተለመደ ነው:: ይህ አመለካከት መተሳሰብንና በሁሉም ነገር መደጋገፍን የሚያስቀር በአሁኑ የለውጥና የእድገት ዘመን ሊታይ የማይገባው ልምምድ ነው። በተቻለ መጠን አለማወቅ፣ በትክክለኛው እውቀት መኖርን አለመልመድና መኖር አለመቻል የሚቀረፍበትን መንገድ እየፈጠሩ ባል ሚስትን ሚስት ደግሞ ባልን የምትረዳበት መንገድ ማሰብ ተገቢ ነው።

ወንድነት ተፈጥሮው ባል፣ አባትና ወንድም የመሆን ሚና አለው። እነዚህ ሚናዎች ተፈጥሯዊ ሚናዎች በመሆናቸው የምንቀበላቸው እንጂ በምርጫ የምንለውጣቸው አይደሉም:: ሌላኛው ከእነዚህ ውጭ መጠቀስ የሚችለው ሙያዊ የሆነው የባልና የሚስት የሥራ ኃላፊነት ምደባ ሲሆን ከባህልና ከልምድ በመነሳት ሙያዊ የሥራ ኃላፊነቶችን ጾታን መሠረት በማድረግ የመመደቡ ሂደት ያደግንበትና ዛሬም በብዙ ባለትዳሮች ቤት የሚታይ እውነታ ነው:: ይህ ጾታ ላይ ብቻ በማተኮር የሥራ ኃላፊነትን የመመደቡ ሂደት ተፈጥሯዊ ያልሆነና ሊለዋወጥ የሚችል የሥራ ኃላፊነት ቢሆንም ብዙዎች ባለትዳሮች ባህላዊ የሆነውን አመለካከት ብቻ በሚከተሉበት ጊዜ ለግጭት መነሻና መባባሻ ምክንያት ሲሆን ይታያል። ነገር ግን ባለትዳሮች ልንረዳው የሚገባን መሠረታዊ ጉዳይ በቤት ውስጥም ይሁን ከቤት ውጭ የሚከናወኑ ልዩ ልዩ የቤተሰብ የሥራ ኃላፊነቶች ሙያን፣ ችሎታንና ተሰጥዖን እንጅ የግድ ጾታዊ ልዩነትን መሠረት ማድረግ የሌለባቸው መሆኑን ነው:: ስለዚህ የትዳር አጋርን ተሰጥዖው/ዋ/ ወይም ዝንባሌው ምንድን ነው? የትኛውን ሥራ ስኬታማ በሆነ መንገድ መሥራት ይቀለዋል/ላታል/? ስራውን ለማከናወን የተሻለ ሙያ ወይም እውቀት ያለው ማን ነው? ... የሚሉ ጥያቄዎችን ባግባቡ በመመለስና እርስ በርስ በመተዋወቅ፣ በመረዳዳት፣ የሥራ ኃላፊነትን የጾታ ልዩነትን ሳይሆን ተሰጥዖንና ችሎታን መሠረት በማድረግ ለትክክለኛው ሰው እየሰጠን ትዳራችንን መንከባከብ ጥበበኛነት ነው።

**የባልና የሚስት የሥራ ኃላፊነቶች ሙያን፣ ችሎታንና ተሰጥዖን እንጂ የግድ ጾታዊ ልዩነትን መሠረት ብቻ በማድረግ ማሰብና ማቀድ አይገባንም ።**

## 5. መጠበቅ፡- የጥንዶቹ የገቢ ምንጭ ምክንያት ቢሆኑም ባይሆኑም የሚዛናዊ ስሜት ባለቤት መሆን

በተለያዩ ምክንያቶች በሚፈጠር የባል የገቢ ምንጭ ምክንያት በመሆንና አለመሆን ጊዜ የተለያዩ እንግዳ ስሜቶች መፈጠራቸው የማይቀር ነው:: ባል ለቤተሰቡ ፍላጎት ማሟላት የሚያስፈልገውን ገቢ ማቅረብ በሚችልበት ወቅት አስቸጋሪ የሚባል ነገር ላይፈጠር ይችላል:: ይህ የተለመደ ማሕበረሰባዊ ባህል ነውና! ነገር ግን ባል ለቤተሰቡ የሚያስፈልገውን ገቢ ማቅረብ ሲሳነው ይህን ሚናውን መወጣት የሚችል ባለመሆኑ ማሕበራዊ ዋጋው እንዳነሰ ስለሚሰማው የስነ ልቦናና የስሜት ቀውስ ሊፈጠርበት ይችላል:: ስለዚህ ባለትዳሮች ይህንን እውነታ በመረዳት የሚፈጠሩትን የተለያዩ እንግዳ ስሜቶች አስቀድሞ መረዳትና መቆጣጠር ለመቻል መዘጋጀት ኃላፊነታቸው ነው። ከባህላችን አንጻር ወንድ ልጅ የገቢ ምንጭ ሆኖ መኖሩ በተለመደበት ማሕበረሰብ አውድ ውስጥ በሚስት የገቢ ምንጭነት የሚገኝን ገቢ የቤተሰብ መተዳደሪያ አድርጎ በትዳር በሰላም መቀጠል የበታችነት ስሜት ይፈጥርበታል። ይህ የበታችነት ስሜት





በቀላሉ ተስፋ የሚቆርጥ፣ ንዴታም፣ ቁጡ፣ መራርና ተነጫናጭ ያደርገዋል። እነዚህ ስሜቶች በጥንዶች የኮሙኒኬሽን ክህሎት ላይ የሚፈጥሩት አሉታዊ ተጽዕኖ ደግሞ ቀላል የሚባል አይደለም።

በባል ላይ የበታችነት ስሜት እየተፈጠረ ባለበት ወቅት ደግሞ በተቃራኒው ለቤቱ የገቢ ምንጭ የሆነችው ሚስት የበላይነት ስሜት ሊሰማት ይችላል። ሚስት የበላይነት ስሜት የተሰማት ከሆነ ቀድሞ ምንም ምርጫ ባልነበረበትና ምናልባትም ባል ሠርቶ በሚያስገባው ገቢ ብቻ በሚተዳደሩ ጊዜ በመካከላቸው የነበረው መቀባበል ይጠፋል። ባል ለሚያሳየው የነጭናጫነትና የቁጡነት ስሜታዊነት ሚስት በኩራትና በማን አለብኝነት አጸፋዊ የትዕቢት ምላሽ ትሰጣለች:: ይህ ዓይነት ባሕርይ ካሁን በፊት አሳይታ ስለማታውቅ ባል የሚስቱን የባሕርይ ለውጥ ሲያይ ገንዘብ ስለሌው የተናቀና ተቀባይነት ያጣ መሆኑ የበለጠ ይሰማዋል:: ጥንዶቹ የተፈጠረው ችግር ገብቷቸው ነገሩን በመረዳት በተረጋጋ ስሜት ሊቃኙትና ተወያይተው ሁኔታውን ሊያረግቡት ካልቻሉ "በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ" እንደሚባለው እየተባባሰ ወደከፋ አለመግባባትና ግጭት ያድጋል:: የበላይነት ስሜት ሲፈጠር አንዱ ለሌላው ሊኖረው የሚገባ መታዘዝ ሊጠፋና በምትኩ በበላይነት የመቆጣጠርና እኔ ያልኩት ብቻ ይሁን የማለት ልምምድ ውስጥ መግባትን ያስከትላል::

የበላይነት ስሜት የተሰማው የትዳር ጓደኛም በቤት ንብረቶች ላይ የሌላውን አካል የመጠቀም ነፃነት የመገደብ፣ በሁሉ ነገር ላይ በበላይነት የመሰልጠንና ግለኝነትን የመንከባከብ ፍላጎቱ እየጨመረ ስለሚመጣ ትዳራቸው ለበለጠ ቀውስ ተጋላጭ ይሆናል:: የጥንዶቹ የትዳር ግንኙነትም የተገነባበት መተማመን እየተሸረሸረ በጥርጣሬ የሚሻከርበት ደረጃ ላይ ይደርሳል። ስለዚህ ባልና ሚስት አስቀድመው በትክክለኛ እውቀት በመታነጽ ቤተሰብን የመመገብ ኃላፊነት የሁለቱም ሚና እንደሆነ መረዳት አለባቸው:: ከዚያም ቢቻል ሁለቱም ያለዚያ ደግሞ ባሉት የሙያና የእውቀት ሀብቶች ምክንያት የተሻለ ገቢ ማምጣት የሚችለው የትዳር ጓደኛ ሠርቶ በሚያስገኘው ገቢ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ቤተሰባቸውን የማስተዳደር ብስለትና ስምምነት ሊኖራቸው ይገባል።

ሥራን መሥራት እንድንችልና የቤተሰብ የገቢ ምንጭ ምክንያት እንድንሆን የረዳንና የሚረዳንም እግዚአብሔር ነው። እኛም በማናችንም በኩል ቤተሰብ የሚተዳደርበት ገቢ የተገኘ ቢሆንም እንኳን በጸጋውና በመልካም አዘጋጅነቱ የረዳንን እግዚአብሔርን እያመሰገንን በተሰጠን ገንዘብና ንብረት የትዳር አንድነታችንና ቤተሰባዊ ደህንነታችንን ልንጠብቅበት ይገባል። በዚህ መርህ አስተሳሰባቸውንና ስሜታቸውን በማሰልጠን ባሎች ሊፈጠርባቸው ከሚችል የበታችነት ስሜት፤ ሚስቶችም ሊፈጠርባቸው ከሚችል የበላይነት ስሜት ሕይወታቸውን በመጠበቅ አሁን ያለውን

ሁኔታ በመቀበል በትህትናና በመታዘዝ ግንኙነትን ለመጠበቅ የሚችል ማንነት ይዘው መገኘት ተገቢ ነው።

### 6. መፍቀድ፡- አንዳንድ ጊዜ ለየት ያለ አጋጣሚንና ልምምድን ለማስተናገድ መፍቀድ

በትዳር ሕይወት ውስጥ በጥንዶቹ ግንኙነት መካከል የሚፈጠሩ የተለያዩና ያልተጠበቁ ክስተቶችን ለመቀበል አስቀድሞ ማሰብና የአዕምሮና የስሜት ዝግጅት ማድረግ ከጥንዶቹ ይጠበቃል፡፡ በትዳር ውስጥ ሊያጋጥሙ ከሚችሉ የተለያዩና ያልተጠበቁ ክስተቶች ጥቂቶቹ፡- መውለድ አለመቻል፣ እርግዝና፣ መውለድ፣ አከታትሎ መወለድ፣ ውርጃ፣ ከወሊድ በኋላ የሚፈጠር ድብርት ወይም ሌላ ያልተጠበቀ ክስተት ... የመሳሰሉት ሊሆኑ ይችላሉ። ሌላው በሕይወት የሚገጥሙ ውጣ ውረዶች፣ ከፍታና ዝቅታዎች፣ የጤንነትና የሕመም ወቅቶች፣ የደስታና የሐዘን ጊዜያት፣ የማግኘትና የማጣት... ሁኔታዎችም ሊፈራረቁባቸው ይችላሉ። እንዲሁም አንዳንድ ጊዜ በሞት መለየት ሊያጋጥም ይችላል፡፡ በእነዚህ አስቸጋሪና የጭንቀትና የደስታ ጊዜያት፣ ምንም ማድረግ በማይቻልበት ወቅትና ነገሮች እንደጠበቅናቸውና እንደ አጀማመራቸው ባልቀጠሉ ጊዜ አንዱ የሌላውን ኃላፊነት የመሸፈን፣ የሌላውን ሚና የመወጣትና የመረዳዳት ባህል እንዲኖረን አስቀድሞ መዘጋጀት አስፈላጊ ነው። ባል የሚስትን፣ ሚስት የባልን የተለመደ ሙያና ኃላፊነት ለሚጠይቁ ወቅቶች የትዳር አጋራቸውን ጠንካራ ጎን የመጠቀምን አስፈላጊነት በሚችሉት መጠን ጥንዶች ሁሉ መረዳታቸውና ለመቀበል ዝግጁ ሆነው መገኘታቸው አስተዋይነት ነው።





## ለጥንዶች በግላቸውና በቡድን ለማጥናት የሚረዷቸው የውይይት ጥያቄዎች

## የምዕራፍ አስራ አንድ (11)

## የውይይት ጥያቄዎች

1. የባልና የሚስት ኃላፊነትና ሚና ማለት ምንድን ነው?
2. መጽሐፍ ቅዱሳዊ የባልና የሚስት ኃላፊነትና ሚና ምንድን እንደሆነ በዝርዝር ተወያዩበት፡፡
3. እንደ ባልና ሚስት ብሎም እንደ አባትና እናት ለግጭት መንስኤ የሆኑና ያልተወጣናቸው ኃላፊነቶችና ሚናዎችን ለይቶ ለማውጣት በፍጹም ነፃነት ውይይት አድርጉ።
4. ሚስት ለባሏ ትገዛ የሚለውንና ባል ሚስቱን ይውደድ በሚለው አምላካዊ ትዕዛዝ ላይ በመወያየት ለውጥ በሚያስፈልጋችሁ አስተሳሰብና ተግባር ላይ እርምጃ ለመውሰድ ተነጋገሩበት፡፡
5. አንድ ጊዜ የቤታችሁን የሥራ ክፍፍል በመቃኘት እንዴት የሥራ ክፍፍል እንዳደረጋችሁ፣ የሥራ ኃላፊነት ጫና ማን ላይ እንደሚበዛና የሥራ ክፍፍላችሁህ ምንን መሠረት በማድረግ የተከፋፈለ እንደሆነ በግልጥነት ተወያዩ፡፡

# ምዕራፍ አስራ ሁለት(12)
# ፖርኖግራፊ

## I. የፖርኖግራፊ ምንነት

*ፖርኖግራፊ፡-* በዘመናዊውና በድህረ ዘመናዊው ዓለም ውስጥ የወንድና የሴት የግል የሰውነት ክፍሎችንና ጾታዊ እንቅስቃሴዎችን በማሳየት ሰዎችን ለፍትወት ለማነሳሳት በጽሁፍ የታተመ ወይም በተንቀሳቃሽ ምስልነት የሚታይ ልቅ የወሲብ ግንኙነት ትእይንት ነው። በአሁኑ ወቅት በአንዳንድ ቦታዎች ሰዎችን ስለወሲብ ግንኙነት፣ ስለወሲብ ግንኙነት የተለያዩ አቅጣጫዎችና እንቅስቃሴዎች፣ በአጠቃላይ ስለ ወሲብ ነክ ተግባራትና የወሲብ ግንኙነት እርካታን ለማሳየት፣ ለመግለጥና ለማስተማር ይጠቀሙበታል። ፖርኖግራፊ ዛሬ ዛሬ ኢንዱስትሪ ሁኖ ዓለምን ከማጥለቀለቁ በፊት በቅርጻ ቅርጽ፣ በስዕልና በስነፅሑፍ ላይ ብቻ ይታይ ነበር። በአሁኑ ወቅት ፖርኖግራፊ የተለያዩ ሚዲያዎችን፣ መጽሔቶችን፣ ፖስት ካርዶችን፣ ስዕሎችን፣ ቅቦችን፣ ድምጾችን፣ ፊልሞችን፣ ቪዲዮዎችንና የቪዲዮ መጫዎቻወችን በመጠቀም ወሲብ የሚስፋፋበት ዋና መንገድ ሆኗል።[41]

በተለይም ዛሬ የመገናኛ መረብ (ኢንተርኔት) ዓለምን እንደ አንድ መንደር ማስተሳሰሩን ተከትሎ የጾታ ስሜትን የሚያነሳሱ ወሲባዊ ቪዲዮዎችን፣ ሥዕሎችንና ጽሑፎችን በመጠቀም የሰለጠነው ዓለም ቴክኖሎጅ ተጠቃሚ የሆኑ የዓለማችን ዳርቻዎችን ሁሉ ሳይቀር በማጥለቅለቅ ላይ መሆኑ ሙግት የማያስፈልገው የአደባባይ ሚስጥር ነው። ሰዎችን ለወሲብ ለማነሳሳት ሲባል በመረጃ መረብ (በኢንተርኔት) አማካኝነት ስለፖርኖግራፊ ገንዛቤ ለሌላቸው የመረጃ መረብ ተጠቃሚዎች ሳይቀር ሳይፈልጓቸው የሚላኩ የተለያዩ ወሲባዊ ይዘት ያላቸው ጽሑፎች፣ ፎቶዎች፣ ማስታወቂያዎችና ቪዲዮዎችን ሥራየ ብለው የሚያሰራጩ ሰዎች መኖራቸው ደግሞ ጉዳዩን እያባባሰው ይገኛል። ቀውሱ በጣም መስፋፋቱም ለመልካም ዓላማ የምንጠቀምባቸውን ስልኮቻችንን ሳይቀር ሰዎችን ለወሲብ ፍላጎት የሚቀሰቅሱና የሚያነሳሱ ወሲባዊ ስዕሎችንና ጽሑፎችን ለመለዋወጥና መልክቶችን ለማስተላለፍ አገልግሎት በማዋል ከፍተኛ በሆነ መንገድ የሞራልን ክቡርነት ዝቅ የሚያደርግና የሚያራክስ አፍራሽ ተጽዕኖ በሰዎች ላይ እንዲያሳድሩ እያደረገ ነው።

## II. የፖርኖግራፊ መስፋፋት

አሁን ያለንበት ዘመን ከመቼውም ጊዜ በበለጠ የወሲብ ልቅነት እየጨመረ የመጣበት ዘመን ነው። ይህ የወሲብ ችግር ከጥንት የነበረ የሰዎች ችግር ቢሆንም የመረጃ መረብ (የኢንተርኔት) ዓለምን እየተቆጣጠርና እያጥለቀለቀ በመምጣቱ በአሁኑና በሚመጣው ዘመን መስፋፋቱ ይበልጥ እየጨመረ የሚሔድ መሆኑን ለመተንበይ ነቢይ

[41] Clinton, Tim & Hawkins, Ron. Biblical Counseling p195





አያስፈልገንም። በአገራችን በኢትዮጵያም ባለፉት ጥቂት ዓመታት ኢንተርኔት እየተስፋፋ ለመሆኑና ብዙዎች የኢንተርኔት ተጠቃሚዎች እየሆኑ ለመምጣታቸው የአይን ምስክሮች ነን። ሰዎች ለመዝናናትና ለማረፊያነት የሚጠቀሙባቸው ሆቴሎች ነፃ የሆነ የኢንተርኔት አገልግሎት የሚሰጡ መሆን አለመሆናቸው የደንበኞች ቋሚ ጥያቄ ከሆነ ውሎ አድሯል፡፡ ሆቴሎችም ደንበኞችን ለመሳብ ከሚጠቀሙባቸው ዋና መንገዶች አንዱና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተለመደ የመጣው ነፃ የኢንተርኔት አገልግሎት አለ የሚለው ማስታወቂያ ነው፡፡

ከኢንተርኔት አገልለግሎት መስፋፋት ጋር በመያያዝ ሊነሳ ከሚገባው የቴክኖሎጅው እድገት አሉታዊ ተጽዕኖ ውስጥ አንዱና ዋነኛው ፖርኖግራፊ ነው። በኢንተርኔት ዓለም ካሉት የተለያዩ ድረ ገጾች መካከል የፖርኖግራፊ ድረ ገጾች ሳይት ብዛት 4.2. ሚሊዮን ሲሆን ይህም ከሌሎች ብዙ ከሆኑ የተለያዩ ድረ ገጾች ጋር ሲነፃፀር የአጠቃላዩን ድረ ገጽ **12%** ያህሉን እንደሚይዝ መረጃዎች ያሳያሉ።[42] በየቀኑ **68** ሚሊዮን የሚሆኑ ሰዎች የፖርኖግራፊ ድረ ገጾችን ይጎበኛሉ። ይህም በአጠቃላይ ከሚጎበኙ ድረ ገጾች ጋር ሲወዳደር **25%** ያህሉን ይይዛል። የፖርኖግራፊ ሱስ ከሌሎች ሱሶች በበለጠ ወንዶችንም ሆነ ሴቶችን፣ ያገቡትንና ያላገቡትን፣ የተማሩትንና ያልተማሩትን... ሊያጠቃ የሚችል ሱስ ነው። በአንድ ጥናት የቀረበ ማስረጃ እንደሚያሳየው በዚህ ሱስ ተጠምደው ቆይተው ከዚህ ሱስ ለመላቀቅና ነፃ ለመውጣት ቃል ከገቡ ሰዎች መካከል **53%** ያህሉ እንደገና ወደ ተጠመዱበት ሱስ እንደተመለሱ አስረድቷል ማለትም ከግማሽ በላይ የሆኑት ሱሰኞች ከተጠመዱበት ሱስ ነጻ የመውጣት ጥረታቸው አልተሳካላቸውም። በአሜሪካን አገር የፖርኖግራፊ ድረ ገጽ ለክርስቲያን ባለትዳሮችም ከፍተኛ ችግር የመሆን ተጽእኖው **47%** እንደደረሰ በዚህ ጥናት ውጤት ተገልጧል።[43]

## III. የፖርኖግራፊ ተጠቃሚዎች አመለካከት

ብዙ ክርስቲያኖች በሕይዎት በመድከማቸው ብሎም ለአመጽ እጃቸውን የሰጡና መለወጥ ያቃታቸው በመሆናቸው የቅዱሳት መጽሐፍት ጥቅሶችን በተሳሳተ መንገድ በመተርጎም ለደካማ ህሊናቸው ምላሽ ለመስጠት ጥረት ያደርጋሉ፡፡ አእምሮቸውን ትክክለኛ ባልሆኑ አመለካከቶች በማሳመንና ልባቸውን በማደንደን እርኩሰት ለሞላበት ሕይወት ፈቃዳቸውን ይሰጣሉ፡፡ በዚህ ሂደት ለፖርኖግራፊ ተጋላጭ የሆኑ ክርስቲያን ወጣቶች፣ ላጤዎችና ባለትዳሮች ቁጥራቸው ጥቂት አይደለም። አንዳንድ ያልተለወጡና

[42] Clinton, Tim & Laaser, Mark. The Quick-Reference Guide to sexuality and relationship counseling Baker books, a division of baker publishing Group: Grand Rapids, Michigan, 2010. p158

[43] Clinton, Tim & Laaser, Mark. The Quick-Reference Guide to sexuality and relationship counseling p158

*ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል።"* /ማቴ 5፡ 27-28/፡፡ ስለዚህ ከእንዲህ ዓይነቱ የፍትዎት ምኞትና ድርጊት መሸሽ እንጅ በምንም ዓይነት ምክንያት ከጋብቻ ውጭ ወደ ሆነ ማንኛውም ዓይነት የወሲብ ልምምድና ፍትዎትን የሚያነሳሳ ተግባር መሳብ ኃጢአት ነው፡፡ የእግዚአብሔር ቃል እውነትም አስረግጦ የሚያስተምረውና የሚመክረው ይህንን ነው፡፡ ከዚህ እውነት ጋር በመስማማት መኖር የእያንዳንዱ ክርስቲያን በተለይም ደግሞ ቤተሰብ በመባል የሚጠሩት ትናንንሽ አብያተ ክርስቲያናት መሪና አገልጋይ የሆኑት የባልና ሚስት ኃላፊነትና የክርስቲያናዊ ሕይወትና አገልግሎታዊ አደራ ግዴታ ነው። *"ከዝሙት ሽሹ። ሰው የሚያደርገው ኃጢአት ሁሉ ከሥጋ ውጭ ነው፤ ዝሙትን የሚሠራ ግን በገዛ ሥጋው ላይ ኃጢአትን ይሠራል"* /1ኛቆሮ 6፡ 18/፡፡

## 2. ሰጋዊ ምኞት ነው

የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ዓይነቱን ልቅ በፍትወት የመቃጠልና የወሲብ ልምምድ ሱስ ነፍስን የሚዋጋ ስጋዊ ምኞት በማለት ይጠራዋል። ክርስቲያኖች ለዚህ ምድር እንግዶችና መጻተኞች እንደመሆናችን መጠን እንዲህ ዓይነቱን ሰዎችን ለስጋዊና ዓለማዊ ምኞት ተገዥ የሚያደርግ ልምምድ ማስወገድና ከዚህ መራቅ ይጠበቅብናል። *"ወዳጆች ሆይ፥ ነፍስን ከሚዋጋ ሥጋዊ ምኞት ትርቁ ዘንድ እንግዶችና መጻተኞች እንደ መሆናችሁ እለምናችኋለሁ፤"* /1ኛጴጥ 2፡ 11/፡፡

## 3. እንዴት መመላለስ እንዳለብን መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳናል

እንደ ክርስቲያን ባለትዳርነታችን መጽሐፍ ቅዱስ ምትክ የለሹና ብቸኛው የግልና የቤተሰብ ሕይወት መመሪያችን ነው፡፡ ይህ የሕይወት መመሪያችን እንዴት መኖርና መመላለስ እንዳለብን አሻሚ ባልሆነ መንገድ በግልጥ ይመክረናል። ቃለ እግዚአብሔር እንደ ብርሃን ልጆች የብርሃን ምሳሌነት የተሞላው ሕይወት እንድንኖር ያዛል። ክርስቲያን ሊመላለስበት የማይገባው ኑሮ፤ በዘፈንና በስካር፣ በዝሙትና በመዳራት እንዲሁም በክርክርና በቅናት መመላለስ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በትምህርቱ እርሱን በመልበስና በማሳየት መመላለስ እንዳለብን ይገልጣል። በእርግጥም ለፍትዎት ፍላጎት አልፈን እንዳንሰጥ ስለስጋ ማሰብን ማቆምና ስለመንፈሳዊና ስለሰማያዊ ጉዳይ ማሰብ እንዳለብን *"በቀን እንደምንሆን በአገባብ እንመላለስ፤ በዘፈንና በስካር አይሁን፥ በዝሙትና በመዳራት አይሁን፥ በክርክርና በቅናት አይሁን፤ ነገር ግን ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን ልበሱት፤ ምኞቱንም እንዲፈጽም ለሥጋ አታስቡ።"* /ሮሜ 13፡ 13-14/ በማለት የሚናገረውን የእግዚአብሔር ቃል ትምህርት በመስማትና በመታዘዝ መኖር ይጠበቅብናል።

## 4. ቅጣቱ የከፋ ነው

የፍትዎት ስሜትን ለማርካት ፖርኖግራፊን የሚጠቀሙና የሚለማመዱ ሰዎች በፍትዎት ሱስ የተጠመዱ የዘመናችን ሴሰኞች፣ አመንዝራዎች፣ ጋለሞታዎችና ዘማውያን ናቸው፡፡ እንደዚህ ዓይነት የሕይወት ልምምድን ፈቅደውና ፈልገው የሚያዘወትሩ ዘማውያን በሱሰኝነት ከመጠመዳቸውም ባሻገር ንስሃ ካልገቡና ከልምምዱ ፈጥነው የማይወጡ ከሆነ አምላካዊ ፍርድና ቅጣት ያገኛቸዋል፡፡ ቀሰ በቀስና ደስ በሚል





ቅጽበታዊ የደስታ ስሜት ተውጠው ፍጻሜው ግን እንደ እሬት ወደ መረረና ሁለት አፍ እንዳለው ሰይፍ ወደተሳለ ሞትና ሲኦል በመውረድ የሕይወትን መንገድ እንደማያገኙት መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጻል። *"ከጋለሞታ ሴት ከንፈር ማር ይንጠባጠባልና፥ አፍዋም ከቅቤ የለሰለሰ ነውና፤ ፍጻሜዋ ግን እንደ እሬት የመረረ ነው፥ ሁለት አፍ እንዳለው ሰይፍም የተሳለ ነው። እግሮችዋ ወደ ሞት ይወርዳሉ፥ አረማመድዋም ወደ ሲኦል ነው፡፡ የቀና የሕይወትን መንገድ አታገኝም በአካሄድዋ የተቅበዘበዘች ናት፥ የሚታወቅም አይደለም።"* /ምሳሌ 5፡ 3-6/ ይህን የእግዚአብሔር ፈቃድ በመረዳት በልምምዱ ውስጥ የገቡና በፖርኖግራፊ ሱስ የተጠመዱ ሰዎች ለእግዚአብሔር ቃል በመታዘዝ ፈጥነው በንስሃ ሊመለሱ ይገባል፡፡ *"ንስሐም እንድትገባ ጊዜ ሰጠኋት ከዝሙትዋም ንስሐ እንድትገባ አልወደደችም። እነሆ፥ በአልጋ ላይ እጥላታለሁ፥ ከእርስዋም ጋር የሚያመነዝሩትን ከሥራዋ ንስሐ ባይገቡ በታላቅ መከራ እጥላቸዋለሁ፤"* /ራዕ 2፡ 21-23/ የሚለውን አምላካዊ የንስሃ ጥሪ በመስማት ንስሃ ለመግባት ለሚፈልጉ ሰዎች ደግሞ አሁንም የመመለስ ጊዜው ገና አልመሸባቸውም፡፡ የፖርኖግራፊ ቪዲዮዎችን፣ ፊልሞችንና ፎቶግራፎችን... ወደማየትና ወደዚህ ርኩሰት የተሞላ ሱስ ልምምድ ያልገቡ ክርስቲያኖች ደግሞ ከእንዲህ ዓይነቱ ክቡሩን ሰው የሚያዋርድ ልምምድ ሕይወታቸውንና ቤተሰባቸውን እንዲጠብቁ የእግዚአብሔር ቃል ያስተምራል።

# V. ባለትዳሮችን ለፖርኖግራፊ ሱስ ተጋላጭ የሚያደርጉ ምክንያቶች

## 1. አጋጣሚ

ሰዎች መጀመሪያ በተለያየ መንገድ ከፖርኖግራፊ ልምምድ ጋር ይተዋወቃሉ ከዚያም ለፖርኖግራፊ ሱስ አልፈው ይሰጣሉ። ይህ ከሚከናወንባቸው የተለያዩ መንገዶች መካከል አንዱ እንደ አጋጣሚ ሌሎች እያዩአቸው ከነበሩ ከፖርኖግርፊ ጋር ተያያዥነት ካላቸው ፊልሞች፣ የተለያዩ የቴሌቪዥን ፕሮግራምና በኢሜል አድራሻቸው ወደሚጠቀሙበት ኮምፒዩተር ከሚመጡ ፖርኖግራፊ አዘል መልእክቶች ጋር በመገናኘት ምክንያት የሚጀመር በፖርኖግራፊ ሱስ የመጠመድ አጋጣሚ ነው። እነዚህ ሰዎች መጀመሪያ ላይ በድንገት ከፖርኖግራፊ ልምምድ ጋር የተዋወቁ ቢሆንም ከዚያ በኋላ ግን ራሳቸው እያሰቡና ምክንያት እየፈለጉ የፖርኖግራፊ ተጠቂዎችና ከትዳር ውጭ የፍትዎት ፍላጎታቸውን ለማርካት የሚደረግ ርኩሰት የሞላበትን የአመንዝራነት ኃጢአት መለማመድ ይጀምራሉ።

## 2. ጓደኞች (በወዳጆች)

ክፉ ባልጀርነት መልካሙን አመል ያጠፋል እንደሚለው የእግዚአብሔር ቃል አንዳንዶች በፖርኖግራፊ ሱስ ወደ መያዝ የሚገቡት በዚህ የወሲብ ሱስ በተጠመዱ ጓደኞቻቸው ምክንያት ነው። በተለያየ ምክንያተ ቅርብ ጓደኝነት መሥርተው አብረው የሚጓዙ ሰዎች እርስ በርስና አንዱ በሌላው ላይ በተለያየ መንገድ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ ማምጣቸው አይቀሬ ነው። አንዳንዶች በቀናነት ሌሎችን ነገሮች እንደሚከፋፈሉ ይህንም ልምምድ አንዱ ለሌላው ማካፈል ይጀምራሉ። ሌሎች ደግሞ

አመጽ መሆኑንና በሕይወታቸውም ሆነ በትዳራቸው ላይ እያመጣ ያለውን አሉታዊ ተጽዕኖ እያወቁ በዓላማ ሌሎችን ጓደኞቻቸውን በከፋ ወጥመዳቸው በማስገባት የከፋታቸው ተካፋይ እንዲሆኑ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ። ስለዚህ ክርስቲያን ወገኖች መልካም አመል የሌላቸው ጓደኞቻቸው ከፉ ተጽዕኖ እንዳያሳድሩባቸውና ወደ ቀውስ እንዳይመሯቸው ሕይወታቸውንና ቤተሰባቸውን መጠበቅ አለባቸው:: በተቃራኒው ግን በከፉ ተጽዕኖ ሥር ያሉና በኃጢያት ርኩሰት ባርነት የተያዙ ሰዎች ነፃ እንዲወጡ በእግዚአብሔር ቃል የእውነት መልዕክት፣ በጽድቅ ኑሯቸውና እግዚአብሔር በሰጣቸው ጸጋ መርዳትና የጽድቅ ተጽዕኖ ማሳደር የሚኖሩለት ዓላማ ሊሆን ይገባል::

## 3. የትዳር ጓደኞች

አንዳንዶች ደግሞ የትዳር አጋሮቻቸው ወደ ትዳር ከመግባታቸው በፊትም ሆነ በኋላ በዚህ የወሲብ ልምምድ ውስጥ በመሆናቸው ምክንያት በፖርኖግራፊ ሱስ ይጠመዳሉ:: የትዳር ጓደኛቸውንም ወደዚህ ወጥመድ ይመራሉ። የፖርኖግራፊ ሱስ ተጠቂ የሆኑ የትዳር አጋሮቻቸው በሚያቀርቡላቸው ግብዣ፣ ማበረታታቻና አሉታዊ ተጽዕኖ ምክንያት ከፖርኖግራፊ ምስሎች አቅራቢ ድረ-ገጾችና የሚዲያ ማሰራጫዎች ጋር ይተዋወቃሉ። አንዳንድ ባለ ትዳሮች ደግሞ በቀጥታ በትዳር ጓደኞቻቸው ባይጋበዙም እንኳን የትዳር አጋሮቻቸው ሲመለከቷቸው የነበሩ የፖርኖግራፊ ድረ-ገጾች ወይም የቪዲዮ ምስሎች ሳይዘጉ እንዲሁ ያገኟቸዋል:: ይህ ክስተት አንዳንድ የትዳር አጋሮችን ሊያስቆጣ ቢችልም አንዳንዶችን ግን የድርጊቱ ተባባሪ እንዲሆኑ ያደረጋቸዋል።

## 4. ማሕበራዊ ድረ-ገጾች

ማሕበራዊ ድረ ገጾች የሚባሉት እንደ ፌስ ቡክ፣ ቲውተር፣ ዩቲዩብና ሌሎች በመገናኛ መረብ (ኢንተርኔት) አማካኝነት ማሕብረሰቡን የሚያገናኙ ድረ-ገጾች ሁሉ ናቸው። እነዚህ ማሕበራዊ ድረ-ገጾች በብዙ መንገድ የሚጠቅሙንንና የምንጠቀምባቸውን ያክል በዚያው መጠን የተለያዩ ፖርኖግራፊ አዘል የሆኑ ማስታወቂያዎች፣ ለወሲብ የሚያነሳሱ የተለያዩ የተቀራኒ ጾታ ፎቶዎች፣ ጽሑፎች፣ ስዕሎችና ቪዲዮዎች ይቀርቡባቸዋል:: በዚህም ምክንያት ፖርኖግራፊ ከመቼውም በበለጠ እየተስፋፋ ብዙዎችን ተጠቂ እያደረገና የብዙዎችን የትዳር ግንኙነት እያሻከረ ያለ አመጻዊ ልምምድ ሆኗል። ለምሳሌ:- ፌስ ቡክ የሚጠቀሙ አንዳንድ ክርስቲያኖች ሳይቀር ባለትዳር እንዳልሆኑ በመናገርና ከሌሎች ሰዎች ጋር በመተዋወቅ የፍቅር መሳሳብ የሚጀምሩበትና ከትዳር አጋሮቻቸው የተደበቀ ሌላ ኢሜል፣ የፌስ ቡክ አካውንትና የስልክ ቁጥር በማውጣት ግንኙነታቸውን በድብቅ የሚቀጥሉበት ድረ-ገጽ አድርገው ይጠቀሙበታል። አንዳንዶች አገልግሎት የሚፈልጉ ሰዎችን እያገለግልኩ ነው ወይም እየረዳሁ ነው.የሚሉ ምክንያቶችን በመስጠት በድፍረት ጤነኛ ያልሆነ አሳባቸውን እየቀጠሉ ወደተወሳሰበ ግንኙነት ይገባሉ።





## 5. የሌላን ሰው ላፕቶፕና ዴስክ ቶፕ መጠቀም

አንድ አንድ ጊዜ በጣም ወሳኝ ሥራ ሲያጋጥመን ወይም አስፈላጊ ጉዳይ ሲኖረን የሌላውን ሰው ማለትም የወዳጅ፣ የስራ ባልደረባ፣ የቅርብ ወይም የሩቅ ዘመድ የግልም ሆነ የመሥሪያ ቤት ላፕቶፕና ዴስክቶፕ ኮምፒዩተሮች ተጠቃሚዎች እንድንሆን እንገደዳለን። ይህ ዓይነት በጋራና በመዋዋስ አንድን ኮምፒዩተር በጋራ የመጠቀም ሁኔታ ሲፈጠር የችግሩ ተጠቂ ያልሆኑ ሰዎች የሚጠቀሙበት ኮምፒዩተር ላይ የተጫኑና ሌሎች ሰዎች ሲመለከቷቸው የነበሩ የፖርኖግራፊ ድረ-ገጾች እንደተከፈቱ ያገኛሉ:: እነዚህን ካሁን በፊት የማይታወቁና በሌላ አጋጣሚ ሊገኙ የማይችሉ ድረ-ገጾችን በቀላሉ ተዘጋጅተው ያገኙ ሰዎች የችግሩ ተጋላጭ ሊሆኑ ይችላሉ።

## 6. የግብረ ስጋ ግንኙነት ፍላጎት (የፍትዎት ፍላጎት)

አንዳንድ ምክር ፈላጊ የሆኑ ክርስቲያን ባለትዳሮች በማማክርበት ወቅት ትክክለኛውን ችግራቸውን ለማወቅ ጥያቄዎችን እጠይቃቸዋለሁ:: ከምጠይቃቸው የተለያዩ ጥያቄዎች መካከል አንዱ የግብረ ስጋ ግንኙነት በሚያደርጉበት ጊዜ ከትዳር አጋሮቻቸው ጋር የሚጣጣሙ መሆኑንና አለመሆኑን የሚመለከት ጥያቄ ነው:: አንዳንዶቹም ከትዳር ጓደኞቻቸው ጋር በግብረ ስጋ ግንኙነት እንደማይጣጣሙ ይገልጻሉ። በዚህ ወቅት ከመጀመሪያው ጥያቄ ወደ ሌላ ቀጣይ ጥያቄ በመሻገር አንዳንዶቹን በፖርኖግራፊ ላይ ያላቸውን አቋምና ልምምድ መረዳት እንድችል የሚረዳ ጥያቄ እጠይቃቸዋለሁ:: ለዚህ ጥያቄየ መልስ የሚሰጡ አንዳንዶች መላሾች የፖርኖ ግራፊ ቪዲዮዎችና ፊልሞች ተጠቃሚ እንደሆኑ በመግለጽ ሐቀኛ ምላሽ ይሰጡኛል። አንዳንዶቹ ልምምዳቸውን እንደ ትክክለኛ እርምጃ አድርገው በመውሰድ "ምን ምርጫ አለኝ?" ይላሉ:: እነዚህ ሰዎች የበደለኝነት ስሜት ቢሰማቸውም "ከሌላ ሰው ጋር በዝሙት ከመውደቅ ይሻላል! ወይም ወደ ፍች ከመሄድ ይሻላል!" በማለት አእምሮቸውን በማሳመን በድርጊታቸው ለመቀጠል ይበረታታሉ:: ራሳቸውንም ያደፋፍራሉ።

በምክር አገልግሎት ካጋጠሙኝ አሳዛኝ ታሪኮች መካከል አንዱ ከኢትዮጵያ ውጭ በሚኖሩ ከተጋቡ ቅርብ ዓመት በሆናቸው ጥንዶች መካከል የተፈጠረ ክስተት ነው:: ባል ለአገሩ አዲስ የሆነ፣ ትምህርት ላይ የሚያተኩርና አብዛኛውን ጊዜ ቤት ውስጥ የሚያሳልፍ ሲሆን ሚስት ደግሞ አዲስ የትዳር ሕይወቷን ለማሳካትና የተለያዩ የቤት ወጭዎችን ለመሸፈን ሁለት ሥራ በመሥራት ብዙ ጊዜዋን ከባሏ ጋር ሳይሆን ሥራ ላይ ታሳልፍ ነበር። ሥራ ላይ ብቻ ያተኮረች ሚስት ከተወሰኑ ዓመታት በኋላ ወደ ትዳሯ ዞወር በማለት ከባሏ ጋር ጊዜ ለማሳለፍ ስትፈልግ እርሱ በእነዚህ ዓመታት ቤት ውስጥ በዋለበትና ከሚስቱ ትኩረት በተነፈገው ጊዜ የተለማመደው የፖርኖግርፊ ልምምድ እንድታጣው ምክንያት ሆነባት። ልቤን በጣም የነካው **"በገዛ እጄ ባሌን አጣሁት"** በማለት የተናገረችው ንግግር ነው:: ባለትዳሮች እርስ በርሳቸው አብረው የሚቆዩበት

ጥሩ ኅብረትና የግብረ ስጋ ግንኙነት የሚያደርጉበት የጋራ ጊዜ የግድ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ይህንን የኅብረት ጊዜ መፍጠርና ሕይወትን መካፈል እንዲሁም መጣጣም ያለበት የግብረ ስጋ ግንኙነት ማድረግ ካልቻሉና የግብረ ስጋ ግንኙነት ፍላጎትን ባለማሟላት አንዱ ሌላውን መቅጣት ከጀመር የትዳር ጓደኛውን ለፖርኖግራፊ ሱስ ተጋላጭ እንዲሆን አሳልፎ እየሰጠ መሆኑን መረዳት ይኖርበታል። እንዲህ ዓይነቱ ስህተት በትዳር ውስጥ ለግጭትና ለአለመግባባት ምክንያት ከመሆኑም በላይ ትዳርን የመበተን ውጤት ሊያስከትል ይችላል፡፡

## 7. የክፉ መንፈስ አሠራርና ተጽዕኖ

ሰይጣን ከመቼውም ዘመን በበለጠ ሰዎች ወደ ትክክለኛ የትዳር ግንኙነት እንዳይደርሱ የጋብቻን ክቡርነት በማቃለል፣ እግዚአብሔር ከደነገገው ውጭ የሆነ ክፉ ልምምድ እንዲበዛ እና ለእግዚአብሔር ሰዎች የማይመችና የማይገባ ልምምድ ውስጥ እንዲገቡ በማድረግ ክፉ ስራውን በተለያየ መንገድ እያስፋፋ ይገኛል። እኛም እንደ ክርስቲያን ባለትዳር ሃሳቡን ልንነቃበትና በጽድቅ ልናሸንፈው ይገባል። ዘመኑ ሰይጣን በራሱ ክፉ አሳብ የኢንተርኔት መርብን በመመጠቀም ክርስቲያኖችንና ክርስቲያን ባለትዳሮችን በፖርኖግራፊ እንዲጠመዱ በማነሳሳት፣ አጋጣሚዎችን በመፍጠር፣ ለፈተና እንዲጋለጡ በማድረግና በትዳራቸው ያጡትን የግብረ ስጋ ግንኙነት ፍላጎት ማርኪያ አማራጭ እንዲጠቀሙ ሰበብ እየሰጠ በዚህ ክፉ ሱስ ተጠቂ፣ ተጋላጭና የወሲብ እስረኛ እንዲሆኑ እያደረገ ያለበት ጊዜ መሆኑን መዘንጋት የለብንም።

# VI. የፖሮኖግራፊ ሱስ አሉታዊ ተጽዕኖ

## 1. መደበቂያና ማምለጫ መንገድ አድርገው መጠቀማቸው

በፖርኖግራፊ የተጠመዱ ሰዎች ፖርኖግራፊን ከተለያዩ ነገሮች እንደ መደበቂያና ማምለጫ አድረገው ይጠቀሙበታል። ለጊዜው የሚሰጠውን ወቅታዊ የሆነ ወሲባዊ የስሜት እርካታና ጊዜያዊ ደስታ ለማግኘት ሲሉም የወሲብ ሱስ እስረኛ ይሆናሉ። አንዳንዶች ራሳቸውን በአልኮል፣ በአደንዛዥ ዕፅ (ድራግ)፣ በትንባሆና በሌሎች ሱስ አመንጭ መንገዶች በመጠቀም በሕይወታቸው ከተፈጠረ ጊዜያዊ ድብርት፣ ጭንቀት፣ ውጥረትና የሕመም ስሜት ለማስመለጥ ጥረት እንደሚያደረጉ ሁሉ የዚህ ሱስ ተጠቂዎች ደግሞ በፖርኖግራፊ ውስጥ ራሳቸውን በመደበቅ ጊዜያዊ ችግራቸውን ለመርሳት ይሞክራሉ።[46] ዘለቄታ ያለው መፍትሔ ከማፈላለግ ይልቅ ጊዜያዊ የሆነ ደስታ ለመፍጠር ቅድሚያ በመስጠት በሚወስዱት ያልታሰበበት እርምጃ ለዕድሜ ልክ እስራት አልፈው ይሰጣሉ።

[46] sexuality and relationship counseling p 158





## 2. ጥልቅ በሆነ የተጎዳ ስሜት ውስጥ መኖር

በፖርኖግራፊ ሱስ የተጠመዱ ሰዎችን በጥልቀት ለማወቅ ጥረት ብናደርግ ስለራሳቸው ያላቸው አመለካከት በጣም ዝቅተኛ ሆኖ ልናገኘው እንችላለን። ማሕበራዊ ግንኙነታቸው በጣም ደካማ ነው፡፡ ከትዳር አጋሮቻቸው፣ ከቤተሰብና ከሌሎች ወዳጆች ጋር ከሚደረግ ማሕበራዊ ግንኙነት ራሳቸውን ያርቃሉ፡፡ በብቸኝነት በጣም የተጠቁ ናቸው፡፡ በሰው ዘንድ ተቀባይነት የለኝም ብለው የሚያስቡና የማንነት ቀውስ ያለባቸው ናቸው። ባጋጠማቸው የማንነት ቀውስ ምክንያት ድብቆችና ገለልተኞች ለመሆን ይገደዳሉ። አንዳንዶች ደግሞ ምናልባት ከአሁን በፊት ጾታዊ ጥቃት ያጋጠማቸው ሊሆኑ ይችላሉ። በአስገድዶ መደፈር ወይም በሌላ በልጅነታቸው በደረሰባቸው ወሲባዊ ጥቃት ... ምክንያት ከተቃራኒ ጾታ ጋር ከሚኖራቸው የግብረ ስጋ ግንኙነት ይልቅ የፖርኖግራፊ ፊልሞችንና ምስሎችን ማየትን በማዘውተር ወይም ራሳቸው በራሳቸው በግለ-ወሲብ (ማስተርቤንሽን)ና በተለያየ መንገድ የወሲብ ስሜታቸውን ማርካትን የሕይወት አማራጭ አድርገው ይወስዳሉ፡፡ ከጊዜ በኋላ ከዚህ ሱስ ለመውጣት ቢሚክሩ እንኳን ካደረባቸው አሉታዊ ተጽዕኖ የተነሳ በቋሚ የዚህ ሱስ እስራት ውስጥ ተጠምደው በባርነት ለመኖር ይገደዳሉ፡፡[47]

## 3. ከትዳር አጋሮቻቸው ጋር ስሜታዊና ግብረ ስጋዊ ግንኙነትን ማቋረጥ ይጀምራሉ

በተለያየ መንገድ በፖርኖግራፊ ሱስ ተጠቂ የሆኑ ባለትዳሮች ልምምዳቸው በግብረ ስጋ ግንኙነት ሱስ ይበልጥ እንዲያዙ ይዳርጋቸዋል። ከመጠን ባለፈ በፍትዎት ፍላጎት ሱስ ከመያዛቸው የተነሳ በትዳራቸው ባለው የግብረ ስጋ ግንኙነት የማይረኩና ስሜታዊ በመሆን ከትዳር አጋሮቻቸው ጋር በየጊዜው የሚጋጩ ይሆናሉ። ሌላው ችግራቸው ከትዳር አጋሮቻቸው ትክክለኛ ያልሆነ ግብረ ስጋዊ ግንኙነትን ይጠብቃሉ፣ ይጠይቃሉ ብሎም የፈለጉትን ለማግኘት የትዳር ጓደኛቸውን ሊያስገድዱ ይችላሉ። ድብቅ በሆነ የፖርኖግራፊ ሱስ በመጠመዳቸው ምክንያት ከትዳር የሚጠበቀውን በእውነተኛ ፍቅር ላይ የተመሠረተውን ጤናማ የሆነ የግብረ ስጋ ግንኙነት ሂደት በማቃለል ወደ ማይፈለግና እንግዳ የሆነ የወሲብ ግንኙነት የመግባት ጥያቄ እንዲያቀርቡ ይገደዳሉ። በክርስቲያን የትዳር ሕይወት ውስጥ በትክክለኛው የግብረ ስጋ የሰውነት ክፍል የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈጸም ተፈጥሯዊ፣ ተገቢና ንጹሕም ነው *"መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ይሁን፤ ሴሰኞችንና አመንዝሮችን ግን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል።"* /ዕብ 13፡ 4/።

[47] sexuality and relationship counseling p 158

## 4. በፖርኖግራፊ ሱስ የተጠመዱ ሰዎች ለሌሎች ችግሮችም ተጋላጭ መሆን ይጀምራሉ

በፖርኖግራፊ ሱስ የተጠመዱ ባለትዳሮች በተያዙበት ሱስ በቀላሉ የማይረኩ፣ ይበልጥ የሚፈልጉና በየጊዜው የሚጨምር የፍትዎት ፍላጎት ያላቸው ናቸው:: ሌሎች ሰዎች ሌላ ነገር እንደሚራቡና እንደሚጠሙ ብሎም ፍላጎታቸውን ለማርካት ዋጋ እንደሚከፍሉ ሁሉ እነዚህ ሰዎችም ብርቱ የሆነ የፍትዎት ፍላጎት ያላቸውና ፍላጎታቸውንም ለማርካት ማንኛውንም ዋጋ የሚከፍሉ ናቸው። የፍትዎት ፍላጎታቸው በተፈለገው ጊዜ ባልተሟላ ወቅት በብርቱ ይቆጣሉ፣ ንዴት ያጠቃቸዋል፣ በከፍተኛ ጥላቻ ውስጥም ይገባሉ። በፖርኖግራፊ የተጠመዱ ባለትዳሮች ከቤተሰቦቻቸው ጋር ከመሆን ብቻቸውን በራሳቸው ክፍል ውስጥ መሆንንና ቀድሞ የነበራቸውን የጓደኝነት ቅርበት በመቀነስ ከትዳር ጓደኛቸው ጋር እንኳን የጊዜ ሰሌዳ በመምረጥ መገናኘት የሚፈልጉ ናቸው::[48]

አንድ ጊዜ የምክር አገልግሎት ስሰጥ ከገጠሙኝ ችግሮች መካከል አንዱ እንዲህ ይመስል ነበር፡- ብዙ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ሁኔታዎችን ለማጣራት ስሞክር ባሏ በፖርኖግራፊ ሱስ የተጠመደባት ሚስት ስለባሏ፡- "ራሱን የቻለ የራሱ ክፍል አለው:: ኮምፒዩተሩን ከእርሱ ውጭ የቤተሰቡ አባል መንካትና መጠቀም አይችልም:: ልጆቹ ወደ እርሱ ክፍል ሲመጡ ዳዲ እየመጣን ነው ወይም ልንመጣ ነው ብለው ድምጽ በማሰማት ማስጠንቀቂያ መስጠት አለባቸው:: ሌሊት ያመሻል ቀን ደግሞ በጣም ይተኛል:: ከሁሉ በላይ ብቻውን መሆን በለመደበት ሰዓት እርሱን ሌላ ስራ ማዘዝ እጅግ በጣም ያስቆጣዋል (ይናደዳል) ብሎም ከእኔ ጋር በከፍተኛ ሁኔታ ይጋጫል::" እያለች ምልክቶቹን በመዘርዘር አጫወተችኝ። እነዚህ ሁሉ በቂ ማስረጃ ሊሆኑ አይችሉም ልትሉ እንደምትችሉ አስባለሁ:: ነገር ግን ይህች ሴት ብዙ ጊዜ እርሱ ሳያውቅ ሲመለከተው የነበረውን የፖርኖግራፊ ድረ ገጽ ሳይዘጋው አግኝታ ነበር:: ጥያቄ በጠየቅሁ ጊዜ ምልክቶቹን በዝርዝር ልታስረዳኝ የሞከረችውም ለዚህ ነበር።

ሌላው የፖርኖግራፊ የቪዲዮ ምስሎችና ፎቶግራፎች አዘውትረው በማየት በወሲብ ሱስ የተጠመዱ ሰዎች የሚታይባቸው ጸባይ የአካል ድካም፣ የእንቅልፍ ብዛት፣ አለመንቃትና ለሥራ ተነሳሽነትና ኃይል ማጣት ነው::[49] እነዚህ ምልክቶች የሚታዩባቸው ሰዎች ሁሉ በጅምላ የፖርኖግራፊ የቪዲዮ ምስሎችና ፎቶግራፎች በማየት ሱስ የጠመዱ ናቸው ማለት አይደለም:: በሥራ ብዛት፣ በትምህርት ላይ ባሉ ሰዎች ላይ ጥናትና የወረቀት ሥራዎች በፈጠሩት እረፍት የለሽ ወከባ፣ በጤና መታወክ፣ የተለያዩ ችግሮች ባስከተሉት ድብርትና የተስፋ መቁረጥ ሁኔታ ... ምክንያት የአካል

[48] sexuality and relationship counseling p 158

[49] sexuality and relationship counseling p 158





ድካም፣ ንቃትና የሥራ ተነሳሽነት ማጣት እንዲሁም የእንቅልፍ ብዛት የመሳሰሉት ችግሮች በሰዎች ላይ ሊከሰቱ እንደሚችሉ አገነዘባለሁ:: ነገር ግን እዚህ ላይ ማሳየት የፈለግሁት በፖርኖግራፊ ፍትወታዊ ሱስ የተጠመዱ ሰዎች የራሳቸውን ማንነት ዝቅ አድርገው የሚያዩ በመሆናቸው በሚፈጠርባቸው የተስፋ መቁረጥ ምክንያትና በተለይ በለመዱት ሰአት የሚፈልጉትን ማግኘት ባልቻሉ ጊዜ ከፍተኛ የሆነ ድብርት የሚያጠቃቸው መሆኑን ነው። በዚህም ምክንያት ራሳቸውንና ማንኛውንም የሕይወት እንቅስቃሴ የሚያዩበት ተስፈኛ የሆነ እይታ ስለማይኖራቸው በጨለምተኛነት፣ በሌላ አካል አስገዳጅነት አንድ ነገር የማድረግ ግዴታ የተጣለባቸው በሚመስልና በጣም በተሰላቸ ስሜት ነገሮችን ሁሉ ያስተናግዳሉ:: ወሲባዊ ፍላጎት አእምሮቸውንና ስሜታቸውን ስለሚቆጣጠራቸው ለሌላ ሃሳብና ድርጊት ክፍትና ንቁ አይሆኑም። በተደጋጋሚ ይህን አመጽ በድብቅ ከመለማመዳቸው የተነሳ ችግር ውስጥ እንዳሉ በተረዱ ጊዜ እንኳን ከችግሩ ለመውጣት እየፈለጉ ባለመቻላቸው በየጊዜው የበደለኝነት፣ የኃፍረትና የጭንቀት ስሜት ይፈራረቅባቸዋል።

## VII. በፖርኖግራፊ ሱስ ለሚፈጠሩ ግጭቶች መፍትሔዎች

### 1. በሱስ የተጠመደ አካል ሊወስደው የሚገባ እርምጃ

#### 1) *መጀመር፡- ኃጢአት መሆኑን ማመንና እርዳታ ለማግኘት ፈቃደኛ ከመሆን መጀመር*

ፖርኖግራፊ በተባለው አስከፊ ሱስ የተጠመዱ ሱሰኞች ከተያዙበት ሱስ ለመላቀቅ ከሁሉ አስቀድመው የእግዚአብሔር ቃል እንደሚነግረን የወደቁበት ወጥመድ ኃጢአት መሆኑን ከመቀበል መጀምር ከችግሩ መውጣት የሚያስችል እርዳታ ለማግኘት ቀዳሚው ጉዳይ ነው። ስለፖርኖግራፊ መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል? የሚለውን ሃሳብ ለመዳሰስ የሞከርኩት አንዳንዶቹ ተጠቃሚዎች አመጽና ክፉ ልምምድን የሚያሰራጬት ምንም ችግር እንዴለለበት፣ ጽድቅና መልካም ሥራ እንደሆነ አድርገው በመናገር ስለሆነ ነው:: ይህን አቋም የሚያራምዱና ጥቅስ በመጥቀስ ክፋታቸውን የሚያዛምቱ አማኝ ነን የሚሉ ሰዎች መኖራቸውን ይህ አቋም ካላቸው ክርስቲያን ነን ባይ ሰዎች ጋር ባደረግሁት ውይይት ለማወቅ ችያለሁ። መጽሐፍ ቅዱሳዊው እውነታ እነርሱ ከሚሉት በተቃራኒ ርኩሰታዊውን ልምምድ በግልጥ ኃጢአት፣ ርኩሰት፣ ፍትዎት፣ አመንዝራነት፣ ሴሰኝነት፣ ክፉት በማለት ይገልጸዋል። ከችግሩ ለመውጣት የመጀመሪያው እርምጃ ይህን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሐቅ በመረዳት አምኖ መቀበልና ከችግሩ ለመውጣት ፈቃደኝነትንና ፍላጎትን ማሳየት ነው /ቆላ 3: 5፣ 1ኛተሰ 4: 3-5፣ 1ኛቆሮ 6: 18/

#### 2) *መግባት፡- ድካምን (ጥፋተኝነትን) አምኖ በመቀበል ንስሃ መግባት*

በዚህ ችግር ውስጥ ያሉ ክርስቲያኖች በአጠቃላይም የዚህ ሱስ ሰለባ የሆኑ ሰዎች ከችግሩ የመውጣት ፍላጎት ካላቸው በቅድሚያ ከቁጥጥር ውጭ የሆነው ወሲባዊ ባሕርያቸው ስህተትና ኃጢአት መሆኑን መቀበል ይኖርባቸዋል:: እግዚአብሔር

የሚያድስ፣ የሚለውጥና ነፃ የሚያወጣ ኃይል እንዳለው በማመን እና ለእግዚአብሔር! ለራሳቸውና ለሌሎች ሰዎች በመናዘዝ ፈቃዳቸውንና ሕይወታቸውን በእግዚአብሔር ጥበቃና ቁጥጥር ስር እንዲሆን መወሰንና መፍቀድ መለኮታዊና ሰብአዊ ድጋፍ ማግኘት ያስችላቸዋል። ሌሎች የሞራል ግድፈቶች ካሉባቸው ደግሞ በእርጋታ ራሳቸውን በመመርመር ለለውጥ መዘጋጀት አስፈላጊ ነው። እውነተኛ ንስሃ በመግባት ተግባራዊ የሕይወት ለውጥ ለማምጣት የውሳኔ ሰው፣ ቆራጥና ጽኑ መሆን ይገባቸዋል።

**3) መለማመድ፡- በክርስቶስ ማንነት ላይ በተመሠረተ የክርስትና ሕይወት መኖርን መለማመድ**

የክርስትና ሕይወት መሠረት በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት ላይ በመመሥረትና በእርሱ በመታመን የሕይወት ውድቀቶችን ለማሸነፍ ዝግጁ መሆን ተገቢ ነው። በክርስቶስ ማንነት ውስጥ ስንሆን እርሱ በእኛ ሆኖ ይረዳናል። ሕይወታችንን ሊለውጥና የቅዱስ መንፈሱ መኖሪያ እንድንሆንና የእርሱን መልክ እንድንመስል በሚያስችል ጸጋው ነፃነትና አቅምም ይሰጠናል። በዚህ የሕይወት መስመር በቋሚነት ለመኖር ደግሞ በክርስቶስ ሕይወት ላይ፣ በጽድቁ ላይ እና በትምህርቱ ላይ መመሥረት የግድ ነው /**1ኛቆሮ 3: 16-17፣ 1ኛቆሮ 6: 16-20፣ 1ኛቆሮ 15: 56-57**/።

በክርስቶስ ማንነት ላይ በመመሥረትና በመታነጽ በየጊዜው እየጨመረ የሚሄድ መንፈሳዊ ሕይወትና እንቅስቃሴ ውስጥ መሆን ተገቢ ነው። በሂደት መንፈሳዊ ፍሬዎችን በሕይወት በመጨመርና በማብዛት፣ ከጌታ የተማርነውን፣ የተቀበልነውን፣ የሰማነውንና ያየነውን በማድረግ (በመታዘዝ) ሕይወትን ከተለያየ ሱስ መጠበቅና ማስመለጥ ይቻላል /**ፊል 4: 8-9**/። የእግዚአብሔር ቃል እንደሚያስተምረው በየቀኑ የልቦናን ወገብ በመታጠቅ፣ በመጠን በመኖር፣ ያለፈን ምኞት ባለመከተልና የተጠራንበትን ዓላማ በመገንዘብ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ራስን መግዛትን በመለማመድ የበኩላችንን ድርሻ መወጣት ትክክለኛው የነጻነት መንገድ ነው /**ኤፌ 2:1-3፣ 2ኛጴጥ 1: 3-4**/ ።

**4) መገንዘብ፡- ኃይል በሚሰጠን በክርስቶስ እንደምንችል መገንዘብ**

መንፈሳዊ ንቃታችሁን በመጠበቅ ተመልሳችሁ በሱስ እንዳትጠመዱ መርሆዎችን መጠበቅና መለማመድ ሕይወትን በማያቋርጥና በተትረፈረፈ ሕይወት መኖር እንዲቻል ጠቀሜታው ላቅ ያለ ነው። እግዚአብሔር ለሕይወት፣ ለመንፈሳዊ ብስለትና እድገት እንዲሁም ለቅድስና እንደጠራችሁ በማመን በቅድስና መመላለስን መለማመድ ቁልፍ መፍትሔ መሆኑን መገንዘብ አስፈላጊ ነው /**1ኛጴጥ 1: 13-16**/። በሱስ የተያዘው ሰው ሊገነዘበው የሚገባ ጉዳይ ቢኖር ከቁጥጥር ውጭ የሆነ የወሲብ ፍላጎትን ለማስወገድና በሱስ የተጠመደውን ሰው የሚረዳ (ደካሞችን ሊረዳ የሚችል) ሁሉን የሚችል አምላክ እንዳለ ማወቅ፣ ማመንና በአቅርቦቱ ለመረዳት እንደሚቻል መገንዘብ አስፈላጊ ነው /**ፊል. 4: 8-13 ኢሳ 40: 27**/።





**5) መጠቀም፡- የተለያዩ የመፍትሔ ሃሳቦችን መጠቀም**

**i. በአሳብና በስሜት መጓዝን መቆጣጠር**

ከፖርኖግራፊ ሱስ ነፃ በመውጣት ጤነኛና ደስተኛ የሆነ ትዳርና ቤተሰብ እንዲኖራቸው ሁሉም አካላት የየበኩላቸውን ጥረት ሊያደርጉ ይገባል። የፖርኖግራፊ ሱሰ ከፍተኛውና የመጀመሪያው አሉታዊ ተፅዕኖ አእምሮንና ስሜትን መቆጣጠር መቻሉ ነው። ስለዚህ የፍትዎት ስሜት አእምሯቸውን በመቆጣጠሩ የተለያዩ ከክርስትና ጋር የሚቃረኑ መንገዶችን ተጠቅመው የፍትዎት ፍላጎታቸውን የማርካት ባሪያ ከሆኑበት ለመላቀቅ ፍላጎት ሊኖራቸው ይገባል። ይህ ፍላጎት ካላቸው ፍላጎታቸውን በተግባራዊ ጥረት ለማገዝ ቆራጥነትና አቋም ያስፈልጋቸዋል። የጥረታቸው የመጀመሪያው እርምጃ ደግሞ በሃሳባቸው የሚመጣ የፍትዎት ፍላጎት በሌላ አሳብ እንዲለወጥ አእምሯቸውንና ስሜታቸውን መቆጣጠር የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠር መሆን አለበት። *"የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ።"* /**ሮሜ 12፡ 2**/ የእግዚአብሔር ቃልም *"አጥብቀህ ልብህን ጠብቅ፥ የሕይወት መውጫ ከእርሱ ነውና።"* /**ምሳሌ 4: 24**/ በማለት አጥብቀን ልባችንን መጠበቅ እንዳለብን የሚያስተምረን አሳባችንን በጤንነት ከጠበቅን ተግባራችንና ኑሯችንም ጤነኛ እንደሚሆን ለማስረዳት ነው።

**ii. የሚፈትኑ ነገሮችን ማራቅና ከእነርሱ መሸሽ**

በፖርኖግራፊ ሱስ የተጠመዱ ሰዎች ከተያዙበት እስራት ነፃ መውጣት ፍላጎታቸውና አቋማቸው ከሆነ ለፖርኖግራፊ ልምምድ ከሚያነሳሱና ከሚያበረታቱ የተለያዩ መጽሔቶች፣ ጽሑፎችና የቪዲዮ ፊልሞች በመራቅና እነዚህን ነገሮች ከአካባቢያቸው በማራቅ ራስን ከፈተና መጠበቅ ጠቃሚ ነው። በዙሪያ ያሉ ተፈታታኝ የሆኑ ጹፎችን ብቻ ሳይሆን ኮምፒዩተር ላይ የተቀመጡ የተለያዩ ቪዲዮችን መደምሰስ ተገቢ ነው። *"ከዝሙት ሽሹ። ሰው የሚያደርገው ኃጢአት ሁሉ ከሥጋ ውጭ ነው፤ ዝሙትን የሚሠራ ግን በገዛ ሥጋው ላይ ኃጢአትን ይሠራል።"* /**1ኛቆሮ 6፡ 18**/። ብቻቸውን በሚሆኑበት ወቅት ለፍትዎት አሳብ ፈተና የሚጋለጡ ከሆነ የቤተሰብ አባል ወይም ሌሎች ሰዎች ባሉበት ወቅት ኮምፑተር መጠቀም ራስን ከፈተና የመጠበቂያ ጥሩ አማራጭ ነው። በተጨማሪ ለሌላ ሰው ተጠያቂ በመሆን ያሉበትን ደረጃ የሚጠይቅ፣ የሚከታተልና ድጋፍ የሚሰጥ መንፈሳዊ፣ ታማኝና ብቃት ያለው አማካሪ ወይም መጋቢ ማግኘት በእግዚአብሔር ቃል እውነት እየተቀረጹና እየታደሱ በአስተሳሰብና በተግባራዊ የለውጥ መንገድ ለመጓዝ እጅግ በጣም አስፈላጊ እርምጃ ሊሆን ይችላል። *"ፊተኛ ኑሮአችሁን እያሰባችሁ እንደሚያታልል ምኞት የሚጠፋውን አሮጌውን ሰው አስወግዱ፥ በአእምሮአችሁም መንፈስ ታደሱ"* /**ኤፌ 4: 22-23**/

**iii. ጠንካራ ክርስቲያናዊ ስነ-ምግባርና መንፈሳዊ ልምምድ ላይ ስር መስደድ**

ሕይወትን ለክርስቶስ መስጠትና ማስገዛት እንዲቻል የሚረዱና መንፈሳዊ አቅጣጫ የሚያሳዩ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ጋር ሕብረት መፍጠር አስፈላጊ ነው።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶችን ለማወቅ፣ ለመለማመድና ሥር በመስደድ መለወጥ እንዲቻል ከሚያስተምሩና ከሚከታተሉ አገልጋዮች እርዳታ የሚያገኙበትን እድል መፈለግ አለባቸው። የፖርኖግራፊ ልምምድ ኃጢአት እንደሆነ መረዳት፣ በእውነተኛ ንስሃ መመለስና ይበልጥ ኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ትኩረት በማድረግ ለእውነተኛ ለውጥ የመዘጋጀት ውሳኔ መወሰን ያስፈልጋል። *"አንተ ግን፥ የእግዚአብሔር ሰው ሆይ፥ ከዚህ ሽሽ፤ ጽድቅንና እግዚአብሔርን መምሰል እምነትንም ፍቅርንም መጽናትንም የዋህነትንም ተከታተል። መልካሙን የእምነት ገድል ተጋደል፥ የተጠራህለትንም በብዙም ምስክሮች ፊት በመልካም መታመን የታመንህለትን የዘላለምን ሕይወት ያዝ።* /**1ኛጢሞ 6፡ 11-12**/

መጽሐፍ ቅዱስ *"ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፥ ሁሉም አዲስ ሆኖአል።"* /**2ኛቆሮ 5፡ 17**/ በማለት እንደሚመሰክረው በክርስቶስ አዲስ ሕይወት እንዳለው አማኝ አሮጌውን ነገር በመተው አዲስ ሕይወትን በትጋት ወደ መለማመመድ መግባት በችግሩ የተያዙ ሰዎች ከተጠመዱበት ሱስ ነፃ ለመውጣት የሚችሉበት ቁልፍ ነው:: ይህን ትጋት የተሳካ ለማድረግ በቅዱሳን መንፈሳዊ ሕብረት በመሳተፍ በኅብረቱ ተጠያቂነትና በረከት ተጠቃሚ መሆን አስፈላጊ ነው። አንዱ ሌላውን ማገልገል እንዲችሉና በማሕበራዊ ግንኙነት የተሳሰረ ሕብረት እንዲኖራቸው ራሳቸውን በጤናማ ኅብረት ህብረት ውስጥ እንዲሳተፉ ማድረግ ከፖርኖግራፊ ሱስ ለመውጣት ባለው ሂደት የሚሰጠው እገዛ ከፍተኛ ነው። አገልጋዮችም ሆኑ የትዳር አጋር በፖርኖግራፊ ልምምድ ውስጥ ያለውን ሰው በመርዳት ሂደት ውስጥ ማረጋገጥ ካለባቸው ነገር መካከል አንዱ እርዳታ ፈላጊዎቹ በመልካም ሰዎች መከበባቸውን ነው። *"አትሳቱ፤ ክፉ ባልጀርነት መልካሙን አመል ያጠፋል"* /**1ኛቆሮ 15፡ 33**/

ቀጣይነት ያለው እርዳታ ለመስጠት ትዳራቸው እንዴት እንደሆነ ማረጋገጥ፣ ነፃ በመውጣቱ ሂደት የተፈጠረባቸውን ስሜት መረዳትና በተለይ የፖርኖግራፊ ልምምድ ውስጥ እንዲሆኑ ያደረጓቸውን ሁኔታዎች በጥንቃቄ መመዘን የመሳሰሉ መልካም እርምጃዎችን መውሰድ አለባቸው:: ከልምምዱ ለመውጣት ጥረት በሚያደርጉ ጊዜ ምን ዓይነት ስሜት እንደሚሰማቸው በመጠየቅ መረዳት ተገቢ ነው። ሊሰማቸው የሚችለውን ስሜትና ያሉበትን ሁኔታ በመረዳት ለማገዝ፣ በጸሎትና በምክር ለመርዳት መትጋት ብሎም በተለያዩ ሥራዎች እንዲጠመዱ ማድረግ ጠቃሚ ነው:: አብሮነትን በማጠናከርም ከፖርኖግራፊ ሱስ ልምምድ እየወጡ እንዲመጡ በጤነኛው የሕይወት መስመር ስር እንዲሰድዱ ለችግሩ ሰለባዎች ያላሰለሰ ድጋፍና ጥረት ማድረግ ትርጉም ያለው ውጤት ያመጣል።

**iv. በጋብቻ አማካሪዎች አገልግሎት ተጠቃሚ መሆን**

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ልዩ ትኩረት በመስጠት ሊጀምሩትና ሊያጠናክሩት ከሚገባው አገልግሎት አንዱ የጋብቻና የቤተሰብ የማማከር አገልግሎት ነው:: ከመቼውም ጊዜ በበለጠ በትዳርና በቤተሰብ ዙሪያ እየደረሱ ያሉ የተለያዩ ቀውሶችን ለመቀነስና ለማስወገድ አንዱ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችና መሪዎች ኃላፊነት የማማከር





አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ አማኞችን መለየት፣ ማሰልጠንና ኃላፊነት በመስጠት የማማከር አገልግሎትን አጠናክሮ መጀመር ነው:: ያን ጊዜ ብቻ ምክርና እርዳታ ፈላጊ ሰዎች በፈለጉት ጊዜና ቦታ የምክር አገልግሎትን መጠቀም የሚችሉበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር ይቻላል:: ይህን ማድረግም ምርጫ ሳይሆን ግዴታ ሊሆን ይገባል። የችግሩን በፍጥነትና አደገኛ በሆነ መንገድ የመስፋፋት ሂደት ለመቆጣጠርና ለመቀነስ እንዲሁም የብዙ ክርስቲያኖችን ትዳር ከቀውስና ከፍርሰት ለማዳን ቤተ ክርስቲያን የጸጋ ስጦታ፣ ሌሎችን የማገልገል ልብ፣ ጊዜ፣ ስልጠናና ልምድ ያላቸውን ሰዎች በማሰለፍ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ልትንቀሳቀስ ይገባታል።

በፖርኖግራፊ ሱስ የተጠመደው የትዳር አጋርም በቤተ ክርስቲያን ባለው የጋብቻና የቤተሰብ የማማከር አገልግሎት ተጠቃሚ በመሆን በለውጡ ሂደት አማካሪዎች አብረው እንዲሆኑ መፍቀድ፣ መተባበርና እርምጃ መውሰድ ይጠበቅበታል። የትዳር አማካሪዎች በፖርኖግራፊ ሱስ የተጠመዱ ባለትዳሮችን በሚረዱበት ወቅት ግለሰቡን እንደ አማኝና እንደ ባለትዳር በማነጋገር ችግሩን ለመፍታት ልዩ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው። የቤተ ክርስቲያን መጋቢዎች፣ መሪዎችና አማካሪዎች እርዳታ የማድረጉ ሂደት ከአቅም በላይ በሚሆንባቸው ወቅት ከምክር ፈላጊው ጋር በመነጋገርና ፈቃደኝነቱን በመረዳት ክርስቲያን ፕሮፌሽናል አማካሪ ወደ ሆኑ ሰዎች ተመካሪውን በመምራት ተገቢውን እርዳታ እንዲያገኝ ማገዝ አስፈላጊ ነው።

**v. ባልና ሚስት አንዱ ለሌላው ግልጥነትና ተጠያቂነትን መፍጠር**

ራስን ከተለያዩ ወሲባዊ ፈተና ለመጠበቅና የትዳር የፍቅር ግንኙነት ለማጠናከር አንዱ ለሌላው ግልጥ የሆነ ተግባቦትና ተጠያቂነት መፍጠር ተገቢ ነው። ባልና ሚስት በቁጥጥር መንፈስ ሳይሆን ነፃነት፣ መተማመመን በተሞላው ግንኙነትና በፈቃደኝነት በተመሠረተ ተጠያቂነት መፍጠር በጥንዶች ላይ ይበልጥ መተማመንና አንዱ ሌላውን መጠበቅ፣ መርዳትና መሸፈን እንዲኖር ያግዛል። በቤት ውስጥ ያሉ ኮምፒዩተር፣ ላፕቶፕ፣ ተንቀሳቃሽ የእጅ ስልኮች፣ በኢንተርኔት መርብ የሚላኩና ገብተን የምንመለከታቸው ድረ ገጾችን፣ የሚታዩ የተለያዩ ቪዲዮዎችና ፊልሞችን አንዱ የትዳር አጋር የሌላውን ማየትና መጠቀም ቢችል ስጋትና ጥል የማይፈጥር ሁኔታ በተገነባ ግልጥነትና ተግባቦት ግንኙነትን መጠበቅ ተገቢ ነው።

**vi. የተለያዩ ሶፍትዌሮችን በመግዛት ከኮምፒዩተር ውስጥ የማይፈለጉ ድረ ገጾችን በማጣራትና በመቆጣጠር ማስቆም**

በፖርኖግራፊ ሱስ የተጠመዱ ባለትዳሮች ከዚህ ችግር ለመውጣት ሲሞክሩ የሚፈትኑ ነገሮችን ማራቅ አንዱ ወሳኝ የመፍትሔ መንገድ ነው:: ራስን መግዛት ችግሩን መቋቋም ካልተቻለ ደግሞ ኮምፒዩተርን ለማጽዳት የሚያግዙ ሶፍትዌሮችን በመግዛት በኢንተርኔት የሚላኩ የተለያዩ ለፍትዎት የሚያነሳሱ ድረ ገጾችን ማጣራትና ማስቆም የሚቻልበትን መንገድ መጠቀም ብልህነት ነው። እዚህ ላይ ይህንን ለማድረግ

የሚያስችሉ የታወቁ ሶፍትዌሮችን በመጥቀስ ማሳወቅ ግንዛቤ ለማስጨበጥና አንዳንድ ወገኖችን ለመርዳት ጠቃሚ ነው። በአገራችን የታወቁ እንዲህ ዓይነቱን ድረ ገጽ የሚከላከሉ ሶፍትዌሮች ስላልተዘጋጁ  በአማርኛ ቋንቋ ስማቸውን የመጥቀሱ ጉዳይ ያስቸግራል። ከዚህም ባለፈ የሶፍትዌሮችን ስም በአማርኛ ቋንቋ መጥቀስ ስለሶፍትዌሮች ግልጥ መረጃ ከማስተላለፍ ይልቅ መደናገር ሊፈጥር ይችላልና በቀጥታ በእንግሊዘኛ በሚጠሩበት የታወቀ ስማቸው ዝርዝራቸውን ላስቀምጥ እወዳለሁ። እናንተም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሶፍትዌሮች በመግዛት እንድትጠቀሙባቸውና ለእግዚአብሔርና በእግዚአብሔር ቃል መርህ መሰረት ራሳችሁንና ትዳራችሁን ለተመሠረተው የትዳር ሕይወት መርህ የማስገዛት ትጋታችሁን እንድትቀጥሉ አደራ እላለሁ።

- Net Nanny parental control
- McAfee safe eyes
- McAfee family protection
- PureSight PC
- CYBERSitter
- Cyber patrol
- Profile parental filter
- im view...  የመሳሰሉ የተለያዩ መንገዶችን መጠቀም ብልህነት እንጅ ሽንፈት አይደለም።

**vii. ከክፉ መናፍስት ተጽዕኖ ነፃ መውጣት**

ሰይጣን በተለያየ መንገድ ሊዋጋ ይችላል። አንዳንዶችን በቁጥጥሩ ሥር በማድረግና የራሱን ፈቃድ እንዲፈጽሙና እንዲያገለግሉት ባሪያ በማደርግ የሚገዛቸው ሲሆን ሌላው ክፉ አሠራሩ ደግሞ በውጭ በመሆን አሳብን በመላክ፣ አማኞችን በመጫን፣ ከሩቅ ሁኖ በመዋጋትና የተለያዩ ክፉ አሳቦችንና የፈተና ወጥመዶችን በመዘርጋት የክፉ ስራው ሰለባ እንዲሆኑ ያደርጋል። በእውነት ክርስቶስ ጌታና አዳኝ ነው ብሎ በሚያምን ዳግም በተወለደ አማኝ ሕይወት ውስጥ ኣጋንት ይኖራል እያልኩ ሳይሆን በየጊዜው በንስሃና በንስሃ ፍሬ መንፈሳዊ ሕይወትን በጽድቅ መንገድ መምራት ካልተቻለ ሰይጣን በአማኞች ሕይወት ላይ እንኳን በክፉ ሥራው ተጽእኖውን በማሳረፍ ባሪያና ተገዥ ሊያደርጋቸው ይችላል። እንደነዚህ ዓይነት በመናፍስት ክፉ ሥራ እስራት ውስጥ ያሉ በጌታ መንፈስ ነፃ ሊወጡ ይገባል። በእርግጥ ሁሉንም ነገር የመንፈስ አሠራር ተጽእኖ ብቻ ማድረግ የለብንም:: ነገር ግን የሰይጣንን አሠራር አሳንሶ በማየት እንደሌለ መቁጠርና ሁሉንም ነገር ተፈጥሯዊና ሰብአዊ  ብቻ በማድረግ በሕክምናና በሌሎች መንገዶች ብቻ ለመፍታት በመሞከር በዲያብሎስ ሥራ እንዳንታለል ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ችግሮችን በመለየት ተገቢውን አገልግሎት የማግኘት አስፈላጊ ነው:: አገልጋዮችም እንደጸጋቸው ተገቢውን አገልግሎት የመስጠት ኃላፊነት አለባቸው::





## 2. በሱስ የተጠመደን አካል (ግለሰብ) ለመርዳት ሊወሰድ የሚገባ እርምጃ

**1) *መጣር:- ችግሩን ይበልጥ ለመረዳት ጥረት ማድረግ***

**I. በፍቅርና በርህራኄ መቅረብ**

በፖርኖግራፊ ሱስ የተጠመደን ሰው ለመርዳት ኃላፊነትና ፍላጎት ያላቸው ሰዎች ሊወስዱት የሚገባው የመጀመሪያው የመነሻ እርምጃ ችግሩን ይበልጥ ለመረዳት እንዲችሉ በችግሩ ውስጥ ያሉ ሰዎችን በርህራኄና በፍቅር መቀበልና መቅረብ ነው። በፖርኖግራፊ ሱስ የተጠመደ የትዳር አጋርን ከዚህ ውድቀት ለማትረፍ የመጀመሪያው እርምጃ በፍቅር ለመርዳት መዘጋጀት እንጅ መፍረድ መሆን የለበትም። በፍቅርና በርህራኄ መቅረብ የችግሩ ተጠቂ ከሆኑ ሰዎች ጋር እርዳታ እየሰጡ ብዙ መንገድ አብሮ ለመዝለቅ ይረዳል። ጌታ ኢየሱስ ደካማ የሆኑ ሰዎችን ለመርዳት *"እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፥ ወደ እኔ ኑ፥ እኔም አሳርፋችኋለሁ።"* /ማቴ 11፡ 28/ ብሎ ወደ ራሱ በፍቅር በመጋበዝ ከእነርሱ ጋር በአስገራሚ ፍቅርና ርህራሄ አብሯቸው እንደነበር ወንጌላት ያስረዱናል። ስታመነዝር የተገኘችውን ሴት በአመንዝራነቷ ሰዎች እንደ ሙሴ ሕግ ሊፈረድባት የሚገባት እንደሆነች በማስረዳት ከሰዋት ነበር:: ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ ሳይፈርድባት ድጋሚ ተመሳሳይ ኃጢአት እንዳትሰራ በማስጠንቀቅ ምህረት ሲያደርግላትና በነፃ ሲለቃት ማየት የዛሬዎቹ ክርስቲያኖች በተመሳሳይ ችግር ውስጥ ያሉ ሰዎችን ለመርዳት ሊከተሉት የሚገባ ትልቅ ምሳሌ ነው። *"ኢየሱስም:- እኔም አልፈርድብሽም፤ ሂጂ ከአሁንም ጀምሮ ደግመሽ ኃጢአት አትሥሪ አላት።"* /ዮሐ 8፡ 11/

**ii. እያለፉበት ያለውን ሁኔታ ይበልጥ ለመረዳት የሚያስችሉንን የሚከተሉትን ተገቢ ጥያቄዎች መጠየቅ**

- የፖርኖግራፊ ፊልሞችን፣ የቪዲዮ ምስሎችንና ፎቶግራፎችን ማየት ከጀመሩ ስንት ጊዜ ሆናቸው? በስንት አመታቸው (እድሜአቸው) ማየት ጀመሩ? የሚያዩት በምን ያህል የጊዜ ርቀት ነው?
- የፖርኖግራፊ ፊልሞችን፣ የቪዲዮ ምስሎችንና ፎቶግራፎችን ለማየት ያነሳሳቸው ምንድን ነው?
- የፖርኖግራፊ ፊልሞችን፣ የቪዲዮ ምስሎችንና ፎቶግራፎችን ማየት የሚያዘወትሩት መቼ ነው? የሚመለከቱበት የጊዜ ሁኔታ ቀን፣ ማታ ወይንስ በየትኛው ሰዓት?

✓ ብቸኛ በሚሆኑበት (ሰው በሌለበት) ጊዜ?
✓ ምን ዓይነት ስሜት ሲፈጠርባቸው ነው ወደ ማየት የሚሄዱት (በሚጨናነቁበት፣ በሚያዝኑበት... ጊዜ)?
✓ ምን ዓይነት የአየር ሁኔታ ባለበት ወቅት (በብርድ፣ በሙቀት...ጊዜ)?
✓ ከሥራ እረፍት በሚሆኑበት ወይንስ ሥራ ላይ ባሉበት ሰዓት?  ወዘተ...

- እያመጣ ያለውን ክፉ ተጽዕኖ አምነው ይቀበላሉ? ስለጉዳዩ ግልጽ ጥያቄ ቢቀርብላቸው ምን ይላሉ?
- ✓ በሕይወታቸው
- ✓ በትዳራቸው
- ✓ በቤተሰባቸው
- ✓ በማሕበራዊ ግንኙነታቸው...
- ልምምዱን ለማቆም ሞክረው ያውቃሉ? ከሆነስ እንዴት? ለምን ያክል ጊዜ አቋርጠው ቆዩ? እንደገና እንዲቀጥሉ ያነሳሳቸውስ ምን ነበር?
- ከዚህ ሱስ ለመውጣት ምን ያክል ፈቃደኛ ናቸው? መውጣት የሚቻልበት ተስፋ አለ ብለው ያስባሉ?
- ስለእግዚአብሔር ረዳትነትና ሕይወታቸውን ሊለውጥ እንደሚችል ምን ያክል ያምናሉ?[50]

**2) መግለጥ፡- የሚፈጥርባቸውን ስሜት በመረዳት በተለያየ መንገድ አብሮነትን መግለጥ**

በፖርኖግራፊ ሱስ የተጠመዱ ሰዎች የሚፈጠርባቸውን እንግዳና መጥፎ ስሜት በመረዳት በተለያየ መንገድ አብሮነትን ለማሳየት ምን ዓይነት ሁኔታ ወደ ፖርኖግራፊ ስሜትና ልምምድ ውስጥ እንዲገቡ እንደሚያደርጋቸው ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነው:: ምን ዓይነት ሁኔታ ወደ ፖርኖግራፊ ስሜትና ልምምድ ውስጥ እንዲገቡ እንደሚያደርጋቸው ለመረዳት ደግሞ፡- ከሥራ ጋር የተያያዘ መሆን አለመሆኑን? በቀኑ ውስጥ በትኛው ሰዓት ላይ ፈተናው እንደሚበዛባቸው? በምን ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ሲሆኑ ማለትም፡ በሚጨናነቁበት ወቅት፣ በሚቆጡ ጊዜ፣ ጥልቅ ሃዘን ውስጥና ተስፋ መቁረጥ ውስጥ ሲሆኑ፣ ከትዳር ጓደኛቸው ጋር ግንኙነታቸው ሲበላሽ ወ.ዘ.ተ? የመሳሰሉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ መወያየት በጣም ጠቃሚ ነው:: በእነዚህ ጊዜያቶች ልንረዳቸው ፈቃደኛ መሆናችንን በግልጥ በማሳየት ተጋላጭነታቸውን ለመቀነስ በዓላማና በእቅድ አብሮ መሆን ተገቢ ነው። በፖርኖግራፊ ሱስ ልምምድ ውስጥ ያሉ ሰዎች ከሚሰሟቸውና ከሚፈጠሩባቸው የተለያዩ ጥልቅ ስሜቶች መካከል ከፍተኛ የሆነ የፍትዎት ፍላጎት፣ ከፍተኛ የሆነ ቁጣና ንዴት እንዲሁም የብቸኝነት ስሜት የመሳሰሉት ናቸው:: ልንረዳው የምንፈልገው ሰው መሠረታዊ የስሜት ችግር የትኛው እንደሆነ መገንዘብም ይህንን ስሜት በሌላ ስሜት መቀየር የሚቻልበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው።

በፖርኖግራፊ ሱስ ልምምድ ውስጥ ያሉ ሰዎችን መርዳት የሚወስደው ጊዜ ቀላል አይደለም። ከሱስ ነፃ የመውጣት ሂደት የእርዳታ ፈላጊውን ፈቃደኝነት መሠረት

[50] sexuality and relationship counseling p 159





በማድረግ የሌሎች የታመኑ ሰዎች እርዳታ የግድ ያስፈልገዋል:: ስለዚህ እርዳታ መስጠት የሚችሉ ሰዎችን በመጠየቅና በመተጋገዝ አስፈላጊውን እርዳታ ለመስጠት፣ የሚፈጠሩ የተለያዩ መጥፎ ስሜቶችን ለመቀነስ፣ የታመኑ ወዳጆችን (ጓደኞችን) በመጋበዝ በጸሎት፣ በምክርና አብሮነትን በመግለጽ ማገዝ መንፈሳዊነትና ክርስቲያናዊ ኃላፊነታችን ነው:: ነገር ግን ይህን ስናደርግ ራሳችንን በመጠበቅና በጥንቃቄ መሆን አለበት/ገላ 6፡ 1-2/።

**3) መምራት፡- ትክክለኛና ሙያዊ ድጋፍ ሊሰጡ ወደሚችሉ ክርስቲያን አማካሪዎች መምራት**

እንደ ትዳር ጓደኛነታችሁና ክርስቲያንነታችሁ በፖርኖግራፊ ሱስ ውስጥ ለወደቁ የትዳር አጋሮች ወይም ወዳጆች አቅማችሁና እውቀታችሁ የሚፈቅድላችሁን ያህል ድጋፍና እርዳታ ካበረከታችሁ በኋላ የሰጣችሁት ድጋፍ በቂና ለውጥ አምጭ መስሎ ካልታያችሁ ሌሎች አማራጮችን ስለማቅረብ ማሰብ አለባችሁ:: የእኛን ጥረቶች ማድረጋችን እንደተጠበቀ ሆኖ የችግሩ ሰለባ የሆኑ ወገኖቻችን ከሌሎች በመንፈሳዊ ሕይወትና በማማከር አገልግሎት ባለሙያ ከሆኑ ሰዎች ድጋፍ ማግኘት ያለባቸው መሆኑን በማስረዳት ማሳመንና ሊረዷቸው ወደሚችሉ ሰዎች መምራት አለብን::

የተሻለ ድጋፍ የሚሰጡ ሰዎች የሚባሉት በሳልና የታመኑ ክርስቲያን ወንድሞችና እህቶች ሆነው በተለይ በማማከር አገልግሎት በሚገባ የሰለጠኑ ፕሮፌሽናል አማካሪዎች ቢሆኑ ይመረጣል:: የሰለጠኑ ክርስቲያን የማማከር አገልግሎት ባለሙያዎች የሌሉ ከሆነ ደግሞ ችግር ውስጥ ያለው ሰው ድጋፍ እንዲያገኝ ወደ ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች፣ መሪዎች፣ ክርስቲያናዊ ድረጅቶችና አገልግሎቶች መምራት አስፈላጊ ነው:: እነዚህ አገልጋዮችና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ደግሞ መንፈሳዊ አቅጣጫ በማሳየት፣ አመለካከቱን በእግዚአብሔር ቃል መርህ በማስተካከልና በመቅረጽ የሞራልን ከቡርነት እንዲረዳ እያገዙት ቀጣይነት ባለው ክትትል እርዳታ ሊያደርጉለትና ትክክለኛ እርዳታ በመስጠት ወደ ትክክለኛው መንገድ ሊመሩት እንዲሁም ሊያበረታቱት ይገባል።

## ለጥንዶች በግላቸውና በቡድን ለማጥናት የሚረዷቸው የውይይት ጥያቄዎች

## የምዕራፍ አስራ ሁለት (12)

## የውይይት ጥያቄዎች

1. ፖርኖግራፊ የሚለውን ቃልና ሃሳብ ምንነት በመግለጥ ተወያዩበት።
2. የፖርኖግራፊ ተጠቃሚ የሆኑ ሰዎች ያሏቸው የተለያዩ አመለካከቶች ምንድን ናቸው? እናንተስ እንዴት ታዩታላቹህ?
3. መጽሐፍ ቅዱስ ስለፖርኖግራፊ ምን እንደሚል በመጽሐፉ የተጠቀሱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን በማውጣትና በማንበብ በሰፊው ተነጋገሩበት።
4. በዚህ ዘመን ባለትዳሮችን አስከፊ ለሆነው የፍትዎት ሱስ (ለፖርኖግራፊ) ተጋላጭ ሊያደርጋቸው የሚችለውን ምክንያት በመዘርዘር በፍጹም ግልጥነት ውይይት አድርጉ።
5. ለፖርኖግራፊ እይታ ተጋላጭ ሁናቹህ ታውቃላቹህን? እንዴት? ከዚያስ ምን እርምጃ ወሰዳችሁ?
6. በፖርኖግራፊ ሱስ የተጠመዱ ባለትዳሮች ላይ ሊፈጠር የሚችል አስከፊ የሆነ አሉታዊ ተጽዕኖና ግጭት ምን እንደሆነ በዝርዝርና በግለጥ ተወያዩ።
7. በፖርኖግራፊ ሱስ የተጠመደ የትዳር አጋር ምን የመፍትሔ እርምጃ ሊወስድ ይገባል? አንድ የትዳር ጓደኛ በዚህ ሱስ የተያዘውን አጋሩን ሊረዳ የሚችልባቸው የመፍትሔ እርምጃዎችን በጥንቃቄ፣ በስፋትና በነፃነት በማንሳት ውይይት አድርጉ።
8. ወደ ፊት አስከፊ ለሆነው የፖርኖግራፊ ሱስ ተጋላጭ ላለመሆን እንደ ባለትዳር ምን ማድረግ አለብን ትላላችሁ?





# ክፍል ሶስት፡- ቅድመ ወሊድ፣ ወሊድና ድህረ ወሊድ

## ለጥንዶች በግላቸውና በቡድን ለማጥናት የሚረዷቸው የውይይት ጥያቄዎች

## የምዕራፍ አስራ ሁለት (12)

## የውይይት ጥያቄዎች

1. ፖርኖግራፊ የሚለውን ቃልና ሃሳብ ምንነት በመግለጥ ተወያዩበት::
2. የፖርኖግራፊ ተጠቃሚ የሆኑ ሰዎች ያሏቸው የተለያዩ አመለካከቶች ምንድን ናቸው? እናንተስ እንዴት ታዩታላቹህ?
3. መጽሐፍ ቅዱስ ስለፖርኖግራፊ ምን እንደሚል በመጽሐፉ የተጠቀሱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን በማውጣትና በማንበብ በሰፊው ተነጋገሩበት::
4. በዚህ ዘመን ባለትዳሮችን እስከፊ ለሆነው የፍትዎት ሱስ (ለፖርኖግራፊ) ተጋላጭ ሊያደርጋቸው የሚችለውን ምክንያት በመዘርዘር በፍጹም ግልጥነት ውይይት አድርጉ::
5. ለፖርኖግራፊ እይታ ተጋላጭ ሁናቹህ ታውቃላቹሀን? እንዴት? ከዚያስ ምን እርምጃ ወሰዳችሁ?
6. በፖርኖግራፊ ሱስ የተጠመዱ ባለትዳሮች ላይ ሊፈጠር የሚችል አስከፊ የሆነ አሉታዊ ተጽዕኖና ግጭት ምን እንደሆነ በዝርዝርና በግለጥ ተወያዩ::
7. በፖርኖግራፊ ሱስ የተጠመደ የትዳር አጋር ምን የመፍትሔ እርምጃ ሊወስድ ይገባል? አንድ የትዳር ጓደኛ በዚህ ሱስ የተያዘውን አጋሩን ሊረዳ የሚችልባቸው የመፍትሔ እርምጃዎችን በጥንቃቄ፣ በሰፋትና በነፃነት በማንሳት ውይይት አድርጉ።
8. ወደ ፊት አስከፊ ለሆነው የፖርኖግራፊ ሱስ ተጋላጭ ላለመሆን እንደ ባለትዳር ምን ማድረግ አለብን ትላላችሁ?





# ክፍል ሶስት፡- ቅድመ ወሊድ፣ ወሊድና ድህረ ወሊድ

# ምዕራፍ አስራ ሶስት( 13)
# መውለድ አለመፈለግና አለመቻል

ይህ ምዕራፍ የሚያጠነጥነው ያለመውለድ ሂደቶች ላይ ነው:: ያለመውለድ ክስተት በሁለት የተለያዩ ምክንያቶች ሊያጋጥም ይችላል:: በጥንዶቹ ፍላጎት ወይንም ጥንዶቹ መውለድ እየፈለጉ መውለድ የአለመቻል ችግር ሲያጋጥማቸው:: በጥንዶች ፍላጎት የሚመጣው ያለመውለድ ሂደት ጥንዶቹ በተለያዩ ምክንያቶች ለጊዜውም ይሁን ለዘለቄታው ወውለድ ካለመፈልጋቸው ጋር ተያያዥነት አለው:: ሌላው ገጽታ ደግሞ ጥንዶቹ ልጅ እንዲኖራቸው እየፈለጉ፣ እየጸለዩ፣ የሚቻለውን ሁሉ እያደረጉ ነገር ግን መውለድ የማይችሉ የሚሆኑበት ክስተት ነው። እነዚህን ሁለት ያለመውለድ ጥንች ባለትዳሮች በስምምነት፣ በመነጋገርና በመግባባት ተገንዝበው ነገሮችን መቆጣጠር ካልቻሉ በግንኙነታቸው ላይ የሚፈጥረው አሉታዊ ተጽዕኖ ቀላል አይሆንም። ይህ ርዕሰ ጉዳይ የተነሳው በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ በማለፍ የትዳራቸው ጤንነትና ደስታ ችግር ውስጥ ለወደቀባቸውና ችግር ውስጥ ለሚወድቅባቸው ጥንዶች ችግሮችን በመለየት ቢቻል ግጭት ውስጥ ከመግባታቸው በፊት አስቀድሞ መከላከል ካልተቻለ ደግሞ ከችግሩ ለመውጣት በጋራ መፍትሔ ማፈላለግ እንዲችሉ ለመርዳት እንዲሁም በማማከር ሊያግዟቸው ለሚችሉ ሰዎች አቅጣጫ ለማሳየትና የማማከር አገልግሎታቸውን ውጤታማ የማድረግ በጎ አስተዋጽዖ ለማበርከት ታስቦ ነው።

## 1. መውሊድ አለመፈለግና አለመቻል

ስለወሊድ ጉዳይ ሲነሳ ሁለት አይነት ጥንዶች እንዳሉ መገንዘብ ይገባናል። መገንዘብ ያለብን የመጀመሪያው ጉዳይ በተለያዩ የግል ምክንያቶች ለጊዜውም ሆነ ለዘለቄታው መውለድ የማይፈልጉ ጥንዶች መኖራቸውን ነው። እንደዚህ ዓይነት ጥንዶችን በየአደባባዩ ለምን አትወልዱም ወይም አትደግሙም የሚሉትን የተለያዩ አስተያየቶች በመሰንዘር ከማሸማቀቅ ይልቅ ጊዜ ሰጥቶ ማውራትና ማማከር የተሳሳቱ ምክንያቶች ካሏቸው እንዲታረሙ ይረዳቸዋል:: ብሎም እንደ እግዚአብሔር ቃል በማበረታታት ምክንያታቸው ጤነኛ፣ አጥጋቢና የጋራ ውሳኔያቸው ከሆነ ለጥንዶቹ አሳብና ውሳኔ ሁኔታውን መተው አስፈላጊ ነው።

ሌሎች ደግሞ ልጅ መውለድ ፈልገው በተለያዩ ምክኒያቶች መውለድ የማይችሉ ጥንዶች ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ የዚህ ዓይነት ችግር ያጋጠማቸውን ባለትዳሮች ታሪክና ያጋጠሟቸውን ልዩ ልዩ ውጣ ውረዶች በመዘገብ ለጉዳዩ ትኩረት መስጠቱትን ግልጥ አድርጓል:: በዚህ ዓይነት ችግር ውስጥ ካለፉና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ታሪካቸው ከተዘገበላቸው ባለትዳሮች መካከል ሐና እና ህልቃና የሚጠቀሱ ናቸው:: ሐና ልጅ ለመውለድ ከፍተኛ ጉጉት ነበራት:: ነገር ግን ልጅ ወልዶ የመሳሙ ጉዳይ የነበራትን ምኞት ያህል በቀላሉ የሚሳካላት አልሆነም:: ሐና ልጅ ለመወለድ የነበራት ከፍተኛ ጉጉት አልሳካ ማለቱ ልቧ እስኪሰበር ጥልቅ ሐዘን ውስጥ እንድትወድቅ፣ ምግብ





በመብላትም ሆነ በሌሎች ማሕበራዊ ደስታዎች እንዳትደስትና የመደሰትም ፍላጎት እንዲጠፋባት አድርጓታል:: እንዲሁም ጣውንቷ ፍናና እና ልዩ ልዩ ሁኔታዎች ተባብረው ባደረጉባት ጫና ለቁጣና ለብስጨት ስትዳረግ ተስተውሏል /1ኛሳሙ 1፡ 11፤ 15-16፤ 8፡ 1-22/::

## 1. መውሊድ አለመፈለግ

አንዳንድ ባለትዳሮች በተለያዩ ምክንያቶች ለጊዜውም ሆነ ለዘለቄታው መውለድ የማይፈልጉ ናቸው። እንደነዚህ ዓይነቶቹ ጥንዶች በጋራ ወይም በአንደኛው አካል ፈቃደኛ አለመሆን ምክንያት ልጅ ለመወለድ የማይፈልጉ እንጅ መውለድ የማይችሉ አይደሉም። መውለድ ባለመፈለግና ባለመቻል መካከል ልዩነት አለና! በዚህ ክፍል ውስጥ በዋናነት ትኩረት ማድረግ የምፈልገው መውለድ እየቻሉ በራሳቸው ምክንያት መውለድ የማይፈልጉ ጥንዶች ላይ ነው።

አንዳንድ ጊዜ ከዕቅድ አንጻር ልጅ ለመውለድ ባለመፈለግ ለተወሰኑ ዓመታት አብዛኛውን ጊዜ ሁለቱ ጥንዶች በመስማማት ወይም አንደኛው የትዳር አጋር ባለመስማማቱ ለጊዜው በተለያየ መንገድ እርግዝናን በመከላከል ጥንዶቹ ልጅ ሳይወልዱ ለመቆየት ጥረት ሲያደርጉ ይታያሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ በጥንዶች በራሳቸው የግል ምክንያት በጋራ ስምምነት ለዘለቄታው ላለመውለድ እርግዝናን በመከላከል ያለመውለድ ፍላጎታቸውን ሲያንጸባርቁ ይደመጣሉ።

ልጅ ለመውለድ አለመፈለግም ሆነ መፈለግ፣ ማግኘትም ሆነ ማጣት፣ መውለድም ሆነ አለመውለድ በባለትዳሮች መካከል ሊፈጠር የሚችል የፍላጎት መለያየት ወይም ተፈጥሮአዊ ክስተት ነው። እነዚህ ነገሮች በሰው ሕይወት የሚፈራረቁ መሆናቸውን በተግባር የሚታየው የአንዳንድ ጥንዶች ገጠመኝም ሆነ የእግዚአብሔር ቃል በተለያየ ቦታ ያረጋግጥልናል። *"አትታበዩ፥ በኩራትም አትናገሩ እግዚአብሔር አዋቂ ነውና፥ እግዚአብሔርም ሥራውን የሚመዝን ነውና፥ ከአፋችሁ የኩራት ነገር አይውጣ። የኃያላንን ቀስት ሰብሮአል፥ ደካሞችንም በኃይል ታጥቀዋል። ጠግበው የነበሩ እንጀራ አጡ ተርበው የነበሩ ከራብ ዐርፈዋል መካኒቱ ሰባት ወልዳለችና፥ ብዙም የወለደችው ደከማለች። እግዚአብሔር ይገድላል ያድናልም ወደ ሲኦል ያወርዳል፥ ያወጣል።እግዚአብሔር ድሀ ያደርጋል፥ ባለጠጋም ያደርጋል ያዋርዳል፥ ደግሞም ከፍ ከፍ ያደርጋል።"* /1ኛሳሙ 2፡ 3-7/

## 2. መውሊድ አለመቻል /መካንነት/

ይህ ችግር ሲከሰት አብሮ በቋሚነት መታሰብ ያለበት ችግሩ በባለትዳሮች ሕይወትና ሕብረት ላይ የሚያስከትለው አሉታዊ ተጽዕኖ ነው:: ብዙዎች ባለትዳሮች ልጅ ባለመውለዳቸው ምክንያት ከግል ሕይወታቸውና ከትዳራቸው ደስታ ሲጠፋ ይታያል። ይህን እውነታ ታሪካቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ከተዘገበላቸውና በችግሩ ውስጥ ካለፉ የተለያዩ ባለትዳሮች ሕይወት መቃኘት ይቻላል። በሣራና በአብርሃም ቤት ልጅ መውለድ ባለመቻል ምክንያት በአብርሃም ዘንድ ባሪያዪ ኤልዔዘር ይወርሰኛል የሚል ስጋት ተፈጥሮ ነበር:: የአብርሃም ሚስት ሣራም ለአብርሃም *"... እነሆ፥ እንዳልወልድ*

*እግዚአብሔር ዘጋኝ ምናልባት ከአርሰዋ በልጅ ኢታነጽ እንደ ሆነ ወደ አርሰዋ ግባ አለችው።"* /ዘፍ 16: 2/ የሚል ማበረታቻ በመስጠት ያጋጠማቸውን የልጅ ማጣት ችግር በራሳቸው መንገድ መፍታት የሞከሩበትን አሳብ አቀረበች፡፡

ብዙዎች ባለትዳሮች ልጅ መውለድ ያለመቻል ችግር ሲያጋጠማቸው ከሚያልፉበት የስሜት ስብራት፣ የስነ ልቦናና ማሕበራዊ ቀውሶች የተነሳ እንደነአብርሃም ቤተሰብ የራሳቸውን መፍትሔ በማሰብ ችግራቸውን ለመፍታት ጥረት ያደርጋሉ፡፡ ያደረጉት ጥረት አልሳካ ሲል ከቀድሞው ወደ ከፋ ሌላ ቀውስ ይሻገራሉ፡፡ እነዚህን የመሳሰሉ ችግሮቻቸው የሚፈጥሩባቸው ስሜቶችም ሰላማቸውና ደስታቸው እንዲጠፋና በምትኩ ፍርሃት፣ ተስፋ መቁረጥና ሐዘንተኛነት ያጋጥማቸዋል፡፡ በመካከላቸውም አለመግባባትና ግጭት እንዲፈጠር ከፍተኛ ዕድል ይሰጣሉ። በያዕቆብና በራሔል ቤት የተፈጠረው ተመሳሳይ ገጠመኝም ራሔል በልጅ አልባነት ሞትን እስከትለምን ያደርሳት ችግር እንደ ነበር ማስተዋል ይቻላል። ሞትን የመፈለግ ሃሳብ እንዲሁ በአንዴ በድንገት የሚመጣ አሳብ አይደለም! ሰው ሁሉ ለመኖር ይፈልጋልና! በዚች ሴት የተፈራረቁባት እንግዳ ስሜቶች ማለትም ቅንዓት፣ መደበት፣ ተስፋ መቁረጥ፣ ምንም ነገር የማያስደስታትና ከእህቷ ጋር ብርቱ ትግል የነበረባት ሴት መሆኗ መኖርን እንድትጠላና ሞትን እንድትፈልግ አድርጓታል ማለት ይቻላል /ዘፍ 30: 1-15/።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ታሪካቸው በተዘገበላቸው የእምነት አባቶች ትዳር መካን በመሆን ምክንያት መውለድ አለመቻል በተፈጠረ ጊዜ ለከስተቱ የተለያየ ሃይማኖታዊ ምክንያት መስጠት የተለመደ ነበር፡፡ በተለይ የብሉይ ኪዳን ቅዱሳት መጽሐፍት እንደዘገቡት በጥንቱ ማሕበረሰብ ዘንድ መውለድ ያልቻለች ሚስት መርገም ያለባት እንደሆነች ይታሰብ እንደነበር ከራሄልና ከሃና ታሪክ መረዳት እንችላለን /ዘፍጥ 29፤ 1ሳሙ 1/፡፡ ይህ ዓይነቱ አመለካከት በተለያየ መልክ በልማዳዊ አመለካከት በተቀረጸው ኢትዮጵያዊ ማሕበረሰብ ዘንድም የተለመደ መሆኑን በዚህ ማሕበረሰብ መካከል ተወልደው ያደጉ ወይም የኖሩ ሰዎች ሁሉ የሚያውቁት ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ ባህላዊ አስተሳሰብ ባሳደረባቸው አሉታዊ ተጽዕኖ ምክንያት መካንነት ያጋጠማቸው ጥንዶች መርገም አለብን የሚል አሳብ በልባቸው ሲሞላባቸውና በእግዚአብሔርም ፊት "ለምን በእኛ ብቻ ይህ ነገር ተከሰተ?" የሚልና ተመሳሳይነት ያላቸውን ጥያቄዎች በመጠየቅ ስሜታዊ ሆነው በእግዚአብሔር ፊት ሲያጉረምርሙና ሲያማርሩ ይታያሉ። ከዚያም ይህ ስሜት ወደ ሐዘን ተለውጦ ልባቸው በሐዘን እንዲመታና ደስታ እንዲርቃቸው በር ይከፍታል። ይህን ደስታ የራቀውን ትዳራቸውን በተደጋጋሚ "አትወልዱም እንዴ? ውለዱ እንጂ! ..." የሚሉና ከመውለድ ጋር ተያይዘው የሚነሱ ቤተሰቦች፣ ወዳጆች፣ የቤተ ክርስቲያን አባላት ... የሚያዘወትሯቸው ጥያቄዎችና አስተያየቶች ግፊት ወደባሰ ቀውስ እንዲገባ ተጽዕኖ ያሳድሩበታል፡፡

ለመውለድ ያላቸው ብርቱ ፍላጎትና ጥያቄ ካለመመለሱ የተነሳ በውስጣችው የሚፈጠረው የተጎዳ ስሜት ልጆች በሚበዙበት ቦታና በልዩ ልዩ ስብሰባዎች ላይ





የመገኘት ተነሳሽነታቸውን ያጠፋባቸዋል፡፡ ስለወለዱ ሰዎች የምስራች መስማት፣ የወለዱ ወዳጆችን መጠየቅ፣ የልጆች የልደት ጥሪ ተካፋይ መሆንና የእናቶችና የአባቶች ቀን ማክበር ሊያሳቅቃቸውና ልባቸውን የማይጠብቁ ከሆነ የሌሎች ሰዎች የደስታ ቀን ለእነርሱ የሐዘን ቀን ሆኖ እንዲያልፍ ሊጋበዙ ይችላሉ። ይህን የሐዘን ስሜት ለማጥፋትና ጠንካራ ስሜት እንዲኖራቸው ለመርዳት የሚያበረታቱአቸውን፣ በተለያየ ስጦታ ለመደገፍ የሚጥሩ ቤተሰቦቻቸውንና ወዳጆቻቸውን የማጽናናት ቃል ሰምተው መጽናናትም ሊከብዳቸው ይችላል።

መውለድ አለመቻላቸውን ሲያረጋግጡ የበደለኝነትና ያለመብቃት ስሜት ሊፈራረቅባቸው ይችላል። ልጅ እየፈለጉ መውለድ በማይችሉ ጥንዶች በተለይም በሚስቶች (በሴቶች) ዘንድ በቀላሉ ያለመጽናናትና በሌሎች ነገሮች ያለመደሰት ይከሰታል፡፡ በመንፈሳዊ ሕይወታቸውም ከእግዚአብሔር ጋርና ከትዳር ጓደኛቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት ሊበላሽባቸው ይችላል። በቤተሰብ፣ በወዳጆችና በቤተ ክርስቲያን ኅብረት ነፃነት እንዳይሰማቸው ሊያደርጋቸው ብሎም ከኅብረት ሊያርቃቸው ስለሚችል ጥንቃቄ ማድረጉ ተገቢ ነው። ስለዚህ መውለድ ባለመቻል ችግር ውስጥ ያሉ ባለትዳሮች ችግሩ ሊያመጣ ያለውን አሉታዊ ተጽዕኖ በመረዳት ተጽዕኖውን ማሸነፍ እንዲቻልና የትዳር ግንኙነታቸውን በመጠበቅ ጤነኛና ደስተኛ ትዳር እንዲኖራቸው መፍትሔ ማፈላለግ አለባቸው፡፡

## II. ባለመውለድ ምክንያት ሊፈጠሩ ለሚችሉ ግጭቶች መፍትሔዎች

### 1. መነጋገር፡- ጥያቄውን በጋራ ማንሳትና መነጋገር

ልጅ አልባ መሆን ማለትም መውለድ አለመቻል ምክኒያቱ የተለያየ ነው። እንደ ምክንያቶቹ ልዩ ልዩነት መፍትሔዎቹም የተለያዩ ናቸው። በትዳር የተጣመርን ጥንዶች በጋራ ይህን ርዕሰ ጉዳይ በአግባቡ አንስተን በመነጋገርና አቅጣጫ በማስቀመጥ የትዳር ግንኙነታችን ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳያሳድርብን የራሳችንን የአእምሮ፣ የስሜትና የስነ ልቦና ዝግጅት በማድረግ ሰላማችንን፣ አንድነታችንን በአጠቃላይም ትዳራችንን ለመጠበቅ መንቃት አለብን፡፡ የጋራ ንግግራችንን ነፃነት ባለለበትና ስሜትን እንደሚገባ ገላጭ በሆነ መንገድ ለማድረግ መፍቀድ፣ መዘጋጀትና በጋራ በስምምነት አስፈላጊውን እርምጃ ሁሉ ለመውሰድ መነሳሳት ተገቢ ነው።

ብዙ ጊዜ በባህላችን ልጅ መውለድ አለመቻል የሚስቶች (የሴቶች) ብቻ ችግር እንደሆነ አድርጎ መውሰድ የተለመደ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት መሸማቀቁ፣ ፍርድን መሸከሙ፣ የወቀሳውና ጣት የመጠቆሙ ሰለባዎች እነርሱ ብቻ ይሆናሉ። ማሕበረሰቡ የሚያሳድርባቸው አድሏዊና አሉታዊ ተጽዕኖ ከፉኛ ስለሚጎዳቸው ከባሎች ይልቅ ሚስቶች ልጅ ሳይወልዱ የመኖሩን እውነታ በመቀበል መኖር የመቻሉን ሐቅ መቀበል እጅግ ይከብዳቸዋል፡፡ ይህን ችግር ለመቀነስ ልጅ መውለድ ያለመቻል ምክንያት በወንዶችም ሆነ በሴቶች እኩል 50% እንደሆነ ሊታወቅ ይገባዋል። ሰናይት ፍስሐ

(ዶ/ር) "የመካንነት ችግር በወንዶች **40%** በሴቶችም እንዲሁ **40%** ሲሆን **20%** ደግሞ ምክንያቱ ያልታወቀ እንደሆነ" ጥናቶችን በመጥቀስ ትናገራለች::[51] ይህንን በመረዳት ከትዳር አጋሮቻው ጋር በጋራ መነጋገር ልጅ መውለድ ባለመቻላቸው ምክንያት ትዳራቸው እንዳይፈርስ ደግሞም የቤታቸው ሰላም እንዳይደፈርስ ለመጠበቅ ያግዛቸዋል:: እንዲህ ዓይነቱ ጥረት ሁለቱም ጥንዶች ቁርጠኛ አቋም መያዝ እንዲችሉና ሌሎች አማራጭ የመፍትሔ አሳቦችን እንዲያፈላልጉ አስተዋፅዖው ሰፊ ነው።

## 2. መተሳሰብ፡- ልጅም ባይኖር ተዋደንና ተሳስበን በቃል-ኪዳን መኖር

ለጊዜውም ሆነ ለዘለቄታው ልጅ የሌላቸው ባለትዳሮች ሊገነዘቡት የሚገባ ወሳኝ ጉዳይ ክርስቲያናዊ ጋብቻ በጌታ የሆኑ አንድ ወንድና አንዲት ሴት እውነተኛ በሆነ ፍቅር ተፈላልገው የሚመሠርቱት እና የሚገቡት ለዕድሜ ልክ የሚጸና የቃል ኪዳን ጥምረት ነው። በቅርብ በተጋቡ ባለትዳሮች ዘንድ መውለድ አለመቻል ለአለመግባባትና ለግጭት ምክንያት የሚሆነው ወደ ጋብቻ የገባንበት ዋና ዓላማ ልጅ መውለድ ሲሆንና ልጅ ለመውለድም ካለን ብርቱ ፍላጎት የተነሳ ነው። በጽድቅ መንገድ ልጅን የምናገኝበት መንገድ በጋብቻ ውስጥ ባለው መኝታው ንጹህ በሆነ የግብረ ስጋ ግንኙነት መሆኑ አጠያያቂ አይደለም። ልጅ የመውለድ ፍላጎትን ብቻ ምክንያት አድርጎ ወደ ጋብቻ ቃል ኪዳናዊ ትሥሥር መግባት ለትዳር እንቅፋት ይፈጥራል።

ልጅ መውለድ በዘገየና መውለድ ባልተቻለ ወቅት አለመግባባትና ግጭት ብሎም መለያየት ያስከትላል። በእንደዚህ ዓይነት ችግር ውስጥ ካለፍን በኋላ ደግሞ እግዚአብሔር ፈቅዶ ልጅን በሚሰጥበት ወቅት ልጆች በትዳር መካከል የሚገቡ የባልና የሚስትን ግንኙነት የሚረብሹ የግጭት ምክንያቶች እንዳይሆኑ ቅድመ ጥንቃቄ ማድረግ እርስ በእርስ ተሳስቦ ለመኖር በጣም ጠቃሚ ነው። ቀድመን ስለችግሩ አስበን ካልተዘጋጀን እንደ ሐና *"እግዚአብሔርም የለመንሁትን ልመናዬን ሰጥቶኛል እኔም ደግሞ ለእግዚአብሔር ሰጥቼዋለሁ ዕድሜውን ሁሉ ለእግዚአብሔር የተሰጠ ይሆናል። "* /1ኛሳሙ 1፡ 28/ የሚል አቋም በመያዝ ተግባራዊ ለማድረግ ይከብደናል። ከብዙ ሐዘንና የልብ ስብራት በኋላ ያገኘናቸው ልጆቻችን ሁሉ ነገሮቻችን በመሆን ከእግዚአብሔርም ከትዳር አጋሮቻችንም ጋር ሊያራርቁን ይችላሉ። ስለዚህ የትዳር አጋርንና የልጆችን ፍቅር ለይቶ ካለማወቅና ሚዛናዊ ካልሆነ አያያዝ ችግር የተነሳ ልጆች ፍቅራችንን ጠቅልለው የሚወስዱ ሊሆኑ ይችላሉ። ይህ ችግር የማማከር አገልግሎት በምንሰጥበት ጊዜ በተደጋጋሚ ያየሁት የባለትዳሮች ችግር ነው:: ልጆቻቸው የጋራ ሆነው ሳለ *"በልጄ አትምጣ!"፣ "ከልጄ ጋር እንኳን አትወዳደርም!"፣ "በልጄ ከምትመጣ አንተ/አንቺ/ ጥንቅር ብለህ /ብለሽ/ መቅረት ትችላለህ/ያለሽ/!"* ... የሚሉ የአንዱን የትዳር አጋር ልብ

---

[51] Senait Fisseha MD, Associate Professor, Obstetrics & Gynecology Helen Show June, 28. 2013





የሚጎዳ፣ ግጭትንና መለያየትን የሚያነሳሳ አስተሳሰብ፣ ንግግርና ድርጊት እንዲገለጥ ይጋብዛል።

## 3. መተማመን፡- ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታዎች መሆናቸውን ማመን

*"እነሆ፥ ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ ናቸው፥ የሆድም ፍሬ የእርሱ ዋጋ ነው።"* /መዝ 127፡ 3/ የሚለው የእግዚአብሔር ቃል እንደሚናገረው ልጅን የሚሰጥ እግዚአብሔር እንጂ ማንም አይደለም። ቃሉን እያወቅንና እየጠቀስን የምንረሳውና የምንሳሳትበት ነገር ቢኖር ልጅን የሚሰጥ እግዚአብሔር እንጂ ማንም ያይደለ መሆኑን ነው። ራሔል በልጅ ጉዳይ *"ራሔልም ለያዕቆብ ልጆችን እንዳልወለደች ባየች ጊዜ በእኅትዋ ቀናችባት ያቆብንም። ልጅ ስጠኝ ይህስ ካልሆነ እሞታለሁ ... ።"* /ዘፍ 30፡ 1/ ስትል ባሏን ያዕቆብን ጠየቀች:: ለዚህ ጥያቄዋም ያዕቆብ *"... በውኑ እኔ የሆድን ፍሬ በነሣሽ በእግዚአብሔር ቦታ ነኝን? ..."* /ቁ. 2/ የሚል በሳልነት የተሞላ መልስ ሰጣት:: በያዕቆብና በሚስቱ በራሔል መካከል የነበረው ልዩነት የልጅ ፍላጎት አለመኖር ሳይሆን ልጅ የሚሰጥ ማን ነው? የሚለው ጥያቄና ለዚህ ጥያቄ የሚሰጠው መልስ ላይ ነበር።

ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታዎች ናቸው የምንለው የሆድ ወይም የማህጸን ፍሬን መስጠት የእርሱ ዋጋ እንጂ የማንም ባለመሆኑ ነው!! በመጽሐፍ ቅዱስ ለተለያዩ ሰዎች እግዚአብሔር መካንነታቸውን ሲያስወግድና ልጅን ሲሰጥ ማንበባችን ቃሉን እንድናምን ያበረታታናል። እምነት ከመስማት፣ መስማትም ከእግዚአብሔር ቃል ነውና! ከቃሉ ምሳሌ የሚሆኑ ሰዎችን ማንሳት አስፈላጊ ነው! በብሉይ ኪዳን ስለ አብርሃምና ሣራ የሚናገረው የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ *"እግዚአብሔርም እንደ ተናገረው ሣራን አሰበ እግዚአብሔርም እንደ ተናገረው ለሣራ አደረገላት። ሣራም ፀነሰች፥ እግዚአብሔርም በተናገረው ወራት ለአብርሃም በእርጅናው ወንድ ልጅን ወለደችለት።"* /ዘፍ 21፡ 1-2/ በማለት ልጅን የሚሰጥ እግዚአብሔር መሆኑን ይመሰክራል:: የአዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጽሐፍትም እግዚአብሔር በካህኑ ዘካርያስና በኤልሳቤጥ ቤት የጸሎታቸው መልስ እንዴት ልጅ የመስጠት ተዓምራትን እንደሠራ *"መልአኩም እንዲህ አለው፡- ዘካርያስ ሆይ፥ ጸሎትህ ተሰምቶልሃልና አትፍራ ሚስትህ ኤልሳቤጥም ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች፥ ስሙንም ዮሐንስ ትለዋለህ። ደስታና ተድላም ይሆንልሃል፥ በመወለዱም ብዙዎች ደስ ይላቸዋል።"* /ሉቃ 1፡ 13-14/ የሚል ዘገባ በማቅረብ ከብሉይ ኪዳን ቅዱሳት መጽሐፍት ምስክርነት ጋር ተስማምተዋል:: ይህ የቅዱሳት መጽሐፍት ምስክርነት ግልጽ እንዳደረገው በእርጅና ወቅት ልጅን መስጠት የሚችል አምላክ አለን። ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና /ዘፍ 18፡ 14 ሉቃ 1፡ 37/!!

ሐና እንደዘመረችው በልጆች የተባረከ ትዳር ያለን ጥንዶች ከእኛ ማንነት የተነሳ ሳይሆን ከእርሱ ምህረትና መልካምነት የተነሳ እንደ ሆነ ገብቶን በትህትና ለእግዚአብሔር ምስጋናና ክብር እየሰጠን ከፈራጅነትና ከንቀት በጸዳ ንጹህ ልብ ልጅ መውለድ ላልቻሉ ጥንዶች እግዚአብሔር በእኛ ላይ ያገነነውን ምህረት በእነርሱም ላይ እንዲያደርግ ልንጸልይ ይገባል! *"አትታበዩ በኩራት አትናገሩ እግዚአብሔር አዋቂ ነውና...!"* /1ሳሙ 2፡ 3/ እግዚአብሔር የወደደውን ማድረግ የሚችል አምላክ ነውና! መካን የነበረችውን

በመምረጥ የምክር አገልግሎት ተጠቃሚ መሆን በእግዚአብሔር ቃል የጽድቅ መርህ የተሞላ አቅጣጫ ሊያሳየን የሚችል ድጋፍ በማስገኘት የምክር አገልግሎት ተጠቃሚ ያደርገናል።

## 6. መመርመር፡- ቢጋራ የሕክምና ባለሙያ በማነጋገር መርመር

እንደ ችግሮቻችን ዓይነት ተወያይተን ወደ አንድ ሃሳብ ከምንደርስባቸው አስፈላጊ ጉዳዮች አንዱ የሕክምና ባለሙያ ማነጋገር ወይም በሐኪም መታየት ነው። በብዙ የጤንነት ጉዳዮቻችን ሕክምና ለማግኘት እንደምናስበውና እርምጃ እንደምንወስደው ሁሉ መውለድ ባለመቻል ችግር ላይም ባለሙያ የሆኑ (ስፔሻላይዝድ ያደረጉ) ሐኪሞችን ለማግኘትና ለመታየት ጥረት ማድረግ አስፈላጊ ነው። በአገራችን በተለምዶ ከሕክምና ጋር ተያይዘው ያሉብን ስጋቶች ወደ ሐኪም እንዳንሄድ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድሩብናል፡፡ ተመርምረን ሌሎች በሽታዎች አሉባችሁ የሚል መጥፎ ዜና ከምርመራው ውጤት ላለመስማት መፈለግና ከዚህም ለማምለጥ ፈጽሞ ወደ ሕክምና መሄድን ማቆም የምንወስደው አማራጭ ይሆናል። ሌላው ችግር ከምርመራው ውጤት በኋላ እንደ ችግሮቻችን ዓይነት በሐኪም የሚታዘዙልንን መድሃኒቶች፣ አንዳንድ እንቅስቃሴዎችንና የምንከለከላቸውን ነገሮች በማሰብ ከሐኪም መሸሽ ነው፡፡ ተጽዕኖውን አሸንፈን ወደ ሐኪም ከሄድን እንኳን የሐኪምን ትዕዛዝ ከመተግበር ይልቅ ችላ በማለት መተላለፍ እንመርጣለን።

መውለድ ያለመቻል ችግር ያለባቸው ጥንዶች ተጽዕኖዎችን በማሸነፍ ወደ ሐኪም መሄድና የሐኪም ድጋፍ መፈለግ አለባቸው፡፡ ይህ ሂደት የችግሩን መሠረታዊ ምክንያት ለይቶ ለማወቅ በጣም ጠቃሚ ነው። ነገር ግን ችግሩ ያለባቸው ጥንዶች የሐኪም እርዳታ ፈልገው ወደ ሕክምና ተቋማት ከመሄዳቸው በፊት የስነ ልቦና ዝግጅት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ ወደ ሕክምና በመሄድ ተመርምረው ውጤቱን በሚረዱበት ወቅት በውስጣቸው የተለያዩ የፍርሃት፣ የስጋትና የተስፋ የመቁረጥ ስሜት ሊፈጠርባቸው እንደሚችል በመረዳት መንፈስ ጠንካራ መሆን ይጠበቅባቸዋል። ችግሩን ለይቶ ማወቅ ቀጣይ የተለያዩ እርምጃዎች ለመውሰድ ማለትም በእግዚአብሔር ፊት አጥብቆ ለመጸለይ፣ የሐኪም ክትትል ለመቀጠልና ሕክምና ለማግኘት ያስችላል፡፡ ስለዚህ ለዚህ ወሳኝ እርምጃ ራስን በማሳመን፣ ራስን በማዘጋጀትና ነገሮችን በመቀበል መረጋጋት አስፈላጊ ነው፡፡ ይህን በማድረግ የእርስ በርስ ግንኙነታችን እንዳይጎዳብን መጠንቀቅና ቀሪ ዘመናችንን በፍቅርና በደስታ ለመኖር የየበኩላችንን ድርሻ መወጣት ይገባናል።

## 7. መስማማት፡- የጉዲፈቻ ልጅ ለማሳደግ ቢጋራ መስማማት

የጉዲፈቻ ልጅ ማለት በተፈጥሮ እርግዝና ያልወለድናቸውን ሕጻናት በስምምነትና በሕግ ወንድና ሴት ልጆች አድርገን የመቀበል ሂደት ነው። የጉዲፈቻ ልጆች ሲታሰቡ የዕለት ምግብ፣ የመኖሪያ አቅርቦትና ማረፊያ ብቻ አዘጋጅቶ ከመስጠት ባለፈ እውነተኛ የወላጅ ፍቅርና እንክብካቤ መስጠትን የሚጠይቅ ኃላፊነት እንደ ሆነ መገንዘብ አስፈላጊ





ነው። በትዳራችን መካከል ያለን ችግር ይፈታል በማለት ብቻ ወደዚህ ሂደት መግባት የለብንም። ነገር ግን ሂደቱን ለጉዲፈቻ ልጆችም በረከት እንደ ሆነ በማሰብ ለእነርሱ መልካም ለማድረግ በሚፈልግ የፍቅር ልብ ማከናወን ተገቢ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ የታወቁ የእግዚአብሔር ሰዎች በተለያየ ምክንያት በጉዲፈቻ እንዳደጉ ይመሰክራል። ምንም እንኳን በአሁኑ ወቅት ያለው የጉዲፈቻ ስርዓትና በመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ የምንጠቅሳቸው ታሪኮች የየራሳቸው የተለያየ አውድ ቢኖራቸውም፡፡ ነገር ግን የተፈጠሮ ወላጆቻቸው ባልሆኑ አሳዳጊ ወላጆች እንክብካቤና ጥበቃ ያደጉና ለትልቅ ኃላፊነት የደረሱ ሰዎች ታሪክ በቅዱሳት መጽሐፍት ውስጥ መገኘቱ መጠቀስ ያለበት እውነት ነው፡፡ የእግዚአብሔር ሰው ሙሴ በፈርዖን ቤት የፈርዖን የልጅ ልጅ ሁኖ ያደገው የፈርዖን ልጅ በጉዲፈቻ ልጁ አድርጋ ስለተቀበለችው ነው፡፡ *"በዚያን ጊዜ ሙሴ ተወለደ በእግዚአብሔርም ፊት ያማረ ነበር፤ በአባቱ ቤትም ሦስት ወር አደገ፤ በተጣለም ጊዜ የፈርዖን ልጅ አነሣችው ልጅም ይሆናት ዘንድ አሳደገችው።"* /ሐዋ 7: 21/። መጽሐፍ ቅዱስ ለአይሁድ ምርኮኞች መፍትሔ የነበረችው አስቴር ወላጅ ስላልነበራት ለአጎቷ መርዶክዮስ እንደ ልጅ ሁና እንዳደገች ቃሉ እንዲህ ሲል ይገልጸዋል፡- *"አባትና እናትም አልነበራትምና የአጎቱ ልጅ ሀደሳ የተባለችውን አስቴርን አሳድጎ ነበር ቆንጆይቱም የተዋበችና መልከ መልካም ነበረች አባትዋና እናትዋም ከሞቱ በኋላ መርዶክዮስ እንደ ልጁ አድርጎ ወስዶአት ነበር።"* /አስቴር 2: 7/፡፡

ልጆችን ለጉዲፈቻ የሚዳርጓቸው የተለያዩ ምክንያቶች ቢኖሩም ጥቂቶቹ፡- ወላጆቻቸውን በኤች አይቪ ወይም በጦርነት ወይም በሌላ ምክንያት በሞት ተነጥቀው አሳዳጊ ማጣታቸው፣ ወላጆቻቸው የኢኮኖሚ አቅም አጥተው ከድህነት በታች የሚባል ኑሮ የሚኖሩ መሆናቸውና ልጆቻቸውን ማሳደግ የማይችሉበት ሁኔታ ላይ መገኘታቸው፣ ወላጆቻቸው በትክክለኛ መንገድ ከማሳደግ ይልቅ በተለያየ መንገድ ልጆቻቸውን ሊጎዱ የሚችሉ በመሆናቸው ሁኔታው ለልጆቹ ሁለንተናዊ ደህንነትና ሕይወት አስጊነቱ ሲረጋገጥና የወላጅነት ወይም የአሳዳጊነት መብታቸው በሕግ ሲገፈፍ እንዲሁም ወላጆች የአእምሮ ጤንኛነት የሌላቸው ሆነው ሲገኙና ሕጋዊ ውሳኔ ሲሰጥ ... ናቸው፡፡ በአጠቃላይ በእነዚህ ወይም ባልተጠቀሱ በሌሎች ምክንያት ሕጻናት በግልም ሆነ በድርጅት የጉዲፈቻ ልጆች ሆነው እንዲያድጉ ይገደዳሉ።

መውለድ ካልቻልንና ልጅ ያስፈልገናል ብለን የምናስብ ከሆነ የጉዲፍቻ ልጅ ማሳደግ ሌላው አማራጭ ሊሆን ይችላል። ጉዲፈቻ ማለት እንደ ልጅ አድርገን የምንቀበላቸው፣ የምንከባከባቸውና እንደ ወላጅ አስፈላጊ የሆነ ፍቅር በመስጠትና መሠረታዊ ፍላጎታቸውን በሚሟላት ልናሳድጋቸው የምንችላቸውን በስጋ ግን ያልወለድናቸውን ልጆች በወላጅነት በመቀበል ሁልጊዜም ልጆቻችን አድርገን መንከባከብና ፍላጎታቸውን ሁሉ አሟልቶ ማሳደግ መሆኑ በደንብ ገብቶን ኃላፊነቱን መወጣት የምንችልበት ቁራጥነት ከሌለን ስሜታዊ ሆነን በሩጫ የምንገባበት አይደለም።

ባንወልዳቸውም እንደ ወለድናቸው ልጆች የእናትነትና የአባትነት ኃላፊነትና ግዴታ እንዳለብን አጥብቆ መረዳት ያስፈልጋል።

እንደ ባለትዳር የጉዲፈቻ ልጅ ለማሳደግ ስናስብ ዝግጁ መሆናችንን ማረጋገጥ አለብን። ዝግጁ መሆናቻንን ከምናረጋግጥበት መንገድ አንዱ በመንፈሳዊ ረገድ ምን ያክል ዝግጁ እንደሆንን ራሳችንን መመዘን ነው። የራሳችንን መንፈሳዊ ሕይወትና አገልግሎት በመጠበቅ ለጉዲፈቻ ልጅ ክርስትናን ለማሳየትና በጋራ በመንፈሳዊ አቅጣጫ እንደ መንፈሳዊ ወላጅ እንደሚገባ በማስተዳደር ለማሳደግ መዘጋጀት ተገቢ ነው። የምንወስነው ውሳኔ ከባለትዳርነት ከሁለት በላይ የቤተሰብ አባላት ወዳሉት ቤተሰብነት የምንገባበት ነው። ይህንን ቤተሰብ በአግባቡ መንፈሳዊ ምግብ በመመገብ እንደ ኢያሱ እግዚአብሔርን ብቻ ወደማምለክ ቤተሰብነት የመምራት ትጋት፣ ታማኝነት፣ አቅምና ቆራጥነት ሊኖረን ይገባል፡፡ *"የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ። እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን።"* /ኢያሱ 24፡ 15/

ለጉዲፈቻ ኃላፊነት ዝግጁ መሆናችንን ከምናረጋግጥበት መንገድ ሁለተኛው ስነ-ልቦናዊ ዝግጅት ያለን መሆናችን ነው። በስነ ልቦና ማለትም በአእምሮና በስሜት ምን ያክል ዝግጁ ነን? ይህንን ጥያቄ በማንሳት በምንሰጠው መልስ ዝግጁነታችንን ማረጋገጥ አለብን፡፡ ዝግጅታችን ኃላፊነቱን ለመቀበል የሚያበቃን ካልሆነም ዝግጁ እስከንሆን ድረስ በትዕግስት እንድንጠባበቅ ውሳኔ ለመወሰን ይረዳናል። የስነ-ልቦና ዝግጁነት ከሌለን በኃላፊነት ከተረከብነው የጉዲፈቻ ልጃችን ጋር አብረን መሆን፣ መንከባከብ፣ መርዳት፣ ፍላጎቱን ማሟላትና ፍቅር ማሳየት አንችልም። ስነ-ልቦናዊ ዝግጅት ከሌለን አይደለም የጉዲፈቻ ልጅ የወለድናቸው ልጆችም ሳይቀሩ በግዴታ በላያችን ላይ የተጫኑብን ሸክሞች ሊሆኑብን ይችላሉ፡፡ ይህም ልጆችን ከእግዚአብሔር በመቀበላችን ራሳችንን በረከት እንደ እንደተቀበለ ሳይሆን የመርገም ፍርድ እንደ ተፈረደበት ሰው በመቁጠር ሁልጊዜ አማራሪዎችና በየምክንያቱ የምንቆጣ ሰዎች እንድንሆን ያደርገናል!!

ሌላው ምን ያክል በቂ የሆነ ፋይናንስና ወደ ፊትም ልጆችን ለማሳደግ የምንችልበት የገቢ ምንጭ እንዳለን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው። የጉዲፈቻ ልጅ ማሳደግ ብቻ ሳይሆን በጉዲፈቻ የምናሳድገው ልጅ ፈልጎ የማግኘቱ ሂደት የሚጠይቀው ወጭ ቀላል አይደለም። በተለይም ደግሞ ከአገር ውጭ ለሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ሕጋዊ ሂደቱን ለማስጨረስ የሚፈጀው ገንዘብ ከበድ ያለ ነውና አቅምን አገናዝቦ መዘጋጀት አስፈላጊ ነው።

ሌላው ልናስብበትና ልንዘጋጅበት የሚገባን ጉዳይ ቢኖር ልጆችን ለማሳደግ የምንችልበት በቂ የሆነ የመኖሪያ ስፍራ ማለትም የመኝታ፣ የመጫወቻና የማረፊያ ... ክፍሎች ያሉን መሆኑን ነው፡፡ አለበዚያም ወደ ሂደቱ በምንገባበት ወቅት ምቹ የሆነ መኖሪያ በመከራየት ወይም በመግዛት ልናስተካክል እንደምንችል አስቀድመን ልናስብና ልንዘጋጅ ይገባል። በተለይ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን በአገራችን እንደምንሆነው ማድረግ እንደማንችል መርሳት የለብንም! የጉዲፈቻ ልጅ ለማሳደግ የሕግ ሂደት





በምንጀምርበት ወቅት መንግሥትና የጉዲፈቻን ሕጋዊ ሂደት የሚያስፈጽሙ የግልም ሆነ የመንግሥት ድርጅቶች አቅማችንን ለማረጋገጥ እነዚህን ሁሉ አስፈላጊ መስፈርቶች ማሟላታችንን መጠየቃቸው አይቀሬ ነው።

በተጨማሪም ልናስብበትና ዝግጅት ማድረጋችንን ልናረጋግጥ የሚገባን ነገር ቢኖር በቂ ጊዜ ያለን መሆን አለመሆኑን ነው። የጉዲፈቻ ሂደቱ የሚጠይቀውን ጊዜ እና የጉዲፈቻን ልጅ ለማሳደግ የሚወስደውን ጊዜ ለመስጠት ዝግጁነት ሊኖረን ይገባል፡፡ የጉዲፈቻ ልጅ ማሳደግ የወለዱትን ልጅ ለማሳደግ ወላጅ የሆኑ ሰዎች ለልጆቻቸው የሚሰጡትን ጊዜ የሚተካከል ጊዜን ይጠይቃል ስለዚህ የወላጅነትን ኃላፊነት ለመወጣት አስቀድሞ ይህንን መረዳትና አቋም መያዝ ጠቃሚ ነው። ልጅን የማሳደግ ሂደት እንደ እናትና አባት ከልጅ ጋር መልካምና ጠንካራ የሆነ ግንኙነት ለመፍጠር በቂ ጊዜና ጊዜን በአግባብ መጠቀምን ይጠይቃል! ግንኙነትን ለማጠናከርና ለእነርሱ ያለንን ፍቅር ለመግለጥ አንዱ መንገድ የተመረጠ ጊዜ አብሮ ከልጆች ጋር ማሳለፍ ነው።

ሌላው ልናስብበትና ልንዘጋጅበት የሚገባን ጉዳይ ከእኛ ውጭ በተጨማሪ ሊረዱን የሚችሉ የቤተሰብ አባላት፣ ጓደኞችና ድርጅቶች መኖራቸውን ነው። በሂደቱ ያለፉ ልምድ፣ እውቀትና መረጃ ያላቸው የሚያማክሩን ሰዎች ያስፈልጉናል። ከዚያም በተጨማሪ በዚህ ጉዳይ ላይ በሚገባ ማሰባችን ጠቃሚ ነው የምንለው ልጆችን በማሳደግ ሂደት ውስጥ በእውቀታቸው፣ በጉልበታቸው፣ በጊዜያቸው፣ በሃሳባቸው፣ በልምዳቸው፣ በገንዘባቸውና በተለያዩ ነገሮች ሊረዱን የሚችሉ ሰዎች በዙሪያችን መኖራቸውን ለማረጋጋጥና ወደ ፊትም እንደሚያስፈልጉን በመረዳት ግንኙነት ለመፍጠር እንዲረዳን ነው።

በአጠቃላይ በዚህ ሂደት የመጀመሪያው ደረጃ እንደ ባልና ሚስት በጋራ የጉዲፈቻ ልጅ መቀበልና ማሳደግ እንፈልጋለን ወደ ሚል ስምምነት መድረስ ነው፡፡ በቀጣዩ ሂደት ደግሞ በጋራ በጥልቀት ልናስብባቸውና ልንነጋገርባቸው የሚገቡ ከጉዲፈቻ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ለይቶ በማንሳት መወያየት አስፈላጊ ነው፡፡ ለምሳሌ አንደኛው የመነጋገሪያ ጥያቄ፡- ለማሳደግ የምንፈልገው ልጅ ጾታ ወንድ ነው ወይስ ሴት? የሚል ሊሆን ይችላል፡፡ ይህን አሳብ በተመለከተ ስምምነት ላይ መድረስ አስፈላጊ ነው። ይህን የምናደርግበት ምክንያት እንደ እናትና አባት የግል የጾታ ምርጫ ስለሚኖረን፣ እንደ ጾታቸው የማሳደግ ኃላፊነት ስላለብን፣ እነርሱን ለማሳደግ አስፈላጊ የሆነውን ኢኮኖሚያዊ አቅማችን መመዘን ስለሚገባን፣ የምናሳድግበት አካባቢ፣ ሁኔታና የልጆች ፍላጎትም ስለሚለያይ ነው።

ለማሳደግ የምንፈልገው ሕጻን የዕድሜ ክልል ስንት ነው? የሚለው ሁለተኛው የመነጋገሪያ ጥያቄ ሊሆን ይችላል፡፡ ገና እንደ ተወለዱ በቀናት፣ በወራትና በዓመት ዕድሜ ክልል ወይንስ የሁለትና የሶስት አመታት ልጅ? በየትኛው የዕድሜ ክልል ውስጥ ያለ ልጅ ማሳደግ እንደምንፈልግ ወደ አንድ የውሳኔ ሃሳብ መድረስ ተገቢ ነው። ይህን

ማድረግ ያስፈለገው እንደ ዕድሜያቸው ፍላጎታቸው ስለሚለያይና ለእድገታቸው አቅርቦታችንን ለማዘጋጀት፣ እንደ ዕድሜ ክልላቸው አቀራረባችንን ለመወሰን፣ ዕድሜ የሚያመጣው ለውጥና እድገት የሚያስከትለውን የፍላጎትና የባሕርይ ለውጥ በአግባብ ለመቆጣጠርና ለማሳደግ ጠቀሜታው ከፍተኛ በመሆኑ ነው።

የዕድሜና የጾታ ምርጫ ካስተካከልን በኋላ የጉዲፈቻ ልጅ የምናገኝበትን አገር፣ ቦታ፣ ዘርና ቀለም መወሰን ይጠበቅብናል። ምናልባት በአገር፣ በዘር፣ በቋንቋና በስጋ ዝምድና ከእኛ ጋር ቅርበት ያለውን ሕጻን ነው የምንመርጠው ወይንስ ከእነዚህ ውጭ ሌላ ትኩረት የምንሰጠው ነገር አለ? የሚሉት ጥያቄዎች ከሚታሰቡባቸው ጉዳዮች መካከል ናቸው። ይህን የምናደርገው አንዳንድ ጊዜ የልጅ ፍላጎታችንን ለማሟላት ብቻ ሳይሆን ዘመድን መጥቀም ባህላችን እንደሆነ በማሰብ ሊሆን ይችላል።

ራሳችንን ልንጠይቅ የሚገባንን መሠረታዊ ጥያቄዎች ከመለስን በኋላ ቀጥሎ ከግለሰቦችና ከድርጅቶች ጋር በመገናኘት የምንፈልገውን የጉዲፈቻ ልጅ እንዴት ማግኘት እንደምንችል መረጃዎችን ማሰባሰብና እውነተኛና ሕጋዊ ሰነዶችን ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው። በዚህ ወቅት በተቻለ መጠን ሕጋዊ መንገድ መጠቀም እጅግ በጣም ተገቢና ከርስቲያናዊ ግዴታችንም ነው። የጉዲፈቻ ልጅ በማግኘት ሂደት እንዳንጭበረበርና ሂደቱ ከተወሰነ ጊዜያት በኋላ ሌላ ሕጋዊ የሆነ እንከን እንዳይገጥመውና እንዳያስጠይቀን ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ነው። እንዲህ ዓይነቱን ሂደት በጥንቃቄ ካለደረግነው በሚፈጠረው ችግር ከግለሰቦች፣ ከድርጅቶች፣ ከመንግሥትና ከትዳር አጋራችን ጋር ከፍተኛ የሆነ አለመግባባትና ግጭት ሊፈጠርና ተጠያቂም ሊያደረገን ይችላል።

የጉዲፈቻ ልጅ የማግኘት ሂደቶችን በሕጋዊ መንገድ ከጨረስንና ከተረከብን በኋላ በማሳደግ ሂደት ለትዳራችን የግጭት ምክንያትና የነበረንን መልካም ግንኙነት ችግር ላይ የሚጥል እንዳይሆን ሌላ ጥንቃቄ ያሻዋል። ይህን ለማለት የምናሳድገው ልጅ አለማግኘት አንድ ችግር ቢሆንም ማግኘትም ሌላ ችግር ሊሆን ስለሚችል ነው። የጉዲፈቻ ልጅን በማሳደግ ሂደት ሊወሰዱ ከሚገባቸው ጥንቃቄዎች መካከል፡- በተቻለ መጠን እንደ አቅማችን የልጆችን መሠረታዊ ፍላጎታት ለማሟላት ጥረት ማድረግ፣ ልንፈጽመው የማንችለውን ተስፋ አለመስጠት፣ ቃል ገብተን ባልፈጸምነው ጉዳይ ላይ በተቻለ መጠን ነገሩን ማብራራትና ለነገው በእኛ ላይ እምነት እንዲኖራቸው ማድረግ ተገቢ ነው።

ልጆችን በማሳደጉ ሂደት ክርስትናን እንደ እግዚአብሔር ቃል በሆነው የሕይወት ምሳሌነት በማሳየትና በየጊዜው ቃሉን በማስተማር በመንፈሳዊ ሕይወት ተኮትኩተው እንዲያድጉ መርዳት አንዱ ከፍተኛው ኃላፊነታችን ነው። ደግሞም እንደ ዕድሜያቸው ሁኔታና እንደ አመችነቱ በመመልከት፣ በመልካምና በፍቅር አቀራረብ ስለማንነታቸው ግልጥ ልናደርግላቸው ይገባል። ስለማንነታቸው ብዥታ እንዳይኖራቸው ግልጥ





ማድረጋችን ነገ የማንነት ቀውስ እንዳይገጥማቸው ከፍተኛ አስተዋጾ ይኖረዋል። እውነቱን በአግባቡ የማንነግራቸው ከሆነ በማሕበራዊ ሕይወት ግንኙነት ማለትም ከጎረቤት፣ ከጓደኛ፣ ከቤተ ክርስቲያን አባላት፣ ከወላጆች በተለያየ መንገድ በመስማት መረጃ ሊኖራቸው ስለሚችልና ከቤት የሚሰሟቸው ተቃራኒ አሳቦች ተጠራጣሪ፣ ግራ የተጋቡ፣ ራሳቸውን የሚጠሉና ራሳቸውን የሚያገልሉ እንዲሆኑ እንዲሁም የባሕርይ ለውጥ... እንዲፈጠርባቸው ያደርጋል፡፡ ስለዚህ በፍቅር ግንኙነት በግልጥ ትክክለኛውን ነገር በማስረዳት እውነተኛ ማንነታቸውን እንዲያውቁ ማድረጋችን እውነታውን ይዘው እንዲያድጉና በኋላ ከሚፈጠር ቀውስ እንዲያመልጡ ይረዳቸዋል።

## ለጥንዶች በግላቸውና በቡድን ለማጥናት የሚረዷቸው የውይይት ጥያቄዎች

## የምዕራፍ አስራ ሶስት (13)

## የውይይት ጥያቄዎች

1. መውለድ ባለመፈለግና ባለመቻል መካከል ያለውን ልዩነት ለመረዳት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌዎችን በማጣቀስና ከነባራዊ ሁኔታ በመንሳት ተወያዩበት።
2. ልጅ ባለመውለድ ምክንያት በባለትዳሮች መካከል በትዳራቸው ለግጭት መንስኤ ሊሆኑባቸው የሚችሉን ጉዳዮች በማንሳት ተነጋገሩበት።
3. ባለትዳሮች ልጅ አለመውለዳቸው የማን ችግር ነው? የባል ወይስ የሚስት? ችግሩንስ ለማወቅና መፍትሔ ለማፈላለግ ምን መደረግ አለበት ትላላችሁ?
4. መውለድ ያልቻሉ ባለትዳሮች በትዳራቸው ግጭት እንዳይፈጠርና ከተፈጠረም ግጭትን ለማስወገድና ለመቆጣጠር ሊወስዱት የሚገባውን የመፍትሔ እርምጃ በመጥቀስ ተወያዩ።
5. ልጅ ላልወለዱ ባለትዳሮች እንደ መፍትሔ እርምጃ ሊወስዷቸው ከሚገቡ እርምጃዎች መካከል አንዱ የጉዲፈቻ ልጅ ማሳደግ ነው፡፡ የጉዲፈቻ ምንነት፣ ሊወሰዱ የሚገባቸው ቅድመ ዝግጅቶች ምንነትና ለጉዲፈቻ ልጅ መደረግ ያለበት ነገር ምን እንደሆነ በመዘርዘር በሰፊው ተወያዩበት።
6. ምናልባት ልጅ እየፈለጋችሁ ልጅ የሌላችሁ ባለትዳሮች ከአሁን በፊት በጋራ ያልወሰዳችህት እርምጃ ምንድን ነው? ምንስ ልታድረጉ ወሰናችሁ? ልጅስ ሳይኖር የእናንተን የትዳር ግንኙነት ደስተኛና ጤነኛ ለማድረግ ምን ማድረግ አለብን ትላላችሁ?





# ምዕራፍ አስራ አራት(14)

# ወሊድን መቆጣጠር

## I. ወሊድን የመቆጣጠር ምንነት

ወሊድን መቆጣጠር ብለን የምንለው በስነ-ተዋልዶ ጤና ሙያና ተቋማት የቀረቡ የተለያዩ የወሊድ መቆጣጠሪያዎችን በመጠቀም ሴቶች ጽንስ እንዳይጸንሱ እና ልጅ እንዳይወልዱ የማድረግ ሂደትን ነው። የእርግዝና መከላከያዎች እርግዝና እንዳያጋጥም ልንጠቀምባቸው የምንችላቸውን የተለያዩ መድኃኒቶች፣ መንገዶችና አግባቦችን ሁሉ ያጠቃልላል። የወሊድ መቆጣጠሪያ የቤተሰብን ብዛት ለመመጠን፣ የመውልጃ ጊዜንና የልጆችን ብዛት ለመወሰን የሚያስችሉ መሳሪያዎችንና መድሃኒቶችን የሚያካትት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለወሊድ መቆጣጠሪያ በግልጥ የሚናገረው ነገር የለም! በዚህም ምክንያት አማኞች የወሊድ መቆጣጠሪያ መጠቀምን በተመለከተ የተለያየ አቋምና አመለካከት ሲያራምዱ ይታያል፡፡ የወሊድ መቆጣጠሪያን በሚመለከት በአማኞች ዘንድ የሚንጸባረቁ ጥቂት አመለካከቶችን በሚቀጥለው ርዕስ ለመቃኘት እንሞክራለን፡፡

## II. በወንጌላዊያን ክርስቲያኖች መካከል ያሉ የተለያዩ አመለካከቶች

### 1. የወሊድ መቆጣጠሪያ መጠቀም ኃጢአት ነው ብለው የሚያምኑ

ብዙ ወንጌላውያን አማኞች የተወሰኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ዋቢ በማጣቀስ ማንኛውንም ዓይነት የወሊድ መቆጣጠሪያ መጠቀም ኃጢአት ነው ብለው ያምናሉ። ይህንን አቋም ለምን እንደያዙ ለማስረዳትም *"እግዚአብሔርም ባረካቸው፥ እንዲህም አላቸው፦ ብዙ፥ ተባዙ፥ ምድርንም ሙሉአት፥..."* /ዘፍ 1፡ 28/ እና *"ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ ናቸው"* /መዝ.127፡3/ የመሳሰሉ ጥቅሶችን በማጣቀስ ይህንን አምላካዊ ሕግ መታዘዝ አስፈላጊ መሆኑን ያብራራሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ጽንስ እንዳይጸነስ በማንኛውም ሰው ሠራሽ መንገድ ማገድ እግዚአብሔር ወደዚህ ዓለም ሊያመጣው ያለውን ሰው እንደመግደል ነው የሚል መከራከሪያን በማቅረብ የወሊድ መከላከያ መድኃኒቶችንና መሳሪያዎችን መጠቀም ዳግም ለተወለደ ክርስቲያን ባለትዳር ተገቢ አይደለም ብለው ይሟገታሉ፡፡

### 2. የወሊድ መከላከያ መጠቀም ኃጢአት አይደለም ብለው የሚያምኑ

ሌሎች ወንጌላውያን ክርስቲያኖች ደግሞ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ የሞራል መርህ ጋር ግልጥ ተጣራሽነት ከሌለው አንድ ክርስቲያን ሌሎችን በሐኪም የታዘዙ መድኃኒቶችን ጤንነቱን ለመጠበቅ ከመጠቀም በተለየ መልኩ ምንም ዓይነት የወሊድ መከላከያ መጠቀም ኃጢአት ነው ተብሎ ሊወገዝ የሚችልበት መጽሐፍ ቅዱሳዊም ሆነ ዶክትሪናዊ መሠረት የለም ይላሉ። ለእነዚህ ወገኖች የወሊድ መከላከያ መጠቀም ምንም ኃጢአት የለበትም። ይህን አመለካከት የሚቀበሉ አማኞች ሊመለስ የሚገባው ጥያቄ ቢኖር የሰው ሕይወት የሚጀምረው መቼ ነው? የሚለው ጥያቄ ነው ይላሉ። ወሊድ መከላከያ የምንጠቀመው የተጀመረን ጽንስ በማቋረጥ ሕይወት ለማጥፋት ሳይሆን ጽንስ

እንዳይፈጠር አስቀድሞ ለመከላከል ነው። ጽንስ የሚፈጠረው የወንድ ዘርና የሴት እንቁላል ሲገናኝ ነው። ኃጢአት ሊሆን የሚችለው ከፈርቲላይዜሽን በፊት ሳይሆን ከፈርቲላይዜሽን በኋላ የተጸነሰን ጽንስ ወደማቋረጥ ከገባን ነው በማለት የወሊድ መከላከያ መድኃኒቶችንና መሳሪያወችን በመጠቀም ጽንስ እንዳይጸነስ መከላከል ስህተት አይደለም ብለው ይሟገታሉ።

በዚህ ጽሑፍ ለማስቀመጥ የምፈልገው የተለያዩ የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴዎችን የማይጠቀሙ ሰዎችን እምነት ለመሸርሸርና የሚጠቀሙ ሰዎችን ለማጽደቅ አይደለም። የተለያዩ የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴዎችን መጠቀም ወይም አለመጠቀም የጥንዶቹ የጋራ ውሳኔ ነው። የወሊድ መቆጣጠሪያ ለማይጠቀሙ ባለትዳሮች የጋራ በጋራ የተስማማችሁበትና በእምነት እንቀጥላለን ለምትሉ እንደ እምነታችሁ ይሁን ለማለት እወዳለሁ። የዚህ ክፍል ዓላማ የወሊድ መቆጣጠሪያ መጠቀምም ሆነ አለመጠቀም የጋራ ውሳኔ እንዲሆን፣ ሁለቱም ዓይነት ምርጫና ውሳኔ ለግጭት ምክንያት እንዳይሆንና የትዳር ግንኙነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳያመጣ በውሳኔ ላይ ልዩ የሆነ ጥንቃቄ ማደረግ አስፈላጊ እንደሆነ ማስገንዘብ ነው።

የወሊድ መቆጣጠሪያ የማይጠቀሙትን ውሳኔያችሁ በጋራ ስምምነት ይሁን በማለት ለሚጠቀሙት ደግሞ በጋራ በመመካከርና ባለሙያ በማማከር እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው ለማስጨበጥና የመፍትሔ አሳቦችን ለመስጠት ነው። የወሊድ መከላከያ የማይጠቀሙ ባለትዳሮች የሚጠቀሙትን አይፍረዱባቸው እንዲሁም የሚጠቀሙ የማይጠቀሙትን ከስልጣኔ ወደ ኋላ እንደቀሩ በማሰብ አትናቋቸው ለማለት እወዳለሁ።

## III. የተለመዱ የቤተሰብን ቁጥር የመመጠን ምክንያቶች

በአሁኑ ወቅት ብዙ ባለትዳሮች የተለያዩ የወሊድ መቆጣጠሪያዎችን በመጠቀም እርግዝናን ይከላከላሉ። የሚወልዷቸውን ልጆች ቁጥርም ይመጥናሉ። የተለያዩ ባለትዳሮች ይህን የሚያደርጉበት የራሳቸው የሆነ ምክንያት አላቸው። ከምክንያቶች አንዱ በወቅቱ ልጆችን ወልዶ ለማሳደግ የኢኮኖሚያዊ አቅም ደካማነት ሊሆን ይችላል። አንዳንዶቹ ደግሞ ልጅ ወልዶ ማሳደግ የሚጠይቀውን ከፍተኛ ኃላፊነት በመረዳት ይህን ኃላፊነት ለመወጣት ዝግጁ አይደለሁም በሚል ምክንያት ልጅ ሳይወልዱ ወይም ልጆች ሳያበዙ በትዳር ውስጥ መቀጠል ሊመርጡ ይችላሉ:: አንዳንዶቻችን ደግሞ እንደ ክርስቲያን ባለትዳርነታችን እግዚአብሔርን በመተማመን መኖር ሲገባን ከዚህ የአማኞች የሕይወት ውበት በመጉደል ወደተጠቀሱት ስጋቶችና ፍርሃቶች ገብተን ሊሆን ይችላል። ኃላፊነትና ባለአደራነት በተሞላው ሕይወት የእግዚአብሔር አባትነትና የቤተሰብ አስተዳዳሪነት መረሳት የለበትም።

ሌላው ልጅ ወልዶ የማሳደግ ኃላፊነት በቂ ጊዜ መስጠትን የሚጠይቅ በመሆኑ አንዳንድ አማኞች ይህንን የጊዜ አስፈላጊነት በመረዳትና የወላጅነት ኃላፊነት





የሚጠይቀው ጊዜ የሌላቸው መሆኑን በማወቅ የወሊድ መከላከያን ተጠቅመው እርግዝና እንዳይፈጠር አስቀድመው ይከላከላሉ። እንደዚህ ዓይነት እርምጃ ለመውሰድ የተገደዱት በወቅቱ የገቡት ውል በመኖሩ፣ ጊዜያቸውን የሚሻማ ወይም ጊዜያቸውን የሚጠይቅ ሌላ ኃላፊነት ያለባቸው በመሆኑ ወይንም በትምህርት፣ በልዩ ልዩ ሥራና እንቅስቃሴ በመጠመዳቸው ምክንያት ሊሆን ይችላል። ዓመትና ከዚያም በላይ የሆነ ጊዜን የሚጠይቅ የአገር ውስጥና የውጭ አገር የትምህርት ዕድልና በሥራ ምክንያት ከቤተሰብ ጋር አብሮ በአንድ ቦታ አለመኖር የሚጠቀሱ ጊዜ ጠያቂ ምክንያቶች ናቸው።

ሌላው ጊዜያዊ ወይንም የዕድሜ ልክ ለሕይወት አስጊ የሆነ የጤንነት መቃወስ ማጋጠሙ አንዱ ባለትዳሮች የወሊድ መከላከያ እንዲጠቀሙ የሚያስገድድ ተጥቃሽ ምክንያት ነው። በእርግዝናና በመውለድ ምክንያት ሊፈጠር የሚችል ውስብስብ የሆነ የጤንነት መቃወስ እንዳለ በተለያዩ ሐኪሞች ምስክርነት ሲሰጥና በምርመራ ውጤት ሲረጋገጥ ማስጠንቀቂያ በተሰጠበት ወቅት እርግዝናን መከላከል የግድ ሊል ይችላል።

አንዳንድ ባለትዳሮች ደግሞ በትዳራቸው ደስተኛ ባለመሆናቸው ምክንያት ከትዳር ጓደኛቸው ልጅ መውለድ ላይፈልጉ ይችላሉ:: ግንኙነታቸው ጤናማ ያልሆነ፣ በስሜትና በስነ ልቦና የተራራቁና አብረው እየኖሩ ነገር ግን እንደሚለያዩ ምልክቶች የሚታይባቸው ጥንዶች አስቀድመው የመውለድ ተስፋቸውን በማጨለምና መውለድ የለብኝም የሚል አቋም በመያዝ ጽንስ እንዳይፈጠር መከላከል ይጀምራሉ። እንደዚህ ዓይነቶቹ ባለትዳሮች ለትዳር ጓደኛቸው በማሳወቅ ወይም ከትዳር ጓደኛቸው ተደብቀው የእርግዝና መከላከያ መድኃኒቶችን ወይም መሳሪያዎችን ሊጠቀሙ ይችላሉ:: በእርግጥ አንዳንዶችም ከትዳር አጋራቸው ይልቅ ለልጅ ከፍተኛ ስፍራ ያላቸው ከሆነ የትዳራቸው ግንኙነት እንደማይቀጥል ቢረዱም ልጅ የማግኛ መንገዱ ግን በዚህ ዕድል ውስጥ የሚገኝ እንደሆነ በመረዳት እርግዝናን መከላከሉን በማቆም ለመውለድ ጥረት ያደርጋሉ።

## IV. የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴዎችና ዓይነቶች

በወሊድ መቆጣጠር ሂደትና መቆጣጠሪያ ዓይነቶች ላይ የተለያዩ አመለካከቶች እንዳሉ የታወቀ ነው:: ስለዚህ እንደየመረዳታችን ጥንዶቹ በምናደርገው ስምምነት፣ ከሐኪም ምክር በምናገኘው ድጋፍ መሠረትና አንዱ በሌላው ላይ ባለመፍረድ የወሊድ ቁጥጥር ማድረግ ይቻላል። የወሊድ መቆጣጠሪያ ሊጠቀሙ ለሚያስቡ የባለትዳሮች የጋራ ስምምነት፣ የሐኪም ምክርና የጤንነት ጉዳይ ማለትም የጎንዮሽ ጉዳት አለማስከተሉ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ናቸው። በአሁኑ ጊዜ የወሊድ መቆጣጠሪያን ለሚጠቀሙና ሊጠቀሙ ለተዘጋጁ የተለያዩ የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴዎችና ዓይነቶች እንዳሉ ማወቅ ለምርጫና ለውሳኔ ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው። ከዚህ በመቀጠል በዚህ ጉዳይ ላይ ትኩረት ያደረገ ቅኝት እናካሂዳለን:-

## 1. ተፈጥሮአዊ የእርግዝና መከላከያ ዘዴዎች

ከግብረስጋ ግንኙነት መታቀብ፣ ማጥባት፣ በግንኙነት ወቅት የወንዱን የዘር ፈሳሽ ከሴቷ ብልት ውጪ ማፍሰስ፣ በጊዜ ሰሌዳ በመታገዝ እርግዝና ሊከሰትባቸው የሚችልባቸውን ቀናቶች መያዝና በእነዚህ ቀናቶች የግብረስጋ ግንኙነት አለማድረግ እንዲሁም ሴቷ የሙቀት መጠኗን በመለካትና የብልት ፈሳሽን ሁኔታ በማጥናት ግንኙነት ብታደርግ ልታረግዝ በምትችልባቸው ቀኖች ከግብረስጋ ግንኙነት መታቀብን የሚያጠቃልል ነው።[52] የእርግዝናን ወቅት በመረዳት ከግብረ ስጋ ግንኙነት መታቀብ (ተፈጥሯዊ የወሊድ መከላከያ ዘዴ) ከወር አበባ በኋላ ያለው አስተማማኝ ጊዜ ማለትም በሰአት ከ100-120 ሰዓታት ወይም ከ4-5 ቀናት የሴት ልጀ እንቁላል ለእርግዝና ዝግጁ በሚሆንበት ወቅት ጾታዊ ግንኙነት ባለማድረግ እርግዝናን መከላከል ይቻላል። ነገር ግን የዑደቱ ርዝመት እና እንቁላሉ ዝግጁ የሚሆንበት ጊዜ ከሴቶች ወደ ሴቶች ስለሚለያይ ይህ መንገድ እጅጉን በጣም የማያስተማምን መንገድ ነው።[53] አዳንዶቹ እንዲህ ዓይነቱን የመከላከል ዘዴ ሲቀበሉ ሌሎች ደግሞ *"... ለጸሎት ትተጉ ዘንድ ተስማምታችሁ ለጊዜው ካልሆነ በቀር፥ እርስ በርሳችሁ አትከላከሉ፤ ራሳችሁን ስለ አለመግዛት ሰይጣን እንዳይፈታተናችሁ ደግሞ አብራችሁ ሁኑ።"* /1ኛቆሮ 7፡ 1-5/ የሚለውን ቃል በመጥቀስ ይህን ዘዴ ይቃወሙታል።[54]

## 2. አካላዊ ግርዶሽ

አካላዊ ግርዶሽ ተብለው ከሚጠሩት መካከል የወንድና የሴት ኮንደሞች፣ ዲያፍራምና የወንዱን ዘር ፍሬ የሚገድሉ ኬሚካሎች ይገኙበታል። ከአካላዊ ግርዶሽ ዘዴ መካከል ኮንደምን በአግባብ ከተጠቀምንበት እርግዝናን ብቻ ሳይሆን በወሲባዊ ግንኙነቶች ከሚተላለፉት በሽታዎች እንደ ኤች.አይ.ቪ የመሳሰሉትን ሊከላከሉ ከሚችሉ ዘዴዎች አንዱ ዘዴ ነው።[55] ኮንዶም የወንድ ዘር ወደ ሴቷ ብልት እንዳይገባ በመከላከል የሚያገለግል የእርግዝና መከላከያና ወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴ ነው። ሌላው አካላዊ ግርዶሽ ተብሎ ከሚመደበው የመከላከያ ዘዴ አንዱ ዲያፍራም/የማህጸን ሽፋን/ ከወንድ ዘር ማምከኛ ክሬም ጋር በሴትዋ ብልት ውስጥ በማድረግ ጽንስን የመከላከል ዘዴ ነው። ብሩክ ዘውዱ (ዶ/ር) እንደገለጹት የአካላዊ ግርዶሽ የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴዎች

[52] http://www.etpharmanet.com/index.php/about-us/42-pregnancy/37-2014-07-11-15-11-49 Written by Super User on 11 July 2014. Accsesed Sep.22, 2014.

[53] Clinton, Tim & Trent, John. Marriage and family Counseling the quiqe referance Giude pp.51-61

[54] Clinton, Tim & Trent, John. Marriage and family Counseling the quiqe referance Giude pp.51-61

[55] Clinton, Tim & Trent, John. Marriage and family Counseling the quiqe referance Giude pp.51-61





እስካሁን አለም ከደረሰባቸው የእርግዝና መከላከያ መንገዶች ቀላሎቹ፣ ወጪ ቆጣቢዎችና የተሻሉ አማራጮች እንደሆኑ ይናገራሉ።[56]

## 3. ሆርሞናል የሆኑ የእርግዝና መከላከያ ዘዴዎች

ሆርሞናል የሆኑ የእርግዝና የመከላከያ ዘዴዎች በመባል የሚታወቁት በውስጣቸው ሆርሞኖችን የሚይዙና በእንክብል መልክ የሚወሰዱ፣ በመርፌ የሚሰጡ፣ በክንድ የሚቀበሩ፣ በቆዳ የሚለጠፉ እንዲሁም በብልት ውስጥ የሚከተቱ የመከላከያ ዘዴዎች ናቸው።[57] በሌላ አገላለጥ ሆርሞናል የሆኑ የእርግዝና የመከላከያ ዘዴ ዓይነቶች ሰው ሠራሽ ከሆነ ሆርሞን የሚሠሩ የተለያዩ በሚዋጥ ክኒን መልክ፣ በመርፌ በክትባት መልክ፣ በሰውነት ክፍል በሚቀበር መልክ፣ የእርግዝና መከላከያ ቀለበትና የሚለጠፍ የእርግዝና መከላከያ ዘዴዎች የመሳሰሉ ናቸው።[58]

## 4. ዘለቄታዊ የሆነ የመከላከያ ዘዴ (ማምከን)

ማምከን ዘላቂ የሆነ የእርግዝና መከላከያ ዘዴ ነው። የሴቶች ማምከን የሚከናወነው እንቁላሎች የሚተላለፉባቸውን ቱቦዎች በመዝጋት እንቁላሎች እንዳያልፉ በመከልከል ነው። ይሄንን በቀዶ ጥገና ወይም ከቀዶ ጥገና ውጭ ማድረግ ይቻላል። ነገር ግን ወንዶችን የማምከን ዘዴ የሚከናወነው በቀዶ ጥገና ሲሆን የወንዱ የዘር ፍሬ የሚተላለፍበትን ቱቦ በመዝጋት ነው።[59] ይህ የማምከን ዘዴ የመጨረሻው የወሊድ መከላከያ ዘዴ ነው። በእንዲህ ዓይነቱ ዘዴ የሚከናወነው የወንድ ልጅ ዘር እንዳይተላለፍ መተላለፊያ ባንቧ መቁረጥ ወይም መዝጋት ነው። ሌላው ተጠቃሽ የማምከን ቋሚ የወሊድ መከላከያ ዘዴ የሴትን ልጅ ማህጸን ፈጽሞ እንዳትወልድ በሚያደርግ ዘዴ መዝጋት ነው። እንዲህ ዓይነቱ ዘለቄታዊ የሆነ የመከላከያ ዘዴ የሚከናወነው በአብዛኛው በቀዶ ጥገና አማካኝነት ነው።[60]

## 5. ድንገተኛ የእርግዝና መከላከያ ዘዴ

ይህ ዘዴ ባለነጠላ አካላዊ ቅመም ሆኖ በአፍ የሚወሰድ ጥንቃቄ በጎደለው የግብረ ስጋ ግንኙነት ሊፈጠር የሚችልን ድንገተኛ የሆነ እርግዝናን የሚከላከል ዘዴ ነው። ይህ የመከላከያ ዘዴ የሴቷን እንቁላል ከእንቁልጢ ተኮርታ እንዳትወጣ በማድረግ፣ የማህጸን

[56] Dr. Brook Zewdu, http://ethiohakim.net/index.php/story/239/contraceptives written june 09,2014, accsesed Sep.22, 2014.

[57] http://www.etpharmanet.com/index.php/about-us/42-pregnancy/37-2014-07-11-15-11-49 Written by Super User on 11 July 2014. Accsesed Sep.22, 2014.

[58] Clinton, Tim & Trent, John. Marriage and family Counseling the quiqe referance Giude pp.51-61

[59] Family Planning Queensland © Version 3 /http://www.fpq.com.au/pdf/Br_Contraception_Choices_Amhar4page.pdf June 2012 accsesed Sep. 22, 2014.

[60] http:// www.etpharmanet.com/index.php/about-us/42-pregnancy/37-2014-07-11-15-11-49 Accsesed Sep.22, 2014.

በር ፈሳሽን በማወፈር የአጣብቂኝ ዓይነት ባህርይ እንዲኖረው በማድረግ፣ የወንድ የዘር ፍሬ ወደ ማህጸን ለመግባት የሚችልበትን መተላለፊያ በመዝጋት እና የማህጸን ግድግዳን በማሳሳት ከወንድ የዘር ፍሬ የተዋሃደችው እንቁላል የምታርፍበትን የማህጸን ግድግዳ ለጽንሱ ቀጣይ እድገት እንዳይመች በማድረግ ያልተፈለገ እርግዝናን እንዳይከሰት ይከላከላል።[61]

ይህን ጥንታዊ ጽሑፍ ያቀረበ ድህረ ገጽ እንደሚገልጸው ይህ የመከላከያ ዘዴ መወሰድ ያለበት ድንገተኛ ጥንቃቄ የጎደለው የግብረ ስጋ ግንኙነት በተፈጸም **በ120 ሰዓታት** ወይም **በ5 ቀናት** ውስጥ የእርግዝና መከላከያ እንክብሎችን በአፍ በመውሰድ ነው፡፡ አለበዚያ ቀኖች እየገፉ በሄዱ መጠን እርግዝናን የመከላከል አቅሙ እየቀነሰ ይሄዳል በማለት ይህን ዘዴ በሚጠቀሙ ሚስቶች ወዲያውኑ እንዲወሰድ ባለሙያዎች ይመከራሉ። ይህም ሁኖ ድንገተኛ የእርግዝና መከላከያ ዘዴ ውጤታማነቱ **85%** ብቻ እንደሆነ ጥናቱ ይጠቁማል።[62]

## V. የወሊድ መቆጣጠሪያን ተጠቃሚ በመሆን ወቅት

### 1. መለየት፡- ስላሉት የተለያዩ የወሊድ መቆጣጠሪያዎች ጥናት በማድረግ መለየት

በተለያዩ ምክንያቶች ላልተወሰነ ጊዜና ለዘለቄታው ወሊድን ለመከላከል ሰዎች ወደ ውሳኔ ይመጣሉ። እንደየአመለካከታቸው የተለያዩ የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴዎችን በመጠቀም እርግዝናን ሲከላከሉ ይታያሉ። ስለወሊድ መከላከያ በተለያየ መንገድ አስፈላጊነታቸውንና እንዴት መጠቀም እንዳለብን ከሆስፒታሎች፣ ከክሊኒኮች፣ ከመመገናኛ ብዙሃን፣ ከጽሑፎችና ከተለያዩ ማስረጃዎች ልናገኝ እንችላለን።

ክርስቲያን ባለትዳሮች የወሊድ መከላከያን ለመጠቀም ከወሰንን ስላሉት የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴዎችና ዓይነቶች መረጃን ከተለያዩ ቦታዎች በመሰብሰብ ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲኖረን ጥረት ማድረግ የትኛውን የወሊድ መከላከያ እንደምንጠቀም ከመወሰናችን በፊት ልናደርገው የሚገባ ቅደመ ዝግጅት ነው። በግልና በጋራ ለትክክለኛ ውሳኔ የሚረዳን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግንዛቤና ሙያዊ ድጋፍ እንድናገኝ የቤተ ክርስቲያን መጋቢዎቻችንን፣ የበሰሉ ክርስቲያኖችን፣ የሕክምና ባለሙያ የሆኑ የቤተ ክርስቲያን አባላትንና ስርዓት ባለው የሕክምና ተቋም የሚሠሩ የተመሰከረላቸው የሕክምና ባለሙያዎችን ማነጋገርን የየበኩላችንን ድርሻ ለመወጣት፣ ለጋራ ውይይትና ውሳኔ እንደ መሠረታዊ መነሻ ልንጠቀምበት እንችላለን።

[61] http://www.mahederetena.com/amharic/archives/2062 written by ማህደር ጤና Augest 18,2014 Accsesed Sep.23, 2014

[62] http://www.mahederetena.com/amharic/archives/2062 written by ማህደር ጤና Augest 18, 2014 Accsesed Sep.23,2014





እጅግ በጣም ጥንቃቄ የተሞላ ውሳኔ የሚጠይቁ የወሊድ መቆጣጠሪ ዘዴዎች መኖራቸው አይዘነጋም። በሁሉም ሂደት ውስጥ ባለትዳሮች በጋራ በመመካከርና ስምምነት ላይ በመድረስ አሃዳዊ አቋም ሊይዙ ይገባል፡፡ ነገር ግን በተለይ የማይለወጡ፣ ቋሚ ወይም ዘለቄታዊ የሆኑ የወንድ ዘር መተላለፊያ ባንቧን ማዘጋት ወይም ማስቆረጥና የሴቶችን ማህጸን ማዘጋትን የመሳሰሉ ሂደቶች በደንብ ሊታሰብባቸውና ሁለቱም የትዳር ጓደኞች በጋራ ሊወስኑባቸው የሚገቡ ዘዴዎች ናቸው።

በአጠቃላይ ባለትዳሮች የወሊድ መቆጣጠሪያ ለመጠቀም ግምት ውስጥ ሊያስገቧቸው የሚገቡ ጉዳዮች ቢኖሩ፡- ውጤታማነት፣ ላጠቃቀም አመቺነት፣ መከላከያው የሚቆይበት የጊዜ እርዝማኔ፣ ዳግም የመውለድ ዕድል፣ ከወሊድ መከላከያ ዘዴው ጋር የሚመጣ የማሕጸን ደም መፍሰስ፣ የጎንዮሽ ጉዳት፣ የመካላከያ መጠን፣ የዋጋው ተመጣጣኝነት፣ ከአባላዘር በሽታ የመከላከል አቅምና ሌሎች መከላከያ መንገዱን ሊከለክሉ የሚችሉ ሁኔታዎች እንደሆኑ የሕክምና ባለሙያዎች ይመከራሉ።[63]

### 2. መመካከርና መጸለይ፡- በጋራ በመነጋገር መጸለይ

ከተለያዩ ግለሰቦች፣ ባለሙያዎችና የተለያዩ በጽሁፍ ደረጃ የተቀመጡ ያነበብናቸው መጽሐፍት ያገኘናቸውን ጠቃሚ ሃሳቦች ይዘን በጋራ በእግዚአብሔር ፊት መጸለይና ደግሞ ደጋግሞ በጋራ ለትዳር አጋራችን ደህንነትና ለግንኙነታችን ጤንነት መወያየት አስፈላጊ ነው። ያገኘነውን እውቀት የውስጥ ሰላም ባለበት መንገድ ለመጠቀም መወሰን እንድንችል በጸሎትና በጾም ጸሎት ለነገሩ ትኩረት ሰጥተን መጸለይ ተገቢ ነው። ከብርቱ ጸሎትና ውይይት በኋላ ለውሳኔ የሚረዱ አማራጭ ሃሳቦችን በማስቀመጥ ወደ አንድ አሳብ መምጣት ይገባል። በሁሉ ነገር እንስማማለን ማለት አይደለም ነገር ግን ለትዳራችን ግንኙነትና ጤንነት ሲባል አንዳንድ ጊዜ ባለመስማማት መስማማት ላይ መድረስ ይኖርብናል። እንደ ባልና ሚስት ለትዳራችን ሰላም ሲባል በተቻለ መጠን ይህን ዘይቤያዊ ንግግር የሆነ ቃል ማሰብ ተገቢ ነው *"በውኑ ሁለት ሰዎች ሳይስማሙ በአንድነት ይሄዳሉን?"* /አሞጽ 3፡ 3/፡፡

### 3. መረዳት፡- ውሳኔያችን በሂደት ሊሻሻል እንደሚችል መረዳት

የወሊድ መከላከያ መውሰድ አለብን ወይስ የለብንም? ከሆነስ መቼ? የትኛውን ዓይነት የመከላከያ ዘዴ እንጠቀም?... የሚሉ ጥያቄዎቻችን ተመልሰውና በጋራ ተስማምተን እርምጃ ከመውሰዳችን በፊትና በኋላ ውሳኔያችንን እንደ ገና እንድንፈትሽ ወይም እንድንለውጥ የምንገደድባቸው ሁኔታዎች መፈጠራቸው አይቀሬ

> **"አንዱን የመከላከያ ዘዴ በመምረጥ ከመጠቀምዎ በፊት ሐኪምዎን ማማከርና የሐኪምን ትዕዛዝ ለመፈጸም ችላ አይበሉ!!**

[63] Dr. Brook Zewdu, http://ethiohakim.net/index.php/story/239/contraceptives written june 09,2014, Accsesed Sep.22, 2014.

ሊሆን ይችላል። ውሳኔያችንን እንደ ገና እንድንመለከት ከሚያደርጉን ምክንያቶች መካከል ምናልባት የሴቷ ተፈጥሮና ሆርሞን ሁኔታ ለጤንነት ችግር ፈጣሪ መሆን መጀመሩ፣ የሚወሰደው የወሊድ መከላከያ የሚፈጥረው አሉታዊ ተጽዕኖ ከፍተኛ መሆንና ሁሉም የወሊድ መከላከያዎች መቶ ፐርሰንት (100%) አስተማማኝና ፍጹም አለመሆናቸው ተጠቃሽ ናቸው። ምንጊዜም ቢሆን የሰው ሥራ ፍጹምነት እንደሚጎድለው መርሳት የለብንም!

## 4. መተሳሰብ፦ ለትዳራችን (ለመልካም ግንኙነት) ማሰብ

ወሊድን ስለመቆጣጠር ስናስብ፣ ስንጸልይና በጋራ ስንወስን ልናስባቸው የሚገቡን ጉዳዮች ብዙ ናቸው፡፡ልጆች ካሉን አሁን ላሉን ልጆች ሁለንተናዊ ጤንነትና እድገት የሚያስፈልገውን አቅርቦት ማሟላት መቻላችን ወይም ልጆች ያልወለድን ከሆንን ቤተሰባችንን በመልካም የምናስተዳድርና ኃላፊነት የሚሰማን ባለትዳሮች ሆነን የመገኘት አስፈላጊነት የመሳሰሉት ልናስብባቸው ከሚገቡ ጉዳዮች መካከል ተጠቃሽ ናቸው። በተቻለ መጠን በጋራ ተነጋግሮ ከመወሰን ሌላ ምርጫ አይኑረን! ነገር ግን በጋራ በተስማማንበትና እርምጃ በወሰድንበት ጉዳይ በሚፈጠሩ አስቸጋሪና የማይመቹ ሁኔታዎች ላይ አንዱ ሌላውን መኰነን፣ ጣት መጠቆምና ማሳበብ እንዳይኖር መስማማት መቻል አለብን። እንዲህ ዓይነቱ ድርጊት ግንኙነታችንን ከማሻከር አልፎ ነገ በሚሆነውና በምንወያይበት ጉዳይ ላይ እንዳንተማምን ትልቅ እንቅፋት ይሆንብናል። ለጋራ ትዳራችን፣ ቤተሰባችን፣ ኑሯችንና ጥቅማችን "አያገባኝም"፣ "እኔ የለሁበትም" ወይም "ድሮም ብየ ነበር!" የሚሉ አንድነትንና ወደ ፊት በጋራ እየተስማሙ የመጓዝን ሂደት የሚረብሹ እንቅፋቶችን አስቀድሞ በማስተዋልና በብስለት ቢቻል ማስወገድ ያለዚያም መቀነስ ጠቢብነት ነው።





# ለጥንዶች በግላቸውና በቡድን ለማጥናት የሚረዷቸው የውይይት ጥያቄዎች

## የምዕራፍ አስራ አራት (14)

## የውይይት ጥያቄዎች

1. ወሊድን መቆጣጠርና ወሊድ መቆጣጠሪያ ስንል ምን ማለታችን ነው? በቂ ውይይት በማድረግ አብራሩ፡፡
2. በወሊድ መቆጣጠርና ወሊድ መቆጣጠሪያ ላይ ክርቲያኖች ያሏቸውን የተለያዩ አመለካከት በመግለጥ ተወያዩ፡፡
3. የተለያዩ የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴዎችን በመጠቀም ወሊድን የሚቆጣጠሩበት የተለያዩ ምክንያቶችን በመጥቀስ በሰፊው ተወያዩበት፡፡
4. ወሊድን ለመቆጣጠር የተለያዩ የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴዎችን ከመጠቀም በፊት ባለትዳሮች ሊወስዱት የሚገባ እርምጃ ምን ሊሆን ይገባል ትላላችሁ?
5. የወሊድ መከላከያ ለመጠቀም በጋራ የተስማሙ ባለትዳሮች ቀጥለው ሊወስዷቸው የሚገቡ የተለያዩ የመፍትሔ እርምጃዎችን ባግባቡ ጥቀሱ፡፡
6. ወሊድን ከመቆጣጠር አንጻር ምናልባት ከበፊቱ የተለየ ውይይትና ውሳኔ የሚጠይቅ የጋራ ጉዳይ ምንድን ነው? ምንስ ልታደርጉ አሰባችሁ? መጽሐፍ ቅዱሳዊ አሳቦችን፣ ቤተሰባዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታችሁንና ክርስቲያናዊ ኃላፊነታችሁን ያገናዘበ ውይይት አድርጉ፡፡

# ምዕራፍ አስራ አምስት(15)
# እርግዝናና ከእርግዝና ጋር የተያያዙ ችግሮች

## I. የእርግዝና ምንነት

እርግዝና የምንለው አንዲት ሴት በሕይወቷ ውስጥ ከጽንስ መፈጠር ጀምሮ እስከ ልጅ መውለድ ባለው ጊዜ ውስጥ የምታልፍበትን ሂደት ነው፡፡ ይሄ ሂደት በተለይ ለአዲስ ወላጆች እንግዳ ስለሚሆን ግራ መጋባትን ሊፈጥር ይችላል። ስለሆነም እርግዝናን ከማረጋገጥ ጀምሮ የጽንሱን መፈጠር ተከትለው ስለሚከሰቱ የሰውነት እና የስሜት ለውጦች በእውቀት መዘጋጀት ይገባል። በቅርብ ተጋብተው የመጀመሪያ ልጃቸውን ለማግኘት ለሚፈልጉና ለሚጠብቁ እርግዝና ታላቅ ደስታ ይፈጥራል። በባለትዳሮች የግብረ ስጋ ግንኙነት ጥምረት ከሚፈጠሩ ተፈጥሮዊ ክስተቶች አንዱ እርግዝና ነው። እርግዝና ሲከሰት በመጀመሪያ የሚያጋጥመው የወር አበባ መቅረት ነው።

የወር አበባ መጥፋት ወይም መዘግየት ዋነኛ ምክንያት እርግዝና ቢሆንም ከእርግዝና በተጨማሪም ሌሎች የተለያዩ ምክንያቶች ይጠቀሳሉ። ብዙ ሴቶች የእርግዝና ጥርጣሬ የሚኖራቸው የወር አበባ ከሚመጣበት ጊዜ ሲዘገይ ነው። የወር አበባ ዘገየ ማለት ግን በእርግጠኝነት እርግዝና ተከሰተ ማለት አይደለም። ስለዚህ እርግዝና መከሰቱን አስቀድሞ ማረጋገጥ ተገቢ ነው፡፡ ይህ እንደተረጋገጠ ለእርጉዟ ሴትና ለጽንሱ ጤንነት ሲባል ለየት ያለ የተለያየ እንክብካቤ የሚያስፈልገው ወቅት ቢኖር የእርግዝና ወቅት ነው። የእርግዝና ወቅት ልጅ ከማግኘት አንጻር የሚያስደስት ሲሆን፣ ሂደቱ ግን አድካሚ፣ ሕመም የሞላበትና ለብዙ ለውጦች ተጋላጭ የሚደርግ ነው።

ይህ ምዕራፍ በእርግዝና ወቅት የሚፈጠሩ ለውጦች ምንድን ናቸው? የሚያስከትሉት ችግርስ ምንድን ነው? በዚህ ወቅት የሚፈጠሩ አለመግባባቶችንና ግጭቶችን በመረዳትና በመተሳሰብ በጋራ ለመሻገር፣ ጠንካራ የትዳር ግንኙነት ለመፍጠርና ጤነኛና ደስተኛ ቤተሰብ ለመመሥረት ምን ማድረግ አለብን የሚሉ መሠረታዊ እውነቶችን በመረዳት ከዚህ ክስተት ጋር ተያይዘው ሊከሰቱ የሚችሉ ግጭቶችን ለመከላከል፣ ለመቀነስና ለመፍታት የሚጠቅም ክፍል ነው።

ጥንዶች በትዳር ሕይወታቸው አንድነታቸውን የሚገልጹት በግብረ ስጋ ግንኙነት እንደሆነ የእግዚአብሔር ቃል ያረጋግጥልናል። እግዚአብሔር የግብረ ስጋ ግንኙነትን ለሰው ልጆች በሚሰጥበት ወቅት አንዱ ዓላማው በትዳር ውስጥ ባለ ግንኙነት ጥንዶች መባዛት ማለትም ዘር መተካት፣ መጸነስ ወይም መውለድ እንዲችሉ አቅዶ ነው፡፡ ሚስት ከጸነሰችበት ቀን እስከ ምትወልድበት ጊዜ ያለው ወቅት የእርግዝና ጊዜ በመሆኑ በዚህ ወቅት የሚፈጠሩ ለውጦች ጥንቃቄዎችንና እንክብካቤን የሚፈልጉ ናቸው፡፡ ስለዚህ የትዳር አጋር አስፈላጊ የሆኑ እንክብካቤዎችን በማሳየትና በማሳሰብ የሚስቶች የእርግዝና ወራቶችን በመረዳትና በመደጋገፍ ሊመጣ ያለውን የልጅ በረከት በደስታ ለመቀበል





የሚያስችል መረጃና ማስረጃ በመስጠት የትዳር ግንኙነትን ጤንነት መጠበቅ እንዲቻል ማመላከት የዚህ ርዕስ ትኩረት ነው።

## II. በእርግዝና ወቅት የሚፈጠሩ ለውጦች

እርግዝና ከጽንስ መፈጠር ጀምሮ እስከ ልጁ መወለድ ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ በብዙ ሂደቶች ማለፍን ይጠይቃል። እነዚህ ሂደቶች በተለያዩ ወቅቶች የሚከሰቱ ለውጦችን የሚያካትቱ ናቸው። ስለሆነም እርግዝና ከተረጋገጠበት ጊዜ ጀምሮ የሚከሰቱ አካላዊ እና ስሜታዊ ለውጦችን ክስተት በንቃት በመከታተል መረዳት አስፈላጊ ነው።

በእርግዝና ጊዜ በአንዲት ሴት ሕይወት ውስጥ ብዙ አካላዊና ስነ ልቦና ለውጦች ይከሰታሉ። በእሷ ላይ የተከሰቱት ለውጦች ደግሞ በራሷ ላይና በባለቤቷ ላይ ተጽዕኖ ማድረጋቸው አይቀሬ ነው። አንዳንድ ጊዜ እነዚህ ለውጦች ከሚገመተው በላይ በመሆን ለእርጉዟ ሴትና ለጽንሱ ሁለንተናዊ ጤንነት ችግር ሊሆኑና ለባለትዳሮች አጠቃላይ ግንኙነት የአለመግባባት ምክንያቶች በመሆን ለግጭት እንዲጋለጡ ሊያደርጓቸው ይችላሉ። በዚህ ሂደት ተፈጥሯዊ ለውጦች መኖራቸው አይቀሬ ነው፡፡ ተፈጥሯዊ ለውጦች ሲከሰቱ ደግሞ በጥንዶቹ ግንኙነት ላይ ተጽዕኖ ማሳደራቸው አይቀሬ ሲሆን የተጽዕኖው ዓይነት እንደ ሰዎቹ ዝግጅት፣ ለተፈጠረው ለውጥ እንደሚሰጠው ምላሽና እንደ የግለሰቡ ሁኔታ የተለያየ ነው፡፡

ከሚከሰቱ ለውጦችና ችግሮች መካከል እርግዝናው ከተከሰተ ከጥቂት ሳምንታት ጀምሮ የማቅለሽለሽና የማስታወክ እንዲሁም የራስ ምታት እና የሆድ ድርቀት የመሳሰሉት ችግሮች ቀዳሚ ክስተቶች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የዚህ ሁኔታ መከሰት ተፈጥሯዊውና ዋናው መነሻ በእርግዝና ጊዜ በልጁና በእንግዴ ልጅ አማካኝነት የሚፈጠሩ የሆርሞን ንጥረ ቅመሞችና ሌሎች ምክንያቶች ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- የእርጉዟ ሴት ስነ ልቦናዊ አቋም፣ የአካባቢው ባህልና ልማድ ሁሉ ለለውጡ መፈጠር ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ።

በእርጉዝ ሴቶች ላይ የሚፈጠሩ ሕመሞችና ክስተቶች የተለያዩ ቢሆኑም በአብዛኛዎቹ እርጉዝ ሴቶች ላይ በመፈጠር ከሚታወቁ የሕመም ስሜቶች መካከል አንደኛው በማለዳ ጊዜ ከእንቅልፋቸው እንደ ተነሱ የሚታይባቸው የማቅለሽለሽና የማስታወክ ሕመም ነው። ሁኔታው ጠዋት ብቻ ተከስቶ የሚያበቃ ሳይሆን በሰአታት ልዩነት በተደጋጋሚ ሊታይ የሚችል ክስተት ነው። ይህ ያልለመዱት ስሜት በተደጋጋሚ ሲከሰት እንግዳ የሆነ ንግግር፣ ድርጊትና እንቅስቃሴ የመሳሰሉ ነገሮች ሊታዩ ስለሚችሉ እርጉዝ ሚስቶች እንዲሁም ባሎቻቸው እንዲህ ዓይነቱን ስሜት ሊረዱትና እንደሚገባ በመቆጣጠር ጊዜውን በሰላም ለማሳለፍ የየበኩላቸውን ጥረት ሊያደርጉ ይገባል።

ሌላው በእርግዝና ጊዜ በተለያዩ መንገዶች የሚገለጹ ችግሮች አሉ፡፡ ብዙውን ጊዜ ከሚከሰቱት ሁኔታዎች መካከል አንዳንድ ነገሮችን የመጥላት ወይም የመውደድ ስሜቶች ሊጠቀሱ ይችላሉ። በተደጋጋሚ ከተደመጡትና ከሚታዩት መካከል የምግብ

ሽታ መጥላት ወይም መፈለግ ተጠቃሽ ነው፡፡ አንዳንዶች ጣፋጭ ምግቦችን ሲወዱ ሌሎች የመጥላት ሁኔታ ይታይባቸዋል። ሌላው የተለያዩ ሽታዎች ለምሳሌ ሽቶ፣ ቤንዚን፣ ሰንደል፣ የሰው ጠረን፣ ባልተለመደ ሁኔታ በጣም የመጥላት ወይም በጣም የመውደድ ዝንባሌ ሊፈጠርባቸው ይችላል። ወይንም ከዚህ የተለዩና ያልተለመዱ ክስተቶች ሊያጋጥሙ ይችላሉ፡፡ ባለቤቴ የመጀመሪያ ልጃችንን ስታረግዝ ካጋጠሙኝ ክስተቶች አንዱ በጣም የምትወደውንና ራሷ የገዛችልኝን ሽቶ በመጥላቷ ምክንያት ሽቶ ሳልጠቀም የተወሰኑ ወራቶች እንዳሳልፍ መገደዴን በምሳሌነት ልጠቅሰው እችላለሁ።

እርግዝና ሲከሰት ሊመገቡት የማይችሉትን ነገር የመፈለግ ሁኔታ በአንዳንድ እርጉዝ ሴቶች ላይ ይታያል። በእርግዝና ወቅት አልፎ አልፎ የሚፈልጉት የምግብ ዓይነት ጨርሶ ሊመገቡት የማይገባ፣ ሊመገቡት የማይችሉት፣ ጽዳቱ አስተማማኝ ያልሆነ፣ ለጤንነታቸው አስጊ የሆነ፣ ለምግብነት ያልዋለና መዋል የሌለበት፣ ከአቅም አኳያ ሊገኝ የማይችል፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ፈጽሞ ሊገኝ የማይችል የምግብ ዓይነት ይሆናል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ፍላጎት ያላቸው እርጉዞች የፈለጉትን ባላገኙ ጊዜ የስሜትና የጸባይ መቀያየር ይፈጠርባቸዋል፡፡ የፈለጉትን ስላላገኙ ለግጭትም ሊጋበዙ ይችላሉ። ባሎች በእርጉዝ ሚስቶቻቸው ፍላጎት ሊናደዱ፣ የሚስቶቻቸውን ፍላጎቶች ባለማሟላታቸው የበደለኝነት ስሜት ሊፈጠርባቸውና ብዙ ዋጋ ከፍለው ለሚስቶቻቸው ያቀረቡት ነገር ደግሞ እርጉዝ በሆኑት ሚስቶች ዘንድ አስቀድሞ የነበረው ፍላጎት በመጥፋቱ ምክንያት ሳይመገቡት ወይም ሳይጠቀሙበት ሲቀሩ ይበልጥ የመናደድና ለግጭት የመነሳት አጋጣሚም ሊከሰት ይችላል፡፡ ባሎች ወደ ፊት ማድረግ ላለባቸው እርዳታና ድጋፍም ተነሳሽነታቸውን ሊያጠፉና በትዳር ግንኙነታቸው መካከል ክስተቱ የአለመግባባትና የግጭት መፈጠር ምክንያት ሊሆን ይችላል።

ባሎችም ሆኑ እርጉዝ ሴቶች ልብ ሊሉት የሚገባ እርጉዝ ሴቶች ብዙውን ጊዜ ተጨማሪ ምግብ ሊያምራቸው የሚችለው ለምንድን እንደ ሆነ ነው? ተጨማሪ ምግብ ሊያምራቸው የሚችለው በሰውነታቸው ውስጥ አይረን የተባለው ንጥረ ነገር እጥረት ሲያጋጥማቸው ነው፡፡ ለዚህም እንደ ተጨማሪ ምግብ ሊያገለግሉ የሚችሉ ቫይታሚኖች በየቀኑ ሊወስዱ ይገባቸዋል። የእርግዝናው ጊዜ በዛ ያሉ ወራትን እስኪያስቆጥር ምግብ የማይወስዱና የሚታመሙ ነፍሰ ጡር ሴቶችም ያጋጥማሉ፡፡ በእንደዚህ ያለው ችግር ሳቢያ ለተረገዙት ልጆች የሚተርፍ የጤና መታወክ ሊፈጠርም ይችላል፡፡ ስለዚህ በተለያዩ የሕክምና ዘዴዎች ምግብ የማስጠላቱ ስሜት እንዲወገድና እናቶችም ሆኑ ጽንሱ የዳበረ ሰውነት እንዲኖራቸው በመርዳትና የጤና ሁኔታቸውን በማሻሻል ጤነኛ ልጅ እንዲወለድ ለማድረግ ወደ አቅራቢያ የሕክምና ቦታ መሄድ ይጠበቅባቸዋል።

ሌላው በእርግዝና ወቅት ባሉ ነፍሰ ጡር ሴቶች ላይ ከሚከሰቱ ችግሮች አንዱ ድብርት (መደበት) በመባል የሚታወቀው ነው። በውስጣቸው የሚፈጠረው የሆርሞን





ለውጥ፣ የሚኖሩበት ሁኔታ፣ ከትዳር አጋራቸው ጋር ያላቸው ሰላም የሌለው ግንኙነት፣ የቤተሰብ ድጋፍ ማጣት፣ የገንዘብ (ፋይናንስ) እጥረት፣ በየጊዜው ከሕክምና ቦታ የሚሰሟቸው መጥፎ ዜናዎች የሚፈጥሩባቸው ጫና እንዲሁም ከአሁን በፊት ያማቸው የነበረ በሽታ ያሳደረባቸው አሉታዊ ተጽዕኖ ተደማምረው ድብርት በመባል የሚታወቀው ችግር እንዲከሰትባቸውና እንዲባባስ ሊያደርጉ ይችላሉ።

ድብርት (መደበት) የሚባለው በተለምዶ ዛሬ ደብሮኛል ወይም ስሜቴ ጥሩ አይደለም እንደምንለው አይደለም። በቀናቶች፣ በሳምንታትና በወራት ሊቀጥል የሚችል ምልክቱም የደስታ መራቅ፣ የኃዘንና ለቅሶ መብዛት፣ የምግብ ፍላጎት መቀነስ (መጥፋት) ወይም ከመጠን ባለፈ የመብላት ችግር፣ እንቅልፍ ማጣትና የእንቅልፍ መብዛት፣ ከመጠን ባለፈ የሰውነት ክብደት መጨመርና የክብደት መቀነስ፣ ብቸኝነትን መምረጥ፣ ለሌሎች ነገሮች ፍላጎት፣ ተነሳሽነትና አቅም ማጣት፣ ከፍተኛ የሆነ ማማረር የመሳሰሉ ክስተቶች የድብርት (የመደበት) በሽታ መገለጫዎች ናቸው።

ይህ ከፍተኛ የሆነ የድብርት (የመደበት) ችግር በባለትዳሮች መካከል ሰላማዊ የሆነ ግንኙነት እንዳይኖር በማድረግ ይበልጥ አለመግባባትን ሊያባብስ ይችላል። ባሎች ከመቼውም ወቅት በበለጠ ሚስቶችን ልንረዳቸው የሚገባን በዚህ ጊዜ ነው። ባለቤቴ የመጀመሪያ ልጃችንን አርግዛ የመጀመሪያውን የእርግዝና ክፍለ ጊዜ ሶስት ወራት ካሳለፈች በኋላ ከነበራት የተደበላለቀ ስሜት መረጋጋት ስትጀምር ርዕሱ **"እነዚያ ሶስት ወራቶች"** የሚል አንድ ግጥም ጽፌላት ነበር። ይህን ያደረኩበት ምክንያት ለጋራ ልጃችን ብቻዋን ላለፈችባቸው የተለያዩ እንግዳ ስሜቶች እውቅና ለመስጠት እንዲሁም በዚያ ጊዜ ሁሉና ወደ ፊትም አብሬሽ ነኝ የሚል መልዕክት ለማስተላለፍ ነበር፡፡ በዕለቱ የምትወደውን የምግብ ዓይነት አብስዬና አዘጋጅቼ ከምትወደው አበባ ጋር ስጦታ አድርጌ በማቅረቤ የተሰማት የደስታ ስሜት ቀላል አልነበረም። በአጠቃላይ ይህን ያደረግሁት "ውድ ባለቤቴ ይገባሻል!" ለማለትና ለማበረታታ ፈልጌ ነው።

## III. በእርግዝና ወቅት ለሚፈጠሩ ችግሮች መፍትሔዎች

### 1. መረዳት፡- በእርግዝና ወቅት የሚፈጠሩ ለውጦችን መረዳት

በእርግዝና ወቅት የሚጠበቅና ያልተጠበቀ ለውጥ ሊከሰት እንደሚችል በማወቅ ራስን ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው። የእርጉዝ ሴት ሰውነት የተለያዩ ለውጦችን ያስተናግዳል። ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ ያክል፡- ከእርግዝና ጋር ተያያዥነት ያላቸው የተለያዩ የሕመም ስሜቶችና ከእርግዝና በፊት የነበሩ የሕመም ስሜቶች በእርግዝና ወቅት መባባስ፣ የሰውነት ክብደት መጨመር፣ የሙድ መቀያየር፣ የፍላጎት መለዋወጥ፣ ለነገሮች ፍላጎት ማጣት፣ ድካምና ድብርት የመሳሰሉ በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው።

እነዚህን ለውጦች እርጉዟ ሴትና የትዳር አጋሯ ሊረዷቸውና እርስ በርስ ሊረዳዱ ይገባል። የተለያዩ ለውጦች እንደሚፈጠሩ አስቀድሞ ማወቅ በነገሮች ቶሎ ተስፋ እንዳንቆርጥና በመካከላችን የሚፈጠሩ አለመግባባቶችና ግጭቶች ለትዳራችን ችግር

እንዳይሆኑ እንድንጠነቀቅ ይረዳናል። አሁን የቴክኖሎጅው እድገት ብዙ ነገሮችን አቅልሎልናል፡፡ ለማወቅ በምንፈልገው አቅጣጫ ነገሮችን ለማወቅ እንድንችል ብዙ መንገዶችን ፈጥሮልናል። አንድ ምሳሌ ለመጥቀስ ያክል፡- ባለቤቴ የመጀመሪያ ልጃችንን እርጉዝ በነበርችበት ወቅት "Baby Center" በመባል የሚታወቀውን አፕሊኬሽን በእጅ ስልኬና በአይፓድ ላይ በመጫን የምታልፍበትንና የሚሰማትን ስሜት እንዲሁም የልጃችን እድገትና ዕድሜ የሚያመጣውን ለውጥ በየቀኑ በመከታተል ይበልጥ እርሷን መረዳትና በምችለው መንገድ ሁሉ መርዳት እንድችል ጠቅሞኛል። ከእርግዝና ጋር በተያያዘ የሚመጡ ለውጦችን ለመረዳት የተለያዩ መጽሐፍትን ማንበብ፣ ልምድ ያላቸውን ሰዎች መጠየቅና ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የቪዲዮ መልዕክቶች መስማትና መመልከትም ጠቃሚ ነው።

በእርግዝና ወቅት በተደጋጋሚ የሕክምና ባለሙያ የምንጠይቅበት ጉዳይ ቢኖር በእርግዝና ወቅት የግብረ ስጋ ግንኙነት ማድረግ ይቻላል ወይ? እስከ ስንተኛው ወር ድረስና በጽንሱ ላይ የሚፈጥረው አሉታዊ ተጽዕኖ የለም ወይ? የመሳሰሉ ጥያቄዎች የተለመዱ ናቸው። በእርግዝና ተጽዕኖ ምክንያት የግብረስጋ ግንኙነት ፍላጎት መጥፋት ወይም በአንዳንዶች ላይ ፍላጎትን ከፍ የማድረግ ክስተት ሊፈጠር ይችላል። በእርግዝና ወቅት በሐኪም የተለየ ትዕዛዝ ከሌለ በስተቀር የግብረ ስጋ ግንኙነትን የሚከለክል ምንም ግልጽ ምክንያት የለም። ባሎች እርጉዝ የሆነችው ሚስት ምቾት እንዲሁም ሚስቶች የባሎችን ፍላጎት ግንዛቤ ውስጥ በመከተት አቅምን አጠራቅሞ የግብረ ስጋ ግንኙነትን መፈጸምና አንዱ ሌላውን ማርካት በእርግዝና ወቅትም ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ የባልና የሚስት ኃላፊነት ነው።

## 2. መጣር፡- ድብርትን ለመቀነስ ጥረት ማድረግ

በእርግዝና ወቅት ከሚፈጠሩ ክስተቶች አንዱ ድብርት መሆኑን አስቀድሞ በሚገባ ዳስሰናል። ድብርት የሚፈጠርባቸው ምክንያቶች የተለያዩ ናቸው። ድብርትን የሚያመጡና የሚያባብሱ ምክንያቶችን በመረዳት ችግሩን ለመቀነስ ጥረት ማድርግ አስፈላጊ ነው። ድብርትን የመቀነስ ሂደት በተለይ በትዳራችን መካከል ያለን መልካም ያልሆነ ግንኙነት በጋራ ተቀምጠን በመነጋገርና በይቅርታ በማስተካከል፣ የሚያስጨንቁንን ነገሮች እየቀነስን እግዚአብሔር ባደረገልን ደስ መሰኘትን በመለማመድ፣ በሌለን ነገር ከማዘንና ከመቆዘም ይልቅ በእግዚአብሔር በመታመን ባለን ነገር መደሰትና ማመስገንን በመምረጥና በመለማመድ ሊከናወን ይችላል። *"እርሱ ስለ እናንተ ያስባልና የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት"* /1ኛጴጥ 5: 7/።

እንደ ክርስቲያን ባለትዳር በእርግዝና ወቅት የሚፈጠርን ድብርት ለመቀነስና ለማስወገድ ባለትዳሮች የእግዚአብሔርን ቃል በማመን በእግዚአብሔር ላይ ማረፍን ሊለማመዱ ይገባል። *"እንግዲህ ምን እንበላለን? ምንስ እንጠጣለን? ምንስ እንለብሳለን? ብላችሁ አትጨነቁ፤ ይህንስ ሁሉ አሕዛብ ይፈልጋሉ፤ ይህ ሁሉ እንዲያስፈልጋችሁ የሰማዩ አባታችሁ ያውቃልና።"* /ማቴ 6: 31-32/





## 3. መዘጋጀት፡- ሁልጊዜ ለመንከባከብና ለመርዳት መዘጋጀት

በእርግዝና ወቅት የሚፈጠሩ የተለያዩ ለውጦችን መረዳት የመጀመሪያው የመረዳዳት እርምጃ ነው፡፡ ዓላማው ደግሞ የበለጠ ለመረዳዳት ነው። ባሎች በእርግዝና ላይ ያሉ ሚስቶቻችንን ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ያሉበትን ሁኔታ ቶሎ ልንረዳና በሚያስፈልጋቸው ሁሉ እንደ አቅማችን ልንንከባከባቸው ይገባል። አካላዊ ጤንነትና ጥንካሬ እንዲኖራቸው የተመጣጠነ አመጋገብ እንዲመገቡ ማድረግ አስፈላጊ ነው። የተመጣጠነ ምግብ ለአንዳዶቻችን ከአቅም አንጻር ከባድ ሊሆን ይችላል። አንድ ጊዜ ሚስቱ እርጉዝ ሁና ለሕክምና ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ይዞ የሄደና እርጉዞች ምን ዓይነት ምግብ መመገብ እንዳለባቸው የሚጠቅስ ጽሑፍ ግድግዳ ላይ ባለቤቱ ከተቀመጠችበት በስተጀርባ ተለጥፎ ያዬ ወንድም ሚስቱን **"ወደ ኋላ ዞር ብለሽ እንዳትመለከችና እንዳታነቢ የተለጠፈው የስህተት ትምህርት ነው"** አልኳት ብሎ አጫወተኝ። እንዲህ እንዲናገር ያደረገው ያ ወንድም ለእርጉዝ ሴት የሚታዘዘውን የተመጣጠነ ምግብ ለማቅረብ የገንዘብ አቅም ስላልነበረው ብቻ ነው። አቅምህ በፈቀደ መጠን ለእርጉዟ ሚስትህና ለሚወለደው ልጅህ የምትችለውን ለማቅረብ ራስህን ማዘጋጀት ይጠበቅብሃል። በአግባቡ በመተኛት በቂ እንቅልፍ እንዴት ማግኘት እንዳለባቸው፣ ከባድ ሥራ መሥራትንና ከባድ እቃ ማንሳትን እንዲያስወግዱ፣ ለእርጉዝ ሴት የሚመች አለባበስ እንዲለብሱ፣ ተጨማሪ ቫይታሚን የሚያገኙባቸው ሁኔታዎች እንዲስተካከሉ ባሎች አስበንበት ሚስቶቻችንን መርዳት ኃላፊነታችን ነው፡፡ ሚስቶችም ለራሳችሁና ለውድ ልጃችሁ ሲባል ሰውነታችሁን ልትከባከቡ ይገባል።

**በእርግዝና ወቅት እርጉዝ ሚስቶች ሰፊ ልብስ ሲያስፈልጋቸው ባሎች ደግሞ ሰፊ ልብ ሊኖራቸው ይገባል።**

ክርስቲያን የሆነች እርጉዝ ሴት መንፈሳዊ እንክብካቤም ያስፈልጋታል። የሰው ሁለንተናዊ እረፍትና ሰላም የመንፈሳዊ፣ ስነ ልቦናዊና አካላዊ ፍላጎትን መሟላት ያጠቃልላል፡፡ ሰው ሁለንተናዊ እንክብካቤ እንደሚያስፈልገው በመርሳትና አንደኛው የሰው ፍላጎት መሟላት ላይ ብቻ ትኩረት በማድረግ ሌላውን ችላ ማለት ተገቢ አይደለም! ነፍሳችን ከእግዚአብሔር ጋር በመንፈስ መገናኘትና እግዚአብሔርን ማምለክና መፈልግ ዋና ተግባሯ ስለሆነ ፍላጎቷ ቸል እንዳይባልባት ባሎችና እርጉዝ ሚስቶች በእግዚአብሔር ቃል፣ በጸሎት፣ በቅዱሳን ኅብረት መንፈሳዊ እንክብካቤ እንዲያገኙ ማድረግ ያስፈልጋል። እርጉዝ ሚስቶች ቀድሞ ከእርግዝና በፊት በነበራቸው ዓይነት መንፈሳዊ እንቅስቅሴዎች ላይ መሳተፍ ሊደከማቸው፣ ላይመቻቸውና ፍላጎት ሊያጡ ይችላሉ፡፡ ባሎች የቤተሰቡ ካህንና መሪ መሆናችንን ሳንዘነጋ ይበልጥ ቃሉን በማንበብ፣ በመጸለይና ከቅዱሳን ጋር በመገናኘት መንፈሳዊ በረከትና መነቃቃት እንዲያገኙ ምቹ ሁኔታዎችን ልንፈጥርላቸው ይገባል።

እርጉዝ ሚስቶች በእርግዝና ምክንያት ከሚፈጠሩባቸው የተለያዩ ለውጦች የተነሳ በስነ ልቦናቸው እንደ በፊቱ ላይሆኑ ይልቁንም የተለያዩ ስሜቶች ድባብ፣ ፍርሃት፣ ድብርት፣ ተስፋ መቁረጥ፣ ጭንቀትና መደናገጥ ሊፈራረቅባቸው ይችላል። በዚህ ወቅት ጠንካራ ስነ ልቦና እንዲኖራቸውና ጊዜያዊ መጥፎ ስሜት ሲሰማቸው አግባብነት የሌለው ውሳኔ በራሳቸው፣ በጽንሱና በትዳር ግንኙነታቸው ላይ በመወሰን ከፍተኛ ችግር እንዳይፈጥሩ ልንረዳቸውና እንዲህ ዓይነቱን ስሜት እንዴት ተቋቁመው ማለፍ እንደሚችሉ በተለያየ አቅጣጫ አብሮነታችንና አጋርነታችንን ልናሳይ ይገባል። እርጉዝ ሚስቶችም የሚሰማቸው ስሜት ጊዜያዊ ነውና ለሚያልፍ ጉዳይ ቀጣይነት ያለው ችግር እንዳይፈጠር ጥንቃቄ ልታደርጉ ይገባል።

## 4. ማገዝ፡- የሐኪም እርዳታና ክትትል እንዲያገኙ ማገዝ

ከላይ የተዘረዘሩትና ሌሎችም በእርጉዝ ሴት ላይ ሊፈጠሩ የሚችሉ አካላዊና ስነ ልቦናዊ ችግሮች ይበልጥ የሚረጋገጡት በሕክምና የምርመራ ውጤቶች እንደ ሆነ አጠንክሬ ላስገነዝብ እወዳለሁ። ከልምድ የምናያቸውና የምንገምታቸው ጉዳዮች ቢኖሩንም ግምታችንን ሁሉ ግን ትክክል ነው ለማለት አያስደፍረንም። የሕክምና ባለሙያዎችም የሕመሙን ሁኔታ ለማጣራትና ለማረጋገጥ ሲሉ የተለያዩ የምርመራ መሳሪዎችንና ዘዴዎችን ሲጠቀሙ የምናየው በግምት ምንም ነገር ማረጋገጥ ስለማይቻል ነው። ደግሞም መሳሪያን መጠቀም ብቻ ሳይሆን ከችሎታቸው በላይ ሲሆን በጉዳዩ ስፔሻላይዝድ ወደ አደረገ የተሻለ ባለሙያ በመላክ (ሪፈር በማለት) እርግጠኛ የምርመራ ውጤትና ትክክለኛ መድኃኒት እንድናገኝ ጥረት ያደርጋሉ።

አንዲት እርጉዝ የሆነች ሴት ቋሚ የሆነ የሐኪም ክትትል ስሚያስፈልጋት በአካባቢዋ ወደሚገኝ ሆስፒታል፣ ክሊኒክና ጤና ጣቢያ በመሄድ አስፈላጊውን የሕክምና ክትትል ልታገኝ ይገባታል። ከቋሚው የሐኪም ክትትል በተጨማሪ እንደሚሰማት እንግዳና የሕመም ስሜት በአፋጣኝ ወደ ሕክምና ቦታ በመሄድ እራሷንም ሆነ በማህጸኗ የተሸከመችውን ጽንስ ሊያጋጥም ከሚችል ከፍተኛ ችግር ልትታደግ ይገባታል። በእንደዚህ ዓይነት ወቅት ባሎችም በግልጥነት ከትዳር አጋር ጋር ተነጋግረን አስፈላጊውን እርምጃ በመውሰድ አጋርነታቻንን ማሳየት አለብን። ሁኔታዎች ከተመቻቹና ዕድሉ ከተገኘ የሐኪም የክትትል ቀጠሮ ጊዜ ባሎች አብረን በመሄድ በባለቤታችንና በጽንሱ ላይ እየተፈጠረ ያለውን ለውጥ በጋራ ለመረዳት መሞከር ለእርጉዟ ሚስት የሚሰጠው ስነ ልቦናዊ ድጋፍ ከፍተኛ ነው።

በሐኪም ክትትል ወቅት እንደ አስፈላጊነቱ በሐኪሙ የሚታዘዙ መድኃኒቶችን ያለሐኪም ፈቃድ ተከታታይነቱን ማቋረጥና ፈጽሞ ማቆም ለእርጉዟ ሴትም ሆነ ለጽንሱ የሚያመጣው አሉታዊ ተጽዕኖ ቀላል አይደለምና ጥንቃቄ ልናደርግ ይገባል። በዚህ ወቅት ባሎች በየጊዜው የሚወሰዱ መድኃኒቶችን ሚስቶች እንዲወስዱ የመከታተል፣ የማስታወስና የማበረታታት ጥረት ሊያደርጉ ይገባል። በሐኪም የታዘዘላቸውን





መድኃኒት መውሰድ ብቻ ሳይሆን ከሐኪም ትዕዛዝ ውጭ እንዲሁ በራሳቸውና ከሌሎች ሰዎች ልምድ በመስማት መድኃኒቶችን አለመውሰድ ኃላፊነታቸው ነው፡፡ ይህን ካላደረጉ ሌላ የከፋ ችግር ያጋጥማቸዋል። ማንኛውንም ዓይነት መድኃኒት ከመውሰዳቸው በፊት የሚከታተላቸውን ሐኪም ማነጋገርና ፈቃድ ማግኘት ይኖርባቸዋል።

## 5. መፍጠር፡- ከሌሎች እርጉዝ ሴቶች ጋር እንዲደጋገፉ ምቹ ሁኔታን መፍጠር

ተመሳሳይ ጾታ፣ የዕድሜ ክልል፣ ፍላጎት፣ ልምድና ዓላማ ያላቸው ሰዎች ሊያገናኟቸው የሚችሉ ብዙ የጋራ ነገሮች ስለሚኖሯቸው የመፈላለግ፣ የመቀራረብና አብሮ በጋራ ልምድ የመካፈል ከፍተኛ ጉጉት ሊኖራቸው ይችላል። ይህ ማለት ሁሉም በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ያሉ ነፍሰ ጡር ሴቶች የመቀራረብና አብሮ ከመሰሎቻቸው ጋር የመሆን ፍላጎት ይኖራቸዋል ወይም ከሁሉም በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ካሉ ነፍሰጡር ሴቶች ጋር የሚደረግ ህብረት ገንቢ ነው ማለት አይደለም፡፡ አልፎ አልፎ የተለየ መጥፎ የሆነ ባሕርይ ያላቸው ማለትም በቅንዓት፣ በራስ ወዳድነትና አብሮ መሆንን በመጥላት ችግር ሊፈጥሩ የሚችሉ እርጉዝ ሴቶች ያጋጥማሉ። ስለዚህ ከሌሎች እርጉዝ ሴቶች ጋር የመደጋገፍ ኅብረት ለመፍጠር የሚደረገው ጥረት በጥንቃቄና በማስተዋል ሊደረግ ይገባል፡፡ ይህን ጥንቃቄ በቸልተኝነት ሳያዩ እርጉዝ ሴቶች የሚሰማቸውን የደስታ፣ የሐዘን፣ የሕመምና ሌሎችን ገጠመኞቻቸውን ለማውራት በጋራ ወጣ ብለው ሊጫወቱ፣ ሊዝናኑና የሰውነት እንቅስቃሴ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ በዚህ ሂደት አብረው መሆናቸው መንፈሳዊ ነገርን ለመከፋፈል እንዲሁም በሚወልዱበት ወቅት የሚያስፈልጉ ጉዳዮችን በመነጋገር ለማዘጋጀት ይጠቅማቸዋል።

እንዲህ ዓይነቱን ጥረት በማድረግ ስሜቶቻቸውን የሚረዱ ሰዎች ለማግኘት፣ እርስ በርስ ለመረዳዳትና ሕብረትን ለመፍጠር በመጣር ሕብረቱ እንዲፈጠር ተነሳሽነቱን መውሰድ፣ ዋጋ በመክፈል አንዱ ሌላው የሚጠቅምበትንና የሚረዳበትን መንገድ ማመቻቸትና ግንኙነቱን ተጠንቅቆ መያዝ ተገቢ ነው። የእርጉዝ ሴቶች በጋራ በመሆን እርስ በርስ የመጠያየቅና የመረዳዳት ባህል ብዙ የተለመደ ባይሆንም ነገር ግን ቢለመድና ለጋራ ጥቅም አብሮ የመሆን ዕድሎችን ቢያገኙ ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው። እንዲህ ዓይነቱ እርምጃ በአንቾ ተነሳሽነት ሊወሰድ ይችላልና የምታውቂያቸውን እርጉዞች ቀንና ሰአት በመወሰን በጋራ ቀለል ያለ ምግብ በማዘጋጀት አብሮ የመመገብ፣ የመጫወት፣ ስሜትን የመግለጽና ልምድን የመከፋፈል ብሎም በጋራ የሰውነት እንቅስቃሴ የማድረግ ፕሮግራም ማዘጋጀት መልካም ነው።

## 6. መጸለይ፡- እያንዳንዱን እንቅስቃሴና ውሳኔ በጸሎት ማጀብ

እግዚአብሔርን ማምለክ፣ እርሱን ማስቀደምና በእርሱ መተማመን በምንም ሁኔታ ሊለወጥ የማይገባው የክርስቲያን ተግባር ነው። እንደ መንፈሳዊ ሰው በትዳር ጉዟችን

ለእርጉዟ ሚስት፣ ለጽንሱ፣ በተለያየ ጊዜ ለሚፈጠሩ ለውጦችና ከስተቶች ብሎም ለምንሰማው መጥፎ የሕክምና የምርመራ ውጤት፣ በምርመራ ሂደቱ ሊፈጠሩ ለሚችሉ ስህተቶች፣ ከተባለውና ከተባለብን በላይ ታላቅ የሆነ አምላክ እንዳለን በመረዳት ዘወትር በፊቱ በጸሎት መቅረብ ቀዳሚ ኃላፊነታችን እንጂ ምርጫ ውስጥ የሚገባ ጉዳይ አይደለም። ከእያንዳንዱና ከማንኛውም እርምጃ በፊትና በኋላ ሁሉንም በስልጣኑ ወደሚቆጣጠረውና መልካም ወደ ሆነው አምላክ መጸለይ ጥቅም እንጂ ምንም ዓይነት ጉዳት የለውም። ብዙ ጊዜ በክርስትና ሕይወታችን ዕድሜ እየጨመርን፣ እያወቅንና እየበሰልን የመጣን በመሰለን ዘመን ወይም በተለያየ ምክንያት ጊዜ የሌለን ሰዎች የሆንን ሲመስለን ስለጸሎት አስፈላጊነት ያለን አቋም የላላ ይሆናል፡፡ ጸሎትም እየቀነሰን እንመጣለን፡፡ መጸለይ የጀማሪ ክርስቲያን ተግባርና ምቹ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ ብቻ የምናደርገው የሐይማኖት ስርዓት አይደለም። ጸሎት ማለት ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር እንደመሆኑ በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ፊት ስንቀርብ እግዚአብሔር የተፈጠሩ ሁኔታዎችን በመለወጥ አሊያም ለእኛ ጸጋውን በመስጠት ከሁኔታዎች በላይ ጠንካሮች እንድንሆን ጸጋውን ያበዛልናል፡፡ ይህም በቤታችን አለመግባባትና ግጭት እንዲፈጠር የሚያደርጉ ተግዳሮቶችን በሳል በሆነ የተረጋጋ ማንነት በማሸነፍ እንድንሻገርና ከእግዚአብሔር ዘንድ በሆነ ሰላም ትዳራችን ያረፈ እንዲሆን ያስችለናል /1ኛሳሙ 1፡ 10-18፤ መዝ 34፡ 1-6፤ ዕብ 4: 16/፡፡





## ለጥንዶች በግላቸውና በቡድን ለማጥናት የሚረዷቸው የውይይት ጥያቄዎች

## የምዕራፍ አስራ አምስት (15)

## የውይይት ጥያቄዎች

1. የእርግዝናን ምንነት ባግባቡ ተወያዩበት፡፡
2. በእርግዝና ወቅት በእርጉዝ ሴቶች /ሚስቶች/ ላይ ሊፈጠሩ የሚችሉ የተለያዩ ለውጦችና የሚፈጥሯቸው አሉታዊና አዎንታዊ ተጽዕኖዎችን በመጥቀስ ተነጋገሩ፡፡
3. በእርግዝና ወቅት ሊፈጠሩ የሚችሉ የግጭት መንስኤዎችን በመዘርዘር በሰፊው ተወያዩ፡፡
4. በእርግዝና ወቅት ለሚፈጠሩ የግጭት መንስኤዎች ምን መደረግ አለባቸው ትላላችሁ?
5. በእርግዝና ወቅት የገጠማችሁን አዲስ እንግዳ ልምምድ በመጥቀስና እንዴት ባለመልኩ እንደተሻገራችሁት ልምድን በመከፋፈል ተወያዩበት፡፡
6. እርጉዝ ሚስቱን ለመርዳት ባል ምን ማድረግ እንዳለበት የተማርከውን አዲስ ነገር ለሚስትህ (ለጎብረቱ) አካፍል።

# ምዕራፍ አስራ ስድስት(16)

# ያልተፈለገና ያልታሰበ እርግዝና

## 1. ያልተፈለገና ያልታሰበ እርግዝና ምንነት

ያለተፈለገና ያልታሰበ እርግዝናና ወሊድ የሚለውን አሳብ ከብዙ አቅጣጫ ማየት ተገቢ ነው። ይህ ችግር ከሚያጋጥማቸው መካከል አዲስ ተጋቢዎች በቅድሚያ ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ በተለያየ ምክንያት ከተጋቡ በኋላ የተወሰኑ ዓመታትን ሳይወልዱ መቆየት እየፈለጉ እንደ ተጋቡ ወዲያውኑ አርግዘው የሚወልዱ ባለትዳሮች የችግሩ የመጀመሪያ ሰለባዎች ናቸው። ገና እንደ ተጋቡ በመጀመሪያው የግብረ ስጋ ግንኙነት የማርገዝ ዕድል የሚገጥማቸው ባለትዳሮች ልጅ ለመውለድ ምንም ዝግጅት ሳያደርጉ ልጅ የመውለድና የማሳደግ ኃላፊነት ውስጥ ስለሚገቡ የዚህ ችግር ሰለባዎች ሆነው በትዳራቸው ሰላም የሚጠፋበት ሁኔታ ይከሰታል። በእርግጥ እንዲህ ዓይነት ክስተት አንዳንድ ባለትዳሮችን ሊያስደስታቸው ይችላል፡፡ ነገር ግን ሌሎች ደግሞ በእንዲህ ዓይነቱ ገጠመኝ ከልብ ሊያዝኑ ይችላሉ።

በትዳር ሕይወት የተወሰነ ዘመን ያሳለፉ እና ልጆች የወለዱ ባለትዳሮችም ያልታሰበና ያልተፈልገ እርግዝና ሲያጋጥማቸው በዚህ ችግር ይፈተናሉ፡፡ በትዳር በቆዩ ባለትዳሮች ዘንድ እርግዝና ድንገት ሲከሰት በሚፈልጉትና አመች ነው ብለው በሚያስቡት ጊዜ የተከሰተ ባለመሆኑ፣ ሳይታሰብ ከመጀመሪያው ልጅ ጋር ተከታትሎ በቅርብ ርቀት በመከሰቱ፣ የሚፈልጉትን ጾታ ባለማግኘታቸውና ከዚህ በኋላ ልጅ መውለድ በቃን ብለው ደምድመው እያለ ሳይፈልጉ እርግዝና ያጋጠማቸው በመሆኑ በምስክርነታቸው ችግሩ የፈተናቸው መሆኑን ሲናገሩ ይደመጣሉ።

በማማከር አገልግሎት ካጋጠሙኝ በችግሩ ውስጥ ያለፉ ሰዎች መካከል ከአገባች አንድ ዓመት ያልሞላትና በትምህርት ላይ የነበረች ሴት ለማርገዝ ሳትዘጋጅ በማረገዟ የተሰማትን ስሜት በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ ይህች እህት ክስተቱ ወደፊት ተምሮ ኑሮን ለመቀየር የምትሄድበትን ጉዞ ለማደናቀፍ እንደመጣባት አሰበች፡፡ ከፍተኛ የሆነ ድብርት ውስጥ በመግባቷ ጸባይዋ እየተለዋወጠ መጣ፡፡ ከባሏ ጉዳዩን በመደበቅ ጽንሱን ለማስወጣት ውሳኔ በመወሰን እቅድ አወጣች፡፡ በዚህ ሁኔታ ላይ እያለች ነበር ይህች ሴት ምክር ፈልጋ የምክር አገልግሎት ወደምሰጥበት ቢሮ የመጣችው፡፡ በምክር አገልግሎቱ ሂደት ውስጥ በቂ ውይይት ካደረግን በኋላ ስህተት የነበረውን አሳቧን በመለወጥ ከኀዘን ይልቅ በመጸነሷ መደሰት ጀመረች፡፡ ከዚያም የወንድ ልጅ እናት ከመሆኗ ባሻገር ደስተኛ የትዳር ሕይወቷን መምራት ቻለች፡፡ በአሁኑ ወቅትም የጀመረችውን ትምህርት አጠናቃ የተሳካ ኑሮ መኖሯን በመቀጠል በትክክለኛው መንገድ ሕይወትን የመምራት ተግባራዊ ጉዞ ለሚያመጣው መልካም ፍሬ ሕያው ምስክር ነች።

ባለተፈለገና ባልታሰበ እርግዝና ወቅት የተለያዩ ስሜቶች ይፈራረቃሉ። እርግዝናው የሚከሰተው ያለፍላጎት ስለሆነ ጥንዶች ደስተኛ ከመሆን ይልቅ





የሐዘንተኛነት ስሜት፣ ጭንቀት፣ ምናልባት ከጤንነት ጋር ተያይዞ የሚፈጠር ፍርሃት፣ ድንጋጤና ሌሎች ሰዎች ሊሰጡ የሚችሉትን አስተያየት በማሰብ ድብርት ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ። ከሚፈጠርባቸው መጥፎ ስሜት የተነሳ ከማሕበራዊ ግንኙነት መራቅ/ራስን ማግለል/፣ በእግዚአብሔር ላይ ማጉረምረምና ማማረር፣ እንግዳ የሆነ ባሕርይ ለቤተሰብ አባላት ማሳየት ሊጀምሩ ይችላሉ። ከተፈጠረባቸው መጥፎ ስሜት ለመገላገል የተለያዩ የመፍትሔ አሳቦች ከማፈላለግ አኳያ በግልም ሆነ ከትዳር አጋር ጋር በጋራ ተስማምቶ ውርጃን ለመፈጸም ሊያስቡም ይችላሉ። ጽንስን ማስወረድ በማሰባቸው እንደ ገና ሌላ የበደለኝነት ስሜት ሊፈራረቅባቸውና ብሎም ለትዳራቸው የአለመግባባትና የግጭት ምክንያት ሊሆን ይችላል።

## II. ያልተፈለገ ና ያልታሰበ እርግዝናና ወሊድ ወቅት ሊወሰዱ የሚገባቸው መፍትሔዎች

### 1. መረዳት፡- በእግዚአብሔር ዘንድ አጋጣሚ እንደሌለ መረዳት

ያልተፈለገ እርግዝና በሚፈጠርበትና ልጅ በሚወለድበት ወቅት አንዱ እንደ ክርስቲያን ባለትዳር ልናስበውና ልናምነው የሚገባን ነገር ቢኖር በእግዚአብሔር ዘንድ አጋጣሚ የሚባል አለመኖሩን ነው። *"... ያልተሠራ አካሌን ዓይኖችህ አዩኝ የተፈጠሩ ቀኖቼ ሁሉ አንድ ስንኳ ሳይኖር በመጽሐፍህ ተጻፉ።"* /መዝ 139: 16/ የሚለው የእግዚአብሔር ቃል ግልጥ እንደሚያደርገው አጋጣሚ የሚባለው ለወላጅ እንጂ ለሰማያዊ አባት አይደለም!

በእግዚአብሔር ዘንድ አጋጣሚ እንደ ሌለ ማመናችን በእግዚአብሔር ዘላለማዊ እውቀት ውስጥ ተስማምተን አሜን ለባሪያዎችህ እንደ ቃልህ ይሁልን በማለት የተጸነሰውን ልጅ የእግዚአብሔር ስጦታ መሆን እንድንቀበል ይረዳናል። እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ ነው። ባለትዳሮች ከእኛ ጥንቃቄ ጉድለት የተነሳ በሚሉት መንገድ ወይም ከብዙ ወሊድ መከላከያ አምልጠው ተረግዘው ስለሚወለዱ ልጆች እግዚአብሔር ያውቃል፡፡ በእነርሱም ሕይወት ዓላማ አለው። ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ ናቸውና ሳናስብበት ልጆችን በመውለዳችን እግዚአብሔር እንደፈረደብንና ሸክም እንደ ጫነብን አድርገን ማሰብ አይገባንም።

### 2. መቀበል፡- የተፈጠረውን እውነታ አምኖ መቀበል

ያልተፈለገ እርግዝና የሚገጥማቸው ሰዎች ባልፈለጉት ጊዜ የተከሰተ ሁኔታ ከመሆኑ የተነሳ ስነ ልቦናዊ ድንጋጤ፣ ጭንቀት፣ ድብርት፣ ተስፋ መቁረጥና ደስተኛ አለመሆን ይፈራረቅባቸል፡፡ ይህ ያጋጠማቸው ሚስቶች እርግዝናቸውን ለትዳር አጋሮቻቸው ለመናገር ፍርሃትና ጭንቀት ስለሚይዛቸው መደበቅን ይመርጣሉ። እንዲህ ሊሆን አይችልም! እግዚአብሔር አያደርገውም! አንድም ቀን ያለመከላከያ የግብረ ስጋ ግንኙነት አልፈጸምንም! ... የሚሉ የተለያዩ ምክንያቶችን በመደርደር እውነታውን አምነው ከመቀበል ይልቅ መካድን በመምረጥ በራሳቸውና በጽንሱ ላይ ጉዳትን የሚያደርሱ እንቅስቃሴዎችንና ድርጊቶችን የሚፈጽሙ ሴቶች ጥቂቶች አይደሉም።

ግዛት የሚኖሩ አነስተኛ የገቢ አቅም ያላቸው ወላጆች ለልጆቻቸው የወደ ፊት ሕይወት በማሰብ ገንዘብ ለማስቀመጥ ፈቃደኛ ከሆኑ ለወላጆች በሶስት እጥፍ ድጋፍ በማድረግ የሚሠራ ድርጅት ነው። ለምሳሌ አንድ ወላጅ ለልጆቹ አንድ ሺ ዶላር ቢያስቀምጥላቸው ድርጅቱ አራት ሺ በማድረግ ለልጆቻቸው የትምህርት መርጃና ሌሎች ክፍያዎቻቸውን ይሸፍንላቸዋል። ይህንንም ሚያደርገው ወላጆች ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ለማበረታታትና ለማትጋት ነው::

ስንፍናንና አለመትጋትን ለይተን መዋጋት መቻል አለብን። ስንፍናን በትጋትና በጥረት በመለወጥ ራሳችንን፣ ትዳራችንን፣ ቤተሰባችንን ልንለውጥ በምንችልበት መንገድ የበኩላችንን ድርሻ መወጣት አስፈላጊ ነው። ባልቻልንበት ጉዳይ ላይ ደግም ሊረዱን ከሚችሉ ግለሰቦች፣ ቤተሰቦችና ድርጅቶች ጋር መልካም ግንኙነት በመፍጠር እርዳታ (ድጋፍ) ማግኘት መቻል መወሰድ ያለበት እርምጃ እንጂ ኃጢአት፣ ውርደትና ሽንፈት አይደለም።





## ለጥንዶች በግላቸውና በቡድን ለማጥናት የሚረዷቸው የውይይት ጥያቄዎች

## የምዕራፍ አስራ ስድስት (16)

## የውይይት ጥያቄዎች

1. ያልተፈለገና ያልታሰበ እርግዝናን ምንነት ግለጡ::
2. ባለተፈለገና ባልታሰበ እርግዝና ባለትዳሮች እንዳይደሰቱ የሚያደርጓቸው የተለያዩ ምክንያቶችን በመዘርዘር ተወያዩባቸው::
3. ባለተፈለገና ባልታሰበ እርግዝና በባለትዳሮች ላይ ሊፈጠሩ የሚችሉ የተለያዩ አሉታዊ ተጽዕኖዎችን በመጥቀስ ተነጋገሩ::
4. ባልተፈለገና ባልታሰብ እርግዝና ምክንያት በባለትዳሮች መካከል ለሚፈጥሩ የተለያዩ የግጭት መንስኤዎች መወሰድ ያለባቸው የመፍትሔ እርምጃዎች ምንድን ናቸው ትላላችሁ?
5. ውርጃ ምን ማለት እንደሆነ በመግለጥ ተወያዩ:: ክርስቲያን ባለትዳሮች ወርጃን መለማመድ አለባቸው ወይስ የለባቸውም ለምን? መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት በማድረግ በሰፊው ተወያዩበት::
6. ይህን ክፍል ስታነቡና ስታጠኑ የተለወጠ አስተሳሰብና ልምምድ ካለ በመግለጥ ልምድን ተከፋፈሉ::

# ምዕራፍ አስራ ሰባት(17)
# ከወሊድ በኋላ ሊፈጠር የሚችል ትኩረት የሚያሻው ለውጥ

## 1. ድህረ ወሊድ ድብርት

ድህረ ወሊድ ድብርት ማለት ከወሊድ በኋላ በአካልና በአኗኗር ዘይቤ ለውጥ ምክንያት በአንዳንድ እናቶች ላይ የሚከሰት ነው።[64] ግማሽ የሚሆኑ ሴቶች በሚወልዱበት ወቅት ከጥቂት ቀናት ጀምሮ ለሳምንት ያክል መደበት (ድብርት) ሊያጋጥማቸው ይችላል፡፡ እንደ ኢትዮጵያ የቢሃይቭ ድህረ ገጽ አገላለጽ ድህረ ወሊድ ድብርት **ከ70-80 በመቶ** የሚሆኑ ሴቶች ላይ ይከሰታል፡፡ እነዚህ ሴቶች ከወሊድ በኋላ (ቤቢ ብሉ) የሚባለው ስሜት ይሰማቸዋል፡፡ ይህም የመከፋት የመጨነቅና የመደበር ስሜት ነው በማለት ይዘግባል፡፡ ከወሊድ በኋላ ሰውነታቸው የሆርሞን ለውጥ፣ ጭንቀትና ድካም እንዲሁም በቂ እንቅልፍ የማጣት ስሜት ይሰማቸዋል። የፍርሃት የመጨነቅና የመደበር ስሜት ለተወሰኑ ቀናት የተለመደ ነው፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ሴቶች ይህ ስሜት ሊቆይባቸው ይችላል፡፡ አስፈላጊ ክትትል ካልተደረገ ሳምንታትና ወራት ድረስ ሊቀጥል ይችላል፡፡[65]

ይህ ማለት ከወሊድ በኋላ ያለው ዋናውና ትክክለኛው የድብርት ወይም የመጫጫን ስሜት (Clinical Depression) ማለት አይደለም።[66] ሌላው "Postpartum psychosis" ድህረ ወሊድ ድብርት ከመጀመሪያዎቹ ሁለትና ሶስት ሳምንታት ጀምሮ ለወራት ሊዘልቅ የሚችልን የድብርት ስሜት የሚያመላክት ነው። ይህ ከውሊድ በኋላ የሚገጥም ከፍተኛ የሆነ የድብርት ሌላው ተጠቃሽ ነው። ይህ ዓይነቱ ከወሊድ በኋላ ያለው ድብርት **0.001-0.02%** የሚያጋጥማቸው ከወለዱ ከአንድ ሺ ሴቶች በቁጥር አንድ ወይም ሁለት ሴቶች ይሆናሉ ተብሎ ይገመታል።[67] በተለይ ላልተፈለገና ላልታሰበ እርግዝና ተጋላጭ የሆኑ ሚስቶች ከፍተኛ ለሆነ ድብርት ተጋላጭ መሆናቸው እሙን ነው።

## II. የድህረ ወሊድ ድብርት መንስኤዎች

በመጀመሪያ ደረጃ የሚጠቀሰው የችግሩ መከሰት ምክንያት በእርግዝና ወራት በከፍተኛ መጠን የሚገኙት የኤስትሮጅን (Estrogen) እና የፕሮጀስትሮን (Progesterone) ሆርሞኖች ከወሊድ በኋላ በአጭር ጊዜ ውስጥ መጠናቸው መቀነሱ

[64] Africa communitties Public health coalitaion. Flyer about Depression.

[65] http://ethiopia.thebeehive.org/content/205/2483 ፖስትፓርተም ዲፕሬሽን Accsesed Oct,11,2014.

[66] Tim & Trent, John. Marriage and family Counseling the quiqe referance Giude page 229.

[67] Tim & Trent, John. Marriage and family Counseling the quiqe referance Giude page 229.





ነው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ችግሩ የሚመጣው የታይሮይድ (Thyroid) ሆርሞን መጠን አነስተኛ ከሆነ ነው፡፡ የታይሮይድ ሆርሞን መጠን ማነስ የምግብ ፍላጎት ማጣት፣ የድካምና የድብርት መጫጫንን ያስከትላል፡፡

የድህረ ወሊድ ድብርት መንስኤዎች ሆርሞናዊ ለውጦች ብቻ ሳይሆኑ ውጫዊ ግፊቶችም ጭምር ናቸው፡፡ ከወሊድ በኋላ በመንፈስ መረበሽ፣ በአካል መድከምና በክብደት መጨመር ምክንያት የሰውነት ቅርፅ መቀየር (መበላሸት) ያጋጥመኛል ብሎ መስጋት፣ ከመደበኛ ሥራ እርቆ በጓዳ ሥራ ብቻ እንደታሰሩ በማሰብ መተከዝ፣ ሌላ የእነርሱን እንክብካቤ የሚፈልግ ሕጻን እንደ ተጨመረባቸው በማሰብ መጨነቅ፣ ያህንንም ኃላፊነት ለመወጣት አብዝቶ ማሰብ፣ ጤናማ ያልሆነ ፅንስ መገላገል፣ የፅንስ በወሊድ ላይ መጥፋት (ሕይወቱ ማለፍ)፣ ረጅም ጊዜያቸውን ከፍቅር ጓደኛ ጋር ወይም ከጎረቤት ጋር ከማሳለፍ ይልቅ በልጅ እንክብካቤ ቤት ውስጥ ብቻ በመወሰናቸው የሚፈጠር ጥሩ ያልሆነ የበታችነት ስሜት፣ በቂ እንቅልፍ አለማግኘት፣ ቀድሞ ሲወዱትና ሲያደርጉት የነበረ የሚያዝናናቸው ድርጊትና እንቅስቃሴ መቋረጥና በመሳሰሉ መንስዔዎች ይከሰታል።[68] ከወሊድ በኋላ የሚፈጠረው ድብርት የሚገለጸው መሠረት የሌላቸው ነገሮች በመስማት፣ በማየት፣ በመናገርና የከንቱነት ስሜትና የአእምሮ ሕመም ሰለባ በመሆን ነው።

## III. ድህረ ወሊድ ድብረት የሚያመጣው ተጽዕኖ

ብዙ ሴቶች ከወሊድ በኋላ ባህሪያቸው ይለወጣል፡፡ ይህ በተለያዩ ምክንያቶች ሊከሠት እንደሚችል ይገመታል፡፡ ለምሣሌ የሆርሞኖች መጠን መዛባት፣ በወሊድ እና በሕመም ወቅት የገጠማቸው የሕመም ስሜት፣ የእንቅልፍ ማጣት፣ አዲስ ሕፃን ልጅ ለማሣደግ የሚጠብቀው ኃላፊነት እና ከወሊድ በኋላ የሚገጥመው ድህረ ወሊድ ድብርት በመሳሰሉት የተነሣ የባሕርይ መለዋወጥ ሊከሠት ይችላል፡፡ የወሲብ ፍላጎት መቀነስ ሌላው ከወሊድ በኋላ ባለ ጊዜ የሚያጋጥም ድብርት ተጽዕኖ ውጤት ሊሆን ይችላል፡፡ ከወሊድ ጋር ተከትለው የሚመጡ እንቅልፍ የሌለባቸው ምሽቶች እና የኢስትሮጅን ሆርሞን መጠን መቀነስ የሴቷን የወሲብ ፍላጎት በከፍተኛ ደረጃ እንዲቀንሱ ያደርጋሉ፡፡[69]

## IV. ድህረ ወሊድ ድብርትን ተቋቁሞ ደስተኛ ባለትዳር ለመሆን

### 1. መረዳት፡- ተፈጥሮአዊ ለውጦችን መረዳት

ድህረ ወሊድ ድብርትን ተቋቁሞ ደስተኛ ባለትዳር ለመሆን የመጀመሪያው አስፈላጊ ነገር ተፈጥሯዊ ክስተቶችን መረዳት ነው። ከወሊድ በኋላ የሚከሠቱ አካላዊ

[68] Medina/መዲና June 2012 volume II No. 4 ሰኔ 2004 ፪ኛ ዓመት ቁጥር ፬ ከዶ/ር ዓብይ ዓይናለም

[69] Medina/መዲና June 2012 volume I No. 4 ሰኔ 2004 ፪ኛ ዓመት ቁጥር ፬ ከዶ/ር ዓብይ ዓይናለም

እና ስነ ልቦናዊ ለውጦችን ለመቆጣጠር ቀዳሚው ነገር ለውጡ በአብዛኛው ነፍሰ ጡር ሴቶችን ሊያጋጥም የሚችል ተፈጥሯዊ ክስተት መሆኑን መርዳት ነው። አስቀድሞ ተፈጥሯዊ ክስተቶችን መረዳት በብዙ አቅጣጫ ቅድመ ዝግጅት ለማድረግ ይጠቅማል። የድህረ ወሊድ ድብርትን ምክንያቶችና ሊያባብሱት የሚችሉ ነገሮችን ለይቶ ማወቅ እና የሚያመጣቸውን አሉታዊ ተጽዕኖዎች መረዳት ቶሎ ችግሩ ሳይባባስና ከፍተኛ ተጽዕኖ ሳያመጣ የመፍትሔ እርምጃ እንድንወስድ ጠቀሜታው ላቅ ያለ ነው።

አስቀድመው ችግሩን መረዳት ግማሽ መፍትሔ ማግኘት ነው እንደሚባለው ችግሩ ከመፈጠሩ በፊት ዝግጁ ሆነን እንድንጠብቅ መፍትሄ ለማግኘቱም ሂደት ጥሩ ግንዛቤ እንድናገኝ መረዳታችንን በተለያዩ መንገዶች ከፍ ልናደርግ ይገባል። ዘመኑ የመረጃ ዘመን ነውና ይህንንም በብዙ መንገድ ማድረግ እንችላለን:: መረጃዎችን ከማሕበራዊ ድረ-ገጾች በማግኘት፣ መጽሐፍትን በማንበብ፣ ልምድ ያላቸውን ሰዎች በመጠየቅና በአካባቢያችን የሚገኙ የሕክምና ባለሙያዎችን በማነጋገር መረዳታችንን ማሳደግና እውቀታችንን ከፍ ማድረግ እንችላለን። ልዩ ልዩ የመገናኛ ብዙሃንም መረጃ በመስጠት በኩል የሚጠቀስ ድርሻ ይኖራቸዋል:: ለምሳሌ:- በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የሚቀርቡ "ጤናችን"ን ወይም "ጤናዎ በቤትዎ"ን የመሳሰሉ ፕሮግራሞች ሊጠቀሱ ይችላሉ:: በአጠቃላይ ባገኘናቸው ጤነኛ እና ምቹ አማራጮች ሁሉ የሕክምና ባለሙያ በማነጋገር፣ የከምና ባለሙያዎች ሕብረተሰቡን ለማስተማር፣ ለመምከርና ለማስጠንቀቅ በሚያቀርቧቸው ልዩ ልዩ ፕሮግራሞች ተሳታፊ በመሆንና የጽሑፍ ማስረጃዎችን አሰበንበት በመዳሰስ መረዳታችንን ማሳደግ ችግሮች የትዳር አጋራችንን ለከፋ ጉዳት ከመዳረጋቸው በፊት ፈጥነን እንድንደርስ ያስችለናል:: በትዳር ግንኙነታችን ላይና በተወለዱት ልጆች ላይም አሉታዊ ተጽዕኖ ሳይፈጠርብን በምንወስደው ቅድመ ጥንቃቄ ድህረ ወሊድ ድብርትን አሸንፎ ደስተኛነትን የተጎናጸፈ ትዳር እንዲኖረን ማድረግ እንችላለን::

## 2. መቀነስ፡- ውጥረት አባባሽ ነገሮችን መቀነስ

ድህረ ወሊድ ድብርትን ተቋቁሞ ደስተኛ ባለትዳር ለመሆን ሁለተኛው ጉዳይ አስጨናቂና ውጥረትን አባባሽ ነገሮችን መቀነስ ነው። ተፈጥሯዊ ክስተት በሆኑ ለውጦች ችግር መፈጠሩ አይቀሬ ከመሆኑ ባሻገር ድህረ ወሊድ ድብርት ይበልጥ እንዲባባስ ሊያደርጉ የሚችሉ ውጫዊ ውጥረቶች ጭንቀትን ሊጨምሩ የሚችሉ ጉዳዮች ናቸው። በሕይወት ብዙ ውጣ ውረዶች መኖራቸው አይቀሬ ነው። ሕይወት ምርጫና ውሳኔ የበዛባት ጉዞ ናት። በትዳር ግንኙነታችን መካከል ምርጫና ውሳኔ ተያይዘውና ተዛዝለው መምጣታቸው የግድ ነው። በእርግዝናና በወሊድ ወቅት ይህ ሲከሰት ከወቅቱና ከሁኔታው የተነሳ ሌላ ጊዜ ልናስብባቸው፣ ለምርጫ ልናቀርባቸውና ልንወስንባቸው የምንችልባቸውን ጉዳዮች ለይተን ማወቅና ለሌላ ጊዜ ማስተላለፍ አስፈላጊ ነው። ለምርጫና ለውሳኔ እንዳቀርብናቸው ጉዳዮች አስፈላጊነት፣ አሳሳቢነት፣ አስቸኳይነትና





ቀዳሚነት ልናያቸው የሚገቡና ለጊዜው የማይመቹ፣ ውጥረትና ከፍተኛ ጭንቀት በመጨመር ይበልጥ ድብርትን የሚያባብሱ፣ ነፍሰ ጡሯን ሚስት የሚጎዱና የትዳር ግንኙነትን የሚያሻክሩ ጉዳዮችን ለጊዜው ትቶ መቆየት ውጥረቶችን ለመቀነስ በጣም ጠቃሚ ነው::

ባለትዳሮች በተለይም ባሎች ውጥረቶችን በመቀነስ በሚስቶቻችን ላይ የሚፈጠር ድህረ ወሊድ ድብርትን ለማስወገድና ተቋቁሞ ለማለፍ ከፈልግን ከሚያነጋግረንና ጭንቀት ከሚጨምርብን ጉዳይ ይልቅ የትዳር አጋሮቻችን፣ የትዳር ግንኙነታችንና ቤተሰባችን እንደሚበልጥ ማሰብ ይጠበቅብናል። ሁኔታዎችን ባለመረዳት የሚነሱ በጣም ወሳኝና ትልቅ የሆኑ ውሳኔዎችና ለውጦች በቅርብ ለወለደች ሚስት የሚሰጡት ትርጉም አሉታዊ ሊሆን ይችላል:: እንዲህ ዓይነት ሁኔታ በመከሰቱ ምክንያት ባሏ ለእርሷ የማያስብ፣ ራስ ወዳድ፣ የምታልፍበት የሕመምና የጭንቀት ሁኔታ የማይገባውና ራስ ተኮር እንደ ሆነ ሊሰማት ይችላል:: ይህ ስሜት ካላት ደግሞ በቀላሉና በከፋ ሁኔታ በቁጣ፣ በውጥረትና በጭንቀት ትሞላለች:: የድህረ ወሊድ ድብርትን ተቋቁሞ ደስተኛ ባለትዳር ለመሆን የምታደርገው ጥረትም ሕልም ብቻ ይሆናል። ስለዚህ ምቹ ጊዜና ሁኔታን ለመምረጥ አንዳንድ ጉዳዮችን አሰበንበት በማዘግየት፣ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ የሚስቶቻችን ተንከባካቢና አፍቃሪ በመሆን አጋርነታችንን ልናሳይና በእኛ በኩል የሚፈጠሩ አባባሽ ነገሮች ልንቀንስ ይገባል።

## 3. መጀመር፡- አዲስ በተወለደው ሕጻን ልጅ መደሰት መጀመር

*"እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ እናንተ ታለቅሳላችሁ ሙሾም ታወጣላችሁ፥ ዓለም ግን ደስ ይለዋል፤ እናንተም ታዝናላችሁ፥ ነገር ግን ኀዘናችሁ ወደ ደስታ ይለወጣል። ሴት በምትወልድበት ጊዜ ወራትዋ ስለ ደረሰ ታዝናለች፤ ነገር ግን ሕፃን ከወለደች በኋላ፥ ሰው በዓለም ተወልዶአልና ስለ ደስታዋ መከራዋን ኋላ አታስበውም። እንግዲህ እናንተ ደግሞ አሁን ታዝናላችሁ፤ ነገር ግን እንደ ገና አያችኋለሁ ልባችሁም ደስ ይለዋል፥ ደስታችሁንም የሚወስድባችሁ የለም"* /ዮሐ 14፡ 20-22/:: በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በምሳሌ የተጠቀሰው የመውለድ ሂደት ልጅ ከመወለዱ በፊት የምጥ ስቃይ መኖሩን እያመላከተ ነገር ግን ችግሩ ለጊዜው መሆኑን ያሳያል። የምጥን ስቃይና መከራ የሚያስረሳ ሕጻን ልጅ ተወልዷልና ደስታ ይሆናል:: ወላጆች አዲሱን ልጅ እንዳቀፉ መከራውን ይረሱታል በማለት ካሳለፍነው የመከራ ጊዜ አሁን ያገኘነው ይበልጣል የሚል ሃሳብ ያስጨብጠናል። እህቴ የመጀመሪያ ልጇን በወለደች ቀን በስልክ ደውዩ እንዴት ነበር? በማለት ጠይቂያት ነበር:: ነገር ግን የመለሰችልኝ መልስ "ሁልተኛ ልጅ የሚባል...!" የሚል ነበር:: እኔም አሰብኩና "እንደ አንቺ ንግግር ቢሆን እናታችን እኔን ብቻ ወልዳ እናንተ አትወለዱም" ነበር አልኳት። የሚገርመው እንዲህ ያለችው እህቴ በአንድ ዓመት ልዩነት ሁለተኛውን ልጇን እርግዛ ወለደች።

ሁልጊዜ የማናውቀውን ነገን እያሰብንና ገና ያልያዝነውን ተስፋ እያደረግን ዛሬ በተሰጠንንና በተቀበልነው ልጅ በመደሰት እግዚአብሔርን ማመስገን፣ ማድነቅ፣ ማክበርና ውድ ስጦታውን ደግሞ መንከባከብ እንዳያስቸግረን መጠንቀቅ ይኖርብናል።

ሳጤ ሳለን በማግባት እንደምንደሰት እናስብ ነበር:: ከአገባን በኋላ ደግሞ በትዳራችን መደሰት ቀንሰን ልጅ ስንወልድ እንደምንደሰት እናስባለን:: እግዚአብሔር ልጅ ሲሰጠን ደግሞ ወንድ ልጅ ከሰጠን ሴት ልጅ ስንወልድ፤ ሴት ልጅ ከሰጠን ደግም ወንድ ልጅ ስንወልድ እንደምንደሰት እናስባለን:: ወንድና ሴት ልጆችን ከእግዚአብሔር ስንቀበል ደግሞ በየደረጃው ሲያድጉ እንደሰታለን እያልን እናልማለን:: ማስተዋል ያለብን በደረስንበት እግዚአብሔር በሰጠን ድንቅ ስጦታ ሳንደሰት የደስታ ተስፈኛ ሁነን እንዳናልፍ ነው:: ስለዚህ *"እግዚአብሔር የሠራት ቀን ይህች ናት ሐሤትን እናድርግ፥ በእርስዋም ደስ ይበለን።"* /መዝ 118፡ 24/ ብለን ከዘማሪው ጋር እያዜምን ዛሬ በጌታ በመኖራችን፣ ጌታ በሰጠንና ባለን ልንደሰትና ደስተኛ ሆነን መኖርን ልንለማመድ ይገባል።

እግዚአብሔር በሰጠን ድንቅ ስጦታ ላይ በማተኮር ሃሳባችንን በጊዜው ባለው ችግር ሳይሆን ባገኘነው በረከት ላይ፤ ባላገኘነው ተስፋ ላይ ሳይሆን በእጃችን ባለው ሙላት ላይ ማተኮር ወይንም ከወሊድ በኋላ ባለው ሕመምና ያልተፈለገ ልጅ በመውለዳችን ማዘን ሳይሆን የእግዚአብሔር ስጦታ በሆነው በተወለደው ሕጻን መደሰት ተገቢ ነው። የተሰጠንን ስጦታ መቀበል ባለመፈለጋችን ምክንያት ሳቅ ከሕይወታችን፣ ከትዳራችን፣ ከቤታችን እንዳይጠፋ ይልቁንም በልጆች ፈጣን ለውጥና እድገት እየተደነቅን የሳቅ ምክንያት እንዲሆኑልን አጋጣሚዎችን ሁሉ በጋራ ለመሳቅ ልንጠቀምባቸው ይገባል።

ምናልባት ያልተፈለገ ልጅ በመውለዳችንና በዚህም ምክንያት ያለፍንባቸውና የምናልፍባቸው የተለያዩ የሕመም እንግዳ ስሜቶች የበለጠ ስቃይ እንደሆኑ ሊሰማን ቢችልም የተወለደውና ያቀፍነው ሕጻን የእግዚአብሔር ስጦታ በመሆኑና እግዚአብሔርም በሕጻኑ ሕይወት ትልቅ ዓላማ ስላለው መጽናናት ይገባናል:: እኛ ወላጆች የዚህ የእግዚአብሔር ዓላማ ያለበት ሕጻን ባለአደራዎች የመሆን ክብር ከእግዚአብሔር ዘንድ በማግኘታችን በደስታና በምስጋና መሞላት እንጂ ማዘን አይጠበቅብንም:: ይህ መንገድ ድህረ ወሊድ ድብርት የሚባለውን ችግር የምናሸንፍበት የድል መንገድ ነው። አሁን ካሉ ሁኔታዎች፣ ከገጠሙን ችግሮችና ወደ ፊት ይገጥሙናል ብለን ከምንፈራቸው ችግሮች ይልቅ ዛሬ እግዚአብሔር የሰጠንን ባርኮቶች እንቁጠርና የምስጋና የጸሎትና የመዘመር ምክንያት ይሁኑልን! *"በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ እርስ በርሳችሁ ተነጋገሩ፤ ለጌታ በልባችሁ ተቀኙና ዘምሩ፤ሁልጊዜ ስለ ሁሉ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አምላካችንንና አባታችንን ስለ ሁሉ አመስግኑ።"* /ኤፌ 5፡ 19-20፣ 1ኛተሰ 5፡ 17-18/

**ድህረ ወሊድ ድብርትን ለማስወገድና ተቋቁሞ ለማለፍ ከፈልግን ከሚያነጋግረንና ጭንቀት ከሚጨምርብን ጉዳይ ይልቅ የትዳር አጋሮቻችን፣ የትዳር ግንኙነታችንና ቤተሰባችን እንደሚበልጥ ማሰብ ይጠበቅብናል።**





### 4. መፍጠር፡- የግል የእረፍት ጊዜ እንዲኖር ምቹ ሁኔታዎች መፍጠር

አራተኛው የግል የእረፍት ጊዜ እንዲኖር ምቹ ሁኔታ መፍጠር ነው። ለማንኛውም በብዙ ሥራ፣ ድካምና ሕመም ለአሳለፈ ሰው የእርፍት ጊዜ አስፈላጊ ነው። ለዘጠኝ ወራት በሰውነታቸው እርግዝና የፈጠረው እንግዳ የሆነ ልምምድ፣ ብዙ ድካም፣ የምቾት አለመኖር፣ እንደ ቀድሞው የሚፈልጉትንና የሚወዱትን አለመሆንና አለማድረግ፣ አለመመገብና አለመልበስ፣ አለመውጣትና አለመንቀሳቀስ የመሳሰሉ ሁኔታዎች በእርግዝና ወቅትና ከወሊድ በኋላ ለሚያጋጥም ድብርት ተጋላጭ እንዲሆኑ የሚያደርግ ከፍተኛ ድካም ያጋጥማቸዋል:: ስለዚህ ሚስቶች ከወሊድ በኋላ ይህን ሁኔታ ሊለውጥ የሚችል ምቹ የግል የእረፍት ጊዜ ሊኖራቸውና አቅም ሊሰበስቡ የሚችሉበት አካባቢና በቂ ጊዜ ልናስተካክልላቸው ይገባል።

ከድህረ ወሊድ በኋላ በተለያዩ ምክንያቶች እንቅልፍ ማጣት ሊፈጠር ይችላል። አዲስ የተወለደውን ሕጻን ለመመገብና ለመንከባከብ ቀንም ሆነ ሌሊት እንቅልፍ አልባ የሆኑ ጊዜያትን ያሳልፋሉ:: ያላቸውንና የሚያስፈልገውን ሁሉ ለአዲሱ ሕጻን ለመስጠት ሲተጉ በፈለጉት ጊዜ መተኛትና ማረፍ ስለማይችሉ ይህን በመረዳት በቂ የሆነ እረፍት የሚያገኙበትን መንገድና ሁኔታ ማመቻቸት በጣም አስፈላጊ ነው። በተለይ ከወሊድ በኋላ የልጁ ጤንነት እክል ከገጠመው፣ ውስብስብ የሆነ የሜዲካል ችግር ከተፈጠረ፣ በቤት ውስጥ ያልተሟሉ ግብዓቶች ካሉና የእነርሱን እንክብካቤ የሚፈልጉ ተጨማሪ የቤተሰብ አባላት ካሉ ... እረፍት የማግኘታቸው ጉዳይ ተጨማሪ ትኩረት ይፈልጋል። ይህ ብቻ ሳይሆን የብዙ ዓመት ልዩነት ሳይኖራቸው በአከታታይ ሲወልዱና ሁለቱም ተመሳሳይ የሆነ ትኩረትና እንክብካቤ የሚያስፈልጋቸው ሲሆኑ ይበልጥ ኃላፊነቱንና ድካሙን ያባብሰዋል።

ድህረ ወሊድ ድብርትን የሚያባብሱ ሁኔታዎችን በመረዳት ሌሎች መልካምና ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ሚስቶች እንዲያርፉ ዕድል መስጠት ተገቢ ነው። እረፍት ብለን ስናስብ በቂ እንቅልፍ ማግኘት አንደኛው መንገድ ሲሆን ከዚህም ባለፈ ካለባቸው የእናትነት፣ የሚስትነትና የእንግዳ ተቀባይነት ኃላፊነት እንዲያርፉ በባሎችና በሌሎች የቤተሰብ አባላት የሚረዱበትን መንገድ መፍጠር መቻል አለብን። ምናልባት ከምንም ሥራ እንዲታቀቡ አድረገ ቀድሞ ይወዱት የነበረ የሚያዝናናቸውን ነገር እንዲያደርጉ ከቤት ይዞ በመውጣት፣ የመያዝናኑ ሁኔታዎችን በማሳየት፣ በማስጎብኘት፣ እንዲንቀሳቀሱ በማድረግ ኃይል እንዲሰበስቡና ትኩረታቸው ከድብርት እንዲያወጡ ምቹ አጋጣሚዎችን መፍጠር በጣም ጠቃሚ ነው:: እናቶችም ዕድሉን በመጠቀም ከችግሩ ለማምለጥ እርምጃ ሊወስዱ ይገባል።

### 5. መፈለግ፡- የሌሎችን ሰዎች እርዳታ መፈለግ

ከችግሩ ብዛትና እያመጣ ካለው ተጽዕኖ የተነሳ ነገሮች ከአቅም በላይ በሚሆኑበት ጊዜ የግድ የሌሎች ሰዎች እርዳታ የሚያስፈልገን መሆኑን ማስተዋል አለብን።

አምስተኛው መፍትሔ በዚህ ብቻችንን መወጣት የማንችላቸው ከአቅም በላይ የሆኑ ጉዳዮች ባጋጠሙን ጊዜ የሌሎች ሰዎችን እርዳታ ለመፈለግና ለመቀበል ፈቃደኛ መሆን ነው፡፡ የሌሎችን እርዳታ መፈለግ ሽንፈት ወይም ውድቀት አይደለም ይልቁንም ብልህነትና ችግራችን የሚወገድበትን ጊዜ ማፋጠን ነው። ካለንበት ችግር የተነሳ የሌሎች እርዳታ የሚያስፈልገን በምን አቅጣጫ ነው? ብሎ ማሰብና ትክክለኛ እርዳታ ማግኘት ይበልጥ በሳልነት ነው።

የሌሎችን እርዳታ ማግኘት ትክክለኛ መረጃ ያላቸውንና ሊመሩን የሚችሉ ሰዎችን ከማግኘት ሊጀምር ይችላል። አንዳንድ ሰዎች በነገሩ ዕውቀት ሳይኖራቸው ነገር ግን ከሌሎች ጋር ብዙ ግንኙነት ያላቸውና ያገኙትን መረጃ ለሌሎች መስጠት የሚያስደስታቸውና ሰዎችን በዚህ አቅጣጫ የሚረዱ ሊሆኑ ይችላሉ። እንዲህ ዓይነቱን አጋጣሚም በአግባቡ መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡ ነገር ግን መረጃ ሁሉ ጠቃሚ ሊሆን አይችልምና ደግሞ ደጋግሞ የመረጃዎችን እርግጠኝነት ማረጋገጥ ተገቢ ነው።

ካለብን የድህረ ወሊድ ድብርት ችግርና ካገኘነው መረጃ ተነስተን የሚያስፈልገን ምን ዓይነት እርዳታ ነው? ምናልባት የምክር አገልግሎት ይሆን? ከሆነስ ማንን ማማከር አለብን? ፓስቶራል አማካሪ፣ ክርስቲያን ፕሮፌሽናል አማካሪ፣ ክሊኒካል ፓስቶራል አማካሪ፣ የጋብቻና የቤተሰብ አማካሪ፣ የአእምሮ ሐኪም ወይንስ በተመሳሳይ ገጠመኝ ውስጥ ያለፈች እናት...? የሚለውን መለየትና እንደ ችግራችን ሁኔታ ትክክለኛ አማካሪ ለማግኘት ጥረት ማድረግ ብልህነት ነው። ምናልባት በመንፈሳዊ ሕይወትና አገልግሎት አቅጣጫ ፓስቶራል እንክብካቤ፣ የቅዱሳን ሕብረትና ጸሎት በማፈላለግ ራስን በጸጋውና በክርስቶስ መልካምነት ውስጥ መሰወር መቻል መንፈሳዊነት ነው።

ከወሊድ በኋላ የሕክምና ምርመራ ማድረግ አስፈላጊ ነው። ከወሊድ በኋላ ብዙ እናቶች ልጅን በመንከባከብ ስለሚባክኑና ለራሣቸው ጊዜ ስለማይሠጡ የራሣቸውን ጤና ቸል ይላሉ፡፡ ይህ ግን መልካም አይደለም፣ አንዲት የወለደች ሴት ከወለደች ቢያንስ **ከ6 ሣምንት** በኋላ የሕክምና ምርመራ እንድታደርግ ይመከራል፡፡[70] ያጋጠማቸውን ወይም የተሠማቸውን ሕመም ሁሉ ለሕክምና ባለሙያ በመናገር ተገቢውን ምክርና ሕክምና ማግኘት አለባቸው፡፡ ከስድስት ሳምንት በኋላ ሐኪማቸውን ማየት አስፈላጊ ነው ሲባል ከዚያ በፊት በእናትየውና በሕጻኑ ላይ ለሚከሰት ለማንኛውም የሕመም እክሎች ሁሉ በአቅራቢያ ወደሚገኝ ሆስፒታል፣ ክሊኒክና ጤና ጣቢያ በመሄድ አስፈላጊውን ሕክምና ማግኘት ተገቢ መሆኑ የተጠበቀ ነው።

[70] ዶ/ር ብርሃኑ ሰንደቀ የጽንስና የማሕጸን ሕክምና ስፔሻሊስት ኢትዮጵያ ብሮድ ካስቲንግ ኮርፖሬሽን (EBC)ጤናዎ በቤትዎ "ቅድመ እና ድህረ ወሊድ ክትትል ዙሪያ የቀረበ ውይይት" ነሐሴ 03 / 2006 ዓ.ም Acceseed Oct.10.2014.





## 6. መጸለይ፡- ሳያቋርጡ በትጋት ወደ እግዚአብሔር በእምነት መጸለይ

ስድስተኛውና የመጨረሻው የማቀርበው መፍትሄ ማግኛ መንገድ ጸሎት ነው። ጸሎት በችግር ጊዜ የምንፈጽመው ሐይማኖታዊ ስርዓት ሳይሆን በማንኛውም ጊዜ ስለሁሉ ነገር ከእግዚአብሔር ጋር የመነጋገር ሂደት ነው። የጸሎት መረዳታችንን በማስተካከል ወደ ፈተና እንዳንገባ እንድንጸልይ /ማቴ **26፡ 41**/፤ በፈተና ውስጥ ሁነንና በምቹ ሁኔታም ውስጥ ሁነን እንድንጸልይ የእግዚብሔር ቃል አጥብቆ ያዘናል /መዝ **32፡ 6**/።

የግል ጸሎት አስፈላጊ እንደ ሆነ ሁሉ በማይመችና በደከመን ጊዜ፣ በችግር፣ በሕመምና በመከራ ውስጥ ስንሆን የሌሎች ቅዱሳን፣ የአገልጋዮችና የመሪዎች እጅ ጭኖ መጸለይ አስፈላጊነቱ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ መርህ የተደገፈ ነው። *"ከእናንተ የታመመ ማንም ቢኖር የቤተ ክርስቲያንን ሽምግሌዎች ወደ እርሱ ይጥራ፤ በጌታም ስም እርሱን ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት"* /ያዕ 5፡ 14/። ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት ከምንቀርብባቸው ምክንያቶች አንዱ እግዚአብሔር ሕመምተኞችን ሊፈውስና ነፍሳችንን ከቆዘምችበትና ከያዛት ድብርት ሊያወጣ የሚችል አምላክ መሆኑ ነው፡፡ ይህን ተረድተን ትካዜያችንን በእርሱ ላይ መጣል ተገቢ ነው። *"ትካዜህን በእግዚአብሔር ላይ ጣል፥ እርሱም ይደግፍሃል ለጻድቁም ለዘላለም ሁከትን አይሰጠውም።"* /መዝ **55፡ 22**/ አሁን ካለንበት ሁኔታ ይልቅ እግዚአብሔር በእኛ ላይ ያለው አሳብ ይበልጣልና ጌታንና የእርሱን ዓላማ አርቀን እንመልከት፤ እንዲህ እንደ ጨለመና ጭጋግ እንደሆነ አይቀጥልምና! *"ለእናንተ የማስባትን አሳብ እኔ አውቃለሁ ፍጻሜና ተስፋ አሰጣችሁ ዘንድ የሰላም አሳብ ነው እንጂ የክፉ ነገር አይደለም።"* /ኤር **29፡ 11**/፡፡

## ለጥንዶች በግላቸውና በቡድን ለማጥናት የሚረዱቸው የውይይት ጥያቄዎች

## የምዕራፍ አስራ ሰባት (17)

## የውይይት ጥያቄዎች

1. የድብርትና የድህረ ድብርትን ምንነት በመግለጥ አብራሩ፡፡
2. ድህረ ድብርት በወለዱ እናቶች ላይ የመከሰቱ ምክንያቶች ምንድን ናቸው ትላላችሁ?
3. ድህረ ወሊድ ድብርት በወለደችው እናትና በትዳር አጋሯ ላይ ሊፈጥር የሚችለው አሉታዊ ተጽዕኖ ምንድን ነው? በመዘርዘር ተወያዩበት።
4. ድህረ ወሊድ ድብርትን ተቋቁሞ በማለፍ ደስተኛ የትዳር ግንኙነት እንዲኖር ምን መደረግ አለበት ትላላችሁ?
5. ድህረ ወሊድ ድብርት በትዳራችሁ አጋጥሟችሁ ያውቃል? ከሆነ እንዴት እንዳለፋችሁት ልምድን በማካፈል ተነጋገሩበት፡፡ ደግሞስ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ያለፉ ባለትዳሮች አጋጥሟችሁ ያውቃል? ከሆነ ሁኔታውን በምስከርነትና በሚያስተምር መልኩ ተወያዩበት።





# ምዕራፍ አስራ ስምንት(18)

# የመጀመሪያ ልጅና ተከታትለው የተወለዱ ልጆችን ማሳደግ

## 1. የመጀመሪያ ልጅንና ተከታትሎ የተወለዱ ልጆችን የማሳደግ ምንነት

ልጅን ማሳደግ ልጅ ከተወለደበት ማለትም ከእናቱ ማሕጸን በመውጣት ወደዚህ ሾምድር ከመጣበት ቀንና ሰዓት ጀምሮ ወላጅ ለተወለደው ልጅ ሁለንተናዊ እድገት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች በማቅረብና በማዘጋጀት ልጅን የመንከባከብ ሂደት ነው። የልጆች ሁለንተናዊ እድገት የሚባለው በአካል፣ በአእምሮ፣ በስነ ልቦና፣ በማሕበራዊ ግንኙነት ጤናማና ሚዛናዊ በሆነ መልኩ የተሟላ ማንነት እንዲኖራቸው ወላጆች የበኩላቸውን ድርሻ ለመወጣት በሚያደርጉት ጥረት በልጆች ሕይወት ላይ የሚታይ የአወንታዊ ለውጥ ሂደት ነው። ልጆች ለእድገታቸው የሚያስፈልጓቸውን መሠረታዊ አካላዊ፣ መንፈሳዊና ማሕበራዊ ... ፍላጎቶቻቸውን አቅም በፈቀደ መጠን በማሟላት የወላጅነትን ኃላፊነት መወጣት ከወላጆች የሚጠበቅ የወላጅነት ኃላፊነት ነው።

ወላጆች ሳያቅዱ ወይም ሳያስቡበት ከአንድ በላይ ልጅ ሲወልዱ በተለይ ደግሞ የተወለዱት ልጆች የዕድሜ ልዩነት ከ11 ወር ጀምሮ እስከ ሁለት ዓመታት መካከል ሲሆን ልጆችን ለማስተዳደርና ለመንከባከብ የሚጠይቀው የገንዘብ፣ የጊዜና የጉልበት አቅም ፈታኝ ይሆናል። አከታትሎ መውለድ በአንድ ወቅት ገንዘብን፣ ጊዜን፣ አቅምንና ትኩረትን ሰብሰብ አድርጎ ልጆችን ለማሳደግ ይጠቅማል፡፡ ልጆች እርስ በርሳቸው ጓደኛ ለመሆን እድል ያገኛሉ፤ ነገር ግን ኃላፊነቱን የመወጣቱ ሂደት እንደሚታሰበው ቀላል አይደለም፡፡

ልጆች በተመሳሳይ ጊዜ አንድ ዓይነት ነገር ሲፈልጉ፣ የወላጅ እንክብካቤና ትኩረት ሲያሻቸውና አንዱ ሕጻን የሌላውን ሕጻንነት መረዳት አልችል ሲል ውጥረት ይፈጠራል። አንዳንድ ጊዜ የወላጅ አቅርቦት አነስተኛ በመሆኑ ልጆች ለአንዱ የበለጠ ትኩረት እንደተሰጠው ባሰቡና ባዩ ወቅት በሚፈጠር ቅንዓት ወይም በሚፈጠሩ ሌሎች ችግሮች ወላጆች የመደናገጥ፣ የመድከም፣ የመበሳጨት፣ የመሰልቸት፣ የመማረርና ለሌሎች ነገሮች ትዕግስትና ጊዜ የማጣት ችግሮች ሊፈጠሩባቸውና ሊፈራረቁባቸው ይችላሉ። በዚህ ጊዜ ለልጆች ቅርብ የሆነ ወላጅ አካላዊ፣ ስነ ልቦናዊ፣ ስሜታዊና ቤተሰባዊ የሆነ ቀውስና የጤና መታወክ ያጋጥመዋል፡፡ መጥፎ ስሜቱንም በልጆችና በትዳር አጋሩ ላይ ሊያንጸባርቅ ይችላል። ይህ ምዕራፍ ተከታትለው የተወለዱ ልጆችን በማሳደግ ሂደት ውስጥ ያሉ መሰረታዊ የወላጅነት ኃላፊነቶችን በመዳሰስና የሚጋጥሙ ተግዳሮቶችን በመጠቆም ባልና ሚስት በዚህ ሂደት ከሚፈጠሩ ግጭቶች (አለመግባባቶች) ትዳራቸውን እንዲጠብቁ፣ ያጋጠሟቸውን ችግሮች በብስለት እንዲፈቱና የቤታቸውን ሰላም እንዲጠብቁ የሚያግዛቸውን አስተዋጽዖ ማበርከት ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡

## II. የመጀመሪያ ልጅንና ተከታትለው የተወለዱ ልጆችን በማሳደግ ሂደት ሊፈጠሩ የሚችሉ የግጭት መንስኤዎች

የተወለደና በሕይወት የቆየ ልጅ ሁሉ ያድጋል። ነገር ግን የተወለደን ልጅ የማሳደጉ ሂደት የወላጅ እና የሌሎችም አካላት ማለትም እስከ መንግሥት ስልጣናት መዋቅር ድረስ ያሉ ተቋማት ሁሉ ኃላፊነትና ግዴታ ነው:: ለዚህ የሕጻናት መብት በአገራችን ሕግ መንግስት **አንቀጽ 36** እውቅና የተሰጠ ሲሆን መንግሥታዊም ሆኑ መንግሥታዊ ያልሆኑ መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች የሕጻናትን መብት የማስቀደም ኃላፊነት እንዳለባቸው **በአንቀጽ 36(2)** ተገልጾ ይገኛል። የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሳያዊ ሪፑሊክ የሕጻናትን መብት በተመለከተ ዓለማቀፋዊ ኃላፊነትና ስምምነት ማለትም የሕጻናት መብቶች ኮንቬንሽን፣ የአፍሪካ ሕጻናት መብቶችና ደህንነት ቻርተር፣ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ድክላሬሽን አንቀጽ 25(2) ተቀብሏል።[71] ነገር ግን በቀዳሚነት ልጆችን ማሳደግ የወላጅ ኃላፊነት ነው። እንደ መንፈሳዊ ሰው የወለድናቸውን ልጆች ከእግዚአብሔር በሆነ ጸጋ፣ በረከትና አቅርቦት እድገታቸው በእግዚአብሔርና በሰው ሁሉ ፊት በአእምሮ፣ በቁመትና በሞገስም የተሳካ እንዲሆን የሚጠበቀውን ጥረት ልናደርግ ይገባል። *" ... ብላቴናውም ሳሙኤል እያደገ ሄደ በእግዚአብሔርም በሰውም ፊት ሞገስ እያገኘ ሄደ።"* /1ኛሳሙ 1፡ 24-28፤ 2፡ 18-19፣ 26/ በአዲስ ኪዳን ኢየሱስ ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ ከድንግል ማሪያም በተወለደበትና እንደ ሰው በቤተሰቡ እያደገ በመጣ ጊዜ የሉቃስ ወንጌል ጸሐፊ ስለእድገቱ *"ኢየሱስም ደግሞ በጥበብና በቁመት በሞገስም በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ያድግ ነበር።* /ሉቃ 2፡ 52/ ሲል ገልጾልናል።

ልጆችን በማሳደግ በኩል ወላጆች የየበኩላቸውን ድርሻ በመወጣትና በጋራ በመተባበር ልጆቻቸውን የማሳደግ ኃላፊነታቸውን መወጣት ካልቻሉ፣ አንዱ የሌላውን አቅም፣ ችሎታና ጊዜ በመረዳት በመተሳሰብ ካልሰሩ ሁኔታው ወደ አለመግባባትና ግጭት ሊመራቸው ይችላል። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ትኩረት የምናደርገው ልጆችን በማሳደግ እረገድ ወላጆች ወደ አለመግባባትና ግጭት ሊመሯቸው የሚችሉ ምክንያቶችን በመዘርዘር አሉታዊ የሆነ ተጽዕኖ በትዳርና በቤተሰብ ግንኙነት ውስጥ እንዳይፈጥሩ ለመለየትና የግጭትም ምክንያት ከሆኑ በጋራ በመመካከር ለችግሮች እልባት መስጠት እንዲቻል ለመጠቆም ነው።

### 1. የማሳደግ ልምድ አለመኖር

በቅርብ በተጋቡ ባለትዳሮች መካከል ከሚፈጠሩት ችግሮችና መፍትሔ የሚያሻው ጉዳዮች አንዱ ልጅ ወልዶ በማሳደግ ሂደት የሚፈጠር ግጭት ነው። ይህ ችግር

[71] http://www.abyssinialaw.com/ በኤፌድሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የጸደቀ. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሳያዊ ሪፐብሊክ ብሔራዊ የሰብዓዊ መብት የድርጊት መርሃ- ግብር 2005-2007 አዲስ አበባ 2005 ዓ.ም Accsesed Oct.11, 2014.





የሚፈጠርበት ምክንያት ልጅ ወልዶ ማሳደግ የመጀመሪያቸው በመሆኑና ምን ማድረግ እንዳለባቸው በቂ እውቀት ስሌላቸው ነው። ልጅን የማሳደግ ልምድ የሌላቸው በመሆኑ ምክንያት የመጀመሪያ ልጃቸውን ወልደው ለማሳደግ ሲሞክሩ ግራ መጋባት፣ መደናገጥ፣ ፍርሃትና ጭንቀት ሊፈጠርባቸውና ሊፈራረቅባቸው ይችላል። ልጆችን እንዴት ማቀፍ፣ ማጥባት፣ ማጠብ፣ ማጽዳት፣ ዳይፐር መቀየር፣ መመገብ፣ ውጭ ይዞ ለመውጣት ማዘጋጀት፣ መኪና ላይ ማሰርና ማስቀመጥና በልጆች የመግፊያ ጋሪ መግፋት የመሳሰሉ ነገሮች እስኪለመዱ ግራ ሊያጋቡና በባለትዳሮች መካከል ወቅታዊ የሆነ አለመግባባትና ግጭት ሊፈጥሩ ይችላሉ።

ሌላው የግጭት ምክንያት ባል ወይም ሚስት ከሁለቱ አንደኛቸው ልጅ በማሳደግ ሂደት ልምድ ያላቸው ከሆነ በልጅ አያያዝ ልምድ የሌለውን ወገን ማመን አለመቻሉ ነው:: በዚህ በኩል አብዛኛውን ጊዜ ችግር የሚፈጠረው እናቶች አባቶችን ማመን ስለሚያቅታቸው ነው። ለእንዲህ ዓይነቱ ችግር አንደኛው መንስኤ አንዳቸው በባሕርያቸው እነርሱ ካላደረጉት ሌሎች ሊሰሩት ይችላሉ ብለው የማመን ችግር ያለባቸው ሰዎች በመሆናቸው ነው። ሁልጊዜ እነርሱ ብቻ የሚያደርጉት ፍጹምና እንከን የለሽ እንደሆነ አድርገው በማሰብ ወይም እጅግ በጣም ከመጠን ያለፈ እንክብካቤ ለልጆች በማድረግ ድንገት ሌላው አካል ልጆችን በሚከባከብበት ወቅት ችግር ከተፈጠረ ይበልጥ ለስጋታቸው እንደ ማረጋገጫ አድርገው ይወስዱታል:: በዚህ መንገድ የራሳቸውን ፍጹምነት ብቻ በማጉላት ሌላው አካል ግን የማይችል መሆኑን ለማሳየት የሚያቀርቡት ሙግት ግጭት እንዲፈጠር ምክንያት ሊሆን ይችላል።

ሌላው በመልካም ጎኑ ባል ወይም ሚስት ከአሁን በፊት ባለፈው ዘመናቸው የሌሎችን ሰዎች ልጆች ማለትም የገዛ ወንዶሞቻቸውንና እህቶቻቸውን፣ የዘመድ ልጆችን ወይም የጓደኛና የሌሎችን ሰዎች ልጆች በማሳደግ ልምድ በማግኘታቸው ምክንያት ልምድ ባለውና በሌለው መካከል የመማርና የማስተማር ትዕግስት ሲጠፋ ግጭት ሊፈጠር ይችላል።

ሌላው ችግር ልጅን የማሳደግን ኃላፊነት ለአንድ ሰው ብቻ መጣል ነው። ይህን ከተለያየ አቅጣጫ ስናየው ምናልባት አንደኛው አካል ይበልጥ ልምዱ ያለው ከመሆኑ የተነሳ ሳይታወቀን ይበልጥ በትዳር ጓደኛችን ላይ በመተማመን ሃሳባችንን እንጥላለን። ለምሳሌ ይህ ችግር በእኛ ቤተሰብ ዘንድ ብዙ ጊዜ ይታያል። በአብዛኛው በባለቤቴ ከመተማመን የተነሳ ለእርሷ የምተዋቸው ብዙ ነገሮች አሉ። በዚህ ክፍል እንደ ምሳሌ ላነሳው የምፈልገው ግን እርሷ በእኔ ላይ ያላትን እምነት ነው። ልጆቻችን ከተወለዱ ጥቂት ቀናት ጀምሮ ልጆች በማጠብ ሂደት ምቾት የሚሰማት እኔ ሳጥባቸው ነው:: ስለዚህ ብዙ ጊዜ እኔ ልጆቻችንን እንዳጥባቸው ግፊት ታደርጋለች።

አንዱ ሌላውን ባለማመን ሳይሆን ለመርዳት ዝግጁ ባለመሆን ልጅን ማሳደግ የሚጠይቀውን ኃላፊነት ለመውሰድ የሚሰንፉ ባሎችና ሚስቶች ይኖራሉ።

ከስንፍናቸው የተነሳ የማሳደጉ ኃላፊነት ለአንዱ አካል ብቻ እንዲተው ያደርጋሉ። የመጨረሻው ባህላችን የፈጠረው የወንድና የሴት፣ የባልና የሚስት ልማዳዊ የሥራ ክፍፍል ባለትዳሮችን ለግጭት በመዳረግ የሚጠቀስ ምክንያት ነው፡፡ ይህ ከስተትም የምንመራበት ባህል ውጤት ነው። መልካም ባህላችን እንደተጠበቀ ሁኖ ነገር ግን የወለድናቸውን ልጆች በማሳደግ ሂደት በጋራ ተንከባክበ የማሳደጉ ኃላፊነት የጋራ እንደሆነ መረዳት መቻል ተገቢ ነው። በተለይ በውጭ አገር ለምንኖር ኢትዮጵያውያን የውጩ ዓለም የአኗኗር ባህል፣ የሥራ ባህልና ሲስተም ኃላፊነትን ለአንድ ሰው በተለይ ለሚስቶች ብቻ መተውን የሚፈቅድ እንዳልሆነ እናውቃለን። ነገር ግን መተግበር ባለመቻላችን ብዙ ጊዜ በእንደዚህ ዓይነት ችግሮች ምክንያት ልጆችን በማሳደግ ሂደት አለመግባባትና ግጭት ይፈጠራል።

## 2. በዕድሜ ለውጥ የሚፈጠር የልጆችን ፍላጎት አለመረዳት

ልጆችን በማሳደግ ሂደት ሌላው መታየት ያለበት በየጊዜው በልጆች ላይ የሚፈጠር የእድገት ለውጥ ነው። ልጆችን ማሳደግ ከሕጻንነታቸው ጀምሮ ባለው የእድገት ደረጃ ፍላጎታቸውን ማወቅንና አቅም በፈቀደ መጠን ለማሟላት ጥረት ማድረግን ይጠይቃል። በተለይ የመጀመሪያ ልጅ በምናሳድግበት ወቅት በጣም እንድንደናገጥ የሚያደርገን ልጆች የማያቋርጥ ለቅሶ የሚያለቅሱበት ጊዜ ነው። አብዛኛውን ጊዜ ሕጻናት ልጆች የሚያለቅሱበት ምክንያት የርሃብ ስሜት ሲፈጠርባቸው፣ እንቅልፍ ሲመጣባቸው፣ ንጽህናቸው ሲጓደል (ዳይፐር መቀየር ሲያስፈልጋቸው) እና ጤንነት ሳይሰማቸው ሲቀር ነው፡፡ ሕጻናት ፍላጎታቸውን የሚገልጹት በለቅሶ ነው። በለቅሶአቸው የገለጡትን ፍላጎታቸውን በመረዳት በጊዜው የሚያስፈልጋቸውን ከማሟላት ይልቅ ግራ ስንጋባ፣ ስንደናገጥና ስንረበሽ እንታያለን፡፡ ይህ ዓይነቱ የመደናገጥ ስሜት በሌሎች ግንኙነቶቻችንና ሥራዎቻችን ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንዲፈጠር እገዛ ያደርጋል።

ከዕድሜያቸው አንጻር የሚመገቡትን መረዳትና ማሟላት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ አለባበሳቸው፣ የሚጫወቱባቸው ዕቃዎች፣ የሚጫወቱባቸው ቦታዎች፣ አብረዋቸው የሚጫወቱ ሰዎች፣ የሚያዩአቸው የቲቪ ፕሮግራሞች፣ ፊልሞችና የቤተ ክርስቲያን ፕሮግራሞች ለእነርሱ ዕድሜ በሚመጥን መንገድ ሊመርጡላቸው ይገባል፡፡ በየትኛው ዕድሜ ምን ያስፈልጋቸዋል? እንዴትስ ይህን ፍላጎታቸውን ማርካት ይቻላል? የመሳሰሉ መሠረታዊ ጥያቄዎችን አለመጠየቅ፣ አለማወቅ፣ ቢታወቅም ለማሟላት የምንሄድባቸው መንገዶች ከትዳር አጋሮቻችን ጋር የግጭት ምክንያቶች ይሆናሉ። ምክንያቶቹም አንዱ በሌላው ላይ እጅ እንዲጠቁም፣ እንዲያመካኝና እኔን አያገባኝም በማለት ከተጠያቂነት ለማምለጥ ጥረት እንዲያደረግና አለመግባባቶች ይበልጥ እንዲባባሱ ሊያደርጉ ይችላሉ።

## 3. የትዳር አጋርን ቸል እስኪሉ አዲሱን ልጅ ማፍቀር

በማማከር አገልግሎት ከሚገጥሙኝ የባለትዳሮች ችግሮች አንዱ ልጅ ከወለድን በኋላ ለእኔ ያላት ወይም ያለው ፍቅርና ትኩረት እጅጉን ቀነሰብኝ የሚል ማጉረምረም





ነው። ልጅ ሲኖርና ሳይኖር የምንሆናቸውና የምናደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ፈጽመው ሊለያዩ ይችላሉ። ልጆች ከተወለዱ በኋላ ልጆችን የመንከባከቡ ኃላፊነት ጊዜንና ትኩረትን የሚጠይቅ በመሆኑ ለትዳር ጓደኛችን ሙሉ በሙሉ እንደ ቀድሞው መሆንና ማድረግ ላይሳካልን ይችላል፡፡ ነገር ግን በደንብ ሊታሰብበት የሚገባ ጉዳይ የልጆች ፍቅርና የባልና የሚስት ፍቅር ፈጽሞ የተለያዩ መሆናቸውን የመረዳቱ ጉዳይ ላይ ነው። የባልና የሚስት ፍቅር ልጆች ከመምጣታቸው በፊት የኖርነው፣ ልጆች ከተወለዱ በኋላም በልጆች ሊተካ የማይገባውና ሊተካም የማይችል ግንኙነት ነው። በተቻለ መጠን የጋራ የሆኑ ልጆቻችንን እኛ ብቻ እንደቀረብንና እንደምናስብላቸው አድርጎ በመቁጠር በልጆች ፊት የጋራ ልጆችን ***"ልጄን፣ ልጆቼን"*** በሚሉ ቃላት እየጠሩና እየተናገሩ አንዱ ሌላውን ማግለልና ኃላፊነት እንደማይሰማው አድረጎ በመቁጠር በልጆችም ዘንድ የተዛባ አመለካከት እንዲኖራቸው ማድረግ ፈጽሞ ሊወገድ ይገባል።

ከጤናማ የትዳር ግንኙነቶች መካከል አንዱ ልጆችን ከእግዚአብሔር በስጦታ ተቀብለን የማሳደግ ኃላፊነት አለብን የሚል አቋም ያለን መሆናችን ነው፡፡ ነገር ግን ልጆችን የትዳር የመጨረሻ ግብ አድርጎ መቁጠር በተደጋጋሚ የሚስተዋል ከፍተኛ የባለትዳሮች ስህተት ነው። እኛ የቤተሰቦቻችን የልጅነት ወራት አልቆ ኮሌጅ በመግባት፣ ሥራ በመያዝና በጋብቻ ምክንያት እንደተውናቸው ልጆቻችንም እንዲሁ ማድረጋቸው አይቀሬ ነው። ከቅደም ተከተል አንጻር ከባለትዳሮች ቀጥሎ ልጆች መሆናቸው መረሳት የለበትም።

ከሕጻንነታቸው የተነሳ የምንሰጣቸው ጊዜ፣ እንክብካቤና ትኩረት አስፈላጊና የወላጅ ኃላፊነት ነው። ነገር ግን ባል ከሚስቱ በበለጠ ወይም ሚስት ከባሏ በበለጠ ልጆችን የሚያፈቅሩ ከሆነ አንዳቸው ለሌላቸው ግድ የማይሰጣቸው መሆናቸውን በመናገር የተሳሳተ መልዕክት ለትዳር ጓደኛቸው ያስተላልፋሉ፡፡ ልጆችን በትዳር መካከል ጣልቃ የሚያስገቡ ወላጆች ባገኙት ልጅ ከመደሰት ይልቅ ልጃቸውን ሰላማቸው የሚደፈርስበት፣ የትዳር ግንኙነታቸው የሚሻክርበት፣ በትዳር ግንኙነት እስከሞት የመኖር ዋስትናቸው ችግር ላይ የሚወድቅበትና በየጊዜው አለመግባባትና ግጭት የሚፈጠርበት የግጭት ምክንያት ያደርጓቸዋል፡፡ወደ ማስተዋል መጥተው ውጥረቱን ለማረጋጋት ካልቻሉ ግንኙነታቸው በመለያየት ወይም በፍቺ ሊያበቅ ይችላል። የልጅና የትዳር አጋርን ፍቅር አለመለየትና ሚዛናዊነቱን በጠበቀ መንገድ ግንኙነትን አለመያዝ ለፍቺ ተጋላጭ እንዲሆኑና ብቻቸውን ልጆችን የሚያሳድጉ እናቶች ወይም አባቶች እንዲሆኑ ያስገድዳቸዋል።

## 4. ቀድሞ ስንሆንና ስናደርግ የነበረውን ማድረግ አለመቻል

ልጆች በማሳደግ ስንጠመድ ልጆች ሳይኖሩ በግልም ሆነ በጋራ ስንሆናቸውና ስናደርጋቸው የነበሩ የተለያዩ ጉዳዮችን ለማድረግ ሁኔታዎች አልፈቅድልን ሲሉ ማየት ከምናልፍባቸው የሕይወት ገጽታዎች አንዱ ሂደት ነው። እንደ ሰው ከሚያስፈልጉን

መሠረታዊ ፍላጎቶቻችን መካከል ምግብ አብሮ የመመገብን፣ በቂ እንቅልፍና የጋራ የመኝታ ጊዜ ማግኘትንና የግብረ ስጋ ግንኙነት የማድረግን ፍላጎቶች ባሰኘን ጊዜና ቦታ ለማሟላት የማንችልበት ገደብ ይፈጠርብናል። ቀድሞ ባልና ሚስት ከቦታ ቦታ፣ ከአገር አገር ይዘዋወሩና ይዝናኑ የነበሩ ጥንዶች ከሆኑ ልጆችን የማሳደጉ ኃላፊነት በሥራ እንዲጠመዱ ስለሚያደርጋቸው ለመዝናናት የታቀዱ የጊዜ ሰሌዳዎች የማይፈጸሙበት እንቅፋት ያጋጥማቸዋል። እንዲህ ዓይነቱ ገጠመኝ በወላጅነት ኃላፊነት ውስጥ ያለን ሰዎች ሁሉ የምናልፍበት ነው::

ወላጅ ከሆንን በኋላ ለራሳችን ፍላጎት ቅድሚያ መስጠታችን ይቀርና የልጆችን ፍላጎት እንድናስቀድም እንገደዳለን። ለራሳችን ፍላጎት መኖር እየቀነሰን ለልጆቻችን ፍላጎት መሟላት እንኖራለን። በዚህ ወቅት ቀድሞ ስንሆነው እና ስናደርገው የነበረ ነገር ይቀራል:: የተፈጠረውን አዲስ ነገር ደግሞ መላመድ ይከብደናል:: የቀሩት ነገሮች የምንወዳቸውና የምንፈልጋቸው ነገሮች ከመሆናቸው የተነሳ በውስጣችን የስሜት ለውጥ ይመጣል:: የተለያዩ እንግዳ የሆኑ መጥፎ ስሜቶችም ሊፈራረቁብን ይጀምራሉ። አንዳንድ ጊዜ የትዳራችንን ሰላም ለመጠበቅ፣ በትዳር ጓደኛችን ላይ ውጥረት ላለመፍጠርና ቤተሰባችንን ላለመረበሽ ስንል መታገስን በመምረጥ ስሜታችንን በውስጣችን አምቀን ለመያዝ እንገደዳለን:: ነገር ግን በውስጣችን የሚፈጠሩ እንግዳና መጥፎ ስሜቶችን በውስጣችን አምቀን መያዛችን እንዳሰብነው የቤተሰባችንን ሰላም ሊጠብቅልን አይችልም:: ይልቁንም ይበልጥ ይጎዳንና ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ምሬት ወይም ቁጣ በሞላበት ንግግር ስሜታችንን በማውጣት እንድንገልጥ ያስገድደናል:: በአድማጮቻችንም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊፈጥርና ለአለመግባባትና ለግጭት መፈጠርና መባባስ ዋና ምክንያት ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ልጆች ከመወለዳቸው በፊት ስንሆናቸውና ስናደርጋቸው የነበሩ ነገሮች በመቀነሳቸው ወይም በመቅረታቸው ምክንያት ስሜታችን ከተጎዳ ከመደበቅ ይልቅ በቅንነት፣ በግልጥነት፣ በትእግስትና ወቅታዊውን እውነታ በመረዳት ተወያይተን ነገሮች መሆን ባለባቸው ትክክለኛ መስመር ላይ እንዲቀጥሉ ገንቢ አስተዋጽኦ ማበርከት እንጅ ስሜታችንን በመደበቅ ቆይቶ ለማቅናት የማንችለው የትዳር ችግር እንዲሆን መፍቀድ የለብንም::

ልጆች ከመወለዳቸው በፊት የነበረን ዓይነት የፈለግነውን ሁሉ የመሆንና የማድረግ ነጻነትም ልጆች ከተወለዱ በኋላ ሊኖረን አይችልም:: ይህንን በመረዳት ልጆችን ለማሳደጉ ኃላፊነት ምኞታችንንና ፍላጎታችንን በተወሰነ ደረጃ ለመሰዋት መዘጋጀት እንጂ ይህ ኃላፊነት የወላጅነት ግዴታችን መሆኑን መርሳት ተገቢ አይደለም:: ይህንን ማሕበራዊ ኃላፊነትና እውነታ ማሕበረሰባችን ለምሳሌ ያክል:- "***ሳትወልድ ብላ***" "***ሳትወልድ ተኛ*** " " ***ሳትወልድ ተዝናና*** " ... በሚባሉ አባባሎች ወይም ማሕበራዊ ፍልስፍናዎች ሲያንጸባርቀው ይታያል። እነዚህ አባባሎች የሚያስተላልፉት መልዕክት ልጆች ከወለድን በኋላ ፈጽሞ አንበላም፣ አንተኛምና አንዝናናም ማለትን ሳይሆን ቀድሞ





ብቻችንን በትዳር ውስጥ እያለን ስንሆናቸውና ስናደርጋቸው የነበሩ ነገሮችን ልጆች ከወለድን በኋላ መሆንና ማድረግ አንችልም የሚል መልዕክትን ነው::

በቅርብ እርቀት አከታትሎ መውለድን በተመለከተ የተለያዩ ሰዎች ጠቀሜታ እንዳለው ሲናገሩ አንዳንዶች ደግሞ ጎጅነቱን በማጉላት አስተያየት ሲሰጡ ይደመጣሉ። እቅደው ወይም እንዲሁ ድንገት በተፈጠረ እርግዝና አከታተለው ልጅ የሚወልዱ ባለትዳሮች በልጆቻቸው መካከል ያለው የዕድሜ ልዩነት ከአስራ አንድ (11) ወር እስከ ሁለት (2) ዓመት ሊሆን ይችላል። ተከታትለው የተወለዱ ልጆችን ማሳደግ በአንድ ጊዜ ብዙ አቅምንና ጊዜን የሚጠይቅ ሲሆን ነገር ግን በአግባብና በመተሳሰብ ካልተረዳዳን በስተቀር በአንድ ሰው ላይ ጫና የሚፈጠር ከሆነ አድካሚ፣ አሰልቺ፣ አስጨናቂና የማያስደስት ሊሆን ይችላል። የተወለዱት ልጆች ተመሳሳይ ጾታ ያላቸው ከሆነ ለታላቁ ልጅ የምናደርጋቸው ነገሮች በአብዛኛው ለታናሹ ልጅም ጠቃሚወች ሊሆኑ ይችላሉ:: ወንድና ሴት ልጆች ካሉን ግን በአንድ ጊዜ የሁለቱን ፍላጎት ለማሟላት የምንጠየቀው መስዋዕትነትና ፈተና ካባድ ሊሆን ይችላል።

እነዚህ ሁኔታዎች ሲደራረቡ ወላጆች የራሳችንን ፍላጎት ለማሟላት የማንችልበትና የልጆቻችንን ፍላጎት ለማሟላት የምንጠየቅበት ውጥረት ውስጥ እንገባለን:: የቀድሞ አስደሳችና አዝናኝ ነጻነቶቻችን ይቀራሉ ወይም እንድንቀንሳቸው እንገዳዳለን:: አንዳችን ለአንዳችን የምንሰጠው እንክብካቤና የግል ጊዜ የፍቅር መቀነስ በሌለበት ወቅት እንኳን የወላጅነት ኃላፊነታችን ከፈጠረብን ጫና አንጻር የቀድሞውን ያህል የተሟላ አይሆንም:: ባለትዳሮች ወደ ወላጅነት ስንሸጋገር ይህንን ሃቅ ወደ መረዳት ብስለትም ጭምር ካልተሸጋገርን እነዚህ ለውጦች በእርግጥም የጤናማ የትዳር ግንኙነት እንቅፋቶችና ችግሮች መሆናቸው አይቀሬ ነው:: ስለዚህ ወላጆች በእውቀትና በብስለት እያደግን ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ለትዳር ጓደኛችንም ሆነ ለልጆቻችን ተገቢውን ፍቅር፣ እንክብካቤና ትኩረት መስጠትን ሁል ጊዜም በመለማመድና በመማር የትዳር ትምህርት ቤት ተማሪዎች መሆን ልንቀጥል ይገባል:: በዚህ መንገድ ስንቀጥል ብቻ ነው ቤተሰባችን ክርስቶስን በሚያከብር የፍቅር ኅብረት የታነጸ፤ ባልና ሚስት በጽኑ ትብብርና መደጋገፍ የሚረዳዱበት የቀጣዩ ትውልድ ማደጊያ ማዕከል መሆን የሚችለው::

ሌላው የመጀመሪያው ልጅ ሕጻንነቱ ሊረሳና እንደ ትልቅ ሰው ብዙ ነገር ልንጠብቅበት፣ ኃላፊነት ልናሸክመው፣ ልናዘውና እንደ አዋቂ ሰው ልናየው እንችላለን። አከታትሎ ታናሽ ወንድም (እህት) ስለመጣባቸው ሕጻናት መሆናቸው ይረሳል። የመጀመሪያው ልጃችንና ሁለተኛው ልጃችን ያላቸው የዕድሜ ልዩነት የአንድ ዓመት ከአንድ ወር (የ13 ወር) ልዩነት ነበርና ትልቁን ልጃችንን አንዳንዴ ሕጻንነቱን በመርሳት እንደ ትልቅ ሰው እያየነው እንቸገር ነበር። ወዲያውኑ ወደ አእምሮችን መለስ በማለት ራሳችንን እናርማለን ወይም አንዳንዴ ባለቤቴ "ሕጻን ነው እኮ!" ትለኛለች:: አንዳንዴ

እኔው ራሴ ሕጻንነቱን እስታውሳታለሁ፡፡ አንዳችን ለአንዳችን እያስታወስንና እያሳሰብን ልጃችንን እንደ ሕጻንነቱ ለመንከባከብ ጥረት እናደርጋለን፡፡

## III. የመጀመሪያ ልጅንና ተከታትለው የተወለዱ ልጆችን በማሳደግ ለሚፈጠሩ ግጭቶች መፍትሔዎች

አከታትሎ በመውለድና በማሳደግ ሂደት ላይ የሚፈጠሩ ችግሮች የአለመግባባትና የግጭት ምክንያት በመሆን የጤነኛና የደስተኛ ትዳር ግንኙነት እንቅፋት እንዳይሆኑ በጥሞና በመመዘን እንደ ባለትዳር፣ እንደ ወላጅና ኃላፊነት እንደሚሰማው ሰው ለችግሮች መፍትሔ ማፈላለጉ የክርስቲያን ባለትዳርና ወላጅ ኃላፊነት ነው። ስለሆነም ከዚህ በታች አማራጭ የሆኑ የመፍትሔ አሳቦችን በመጠቆም ለመግለጥ እወዳለሁ።

### 1. መረዳት፡- የመልካም ወላጅ ባሕርይን መረዳትና በየጊዜው መለማመድ /ማቴ.6:9፣ ሮሜ.8:15፣ገላ.4:6 እና ኤፌ.3: 15/

ክርስቲያን ወላጆች ልንከተለውና ልንመስለው የሚገባን የእግዚአብሔርን የአባትነት ምሳሌነት ነው። *"በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፥... በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና። አባ አባት ብለን የምንጮኽበትን የልጅነት መንፈስ ተቀበላችሁ እንጂ እንደገና ለፍርሃት የባርነትን መንፈስ አልተቀበላችሁምና።"* በማለት በእኛና በእግዚአብሔር መካከል ያለው ግንኙነት የአባትና የልጅ ግንኙነት እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ አስረግጦ ይነግረናል። በእነዚህ የቅዱሳት መጽሐፍት ክፍሎች እንደተገለጠው የእግዚአብሔርን አባትነት ይበልጥ መረዳትና መለማመድ የምንጀምረው ልጆችን ወልደን ስናሳድግ ነው። እንደ ክርስቲያን ወላጅ ልንከተላቸው ከሚገቡን የእግዚአብሔር የአባትነት ምሳሌነቶች መካከል ጥቂቶቹን ከዚህ በመቀጠል እንዳስሳለን፡-

#### 1) በማይለዋወጥ ፍቅር መውደድ

እግዚአብሔር በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ እንዲሁ ወድዶናል፤ ከታላቅ ፍቅሩም የተነሳ በምህረቱና በጸጋው በመሸከምና ዋጋ በመክፈል በቤቱ ልጆቹ ሆነን እንድንመላለስ ተቀብሎናል፡፡ ይህን የአባትነት ምሳሌ በመከተል ልጆቻችንን በእውነተኛ ፍቅርና በየጊዜው ምህረት በማድረግ በልበ ሰፊነት ልንሸከማቸውና ፍቅራችንን በተለያየ መንገድ ልንገልጽላቸው ይገባል /ሮሜ 8: 31-32፣ 2ተሰ 2፡ 16፤ ዮሐ 16፡ 27/።

#### 2) በልጆቻችን መደሰት

እግዚአብሔር በልጆቹ ደስ እንደሚለው ሁሉ በወለድናቸው ልጆች መደሰት መቻል አስፈላጊ ነው። በልጆቻችን መደሰት ከቻልን ብዙ ጊዜና መሥዋዕትነት ጠያቂ ለሆነው ልጆችን የማሳደግ ኃላፊነት አቅምና ኃይል ይኖረናል። *"አምላክሽ እግዚአብሔር በመካከልሽ ታዳጊ ኃያል ነው በደስታ በአንቺ ደስ ይለዋል፥ በፍቅሩም ያርፋል፣ በእልልታም በአንቺ ደስ ይለዋል ይባላል።"* /ሶፎ 3: 17/





#### 3) በጽድቅ ወደ ጽድቅ መንገድ መምራት

እግዚአብሔር በባሕርይው፣ በሥራውና በመንገዱ ሁሉ ጻድቅ አምላክ ነው። *"እግዚአብሔር በመንገዱ ሁሉ ጻድቅ ነው በሥራውም ሁሉ ቸር ነው።"* /መዝ 145: 17/ እግዚአብሔር ልጆቹን በጽድቁ፣ ወደ ጽድቅ የሚመራ መልካም አባት ነው። *"... እንደ አምላካችንም ጻድቅ የለምና ከአንተ በቀር ቅዱስ የለም።"* /1ኛሳሙ 2፡ 2/ በዚህ በመልካሙ አባት መንገድ በመጓዝ ክርስቲያን ወላጆች ልጆችን በምክር፣ በማስተማር፣ ምሳሌ በመሆን፣ በማስጠንቀቅ፣ በመገሰጽና የሚመርጧቸው ነገሮች ሊያስከትሉ የሚችሉትን ውጤት ቀድመው እንዲያስቡ በማሳየት ልጆቻችንን ወደ ጽድቅ መንገድ የመምራት ድርሻችንን በጥንቃቄ ልንወጣ ይገባል።

#### 4) ለልጆች የምንገባውን የተስፋ ቃል ለመጠበቅ ጥረት ማድረግ

እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን የማይዋሽና ለልጆቹ የገባውን ቃል ኪዳን (የተስፋ ቃል) የሚፈጽም የታመነ አባትና አምላክ ነው። *"ደግሞ እኔ ግብፃውያን የገዙአቸውን የእስራኤልን ልጆች ልቅሶ ሰማሁ ቃል ኪዳኔንም አሰብሁ። ስለዚህም ለእስራኤል ልጆች እንዲህ በላቸው። እኔ እግዚአብሔር ነኝ፥ ከግብፃውያንም ባርነት አወጣችኋለሁ፥ ከተገዥነታቸውም አድናችኋለሁ በተዘረጋ ክንድ በታላቅ ፍርድም እታደጋችኋለሁ፥ለእኔም ሕዝብ እንድትሆኑ እቀበላችኋለሁ፥ አምላክም እሆናችኋለሁ እኔም ከግብፃውያን ባርነት ያወጣኋችሁ እግዚአብሔር አምላካችሁ እንደሆንሁ ታውቃላችሁ።ለአብርሃምና ለይስሐቅ ለያዕቆብም እሰጣት ዘንድ ወደ ማልሁባት ምድር አገባችኋለሁ እርስዋንም ርስት አድርጌ እሰጣችኋለሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝ።"* /ዘጸ 6: 5-8፤ 12: 51/ በማለት መጽሐፍ ቅዱስ ከሚሰጠው ምስክርነት እግዚአብሔር ቃሉን የሚጠብቅ አባት መሆኑን እንማራለን። እዚህ ላይ እንደ እግዚአብሔር ሁሉን እንችላለን እያልኳችሁ አይደለም ነገር ግን ለልጆቻችን ልናደርገው የምንችለውን ብቻ ቃል መግባትና የገባነውን ተስፋ መፈጸም መቻል ተገቢ መሆኑን ለማሳየት ነው። ወደ ፊት በእኛ ላይ ያላቸው እምነት እየጠፋ እንዳይመጣ የሰጠነውን ተስፋ መፈጸም ባልቻልን ጊዜ ደግሞ ለምን መፈጸም እንዳልቻልን ማስረዳትና ይቅርታ መጠየቅን ማስለመድ ይጠበቅብናል፡፡ በተሳካልንና በቻልን ጊዜ የሰጠነውን ተስፋ ለመፈጸም መትጋት እንጂ ውሸትን ለልጆቻችን እንዳናስተምራቸው መጠንቀቅ ያስፈልገናል።

#### 5) ለቁጣ መዘግየት

እግዚአብሔር ለቁጣ የዘገየ ነው። ቃሉ እንደሚናገረው እግዚአብሔር ለቁጣ የማይፈጥነው ርኅሩኅና መሐሪ አባት በመሆኑ ነው። *"እግዚአብሔር ርኅሩኅና መሐሪ ነው፥ ከቍጣ የራቀ፥ ምሕረቱም ብዙ ነው እግዚአብሔር ለሚታገሡት ቸር ነው። ምሕረቱም በሥራው ሁሉ ላይ ነው።"* /መዝ 145: 8-9/ ይህ የእግዚአብሔር ታጋሽነት ወላጆች ከልጆቻችን ጋር ባለን ግንኙነት ልንከተለው የሚገባን ሌላው የመልካሙ አባት ምሳሌነት ነው። በሚያጠፉት ነገር ልጆቻችንን መቆጣት ሊገባን ይችላል። ነገር ግን ሁልጊዜ ለቁጣ መፍጠን የለብንም። ለልጆቻችን ርኅሩኅና መሐሪ በመሆን ይቅርታንና መቻልን እያስተማርናቸው ጥፋታቸውን በግልጥ በማሳየትና በማሳመን አልፎ አልፎ የምንቆጣበትን ምክንያት እንዲረዱ ልናግዛቸው ይገባል። መቆጣት ማለት የእግዚአብሔር ቃል እንደሚናገረው

በጌታ ምክርና ተግሳጽ ማሳደግ እንጅ መጮኸ፣ መናደድና በዱላ መደብደብ የመሳሰሉትን ማድረግ ማለት አይደለም። ስለዚህ ወላጆች ልጆቻችንን ማስመረርን በማስወገድ በጌታ ምክርና ተግሳጽ የማሳደግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መንገድ ሁል ጊዜ መከተልና መለማመድ ይጠበቅብናል። *"እናንተም አባቶች ሆይ፥ ልጆቻችሁን በጌታ ምክርና በተግሣጽ አሳድጉአቸው እንጂ አታስቆጡአቸው።"* /ኤፌ 6: 4/

### 6) ያለአድልዎ ማሳደግ

እግዚአብሔር ከባሕርይው ፊትን አይቶ አያዳላም። *"እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ ተብሎ ስለ ተጻፈ የጠራችሁ ቅዱስ እንደ ሆነ እናንተ ደግሞ በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ። ለሰው ፊትም ሳያደላ በእያንዳንዱ ላይ እንደ ሥራው የሚፈርደውን አባት ብላችሁ ብትጠሩ በእንግድነታችሁ ዘመን በፍርሃት ኑሩ።"* /1ጴጥ 1፡ 2/ እግዚአብሔር የሁሉ አባት ነው። *"ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሠራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ።"* /ኤፌ 4: 6/ ንጉስ ኢዮሳፍጥ በሰው ፊት በማድላት እንዳይሰሩ በመንግስቱ ውስጥ የነበሩ የፍትህ ባለስልጣናትን ሲመክር ማዳላት እግዚአብሔር የሚጠላው ባሕርይ እንደሆነ *"... ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰው አትፈርዱምና፥ እርሱም በፍርድ ነገር ከእናንተ ጋር ነውና የምታደርጉትን ተመልከቱ። አሁንም እግዚአብሔርን መፍራት በእናንተ ላይ ይሁን በአምላካችንም በእግዚአብሔር ዘንድ በደልና ለሰው ፊት ማድላት መማለጃም መውሰድ የለምና ሁሉን ተጠንቅቃችሁ አድርጉ ..."* /2ዜና 19: 7/ በማለት አስጠንቅቋቸዋል።

ወላጆች ልጆቻችንን በአድልዎ የምናሳድጋቸው ከሆነ ቅናትና ጠላትነት በመካከላቸው እንዲፈጠር እያደረግን ነው። ልጆች በወላጆቻቸው እንደማይወደዱ፣ ተቀባይነት እንደሌላቸውና ትኩረት እንደማይሰጣቸው ይሰማቸዋል። የስነ-ልቦና ጉዳትም በእድገታቸው ላይ ይፈጠርባቸዋል። *"እስራኤልም ዮሴፍን ከልጆቹ ሁሉ ይልቅ ይወደው ነበር፥ እርሱ በሽምግልናው የወለደው ነበርና በብዙ ኅብር ያጌጠችም ቀሚስ አደረገለት። ወንድሞቹም አባታቸው ከልጆቹ ሁሉ ይልቅ እንዲወደው ባዩ ጊዜ ጠሉት፥ በሰላም ይናገሩትም ዘንድ አልቻሉም።"* /ዘፍ 37፡ 2-4/

### 7) ከጉዳት መጠበቅ

የእግዚአብሔር አባትነቱን ከገለጠበት *ሥራው* አንዱ ልጆቹን (ሕዘቡን) ከተለያዩ ጠላቶች፣ አስቸጋሪ ሁኔታዎችና ሊያጠፋቸው ከሚመጣ ማንኛውም ነገር መጠበቅ ነው። ለሕዝቡ ካለው ታላቅ ፍቅር የተነሳ ሕዝቡን ይጠብቃቸዋል። የእግዚአብሔር ጥበቃ ልጆቹ ይበልጥ በእርሱ እንዲተማመኑበት ያደርጋቸዋል። *"ስለ ብንያምም እንዲህ አለ በእግዚአብሔር የተወደደ በእርሱ ዘንድ ተማምኖ ይኖራል፤ ቀኑን ሁሉ ይጋርደዋል፥ በትከሻውም መካከል ያድራል"* /ዘዳ 33፡ 12/። ይህ እውነታ የወላጅነት አንዱ መሠረታዊ ኃላፊነት ልጆችን ከተለያዩ ጎጂ ነገሮች በሚችሉት መንገድ ሁሉ መጠበቅ፣ መከላከል፣ ማስጠንቀቅና ማስጣል (መታደግ) መሆኑን ያስታውሰናል። ወላጆች እንደ እግዚአብሔር በሁሉ ቦታ የምንገኝና ሁሉን ቻይ ባንሆንም በምንችለውና አቅማችን በፈቀደ መጠን ልጆቻችን አካላዊ፣ ስነልቦናዊና መንፈሳዊ ደህንነታቸው የተጠበቀ እንዲሆን ከክፉ፣ ከሚጎዳ፣ ከሚያጠፋ፣ ከስህተት ትምህርትና ከጽድቅ መንገድ ከሚያስወጣ ማንኛውም ነገር ለመጠበቅ ማንኛውንም መስዋትነት የመክፈል ታላቅ ኃላፊነት አለብን።





### 8) የሚስፈልጋቸውን ማቅረብ

የ"አባት" ትርጓሜ ብዙ ጊዜ የአንድ ነገር ምንጭ ወይም ጀማሪና አቅራቢ መሆንን ያመለክታል። የእግዚአብሔር አባትነት አንድያ ልጁን ለደህንነታችንን በመስጠት ተገልጿል። ቅዱሳት መጽሐፍት እንደሚመሰክሩት፡- እግዚአብሔር ሕይወት ሰጭ /ገላ 1፡4/፣ የመንፈሳዊ በረከት ምንጭ /ኤፌ1፡ 3/፣ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ለአማኞች የሚሰጥ /ሐዋ 2፡ 33/ እና ከሁሉ በላይ የሚሆን፣ በሁሉም የሚሠራ፣ በሁሉም የሚኖር /ኤፌ4፡ 6/ አባት ነው። *"ለምኑ፥ ይሰጣችሁማል፤ ፈልጉ፥ ታገኙማላችሁ፤ መዝጊያን አንኳኩ፥ ይከፈትላችሁማል። የሚለምነው ሁሉ ይቀበላልና፥ የሚፈልገውም ያገኛል፥ መዝጊያንም ለሚያንኳኳ ይከፈትለታል። ወይስ ከእናንተ፥ ልጁ እንጀራ ቢለምነው፥ ድንጋይን የሚሰጠው ከእናንተ ማን ሰው ነው? ዓሣስ ቢለምነው እባብን ይሰጠዋልን? እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠትን ካወቃችሁ፥ በሰማያት ያለው አባታችሁ ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መልካም ነገርን ይሰጣቸው?"* /ማቴ 7፡ 7-11፣ መዝ 68፡ 5/ ይህ የእግዚአብሔር የመልካም አባትነት ባህርይ ወላጆች አቅማችን እንደ ፈቀደ ለልጆች ሁለንተናዊ እድገት የአቅርቦት ኃላፊነት ያለብን መሆኑን የሚያሳይ ምሳሌ ነው። ክርስቲያን ወላጆችም የመልካሙን አባት መልካም ምሳሌነት በመከተል ልንኖር ይገባናል።

## 2. መጣል፡- ለጤናማና ደስተኛ ቤተሰብነት የግንኙነት መሠረት መጣል

ጤናማና ደስተኛ ትዳር ለጤነኛና ለደስተኛ ቤተሰብ መሠረት ነው። ጤነኛ የሆነ ቤተሰብ መመሥረትና መምራት የሁለቱም ባለትዳሮች የጋራ ኃላፊነት መሆኑ መዘንጋት የለበትም። ለጤነኛና ደስተኛ ቤተሰብ መልካም የሆነ ተግባቦትና የእርስ በርስ መከባበር መኖሩ በጣም አስፈላጊ ነው። መልካም ተግባቦት በቤተሰብ መካከል ካለ አንዱ የሌላውን ሃሳብ፣ ችግርና ፍላጎት ለመረዳት ዕድል ይሰጣል። መልካም ተግባቦት ወላጆች ከልጆቻቸው ጋር ተገቢውን ግንኙነት በማድረግ ልጆች ግዴታቸውን፣ ገደባቸውን፣ መብታቸውንና ኃላፊነታቸው በግልጥ እንዲረዱ እንዲያግዟቸው ከማስቻሉም ባሻገር ልጆች ፍላጎታቸውን በነፃነት የመግለጥ እድል እንዲያገኙ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው።

ጤናማና ደስተኛ ቤተሰብ በጋራ እግዚአብሔርን በማምለክ ይመሠረታል። ወላጆች በቤታቸው ከእግዚአብሔር ጋር በጸሎትና ቃሉን በማጥናት በሚያደርጉት መንፈሳዊ ሕብረት ለልጆቻቸው መንፈሳዊ ልምምድን ማካፈልና ማውረስ ይጠበቅባቸዋል። *"የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ። እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን"* /ኢያሱ 24፡ 15/። የሕጻኑ የኢየሱስ ቤተሰቦች ዮሴፍና ማሪያም እንደ ሙሴ ሕግ መሥዋዕት ለማቅረብ ወደ ኢየሩሳሌም መሄዳቸው፣ ሕጻኑንም ለካህኑ ለስምዖን በመስጠት በመቅደስ ውስጥ እንዲጸለይለት ማድረጋቸው፣ በየዓመቱ የፋሲካ በዓል በሚከበርበት ወቅት ወደ ኢየሩሳሌም መውሰዳቸውና እንደ ወጋቸው በ12 ዓመቱ ወደ መቅደስ ማምጣታቸው ለእግዚአብሔር በመገዛት እንደሚኖር ወላጅ ለመንፈሳዊ ነገር ግድ የሚላቸው እንደነበሩ ያሳየናል። የዚህ መልካም ጥረት ውጤት ሕጻኑ ኢየሱስ በመቅደስ በመምህራን መካከል ተቀምጦ በመስማትና በመጠየቅ ባሳየው ትጋት፣ በአባቱ ቤት መኖር እንዳለበት

በማስረዳቱና ወደ ናዝሬት በመመለስ ለወላጆቹ መታዘዝ በመቀጠል በተወልን ምሳሌነትም ተንጸባርቋል /ሉቃ 2: 22-52/፡፡

ወላጆች በልጆቻችን ላይ በልጅነታቸው የምንጥለው መሠረት ለነገው መንፈሳዊ፣ ቤተሰባዊና ማሕበራዊ እሴቶቻቸው፣ ለተለያዩ ክህሎታቸውና የሕይወት ጉዟቸው አስተዋጾው ከፍተኛ ነው። በወላጆች መካከል ያለው በጋራ እየተወያየን፣ አለመግባባቶችንና ግጭቶችን በግልጥነትና በመመካከር እየፈታን፣ ለአጠፋናቸው ጉዳዮች ራሳችን ኃላፊነትን እየወሰደን፣ ይቅርታ እየጠየቅንና እየሰጠን የመኖር ሂደት ምሳሌነታችንን ተከትለው በትክክለኛው የሕይወት መንገድ ወደ ፊት መራመድን እንዲማሩ መልካም መሠረት ይጥላል። ሰው ከሰው ጋር ሲኖር አለመግባባትና ግጭት አይቀሬ ነውና አለመግባባትን በጋራ በመነጋገር በሰላምና በይቅርታ መፍታት እንደሚቻል ትልቅ ትምህርት እንዲያገኙ ማድረግ በቀጣይ ኑሯቸው ላይ የሚያመጣው አዎንታዊ ተጽዕኖ ጉልህ ነው። *"ልጅን በሚሄድበት መንገድ ምራው፥ በሸመገለም ጊዜ ከእርሱ ፈቀቅ አይልም።" /ምሳሌ 22: 6/*[72]

## 3. መለማመድ፡- መርሆዎችን በመተግበር በጋራ መለማመድ

ተከታትለው በሚወለዱ ልጆች ምክንያት የሚፈጠሩ ግጭቶችንና አለመግባባቶችን ለመቀነስ እንዲቻል የሚረዱ መርሆዎችን መማር፣ መረዳትና መተግበርን መለማመድ በጣም ጠቃሚ እርምጃ ነው፡፡ ወላጆች እነዚህን ጠቃሚ መርሆዎች በአጭሩ ለመያዝና ለማስታወስ እንድንችል በማሰብ እንደ ወላጅ በየጊዜው ልንለማመዳቸው የሚገቡንን ዘጠኝ መሠረታዊ እውነቶችን እንደሚከተለው እንቃኛለን:-

### 1) እንጀምር፡- በተሰጡን ልጆች በጋራ መደሰትና እግዚአብሔርን በማመስገን የወላጅነትን ኃላፊነት ጉዞ እንጀምር

በተሰጡን ልጆች በጋራ በመደሰትና እግዚአብሔርን በማመስገን የወላጅነትን ኃላፊነት ጉዞ እንጀምር። በወላጅነት የሕይወት ጉዞ ውስጥ የመጀመሪያው መሠረታዊ መርህ እግዚአብሔር በሰጠን ልጆች መደሰት ነው። ምጥን፣ ሕመምን፣ ስቃይን በመርሳት በተሰጡን ድንቅ ስጦታዎች እግዚአብሔርን በማመስገን መደሰት አስፈላጊ ነው። ልጆች ለትዳራችንና ለቤተሰባችን የደስታ ምክንያት በመሆን በቤታችን የመሳቅ፣ ነፃነት ባለው መንገድ የመጫወትና የመዝናኛ ምክንያት እንዲሆኑ ሁኔታዎችን መምረጥ፣ ማዘጋጀት፣ መወሰንና ማመቻቸት የዚህ ጣፋጭ ሕይወት ተካፋዮች እንድንሆን ያስችለናል። *"መልአኩም እንዲህ አለው:- ዘካርያስ ሆይ፥ ጸሎትህ ተሰምቶልሃልና አትፍራ ሚስትህ ኤልሳቤጥም ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች፥ ስሙንም ዮሐንስ ትለዋለህ።ደስታና ተድላም ይሆንልሃል፥ በመወለዱም ብዙዎች ደስ ይላቸዋል። /ሉቃ 11: 3-14/*

[72] www.faiththerapy.org/answer-by-topic-disfunctionla and healthy familes Accssed Apiril 13, 2014.





ሁለተኛው መርህ እንደ ወላጅ በጋራ ያለንን ኃላፊነት በመከፋፈል ለልጆቻችን መልካም እናትና አባት የመሆንን አስፈላጊነት የመረዳት መርህ ነው! መልካም ወላጆች ማለትም በፍቅር ለልጆቻቸው ምሳሌነት በተሞላ ሕይወት አፍቃሪዎች፣ መልካም አሳቢዎች፣ የልጆቻቸውን ፍላጎት ለማሟላት የሚጥሩ፣ የልጆችን የወደፊት ሕይወት በማሰብ ችሎታቸውን፣ ጸጋቸውን፣ ዝንባሌያቸውን፣ ፕሮፌሽናቸውንና ራዕያቸውን ለይተው እንዲዘጋጁና በነገር ሁሉ እንዲያድጉ የሚረዱ ወላጆች እንድንሆን ያስፈልጋል። *"እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠት ካወቃችሁ፥ በሰማይ ያለው አባት ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸው?" /ሉቃ 11: 13/*

### 3) እንማር፡- በአገኘነው አጋጣሚና ሁኔታ እንማር

ፍጹምና እንከን የለሽ ወላጅ ልንሆን እንደማንችል በመረዳት ሁልጊዜ ከድካማችን፣ ከሌሎች ሰዎችና ከተለያዩ ሁኔታዎች በመማር ለመለወጥ ዝግጁ መሆን ይገባናል። እንደ ማንኛውም ሰው አቅማችንና እውቀታችን ውስን በመሆኑ ብርቱና ደካማ ጎን አለን፡፡ ብዙ ሁኔታዎችም ይገድቡናል፡፡ የልጆች ተፈጥሮ "የእናት ሆድ ዝንጉርጉር" እንዲሉ የተለያየ ነው፡፡ ወላጆች የልጆችን የተለያዩ ፍላጎቶች ማሟላት ባልቻልን ጊዜ የአቅርቦቶች እናሳነትና አለመኖር ተደማምረው እንደምንፈልገው ዓይነት ፍጹም ወላጅና አሳዳጊ እንዳንሆን ያደርጉናል። ስለዚህ ልጆችን የማሳደግን ሂደት እንዲሁም ሌሎችን ምቹ የሆኑና ምቹ ያልሆኑ ገጠመኞች ሁሉ የመማሪያ መንገዶች አድርገን በመጠቀም ዘወትር ተማሪዎችና የተሻለ ወላጅ ለመሆን ጥረት በማድረግ ማስተዋል ባለጠጎች ልንሆን ይገባል።

### 4) እንረዳዳ፡- የወላጅነት ኃላፊነት የጋራ መሆኑን በመገንዘብ እንረዳዳ

ልጆቻችን የጋራ ልጆች ናቸውና በጋራ ለማሳደግ በማኛውም ሁኔታ ውስጥ መረዳዳት የእናትና የአባት የሁለትዮሽ የወላጅነት ኃላፊነት ነው። የጋራ ልጆቻችንን በጋራ የማሳደግ መረዳዳት በሌለበት ቤተሰብ ውስጥ የወላጅነት ኃላፊነት የአንድ አካል ብቻ የሆነ ግንኙነት፣ ፍቅር፣ እንክብካቤና ጥረት ይሆናል፡፡ ይህ ክፍተት በልጆች መንፈሳዊ፣ ስነ ልቦናዊና ማሕበራዊ ሕይወት ላይ ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ ይፈጥርባቸዋል። በአንድ ወቅት ለአንድ ቤተሰብ የትዳር ችግር የምክር አገልግሎት ከሰጠሁና የምክር አገልግሎቴ ውጤታማ ከሆነ በኋላ እናት ስለምክር አገልግሎቱ ውጤት ስትገልጥ "በ19 ዓመታት የትዳር ዘመኔ ይሰማኝ የነበረ ስሜት ብቻየን ልጆችን የማሳድግ ሴት እንደሆንኩ ነበር፡፡ ነገር ግን ዛሬ ለመጀመሪያ ጊዜ ተስፋ ተሰማኝ" አለች። ይህች እናት ይህንን የተናገረችው ልጆችን በማሳደግ ሂደት ውስጥ የቤት ወጭ ከመስጠት በስተቀር ሌላ የባልነትና የአባትነት ኃላፊነት የመወጣትን ጉዳይ በተመለከተ ግንዛቤና ልምድ ከሌለው የትዳር ጓደኛዋና የልጆቿ አባት ጋር ትኖር ስለነበር ነው።

ልጆችን በማሳደግ ሂደት በጋራ በመረዳዳት በልጆች እድገት ላይ መልካም ተጽዕኖ ማምጣት ተገቢ ነው። ብዙ በጋራ ልንረዳዳባቸው የሚገቡን ጉዳዮች አሉ፡፡ ልጆችን መመገብ፣ ልብሳቸውን መቀየር፣ ንጽህናቸውን መጠበቅና ትምህርታቸውን በሚገባ

መዝናኛ ቦታ መዝናናት፣ ወደ ሕጻናት መጫዎቻ ቦታዎች በመሄድ ጓደኞቻቸውን አግኝተው ማውራት፣ መጫወትና መዝናናት ይፈልጋሉ። ወላጆች ለልጆቻቸው ጊዜ በመስጠት ስለቆይታቸው፣ ስለትምህርታቸው፣ ስለጓደኞቻቸው፣ ስለመንፈሳዊ ሕይወታቸው፣ በሰንበት ትምህርት ስለተማሩት የእግዚአብሔር ቃል፣ ስለ ግላዊ ፍላጎታቸውና ስለወደፊት የሚያስቡትን ለወላጆቻቸው እንዲያካፍሉ እድል መስጠት አስፈላጊ ነው።

ለልጆች ጊዜ መስጠት ማለት ከልጆች ጋር አብሮ በመሆን ልጆች ማውራት የሚችሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት ብቻ ሳይሆን ሙሉ ትኩረት በመስጠት ጥሩ አድማጭ መሆን ማለት ነው። ከልጆች ጋር ጊዜ መድቦ አብሮ ማሳለፍ አንዱ የፍቅር መግለጫ ነውና ልጆች ይበልጥ እንደተወደዱና ትኩረት እንደተሰጣቸው በመረዳት ጥሩ ስሜት እንዲሰማቸውና በወላጆቻቸው ይበልጥ እንዲተማመኑ ይረዳቸዋል። ይህን ማድረጋቸው በወላጆች መካከልም መልካም ተግባቦት እንዲጎለብትና ግጭት እንዲቀነስ ከተቻለም እንዳይኖር ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡ የጤናማና የደስተኛ ቤተሰብ አንዱ መለያ በጋራ አብረው ጊዜ ማሳለፋቸውና መግባባት መቻላቸው ነው።





## ለጥንዶች በግላቸውና በቡድን ለማጥናት የሚረዷቸው የውይይት ጥያቄዎች

## የምዕራፍ አስራ ስምንት (18) የውይይት ጥያቄዎች

1. የመጀመሪያ ልጅና ተከታትለው የተወለዱ ልጆች ማሳደግ ማለት ምን ማለት ነው?
2. የመጀመሪያ ልጅንና ተከታትለው የተወለዱ ልጆችን በማሳደግ ሂደት በባለትዳሮች መካከል ለግጭት መንስኤ ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮች ምንድን ናቸው? በመዘርዘር ተነጋገሩበት፡፡
3. የመጀመሪያ ልጅንና ተከታትለው የተወለዱ ልጆችን በማሳደግ በባለትዳሮች መካከል ለሚፈጠሩ የግጭት ምክንያቶች የመፍትሔ መንገዶችን በመዘርዘር ተወያዩ፡፡
4. የመጀመሪያ ልጅንና ተከታትለው የተወለዱ ልጆችን ስለማሳደግ ባለትዳሮች ከእግዚአብሔር የአባትነት ምሳሌነት ምን እንደተማራችሁ በመጥቀስ አንዱ ለሌላው ያካፍል።
5. በመጽሐፉ ውስጥ እንደ የመፍትሔ ሃሳብ ከተጠቀሱት መካከል እንደ መርህ አድረገን በመውሰድ ልንለማመዳቸው የሚገቡ ዘጠኝ መርሆችን በመጥቀስ በሰፊው ተወያዩበት።
6. ልጆችን በማሳደግ እረገድ ጠንካራ ጎናችን ነው የምትሉትን ለሌሎች የምታካፍሉት መልካም ልምድ እንዲሁም የተቸገራችሁበትንና ከሌሎች ልምድ ለመካፈል የምትፈልጉበትን ልምድ በማጣቀስ እርስ በእርስ በመጠያየቅ ተወያዩ።

# ምዕራፍ አስራ ዘጠኝ(19)
# የእንጀራ ልጅን ማሳደግ

ይህ ርዕስ ባለትዳሮች በጋራ ያልወለዱትን ልጅ በማሳደግ ሂደት ሊፈጠሩ የሚችሉ የግጭት ምክንያቶችን የሚመለከት ነው። ይህ ርዕስ ያስፈለገው እንዲህ ዓይነት ሁኔታ የተፈጠረባቸውና ወደ ፊት ሊያጋጥማቸው የሚችሉ ሰዎች ማድረግ ስለሚገባቸው ነገር፣ መውሰድ ስላለባቸው ጥንቃቄና ተግባራዊ እርምጃዎች ግንዛቤ በማስጨበጥ መልካም ግንኙነት ፈጥረው መልካም ወላጅና ባለትዳር ሆነው እንዲቀጥሉ ለመርዳት ነው። በችግሩ ውስጥ ሆነን የምንጠቅሰው ቀውስ ያላጋጠመን ብንሆንም እንኳን አስቀድሞ ሊፈጠሩ የሚችሉ የተለያዩ ችግሮችን ማወቅ ለመጠንቀቅ ይረዳናል። የእንጀራ ልጅ ባላቸው ባለትዳሮች መካከል አብዛኛውን ጊዜ የሚሰሙና የሚታዩ ችግሮችን መረዳት ነገ በራሳችን እንዳይደገም ቅድመ ዝግጅት ለማድረግ በጣም ጠቃሚ ነው። ሌላው ቀርቶ በወለዷቸው ልጆችና በእንጀራ ልጆች መካከል የሚፈጠሩ የተለያዩ ክስተቶች በትዳርና በመልካም ቤተሰብ ግንኙነት ውስጥ የሚፈጥሩት አለመግባባትና ግጭት ቀላል አይሆንም።

## I. የእንጀራ ልጅ ምንነት

በዚህ መጽሐፍ አውድ መሠረት፡- የእንጀራ ልጅ ማለት የባልና ሚስት የሁለቱ የጋራ ልጅ ያልሆኑ፣ ባል ወይም ሚስት ከሌላ የወለዷቸውን ልጆች የሚያመለክት ነው። እንዲህ ዓይነት ክስተት ሊፈጠር የሚችለው ምናልባት ባል ወይም ሚስት ካሁን በፊት ትዳር ኖሯቸው የትዳር ጓደኛቸው በሞት በመለየታቸው ምክንያት እናት ወይም አባት ሁለተኛ ሲያገቡ ከሟች የተወለዱት ልጆች የእንጀራ ልጅ የመሆን እድል ሲያጋጥማቸው ነው፡፡ ባል ወይም ሚስት በጌታ አምነው ክርስቲያን ከመሆናቸው በፊት በነበረ ልምምዳቸው፣ ክርስቲያን ሆነው በዝሙት ኃጢአት በመውደቅ ወይም በአስገድዶ መደፈርና መድፈር የተወለዱ ልጆች ሁሉ የእንጀራ ልጅ በመባል በሚታወቀው ቡድን ውስጥ ሊጠቃለሉ ይችላሉ።

በዚህ ክፍል ላስተላልፍ የምፈልገው መልዕክት ከላይ ከጠቀስኳቸው ምክንያቶች ውጭ ዳግም ጋብቻን በማበረታታት ከመጽሐፍ ቅዱስ አሳብ ጋር ለመቃረን አይደለም። ከመጀመሪያ ትዳራቸው የተወለዱ ሲባል አግብቶ በመፍታትና ዳግም በማግባት በማመን፣ ይህን በማበረታታትና የፍችንና ዳግም ጋብቻ አቋምን በማራመድ እንዳልሆነ እንድትገነዘቡኝ እወዳለሁ። ፍችና ዳግም ጋብቻ እምነቴም፣ ትምህርቴና የማማከር አገልግሎቴ አቋምም አይደለም!! ነገር ግን ይህን ርዕሰ ጉዳይ ማካተት ያስፈለገው ችግሩ በአንዳንድ ክርስቲያን ባለትዳሮች መካከል የሚገኝ እንደመሆኑና ሌሎችም ችግሩ ሊያጋጥማቸው የሚችል እንደመሆኑ ችግሩ ያጋጠማቸው ባለትዳሮች እንደገና ለሌላ ችግር እንዳይጋለጡ ለመርዳት በማሰብ ነው፡፡ ዋናው ዓላማውም ባለትዳሮች ከዚህ ችግር ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የግጭት መንስኤዎች ለይተው በመረዳት እርስ በርስ





በጋራ ገንቢ በሆነ መንገድ ግጭቶቻቸውን እንዲፈቱና ጤናማና ደስተኛ የትዳር ግንኙነትና ቤተሰብ እንዲኖራቸው ለመርዳት ነው።

## II. የእንጀራ ልጅን በማሳደግ ሂደት ሊፈጠሩ የሚችሉ የግጭት መንስኤዎች

በአጠቃላይ የእንጀራ ልጅን በማሳደግ ሂደት ውስጥ ባለትዳሮች በመካከላቸው ለሚፈጠር አለመግባባትና ግጭት ሊዳርጓቸው የሚችሉትን ምክንያቶች አስተዋይነት በሞላበት መንገድ መለየት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህን በማድረጉ ሂደት ይበልጥ ጥንቃቄ እንዲያደርጉና ችግሮች ተፈጥረው ከሆነም በጋራ መፍትሔ እንዲያፈላልጉ በችግሩ ውስጥ ያሉ ጥንዶችን ለመርዳት ይህ ርዕሰ ጉዳይ ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው፡፡ በቅርብ የተጋቡ ባለትዳሮች በመካከላቸው ሊፈጠሩ የሚችሉ ችግሮችን ምክንያቶች በመገንዘብ ቅድመ ጥንቃቄ እንዲያደርጉና ችግሩ ባጋጠማቸው ጊዜም በአግባቡ መፍታት እንዲችሉ ለመርዳት የእንጀራ ልጅ በማሳደግ ሂደት የሚያጋጥሙ የግጭት ምክንያቶችን ከዚህ በታች ለመዘርዘርና ለመጠቆም እፈልጋለሁ፡፡

### 1. አድሎዎ የሚታይበት እንክብካቤ

የመልካም ወላጅ አንዱ ባሕርይ ያለአድሎ ልጆችን መንከባከብና ማሳደግ መቻል ነው። ወላጆች ለልጆች የወላጅነት ፍቅር ማሳየት ይገባቸዋል፡፡ ልጆቻቸውን መንከባከብና መሠረታዊ ፍላጎታቸውን ማሟላትም የወላጅነት ኃላፊነት ነው። እንዲህ ዓይነቱን የወላጅ ኃላፊነት በተወሰነ መጠን ለእንጀራ ልጅ መቀነስ ወይም ፈጽሞ አለማድረግ በሚታይበት ወቅት በባለትዳሮች መካከል እንዲሁም በእንጀራ ልጅና በእንጀራ አባት ወይም በእንጀራ እናት መካከል ቀጣይነት ያለው አለመግባባትና ግጭት ሊፈጠር ይችላል። ወላጅ የሆነው አካል ከትዳር አጋሩ ተደብቆና ተጠያቂነት በጎደለው መንገድ የልጁን ፍላጎት ለማሟላት ጥረት ማድረግ፣ የእንጀራ ልጆች የሚፈልጉትን ነገር በተከለከሉ ወቅት ከልጃቸው ጋር አብረው ተደርበው ማኩረፍ ወይም ቅሬታ ማሰማት በልጃቸውና በእንጀራ አባት ወይም በእንጀራ እናት መካከል ያለው ግንኙነት እንዲሻክር ማባባስ ነው። ሁልጊዜ አድሎና መገለል ባለበት ቤተሰባዊና ማሕበራዊ ግንኙነት ውስጥ አለመግባባት፣ ግጭት ብሎም መለያየት መፈጠሩ አይቀሬ ነው።

ከአድልዎ ጋር የተያያዘ ችግር የሚፈጠረው የእንጀራ ልጅ ከእንጀራ እናት ወይም አባት ጋር በሚያደርገው ግንኙነት ብቻ ሳይሆን እንጀራ ልጅ ከወላጅ እናቱ ወይም አባቱ ጋር በሚያሳየው አድሏዊ የሆነ ግንኙነት ምክንያትም ጭምር ነው። የእንጀራ ልጅ በተለያየ መንገድ የሚያሳያቸው ወይም የሚገልጻቸው የተለያዩ የአድሎና የመገለል ስሜቶችና ክስተቶችም በጥንዶቹ መካከል ለአለመግባባትና ለግጭት ብሎም ለፍች ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ። የተለያዩ የቃላትና የድርጊት እሰጥ-አገባዎችም ሊታዩ ይችላሉ። እነዚህ በሁለቱ አካላት መካከል በሚፈጠሩ የአድሎና የመገለል ሰበቦች

ትዳርና ቤተሰብ ላልተፈለገ አለመግባባት፣ ግጭትና መለያየት አልፎ እንዳይሰጥ ከወዲሁ መጠንቀቅ አስፈላጊ ነው።

## 2. እንደ ጠበቁት ሁኖ አለመገኘት

አንድ አዲስ ለውጥ ለማድረግ ስንወስንና ስናስብ የምንጠብቀው ወይም ይሆናል! ይሳካል፣ ይገኛል... ብለን ተስፋ የምናደርገው አንድ ነገር መኖሩ አይቀሬ ነው። ብዙ ነገር ጠብቀን ከምንገባባቸውና ከምንወስንባቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ ትዳር ነው። ከትዳር እናገኛቸዋለን ብለን የምንጠብቃቸው ብዙ መልካም ነገሮች አሉ፡፡ ነገር ግን የምንጠብቃቸው መልካም ነገሮች ተሟልተው ለማየት የምንችለው የሚጠበቅብንን ስናደርግና ስንወጣ ብቻ ነው።

**ከትዳር የምንጠብቀውን ማየትና ማግኘት የምንችለው የሚጠበቅብንን ስናደርግና ስንወጣ ብቻ ነው!!**

በተለይ ልጆች ይዘው ወደ አዲስ ትዳር የሚገቡ ባለትዳሮች የሚፈልጉትን መልካም ነገር ማሟላት እንዳይችሉ የሚያደርጓቸው ምክንያቶች ከአንድ ወገን ብቻ ሳይሆን ከሶስት ወገን ሊፈጠሩባቸው ይችላሉ፡፡ ይህንን መረዳት ከሌላ ሰው ብቻ መልካምነትን ለማግኘት እየጠበቁ የሚጠበቅባቸውን ሳይወጡና ሳያሟሉ እንዳይቀሩ እንዲያስቡበት ይረዳቸዋል። የመጀመሪያው ጥበቃ የልጁ ወላጅ የሆነው አካል ከእንጀራ እናት ወይም ከእንጀራ አባት ለማግኘት ተስፋ የሚያደርገው ነገር ነው። የልጁ ወላጅ እንጀራ እናት ወይም አባት ከእንጀራ ልጃቸው ጋር ሊኖራቸው ስለሚገባ ግንኙነት፣ ወላጅነትና የተለያዩ አስፈላጊ ነገሮች መሟላት ከፍተኛ እምነት አላቸው፡፡ ከልጃቸው እንጀራ አባት ወይም እንጀራ እናት ጋር ትዳር ሲመሠርቱ የጠበቁትን መልካም ነገር እንደሚያገኙ እርግጠኛ ናቸው፡፡ ነገር ግን እንዲሟላላቸው የሚፈልጉትና ተስፋ አድርገው የጠበቁት ነገር እንደ ጠበቁት ላይሟላ ይችላል፡፡ የጠበቁት ተስፋ አለመሟላቱም ሊያስቆጣቸውና ባሕርያቸው እንዲቀያየርና ወደ ግጭት እንዲያመሩ የሚያደርጉ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ሊያደርግ ይችላል። ምንም ሳናደርግና የግላችንን ኃላፊነት ሳንወጣ እንዲሁ ለእኛ የሚጠቅም መልካም ነግር ለማግኘት በተዘጋጀ ከፍተኛ ጥበቃ ወደ ትዳር መግባት ተገቢ አይደለም፡፡

ከዚህ በተቃራኒ ደግሞ በጨለምተኛነት ዝቅተኛ ግምት ይዘን ወደ ትዳር መግባትም ሌላው የተሳሳተ ጽንፍ ነው፡፡ ይህ ዓይነት ስሜትና ግምት ይዞ ወደ ትዳር መግባት ከወዲሁ ተስፋ ቆርጦ ነገሮች እንደማይለወጡ አድርጎ በመቁጠር ለሚፈራው ችግር ራስን አሳልፎ ለመስጠት አስቀድሞ መዘጋጀት ነው። እንዲህ ዓይነቱን ከፍተኛና ዝቅተኛ የሆነ ጥበቃ ይዞ ወደትዳር መግባት የአለመግባባት፣ የግጭትና የመለያየት አብይ ምክንያት ይሆናል። የልጁ ወላጅ የሆኑ እናት ወይም አባት ስለትዳራቸውና





ስለልጆቻቸው የሚጠብቁት ተስፋ እንደ ተጠበቀ ሳይሆን ሲቀር ***"ባትወልደው" / "ባትወልጂው"*** ነው እንጅ ይህንና ያን ታደርግለት ነበር ወይም ***"ልጅህ" / "ልጅሽ"*** ቢሆን ኖሮ ይህንና ያን አታደርግበትም ነበር ... የሚሉ ቃላቶችን መናገር ይጀምራሉ፡፡ ይህ ዓይነቱ ስሜታዊነትና ትርፍ ንግግር ደግሞ ግጭት እንዲኖርና የእንጀራ አባትን ወይም የእንጀራ እናትንና የእንጀራ ልጅን ስሜት ይጎዳል። ስሜት በተጎዳ መጠን ደግሞ በቤተሰቡ መካከል ያለው የፍቅር ግንኙነት እንዲሻክርና የስሜት መራራቅ እንዲፈጠር ያደርጋል።

ሌላው በእንጀራ ልጅ በኩል የሚጠበቁ ተስፋዎች አለመፈጸም ወይም ምንም ተስፋ የለኝም የሚል የጨለምተኝነት አስተሳሰብ መፈጠር የሚያመጣው አሉታዊ ተጽዕኖ አለ። ልጅ ከእንጀራ አባት ወይም እናት የሚጠብቀው ከፍተኛ የሆነ ግምት እንዳሰበው ሳይሆን ሲቀር ቅሬታን በተለያየ መንገድ መግለጥና ማንጸባረቅ ይጀምራል፡፡ በቤተሰብ መካከልም ግጭት መፈጠሩ አይቀሬ ይሆናል። ከማሕበረሰቡ ባህላዊና ልማዳዊ አስተሳሰብ በወረሰው ቅድመ ግንዛቤ ልጁ ስለእንጀራ እናትና አባት ባለው የተሳሳተ ግምት ምክንያት የሚደረግለትን መልካም ነገር ሁለ ዝቅ የማድረግና የሚወሰድበትን የልጅነት የስነ ስርዓት እርምጃ (ቅጣት) አጋንኖ የማየት ዝንባሌ ይኖረዋል፡፡ ይህም ዝንባሌው ተስፋ የመቁረጥ ሁኔታ ስለሚፈጥርበት በሚደረግለት ነገር ከመደሰት ይልቅ ማጉረምረም፣ ከተደረገለት ይልቅ ያልተደረገትን መቁጠር፣ ከሞላለት ይልቅ የጎደለውን ማሰብ፣ በሰላም ካሳለፋቸው ቀናት ይልቅ የተጋጨበትን ሁኔታ አጉልቶ ማየትና ማሳየት የዘወትር የሕይወት ጉዞው አካል ይሆናል፡፡ ለወላጁና ለእንጀራ እናት ወይም አባት የትዳር ግንኙነትም ዋና የአለመግባባትና የግጭት ሰበብ ብሎም ለቤተሰብ መበጥበጥና መበተን ምክንያት ሊሆን ይችላል።

## 3. ሚዛናዊነትን ያልጠበቀ ቁጥጥር

ወላጅ እንደመሆናችን ልጆች በመልካም ስነ-ምግባር ታንጸው እንዲያድጉ ለመርዳት ተገቢ የሆነ ሚዛኑን የጠበቀ ቁጥጥር ማድረግ አስፈላጊ ነው። ምንጊዜም ቢሆን ሚዛኑን ያልጠበቀ ነገር ሁሉ ችግር መፍጠሩ የማይቀር ነው። በእንጀራ ልጅና በእንጀራ አባት ወይም እናት መካከል ሚዛኑን ያልጠበቀ ቁጥጥር እንዲኖር ሊያደርጉ ከሚችሉ ምክንያቶች አንደኛው የመልካም ወላጅ ባሕርይ ባለማሳየት ምክንያት ከፍተኛ የሆነ ነፃነት የሚያሳጣና ሰላምን የሚነሳ ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግ ሲሆን ሌላው ደግሞ አያገባኝም በሚል መንፈስ ግዴለሽነት የሚንጸባረቅበት ቁጥጥር ማድረግ ወይም ቁጥጥሩ ሌላ ትርጉም እንዳይሰጠው በሚል ፍርሃት ቁጥጥርን መቀነስ አለዚያም ፈጽሞ መተው ናቸው። ሁለቱ የቁጥጥር ዓይነቶች ጤናማ ግንኙነት በሌለበት ቤተሰባዊ አኗኗር ውስጥ የተለመዱ የሕይወት ገጽታዎች ናቸው። ምንጊዜም ፍርሃትና ስጋት ያለበት ግንኙነት ጊዜ ጠብቆ አለመግባባት፣ ግጭትና መለያየት ሊፈጥር እንድሚችል መንቃትና ፈጥኖ ማስተካከልን መምረጥ አስተዋይነት ነው።

## 4. ተመጣጣኝ ያልሆነ ተግሳጽና ቅጣት

ልጆች ሲያጠፉ አግባብ በሆነ መንገድ እንደ ጥፋታቸው መጠን ልንመክር፣ ልንገስጽና ልንቀጣ ይገባል። በዚህ ወቅት ሊታሰብበትና ልንለየው የሚገባን መቅጣትንና መጉዳትን ነው። መቅጣትና መጉዳት ሁለት የተለያዩ ነገሮች ናቸው። የእንጀራ እናትና አባት ለእንጀራ ልጅ መልካም እናትና አባት ባለመሆንና እውነተኛ ፍቅርና ርህራሄ ሳያሳዩ ከጥፋቱ ጋር ተመጣጣኝ ባልሆነ መንገድ መገሰጽና መቅጣት ሲጀምሩ በቤተሰብ ውስጥ ቀውስ መፈጠሩ አይቀሬ ነው። በእውነተኛ ፍቅርና ርህራሄ እጦት ምክንያት ምን አገባኝ፣ የፈለገውን ይሁን ወይም ያድርግ የሚሉና የእንጀራ ልጆች ሲያጠፉ መቅጣት በሌላ ሊታሰብና ሊያገጨን ይችላል የሚል ፍርሃትና ስጋት መኖር ሌላኛው ችግሩን የሚያባብስ ክፍተት ነው። ይበልጥ ችግሮችን የሚያባብሳቸው ደግሞ "ልጄን ጫፉን እንዳትነካው(ኪው)!"፣ "በልጄ የመጣ ሁሉ ነገር ሊቀር ይችላል!" "ከእርሱ (ከእርሷ) ላይ ትበረታለህ (ቻለሽ)! " ... የሚሉ የማይገቡ ቃላቶችን መጠቀም ነው:: በእንደዚህ ዓይነቱ አስተሳሰብና ምላሽ ምክንያት ከትዳር ይልቅ ግለኝነትን የሚያጎሉ ሁኔታዎች ይፈጠራሉ። እነዚህ ቀላል የሚመስሉ ነገር ግን ለትዳርና ለቤተሰብ አንድነት እንቅፋት የሚሆኑ ግንኙነቶችን ፈጥኖ ማስወገድና ማሻሻል በጣም አስፈላጊ ነው።

## 5. የእንግድነት ስሜት መፈጠር

የቤተሰብ አባል የሆነ ሰው ለቤተሰቡ እንግዳ ሲሆንና የእንግድነት ስሜት ሲፈጠርበት ካየን "ይህ ሰው ከቤተሰቡ ጋር ያለው ዝምድናና ግንኙነት ምንድን ነው?" የሚል ጥያቄ መጠየቃችን አይቀሬ ነው:: ሁኔታው በመካከላቸው የተፈጠረ የግንኙነት ችግር እንዳለ ወይም ሊኖር እንደሚችል እንድንገምት ያስገድደናል። እዚህ ላይ የእንጀራ ልጅ ከእንጀራ እናትና አባት ጋር ባለው ግንኙነት የእንግድነት ስሜት ሊፈጠርበት የሚችልበትን ምክንያት ማጤኑ መልካም ነው። የእንግድነት ስሜት እንዲፈጠር ሊያደርጉ ከሚችሉ ምክንያቶች የመጀመሪያው እርስ በርስ እውነተኛ በሆነ ፍቅር መዋደድና መቀራረብ አለመቻል ነው።

ሌላው የእንግድነት ስሜት እንዲፈጠር ምክንያት ሊሆን የሚችለው የእንጀራ ልጅ ከሌላ ቦታ ማለትም ከእናታቸው ወይም ከአባታቸው ብቻ ወይም ከአያታቸውና ከዘመድ ጋር ማደጋቸው ሊሆን ይችላል። ሌላ ቦታ አድገውና ኑረው መምጣትና ወደ አዲስ ቤተሰብ መቀላቀል ሌላው የእንግድነት ስሜት እንዲሰማቸው የሚያደርግ ምክንያት ነው። ይህ የእንግድነት ስሜት አብሮ አለመኖርና አለማደግ የሚፈጥረው ስለሆነ ይህን ስሜት ለማጥፋት ጠንካራና ቅርብ የሆነ ግንኙነት መፍጠር በጣም አስፈላጊ ነው:: ጠንካራና ቅርብ ግንኙነት መፍጠር ደግሞ ፈቃደኝነትን፣ ጥረትንና ጊዜን ይፈልጋል።

ሌላውና የመጨረሻው የእንግድነት ስሜት እንዲሰማቸውና እንዲፈጠርባቸው የሚያደርግ ምክንያት ሌላኛው ወላጅ እናታቸው ወይም አባታቸው በቅርብ አካባቢ





መኖራቸውና በየጊዜው በተለያዩ ቤተሰባዊ በሆኑ ጉዳዮች ቶሎ ቶሎ የሚገናኙ መሆኑ ነው። የእንግድነት ስሜት በተለያዩ ምክንያቶች የሚፈጠር መሆኑን መረዳት ችግሩን ለማስወገድ እቅጣጫ ይሰጣል። ይህን የእንግድነት ስሜት አስወግዶ ጤናማና ደስተኛ የሆነ ትዳርና ቤተሰባዊነት እንዲኖር መልካም ግንኙነት መፍጠር ተገቢ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የእንግድነት ስሜትን መቀነስና ማጠፋት መቻል ግጭትና ውጥረት የሌለበት በመልካም ግንኙነት የተሳሰረ ቤተሰብ ለመመሥረት ከፍተኛ አስተዋጽዖ ይኖረዋል።

## III. የእንጀራ ልጅን በማሳደግ ለሚፈጠሩ የግጭት ምክንያቶች መፍትሔዎች

### 1. ማሳወቅ:- ስለእንጀራ አባት ወይም የእንጀራ እናትና የእንጀራ ልጅ በግልጥ ማሳወቅ

እንደ ልጆች ዕድሜ፣ ጾታና ብስለት በሚገባ ግልጥ ሊሆኑላቸው የሚገቡ ጉዳዮችን ከማግባት በፊትና በኋላ እንደ ሁኔታዎች ምቹነት ወላጅ የሆነው አካል ሊያሳውቅ ይገባል። እንደ ዕድሜያቸውና ብስለታቸው ሁኔታ ወላጅ የሆነ አካል ወደ ትዳር ከመግባቱ በፊት በትዳር ሕይወት ሲኖሩ ልጃቸው ከትዳር አጋራቸው ጋር ሊኖረው ስለሚገባ ግንኙነት፣ ገደብ፣ ሚና፣ ግዴታ በየደረጃው ጊዜ እየሰጡ ማውራት፣ መመካከር፣ አስቀድሞ ማስጠንቀቅና ከወዲሁ ከልጁ ጋር በግልጥ በመወያየት መንገድ መጥረግና ሁኔታዎችን ማመቻቸት አስፈላጊ ነው። ወደ ትዳር ከመግባት በፊት ብቻ ሳይሆን በትዳር ዓለም ችግሩ በሚፈጠርበት ወቅት በግልጥ ቁጭ ብሎ የችግሩ መንስኤ ምንድን እንደሆነና ወደ ፊት እንዳይደገም በግልጥነት በመነጋገር መተማመን ይገባል።

እንዲህ ዓይነቱን ጉዳይ አስቀድሞ በመገመት ለግል ሕይወት፣ ለሚጀመርና ለተመሠረተ ትዳር እንዲሁም ለቤተሰባችን ለመጠንቀቅ መነጋገርና ቀድሞ ችግሮችን መቀነስ ከባህላችን አንጻር የተለመደ ባይሆንም ችግሮች ግን እፍጥጠው ለውጥ እንድናመጣ እየሞገቱን ይገኛሉ። ዘመኑ የመረጃ ዘመን ነውና ትክክለኛ መረጃ በትክክለኛ ጊዜና መንገድ ለተገቢው ሰው ሊተላለፍ ይገባዋል። መረጃዎችን ለማሳወቅ ልንጠይቃቸው የሚገቡን ጥያቄዎች አሉ:: ለምሳሌ:- ለምን ማሳወቅ አስፈለገ? ጠቀሜታው ምንድን ነው? መቼ ነው ማሳወቅ ያለብኝ? እንዴትና በምን መንገድ ማሳወቅ አለብኝ? ... የሚሉትን ጥያቄዎች አስቀድሞ በመጠየቅ መልስ ለመስጠት መሞከር አስፈላጊ ነው። የእንዲህ ዓይነቱ ተግባቦት መፈጠር ለልጆች መንፈሳዊ፣ ስነ ልቦናዊና አካላዊ ጤንነት መጠበቅ፣ የማንነት ቀውስን ለማስወገድ፣ ለቤተሰባዊና ለማሕበራዊ ግንኙነታቸው መጎልበት እንዲሁም ለአካዳሚክ ውጤታማነት አስተዋጾው ከፍተኛ ነው።

በፍጹም ግልጥነት መወያየትና መግባባት የሚያስፈልገው ወላጅ ለልጅ በማሰቡ ብቻ ሳይሆን የትዳር አጋር ስለእንጀራ ልጅ ባሕርይ፣ አዘውትረው ስለሚያደርጉት ነገር፣

ስለሚያስፈልገውና ስለሚፈልጋቸው ነገሮች እና ሁለቱ ሊኖራቸው ስለሚገባ ግንኙነት በሚገባ እንዲያውቅ ለማገዝ ነው፡፡ እንዴት በጋራ ልጆችን ሊያሳድጉ እንደሚችሉ ሁለቱ ወላጆች አስቀድሞ በመነጋገርም ጭምር ለሕብረታቸው ጥሩ መሠረት ከጣሉ አለመግባባትና ግጭት በተፈጠረ ወቅት ችግሩ አድጎ ሌላ አሉታዊ የሆነ ተጽዕኖ ከማምጣቱ በፊት በመልካም ሁኔታ ግጭቱን መፍታት አይከብዳቸውም፡፡ በሂደቱም ተምረውበት ጤነኛና ደስተኛ የሆነ በችግር የማይፈታ ትዳርና ቤተሰብ ይኖራቸዋል፡፡

## 2. ማነሳሳት፡- ለመቀበልና ተንከባክቦ ለማሳደግ ራስን ማነሳሳት መጀመር

በተለያየ ምክንያት ልጅ ኑሯቸው ትዳር ለመሠረቱና ለሚመሠርቱ ባል ወይም ሚስት አስቀድመው ሊያዩት የሚገባ አንዱ ጉዳይ የሚያገቡት ሰው ለልጃቸው ያለውን መረዳትና ልጃቸውን እንደ ልጅ ተቀብሎ እየተንከባከበ ሊያሳድግ ፈቃደኛ መሆኑን በተመለከተ ያለውን አቋም ነው። ትዳሩ ከመመሥረቱ በፊት ወላጅ ያልሆነው አካል የእንጀራ ልጅን እንደ ልጅ በፍቅር ተቀብሎ ለእድገት የሚያስፈልገውን መሠረታዊ ፍላጎት በማቅረብ፣ በማሟላትና በመንከባከብ ለማሳደግ ፈቃደኛ መሆንና አዎንታዊ መነሳሳት ማሳየት ይኖርበታል።

ሌሎችን ነገሮች ከማድረግ በፊት መጀመሪያ መቀባበል አስፈላጊ ነው። የእንጀራ እናት ወይም የእንጀራ አባት የእንጀራ ልጅን እንደ ወላጅ ሁኖ ለመንከባከብ የሚያሳየው ፈቃደኝነት ብቻ ሳይሆን የእንጀራ ልጅም እንደ ልጅ ሁኖ እንክብካቤ ለማግኘት የመፍቀዱና ራሱን የማዘጋጀቱ ጉዳይ ሌላው ሥራ የሚጠይቅ ጉዳይ ነው። በእንደዚህ ዓይነት ጊዜ ወላጅ የሆነው ሰው በመካከል የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ሊሆን ይገባል። በእንጀራ ልጅና በእንጀራ እናትና አባት መካከል የመገናኘት ምክንያት ወላጅ ነውና መልካም ወላጅና የትዳር አጋር ለመሆን ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል።

## 3. ማጠናከር፡- መልካም ግንኙነትን ማጠናከር

በእንጀራ እናት ወይም በእንጀራ አባትና በእንጀራ ልጅ መካከል ከሚፈጠረው ችግር አንዱ በተለያዩ ምክንያቶች የእንግድነት ስሜት የመሰማት ሁኔታ ነው። ይህን ስሜት በማስወገድ ከእንጀራ ልጅ ጋር መልካም የሆነ ግንኙነት ለመፍጠርና ግንኙነትን ለማጠናከር ጊዜ መስጠት ወሳኝ ነው። ስለዚህ ወሳኝ የሆነውን ጊዜ እየበጀቱ ባልተከፋፈለና ባልባከነ ሁኔታ በዓላማ ከትዳር አጋር፣ ከእንጀራ ልጅና ከጠቅላላ የቤተሰብ አባላት ጋር የተመረጠ ጊዜ ማሳለፍ አስፈላጊ ነው። *"ኢየሱስ ግን ሕፃናትን ወደ እርሱ ጠርቶ። ሕፃናትወደ እኔ ይመጡ ዘንድ ተውአቸው አትከልክሉአቸውም፤ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደ እነዚህ ላሉት ናትና።"* /ሉቃ 18፡ 16/ እንደሚለው የእግዚአብሔር ቃል የእንጀራ ልጆች ወደ እንጀራ እናት ወይም አባት እንዲቀርቡና አብረው ጊዜ እንዲያሳልፉ ሊያደርግ የሚችል ፍላጎት ማሳየት፣ ነጻነት የሚሰጥ አቀራረብ መቅረብ፣ በሚወዱት ስፍራ መሄድና አቅም በፈቀደ መጠን የሚፈልጉትን የሚያገኙበት እድል መስጠት ግንኙነትን የበለጠ ለማጠናከር ጠቃሚ ነው፡፡





ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የነበረውን ግንኙነት ለማጠናከርና ለሚፈልገው ዓላማ እነርሱን ለመላክ ሲፈልግ መጀመሪያ የወሰደው እርምጃ መጥራትና ከእርሱ ጋር እንዲኖሩ ዕድል መስጠት ነው። ብዙ የተለያዩ አጋጣሚዎችን በመጠቀም ከእርሱ ጋር አብረውት እንዲሆኑ ዕድል መስጠቱ ሌሎችን ይበልጥ ለማወቅና እንደ አመላቸው ለመያዝ መደረግ ያለበትን ነገር የሚያሳይ ምሳሌ ነው። *"ወደ ተራራም ወጣ፥ ራሱም የወደዳቸውን ወደ እርሱ ጠራ፥ ወደ እርሱም ሄዱ። ከእርሱም ጋር እንዲኖሩና ለመስበክ እንዲልካቸው፥ ድውዮችንም ሊፈውሱ አጋንንትንም ሊያወጡ ሥልጣን ይሆንላቸው ዘንድ አሥራ ሁለት አደረገ"* /ማር 3፡ 13-15/

## 4. ማበረታታት፡- አድሎ የሌለበት የቤተሰብ አስተዳደር መመሪያ በመጠቀም ቤተሰብን ማበረታታት

አድሎንና መገለልን ለማስወገድ ሁሉንም ልጆችና የቤተሰብን አባላት የሚያስተዳድር ግልጥ የሆነ ግዴታንና ኃላፊነትን የሚያሳይ መምሪያ ማውጣት፣ መነጋገር፣ ማሳወቅና ሁሉንም ተጠያቂ የሚያደርግ አስተዳደር መስጠት ጠቃሚ ነው። በእንጀራ ልጅና በሌሎች ልጆች መካከል ሚዛናዊ ያልሆነ ቁጥጥር እንዳይፈጠር፣ የእንጀራ ልጅ ነፃነት እንዳያጣና ተመጣጣኝ ባልሆነ ቅጣት እንዳይመረር በቃል ይሁን በጽሑፍ ለሁሉም የሚሠራ የቤተሰብ መመሪያ ጥቅም ላይ ማዋል ተገቢ ነው። መመሪያው የእንጀራ ልጅን ለማስመረርር ሳይሆን ቤተሰቡን ለማስተማር፣ ለማራቅ ሳይሆን ለማቅረብና ለመጉዳት ሳይሆን ለመርዳት ሊወጣና ሊተገበር ይገባዋል።

ደንቦችና መመሪያዎች ከምህረት ጋር አብረው ካልተጣመሩ ሕግ ብቻ የትም አያደርስም እንዲያውም ሕግ ተላላፊው ይበዛና ፈጽሞ የቤተሰብ ደንብ እንዳይኖር ሊያደርግ ይችላል። በአገራችን በኢትዮጵያ ቆሻሻ የሚበዛው **"ከዚህ አካባቢ መጸዳዳት ወይም ቆሻሻ መጣል በሕግ ያስቀጣል"** ተብሎ ማስታወቂያ ከተለጠፈበት ቦታ ላይ ነው ይባላል። እውነትን በፍቅር፣ ሕግን በጸጋና መተላለፍን በምህረት እያለፍን ልንይዝና ቤተሰብን ልናስተዳድር እንችላለን፡፡ ነገር ግን የቤተሰብ አስተዳደር አጥፊውን ሁሉ ጥፋተኛ አድርጎ የሚጠይቅ ሁኖ መገኘትና ለመገሰጽ፣ ለመቅጣትና ለማስተዳደር አድሎን ያስወገደ እንዲሆን ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

አጥፍተው በሚቀጡበት ወቅት ወላጅ የሆነው ግለሰብ የጋራ ልጅ ባልሆነው በእንጀራ ልጅ ፊት ምን አደረገ? ለምን ይቀጣል? ከእርሱ/ሷ/ ላይ ትበረታለህ/ሽ/ በማለት ይበልጥ ሊያራርቅ፣ በመካከል ያለውን ቅሬታ ሊባብስና አንዱን "ተቀርቋሪ ነው" ሌላውን ደግሞ "የማያስብ ነው" የሚሉ የተሳሳቱ መልዕክቶችን የሚያስተላልፍ ጣልቃ ገብነትን ማስወገድ አለበት፡፡ ወላጅ ለትዳሩና ለልጁ ደህንነት ሲል በተቻለ መጠን ጣልቃ መግባቱን ትቶ ከትዳር ጓደኛው ጋር መነጋገር የሚችሉበትን ሌላ ምቹ ጊዜ ማመቻቸት ይኖርበታል። በንግግር ወይም በድርጊት የተፈጠረ ስህተት ቢኖርም እንኳን እንደ ባለትዳር በግል መነጋገርና መተራረም ይሻላል እንጂ ጣልቃ በመግባት እንዲራራቁ አለመፍቀድ መልካም ነው። ይህን ሁሉ የምናደርገው ከችግሩ በላይ የትዳር

ግንኙነታችንና ቤተሰባችን ስለሚበልጥ ብቻ ነው። ሁልጊዜ ሶስተኛ ወገን የትዳር ግንኙነታችንን እንዳይነካ፣ እንዳያፈርስና የመለያየት ምክንያት እንዳይሆን መንገድ መዝጋት፣ አጥር መሥራትና ግንኙነትን ይበልጥ ማጠናከር ጤነኛና ደስተኛ ትዳር ብቻ ሳይሆን በመልካም ግንኙነት የታነጸ ቤተሰብም እንዲኖረን ይረዳናል።





## ለጥንዶች በግላቸውና በቡድን ለማጥናት የሚረዱቸው የውይይት ጥያቄዎች

## የምዕራፍ አስራ ዘጠኝ (19)

## የውይይት ጥያቄዎች

1. የእንጀራ ልጅ ምንነትና እንዴት በክርስቲያን ባለትዳሮች መካከል የእንጀራ ልጅ ሊኖር የሚችልበት የተለያዩ ምክንያቶችን በመጥቀስ ተወያዩበት::
2. የእንጀራ ልጅ በማሳደግ ሂደት በባለትዳሮች መካከል ለግጭት መንስኤ ሊሆኑ የሚችሉትን በመጥቀስ ተወያዩ።
3. የእንጀራ ልጅ በማሳደግ ሂደት የእንጀራ አባት ወይም እናት ለደስተኛ ትዳርና ለመልካም ለቤተሰብነት ምን ሊያደርጉ ይገባል ትላላችሁ?
4. በእንጀራ ልጅና በእንጀራ አባት ወይም እናት መካከል የእንግድነት ስሜት እንዲፈጠር የሚያደርጉትን ምክንያቶች በመዘርዘርና የእንግድነትን ስሜት ለማስወገድ ምን ሊደረግ እንደሚገባ በስፋት ተወያዩበት።
5. እንዲህ ዓይነት ገጠመኝ ካላችሁ ያጋጠማችሁንና ያለፋችሁበትን ልምድ ለሌሎች ትምህርት እንዲሆን አካፍሉ።

# ምዕራፍ ሃያ (20)
# ልጆችን በአግባቡ በመቅጣት ማሳደግ

## 1. ልጆችን በአግባብ በመቅጣት የማሳደግ ምንነት

ልጆች በስነ ስርዓት ታንጸው እንዲያድጉ፣ ላጠፉትና ለማይገባ ባሕርያቸው መልካም መስሎ እየታያቸው እንዳይቀጥሉ ለጥፋታቸው ተመጣጣኝ የሆነ ቅጣት መቅጣት ተገቢ ነው:: ቅጣቱ ግን ክፉና መልካሙን፣ የሚገባና የማይገባውን ለይተው እንዲያውቁና ኃላፊነት በመውሰድ አጥፍቻለሁ፣ ተሳስቻለሁ በማለት መታረም እንዲችሉ የሚያግዝ ሊሆን ይገባል። ትክክለኛው ወላጅ ልጆችን የሚቀጣበት ሂደትና መርህ የእውነተኛ ፍቅር መግለጫ ነው። ቅጣት ወላጆች ልጆቻቸውን በትክክለኛ መነሻ አሳብ፣ በርህራኄ፣ ራስን በመግዛትና በመቆጣጠር፣ ኃላፊነትንና ግዴታን በማሳየት፣ ለእነርሱ የተሻለውን በማሰብና በማየት ሊከናወን የሚገባው ልጆችን የማሳደግ አንዱ መርህ ነው። እግዚአብሔር እንደ መልካም አባት ካለው እውነተኛ ፍቅር የተነሳ ልጆቹን ይቀጣል። መጽሐፍ ቅዱስ *"እንደ ልጆችም ከእናንተ ጋር፥ ልጄ ሆይ፥ የጌታን ቅጣት አታቅልል፥ በሚገሥጽህም ጊዜ አትድከም፤ ጌታ የሚወደውን ይቀጣዋልና፥ የሚቀበለውንም ልጅ ሁሉ ይገርፈዋል ብሎ የሚነጋገረውን ምክር ረስታችኋል። ለመቀጣት ታገሡ፤ እግዚአብሔር እንደ ልጆች ያደርግላችኋልና፤ አባቱ የማይቀጣው ልጅ ማን ነው? ነገር ግን ሁሉ የቅጣት ተካፋይ ሆኖአልና ያለ ቅጣት ብትኖሩ ዲቃላዎች እንጂ ልጆች አይደላችሁም። ከዚህም በላይ የቀጡን የሥጋችን አባቶች ነበሩን እናፍራቸውም ነበር፤ እንዴትስ ይልቅ ለመናፍስት አባት አብልጠን ልንገዛና በሕይወት ልንኖር በተገባን? እነርሱ መልካም ሆኖ እንደ ታያቸው ለጥቂት ቀን ይቀጡን ነበርና፥ እርሱ ግን ከቅድስናው እንድንካፈል ለጥቅማችን ይቀጣናል። ቅጣት ሁሉ ለጊዜው የሚያሳዝን እንጂ ደስ የሚያሰኝ አይመስልም፥ ዳሩ ግን በኋላ ለለመዱት የሰላምን ፍሬ እርሱም ጽድቅን ያፈራላቸዋል።"* /**ዕብ 12: 9-11፤ ራዕ 3፡ 19**/ በሚለው መልዕክቱ የማይቀጣ ልጅ ዲቃላ እንጂ እውነተኛ ልጅ አለመሆኑን ይናገራል።

እግዚአብሔር ከቅድስናው እንድንካፈል ለጥቅማችን ይቀጣናል። የእግዚአብሔር ቅጣት የሰላምን ፍሬ እርሱም ጽድቅን በማፍራት በሕይወት እንድንኖርና እንድንመላለስ እንደሚጠቅመን ሁሉ እንዲሁ ልጆቻችንን ለጥቅማቸው በመቅጣት ማሳደግ ተገቢ ነው። ልጆችን የመቅጣት ሂደት በብዙ ወላጆች ዘንድ የአመለካከት፣ የአቋምና የምርጫ ልዩነት የሚፈጠርበትና ለግጭት መንስኤ በመሆን በትዳር ውስጥ ያለመግባባት ምክንያት ይሆናል:: ይህ ምዕራፍ ልጆችን በመቅጣት ሂደት ውስጥ ወላጆች የተለያየ አቋም እንዲይዙ የሚያደርጓቸውን የልዩነት ምክንያቶች ባግባቡ እንዲረዱና በነዚህ ልዩነቶች ምክንያት ከሚፈጠር ግጭት ቤተሰብን ለመጠበቅ የሚያስችል ዝግጅት እንዲያደርጉ ማገዝ ላይ ትኩረት ያደርጋል:: ይህንንም ለማሳካት በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ልጆችን ከመቅጣት ጋር የተያያዙ የግጭት መንስኤዎችንና መፍትሄዎቻቸውን ከዚህ በመቀጠል እንዳስሳለን::





## II. ልጆችን በመቅጣት ሂደት ሊፈጠሩ የሚችሉ የግጭት መንስኤዎች

### 1. በልጆች ላይ የቅጣት እርምጃ የመውሰድን ምንነት ጠንቅቆ አለማወቅ

ወላጆች ልጆችን በፍቅር መቅጣት ስናስብ ልጆችን ስለመቅጣት የሚያስተምሩ መጽሐፍ ቅዱሳዊና መሠረታዊ እውነቶች መረዳት ይጠበቅብናል። እግዚአብሔር አባታችን ልጆቹን የሚቀጣበት መርህ እኛም እንደ ወላጅ ልጆቻችን ለመቅጣት ስናስብ ልንለማመደው የሚገባን መርህ ነው። ልንከተላቸው ከሚገቡን መርሆዎች ጥቂቶቹን እንደሚከተለው እንዳስሳለን::

***የመጀመሪያው*** መርህ የቅጣት አስፈላጊነት ምንድን እንደሆነ ራስን በመጠየቅ ምላሽ የማግኘት አስፈላጊነት ነው። በ**ዕብራዊያን 12: 4-11** በግልጽ እንደተጻፈው ልጆችን መቅጣት አስፈላጊ የሆነው ልጆችን ከእውነት፣ ከትክክለኛ ጎዳና፣ ከመልካም ባሕርይና ከጽድቅ ሕይወት ወደ ኋላ ከሚያደርጉ ነገሮች ለመጠበቅና በመልካም ባሕርይ ጸንተው እንዲጓዙ ለማድረግ ነው።

***ሁለተኛው*** መርህ ልጆችን የመቅጣት መንገድ የሚመለከት ነው:: ይህ መርህ ልጆችን እንዴት ነው መቅጣት ያለብን? የሚለውን ጥያቄ ሊመልስልን የሚችል መርህ ነው። ልጆችን የምንቀጣበት የቅጣቱ መንገድ በቃልና በድርጊት የሚከናወን ነው። ልጆች ጥፋት ወደሚያመጣባቸው የውድቀት መንገድ ሲሄዱ በቃል በመምከር፣ በመገሰጽና በማስጠንቀቅ የመረጡትን መንገድ ከተከተሉ ውጤቱ ምን እንደሆነ በማሳየት የስነ ስርዓት እርምጃ መውሰድና ልጆችን ከጥፋት መጠበቅ አስፈላጊ ነው። ልጆችም ይህንን እግዚአብሔር ትውልድን ለመቅረጽ ያዘጋጀውን መንገድ አስተውለው ሳይመረሩ ከተጠቀሙበት ከጥፋት ወጥመድ ያመልጣሉ *"ልጄ ሆይ የእግዚአብሔርን ተግሣጽ አትናቅ በገሰጸህም ጊዜ አትመረር"* /**ምሳሌ 3: 11**/::

***ሶስተኛው*** መርህ ልጆችን የምንቀጣበትና ለመቅጣት የምንነሳሰበት መነሻ የውስጥ አሳባችን ምንድን እንደሆነ መቃኘት ላይ ትኩረት የሚያደርግ ነው። ልጆችን ለመቅጣት የሚያነሳሳን የውስጥ መነሻ አሳብ ፍቅር ሊሆን ይገባል። ወላጆች የእግዚአብሔርን የአባትነት ምሳሌነት መከተል አለባቸው:: እግዚአብሔር ልጆቹን የሚቀጣበትና የሚገስጽበት ዋና ምክንያት ፍቅር እንደሆነ *"ጌታ የሚወደውን ይቀጣልና"* /**ዕብ 12: 6**/ በሚለው ቃሉ ግልጥ አድርጓል::

***አራተኛው*** መርህ ወላጆች ልጆችን የሚቀጡበት ግብ ላይ የሚያተኩር ነው:: ወላጆች ልጆችን ከመቅጣታቸው በፊት ልጆችን ስለሚቀጡበት ግብ በማስተዋል ማሰብ አለባቸው:: ልጆችን በመቅጣት ልንደርስበት የምንፈልገው ግብ ምንድን ነው? የሚለውን ጥያቄ መመለስ ልጆችን ከመቅጣት በላይ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ መሆን አለበት:: መሠረታዊው ልጆችን የመቅጣት ግብም በቋሚነት ለእግዚአብሔር በመታዘዝ መኖር እንዲችሉ ለማድረግ መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው። *"እንዴትስ ይልቅ ለመናፍስት አባት አብልጠን ልንገዛና በሕይወት ልንኖር በተገባን?"* /**ዕብ 12: 9**/:: ወላጆች ልጆች መታዘዝን

እንዲለማመዱ በመቅጣት ሂደት ውስጥ በመካከላቸው ፍቅርና መተማመንን መፍጠር አለባቸው።

**የመጨረሻውና አምስተኛው** መርህ ቅጣት ለጊዜው ህመም ያስከትላል ነገር ግን ከጊዜ በኋላ በእድገታቸውና በወደፊት ሁለንተናዊ ሕይወታቸው ላይ የሚያመጣው በጎ ተጽዕኖ ግን የምድር ዘመናቸውን የሚያከልና ከዚያም የሚያልፍ ነው። የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይላልና፦ *"እነርሱ መልካም ሆኖ እንደ ታያቸው ለጥቂት ቀን ይቀጡን ነበርና፥ እርሱ ግን ከቅድስናው እንድንካፈል ለጥቅማችን ይቀጣናል። ቅጣት ሁሉ ለጊዜው የሚያሳዝን እንጂ ደስ የሚያሰኝ አይመስልም፥ ዳሩ ግን በኋላ ለለመዱት የሰላምን ፍሬ እርሱም ጽድቅን ያፈራላቸዋል።"* /ዕብ 12: 10-11/፡፡

የቅጣትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርህና አስፈላጊነቱን፣ የሚደረግበትን መንገድ፣ መነሻ አሳባችንን፣ ግቡንና ውጤቱን በመቃኘት ለመረዳት የሞከርነው እንዲሁ ወላጆች የተለያዩ ስሜቶች ድባብ በተፈራረቁባቸውና በተናደዱ ወቅት ልጆቻቸውን የቁጣቸው መወጫ እንዳይሆኑ ቅጣት በመርህ የሚከናወን መሆኑን ለማሳየትና ለማስጠንቀቅ ነው። ልጆችን ለጥቅማቸው በምንቀጣበት ወቅት ለጥቅማቸው ያሰብነው መልካም ነገር ከቅጣትነት አልፎ ሁለንተናዊ የሆነ ጉዳት የሚፈጥርባቸው እንዳይሆን ልዩ ጥንቃቄ ማደረግ ተገቢ ነው። ተገቢውን ጥንቃቄ እያደረጉ መጽሐፍ ቅዱስ *"በበትር ከመምታት የሚራራ ሰው ልጁን ይጠላል ልጁን የሚወድድ ግን ተግቶ ይገሥጸዋል።"* /**ምሳሌ** 13፡ 24/ *"ስንፍና በሕፃን ልብ ታስሮአል የተግሣጽ በትር ግን ከእርሱ ያርቃታል።* /**ምሳሌ** 23፡ 15/ እንደሚል ባግባቡ ልጆችን መቅጣት ልጆችን በእውነት የመውደድ መግለጫ እና የማይጠቅማቸውን ድካም ከእነርሱ የማራቂያ መንገድ ነው፡፡

የቅጣት እርምጃ በምንወስድበት ወቅት ወላጆች ለልጆች፡- **በመጀመሪያ፡** ግልጥ የሆነ ማስጠንቀቂያ መስጠትና የሚቀጡት ለምን እንደሆነና ቀጥሎ በሚያጠፉት ጥፋት እርምጃ የሚወሰድባቸው በምን ምክንያት እንደሆነ አስቀድመው እንዲያውቁና በሚቀጡበት ወቅት ጥፋታቸውን ተረድተው እንዲቀጡ ይረዳል።

**ሁለተኛ፡** ቅጣቱን ለምን እንደሚያደርጉት፣ ልጆች በመቀጣታቸው ምን እንደሚጠቀሙ ማሳየት ቅጣቱ ሊፈጥርባቸው የሚችለውን አሉታዊ ተጽዕኖ ይቀንሰዋል፡፡ ልጆች በሚቀጡበት ወቅት በእነርሱ ስሜት ላይ የሚፈጠርባቸውን ተፅዕኖ መጠየቅ ከዚያም ትክክለኛውን የቅጣት መልካም ተጽዕኖ ማሳየትና ማስረዳት ተገቢ ነው። ይህም ልጆች ራሳቸው ኃላፊነትን መሸከምና ኃላፊነትን መውሰድ እንዲለማመዱ ይረዳቸዋል። የምንቀጣበት አንዱ ምክንያት ራሳቸው በራሳቸው ኃላፊነት የሚሰማቸው ልጆች እንዲሆኑ ነው።

**ሶስተኛ፡** ልጆችን በምንቀጣበት ጊዜ በየቦታው ማሸማቀቅን ማስወገድ አስፈላጊ ነው። ልጆች በጓደኞቻቸው መካከል፣ ሰዎች ባሉበትና በዘመድ...ፊት በየጊዜውና በቁጣ፣ በስድብ፣ በሚያሳፍር ንግግር፣ ስነ ልቦናዊ በሆነ ጉዳት እንዲጎዱ የሚያደርግ ቅጣት መቀጣት የለባቸውም፡፡ ይህ ዓይነቱ ቅጣት የበታችነት ስሜት የሚሰማቸው፣



የግጭት መንስኤዎችና መፍትሔዎቻቸው በጋብቻ ውስጥ!

የሚጨነቁ፣ የሚሸማቀቁና በስነልቦና ተጽዕኖ የሚሰቃዩ ያደርጋቸዋል፡፡ ስለዚህ ልጆችን በመቅጣት ሂደት ልዩ ጥንቃቄ ማድረግ በጣም ጠቃሚ ነው።

**አራተኛ፡** ልጆች ባጠፉት፣ መልካም ባልሆነ ባሕርያቸው እንደ አዘንን፣ እንደ ተጎዳን፣ እንደ ተበሳጨን፣ ጥሩ ስሜት እንዳልተሰማን ሊረዱበት የሚችሉበትንና ስሜታችንን ሊጋሩ የሚችሉበትን ዕድል መፍጠር ተገቢ ነው። ይህ ማለት ተናደን እንቀጣቸው ማለት አይደለም። በንዴት ሁነን የምንቀጣበት ሂደት ጉዳት ሊያስከትልና እንደገና ሌላ ስህተትና ጸጸት እንዳይፈጠርብን ቆም ብለን ማሰብ ይገባናል።

**አምስተኛ፡** ልጆችን መቅጣት ጥፋታቸውን አምነው እንዲቀበሉና በእውነተኛ ጸጸት ንስሃ መግባት እንዲችሉ መርዳት ነው። ጥፋተኛ ነኝ፣ ተሳስቻለሁ፣ ሁለተኛ አልደግምም፣ እናንተን እንዲህ የሚያስቆጣና የሚጎዳ ከሆነ በማለት በጸጸት መመለስ እንዲችሉ ማገዝ አንዱ ልጆችን የመቅጣት ሂደት ውጤት ነው።

**ስድስተኛ፡** የቅጣት ሌላኛው ጥቅም ልጆችን በእውነተኛ ልብ እንደምንወዳቸው ፍቅራችንን የምናሳይበት ነው። ልጆች አጥፍተው ስናገኝ ለመቅጣት ያነሳሳን ፍቅር ሊሆን ይገባል፡፡ ከቅጣትም በኋላ በተግባር ፍቅራችንን መግለጽ ተገቢ ነው። እግዚአብሔር የሰጠንን ድንቅ የሆኑ ስጦታዎች ቆንጆ፣ ጎበዝና ጥሩ ልጅ ... ስለሆንክ ብሎ ማመስገን፣ ስለእነርሱ ወደ እግዚአብሔር በምስጋና በመቅረብ መጸለይና ልባችንን ማሳየት ተገቢ ነው፡፡[74]

## 2. የተለያዩ ወላጆች ልጆችን ለመቅጣት የተለያየ አቀራረብ ያላቸው መሆናቸው

የተለያዩ ዓይነት ወላጆች  እንዳሉ መረዳት ምን ዓይነት ወላጅ እንደሆንና ለውጥ የሚያስፈልገን በምን በኩል እንደሆነ እንድንለይና ራሳችንን እንድናሻሽል ይረዳናል። በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የተደረጉ ጥናቶች አራት የተለያዩ ዓይነት ወላጆች እንዳሉ ይገልጻሉ፦ **የመጀመሪያዎቹ** ወላጆች ልጆቻቸውን ይወዳሉ ነገር ግን ልጆቻቸውን ልቅ የሚሰዱ፣ የልጆችን ገደብ የማያሳዩ፣ የማይቆጣጠሩና ልጆች በራሳቸው ፈቃድና ፍላጎት ብቻ እንዲመላለሱ ዕድል የሚሰጡ ወላጆች ናቸው። እንዲህ ሁነው የሚያድጉ ልጆች በነገ ሕይወታቸው ላይ እኔ ያልኩት ካልሆነ ወይም የእኔ ፍላጎት ካልተፈጸመ የሚሉና ይህ ካልሆነ አብዮት የሚያስነሱ ናቸው፡፡ ስለራሳቸው ያላቸው ግንዛቤም ሚዛኑን ያልጠበቀ ነው፡፡ ከስተቱ አንዳንዶቹን ስለራሳቸው በጣም ከፍተኛ ግምት እንዲኖራቸው ሲያደርግ ሌሎቹን ደግሞ ስለራሳቸው ዝቅተኛ የሆነ ግምት እንዲይዙ ሊያደርጋቸው ይችላል።

[74] focus on the family:  Taken from *Effective Parenting in a Defective World* published by Tyndale House Publishers, Inc. Copyright © 2006 by Chip Ingram. visited 12/31/2014

**ሌሎች ሁለተኛዎቹ** ዓይነት ወላጆች ደግሞ ለልጆች ፍቅር የሌላቸው ደግሞም ልጆቻቸው እንዴት እያደጉ እንደሆነ ግድ የሌላቸው ናቸው። እናት ወይም አባት አንዱ አካል ግድ የሌለው በሚሆንበት ወቅት ልጆች ትኩረት ወደሚሰጣቸው ወላጅ ብቻ በማዘንበል ሌላውን አካል እንደ ወላጅ ላይቆጥሩት ይችላሉ። ምናልባትም እያደጉ ሲመጡ ይበልጥ ስነ ልቦናዊ ጉዳት ሊፈጠርባቸውና በቁጣ፣ በጸጸት፣ መልካም ትዝታ ሳይኖራቸው ብስጩ ሊሆኑ ይችላሉ። ለልጆቻቸው ፍቅር የሌላቸው ይልቁንም ግድሌሽ የሆኑ ወላጆች ምናልባት በትዳራቸው ደስተኛ ያልሆኑ፣ በተለያዩ ሱሶች ተጠቂ የሆኑ ወይም በሕይወታቸው ሌላ የራሳቸው ችግር ሊኖርባቸው ይችላል። ችግሮቻቸውን ቶሎ በመፍታት ከልጆቻቸው ጋር ያላቸውን ግንኙነት በፍቅር ማደስ ካልቻሉ ወላጅም ሆነ ልጆች የቤተሰብ ፍቅር ባለመስጠትና ባለመቀበል ምክንያት በሁለንተናዊ ማንነታቸው ላይ የሚፈጠር ቀውስ ተጠቂዎች ይሆናሉ።

**ሶስተኛዎቹ** ዓይነት ወላጆች ደግሞ በምንም ዓይነት መንገድ ለልጆቻቸው ያላቸውን ፍቅር የማይገልጹ፣ የማያሳዩ ይልቁንም ቁጥጥርና ቅጣት ላይ ብቻ የሚያተኩሩ ወላጆች ናቸው። አንድም ቀን ልጆቻቸውን እንደሚወዷቸው በቃልም ሆነ በተግባር ሳያሳዩ እንዲሁ በቤት ውስጥ በልጆች እንደተፈሩ ይኖራሉ። የልጆችና የወላጆች ግንኙነት አድርግና አታድርግ በሚል ሕግና መምሪያ ላይ ብቻ ያተኮረ ይሆናል። ይህም ሂደት ልጆች እያደጉ ሲመጡ የመጠየቅ፣ የመቃወም፣ የመከራከርና የማሸነፍ ጥረት የሚያደርጉ እንዲሆኑ ሊገፋፉቸው ይችላል። በእንደዚህ ዓይነት የሚያድጉ ልጆች ከወላጅ ተደብቀው የተለያዩ መጥፎ ልምምዶችን እንዲለማመዱ ሊያነሳሳቸው፣ ቤታቸውን ሊጠሉና ቶሎ አድገው ራሳቸውን መቻልና ከቤት መውጣትን ሊናፍቁ ይቻላሉ።

**አራተኛዎቹ** ዓይነት ወላጆች ለልጆቻቸው ሚዛኑን የጠበቀ ፍቅርና ልጆችን የመቅጣት መርህ ያላቸውና የሚለማመዱ ናቸው። እንዲህ ዓይነት ወላጆች ያሏቸው ልጆች በቤት ውስጥ ማን አለቃ እንደሆነ፣ ኃላፊነታቸውና ግዴታቸው ምን እንደሆነ በመረዳትና ገደባቸውን ጠንቅቀው ለይተው በማወቅ ከወላጆቻቸው ጋር መልካም ግንኙነት እንዲኖራቸው ዕድል የተፈጠረላቸው ልጆች ናቸው። እንዲህ ዓይነት በወላጅና በልጆች መካከል መልካም የሆነ ግንኙነት ያላቸው ቤቶች ጤነኛ፣ ጠንካራና ደስተኛ የሆነ ቤተሰብ ይኖራቸዋል፡፡ ከዚያም ባለፈ በቤት ውስጥ ካለው መልካም ተጽዕኖ የተነሳ ሴት ልጅ ወደ ፊት እንደ አባቷ ዓይነት ጓደኛና ባል እንዲኖራት ስትመኝ ወንዶች ልጆች ደግሞ እንደ እናታቸው ዓይነት ጓደኛና ሚስት እንድትኖራቸው ሊመኙ ይችላሉ።

ወላጆች ከልጆቻችን ጋር ያለን ግንኙነትና አቀራረብ የትኛው ዓይነት እንደሆነ በግል ጊዜያችን እንደ ጥንድ ራሳችንን ማየት፣ ለውጥና ማሻሻል ማምጣት ያለብን የቱ ጋ እንደሆነ መረዳትና ፈጥነን እርምጃ መውሰድ ይጠበቅብናል፡፡ መልካምና ጤነኛ የሆነ ግንኙነት ከልጆች ጋር እንዲኖረን የሚያስችል ሁኔታና አካባቢ መፍጠር መቻል አለብን።





እንደ መልካም ወላጅ ልጆቻችንን ማፍቀር፣ መንከባከብና አቅማችን በፈቀደ መጠን የሚያስፈልጋቸውን ለማሟላት ጥረት ማደረግ አስፈላጊ ነው። አግባብነት ባለው መንገድ ልጆችን መቅጣትና መቆጣጣርም የፍቅር መግለጫ እንደሆነ በማሰብ ሚዛኑን በጠበቀ መንገድ ልጆችን ለመቅጣት በጋራ መስማማት አልያም ቢያንስ በልጆች ፊት ስንሆን ባለመስማማት መስማማት መቻል ይኖርብናል።[75]

## 3. እንዴት መቅጣት እንዳለባቸው እንደሚገባ ባለማወቅ

ልጆች በስነ ስርዓት ታንጸው እንዲያድጉ ከሚደረጉ የተለያዩ የጥረት መንገዶች አንዱ በአግባብ መቅጣት ነው። ልጆችን በአግባብ መቅጣት አስፈላጊ እንደሆነ ተረድተው ነገር ግን እንዴት መቅጣት እንዳለባቸው ካለማወቅ የተነሳ በልጆች ላይ የሚፈጠር የተለያየ አሉታዊ ተጽዕኖ በባለትዳሮች መካከልም አለመግባባት ብሎም ከፍተኛ የሆነ ግጭት እንዲታይ ያደርጋል። ባለትዳሮች የሚከተሉት የቅጣት መንገድም እንደ ራሳቸው የቁጣ ስሜት፣ የቤተሰብ የቅጣት ልምምድና እንደ ልጆቻቸው ቅርበትና ርቀት የተለያየ ሊሆን ይችላል። በዚህ የተለያየ የቅጣት ዓይነት ባለትዳሮች አንዱ በሌላው ላይ በሚሰጠው አስተያየት፣ የቁጣ ስሜትና የማይገባ ንግግር ለግጭት በር እንዲከፈትና ግጭቶች እንዲባባሱ ዕድል ይሰጣል።

## 4. ከልጆች ዕድሜ፣ ማንነትና ጥፋት ጋር ተመጣጣኝ ያልሆነ ቅጣት

ሌላው ልጆችን በመቅጣት ዙሪያ መነሳት ያለበት ጉዳይ የልጆችን ዕድሜ ያላማከለ ወይም ተመጣጣኝ ያልሆነ ቅጣት የመቅጣት ችግር ነው። እስከ አንድ ዓመት ከስድስት ወር ( 1 1/2) እድሜ ያላቸው ሕጻናቶችና ከ2-8 ዓመት ያሉ ልጆች ሊቀጡ የሚችሉበት ዘዴና የቅጣት መጠን ሊለያይ ይገባዋል። እንደ ዕድሜያቸው የቅጣቱ ዘዴና መጠን ሊለያይ ሲገባው አንድ ወጥ በመሆን የቅጣት መጠንና ዘዴ በመጠቀም ልጆችን መቅጣት በልጆች ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያስከትላል፡፡ የልጆች መጎዳት ደግሞ ወላጆችም ስምምነት እንዳይኖራቸው ብሎም ለግጭት ተጋላጭ እንዲሆኑ ያስገድዳቸዋል።

የልጆችን ዕድሜ ብቻ ሳይሆን ልጆች የተለያየ ባሕርይ እንዳላቸው አለመረዳትም ሌላው ችግር ነው። ልጆችን ጠንቅቆ ማወቅ የሚረዳው እንደ ባሕርያቸው ለመያዝና ለማሳደግ የሚሰጠው ጠቀሜታ ከፍተኛ በመሆኑ ነው። በማሳደግ ሂደት ውስጥ ደግሞ ልጆች ሲያጠፉና የተበላሸ ድርጊት ሲለማመዱ ለመመለስና ለማስተካከል የተለያዩ የቅጣት እርምጃዎች መወሰዳቸው አይቀሬ ነው። አባትና እናት በልጆች ቅጣት ላይ እርስ በርሳቸው እርሱን/ሷን/ እያወቅህ/ሽ/ በማለት እሰጣ ገባ ይፈጥራሉ፡፡ የቃላት ምልልሱም ወደ ግጭት ሊያድግ ይችላል።

---

[75] Reuben Hill's research as presented by Dr. Richard Meier in a seminar on parenting, MinirthMeier Clinic, Dallas, Texas, 1988.

ሌላው ተጠቃሽ ምክንያት ደግሞ ልጆች አጠፉ የተባሉትና የቅጣቱ እርምጃ ተመጣጣኝ አለመሆኑ ነው። በጣም የሚያቀርቧቸውን ልጆች ከፍተኛ የሆነ ጥፋት በዝቅተኛ ቅጣት ሲያልፉ ሌሎችን ደግሞ ዝቅተኛ የሆነ ጥፋት አጥፍተው ከፍተኛ የሆነ ቅጣት ሊቀጧቸው ይችላሉ። ሚዛኑን ያልጠበቀን ጥፋት፣ ጥፋተኝነትና ቅጣት የተመለከቱ ልጆች በሚያነሷቸው አግባብነት ያላቸው ጥያቄዎችና የቅጣቱን እርምጃ በወሰደና ባልወሰደ ወላጅ መካከል የሚደረግ የሃሳብ ቅብብሎሽ ወደ ቁጣ፣ ወደማይገባ ንግግርና ግጭት ውስጥ ሊገባ ይችላል።

## 5. መቅጣት ሳይሆን መጉዳት

ልጆችን መቅጣት አስፈላጊ ቢሆንም ለጥፋቱ ተመጣጣኝ ባልሆነ መጠን ለመቅጣት የምንጠቀምባቸው መንገዶች ልጆችን ይበልጥ የሚጎዱ ናቸው:: በየጊዜው በኃይል በመቆጣትና ከቁጥጥር ውጭ በመሆን የሚወሰዱ እርምጃዎች ጸጸት ውስጥ ሊከቱ ይችላሉ:: የዚህ ዓይነቱ ልምድ ባልና ሚስትን ሊያጋጭ የሚችልና በመንግሥታዊ አካላትም ሊያስጠይቅ የሚችል ነው:: ባልተመጣጠነ ቅጣት ምክንያት አካላዊ ጉዳት መፈጠር ነው። በልጆች ላይ የሚከሰተው ጉዳት አካላዊ ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊ፣ ስነ ልቦናዊ፣ ስሜታዊ፣ ማሕበራዊና አካዳሚካል ሊጎዱ ይችላሉ። ልጆችን በአግባብ ባለመቅጣት የሚፈጠር ጉዳት ባለትዳሮችን ሊያጋጭና በሌሎች ልጆች በወላጆቻቸው ላይ ያላቸው ግንኙነት በከፍተኛ ፍርሃት እንዲመሠረት ሊያደርግ ይችላል።

## III. ልጆችን እየቀጡ በማሳደግ ሂደት ለሚፈጠሩ ግጭቶች መፍትሔዎቻቸው

### 1. መረዳት፦ የልጆችን የዕድሜና የፍላጎት ለውጥ መረዳት

የልጆች እድገት ፈጣን ከመሆኑ የተነሳ በየጊዜው ዕድሜ አመጣሹ የልጆችችን ፍላጎት መረዳት ተገቢ ነው። ልጆችን እንደ አዋቂ ከማየት ወይም አድገው እያሉ አሁንም ሕጻን እንደሆኑ አድርጎ በመቁጠር ዕድሜያቸውን ያላማከለ ቅጣት ከመቅጣት መታቀብ ተገቢ ነው። የልጆችን ዕድሜ፣ ባሕርይና ፍላጎት በመረዳት አግባብነት ያለውና ተመጣጣኝ የሆነ የቅጣት እርምጃ በመውሰድ ልጆችን በስነ ስርዓት ታንጸው እንዲያድጉ መርዳት ተገቢ ነው። የልጆችን ዕድሜ አመጣሹን ፍላጎትና ባሕርይ ለመረዳት ከልጆች ጋር በፍቅር የሆነ የቅርብ ግንኙነትና ተግባቦት ሊኖረን ይገባል።

### 2. መጠቀም፦ የተለያዩ የቅጣት ዘዴዎችን መጠቀም

የልጆችን እድሜ፣ ፍላጎትና ባህርይ መረዳት ምን ዓይነት የቅጣት የስነ ስርዓት እርምጃ መውሰድ እንደሚያስፈልግ ለመመለየት ይረዳል። በልጆች ላይ ከፍተኛ የሆነ አካላዊም ሆነ ሌላ በሁለንተናዊ ማንነታቸውና እድገታቸው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳይፈጠር ጥንቃቄ በማድረግ የተለያዩ የቅጣት ዘዴዎችን መጠቀም አስፈላጊ ነው። በጣም ሕጻናት ለሆኑ ልጆች ማለትም እስከ **18 ወር ዕድሜ** ያላቸውን ሕጻናት ጠንካራ የሆነ ቅጣት ሳይሆን ትኩረታቸውን ወደ ሌላ ሊወስድ የሚችል ሌሎች ነገሮችን





መጠቀም አስፈላጊ ነው። **ከሁለት ዓመት እስከ 8** ዓመት ድረስ ያሉትን ልጆች ደግሞ ከጭዋታ ውጭ/ Time Out/ በማድረግ መቅጣት አንዱ የተሻለ የቅጣት መንገድ ነው። ይህ ሲሆን ለአጭር ጊዜ መሆን አለበት:: የቅጣቱንም ጊዜ በመጥቀስና ደቂቃ በመያዝ ከምንም ዓይነት ጭዋታና ቴሌቭዥን ከማየትም መከልከል ጥሩ ሊሆን ይችላል።

ሌላው ከጭዋታ ውጭ ማድረግ ካልሠራ ሌላ መንገድ መጠቀም ይቻላል:: ለምሳሌ በጣም የሚወዱቱን፣ የሚጠቀሙበትንና ወደ ፊት እንዲደረግላቸው የሚፈልጉትን የተለያየ ጥቅማ ጥቅም እንደ ዕድሜያቸው መጠን ለተወሰነ ሰዓት፣ ቀንና ሳምንት በመከልከል የተቀጡበትን ምክንያት እንዲያውቁና ወደ ፊት ከስነ ስርዓት ውጭ እንዳይሆኑ ለመርዳት መጣር ሌላው አማራጭ ነው:: እርምጃው ዛሬ በተወሰደባቸው የስነ-ስርዓት እርምጃ ተምረው ለነገ እንዲፈሩ፣ እንዲያስቡና ጥንቃቄ ማድረግ እንዲጀምሩ ያደርጋቸዋል። ሌላው አካላቸው እንዳይጎዳ በመጠንቀቅ መቀመጫቸው ላይ በትንሹ መግረፍ ወይም መምታት ስርአት እንዲይዙ ይረዳቸዋል።[76]

### 3. መለማመድ፦ መጉዳትን ማስቀረትን መለማመድ

እንደ ወላጅ ልጆችን መቅጣት አለብን ብለን ስናስብ መጠየቅ ያለብን "ልጆችን መቅጣት የሚያስፈልገው ለምን፣ መቼ፣ እንዴትና የት ነው?" የሚሉ ጥያቄዎችን ነው:: እነዚህን ጥያቄዎች በማንሳት በአግባቡ መመለስ መቻል ልጆችን ወደ መቅጣት እርምጃ ስሜታዊ ሆነንና ለልጆች መሻሻል በማይጠቅም ጎጂ መንገድ እንዳንገባ እንዲሁም ተገቢ ባልሆነና አቅማቸውን ባላገናዘበ መንገድ በመቅጣት እንዳናስመርራቸው አስቀድመን እንድናስብበት ይረዳናል። በአካላቸው ላይ ጠባሳ፣ ጉዳት ወይም ስብራት እስኪኖር ድረስ መቅጣት ተገቢ አይደለም። እንዲህ ዓይነቱ እርምጃ ልጆችን የሚጠቅም ቅጣት ሳይሆን በልጆች ላይ አካላዊ፣ ስነ ልቦናዊና ስሜታዊ ቀውስ የሚያስከትል ጉዳት ነው። በዚህ መንገድ ሲቀጡ በስነ ልቦናቸው ላይ የሚደርስባቸው ጎጂ ተጽዕኖ የፍርሃት ስሜት የሚሰማቸው፣ በነገሮች ሁሉ የሚደነግጡ፣ ድፍረት የሌላቸውና ከፍ ያለ ድምጽ ሲሰሙ የሚበረግጉ ያደርጋቸዋል:: በሚፈጠርባቸው አሉታዊ ተጽዕኖ ምክንያትም ወላጆቻቸውን፣ ከእንደዚህ ዓይነት ቤተሰብ መወለዳቸውንና በሕይወት መኖራቸውንም የሚጠሉ ይሆናሉ:: ከስተቱም እንደ ተፈረደባቸው አድርገው እንዲቆጥሩና በአካላዊ፣ በአእምሯዊና በመንፈሳዊ እድገታቸው ላይ ከፍተኛ የሆነ ከፉ ተጽዕኖ እንዳይፈጥርባቸው ጥንቃቄ ማደርግ ያስፈልጋል። *"... እናንተም አባቶች ሆይ፥ ልጆቻችሁን በጌታ ምክርና በተግሣጽ አሳድጉአቸው እንጂ አታስቆጡአቸው።"* /ኤፌ 6: 4/[77]

---

[76] http://www.focusonthefamily.com/parenting/effective-biblical-discipline/approaches-to-discipline/approaches-to-discipline-ageappropriate-discipline Accesed 12/30/2014

[77] my.cbn.com/.../display.php?topicid *Biblical Models of Functional and Dysfunctional Families Accsesed Apiril 23, 2014.*

## 4. መተግበር፡- የቅጣትን እርምጃ ያለአድሎ መተግበር

ልጆችን ከልጆች አበላልጦ ማየት፣ ማቅረብና ማግለል፣ መስጠትና መከልከል ብሎም መቅጣትና መጉዳት የሚሉ ሚዛናቸውን ያልጠበቁና አድሎ የተሞላባቸው አቀራረቦችን ማስወገድ ተገቢ ነው። አድሎ ማድረግ በልጆች መካከል ጠብና አለመግባባት እንዲፈጠር ሊያደርግና ወዳጅነት ሳይሆን ጠላትነት ሊያስከትል ይችላል። አሁን ባለው እድገታቸው ብቻ ሳይሆን አድገው ከቤት ከወጡ በኋላም በአእምሮቸው ሊመጣ የሚችል የቁጣና ንዴት፣ የጸጸትና ምሬት፣ የበታችነት ስሜትና ይፈቀሩ እንዳልነበር የሚያስታውሳቸው ትዝታ ስሜት እንዲኖራቸው ያደርጋል።

ወላጆች በልጆች ላይ በሚያሳዩትና በሚያደርጉት አድሏዊ ግንኙነትና የቅጣት እርምጃ በልጆች ላይ ጥያቄና ማጉረምረም ሲፈጥር በባልና ሚስት መካከልም ለእርሱ/ሷ/ ግድ የለህም/ሽም/ የሚል ክስ ሊያስከትልና በቤት ውስጥ ሁለት የተለያየ ጎራ እንዲኖር ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል። ልጆች እንደ ቤተሰብ፣ ባልና ሚስት እንደ ባለትዳር አንድነት እንዳይኖራቸውና በልጆች ምክንያት አለመግባባት፣ ጠብ፣ ግጭት ብሎም የቤተሰብ መለያየት ምክንያት እንዳይሆን ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

## 5. መጠበቅ፡- የገቡትን ቃልና ተስፋ መጠበቅና መፈጸም

ልጆችን በስነ ስርአት አንጾ በማሳደግ ሂደት የወላጅን አስተዋጾ ከፍተኛና ዋና ከሚያደርጉት ምክንያቶች አንዱ ለልጆች ላቅ ያለ ምሳሌነት የሚያሳዩ መሆናቸው ነው። ልጆች እንዳያደርጉ የሚታሰበውን ወላጆች ቀድመው ምሳሌ በመሆን አለማድረግ ካደረጉም ይቅርታ መጠየቅን ማለማመድ ይኖርባቸዋል። ይህን ምሳሌነት ከሚያሳዩበት መልካም ተግባር አንዱ የገቡትን ተስፋ መፈጸም መቻላቸው ነው፡፡ ወላጆች መጠንቀቅ ያለባቸው የማይወጡትን፣ የማይችሉትን፣ አቅምን ያላገናዘበና ተፈጻሚነት የሌለው ተስፋ ለልጆች ከመስጠት መቆጠብ መቻል ላይ ነው። ልጆች የተገባላቸው ተስፋ ሲፈጸምላቸው ከማየት የበለጠ የሚያስደስታቸው ድርጊት እንደሌለ ወላጆች ሊገነዘቡት ይገባል። የተገባላቸው ተስፋ ሲፈጽምላቸው ማየት የሚያስደስታቸውን ያክል ባለተፈጸሙ ዝናብ የሌላቸው ደመናዎች በሆኑ ተስፋዎች እጅግ ይናደዳሉ፡፡ ነገሩ ከተደጋገመ በወላጆቻቸው ላይ ያላቸው አመኔታም እየቀነሰ ይመጣል።

ስለዚህ ወላጆች የተስፋ ቃሎች በምንሰጥበት ጊዜ ተጠንቅቀን እንናገር፣ የተናገርነውን የተስፋ ቃል ለመፈጸም ጥረት እናድርግ ብሎም ሊፈጸሙ ባልተቻሉ ጉዳዮች ላይ ምክንያቶችን ለማብራራት ጥረት ማድረግና በግልጥ ይቅርታ መጠየቅን እንልመድ፡፡ ይህን ስናደርግ በመካከላችን ሊኖር የሚገባውን የወላጅና የልጆች መልካም ግንኙነት መጠበቅ እንችላለን። የልጆች አእምሮ እርጥብ ሲሚንቶ ነው እንደሚባለው በአእምሮቸው ላይ የምንጽፈውና የምናስቀምጠው የቃልና ተግባር ምሳሌነት ከፍተኛ



የግጭት መንስኤዎችና መፍትሔዎቻቸው በጋብቻ ውስጥ

እንደሆነ በመገንዘብ ከፍተኛ የሆነ ጥንቃቄ ማድረግ የተሻለ ትውልድ ለማፍራት እገዛው ታላቅ ነው፡፡

## 6. መፈለግ፡- የሌሎች ሰዎችን እርዳታ መፈለግ

ልጆችን ወልዶ ማሳደግ ራሱን የቻለ አዲስ ልምምድ ነው። ልጆችን በማሳደግ ሂደት መካከል ልጆች የተለያየ የሚገባና የማይገባ ባሕርይ ማሳየታቸው የተለመደ ነው። ልጆች በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ለሚያጠፏቸው የተለያዩ ጥፋቶች በስነ ስርአት ታንጸው እንዲያድጉ ለመርዳት ወላጆች የሌሎች ሰዎች ሙያና ልምምድ ሊያስፈልጋቸው ይችላል። እንደ ልጆች ዕድሜና ባሕርይ የሌሎችን ሰዎች እርዳታ መፈለግ ተገቢ ነው። ወላጆች ከሌሎች ሰዎች የሚፈልጓቸው የተለያዩ እርዳታዎችን ማግኘት አለባቸው፡፡ ለምሳሌ፡ ወላጆች በጸሎት መደገፍ፣ በእግዚአብሔር ቃል መማር፣ መመከርና የልምድ ልውውጥ ማድረግ ከሌሎች ሰዎች ሊያገኟቸው ከሚችሏቸው ድጋፎች መካከል ተተቃሾች ናቸው፡፡ ከዚህም ባለፈ በልጆችና በቤተሰብ ላይ ባለሙያ በሆኑ ክርስቲያን አማካሪዎች በምክር አገልግሎት መደገፍ ጥበበኛነት ነው። ለችግሮቻችን ትክክለኛ የሆነ እገዛና አገልግሎት የሌሎች ድጋፍ እንዲደረግልን ሰዎችን ማግኘት በጥንቃቄ ሊታሰብበት የሚገባ ጉዳይ መሆኑንም መዘንጋት የለብንም።

## ለጥንዶች በግላቸውና በቡድን ለማጥናት የሚረዷቸው የውይይት ጥያቄዎች

## የምዕራፍ ሃያ (20)
## የውይይት ጥያቄዎች

1. ልጆችን በአግባቡ በመቅጣት ማሳደግ በሚለው ሃሳብ ላይ መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት በማድረግ ተወያዩ።
2. ልጆችን እየቀጡ በማሳደግ ሂደት በባለትዳሮች መካከል ሊፈጠሩ የሚችሉ የግጭት መንስኤዎችን በመዘርዘር ተወያዩባቸው።
3. ልጆችን በመቅጣት ሂደት ከሚፈጠሩ ችግሮች መካከል አንዱ የቅጣት እርምጃ የመውሰድ ምንነትን እንደሚገባ ጠንቅቆ አለመረዳት ነውና ልናውቃቸውና ልንወስዳቸው የሚገቡ በመጽሐፉ የተጠቀሱ ስድስት መርሆችን በመዘርዘር በሰፊው ተወያዩባቸው።
4. በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱ አራት ዓይነት ወላጆችን በመጥቀስ እናንተ የትኛው ውስጥ ልትመደቡ እንደምትችሉ ራሳችሁን በመፈተሽና ለውጥ የሚያሻችሁ ምን ላይ እንደሆነ ለመለየት ውይይት አድርጉ።
5. ልጆችን በአግባቡ ከመቅጣት ይልቅ የተለያየ ጉዳት እንዲደርስባቸው የምናደርገው በምን ምክንያት ነው? ደግሞስ እንዳንጎዳቸው ምን ማድረግ አለብን ትላላችሁ?
6. በአጠቃላይ ልጆችን በመቅጣት ሂደት በባለትዳሮች መካከል ለሚፈጠሩ ግጭቶች የመፍትሔ ሃሳቦችና እርምጃዎች ምንድን ናቸው?
7. ከዚህ ውይይት በኋላ ልትወስዷቸው የሚገቡ ተግባራዊ እርምጃዎች ምንድን ናቸው?





# ምዕራፍ ሃያ አንድ (21)
# በቂ እንቅልፍ ማጣት

## I. በቂ የሆነ እንቅልፍ የማጣት ምንነት

እግዚአብሔር የሰው ልጅ እረፍት እንዲያደርግባቸው ከሰጣቸው ስጦታዎች መካከል አንዱ እንቅልፍ ነው። እንቅልፍ ለሰው ልጅ ከሚያስፈልጉት መሠረታዊ ፍላጎቶች ውስጥ ይመደባል። ብዙ ጥናቶች የሰው ልጅ በቀን ከ7-9 ሰዓት ያክል በቂ የሆነ እንቅልፍ ሊያገኝ እንደሚገባው ይገልጻሉ።[78] ለሰው ልጅ እንቅልፍ እንዲተኛ የተመደበለት ሰዓት ብርሃን በጨለማ የሚተካበት የምሽቱ ወይም የሌሊቱ ሰዓት እንደሆነ የእግዚአብሔር ቃል ይናገራል **/ማቴ 25፡ 6-7/**፡፡ የሰው ልጆች ልምምድም ይህንኑ ይመሰክራል። ሐዋሪያው ጳውሎስ በቀንና በጨለማ መካከል የተለያዩ ሥራዎች እንዳሉ ለማሳየት ምሳሌ በማድረግና በማወዳደር ሲገልጽ የምንመለከተው ነባራዊውን (ገሃዳዊውን) የሰው ልጆች ልምምድ መሠረት በማድረግ ነው። *"ከእንቅልፍ የምትነሡበት ሰዓት አሁን እንደ ደረሰ ዘመኑን እወቁ፤ ካመንንበት ጊዜ ይልቅ መዳናችን ዛሬ ወደ እኛ ቀርቦአልና። ሌሊቱ አልፎአል፥ ቀኑም ቀርቦአል። እንግዲህ የጨለማውን ሥራ አውጥተን የብርሃንን ጋሻ ጦር እንልበስ። በቀን እንደምንሆን በአገባብ እንመላለስ፤ በዘፈንና በስካር አይሁን፥ በዝሙትና በመዳራት አይሁን፥ በክርክርና በቅናት አይሁን፤"* **/ሮሜ 13፡ 11-13/**

በቂ እንቅልፍ አለማግኘት ሁልጊዜ ከትክክለኛውና ከተመጠነው በላይ ራሱን የቻለ አሉታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል። በቂ የሆነ እንቅልፍ ማጣትም ሆነ ብዙ መተኛት ራሳቸውን የቻሉ የተለያዩ ችግሮች ናቸው። በቂ እንቅልፍ ማግኘትን ዳዊት እንዲህ ሲል ይገልጸዋል፡- *"በሰላም እተኛለሁ እንቀላፋለሁም አቤቱ፥ አንተ ብቻህን በእምነት አሳድረኸኛልና።"* **/መዝ 4፡ 8/**፡፡ ብዙ መተኛትና እንቅልፍ ማብዛትንም *"የእንቅልፍም ብዛት የተቦጫጨቀ ጨርቅ ያስለብሳልና።"* **/ምሳ 23፡ 31/** በማለት ይገልጠዋል፡፡ በቂ የሆነ እንቅልፍ ማጣት ማለት በተለያዩ ምክንያቶች ወይም አስገዳጅ ሁኔታዎች የሰው ልጅ በመደበኛነት በየዕለቱ **ከ7 - 9 ሰዓታት** ለሚረዝም ጊዜ ማግኘት ያለበትን እንቅልፍ ማግኘት ያለመቻል ሂደትና የሚያስከትለው የጎንዮሽ ተጽዕኖ ነው፡፡

የትዳር ጓደኞች በየቀኑ ማግኘት ያለባቸውን እንቅልፍ የሚያጡ ከሆነ አእምሯቸውና ሰውነታቸው ጤናማ ስለማይሆን የባልነትና የአባትነት ወይም የሚስትነትና የእናትነት ኃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣት ያቅታቸዋል፡፡ ይህም ከትዳር ጓደኞቻቸው ጋር ጤናማ ግንኙነት እንዳይኖራው ስለሚያደርግ አለመግባባትና ግጭት እንዲፈጠር የሚያደርግ አሉታዊ ተጽዕኖን ያስከትልባቸዋል፡፡ የዚህ ምዕራፍ ዋና ትኩረት በቂ እንቅልፍ አለማግኘት በትዳር ግንኙነት ላይ የሚያስከትለውን አሉታዊ ተጽዕኖ በማስረዳት በዚህ ምክንያት በባልና በሚስት መካከል ሊፈጠር የሚችልን

[78] Rath, Tom. Eat, Move Sleep. Mssionday united states, 2013.

ግጭት አስቀድሞ ለመከላከል፣ ችግሩ በተፈጠረ ጊዜ ደግሞ አፍራሽ ተጽዕኖውን በመቀነስ ችግሩን ለመፍታትና ትዳርን በጤናማነት ለመምራት የሚያግዝ ገንቢ ሚና መጫወት ነው:: ይህንንም ትኩረት በተሳካ መንገድ ለመወጣት በቂ እንቅልፍ የማግኘትን አስፈላጊነት፣ በቂ እንቅልፍ አለማግኘት በትዳር ውስጥ የሚያስከትለውን ችግርና የመፍትሔ አሳቦችን በዚህ ምዕራፍ ውስጥ አቀርባለሁ::

## II. የበቂ እንቅልፍ አስፈላጊነት

ምናልባት የሰው መሠረታዊ ፍላጎቶች ተብለው የተማርናቸውና የሰማናቸው ነገሮች ሶስት ብቻ ሊሆኑ ይችላሉ:: ነገር ግን በቂ እንቅልፍ ማግኘትም ከሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጎቶች መካከል አንዱ ነው። በቂ እንቅልፍ መተኛት ሰውነታችንና አእምሯችን ጤናማ እንዲሆን ይረዳል። እንቅልፍ ስንተኛ እድገትን የሚቆጣጠረው ሆርሞን ከፍተኛ ደረጃ ላይ ይደርሳል። ሰውነትን በቂ የሆነ እንቅልፍ እንዳያገኝ ማድረግ ለከፋ ጉዳት ሊዳርገን ይችላል። የተፈጠርነው የሕይወታችንን **አንድ ሶስተኛውን**( 1/3) ዕድሜ እንድንተኛ ማለትም በእንቅልፍ እንድናሳልፍ ሆነን የተፈጠርነው። ለማንም ሰው በቀን **በ24 ሰዓት ውስጥ ለ8 ሰዓት** ያክል በመተኛት ተመጣጣኝ የእርፍት ጊዜ እንዲኖረው ማድረግ እጅግ በጣም አስፈላጊ እንደሆነ ይታመናል።[79]

በምሥራብት የካውንስሊግ ሴንተር በጋራ በየወሩ "ራሳችንን ምን ያክል እንደምንከባከብ" እንጠየቃለን ምክንያቱም በአብዛኛው የማማከር አገልግሎት ከችግሮች ጋር በተያያዘ ሌሎችን ሰዎች መርዳት ስለሆነ ሌሎችን መርዳት እንድንችል የራሳችንን ደህንነት መጠበቅ አስፈላጊ ነው። ብዙ ጊዜ ሰዎችን በመርዳት ብቻ ራሳችንን፣ ትዳራችንንና ቤተሰባችንን እንዳንጎዳ ጥንቃቄ እንድናደርግ "Self Care" የሚባል ፕሮግራም አለን። በወር አንድ ጊዜ ባለን በዚህ ፕሮግራም ላይ "Eat Move Sleep" የሚል መጽሐፍ በግል አንብበን ምን ያክል በተግባር እየተረጎምነው እንደሆነ እንወያየለን፣ አንዱ ሌላውን ያበረታታል ብሎም ብዙ ራሱን የተንከባከበ በድምጽ ብልጫ ይሸለማል። በዚህ ወርሃዊ ፕሮግራም ላይ ከምናጠናቸው መጽሐፍት ውስጥ አንዱ የሀርቫርድን የሕክምና ትምህርት ቤት ጥናት መሠረት አድርጎ የተጻፈና በቂ የሆነ እንቅልፍ አለማግኘት ምን ያክል አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳለው መረዳት እንድንችል የሚያግዘን መጽሐፍ ነው። የመጽሐፉ ጸሐፊ ሲገልጽ "አሜሪካኖች በቂ እንቅልፍ በአላገኙ ሠራተኞች ብቻ በአመት **63 ቢሊዮን ዶላር** ይከስራሉ" ይላል። የዚህም ምክንያቱ ሠራተኞች በሥራ ገበታቸው ላይ የሚገኙ ቢሆንም ከድካም የተነሳ መሥራት ያለባቸውን እንዳይሰሩ በማድረግ ውጤታማነታቸው ላይ በቂ እንቅልፍ አለማግኘት ያሳደረባቸው አሉታዊ ተጽዕኖ መሆኑን ይገልጻል:: ይህ ሰው አንድ ሳይንቲስት

[79] The Popular Encyclopedia of Christian Counseling page 212





ያደረገውን ጥናት መሠረት በማድረግ ከትክክለኛ የእንቅልፍ ሰዓት አራት ሰዓት የቀነሰ ሰውና ስድስት ጠርሙስ ቢራ የጠጣ ሰው እኩል እንደሆኑ በማወዳደር ያስቀምጣል።[80]

## III. በቂ እንቅልፍ ማጣት የሚያስከትለው ተጽዕኖ

የተመጣጠነ እንቅልፍ አለማግኘት በሰው ሕይወት ላይ የሚያስከትለውን አሉታዊ ተፅዕኖ መመልከት ከጉዳቱ አስቀድሞ ለመጠንቀቅ ይጠቅማል። በቂ እንቅልፍ እንዳይኖር ሊያድርጉ የሚችሉ የተለያዩ ምክንያቶች ናቸው። ይህ ርዕስ የሚያተኩረው ከወሊድና ልጆችን ከማሳደግ ጋር ተያይዞ ሊፈጠር ያለውን የእንቅልፍ እጥረት በመዳሰስ የተወሰነ ግንዛቤ ማስጨበጥ ላይ ነው። ይህን ማድረጋችን ከወዲሁ ሊፈጠር ከሚችል ችግር አስቀድሞ ለመጠንቀቅ፣ ችግሩን ለማስተካከልና ጥንዶቹ የትዳር ሕይወታቸውን በማየት ፈጥነው እርምጃ እንዲወስዱ ለመርዳት እገዛው ከፍተኛ ነው። በቂ እንቅልፍ ማጣት የሚያስከተለውን ችግር በሁለት ጊዜያት በመከፈል ለማየት እንሞክራለን::

### 1. የአጭር ጊዜ ችግሮች

በቂ እንቅልፍ አለማግኘት በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊፈጥራቸው ከሚችላቸው ችግሮች መካከል አንዱ እንቅልፍ ያጣው የትዳር ጓደኛ በድብታ (በድብርት) የመያዝ ሁኔታ የሚያጋጥመው መሆኑ ነው። ይህ የድብርት ችግር በቀን ዕለታዊ ተግባር ላይና ሥራ የመፍጠር፣ የማቀድና የማከናወን ችሎታ ላይ ተጽዕኖ ያመጣል። ሌላው በቂ እንቅልፍ አለማግኘት ከአሁን በፊት ያልነበረ ድንገተኛ የጠባይ መለዋወጥ እንዲከሰትና ቀድሞ የነበረ መልካም ያልሆነ ጠባይ ደግሞ እንዲባባስ አስተዋጾ ያደርጋል።

በቂ የሆነ እንቅልፍ አለማግኘት ጊዜያዊ የመርሳት ችግርም ሊያስከትል ይችላል። የመርሳት ችግር በዕለት ተግባር፣ በትዳር ግንኙነትና ልጆችን በማሳደግ እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያመጣል። የመርሳት ብቻ ሳይሆን የዕለት ተግባርን በትኩረት የመከታተል ችሎታን ያሳጣል። እንደ ግለሰብና እንደ ባለትዳር በዕለት ኑሮ ላይ ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች መኖራቸው አይቀሬ ነው። ለአጭር ጊዜ ትኩረት የሚያሻቸውን ነገሮች በትኩረት ባለመከታተል የሚፈጠር ስህተትና ችግር ለከፋና ዘለቄታ ላለው ችግር አሳልፎ ሊሰጥ ይችላል። ለምሳሌ ለመጥቀስ ያክል በቂ እንቅልፍ ሳያገኙ መኪና የሚያሽከረክሩ ሰዎች ለከፋ የመኪና ግጭት እና ያንን ተከትሎ ለሚከሰት የአካል ጉዳት ብሎም ለሞት ሊያጋለጡ እንደሚችሉ ጥናቶች ይጠቁማሉ።[81] **በ2010** የሕንድ አየር መንገድ **737** የአውሮፕላን አደጋ አጋጥሞታል። አደጋው **የ158** ሰዎች ሕይወት ለህልፈት እንዲዳረግ ምክንያት ሆኗል። የደረሰው አደጋ ምክንያት ሲጠናና ዳታው ሲደመጥ *"በእንቅልፍ ምክንያት የማንኮራፋት ድምጽ"* ተከስቶ እንደነበር መረጃዎች ጠቁመዋል።[82]

[80] Rath, Tom. Eat, Move Sleep. Mssionday united states, 2013 page 80
[81] Rath, Tom. Eat, Move Sleep. Mssionday united states, 2013 page 80
[82] Rath, Tom. Eat, Move Sleep. Mssionday united states, 2013 page 80- 81

## 2. የረዥም ጊዜ ችግሮች

በቂ የሆነ እንቅልፍ ማጣት ወይም አለማግኘት የሚያስከትላቸው አሉታዊ ተጽዕኖዎች የአጭር ጊዜ ብቻ ሳይሆኑ የረጅም ጊዜ ጭምር ናቸው፡፡ የእንቅልፍ እጦት በጥንዶች ሁለንተናዊ ሕይወት ላይ ሊፈጥር የሚችለውን ችግር መገንዘብ ባለትዳሮች ልጆችን በማሳደግ ሂደት በጋራ ለመደጋገፍ እንዲችሉ ይረዳቸዋል። አንዳንድ በጥንዶች ላይ የሚታዩ እንደ ፍዘት፣ የባሕርይ ለውጥ፣ የጤንነት መታወክና የማሕበራዊ ግንኙነት ቀውስ የመሳሰሉ ችግሮች በቂ የሆነ እንቅልፍ ባለማግኘት የሚከሰቱ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ የሚከተሉትን በቂ እንቅልፍ አለማግኘት የሚፈጥራቸውን የረጅም ጊዜ ችግሮች መረዳት አስፈላጊ ነው። በአጠቃላይ በቂ እንቅልፍ አለማግኘት የሚያመጣቸው የረጅም ጊዜ ችግሮች ብዙ ቢሆኑም የተወሰኑትን ከዚህ በመቀጠል ለመጥቀስ እሞክራለሁ፡፡

### 1) አካላዊ

በእንቅልፍ እጦት ምክንያት ሰውነት ከልክ በላይ በመወፈር ክብደት ሊጨምር ይችላል። የሰውነትን ክብደት መጨመር ተከትሎ የሚመጡት የተለያዩ በሽታዎች ደግሞ ጥቂቶች አይደሉም። በቂ እንቅልፍ አለማግኘት ለኢንፌክሽን፣ ለስኳር በሽታ፣ ለሥርዓተ ልብ ቧንቧ በሽታዎች፣ ለጨጓራና ለአንጀት በሽታዎች ተጋላጭ ያደርጋል። ሌላው በቂ እንቅልፍ ካገኙ ሰዎች ይልቅ በቂ እንቅልፍ ያላገኙ ሰዎች ከዕድሜያቸው ቀድመው ለማርጀትና ረጅም ጊዜ ለሚቆይ ድካም ተጋላጭ ሊሆኑ ይችላሉ።

### 2) ስነ ልቦናዊ

በቂ እንቅልፍ አለማግኘት በሰውነት (በአካል) ላይ ብቻ ሳይሆን በሰው ስነ ልቦና ላይም አሉታዊ ተጽዕኖ ያመጣል። ከሚያስከትላቸው ችግሮ መካከል ሥር ለሰደደና ለከፍተኛ  የመርሳት ችግር አሳልፎ ይሰጣል። በቂ እንቅልፍ ማጣት የሰው አዕምሮ በትኩረት የመከታተል ችሎታው እንዲያንስና ፈጽሞ እንዲጠፋም ሊያደርግ ይችላል። የምንኖረው ኑሮና የምናደርገው ነገር ሁሉ የአስተሳሰባችን ውጤት ነው። በትክክልና በንቃት መልካም ለማሰብ አእምሮአችን አስፈላጊውን እረፍት ሊያገኝ ይገባዋል። አእምሮአችን በቂ እረፍት እንዲያገኝ የሚያስችለው በተፈጥሮ የተሰጠን ስጦታ ቢኖር እንቅልፍ ነው። ስለዚህ በቂ እንቅልፍ በማግኘት አእምሮን ማሳረፍ ተገቢ ነው። ያረፈ አእምሮ ለመልካም ተግባቦት፣ ለውጤታማነትና ፍሬያማ ለመሆን አስተዋጸው ቀላል አይደለም።

### 3) መንፈሳዊ

በቂ እንቅልፍ አለማግኘት በመንፈሳዊ ሕይወታችንና በአገልግሎታችን ላይም አሉታዊ ተጽዕኖ ማምጣቱ አይቀሬ ነው። በቂ እንቅልፍ ካለማግኘት አሉታዊ ተጽዕኖዎች መካከል በአካላችን ላይ የሚፈጠረው ድካም በንቃትና በትጋት እንዳንጸልይ እና የእግዚአብሔርን ቃል በንቃት እንዳናጠናና እንዳንሰማ ማድረጉ ተጠቃሽ ነው፡፡ እግዚአብሔር በሰጠን ጸጋ ሌሎችን የመጥቀሙ አገልግሎት ያረፈና የተረጋጋ አዕምሮ





ይፈልጋል። የእንቅልፍ እጦት ከቅዱሳን ጋር መንፈሳዊ ኅብረት ለማድረግ፣ ለመገልገልና ለማገልገልም እንዳንችል ተጽዕኖ ሊያሳድርብን ይችላል።

ኢየሱስ ክርስቶስ *"ወደ ደቀ መዛሙርቱም መጣ፤ **ተኝተውም** አገኛቸውና ጴጥሮስን። እንዲሁም ከእኔ ጋር አንዲት ሰዓት እንኳ ልትተጉ አልቻላችሁምን? ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉና ጸልዩ፤ መንፈስስ ተዘጋጅታለች **ሥጋ ግን ደካማ ነው** አለው። ደግሞ ሁለተኛ ሄዶ ጸለየና። አባቴ፥ ይህች ጽዋ ሳልጠጣት ታልፍ ዘንድ የማይቻል እንደ ሆነ፥ ፈቃድህ ትሁን አለ። ደግሞም መጥቶ **ዓይኖቻቸው በእንቅልፍ ከብደው ነበርና ተኝተው አገኛቸው።** ደግሞም ትቶአቸው ሄደ፥ ሦስተኛም ያንኑ ቃል ደግሞ ጸለየ። ከዚያ ወዲያ ወደ ደቀ መዛሙርቱ መጥቶ። እንግዲህስ **ተኙ ዕረፉም፤** እነሆ፥ ሰዓቲቱ ቀርባለች የሰው **ልጅም** በኃጢአተኞች እጅ አልፎ ይሰጣል።"* /**ማቴ 26፡ 40-45**/ በማለት ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በነበረው ጸሎት ላይ የተናገራቸው ቃላቶች ይህን እውነት የሚገልጡ ናቸው።

ሐዋርያው ጳውሎስም ካለፈባቸው የወንጌል አገልግሎት ችግሮች፣ ተግዳሮቶችና ፍርሃቶች መካከል ብዙ ጊዜ እንቅልፍ በማጣት ማሳለፉ አንዱ እንደሆነ *"በድካምና በጥረት ብዙ ጊዜም እንቅልፍ በማጣት፥ በራብና በጥም ብዙ ጊዜም በመጦም፥ በብርድና በራቁትነት ነበርሁ።"* **2ኛቆሮ ፲፩፡ 7** *"ብዙ ጊዜ በመንገድ ሄድሁ፤ በወንዝ ፍርሃት፥ በወንበዴዎች ፍርሃት፥ በወገኔ በኩል ፍርሃት፥ በአሕዛብ በኩል ፍርሃት፥ በከተማ ፍርሃት፥ በምድረ በዳ ፍርሃት፥ በባሕር ፍርሃት፥ በውሸተኞች ወንድሞች በኩል ፍርሃት ነበረብኝ፤ በድካምና በጥረት **ብዙ ጊዜም እንቅልፍ በማጣት፥** በራብና በጥም ብዙ ጊዜም በመጦም፥ በብርድና በራቁትነት ነበርሁ።"* **2ኛቆሮ ፲፩፡ 26-27** በማለት ገልጿል፡፡

### 4) ስሜታዊ

በቂ እንቅልፍ አለማግኘት ሌላውን ተጽዕኖውን የሚያሳርፈው በስሜታችን ላይ ነው። በቂ እንቅልፍ የሌለው ሰው ሊሰሙት ከሚችሉ ስሜቶች መካከል አንደኛው በምንምና በማንም እርካታ የማይኖረው ሰው ሊሆን መቻሉ ነው። ከእርካታ የለሽነት የተነሳ በትንሹም በትልቁም ነገር የሚነጫነጭ፣ ቶሎ ስሜቱ የሚነካና ብስጩ ሰው እንዲሆን ሊገደድ ይችላል። በቂ እንቅልፍ አለማግኘት የተስፋ ቢስነት ስሜት እንዲሰማውም ያደርገዋል። ሰው ተስፋ ቢስነት የሚሰማው ሲሆን ደስተኛ ከመሆን ይልቅ ሐዘንተኛ፣ ተመራሪና በቀላሉ የሚያኮርፍ መሆን ሊያዘወትር ይችላል። እንደዚህ ዓይነት ስሜት በእነርሱ ላይ በመፈራረቁ በባለትዳሮች ግላዊ፣ ቤተሰባዊና ማሕበራዊ ሕይወትና ግንኙነት ላይ ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ ይፈጠራል።

### 5) ማሕበራዊ

በትዳር ውስጥ ባለ ሰው ላይ በቂ እንቅልፍ አለማግኘት የሚፈጥረው ሌላው እንግዳ የሆነ መጥፎ ተጽዕኖ ከግል ሕይወቱ ባለፈ ከትዳር አጋሩ ጋር የሚኖረው ግንኙነትም የሚዛባ መሆኑ ነው፡፡ ደግሞም ከሌሎች የቤተሰብ አባላት፣ ከጎረቤትና ከቤተ ክርስቲያን አባላት ጋርም በሚኖረው መንፈሳዊና ማሕበራዊ ግንኙነት በንቃት እንዳይሳተፍና ገለልተኛ እንዲሆን ተጽዕኖ ሊፈጥርበት ይችላል።

## IV. በቂ የሆነ እንቅልፍ በማግኘት የትዳርና የቤተሰብን ጤንነት ለመጠበቅ የሚረዱ መፍትሔዎች

እግዚአብሔር ልጆችን ስጦታ አድረጎ ሰጥቶን የወላጅነት ኃላፊነት ላለብን የቅርብ ዓመት ባለትዳሮች ብዙ ነገሮች አዲስ ልምምዶች ሊሆኑብን ይችላሉ:: በዚህ ወቅት ለውጦችን በአግባቡና በብስለት ለመቆጣጠር እንዲቻል በጋራ ለመማርና ለማደግ መዘጋጀት አስፈላጊ ነው። ልጆችን በማሳደግ ሂደት ውስጥ አንዱ ፈተና በቂ የሆነ እንቅልፍ አለማግኘት ነው:: ልጆች በራሳቸው የጊዜ ሰሌዳ መተኛታቸውና መንቃታቸው የቀድሞ የመኝታ ልምምዳችን እንዲዛባ የሚያደርግ ችግር ይፈጥራል። ይህ ከሰተት የጸባይ ለውጥና አለመግባባት የሚፈጥር ምክንያት ሊሆን ይችላል:: በቂ የሆነ እንቅልፍ በማጣት ሊፈጠሩ የሚችሉ አለመግባባቶችና ግጭቶችን በማስወገድ በደስታ፣ በመልካም ተግባቦትና እርስ በርስ በመተሳሰብ መረዳዳትና አንዱ ሌላውን ማገዝ እንዲቻል መሠረታዊ እውነቶችን መረዳት ተገቢ ነው። ስለዚህ ችግሩን ለመቀነስ እንደሚዋደድ ባልና ሚስት ወይም ወላጅ በቂ የሆነ እንቅልፍ በማግኘት የወላጅነትን ኃላፊነት ለመወጣት ልናደርጋቸው የሚመከሩ አሳቦችን እንደሚከተለው ለማስቀመጥ እሞክራለሁ።

### 1. መረዳዳት፡- እርስ በርስ መረዳዳት

ከትዳር ዓላማዎች አንዱ የትዳር ጓደኛን ከመረዳትና መርዳት ጋር ተያያዥነት ያለው ነው። ባልና ሚስት ብቻቸውን ሲኖሩና ሲረዳዱ ከነበሩት በላይ እርስ በርስ መረዳዳት የሚያስፈልጋቸው ጊዜ ቢኖር ልጆች የሚወለዱበትና የሚያሳድጉበት ጊዜ ነው። በልጆች አስተዳደግ የባልና የሚስት ችሎታ፣ ልምምድና ዝንባሌ ሊለያይ ይችላል፤ ነገር ግን አንዱ ሌላውን በመረዳት መርዳት አስፈላጊ ነው። አንድ ቀላል የሆነ የእኛን ቤተሰብ ምሳሌ ባካፍላችሁ አሳቤን ለማገለጥ ይረዳኛል፡- ሁለቱ ልጆቻችን ተወልደው ከሆስፒታል ከወጡ ጀምሮ አብዛኛውን ጊዜ ገላቸውን የማጥባቸው እኔ ነኝ:: ነገር ግን የማለብሳቸውን ልብስ መርጣ የምታስቀምጥልኝ ባለቤቴ ናት:: አልሳካ ካለ ብቻ የሚለብሱትን ልብስ እኔው መርጬ ለማልበስ እሞክራለሁ። በእኛ ቤተሰብ ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ የልጆችን ልብስ ማጠብ፣ ማስተካከልና መርጦ ማልበስ የባለቤቴ ሥራ ሲሆን ሰውነታቸውን ማጠብ ደግሞ የእኔ ሥራ ነው ማለት ነው። እርስ በርሳችን በጋራ ለመረዳዳት የምንችለውን፣ ደስ የሚለንንና የምንወደውን በመረዳት በጋራ ልጆቻችንን የማሳደግ ኃላፊነታችንን ለመወጣት ጥረት እናደርጋለን።

በትዳር ውስጥ አንዱ ሰው ብቻ እንዳይጎዳ እርስ በርስ መረዳዳት በጣም አስፈላጊው የሕይወት ጥራት ነው! በአብዛኛው ልጆችን ማሳደግ የሚስቶች(የእናቶች) ሥራ ብቻ እንደሆነ አድርጎ ማሰብና መቁጠር፣ ኃላፊነትን በአንድ ሰው ላይ ብቻ መተውና ለወር ቀለብ የሚሆን ገንዘብ ሠርቶ ከማምጣት ውጭ ሌላ እርዳታ በቤት ውስጥ እንደማያስፈልግ ማሰብ ኢትዮጵያዊው ባህላችን የጫነብን ዘመን ያላስረጀው





ችግራችን ነው:: ይህንን ብዙዎችን ከስኬታማ የትዳር ሕይወት ወደ ኋላ የጎተተ ተግዳሮት ከዛሬውና ከነገው የትዳር ጉዟችን አስወጥተን የትላንት ታሪክ ብቻ እንዲሆን ማስወገድ ተገቢ ነው።

**በኃላፊነት ብዛት አንዱ አካል ብቻ እንዳይጎዳ እርስ በርሳችን በመተሳሰብ እንረዳዳ!**

### 2. መፍጠር፡- በቂ እረፍት የሚገኝበትን ሁኔታ መፍጠር

ልጆችን በማሳደግ ምክንያት የተዛባው የመኝታ ጊዜያችንን በሌላ መንገድ ሊካካስ የሚችልበትን መንገድ መፍጠር ጠቃሚ ነው። ልጆች የሚተኙበትን ጊዜ በማወቅ አብሮ እረፍት መውሰድ የሚቻልበትን ሁኔታ ማመቻቸት ሌላው አማራጭ መፍትሔ ነው። እንዲህ ዓይነቱን ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ሂደት ላይም አንዱ ሌላውን መርዳት ካልቻለ በስተቀር አስፈላጊውን እረፍት ማግኘት አይቻልም። ምናልባት አንዱ ሲያርፍ ሌላው ልጆችን በመያዝ እንዲጠብቅ በማድረግ ችግሩን ማስተካከል ይቻል ይሆናል።

እረፍት ለመውሰድ የምናስብበት ቦታ በተቻለ መጠን ድምፅ የሌለበት፣ ልጆችና የቤተሰብ አባላት ሊረብሹን የማይችሉበት እንዲሆን ምቹ ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ ነው:: በጥቂት ጊዜ የተወሰነ እረፍት ማድረግ እንድንችል ጥረት ማድረግ ለግል ጤንነት፣ መልካም ግንኙነት ላለው ትዳርና ልጆችን በደስታ ለማሳደግ ጠቀሜታው ከፍ ያለ ነው። በቂ የሆነ እንቅልፍ ለማግኘት የተለያዩ ዘዴዎችን መፍጠር ለነገ ሕይወታችን፣ ለትዳራችንና ለልጆቻችን በንቁ አእምሮ አዲስ ነገር ለመፍጠርና ወደ ተሻለ ኑሮ ለመሸጋገር ኢጋዥነቱ ጥቂት የሚባል አይደለም።

### 3. መምረጥ፡- ምቹ ጊዜያትን መምረጥ

በቂ እንቅልፍ በማግኘት ማረፍ እንዲቻል ምቹ ጊዜያትን መምረጥ ተገቢ ነው። ምናልባት በምርጫ ሂደት ወቅት ልጆች የሚተኙበትን፣ የሚነቁበትን፣ የሚመገቡበትንና የተለያዩ የልጆች ሁኔታዎችን፣ የመደበኛ የሥራ የጊዜ ሰሌዳን፣ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎትንና ቤተሰባዊና ማሕበራዊ ሕይወትን መቃኘት አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። የትኛው ምቹ ጊዜ ነው? ብሎ ማሰብ፣ መጠየቅ፣ መመካከርና ፈጥኖ እርምጃ መውሰድ አስተዋይነት ነው። በቂ እንቅልፍ ባለማግኘት ምክንያት ተቀምጠው እንቅልፍ የወሰዳቸውና ሕጻን ልጆቻቸውን በእንቅልፍ ልብ የጣሏቸው፣ የተጫኗቸው እንዲሁም በእንቅልፍ ልብ ሌሎች አስደንጋጭ ነገሮችን ያደረጉ እናቶች ጥቂቶች አይደሉም። ባሳለፍናቸው ዘመናት እኔና ባለቤቴ የሌሊቱን ክፍለ ጊዜ በመከፋፈል የልጆቻችንን ዳይፐር ለመቀየርና ወተት ለማጥባት የትኛው ጊዜና ሰዓት ለእያንዳንዳችን ምቹ እንደሆነ በመነጋገር፣ በመተሳሰብና በመረዳዳት ልጆቻችንን ለማሳደግ ጥረት ስናደርግ ነበር።

## 4. መፈለግ፡- የሌሎችን እርዳታ መፈለግ

በቂ እንቅልፍ አግኝቶ ለማረፍና ልጆችን በአግባብ ለማሳደግ በሚያስፈልግ ጊዜ የትዳር ጓደኞቻችንን ወይም ሌሎችን ሰዎች እንዲረዱን መጠየቅ አንዱ የመፍትሔ አሳብ ነው። እንዲረዱን የምንፈልጋቸው ሰዎች ምናልባት የቤተሰብ አባላት፣ ጓደኞች፣ ወዳጆች ወይም በከፍያ ሕጻን የሚጠብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። በሚያስፈልግ ጊዜና ሁኔታ የሚያስፈልግ እርዳታ መጠየቅ ተገቢ ነው። የሌሎች ሰዎች እርዳታ ባስፈለገን ጊዜ እኔን ያሳደገችኝ አልበቃ ብሏት የልጅ ልጆቿን በማሳደግ ከፍተኛ እርዳታ ላደረገችልን ውድ እናቴ (የሸጥላ ካሳ) እንዲሁም ከአገር ቤት ድረስ እኛን ለመርዳት ወደ አሜሪካ እንድትመጣ በመፍቀድ ብቻውን የመሆን መሥዋዕትነትን በመክፈል ለተባበረን ለውድ አባቴ እኔና ቤተሰቤ የምናቀርበው ምስጋናችን ላቅ ያለ ነው። በዚህ ቦታ ላይ በስም መጥቀስ ባያስፈልግም በዙሪያችን ባሉ ወዳጆቻችን በኩል የተደረገልን እርዳታም ቀላል አልነበረምና ጌታ ይባርካቹህ ለማለት እንወዳለን።

በቂ እንቅልፍ በመተኛትና በቂ የሆነ እርፍት በማግኘት ሂደት ውስጥ የሌሎችን እርዳታ ስንፈልግ አስፈላጊ የሆኑ ጥንቃቄዎች ማድረግም ተገቢ ነው። ምናልባት የሚረዳን አካል የቤተሰብ አባል ከሆነ መረዳዳት ወደ መጎዳዳት እንዳይለወጥና መልካም ግንኙነታችን እንዳይሻክር፣ ቤተሰብነቱን እንዳናጣው፣ ሸክሙ በዝቶባቸው እንዳይመረሩ፣ በውዴታ እንጂ ግዴታ የሌለባቸው ሰዎች እንደ ሆኑ ግንዛቤ ውስጥ መግባት ይኖርበታል። እኛም የሌሎች እርዳታ እንደሚያስፈልገን፣ እንደጠየቅንና እንደተረዳን ሁሉ እንዲሁ ለሌሎች በሚያስፈልጋቸው ጊዜ ለመርዳት መዘጋጀት ሰብዓዊ፣ ማሕበራዊና መንፈሳዊ ኃላፊነታችን ነው።

## 5. መዋጀት፡- አላስፈላጊና እንዲሁ የሚባክኑ ጊዜያቶችን መዋጀት

ሌላው በቂ እንቅልፍ ለማግኘት እንዲቻል ሊታሰብበት የሚገባ ጉዳይ አላስፈላጊ በሆኑ ሁኔታዎችና ድርጊቶች እንዲሁ የሚቃጠሉ ጊዜዎችን መዋጀትና መጠቀም የመቻል የመፍትሔ አሳብ ነው። እንዲሁ የተለያዩ የቴሌቪዝን ቻናሎችን በመቀያየር የሚቃጠሉ ጊዜያትን፣ በጣም ሳይታወቅ ጊዜ ጨራሹን የኢንተርኔት መርብንና ማሕበራዊ ድረ-ገጾችን በመጎብኘት የምናጠፋውንና የምንቆጭበትን ጊዜ መዋጀት ተገቢ ነው። ማሕበራዊ ድረ-ገጽ ስንል ለምሳሌ ፌስ ቡክ፣ የተለያዩ ድረ-ገጾችን መጎብኘት፣ መጻጻፍና በስልክና በቪዲዮ እየተያዩ በማውራት ጊዜ ማባከን ሌላው ሊታሰብበት የሚገባ ጉዳይ ነው። በጥንቃቄ እንድትረዱኝ የምፈልገው ነገር ቢኖር ማሕበራዊ ድረ-ገጾች አያስፈልጉም፣ ፈጽሞ ተጠቃሚ አይደለሁም፣ እኔም የዚህ ሰለባ አይደለሁም እያልኩ አይደለም፡፡ ነገር ግን መስተካከል ያለባቸው አጉል ልምዶቻችን እንዲስተካከሉ ሁላችንንም ማሳሰብ ዋናው ፍላጎቴ ነው።

ማሕበራዊ ድረ-ገጽን በአግባብ አለመጠቀም በቂ የሆነ እረፍት እንዳናገኝና ጊዜን በአግባብ እንዳንጠቀም ከማድረጉ ባሻገር የምንጎበኛቸው ድረ ገጾች ሁሉ ጤነኞችና





ጠቃሚዎች አይደሉምና ለሌላ አላስፈለጊ ለሆነ ችግር አሳልፈው ሊሰጡንም ይችላሉ። ማሕበራዊ ድረ-ገጾችን በመጎብኘት ሱሰኛ መሆን ለሌላ የአመጽ ሱስ አሳልፎ ሊያጋልጠንና የግል ሕይወታችንን፣ ትዳራችንንና ቤተሰባችንን ሊበትን የሚችል አደጋ ላይ ሊጥለን ይችላል።

## ለጥንዶች በግላቸውና በቡድን ለማጥናት የሚረዷቸው የውይይት ጥያቄዎች

## የምዕራፍ ሃያ አንድ (21)

## የውይይት ጥያቄዎች

1. የእንቅልፍንና በቂ እንቅልፍ የማግኘትን ምንነት መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት በማድረግ ተነጋገሩበት::
2. ለባለትዳሮች ልጆችን በማሳደግ ሂደት ውስጥ በቂ እንቅልፍ የማግኘትን አስፈላጊነት በመጥቀስ በሰፊው ተወያዩ::
3. በቂ እንቅልፍ ባለማግኘት ለአጭር ጊዜ በግለሰብና በባለትዳሮች መካከል የሚፈጥረው አሉታዊ ተጽዕኖ ምንድን ነው?
4. በቂ እንቅልፍ ባለማግኘት በረጅም ጊዜ በጥንዶች ሁለንተናዊ ማንነት ላይ ሊፈጠር የሚችለውን አሉታዊ ተጽዕኖ በመዘርዘር ተወያዩበት።
5. በቂ እንቅልፍ አግኝተን በማረፍ፣ የትዳርን ግንኙነት መጠበቅና ልጆችን በደስታ ማሳደግ እንድንችል ምን ማድረግ አለብን?
6. ጊዜያችንን በአግባቡ በመጠቀም ባገኘነው አጋጣሚ ማረፍ እንዳንችል የሚያደርጉን የተለያዩ ችግሮችን በመዘርዘር የመፍትሔ እርምጃ ለመውሰድ በማቀድ ተወያዩ።





# ክፍል አራት፡- እርቅ፣ የፍች ሂደትና ከፍች በኋላ አዲስ ቀጣይ ኑሮ

# ምዕራፍ ሃያ ሁለት(22)
# ፍችና የፍች ሂደት

## I. የፍች ምንነት

በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል የተዘጋጀው መዝገበ ቃላት ፍች ማለት "የትዳር ወይም የጋብቻ መፍረስ፣ መፋታት" መሆኑን ያመለክታል። ፍች ሕጋዊና ሙሉ በሙሉና ፈጽሞ ከጋብቻ ጥምረት መለያየትን ያጠቃለለ ትርጉም የያዘ ነው። ፍች በባለትዳሮች መካከል ከፍተኛ የሆነ ክፉ ተጽዕኖን የሚያመጣ ክስተት ነው።[83] የፍች አሉታዊ ተጽዕኖ በጥንዶቹ ላይ ብቻ ሳይሆን በልጆች፣ በቤተ ዘመዶች፣ በጓደኞች፣ በቤተ ክርስቲያንና በሥራ ባልደረቦች ላይ ጭምር ነው። ፍች በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠላ ነው። ፍች በእግዚአብሔር ብቻ ሳይሆን በግለሰቦችና በሕብረተሰቡ ዘንድም የተጠላ ድርጊት ነው። *"መፋታትን እጠላለሁ፥ ይላል የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር"* /**ሚል**2: 16/

## II. ፍች በመጽሐፍ ቅዱስ እይታ

### 1. በብሉይ ኪዳን /ዘዳ 24፡ 1-4/

ስለፍች **በዘዳ 24: 1-4** የሙሴ ሕግ አንድ ሰው ሴትን ወስዶ ቢያገባና የእፍረት ነገር ቢያገኝባት፣ በባሏ ዘንድ ሞገስ ባታገኝና ቢፈታት የፍችዋን ጽሕፈት በእጅዋ በመስጠት መስደድ እንደሚችል ይደነግጋል። ይህ መመሪያ ጋብቻ ሐይማኖታዊ ብቻ ሳይሆን ሕጋዊም እንደሆነ ግልጽ ያደርጋል። ሙሴ ይህን ሕግ የሰጠበት ምክንያት ከእስራኤል ሕዝብ የልብ ጥንካሬ የተነሳ እንጂ ከጥንት የእግዚአብሔር አሳብ ባሎች ሚስቶቻቸውን እንዲፈቱ ሳይሆን ባልና ሚስት ሳይለያዩ በቃል ኪዳን ለሁልጊዜ አብረው እንዲኖሩ ነው። *"እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየው። እርሱም፡- እንኪያስ ሙሴ የፍችዋን ጽሕፈት ሰጥተው እንዲፈቱአት ስለ ምን አዘዘ? አሉት። እርሱም፡- ሙሴስ ስለ ልባችሁ ጥንካሬ ሚስቶቻችሁን ትፈቱ ዘንድ ፈቀደላችሁ፤ ከጥንት ግን እንዲህ አልነበረም።"* /**ማቴ** 19: 6-7/

### 2. በኢየሱስ ክርስቶስ ዘመን

ፈርሳዊያን ወደ ኢየሱስ ቀርበው *"ሰው በሆነው ምክንያት ሚስቱን ሊፈታ ተፈቅዶለታልን?"* በማለት የፈተኑት የሙሴን ትእዛዝ መሠረት በማድረግ ነበር። የኢየሱስ ክርስቶስም ምላሽ፡- ከመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰውን ወንድና ሴት አድርጎ እንደፈጠረ፣ ሰው አባቱንና እናቱን በመተው ከሚስቱ ጋር እንደሚተባበር፣ ሁለቱም አንድ ስጋ እንደሆኑ፣ አንድ ስጋ እንጂ ወደ ፊት ሁለት እንዳይደሉ፣ እግዚአብሔር ያጣመረውን ሰው ሊለየው እንደማይችል፣ ሙሴም የፍችን ትዕዛዝ የሰጠው ስለልባቸው ጥንካሬ እንጂ ከጥንት

[83] የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል አማረኛ መዝገበ ቃላት፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡ አዲስ አበባ 1993 ዓ.ም ገጽ 593





የእግዚአብሔር አሳብ እንዲህ እንዳልነበረ በመግለጥና በማብራራት ስለጋብቻ ሲሚገትና ፍችን ሲቃወም እንመለከታለን /**ማቴ** 19፡ 1-12/።

ትዳርን በሚመለከት የእግዚአብሔር አሳብ የዕድሜ ልክ፣ እስከሞት የሚዘልቅና ሙሉ በሙሉ መሰጠትን የሚጠይቅ ቃል ኪዳናዊ ትሥሥር እንደሆነ ያስረዳናል። ፍች ከልብ ድንዳኔና ጥንካሬ የሚመነጭ የችግር ውጤት እንጂ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ከፍጥረታቸው ይኖሩበት ዘንድ ባሰበላቸው ፈቃዱ የተሰጠ ምርጫ አይደለም። ሙሴም ፍችን ያዘዘውና የፈቀደው ፍችን ለማስፋፋትና ለማበረታታት አልነበረም። *"እርሱም፡- ሙሴስ ስለ ልባችሁ ጥንካሬ ሚስቶቻችሁን ትፈቱ ዘንድ ፈቀደላችሁ፤ ከጥንት ግን እንዲህ አልነበረም።"* /**ማቴ** 19: 8-9/ ኢየሱስ ክርስቶስ በዝሙት ምክንያት ካልሆነ በስተቀር መፍታት እንደማይቻል ግልጥ መመሪያ ሰጥቷል፡፡ ይህም መመሪያ ተበዳይ ምህረት ማድረግ ካቃተውና አብሮ መኖር ከከበደው የሚፈጸም ነው እንጂ ይቅርታ በማድረግ ተማምነው ለመኖር ጥንዶቹ ከተስማሙ ፍች መፈጸም የለበትም።

### 3. በሐዋሪያው ጳውሎስ መልዕክቶች

ሐዋሪው ጳውሎስ ስለፍች ከገለጠባቸው ክፍሎች አንዱ የሚያምን ከማያምን ሰው ጋር እንዴት መኖር እንዳለበት በማስረዳት ለጥንቶቹ አማኞች ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት የተናገረበት ክፍል ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ኛ **ቆሮ 7፡ 15** *"የማያምን ግን ቢለይ ይለይ፤ ወንድም ቢሆን ወይም እኅት እንዲህ በሚመስል ነገር አይገዙም፤ እግዚአብሔር ግን በሰላም ጠርቶናል። አንቺ ሴት፥ ባልሽን ታድኚ እንደ ሆንሽ ምን ታውቂአለሽ? ወይስ አንተ ሰው፥ ሚስትህን ታድን እንደ ሆንህ ምን ታውቃለህ?"* በሚለው መመሪያው ግልጥ እንዳደረገው በምንም መንገድ አማኝ የሆነው አካል ትዳሩን ማፍረስ ወይም አማኝ ያልሆነውን የትዳር አጋር በራሱ ምርጫ ትቶ መሄድ የለበትም። የማያምነው አካል አቋምና ምርጫ መለየት ከሆነ ግን መለየት ይችላል። ጳውሎስ በጋብቻ ላይ ያለውን አቋም መፋታትን ለምርጫ እንዳያቀርቡና በልባቸውም እንዳይሹ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈውና መመሪያ በሰጠበት ደብዳቤው አስታውቋል። *"በሚስት ታስረህ እንደ ሆንህ መፋታትን አትሻ..."* /1ኛ**ቆሮ** 7፡ 27/

## III. ስለፍች የተለያዩ አመለካከቶች

### 1. ከስነ-መለኮታዊ እይታ አንጻር፡- ማቴ 19፡ 8

ከጥንት ጀምሮ በባለትዳሮች መካከል ከሚፈጠሩ የፍች ምክንያቶች አንዱ የጠነከረ ልብ እንደሆነ ከእግዚአብሔር ቃል ተመልክተናል። የፍችን ድርጊት በስነ-መለኮታዊ እይታ የሚደግፉ ሰዎች ከሰው ልብ ጥንካሬ አንጻር ፍች ሊፈቀድ የሚገባው መሆኑን ያመላክታሉ። ሰው በኃጢአት ከወደቀ በኋላ በየጊዜው ከፋት እየጨመረ እንደመጣ ከቃሉም ሆነ ከነባራዊ ዓለም ክስተቶች ማየት ይቻላል። ይህ የሰው ልብ ጥንካሬ *"የሰው ልብ ከሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ እጅግም ክፉ ነው ማንስ ያውቀዋል? እኔ እግዚአብሔር ለሰው ሁሉ እንደ መንገዱ፥ እንደ ሥራው ፍሬ እሰጥ ዘንድ ልብን እመረምራለሁ ኵላሊትንም እፈትናለሁ።"* /**ኤር** 17፡ 9-10፤ 2ኛጢሞ 3፡ 1-7/ በሚለው የእግዚአብሔር ቃል እንደተገለጠው በኃጢአት የተበከለው የአዳም ዘር ሁሉ ችግር ነው፡፡

## 2. ከማሕበራዊ እይታ አንጻር

ሌላው ከማሕበራዊ እይታ አንጻር በመመልከት ፍችን የሚጠይቁና የሚያበረታቱ ቡድኖች እዚህ ላይ ተጠቃሽ ናቸው። ይህ እይታ እንደ ፈረሳዊያን ዓይነት አመለካከት ያለው ማንም ሰው በራሱ እይታና የግል ችግር መነጽር መጽሐፍ ቅዱስን ሲተረጉምና ሊተገብር ሲፈልግ የሚፈጠር ነው። *"ሰው በሆነው ምክንያት ሁሉ ሚስቱን ሊፈታ ተፈቅዶለታልን? አሉት።"* /ማቴ 19፡ 3/ ከማሕበራዊ እይታ አንጻር ፍችን የሚመለከቱ ሰዎች፡ ፍችን በጥንዶች ደስተኛ መሆንና አለመሆን፣ በጥንዶቹ የግል አስተሳሰብና በመካከላቸው በሚፈጠሩ አለመግባባቶች፣ ግጭቶች፣ ውጥረቶችና ጦርነቶች ሊወሰን የሚችል እንደሆነ ያስባሉ።[84]

## 3. ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረቶች አንጻር

ፍች ከመጽሐፍ ቅዱስ አንጻር ሊፈጸም የሚችለው ከባለትዳሮች መካከል አንዱ አካል በዝሙት ኃጢአት ሲወድቅ ብቻ እንደሆነ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለፈርሳዊያን ከሰጠው *"እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን ፈትቶ ሌላዪቱን የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል፥ የተፈታችውንም የሚያገባ ያመነዝራል አላቸው።"* /ማቴ 19፡ 8-9/ ከሚለው ምላሽ መመልከት ይቻላል። በዝሙት ምክንያት መፍታት እንደሚችሉ በማሳየት ጥያቄያቸውን መመለስ ብቻ ሳይሆን የተፈታችውንም የሚያገባ እንደሚያመነዝር አያይዞ ግልጥ አድርጓል። ሌላውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምክንያት የማያምን የትዳር አጋር መለየት ቢፈለግ መለየት እንደሚችል ጳውሎስ የቆሮንጦስ ቤተ ክርስቲያን አማኞች ለጠየቁት ጥያቄ ምላሽ ሲሰጥ ግልጥ ማድረጉን መመልከት ይቻላል። *"... የማያምን ግን ቢለይ ይለይ፤..."* /1ኛ ቆሮ 7፡ 15/

# IV. የፍች ደረጃዎች

ባለትዳሮችን በትዳራቸው መካከል የሚፈጠሩ የተለያዩ ችግሮች፣ አለመግባባቶችና ግጭቶች ወደ በፍች ሲያደርሷቸው በተለያየ ጊዜ እንመለከታለን። የፍች ተግባርና ሂደት በሙሴ ዘመን የነበረ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ በአካለ ስጋ ባገለገለበት ዘመን የቀጠለና ከጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ተግዳሮቶች አንዱ በመሆን ተጠቃሽ ችግር ነው፡፡ አሁን ባለንበት ዘመን ደግሞ እጅግ እየበዛና እንደ ነውር መቆጠሩም እየቀረ መጥቷል። ፍች በየአካባቢው፣ በየቤተ ክርስቲያኑ፣ በየከተማው፣ በየአገሩና በዓለም አቀፍ ደረጃም ጎልቶ የሚታይና የሚደመጥ የቤተሰብ፣ የቤተ ክርስቲያን፣ የማሕበረሰብና የአገር ተግዳሮት ነው። ፍችን ሙሉ በሙሉ ማጥፋት ባይቻልም መቀነስ እንዲቻል ሁላችን የየበኩላችንን ድርሻ መወጣት ይኖርብናል። በፍች ሂደት ካለፉ ጥንዶች ምስክርነት፣

[84] Wright. H. Normal <u>Marriage Works</u> page 277-280





ከሰው ሁለንተናዊ ማንነት፣ ከጋብቻ ባሕርይና ከዓለም ነባራዊ ሁኔታ በመነሳት ፍች ራሳቸውን የቻሉ ሂደታዊ ደረጃዎች እንዳሉት በሚከተሉት ነጥቦች እንዳስሳለን፡-

## 1. ስነ ልቦናዊና ስሜታዊ የሆነ ፍች

በብዙ አለመግባባትና ግጭት ውስጥ የነበሩና ያሉ ጥንዶች ችግሮቻቸውን በጊዜው መፍታት ካልቻሉ በመካከላቸው በስሜት መራራቅ ይፈጠራል። በየጊዜው የሚፈጠረው ግጭት የጥንዶችን ስነ-ልቦና ስለሚጎዳ በስሜት ብዙ እርቀት ሊጓዙና ከፍተት ሊፈጥሩ ይችላሉ። ስሜቱ የተጎዳ ሰው ምሬት፣ ቁጣ፣ ፍርሃት፣ ተስፋ መቁረጥ፣ ሐዘን፣ ድፍረትና ነፃነት ማጣት፣ ድብርትና ጭንቀት ሊፈራረቅበት ይችላል። በዚህ ስሜት ውስጥ በሚያልፉበት ወቅት የነበራቸው የፍቅር ግንኙነት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽዕኖ ይፈጠርባቸዋል። ባል ከሚስት ሚስትም ከባሏ ጋር እንደ መልካሙ ጊዜያት መፈላለግ፣ መቀራረብና መተማመን እየጠፋባቸው ይመጣል።

በተለያዩ ጊዜያትና በተለያዩ የግጭት ምክንያቶች የተጎዳዱና ስነ-ልቦናዊ ጉዳት ውስጥ ያሉ ጥንዶች አብረው መቀመጥና ማውራት አለመቻል፣ በነጻነት የተሞላ የነበረው የተግባቦት ደረጃቸው እጅግ በጣም ዝቅተኛ እየሆነ መምጣት፣ አንዱ ሌላውን መረዳት አለመቻል፣ መረዳዳት መጥፋት፣ አንዱ በሌላው ላይ ማመካኘት፣ የግብረ ስጋ ግንኙነት የማድረግ ፍላጎት ማጣት፣ የግብረ ስጋ ግንኙነትን ፈጽሞ ማቋረጥና አልጋ መለየት የመሳሰሉ ችግሮች በሂደት ያጋጥሟቸዋል። ሂደቱ ባስከተለው ውጤት ምክንያት ጥንዶቹ በአንድ ቤት ውስጥ እየኖሩ ነገር ግን በስነ ልቦና የተፋቱና ስሜት ለስሜት እጅግ በጣም የተራራቁ ይሆናሉ።

አንዳንድ ባለትዳሮች ሕጋዊ ፍች ሊፈጽሙ በሂደት ላይ ናቸው ሲባል እጅግ በጣም እንደነግጣለን ነገር ግን እነዚህ ሰዎች በብዙ ነገር ስሜት ለስሜት በመጎዳዳት አብረው የሚኖሩ የሚመስሉ ነገር ግን በድብቅ ከተፋቱ የቆዩ ሊሆኑ ይችላሉ። የፍች ሂደት የሚጀምረው ለትዳር አጋር የነበረንና የሚፈልቅን የፍቅር ስሜት ከማጣት ነውና ይህ ዓይነት ስሜት የሚሰማቸው ባለትዳሮች ችግሩ ብዙ እርቆ ሊስተካከል ወደማይችልበት የሚቀጥለው ደረጃ ከመድረሱ በፊት እርምጃ በመውሰድ የሚከፈለውን ዋጋ ከፍለው ለመቀራረብና ፍቅራቸውን ለማደስ ጊዜ መውሰድ ይጠበቅባቸዋል። በዚህ ችግር ውስጥ ብዙ እርቀት የተጓዙትን ጥንዶች በምንረዳበት ወቅት በስሜቶቻቸው ምን ያክል እንደተራራቁ በመገንዘብ የእነርሱ መቀራረብ ጊዜ እንደሚወስድ ማስተዋል ይኖርብናል፡፡ ለየብቻና በጋራ በማነጋገር ቀስ በቀስ እርስ በርሳቸው በመቀራረብና በመፈላለግ በመካከላቸው መተማመን እንዲጎለብት ጥረት ማድረግም አስፈላጊ ነው።

## 2. ሕጋዊ ፍች

በስሜት ብዙ የተራራቁና በመካከላቸው መፈላለግና መተማመን የጠፋባቸው ባለትዳሮች መለያየታቸውን በሕግ ለመፈጸም እርምጃ መውሰድ ይጀምራሉ። *"የፍችዋን ጽሕፈት ጽፎ በእጅዋ ይሰጣት፥ ከቤቱም ይሰደዳት።"* /ዘዳ 24፡ 1/ እንደሚለው የሙሴ ሕግ ሕጋዊ

የፍች ሰርተፍኬት ለማግኘትም ይንቀሳቀሳሉ። አንዳንዶቹ እራሳቸው የሕግ ሂደቱን ሲፈጽሙ፣ ሌሎች ጠበቃ ወይም የሕግ አማካሪ በመቅጠር ሂደቱን እንዲከታተሉላቸው በማድረግ ሕጋዊ ፍችን ይፈጽማሉ። በአሜሪካ አገር ራሳቸውን የቻሉ የሕግ ባለሙያዎች በፍች ሂደት የሚያልፉ ጥንዶችን ጉዳዮች በማስፈጸም ፍቻቸውን ሙሉ በሙሉ ሕጋዊ ያደርጉታል። ፍችና የፍች ሂደት የሚያስከፍለው ዋጋም ከፍተኛ ነው።

ፍርድ ቤቶች ጉዳዩ እንደቀረበላቸው ፍችን ከማጽደቅ ይልቅ ጥንዶቹ ትዳራቸውን ለማዳን የሚችሉበት እድል ካለ እንዲያስቡበትና እንዲጠቀሙበት የተወሰነ የጊዜ ገደብ ይሰጧቸዋል፡፡ የተሰጠው የጊዜ ገደብ ከተጠናቀቀ በኋላም የጥንዶቹ አቋም ፍችን ለመፈጸም ባላቸው ፍላጎት ላይ ከጸና ሕጋዊ ፍች ይከናወናል፡፡ ለምሳሌ፡- የኢትዮጵያ መንግሥት ፍርድ ቤት የሚሰጠው ገደብ ከፍች በፊት ጥንዶች እንዲያስቡበት የሚሰጥ የጊዜ ገደብን የሚመለከተው የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 **አንቀጽ 78 ቁጥር 1፡** … "የመፋታት ጥያቄ ሲቀርብለት ፍርድ ቤቱ ባልና ሚስቱን በተናጠል ወይም በአንድ ላይ በማስቀረብ ስለ ጥያቄያቸው ያነጋግራቸዋል፡፡ እንዲሁም የመፋታት አሳባቸውን እንዲለውጡ ይጠይቃቸዋል፡፡" ይላል፡፡ **ቁጥር 2፡** ደግሞ "ባልና ሚስት የመፋታት አሳባቸውን የማይለውጡ መሆኑን የገለጹ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ እንደነገሩ ሁኔታ ከሶስት ወር የማይበልጥ የማሰላሰያ ጊዜ በመወሰን ሊያሰናብታቸው ይችላል፡፡" ብሎ ይደነግጋል፡፡ **አንቀጽ 82(2) ቁጥር 1፡** "በዚህ ሕግ አንቀጽ 81 መሠረት ጋብቻው በፍቺ እንዲፈርስ ጥያቄ ሲቀርብለት፡ ፍርድ ቤቱ ባልና ሚስቱን በተናጠልም ሆነ በአንድነት በማነጋገር የፍቺው ጥያቄ የሚቀርብበትንና አለመግባባቱን በስምምነት ለመፍታት የሚችሉበትን ሁኔታ ለመፍጠር እንዲችሉ ያግባባቸዋል፡፡" ሲል **ቁጥር 2** ደግሞ "ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው መሠረት ምክሮ ውጤት ያላገኘ እንደሆነ ባልና ሚስቱ ከፍርድ ቤት ውጭ ራሳቸው በሚመርጧቸው ሽማግሌዎች አማካይነት ጉዳያቸውን እንዲጨርሱ ሊጠይቃቸው ይችላል።" የሚል አሳብ ይሰጣል፡፡ **ቁጥር 3፡** "ባልና ሚስቱ ጉዳያቸውን በሽማግሌ አማካኝነት በዕርቅ ለመጨረስ ያልተስማሙ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ **ከሦስት ወር** ያልበለጠ የማሰላሰያ ጊዜ በመወሰን ሊያሰናብታቸው ይችላል።"[85] በማለት የህግ ስርዓቱ ፍችን የማያበረታታ መሆኑን ግልጽ ያደርጋል፡፡ በአሜሪካ አገር በካሊፎርንያ ግዛት ፍርድ ቤት የሚሰጠው የጊዜ ገደብ ለተጠቀሰው የፍች ሂደት ማሳያ ሊሆን ይችላል። በአሜሪካ የካሊፎርንያ ግዛት ፍርድ ቤት ፍችውን ሕጋዊ ከማድረጉ በፊት የስድስት ወር ጊዜ ይሰጣል።[86] ይህን

[85] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 78 ቁጥር 1, 2 አንቀጽ 82(2) ቁጥር 1-3 ገጽ 24 እና 26

[86] California Courts the jugdical branch of California Responding to Divorce or Separation divorce or Separation selfhelp. http://www.courts.ca.gov/1034.htm Accsesed Oct.10, 2014.





የሚያደርግበት ምክኒያትም ጥንዶቹ መታረቅ፣ መመለስና መስተካከል...የሚችሉበት ዕድል ካለ ጊዜ ለመስጠት ነው።

## 3. ንብረት ክፍፍል በማድረግ መፋታት

ባለትዳሮች በመካከላቸው በተፈጠረው አለመግባባትና ግጭት ምክንያት በስነ ልቦናና በሕግ ከጸደቀው ሕጋዊ ፍች በመቀጠል በጋራ ንብረታቸው ላይ አብረው ተጠቃሚ ከመሆን መፋታት ይጀምራሉ። አንዳንዶቹ ከመጋባታቸው በፊት የነበረ ንብረት ውል ውስጥ ባለማስገባት የተወሰነ ንብረት ካለ የግላቸው እንዲሆን አቋም ይይዛሉ፡፡ ከዚህ ውጭ የሆነውን በጋራ በመሆን ያፈሩትን ንብረት ግን በመከፋፈልና የውርስ መብትን በማስጠበቅ ይፋታሉ። በጣም የተጎዳ ስሜት ያላቸው ጥንዶች በንብረት ክፍፍል ወቅት ከቀድሞ የከፋ ስሜት ማለትም ቁጣ፣ በቀል፣ ጠብ፣ ድብድብ መፈለግና ከዚያም ባለፈ ለግድያ የመፈላለግ ስሜት ማንጸባረቅ ሊጀምሩ ይችላሉ። በዚህ ወቅት በትዳር አጋርነት አብረው መቆየታቸው፣ የቀድሞ መልካም ጊዜያቶች፣ በመካከል በጋራ የተፈጠሩ ልጆች አባትና እናት መሆን የመሳሰሉት መልካም ነገሮች ይረሱና ንብረት ላይ ብቻ ትኩረት የማድረግ ሁኔታ ይፈጠራል። ፍች በመፈጸም የእግዚአብሔርን ፈቃድ በሚቃረን የሕይወት እርምጃ ውስጥ ከመገኘትም ባሻገር የሚቻለውን ዋጋ በመክፈልና የክርስቲያናዊ ስነ ምግባርን ክቡርነት ዝቅ በሚያደርግ መንገድ በማንኛውም መሥዋዕትነት ያሉትን ንብረቶች በከፍተኛ ደረጃ የራስ ለማድረግ የሚኬደው ሌላው መንገድ ይበልጥ ጎጅና አሳፋሪ ነው።

## 4. በጋራ ልጆቻቸውን ከማሳደግ መፋታት

ጥንዶቹ በተለያዩ የፍች ደረጃዎች ውስጥ ካለፉ በኋላ የሚያጋጥማቸው ቀጣዩ የፍች ደረጃ ልጆቻቸውን በጋራ ሆነው ከማሳደግ መፋታት መጀመራቸው ነው። ምናልባት ልጆቻቸውን ለማሳደግ በየግል የራሳቸውን ጥረት ሊያደርጉ ይችላሉ። በውጬ ዓለም በፍርድ ቤት የፍች ሂደታቸውን ለመፈጸም እርምጃ ሲወስዱ አስቀድመው የሚታዩ ቅድመ ሁኔታዎች አሉ። ከቅድመ ሁኔታዎች መካከል ጥቂቶቹ፡- ለተወሰኑ ሰዓታት በፍች ውስጥ ሆነው እንዴት ልጆቻቸውን ማሳደግ እንደሚችሉ ትምህርት ይወስዳሉ፡፡ ልጆችን ለማሳደግ ማን የተሻለ የገንዘብ አቅም እንዳለው ይጠናል፡፡ ለልጆች እድገት ምቹ የሆነ ሁኔታ ያለው ወላጅ ልጆችን ለማሳደግ ተመራጭ ይሆናል፡፡ ለማሳደግ ይችላል ተብሎ የሚመረጠው ወላጅ ከሚለካባቸው መለኪያዎች አንዱ የጤና እንከን የሌለበት መሆኑን ማረጋገጥ ነው፡፡ በዚህ ሂደት ተመዝነው እናት የልጆች አሳዳጊ የመሆን ኃላፊነት ከተሰጣት አባት ለልጆች ማሳደጊያ የተወሰነ ገንዘብ እንዲረዳ በፍርድ ቤት ይወሰንበታል፡፡ የልጆች የወደፊት እጣ ፈንታ ከመወሰኑ በፊት ግን እነዚህን የመሳሰሉ ጉዳዮች በሚገባ እንዲታዩ ይደረጋል።[87]

[87] Wright. H. Normal Crisis Counseling

ኢትዮጵያ ሕግም በፍች ወቅት ስለልጆች ደህንነትና መብት በተመለከተ እንዲህ ሲል ይገልጻል፡- የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ **ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 113 ቁጥር 1፡** "ፍርድ ቤቱ ጋብቻው እንዲፈርስ ሲወስን ልጆች ከማን ጋር ሊኖሩ እንደሚገባ፡ ስለትምህርታቸው እና ስለጤናቸው አጠባበቅ፡ ስለቀለባቸውና በአጠቃላይም ስለአኗኗራቸው እንዲሁም ወላጆችና ልጆቻቸው ለመጠያየቅ ስላላቸው መብት መወሰን አለበት፡፡" **ቁጥር 2፡** "ፍርድ ቤቱ ከዚህ በላይ በተመለከተው ሁኔታ ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ፡ የወላጆችን የገቢ፡ የዕድሜ፡ የጤና እና የአኗኗር ሁኔታ እንዲሁም የልጆቹን ዕድሜ፡ ጥቅማቸውና ፍላጎታቸው የሚጠበቅበትን ሁኔታ ማገናዘብ ይኖርበታል፡፡" **ቁጥር 3፡** "ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ መሠረት ስለልጆች አያያዝና አጠባበቅ የሚሰጠው ውሳኔ የሁኔታዎች መለወጥን ምክንያት በማድረግ በሚቀርብ ጥያቄ ሊሻሻል ወይም ሊለወጥ ይችላል፡፡"[88]

ባለትዳሮች ልጆቻቸውን በጋራ ሁነው ከማሳደግ በሚፋቱበት ወቅት ልጆች ከአባት ወይም ከእናት ጋር እንደ ተለያዩ የሚሰማቸው፣ የሚያስቡበት፣ የሚጨነቁበትና የተለያዩ ጥያቄዎችን የሚጠይቁበት ወቅት ይመጣል፡፡ ወላጆች አንዳቸው በሌላው ላይ የሚያመካኙበት ሁኔታም ይፈጠራል፡፡ እንዲህ ዓይነት ችግር ካለ ደግሞ ልጆች ከቀድሞው የሚበዙ ሌሎች ጥያቄዎች በአእምሮአቸው ይፈጠሩባቸዋል፡፡ ይህ ወቅት ብዙ ክሶችን የሚያቀርቡበት፣ ብዙ ቁጣና መነጫነጭ የሚያሳዩበት፣ ድብርት ውስጥ ሊገቡ የሚችሉበት፣ በሁለንተናዊ ማንነታቸው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊፈጠርባቸው የሚችልበትና የማንነት ቀውስ ውስጥ የሚገቡበት ወቅት ነው። በልጆች መንፈሳዊ፣ ስነ ልቦናዊና አካላዊ ጤንነት ላይ ልዩ ልዩ ዓይነት ችግሮች ሊታዩ ይችላሉ። የትምህርት እንዲሁም ማሕበራዊና ስነልቦናዊ እክሎች ይገጥሟቸዋል፡፡[89] በፍች ውስጥ የሚያልፉ ጥንዶች ይህንን እውነታ በመረዳት የልጆቻቸውን ሁኔታ ሊያስቡ፣ ሊከታተሉ፣ ጥበቃና ጥንቃቄ ሊያደርጉላቸው ይገባል።

## 5. ከሕብረተሰቡ (ከማሕበራዊ ግንኙነት) መፋታት

በፍች ሂደት የሚያልፉ ጥንዶች ቀድመው ሲያደርጉትና ሲሆኑት የነበረ ማሕበራዊ ግንኙነትን በመቀነስ ራሳቸውን ከማሕበራዊ ቡድኖች ማግለል ከፍች በኋላ ሲውስዱት የሚታይ እርምጃ ነው፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ብቸኝነት ሊያጠቃቸው ይችላል። ለዚህ እርምጃቸው ምክንያቶቹ የተለያዩ ናቸው፡፡ በፍች ሂደት በሚያልፉበት ወቅት የተለያዩ ሃሜቶች፣ ወሬዎችና ትችቶች ሰለባዎች መሆናቸው ራሳቸውን ለማግለላቸው አንዱ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

---

[88] የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 113 ቁጥር 1. ገጽ 36-37

[89] Wright. H. Normal Crisis Counseling





ሌላው ምክንያታቸው ደግሞ በማሕበረሰቡ ዘንድ አስቀድሞ የነበራቸው ማሕበራዊ ስፍራ መቀየሩ ነው፡፡በፍች ሂደት ከማለፋቸው የተነሳ በማሕበረሰቡ ዘንድ ያገቡ መሆናቸው ይቀየርና ፈት በመባል መታወቅ ይጀምራሉ። ባለትዳር የሚለው ማሕበራዊ ስፍራቸው ተለውጦ ፈት ወይም ብቻቸውን ልጆቻቸውን የሚያሳድጉ ብቸኛ እናት ወይም አባት በመባል መጠራት ይጀመራሉ። እንደ የክርስቲያን ሕብረተሰቡ አውድ ከቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ዘርፍ መታገድ ያጋጥማቸዋል፡፡ ከሚሰማቸው የበደለኝነትና የውድቀት ስሜት የተነሳ እነርሱ ራሳቸውም ራሳቸውን ከእምነት ቤተሰቦቻቸው ማግለል ይጀምራሉ፡፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለባለትዳሮች ከሚዘጋጁ አስቀድሞ ይሳተፉባቸው ከነበሩ ፕሮግራሞችም ውጭ ይሆናሉ። ይህ ሁኔታ ባለትዳሮች ፍች ሲፈጽሙ የሚያልፉበት የፍች ሂደት አንድ ብቻ አለመሆኑን ያሳየናል፡፡ ከላይ እንደተገለጸው ከሚያልፉባቸው የፍች ደረጃዎች አንዱ ይህ ማሕበራዊ ፍች በመባል የሚጠቀሰው ፍች ነው፡፡

## 6. ከትዳር ጓደኛ ጋር ሁኖ ራስን ከማስተዳደር መፋታት

ጋብቻ አንድ ወንድና አንድ ሴት በፍቅርና በፍቃደኝነት በጋራ በመተሳሰብና በመረዳዳት አንድ አካል በመሆን የሚኖሩት ቃል ኪዳናዊ ትሥሥር ነው። ይህ ቃል ኪዳን በሚፈርስበት ወቅት ጥንዶቹ እንደ ቀድሞው በጋራ አንዱ ለሌላው ማሰብ፣ መልካሙን መመኘትና አብሮ መኖር ማቆም ይጀምራሉ። ፍች ሲፈጽሙ ባለትዳር በነበሩበት ጊዜ ሲኖሩበት የነበረው ከሌላ ሰው ጋር አብሮ መሆን፣ አብሮ ማሰብ፣ የጋራ አሳብ መያዝና ውሳኔ ላይ መድረስ ይቀራል። ፍች እንደ ጥንድ ሁለንተናዊ የሆነ የሌላው ሰው እገዛ እንዳይኖር ራስን ማውጣት የሚከሰትበትና ራስን በራስ ማስተዳደር የሚጀምሩበት እርምጃ ነው። ቀድሞ ላጤ እንደ ነበሩና ራሳቸውን በራሳቸው ሲያስተዳድሩ እንደነበር ሁሉ ብቻቸውን መቀጠል ይጀምራሉ። ላጤ ከነበሩበት የሕይወት ጉዞ ወጥተው ባገቡበት ወቅት "በአዲስ የጋራ አስተዳደር" ወደ መኖር የሕይወት መርህ ገብተው ነበር፡፡ አሁን ደግም በፍች ሂደት ሲያልፉ "ራስን በራስ ማስተዳደር" ወደ ሚል ራስ ገዝ ወደ ሆን የፍች የሕይወት ልምምድ ገብተዋል።

## V. በፍች ሂደት በሚያልፉ ጥንዶች ላይ ሌሎች ሰዎች ሊፈጠሩባቸው የሚችሉ የተለያዩ ስሜቶች

በፍች ሂደት በሚያልፉበት ወቅት የመጀመሪያዎቹ ተጎጅዎች ጥንዶቹ ናቸው፡፡ ነገር ግን ፍች የሚያስከትለው ቀውስና ጉዳት ሰለባዎች ከጥንዶቹ ባሻገር ልጆች፣ ቤተሰብ፣ ወዳጆች፣ ቤተ ክርስቲያን ብሎም ሌላው ሕብረተሰብና አገር በሙሉ ነው፡፡ ፍች በእነዚህ አካላት ሁሉ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ማምጣቱ አይቀሬና የአደባባይ ሚስጥር ነው። በተለያዩ ምክንያቶች በትዳር ውስጥ የነበሩ ጥንዶች መጋጨታቸው፣ መለያየታቸውና መፋታቸው በሚሰማበትና በሚታወቅበት ወቅት በሌሎች ሰዎች ላይ የሚፈጠሩ የተለያዩ ስሜቶች መኖራቸው አጠያያቂ አይደለም።

በፍች ሂደት በሚያልፉ ሰዎች ሁኔታ ምክንያት በሌሎች ሰዎች ላይ ሊፈጠር የሚችለው የተለያየ ስሜትና አስተያየት እንደ ሰው ማንነት፣ ብስለት፣ ባሕርይ፣ ቅርበትና እሴት ይለያያል እንጂ የሚያውቃቸውና የሚሰማ ሰው ሁሉ የሚያንጸባርቀው ስሜታዊ ምላሽ ይኖረዋል። ጥንዶቹ እነዚህን ስሜታዊና ማሕበራዊ ምላሾች በየቦታው በሚጋፈጡበት ጊዜ አስቀድሞ ከተጠቀሱት የተለያዩ ችግሮች በተጨማሪ የሚከተሉት ሌሎች ስሜታዊ ችግሮች ያጋጥሟቸዋል:: በፍች ሂደት የሚያልፉ ሰዎችን በተመለከተ ሌሎች ሰዎች ማለትም ቤተሰብ፣ የቅርብ ዘመዶችና ወዳጆች፣ ጎረቤቶች፣ የቤተ ክርስቲያን ሰዎች፣ የመሥሪያ ቤት ሰዎች... የተለያዩ ስሜቶችና አስተያየቶች ይኖሯቸዋል:: በዚህ ርዕስ ውስጥ ይህን ሁኔታ በመጠቀም በፍች ሂደት የሚያልፉ ሰዎች ሊያጋጥማቸው የሚችል ሌላ ተጨማሪ ጉዳት እንዳለ ለማሳሰብ፣ የተለያዩ ሁኔታዎች ሊፈጠሩ እንድሚችሉ እንዲጠብቁና ራሳቸውን እንዲያዘጋጁ ለማሳየት እፈልጋለሁ:: ችግር ውስጥ ያሉ ባለትዳሮችን ለመርዳት የምንቀሳቀስ አገልጋዮችም እነዚህን ሁሉ ከግምት ውስጥ በማስገባት ለመርዳት መዘጋጀት መቻል አለብን። ነገር ግን እርዳታችን በቋሚነትና በቀዳሚነት ትኩረት መስጠት ያለበት ፍችው ሊቀር የሚችልበትን መንገድ ለማግኘት ነው:: ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ የሚናገረው ፍች በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደ አለመሆኑን ነው /ሚልክ 2፥16/::

ችግር ውስጥ ያሉት ባልና ሚስትም በፍችው የሚቀጥሉ ከሆነ በራሳቸው ቤትና ሕይወት ላይ ብቻ ሳይሆን በቤተሰቦቻቸው ፣ በክርስቲያን ወገኖቻቸው ፣ በማሕበረሰብ ላይና በአጠቃላይ በአገር ላይ የሚስከትሉትን ፍርሰትና ቀውስ ሊረዱት ይገባል:: በሌሎች ላይ የሚያስከትሉት ቀውስ ደግሞ ተመልሶ በራሳቸው ላይ ከሚገምቱት በላይ የሆነ ሁለንተናዊ ቀውስ ያስከትልባቸዋል:: ከዚህ በመቀጠል በባለትዳሮቹ መካከል በተፈጠረው ችግር ላይ ሌሎች ሰዎች ያላቸው የተለያየ ስሜትና አስተያየት እንዲሁም ይህ ሁኔታ ችግር ውስጥ ባሉት ጥንዶች ላይ ሊያስከትል የሚችለውን አሉታዊ ተጽዕኖ ለመግለጽ እሞክራለሁ:-

## 1. ጭንቀትና ፍርሃት

አንዳንዶች በፍች ሂደት የሚያልፉ ሰዎች በሌሎች እንደ ሞዴል የሚታዩና በውጫዊ ማንነታቸው መልካም ምስክርነት ያላቸው ሊሆኑ ይችላሉ:: እንደዚህ ዓይነቶቹ ጥንዶች እነርሱ ይዋደዳሉ በማለት በትዳራቸው ምንም ሊፈጠር አይችልም ተብሎ የሚነገርላቸውና በቤተ ክርስቲያን መድረኮችና ለሕዝብ ተጋላጭ በሚያደርጉ አገልግሎት ዘርፎች ተሳታፊ በመሆን የሚታወቁ ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህና ሌሎች ምክንያቶች ተደማምረው በፍች ውስጥ የሚያልፉ ጥንዶችን ያስጨንቋቸዋል። ፍርሃትም ይፈጥሩባቸዋል። እነርሱ እንዲህ ከሆኑ፣ በእነርሱ ላይ እንዲህ ከተፈጠረ "በእኛስ"፣ "የእኛስ ምን ዋስትና አለን?"፣ "አገልጋዮች፣ መሪዎች ላይ እንዲህ ከሆነ የእኛማ ምን ሊሆን ይችላል?" በማለት ሰዎች ጥያቄ ውስጥ ሊገቡ እንደሚችሉ በማሰብ መጠየቅ፣





መጨነቅ፣ መፍራትና ተስፋ መቁረጥ ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ። ጥንዶቹ ይህን እውነታ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት መከፈል ያለበትን መሥዋዕትነት ከፍለው ትዳራቸውን ማዳንና መልካም ምስክርነታቸውን መጠበቅ ሊወጡት የሚገባ ኃላፊነታቸው ነው:: ሌሎቻችን ደግሞ ከሌሎች ሕይወት መማር እንጂ መፍራትና መጨነቅ አይገባንም። በፍች ሂደት ያለፉ ጥንዶችና የሌሎች ትዳር የተለያየ እንደሆነም ማሰብ ያስፈልገናል።

## 2. ኃፍረት

ምናልባት ጥንዶቹ ችግሮቻቸውን ለመፍታት መሞከር የሚችሏቸው አማራጮች እያሏቸውና ያንን ለማድረግ እውቀቱም እያላቸው ምንም ጥረት ሳያደርጉ ቀርተው ፍችን እንደ ብቸኛ አማራጭ አድርገው በመውሰድ ከተለያዩ በቅርበት ሁነን የምናውቃቸው ሰዎች የምንታዘባቸው መሆኑን ሲያውቁ ኃፍረት ይሰማቸዋል:: ባልተግባቡና በተጋጩ ወቅት ትዳራቸውን ለማዳን የቤተ ክርስቲያን መጋቢዎችን፣ ፕሮፌሽናል ክርስቲያን አማካሪዎችን፣ በቤተ ክርስቲያን የበሰሉ ሰዎችንና የወዳጆቻቸውን እርዳታ ያልጠየቁና ያልተጠቀሙ ከሆነ እነዚህን ሁሉ ሰዎች የማፈር ስሜት ይፈጠርባቸዋል። የፍች አሳብ፣ ድርጊትና ሂደቱ ሌሎችን ክርስቲያኖችና የቅርብ ሰዎችንም ሊያሳፍር ይችላል።

## 3. ከመጠን ባለፈ የአዕምሮ ጭንቀት መያዝ

በጥንዶች በተፈጠረው የፍች ችግር ምክንያት ሌሎች ሰዎች ከመጠን ያለፈ ወሬ በማውራት፣ ብዙ ጥያቄዎች በየጊዜው ደጋግሞ በመጠየቅ፣ ከትዳር ሕይወታቸው ባለፈ ጠልቆ ስለግል ጉዳዮቻቸው ለማወቅ ጥረት በማድረግ፣ ስለልጆቻቸው፣ ስለንብረታቸው፣ እንዴት እንደሚያደርጉ በማሰብ፣ ትክክል ባልሆነ አሳብና መንገድ ጣልቃ ለመግባት ጥረት የሚያደርጉ የሌሎች ሰዎች ተጽዕኖ በችግሩ ውስጥ ያሉትን ጥንዶች ከመጠን ባለፈ የአእምሮ ጭንቀት እንዲጠቁ ሊያደርጋቸው ይችላል። አንዳንድ ዓለማዊነት የሚያጠቃቸው ሰዎች ደግሞ አጋጣሚውን በሩካቤ ስጋ ፍላጎት ምኞት ውስጥ በመግባትና ከፍተኛ የሆነ ትኩረት በመስጠት የተመኙትን ለማግኘት ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ሊጠቀሙበት ያስባሉ:: ከጥንዶቹ ወደ አንዱ እንደ ወዳጅ ለመቅረብ ጥረት ማድረግ ሊጠናወታቸውም ይችላል።

## 4. በጥንዶች መፋታትና በሚያልፉበት ችግር መደሰት

በጥንዶች መፋታትና በሚያልፉበት ችግር መደሰት የሚፈልጉና መደሰት የሚጀምሩ ጤናማ መንፈስ የሌላቸው ሰዎችም አይጠፉም። እንደዚህ ዓይነት ስሜት የሚኖራቸው ሰዎች አስቀድመው ጥንዶች በአንድነት በነበሩበት ወቅት በነበራቸው ግንኙነት፣ ሕይወት፣ ገንዘብ፣ ንብረት፣ ንግድና ጥንዶቹ በነበራቸው ማሕበራዊ እንቅስቃሴ፣ ተቀባይነትና ችሎታ ሲቀኑ የነበሩ ሊሆኑ ይችላሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ በራሳቸው ሕይወት ደስታና ስኬት የሌላቸው ሊሆኑ ይችላሉ። ይህ ስሜት ሰው ሁሉ እንደ እነርሱ ከተቻለ ከእነርሱም በታች የሆነ ኑሮ እንዲኖር የሚፈልጉና በሰዎች ስኬት ደስ የማይላቸው ጤና የጎደላቸው ሰዎች የሚያንጸባርቁት ስሜት ነው።

## 5. በራስ የትዳር ሕይወት መታበይ (የበላይነት ስሜት መሰማት)

እነዚህ ሰዎች በፍች ሂደት የሚያልፉ ጥንዶች ያልተግባቡበትንና ለፍች ያበቃቸውን ምክንያት በማድመጥ፣ በፍች ሂደት የተከናወኑ የተለያዩ አስቸጋሪና አስከፊ ሁኔታዎችን በመመልከት ራሳቸውን በማሞገስ ስሜታቸውን የሚገልጡ ናቸው። እንዲህ ዓይነት ስሜት ያለን ሰዎች ከሆንን ትዳርን በየጊዜው በመገንባት ጤነኛ ግንኙነትና ደስተኛ የሆነ ጥንድ እንድንሆን እየተደረጉ ያሉ ጥረቶችን መጠበቅ፣ ከሌሎች በመማር ይበልጥ ትዳርን ለመገንባት መነሳሳት፣ የቆምነው በእግዚአብሔር ጸጋና ምህረት እንደሆነ ባለመዘንጋት ከመኩፈስ ይልቅ በትህትና ሌሎችን ለመርዳት መዘጋጀት አስፈላጊ ነው።

## 6. በድንጋጤና በመገረም መሞላት

ፍችው በአንዳንዶች ዘንድ ያላሰቡትና ያልጠበቁት ከመሆኑ የተነሳ በፍች ስለሚያልፉ ሰዎች ወሬ በሚሰሙበትና በሚያውቁበት ወቅት የመደንገጥና የመገረም ስሜት ሊሞላባቸው ይችላል። ከስተቱ ያልታሰበና ያልተጠበቀ ነገር ከሆነም ሊያስደነግጥና ሊያስፈራ ይችላል። እንደ ሰዎቹ ማንነት፣ ባሕርይና ስሜታዊነት ነገሮችን የሚይዙበት መንገድ ቢለያይም ከአሁን በፊት በጥንዶች የተጠቀሙና ቅርበት ያላቸው ሰዎች ከመሆናቸው የተነሳ በመጠኑም ቢሆን ስሜታቸው ሊጎዳና ሊያዝኑ ይችላሉ።

ከላይ የተዘረዘሩት የተለያዩ ስሜቶች ሊፈራረቁ እንደሚችሉ ለማሳየት እንጂ አንዱን ለመደገፍ ሌላውን ለማጣጣል አይደለም። በፍች ሂደት የሚያልፉ ሰዎች ከሚፈጠሩባቸው የተለያዩ ስነ ልቦናዊ፣ መንፈሳዊ፣ አካላዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ቀውሶችና አሉታዊ ተጽዕኖዎች በተጨማሪ በሌሎች ሰዎች ላይ በሚፈጠሩና በሚንጸባረቁ የተለያዩ ስሜቶች ምክንያት ይበልጥ ጉዳት ያጋጥማቸዋል:: ይህን በማስተዋል ከገቡበት ቀውስ ለመውጣት ተገቢውን ጥረት እንዲያደርጉ ችግር ውስጥ ያሉትን ጥንዶች መምከር የዚህ ርእስ አብይ ትኩረት ነው:: በዙሪያቸው ያለን ሰዎች በግል ስለእነርሱ የሚሰማንን ስሜት በመቆጣጠር ራሳችንን አላስፈላጊና ትክክለኛ ካልሆነ እርምጃ በመጠበቅ፣ የራሳችንን ትዳር መገንባት ላይ ትኩረት በማድረግ በፍች ሂደት የሚያልፉ ጥንዶችን በመረዳት ከተለያዩ ሕመማቸው ማገገም እንዲችሉና ከተቻለም ትዳራቸው ተመልሶ እንዲቃና ባላሰለሰ ትጋት እነርሱን ለመርዳት ጥረት እንድናደርግ መምከር ፍላጎቴ ነው።

# VI. ይቅርታና እርቅ

ግጭት ውስጥ ያሉና ወደ ፍች ያመሩ ጥንዶች በማንኛውም ደረጃ ላይ ይገኙ ከጥላቻና ከመራርነት ስሜት ወጥተው በሂደት ማሰብ ያለባቸው ይቅርታ የማድረግንና ይቅርታ የመቀበልን አስፈላጊነት ነው:: በጌታ ሆነን መኖርና ዘመናችንን መፈጸም አቋማችን ከሆነ እንደ እግዚብሔር ቃል መኖር የመጀመሪያው ኃላፊነታችን ነው:: ይህን በመገንዘብ ምንም እንኳን በተፈጠሩ ችግሮች ምክንያት የወሰድናቸው የተለያዩ እርምጃዎች ቢኖሩም እርምጃዎቻችንን በመመዘን ትዳራችንን በይቅርታና በእርቅ





ለማዳን ጥረት ማድረግ አለብን:: ይህን ለማድረግ ይቅርታን መስጠት የማይቻል ከባድ ነገር አድርገን ማሰብ የለብንም:: ስለይቅርታ ሲታሰብ ከባድ፣ አስቸጋሪና የማይቻል ተድርጎ መወሰዱ በትዳር መካከል በሚፈጠረው ግጭት የተለያዩ ጥንዶች ችግሮቻቸውን አስተካክለው በትዳር እንዲቀጥሉ የማስታረቁን ሂደት በማክበድ፣ ጊዜና ኃይል ጨራሽ ያደርገዋል።

ይቅርታ ለክርስቲያኖች የየዕለቱ ተግባርና ልምምድ ሊሆን የሚገባው መንፈሳዊ መርህ ነው። የይቅርታ ሞዴላችን ራሱ እግዚአብሔር እንደ ሆነ በቃሉ ያረጋግጥልናል። *"ለሰዎች ኃጢአታቸውን ይቅር ብትሉ፥ የሰማዩ አባታችሁ እናንተን ደግሞ ይቅር ይላችኋልና፤ ለሰዎች ግን ኃጢአታቸውን ይቅር ባትሉ፥ አባታችሁም ኃጢአታችሁን ይቅር አይላችሁም።"* /ማቴ 6:14-15/ ይቅርታ ሁሉም አማኝ ሊሳተፍበት የሚገባ የክርስትና ልምምድ ነው። በየጊዜው ይቅርታን የማንለማመድ ከሆነ ለመራርነት አልፈን እንሰጣለን። ይቅር ማድረግ ባለመቻላችን የመራርነት ፍሬን ማፍራት ብቻ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙነታችን ይቋረጣል። ይቅርታ ለማድረግ ይቅርታ ማለት ምን ማለት እንደሆነና ምን ማለት እንዳልሆነ መረዳት ይጠበቅብናል:: የሚከተሉት ነጥቦች ይህን መረዳት ለመፍጠር እገዛ ያደርግልናል::

## 1. ይቅርታ

### 1) ይቅርታ የሚመስል ነገር ግን ያልሆነ

**የመጀመሪያው** ይቅርታ የሚመስለን ነገር ግን እውነተኛ ይቅርታ ያልሆነው ጉዳይ ስሜታዊነት ነው:: ይቅርታ ስሜት ብቻ አይደለም። ይቅርታ አልተሰማኝም የምንለው ልምምድም አይደለም:: ይቅርታ ማድረግና መቀበል የሆነ ስሜት እስኪሰማን ድረስ የምንጠብቀው ጉዳይ ሳይሆን ከስሜታችን ባለፈ በቋሚነት ልንኖርበት የሚገባን የክርስትና መርህ ነው:: የእግዚአብሔር ልጅ የመሆን ስጦታን የተቀበልነውና ክርስቲያንነትን ያገኘንበት ብቸኛው መንገድም ይቅርታ እንደሆነ ሳናመቻምች መቀበል አለብን።

ሌላውና **ሁለተኛው** ጉዳይ ይቅርታ ማለት እንዳልተጎዱ አድርጎ ማስመሰል አይደለም። በጥንዶች መካከል በሚፈጠረው አለመግባባትና ግጭት የመጀመሪያዎች ተጎጅዎች ጥንዶቹ ራሳቸው ናቸው። ግጭቱ የፈጠረው ስነ ልቦናዊ፣ መንፈሳዊ፣ ስሜታዊና አካላዊ ጉዳት እያለ እንዳልተጎዱ አድረጎ ማስመስልና ማለፍ ተገቢ አይደለም። ሁልጊዜ በማስመሰል እንዳልተጎዱ አድረጎ መቁጠርና ማለፍ አንድ ቀን ጉዳቱ ተጠራቅሞ እንዲፈነዳና ምን ነካቸው፣ በዚህ ዓይነት መንገድ አላውቃቸውም ነበር እስከንባል ድረስ ሰዎችን ሊያስደነግጥ የሚችል ችግር ውስጥ እንድንገባ ያደርገናል። በማስመሰልና በመሆን መካከል ከፍተኛ የሆነ ልዩነት አለና!! ስለዚህ ከጉዳት ለመፈወስ ደግሞ መጎዳትን መረዳትና ይቅርታን መቀበል አስፈላጊ ነው:: ይቅርታ የተሟላ የሚሆነው ይቅር በማለት ብቻ ሳይሆን ይቅርታን በመቀበልም ጭምር ነው::

ሶስተኛ ይቅርታ ማለት የሌላውን አካል ትክክል ያልሆነ ድርጊት አለመግለጥ ማለት አይደለም። አንዳንዶች ጥንዶች ችግሮችን በመደፋፈን የሚያምኑ ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ በግልጥነት በመነጋገርና በመተማመን የሚያምኑ ናቸው። አንዳንዶች እያንዳንዱን ጉዳይ የሚያካብዱ ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ ሁሉንም ነገር የሚያቃልሉ ሊሆኑ ይችላሉ። ምንጊዜም አንድ ጽንፍ መያዝና መለማመድ ራሱን የቻለ ችግር አለው። እንደ ችግሩ ዓይነት፣ ሁኔታ፣ ያሉበትን የጊዜና የቦታ ሁኔታ፣ የሚያመጣውን አሉታዊ ተጽዕኖና ችግሩ የተፈጠረበትን ምክንያት ማጤንና ግልጥ ማድረግ አስፈላጊ ነው። በአጠቃላይ ግን ድርጊቱ ትክክል እንዳልሆነ፣ ብሎም ከእግዚአብሔር ቃል የወጣና አመጽ የሆነ ድርጊትና መንገድ እንደሆነ እያወቁ ዝም ማለት የእውነተኛ ይቅርታ መገለጫ አይደለም።

**የመጨረሻው** ይቅርታ መስሎ የሚታየን ነገር ግን ይቅርታ ያልሆነው ጉዳይ፤ ይቅርታ ማለት የሌላውን አካል ኃላፊነት ቀለል አድርጎ ማየት (መተው) እንደሆነ አድርጎ መውሰድ ነው። ብዙ ጊዜ በጥንዶች መካከል የሚፈጠረው አለመግባባትና ግጭት በጊዜው በመካረር በይቅርታ እንዳይስተካከል የሚያደርገው ስለይቅርታ ያለን የተዛባ አስተሳሰብ ነው። በጥፋት ውስጥ የተገኘውን ሰው ጥፋተኝነቱን ቀለል አድርጎ ማየትና መተው ሳይሆን አምኖ እንዲቀበል መርዳትና ሌላ ጊዜ እንዳይፈጽመው ማሳመን በጣም አስፈላጊ ነው። ይህም በትህትና፣ በትዕግስት፣ በመግባባት እና በፍቅር ብቻ ሊደረግ ይገባል።

**2) እውነተኛ ይቅርታ**

**አንደኛ፡-** እውነተኛ ይቅርታ እያንዳንዱ ባለትዳር ነፃ በሆነ ፈቃድ የሚመርጠው ትክክለኛ የሕይወት ምርጫ መሆን አለበት። *"አቤቱ፥ ኃጢአትንስ ብትጠባበቅ፥ አቤቱ፥ ማን ይቆማል? ይቅርታ ከአንተ ዘንድ ነውና። አቤቱ፥ ስለ ስምህ ተስፋ አደረግሁህ ነፍሴ በሕግህ ታገሠች።"* /መዝ 130፡ 4-5/ ይቅርታ መቀበልና መስጠትን በየጊዜው መርጠን የምንለማመደው ለክርስትና ሕይወትና ቀጣይነት ላለው መልካም ግንኙነት ከፍተኛ ሚና የሚጫወት መርህ ነው። እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል ሰውን ለማዳን በሰጠው ይቅርታ ለመኖር ፈቅደው ምርጫ ያደረጉ ሰዎች በትዳራቸው የሚፈጠረውን ግጭት ለመፍታት ይቅርታን የመስጠት ምርጫ ለማድረግ ሊቸገሩ አይገባም።

**ሁለተኛ፡-** ትክክለኛ ይቅርታ ውሳኔ ነው። ይቅርታን መርጦ በይቅርታ ለመኖር ውሳኔ በጣም አስፈላጊ ነው። *"በእርሱ ላይ ምንም እንኳ ያመፅን ብንሆን፥ በባሪያዎቹም በነቢያት እጅ በፊታችን ባኖረው በሕጉ እንሄድ ዘንድ የአምላካችንን የእግዚአብሔርን ቃል ምንም እንኳ ባንሰማ፥ ለጌታ ለአምላካችን ምሕረትና ይቅርታ ነው።"* /ዳን 9፡ 9/ ይቅርታን ለመምረጥ ውሳኔ የመወሰን መሠረታችን የእግዚአብሔር ቃል ነው። ይቅርታ ተደርጎልን የዳንበትን ምህረት በማሰብና የትዳር ጓደኞቻችን በእግዚአብሔር መልክና አምሳል የተፈጠሩ ሰዎችና የትዳር አጋሮቻችን መሆናቸውን በመረዳት ትክክለኛ የይቅርታ የውሳኔ እርምጃ መውሰድ ተገቢ ነው።





**ሶስተኛ፡-** ይቅርታ መስጠትና መቀበል ልንታዘዘው የሚገባ የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ነው፡ የእግዚአብሔር ፈቃድ የሆነውን ይቅርታን መለማመድ እግዚአብሔርን መታዘዝ ነው። *"ለጸሎትም በቆማችሁ ጊዜ፥ በሰማያት ያለው አባታችሁ ደግሞ ኃጢአታችሁን ይቅር እንዲላችሁ፥ በማንም ላይ አንዳች ቢኖርባችሁ ይቅር በሉት።"* /ማር 11፡ 25/ ንጉስ ዳዊትም ከራሱ ሕይወት ልምምድ በመነሳት እንዲህ ይላል፡- *"በልቤስ በደልን አይቼ ብሆን ጌታ አይሰማኝም ነበር።"* /መዝ 66፡18/። ለእግዚአብሔር ያለን ፍቅር የሚለካው ለቃሉ ባለን መሰጠትና መታዘዝ ነው። *"ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ።"* /ዮሐ 14፡ 15/

**አራተኛ፡-** ይቅርታ የአንድ ጊዜና የአንድ ሰሞን ክንውን አለመሆኑ ነው። ይቅርታ እንደ ሁኔታውና እንደ ደረጃው በየጊዜው የሚሆን ሂደት ነው። የእግዚአብሔር ቃል **በማቴ 18፡ 21-22** እንዲህ ይላል፡- *"በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ ወደ እርሱ ቀርቦ። ጌታ ሆይ፥ ወንድሜ ቢበድለኝ ስንት ጊዜ ልተውለት? እስከ ሰባት ጊዜን? አለው። ኢየሱስ እንዲህ አለው፡- እስከ ሰባ ጊዜ ሰባት እንጂ እስከ ሰባት ጊዜ አልልህም።"* በየጊዜው ይቅርታ ስጠይቅ ባለቤቴ "ከእኛ ቤት ይቅርታ በቤቱና በየግድግዳው ላይ ተለጥፎ ነው ያለው" ትላለች። ጋብቻ ሁለት ፍጹም ያልሆኑ ሰዎች አብረው የሚኖሩበት ተቋም በመሆኑ በየጊዜው ግጭት አይቀሬ ነው። በየጊዜው በሚፈጠረው አለመግባባትና ግጭት "አጥፍቻለሁ"፣ "ተሳስቻለሁ"ና "ይህ የእኔ ጥፋት ነው" በሚሉ መግለጫዎች በእውነተኛነት ጥፋትን አምኖ መቀበልና ይቅርታ መስጠት ግንኙነታችንን ነጻና ዘላቂ እንዲሆን ያደርጋል።

**አምስተኛ፡-** እውነተኛ ይቅርታ ትክክለኛ ላልሆነውና ጥፋት ለተሞላው አስተሳሰባችንና ድርጊታችን ኃላፊነትን መውሰድ ነው። አንድ አሳብና ሰላም ያለን እንድንሆን የበኩላችንን ድረሻ በማሳየት ከዚያም አንድ እንዳንሆን የሚያደርጉንን ክፉ ሃሳቦችንና ድርጊቶችን በማስወገድ ኃላፊነታችንን መወጣታችንን ያሳያል። *"እርስ በርሳችሁ በአንድ አሳብ ተስማሙ፤ የትዕቢትን ነገር አታስቡ፥ ነገር ግን የትሕትናን ነገር ለመሥራት ትጉ። ልባሞች የሆናችሁ አይምሰላችሁ። ለማንም ስለ ክፉ ፈንታ ክፉን አትመልሱ፤ በሰው ሁሉ ፊት መልካም የሆነውን አስቡ።ቢቻላችሁስ በእናንተ በኩል ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ። ተወዳጆች ሆይ፥ ራሳችሁ አትበቀሉ፥ ለቍጣው ፈንታ ስጡ እንጂ፤ በቀል የእኔ ነው፥ እኔ ብድራቱን እመልሳለሁ ይላል ጌታ ተብሎ ተጽፎአልና። ጠላትህ ግን ቢራብ አብላው፤ ቢጠማ አጠጣው፤ ይህን በማድረግህ በራሱ ላይ የእሳት ፍም ትከምራለህና። ክፉውን በመልካም አሸንፍ እንጂ በክፉ አትሸነፍ።"* /ሮሜ 12፡ 16-21/

**ስድስተኛ፡-** ይቅርታ ማድረግና መቀበል ሁልጊዜ ለማይገባው ሰው የሚሰጥ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሆኖ የይቅርታ ምልጃ ያደረገላቸው ሰዎች እነማን እንደሆኑ ስንመለከት ወንበዴ የነበሩ ሰዎች፣ የሰቀሉት ሰዎችና እያንዳንዳችን ኃጢአተኞች መሆናችንን እናስተውላለን። እነዚህ ሰዎች ሁሉ ይቅርታ እንዲያገኙ የማይገባቸው ናቸው። *"ቀራንዮም ወደሚባል ስፍራ በደረሱ ጊዜ፥ በዚያ እርሱን ከፉ አድራጊዎቹንም አንዱን በቀኝ ሁለተኛውንም በግራ ሰቀሉ። ኢየሱስም፡- አባት ሆይ፥ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው አለ። ልብሱንም ተካፍለው ዕጣ ተጣጣሉበት።"* /ሉቃ 23፡ 33-34/

**ሰባተኛ፡-** ይቅርታና መታረቅ ወይም እርቅ በማድረግ አብሮ ለመኖር መስማማት የተለያዩ ነገሮች ናቸው። ሁለት የተጋጩ ሰዎች ይቅርታ መባባል በፈቃደኝነት ላይ

የተመሠረተ ክርስቲያናዊ ግዴታ ሲሆን ነገር ግን ይቅርታ የተባባሉት ሰዎች አብረው ለመሆን ላይታረቁ ይችላሉ። በእርግጥ በእውነተኛ እርቅ አብሮ በመኖር ለመቀጠል ይቅርታ ሊቀድም ይገባል። የሚታረቁ ሁሉ ይቅርታ ሊጠያየቁ ይገባል፤ ይቅርታ የተጠያየቁ ሁሉ ግን አብረው ለመሆን ላይታረቁ ይችላሉ። *"እንግዲያስ ሰላም የሚቆምበትን እርስ በርሳችንም የምንታነጽበትን እንከተል።"* /ሮሜ 14፡ 19/ *"በውኑ ሁለት ሰዎች ሳይስማሙ በአንድነት ይሄዳሉን?"* አሞ. 3፡3[90] ክርስቲያን ባለትዳሮች እንደ ክርስቲያንነታቸው ይቅርታ መስጠትና መቀበል፣ እርቅን መፈጸምና በአንድነት በመተሳሰብ ለመኖር ዓላማ ማድረግ አስፈላጊ ብሎም ክርስቲያናዊ ልምምዳችን ሊሆን ይገባል።

## 2. እርቅ (መታረቅ)፡- መዝ 51፡ 10፤ 2ኛቆሮ 5፡ 17-19

### 1. የእርቅ ደረጃዎች

#### 1) ወዳጅነትን ለማደስ የሚደረግ ጥረት

እርቅ ሲታሰብ የተለያዩ ደረጃዎች እንዳሉት መገንዘብ ያስፈልጋል። የእርቅ የመጀመሪያ ደረጃ ወዳጅነትን ለማደስ የሚደረግ ጥረት ሂደት ነው። *"ስለዚህም ምክንያት ትጋትን ሁሉ እያሳያችሁ በእምነታችሁ በጎነትን ጨምሩ፥ በበጎነትም እውቀትን፥ በእውቀትም ራስን መግዛት፥ ራስንም በመግዛት መጽናትን፥ በመጽናትም እግዚአብሔርን መምሰል፥እግዚአብሔርንም በመምሰል የወንድማማችን መዋደድ፥ በወንድማማችም መዋደድ ፍቅርን ጨምሩ።"* /2ኛጴጥ 1፡ 5-8/ ይህ ሂደት የውስጥ የልባችንን፣ ስሜታችንን፣ ፍላጎታችንንና ድካማችንን አምነን ልናካፍላቸው በምንችልበት ደረጃ ወዳጅነታችን ማደስ ስንችል የሚያሳይ ነው።

#### 2) የፍቅር ግንኙነትን ማደስ

ሌላው የእርቅ ደረጃ የፍቅር ግንኙነትን ለማደስ የሚደረግ የእርቅ ሂደት ነው። ይህ ሂደት በተለያየ ጊዜ ባጋጠመ ችግርና አለመግባባት የተጎዳ የፍቅር ግንኙነት መታደስ እንዲችል[9]" የሚረዳ ሂደት ነው። እጅግ በጣም የተራራቀ ስሜት፣ የሻከረ ግንኙነትና የተቆረጠ የግንኙነት መስመር ያላቸው ወዳጆች የፍቅር ግንኙነታቸው እንዲታደስ እድል የሚሰጥ ሂደትም ነው። *"ፍቅር ይታገሣል፥ ቸርነትንም ያደርጋል፤ ፍቅር አይቀናም፤ ፍቅር አይመካም፥ አይታበይም፤ የማይገባውን አያደርግም፥ የራሱንም አይፈልግም፥ አይበሳጭም፥ በደልን አይቆጥርም፤ ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ ዓመፃ ደስ አይለውም፤ ሁሉን ይታገሣል፥ ሁሉን ያምናል፥ ሁሉን ተስፋ ያደርጋል፥ በሁሉ ይጸናል።"* /1ኛቆሮ 13፡ 4-7/





#### 3) የትዳርን ግንኙነት ማደስ

የመጨረሻው ደረጃ የትዳርን ሕይወት ለማደስ የሚደረግ የእርቅ ደረጃ ነው። በባለትዳሮች መካከል በሚፈጠር አለመግባባትና ግጭት ብሎም በፍች ሂደት ያለፉ ጥንዶችን ለማስታረቅ የእርቅ ደረጃዎችን መረዳት በሂደት ጥንዶችን ለመርዳት ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው። የወዳጅነት ደረጃው ከፍ እንዲል፣ የፍቅር ግንኙነት እየጨመረ እንዲመጣና ትዳራቸው እንዲታደስ ለእርቅ በተዘጋጀ ስሜት፣ በትዕግስትና በማስተዋል ሂደቱን ማስኬድና መከታተል ተገቢ ነው።

## VII. በባለትዳሮች መካከል እርቅ ያስፈለገበት ምክንያት

ባለመግባባት፣ በግጭት፣ በመለያየትና በፍች ሂደት ያሉ ባለትዳሮች በየጊዜው ይቅርታን መለማመድና እርቅን መፈጸም ሊለማመዱት የሚገባ የክርስትና መርህ ነው። መታረቅ አስፈላጊ መሆኑን መረዳትና ሁልጊዜም ቢሆን ለእርቅ መዘጋጀት አስፈላጊ ነው። በተለይ በትዳር ሕይወት እርቅ አስፈላጊ የሆነበትን ምክንያት መረዳት ለእርቅ የማነሳሳትና የማዘጋጀት አቅም አለው።

### 1. ፍች የእግዚአብሔር ፈቃድ ባለመሆኑ

ፍች የእግዚአብሔር ፈቃድ አለመሆኑና ክርስቲያን ባለትዳሮች ፍችን በመተው በእርቅ አብረው ወደ መኖር የመምጣታቸው ጉዳይ አምላካዊ መርህ ነው። እርቅ ለክርስቲያን ባለትዳሮች አምላካዊ መርህ መሆኑ የእርቅን አስፈላጊነት ዋናና የመጀመሪያ የሚያደርገው ጉዳይ ነው። በግጭትና በመለያየት ላይ ያሉ ባለትዳሮች የእግዚአብሔርን ቃል በግላቸው ብሎም ከሌሎች በተለያዩ መንገዶች በመስማት፣ በመጸጸት፣ በመመለስና ለቃሉ ምላሽ በመስጠት ለእርቅ ሊነሳሱና እርምጃ ሊወስዱ ይገባል።

በፍች ሂደት ያለፉ ባለትዳሮች እርቅን ሊሹና እርምጃ ሊወስዱ የሚገባበት ምክንያት እግዚአብሔር ስለሚፈልገው ነው። እግዚአብሔር እርቅን ከመፈለጉ የተነሳ ሰዎችን በአንድ ልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ከራሱ ጋር አስታረቀን። *"ነገር ግን የሆነው ሁሉ፥ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስታረቀን የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን፥ ከእግዚአብሔር ነው፤ እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና፥ በደላቸውን አይቆጥርባቸውም ነበር፤ በእኛም የማስታረቅ ቃል አኖረ።እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማልድ ስለ ክርስቶስ መልክተኞች ነን፤ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለ ክርስቶስ እንለምናለን።"* /2ኛቆሮ 5፡ 18-20/

እግዚአብሔር አስቀድሞ ከራሱ ጋር አስታረቀን ደግሞም የእርቅ ተነሳሽነትን፣ መንገድንና መርህን ሰጠን። እርቅ የእግዚአብሔር ፈቃድና ፍላጎት በመሆኑ ጥንዶቹ እግዚአብሔርን ከመፍራትና ከመታዘዝ የተነሳ እርቅን ሊፈልጉ ይገባል። አንዳንዶቹ እግዚአብሔርን መፍራትና መውደድ የጠፋባቸው በመሆኑና ለቃሉና ለጽድቅ ያላቸው ስፍራ በመቀነሱ ለፍች ሊፈጥኑና የሚወስዱት እርምጃ ምንም ላይመስላቸው ይችላል። ከተወሰኑ ወራትና አመታት በኋላ መንፈሳዊ ሕይወታቸው መታደስ፣ ለቃሉና ለጽድቅ መታዘዝ ሲጀምሩ በመጸጸት በንስሃና በእርቅ ትዳራቸውን ሊፈልጉ ይችላሉ። እግዚአብሔር መፋታን ይጠላልና /ሚል 2፡ 16/!

## 2. በጋራ መልካምና አስቸጋሪ ጊዜያቶችን አብረው ስላሳለፉ

ጥንዶቹ በትዳር ባሳለፉባቸው አመታት በጋራ ያሳለፉት መልካምና አስቸጋሪ ጊዜያቶችን ነው። በትዳር ሕይወት ስንኖር እጅግ በጣም መልካም የደስታ፣ የሰላም፣ የስኬት፣ የጤንነት፣ የማግኘት፣ የጭዋታና የማይረሱ የፍቅር ቀናት እንኖራለን:: በዚያው ልክ ደግሞ ትዳር አስቸጋሪ የሆኑ የመከራ፣ የሐዘን፣ የግጭት፣ የማጣትና የሕመም ጊዜያቶች የሚፈራረቁበት ተቋም መሆኑ እውነት ነው። ለእርቅ እነዚያን መልካም ቀናትና የተለያዩ መጥፎ ስሜቶች እንዲፈራረቁ ያደረጉ አስቸጋሪ ጊዜያትን ማሰብ መልካም ነው። ባልተስማሙ ወቅት እንዳለ የነበሩትን መልካም ቀናት መርሳትና የትዳር አጋር ያደረገውን መልካም አሳብና ተግባር ፈጽሞ አለማስታወስ እርቅን ይበልጥ እንዲጠላ ያደርገዋል:: ከእርቅ መሸሽንም ያበረታታል። ስለዚህ ይህን በመገንዘብ አስበንበት በትዳር ውስጥ ያሳለፍናቸውን መልካም ቀናቶች ማስታወስና መንከባከብ እውነተኛ እርቅ እንድናደርግ ስለሚረዳን በጣም አስፈላጊ ነው:: ይህንን ማድረጋችን ጠቃሚ የሆነውም:-

### 1) አሉታዊ ጭንቀትን ስለሚቀንስ

ባለመግባባት፣ በግጭትና በመለያየት ላይ ያሉ ባለትዳሮች በተቻለ መጠን እርቅን ሊፈልጉና ሊያስቡ ይገባቸዋል። ግጭት፣ መለያየትና ፍች የሚፈጥሩት አሉታዊ ተጽዕኖ ቀላል አይደለም። አሉታዊ ተጽዕኖውም ጥንዶች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነት እንዲቋረጥ፣ በስነ ልቦናዊ ጉዳት በጭንቀት ውስጥ እንዲሆኑ፣ ለፍርሃት፣ ለሐዘንና ለድብርት ተጋላጭ እንዲሆኑ ያደርጋል። እርቅን ማሰብና መፈለግ ብሎም መታረቅ በጥንዶቹ ላይ የሚፈጠረውን ይህን መሰል አሉታዊ ጭንቀት ይቀንሳል።

### 2) ልጆች የወላጆቻቸውን መታረቅ ስለሚፈልጉ

ጥንዶች የፈራረሰውን የትዳር ግንኙነታቸውን በመታረቅ የማደስ ፍላጎት ሊያጡ ይችላሉ። እርቅን ጥንዶች ባይፈልጉትም ከሁለቱ የተገኙ ልጆች የወላጆቻቸውን አንድነት ሊናፍቁ ይችላሉ። በልጆች ጣልቃ ገብነት የታረቁ ባለትዳሮች ብዙ ናቸው። አንዳንዶች በልጆቻቸው ላይ በተፈጠሩ የተለያዩ ጉዳቶች፣ ልጆች በየጊዜው በሚያነሷቸው ጥያቄዎች፣ ልጆች የእርቅን መልካም አሳብ በማፍለቅ፣ የሁለቱንም ስሜት በማየትና ተለያይተው የሚተሳሰቡ መሆናቸውን በመረዳት፣ በመካከል በመሆን በስልክ እንዲያወሩ በማድረግ፣ በአንዳንድ የደስታና የሐዘን ጊዜ በማገናኘትና ሌሎች ሰዎችና ሽማግሌዎችን በመጋበዝ እንዲታረቁ አድርገዋልና ለእርቅ እንዲበቁም ያደርጋሉ።

### 3) ኢኮኖሚያዊ አቅም ለማግኘት

የባለትዳሮች መለያየትና ፍች ከሚያመጣው አሉታዊ ተጽዕኖ አንዱ የኢኮኖሚያዊ አቅምን ማዳከሙ ነው። አንደኛው የትዳር አጋር ኢኮኖሚያዊ ጥገኛ ሊሆን ይችላል። በዚህ ወቅት ይህን ችግር ለማስወገድ እንደ ገና ሳይፈልጉ እርቅን እንዲፈልጉ





ሊያደረጋቸው ይችላል። አንዳንድ ባለትዳሮችን በማማከርበት ወቅት አንደኛው አካል በተለይ ሚስቶች "ልጆቼን የማሳድግበት የገንዘብ አቅም ስለሌለኝ እንጂ..."፣ "ትቶ እንዳልወጣ በምን እተዳደራለሁ?"፣ "ስራ ስለሌለኝ እንጂ..." "ተበድረው የተማሩበትን፣ ቤትና መኪና የገዙበትን ዕዳ የምከፍለው ስለሌለኝ እንጂ?!"፣ "በቅርቡ ከሥራ ስለተቀነስኩና ሥራ ብፈልግ ላገኝ ስላልቻልኩ እንጂ.." ሲሉ ይደመጣሉ:: ከእነዚህም አሳቦች የምንረዳው ሳይፈልጉ በትዳር የሚቆዩና የገንዘብ አቅም እስኪያገኙ የሚጠባበቁ መኖራቸው የማይደበቅ ሀቅ መሆኑን ነው።

በፍች ላይ ያሉ አንዳንድ ባለትዳሮችን ታሪክ ስንመረምር አንደኛው አካል በተፈጠረበት የገንዘብ ችግር ምክንያት የኢኮኖሚ አቅም ለመገንባት እንደ ገና የእርቅ እርምጃ ለመውሰድ ሲፈልግ ልናገኘው እንችላለን ማለት ነው። ይህ ማለት ምክንያቱ ትክክለኛና ክርስቲያናዊ ተግባር ነው ማለት አይደለም። ካለው ነባራዊ ሁኔታ አንዳንድ ጥንዶች ለገንዘብ ብቻ ተጋብተው ንብረት ተካፍለው ለመውጣት እንደሚያስቡ ሁሉ የኢኮኖሚ አቅማቸው አናሳ ከመሆኑ የተነሳ ራሳቸውን አስጨንቀው፣ በግብዝነትና ሁኔታዎች ተለውጠው ምቹ አጋጣሚዎች እስኪያገኙ እንደሚጠብቁ ለማሳየት ነው።

አንዳንዶች በዚህ የጊዜ ገደብ አስተሳሰባቸው፣ ስሜታቸው፣ ልባቸው፣ የትዳር ግንኙነታቸው በሂደት ከኑሮ በመማር፣ በቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች፣ በሚመክሩ ሰዎችና በወዳጅ ብሎም አንዳንዶች በልጆቻቸው ምክንያት እውነተኛና ልባዊ የሆነ እርቅ ሲያደርጉና ከበፊቱ በተሻለ መልካምና ጤነኛ የሆነ ግንኙነት ሲኖራቸው ይታያሉ፣ ሲመሰክሩም ይደመጣሉ። ሌሎች ባለትዳሮች ደግሞ ለተወሰነ ጊዜ፣ በዓላማና ራሳቸውን በማስጨነቅ ደስተኛ ባልሆነ ግንኙነትና ስሜታዊ በሆነ መለያየት ተፋትተው ማውራትና መነጋገር አቁመው፣ አልጋና የምኝታ ክፍል ቀይረው በልጆቻቸው መካከለኝነት የሚኖሩ ጥቂቶች አይደሉም።

### 4) በተመሳሳይ የጋራ ሰዎች ስለሚሳቡ

ባለትዳሮች በአንድነት በነበሩበት ወቅት የነበሯቸው የጋራ ቤተሰቦች፣ ወዳጆች፣ ጓደኞች አገልጋዮችና የሥራ ባልደረቦች አሏቸው። ቀድሞ በጋራ ጠንካራ በሆነ ግንኙነት የፈጠሩትንና የጠበቁትን ቤተሰብነት፣ ወዳጅነትና ጓደኝነት በፍች ወቅትም ፍጹም ሙሉ በሙሉ ማቋረጥ ሊቸገሩ ይችላሉ። በፍች ውስጥ ያለፉ ጥንዶች በእነዚህ  የጋራ በሆኑ ሰዎች ምክንያት በጋራ የመገናኘትና የማውራት እድል ሊያገኙ ይችላሉ። በየጊዜው በተመሳሳይ ሰዎች ምክንያት የሚፈጠረው ግንኙነት ለእርቅ ሊያነሳሳና እድል ሊሰጥ ይችላል። የጋራና ተመሳሳይ በሆኑ ወዳጆች ልመናና ማነጋገር አንዱ አካል ለሰዎች ስሜቱን ገልጦ በማካፈሉና እርዳታ በማግኘቱ አጋጣሚዎችን እየፈጠሩ እንደገና እንዲገናኙ በማድረግ ለእርቅ ሊያነሳሱአቸው ይችላሉ።

**5) በወቅቱ የነበረው መለያየትና የፍች ሂደቱ የፈጠነ ሲሆን**

አለመግባባትና ግጭት በጥንዶች መካከል መፈጠሩ አይቀሬ መሆኑ ይታወቃል። አንዳንዶች በትዳራቸው መካከል ለተፈጠረው ችግር መፍትሔ ለማግኘትና የትዳራቸውን ግንኙነት ለመገንባት የወሰዱት የግልና የጋራ ጥረት ባለመኖሩ ምክንያት ብቻ ፍች ሊፈጸም ይችላል። ከመለያየትና ወደ ፍች እርምጃ ከመሄዳቸው በፊት የተወሰደ እርምጃ ባለመኖሩ ምክንያትም እንደ ገና ውሳኔያቸውን በመመልከትና በመመዘን የተለያዩት ጥንዶች እርቅን ሊፈልጉ ይችላሉ። ፍች ራሱን የቻሉ ደረጃዎች አሉት። ጥንዶች በመካከላቸው በተፈጠረው ግጭት በመደናገጥ፣ እንዴት አድረገው መቆጣጠር እንዳለባቸው ባለማወቅና ጊዜያዊ የሆነ ቁጣና ትክክል ያልሆነ ውሳኔ ወደ ፍች አድርሷቸው ሊሆን ይችላል። ይህንን ሲረዱ ጉዳያቸውን በእርጋታ በማየትና ይቅርታ በመጠያየቅ እርቅ የሚፈጽሙ ጥንዶች አሉ፡፡

**6) ሕይወትን ለማረጋጋት**

እርቅ በፍች ምክንያት በባለትዳሮች፣ በቤተሰብ፣ በወዳጅና በዘመድ መካከል የሚፈጠር የተወሳሰበ ችግርን የመፍታትና የማረጋጋት አቅም አለው። የፍች ሂደት በሰው ሁለንተናዊ ማንነት ላይ የሚያመጣው አሉታዊ ተጽዕኖ በቀላል የሚታይ አይደለም። በፍች ሂደት የሚያልፉ ሰዎች የሚያጋጥማቸው አንዱ ችግር የተረጋጋ ሕይወት ሊኖራቸው አለመቻሉ ነው። በአእምሯቸው በሚፈጠር የተለያየ የማያረጋጋ አሳብ፣ ከሌላው የትዳር አጋር በኩል በሚሰነዘር አፍራሽ የሆነ ቃልና ተግባር፣ በሌሎች ሰዎች አስተያየትና የፍርድ ቃል፣ በፍች ችግር ውስጥ ባሉ ጥንዶች ላይ በተፈጠረ የኑሮ ጫና፣ የጤንነት መታወክ እና የሥነ ልቦናና የማንነት ቀውስን ለማረጋጋት ጥንዶቹ እርቅ ሊፈልጉ ይችላል።

## VIII. እውነተኛ እርቅ የሚጠይቀው

### 1. የሁለት ሰዎችን ስምምነት

እርቅ የሚፈጠረው ሁለትና ከዚያም በላይ በሆኑ ሰዎች መካከል ነው። ሁለት ሰዎች በተለያዩ ምክንያቶች ላይግባቡና ሊጋጩ ይችላሉ። በሁለታቸው መካከል የነበረው ወዳጅነት ወደ ጠላትነት ሊለወጥ ይችላል። *"ሁለት ሰዎችም ቢጣሉ፥..."* /ዘጸ 21፡ 18/ በሁለቱ ሰዎች ወይም ባለትዳሮች መካከል የተፈጠረውን አለመግባባት በማስወገድ ግንኙነታቸው እንዲታደስ፣ እርቅና ሰላም እንዲፈጠር ይደረጋል። ይህ እንዲከናወን ግን የሁለቱ ሰዎች ስምምነት የግድ አስፈላጊ ነው *"በውኑ ሁለት ሰዎች ሳይስማሙ በአንድነት ይሄዳሉን?"* /አሞጽ 3፡ 3/፡፡

### 2. ያለፉትን ችግሮችና የግል ስህተቶች እውነተኛ በሆነ መንገድ መገምገምን

ባለትዳሮች እንዳይግባቡ፣ እንዲጋጩና እንዲለያዩ ያደረጋቸውን መሠረታዊ ችግር ለይተው ማወቅ ይጠበቅባቸዋል። ያለፈውን የግልና የጋራ የግጭት ምክንያቶችን ለይቶ





ለማወቅና እርቅ ለመፍጠር ፈቃደኛ መሆን የእርቅ ሂደት እንዲቀጥል ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። ለዛሬው መለያየት ጠንቅ የሆነውን ችግር መለየት እርቅ ለመፍጠር ብቻ ሳይሆን በቀጣይ የጋራ ኑሮ የትዳር ሕይወት የከፋና አስቸጋሪ ወደ ሆነ ቀውስ እንዳይገባ ይረዳል። ውጤታማ በሆነ መንገድ እርቅን ለማከናወን የጥንዶች የየግላቸውን ችግር፣ ጉድለት፣ ጥፋትና ስህተት አምነው ለመቀበልና ኃላፊነትን ለመውሰድ ዝግጁ መሆን አለባቸው። ለብዙ ጊዜ ያጋጫቸውንና ያለያያቸውን ችግር በጥሩ ልብ፣ በቀና መንፈስና በእውነተኛ መንገድ በማንሳት ለችግሩ መፈጠርና ማደግ የየግል አስተዋጽዖ ማየትና መገምገም ከቻሉ ጥንዶቹ ከቀውስ መውጣት የሚችሉበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል ማለት ይቻላል። እውነተኛ ችግሩ ያልታወቀለት ጉዳይ መፍትሔ ሊገኝለት አይችልምና።

### 3. የሁለትዮሽ ንስሃንና ይቅርታን

እርቅ የጥንዶችን የሁለትዮሽ እውነተኛ ንስሃና ይቅርታ ይጠይቃል። ለግጭትና ለመለያየት ምክንያት የሆነው ችግር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሁለቱ የጥንዶች አስተዋጾ እንዳለው አምኖ መቀበል ያስፈልጋል። እውነተኛ ንስሃ ጥፋትን ከመረዳትና ከመጸጸት ይጀምራል *"እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ኀዘን ጸጸት የሌለበትን፥ ወደ መዳንም የሚያደርሰውን ንስሐ ያደርጋልና፤ የዓለም ኀዘን ግን ሞትን ያመጣል።"* /2ኛቆሮ 7፡ 10/፡፡ ጥፋትን መሰወር ሳይሆን መረዳት፣ መናዘዝና መተው ከእግዚአብሔር ዘንድም ሆነ ከሌላ ሰው ምህረት የማግኘት መርህ ነው *"ኃጢአቱን የሚሰውር አይለማም የሚናዘዝባትና የሚተዋት ግን ምሕረትን ያገኛል።"* /ምሳ 28፡ 13/፡፡ እውነተኛ እርቅ ከእውነተኛ ንስሃና ይቅርታ ይጀምራል *"ክፉ ሰው መንገዱን በደለኛም አሳቡን ይተው ወደ እግዚአብሔርም ይመለስ እርሱም ይምረዋል፥ ይቅርታውም ብዙ ነውና ወደ አምላካችን ይመለስ።"* /ኢሳ 55፡ 7/።

### 4. እመኔታን እንደ ገና መገንባት የሚያስከፍለውን መስዋዕትነት መክፈልን

ብዙ ጊዜ የቆየ አለመግባባት፣ ግጭትና መለያየት በሂደት የጥንዶችን ግንኙነት ማሻከሩ፣ ግንኙነታቸው እንዲቋረጥ ማድረጉና በመካከላቸው ያለውን መተማመንን ማፈራረሱ የማይቀር ነው። አንድን ነገር ለማፍረስና ለመገንባት የሚወስደው ጊዜና ጉልበት የተለያየ መሆኑ ደግሞ የታወቀ ነው። አንድ ሕንጻ ለመገንባት የሚፈጀው ጊዜ፣ ጉልበትና ገንዘብ ለማፍረስ ከሚፈጀው ጊዜ ጋር ፈጽሞ የማይቀራረብ ነው። በቀላሉ የፈረሰን ሕንጻ መልሶ ለመገንባት ከመጀመሪያው ወይም ከዚያም የበለጠ ጊዜና ዋጋ ሊጠይቅ ይችላል። በተደጋጋሚ የተጎዳው የጥንዶች ግንኙነትም አንዱ ሌላውን በማመን መልሶ ለመገንባት እንዲቻል የሚፈጀው ጊዜ፣ አቅምና ሂደት ቀላል ሊሆን ስለማይችል ከፍተኛ ትዕግስት ይጠይቃል።

ጥንዶቹ አንዱ ሌላውን እንዲያምነው በቃላት ከመግለጽ ባሻገር በኑሮ፣ በተግባርና ጊዜ በመስጠት ተአማኒነት እንዲፈጠርና እንዲገነባ ዕድል መስጠት ይጠበቅባቸዋል። ጥንዶችን ለማስታረቅ መሐከለኛ የሚሆኑ ሰዎች፣ አገልጋዮችና አማካሪዎችም እርቅ

አድረገው አብረው የመቀጠል ሂደት ጊዜ ወሳጅ መሆኑን በመረዳት እርስ በርስ አመኔታ እንዲያሳድጉ ዕድል መስጠትና መከታተል ያስፈልጋቸዋል።

# IX. ለእውነተኛ እርቅ መዘጋጀት

## 1. ለጽድቅና ለቃሉ ስልጣን ራስን ከመስጠት ይጀምራል

በግጭትና በፍች ሂደት ውስጥ ያሉ ባለትዳሮች የእርቅ አሳብና ሂደት ለጽድቅና ለሰላም ራሳቸውን ከመስጠት እንደሚጀምር በመረዳት መዘጋጀት ይኖርባቸዋል። ከአመጽ ጋር ላለመተባበርና ለትክክለኛ ፍትሕና ጽድቅ ለመኖር በቁርጠኝነት በመነሳት መስጠታቸውን ሊያሳዩ ይገባል። *"በቀረውስ፥ ወንድሞች ሆይ፥ እውነተኛ የሆነውን ነገር ሁሉ፥ ጭምትነት ያለበትን ነገር ሁሉ፥ ጽድቅ የሆነውን ነገር ሁሉ፥ ንጹሕ የሆነውን ነገር ሁሉ፥ ፍቅር ያለበትን ነገር ሁሉ፥ መልካም ወሬ ያለበትን ነገር ሁሉ፥ በጎነት ቢሆን ምስጋናም ቢሆን፥ እነዚህን አስቡ፤..."* **/ፊል 4፡ 8/**

የክርስትና ኑሮ መርህ፣ የየዕለት እንቅስቃሴ፣ ምርጫና ውሳኔ የሚመዘነው የጥንዶች የትዳር ሕይወት መመሪያ ሊሆን በሚገባው በእግዚአብሔር ቃል ነው። የቃሉ የበላይነት የማይታይበትና የማይረጋገጥበት ግንኙነትም ሆነ የክርስትና ኑሮ ዘለቄታው አስተማማኝ ሊሆን አይችልም። ባልና ሚስት በእግዚአብሔር ቃል የበላይነት፣ ዳኝነትና መመሪያነት የጋራ ስምምነት ላይ ሊደርሱና ራሳቸውን ሊሰጡ ይገባል። የእግዚአብሔርን ቃል በራሳቸው ፍላጎት መተርጎምና የእነርሱን ድካም እንዲደግፍ ጥረት ማድረጉን ትተው መከሮ መመለስ ለሚችለው ቅዱስ ቃል ሁለንተናቸውን በማስገዛት በታዛዥነት ለመኖር መፍቀድ አቋማቸው ሊሆን ይገባል። *"ስለዚህ ይህን ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው ሁሉ ቤቱን በዓለት ላይ የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል። ዝናብም ወረደ ጎርፍም መጣ ነፋስም ነፈሰ ያንም ቤት ገፋው፥ በዓለት ላይም ስለ ተመሠረተ አልወደቀም።"* **/ማቴ 7፡ 24-25/**

በእርቅ ሂደት ውስጥ እንደ እግዚአብሔር ቃል ለማስታረቅ በጥንዶቹ መካከል የሚቆሙ ሰዎች ሊኖሩ የግድ ነው። ብዙ ጊዜ ለማስታረቅ በጥንዶች በራሳቸው ተነሳሽነት ጣልቃ ሊገቡ የሚችሉ ሰዎች፡- የቤተ ክርስቲያን አማካሪዎች፣ ሽማግሌዎች፣ መጋቢዎች፣ የበሰሉና ልምዱ ያላቸው ሰዎች፣ ወዳጆችና ቤተ-ዘመዶች ሊሆኑ ይችላሉ። በተቻለ መጠን ያለአድሎ የጥንዶችን እርቅ ሂደት ለማከናወን ልዩ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። ጥንዶቹም በሚችሉት ሁሉ ለእግዚአብሔር ቃል፣ ለቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ለአገሩ ሕግ በየደረጃውና እንደ ሁኔታው ለመታዘዝ ራሳቸውን መስጠታቸው አስፈላጊ ነው። *"ለገዦችና ለባለ ሥልጣኖች የሚገዙና የሚታዘዙ፥ ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጁ፥ ማንንም የማይሰድቡ፥ የማይከራከሩ፥ ገሮች፥ ለሰው ሁሉ የዋህነትን ሁሉ የሚያሳዩ እንዲሆኑ አሳስባቸው።"* **/ቲቶ 3፡ 1-2/**

## 2. ከልብ የሆነ ይቅርታን ይጠይቃል

ጥንዶች እርቅ ከእውነተኛ ይቅርታ እንደሚጀምር መረዳትና የመጀመሪያውን እርምጃ ከልብ መፈጸማቸውን በማረጋገጥ ለሚቀጥለው እርምጃ መዘጋጀት ይኖርባቸዋል። እርስ በርስ ይቅር አለመባባል እርቅ እንዳይሳካና እንደ ተፈለገው





እንዳይቀጥል ያደርገዋል። እርቅ እውነተኛ የሆነ መናዘዝን፣ ንስሃንና ራስንና የትዳር አጋርን ከልብ ይቅር ማለትን ይፈልጋል። በተቻለ መጠን የሚከፈለውን ዋጋ ከፍሎ ለእርቅ ለመዘጋጀት እንዲቻል ጥንዶቹም ሆኑ በመካከል የሚገቡ ሰዎች እርቅን ሊያበረታቱ ይገባል። *"ወንድምህም ቢበድልህ፥ ሄደህ አንተና እርሱ ብቻችሁን ሆናችሁ ውቀሰው። ቢሰማህ፥ ወንድምህን ገንዘብ አደረግኸው፤ ባይሰማህ ግን፥ በሁለት ወይም በሦስት ምስክር አፍ ነገር ሁሉ እንዲጸና፥ ዳግመኛ አንድ ወይም ሁለት ከአንተ ጋር ውሰድ፤ እነርሱንም ባይሰማ፥ ለቤተ ክርስቲያን ንገራት፤ ደግሞም ቤተ ክርስቲያንን ባይሰማት፥ እንደ አረመኔና እንደ ቀራጭ ይሁንልህ።"* **/ማቴ 18፡ 15-17/**

ጥንዶች ሊያስቡት የሚገባ ጉዳይ ቢኖር ለፍች አለመፍጠን አስፈላጊ መሆኑን ነው። ማፍረስ በማንኛውም ጊዜና ሰዓት ሊፈጽሙት የሚችሉት ምርጫና ውሳኔ ነውና! እንደ እግዚአብሔር ቃል ለመኖር ከእግዚአብሔር ባሕርይ ሊማሩት የሚገባ ጉዳይ እግዚአብሔር መሓሪ፣ ይቅር ባይ፣ ለቁጣና ለቅጣት የዘገየ አምላክ መሆኑን ነው። *"እግዚአብሔር መሓሪና ይቅር ባይ ነው፥ ከቍጣ የራቀ ምሕረቱም የበዛ። ሁልጊዜም አይቀሥፍም፥ ለዘላለምም አይቈጣም።"* **/መዝ 103፡ 8-9/።**

## 3. በጥበብና በማስተዋል ማደግን ይጠይቃል

የእርቅ ሂደቱ በየጊዜው መልካም የሆነ እድገት እንዲያሳይና ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲጠናቀቅ ጥበብ አስፈላጊ ነው። *"መለየትን የሚወድድ ምኞቱን ይከተላል፥ መልካሙንም ጥበብ ሁሉ ይቃወማል።"* **/ምሳሌ 18፡ 1/** ጥንዶች በመታረቅ ሂደት በየጊዜው በአቀራረብ፣ በንግግርና የችግሮችን መፍትሔ ለማፈላለግ በሚደረገው እንቅስቃሴ ውስጥ ከባለፈው ድካም፣ ከሌሎች ሰዎች ምስክርነት፣ በማንበብና መልካም ምሳሌነት ካላቸው ጥንዶች በመስማት ጥበብን የራስ ገንዘብ በማድረግ ብልህነት መሻሻል አለባቸው። ግዴሌሽ በመሆን ወደ እርቅ የሚያደርሱ መንገዶችን ላለመዘጋት ጥበበኛ መሆን ጥቅም እንጂ ምንም ጉዳት የለውም። *"ጥበብ ከቀይ ዕንቍ ትበልጣለችና የከበረ ነገር ሁሉ አይተካከላትም።"* **/ምሳሌ 8፡ 11/**

ጥንዶችን ለማስታረቅ በምንቀርብበት ወቅት አቀራረብ ማለትም አለባበስ፣ የድምጽና የሰውነት እንቅስቃሴ ከጅምሩ የእርቁ ሂደት እንዲቀጥል ወይም እንዲያቆም አስተዋጽዖ ሊያደርጉ ይችላሉ። በእርቅ ሂደቶች የማዳመጥ ክህሎት፣ የምንጠቀምባቸው ቃላት፣ የአነጋገር ዘይቤ፣ ነገሮችን ለማረጋገጥ የምንጠቀባቸው ዘዴዎች፣ በሚታረቁ ሰዎች ስሜት ውስጥ ሁኖ መስማትና መናገር በየጊዜው እያደጉ ሊመጡ የሚገባቸው ክህሎቶች ናቸው። ጥበብ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚሰጥ ነውና ወደ እግዚአብሔር በጸሎትና በልመና መቅረብና ጥበብን ማግኘትም ተገቢ ነው። *"ከእናንተ ግን ማንም ጥበብ ቢጎድለው፥ ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን፥ ለእርሱም ይሰጠዋል"* **/ያዕ 1፡ 5/** የነገው የእርቅ ስምምነትና ሂደት በዛሬውና በየጊዜው በሚደረገው የእርቅ እንቅስቃሴ ይወሰናልና እያንዳንዷን ጊዜ በጥበብ መልካም መሠረት ጥሎ ለማለፍ የአላዋቂነትን ስንፍና በማስወገድ ጥረት ማድረግ አስፈላጊ ነው። *"ሰነፍ የጥበብን ነገር አይወድድም በልቡ ያለውን ሁሉ መግለጥ ብቻ ይወድዳል እንጂ።"* **/ምሳሌ 18፡ 2/**

ከእርቅ በኋላ ጥንዶች አብረው በጋራ ለመኖር እንዲችሉና የተራራቀው ስሜታቸው እንዲቀራረብ የሚገናኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት አለባቸው፡፡ አብረው መቀመጥ፣ ማውራትና አብረው ማደር እንዲችሉና ግንኙነታቸው ታድሶ እንዲቀጥል በማስታረቅ ሂደት ተሳታፊ የሆኑ ሰዎችም እድል ሊሰጧቸው እንጂ ሊያሰቸኩሏቸው አይገባም። ይህ ማለት ግን የቅርብ ክትትል፣ በየጊዜው ያለውን እድገት መቃኘትና አንዳንድ ኃላፊነት በመስጠት መርዳት የለብንም ማለት አይደለም። አብረው መኖር እንዲጀምሩ በሌሎች ሰዎች ግፊት የተደረገባቸው ጥንዶች ለሁለተኛ ጊዜ ሲለያዩ የሚያጋጥማቸው ችግር ከቀድሞው በበለጠ የከፋ ሊሆንና ግጭቱን በእርቅ ለማስተካከል ጥረት የሚያደርጉ አስታራቂ ሰዎች ተስፋ እንዲቆርጡ ሊያደርግ ይችላል። ከማንም ሰው በላይ በመለያየት ላይ ያሉ ጥንዶች /ባለጉዳዮች/ ፍችው እያመጣ ያለውን አሉታዊ ተጽዕኖ በመገንዘብ እርቅን ሊፈልጉ፣ ለእርቅ ፈቃደኛ ሊሆኑና እንደ እግዚአብሔር ቃል እግዚአብሔር ከሚጠላው ሕይወት ለመራቅ ያላሰለሰ ጥረት ለማድረግ ሊወስኑ ይገባል፤ *"...መፋታትን እጠላለሁ"* /ሚልክ 2፡ 16/።





## ለጥንዶች በግላቸውና በቡድን ለማጥናት የሚረዷቸው የውይይት ጥያቄዎች

## የምዕራፍ ሃያ ሁለት (22)

## የውይይት ጥያቄዎች

1. የፍችን ምንነት በመጽሐፍ ቅዱስ እይታ በመመርመር ተወያዩበት፡፡
2. በፍች ሂደት ላይ ያሉትን የተለያዩ አመለካከቶች በመጥቀስ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምላሽ ለመስጠት ተወያዩ፡፡
3. የተለያዩ የፍች ደረጃዎችን በመጥቀስ ገና ከጅምሩ ባለትዳሮች በስሜት መራራቅ ሲጀምሩ ምን ሊያደርጉ ይገባል ትላላችሁ?
4. ፍችን እግዚአብሔር የሚጠላው ቢሆንም ነገር ግን በየዘመኑ ሰዎች በራሳቸው ፈቃድ ፍችን ሲያከናውኑ ይታያሉ፡፡ ፍችን በሚያከናውኑ ሰዎች ምክንያት በሌሎች ሰዎች ላይ ሊፈጠሩ የሚችሉ የተለያዩ ተጽዕኖዎች ምንድን ናቸው? ሌሎች ሰዎች በፍች ሂደት ውስጥ ስላሉ ጥንዶች የሚያንጸባርቋቸው ስሜታዊና ማህበራዊ ምላሾችስ በችግር ውስጥ ባሉ ጥንዶች ላይ የሚያስከትሉት ተጽእኖ ምንድን ነው? ውይይት አድርጉ፡፡
5. በክርስቲያን ባለትዳሮች ዘንድ ከፍች ይልቅ እርቅ ሊወሰድ የሚገባው ትክክለኛ እርምጃ ነው፡፡ ችግር ያጋጠማቸው ክርስቲያን ጥንዶች ወደ እርቅ ሲመጡ ሊረዱት የሚገባ የእርቅ እሳቤ ምንድን ነው? ትክክለኛ እርቅን ትክክለኛ ካልሆነው የእርቅ አስተሳሰብ ጋር በማነጻጸር ተወያዩ፡፡
6. የእርቅ የተለያዩ ደረጃዎችን በመጥቀስ ባለትዳሮች ለእርቅ ከፍተኛ ስፍራ ሊሰጡ እንደሚገባቸው ተወያዩበት።
7. አጠቃላይ በፍች ሂደት ያለፉና እያለፉ ያሉ ወገኖች ይቅርታ መለማመድ የሚያስፈልጋቸው በምን ምክንያት ነው?
8. ትክክለኛ እርቅ የሚጠይቀው ምንድን ነው? የእናንተን ልምምድ በማካፈል በግልጥነት ተወያዩ፡፡
9. በግጭት፣ በመለያየትና በፍች ሂደት ያሉ ባለትዳሮች ለእርቅ መዘጋጀት ያለባቸው እንዴት ነው?
10. በዚህ ወይይት መሠረት እንደ ክርስቲያን ባለትዳር እናንተ ልትወስዱት የሚገባ ተግባራዊ እርምጃ ምንድን ነው?

# ምዕራፍ ሃያ ሶስት (23)
# ከፍች በኋላ አዲስ ቀጣይ ኑሮ

## I. ከፍች በኋላ የአዲስ ቀጣይ ኑሮ ምንነት

ፍች የነበረና የሚኖር በብዙ ግጭቶች ምክንያትና ግጭትታቸውን እንደሚገባ መፍታት ባልቻሉ በጋብቻ ተጣምረው ይኖሩ በነበሩ ጥንዶች መካከል የሚከሰት ስሜታዊ፣ ሕጋዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ቤተሰባዊና ማሕበራዊ ግንኙነትንና አንድነትን በማፈራረስ የመበታተን ቀውስ ሂደት ነው:: ፍች በእግዚአብሔር የተጠላ ሂደት ነው። የትኛውም ሃይማኖት፣ አገርና መንግሥትም ቢሆን ፍችን የሚያበረታታና የሚደግፍ መመሪያ ወይም ፓሊሲን አያራምድም:: ይህ ማለት ግን ፍችን የሚፈቅድ ሃይማኖት፣ አገርና መንግሥት የለም ማለት አይደለም:: ፍች በሕጋዊነትና የፍችን ሂደት ለማከናወን በተቋቋሙ ተቋማት አማካኝነት ጥቂት በማይባሉ የሃይማኖት ተቋማት እንዲሁም መንግሥታዊና ማሕበራዊ ተቋማት አማካኝነት በየዕለቱ በመፈጸም ላይ የሚገኝ ሂደት ነው::

ፍችን ኃጢአትና በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠላ ተግባር እንደሆነ የማያምኑትና የማይቀበሉት ፍችን የሚያስፈጽሙ ተቋማት እንኳን በማሕበራዊ፣ ቤተሰባዊ፣ ስነ ልቦናዊና ስሜታዊ... ቀውስነቱ ያውቁታል:: ቀውሱንም ለመቀነስ ይጥራሉ:: የፍች ችግር በሙሴ ሕግ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር በአካለ ስጋ ባገለገለበት ወቅትና በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ዘመን የነበረና አሁንም በስፋት የሚታይ የጋብቻ ተቋም ተግዳሮት ነው። ባለትዳሮች በተለያዩ ምክንያቶች ግጭቶቻቸውን በመነጋገርና በይቅርታ መፍታትና መታረቅ ሲያቅታቸው ፍችን እንደ መጨረሻ አማራጭ የሚወስዱት እርምጃ ነው።

በአጠቃላይ ፍች ጥንዶች የነበራቸውን ስሜታዊ፣ አካላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ቤተሰባዊና ማሕበራዊ ግንኙነትና አንድነት በማቋረጥ በእግዚአብሔርና በሰው ፊት የገቡትን ቃል ኪዳን የማፍረስ ሂደት ነው:: ነገር ግን ይህ ክስተት በአንድ ጊዜ ተፈጽሞ የሚያበቃ ቅጽበታዊ ክንውን ብቻ ሳይሆን ባለትዳሮች የጋብቻ ስምምነታቸውን (ቃል ኪዳናቸውን) ካፈረሱበት ጊዜ ጀምሮ ፊት በመባል የሚኖሩበትን የሕይወት ጉዞና ልምምድ ውጤት የሚያስከትል ሂደትም ነው። ከፍች በኋላ አዲስ ሕይወት መጀመር ማለት ደግሞ የፍች ውጤት የሆነው በተለይም ሕጋዊ ፍች ከተፈጸመበት ዕለት ጀምሮ ያለው ፈት የሆኑ ሰዎች የሚያልፉበት የሕይወት ሂደት ነው:: ፍች እስከፈጸሙበት ጊዜ ድረስ በትዳር የታሰሩና በሁለት ሰዎች ስምምነት በተመሠረተ ጋብቻ የሚባል ኅብረት ውስጥ ሲኖሩ ነበር:: ትዳራቸው ሰላም ያልነበረው ቢሆንም እንኳን ባለትዳር መሆናቸው ወይም ባለትዳር ነው /ናት/ ተብለው መታወቃቸው በግላዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ማሕበራዊ፣ ሕጋዊ፣ ስሜታዊና ኢኮኖሚያዊ የማንነት ገጽታቸው የሚተረጎምበት የእይታ አውድ ነው::





ፍች ሲፈጸም እነዚህ ማንነታቸው የሚተረጎምባቸው አውዶች ሁሉ ፈራርሰው ቀውስ ውስጥ ይገባሉ። በዚህ ቀውስ ውስጥ ሲገቡ የፈራረሱባቸውን ልዩ ልዩ የሕይወት ዋጋዎችና አውዶች በደንብ ማየትና መረዳት ይጀምራሉ።በዚህ ጊዜ ራሳቸውን መቀበል ያቅታቸዋል። የሕይወት መሠረታቸውም ይናጋል:: ማሕበረሰቡም በአዲስ ማንነትና እይታ እነርሱን ማየት ይጀምራል:: እነርሱም ከዚህ ጊዜ በኋላ በፍች ቀውስ ውስጥ መኖራቸው የሚቀጥል እውነታ ይሆናል:: ይህ የፍች ቀውስ በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠላ የመሆኑ እውነታ ላይ ክርስቲያኖች ሁሉ በተለይም በችግሩ ውስጥ ያሉ ሰዎች የማያወላውል አቋም ሊይዙ ይገባል:: ይህንን በመረዳትም ፍችን ለማስቀረትና በትዳር ለመቀጠል ከእነርሱ በኩል የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት ሁሉ ለመወጣትና መስዋዕትነትን ለመክፈል መዘጋጀት ግዴታቸው ነው:: ማድረግ ያለባቸውን ሁሉ አድርገው ፍች የግድ የሚያልፉበት የሕይወት መንገድ ከሆነ (አይቀሬ ከሆነ) ከላይ የተጠቀሱትን ሁኔታዎች ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ፍች ከሚፈጥራቸውና ከሚያመጣቸው የተለያዩ ቀውሶች በማገገምና ወደ ቀጣይ ሕይወት በመሸጋገር ከባለትዳርነት ወደ ፈትነት እና ፈት እናትና አባት ሁኖ ወደ መኖር ሲገቡ የተረጋጋ የወላጅነት ሚናቸውን እንዲወጡ፣ እግዚአብሔርን ማምለክ እንዲቀጥሉ፣ በንስሃ ራሳቸውን አስተካክለው በአስተሳሰብ ለውጥ እንዲቀጥሉ ለመርዳት ሲባል ይህ ምዕራፍ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እንዲካተት ተደርጓል::

## II. ከፍች በኋላ አዲስ ቀጣይ ኑሮ ለመለማመድ ጥረት የማድረግ አስፈላጊነት

### 1. በፍች ሂደት ለሚያልፈው ሰው

ከፍች በኋላ አዲስ ኑሮ የመጀመሩን ሕይወት የመለማመድ ጥረት በፍች ሂደት ለሚያልፉ ወገኖች በግል ሕይወታቸው ከሚፈጠርባቸው መንፈሳዊ፣ ሞራላዊ፣ ስሜታዊ፣ ስነ ልቦናዊ፣ አካላዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ቀውስ በማገገም ሕይወታቸውን በመረጋጋት መምራትና ማስተዳደር እንዲችሉ ለማገዝ ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው። ፍች ለክርስቲያን ኃጢያትና ፈጽሞ የሕይወት አማራጭ ተደርጎ መወሰድ ያለበት አይደለም:: ፍች አይቀሬ ከሆነ ግን በፍች ውስጥ ያለፉ ወገኖች በገጠማቸውና እያለፉበት ባለው የሕይወት ቀውስ የተለያዩ አስቸጋሪ ሂደቶች ተስፋ ቆርጠውና ሕይወትን አጨልመው በማየት ብቻ ግራ ተጋብተው መኖር መቀጠል የለባቸውም:: በእርግጥ ፍች በመፈጸማቸው በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአት ሠርተዋል:: የክርስትናን መርህም የሚቃረን ተግባር ፈጽመዋል። ነገር ግን ሕይወት ከፍች በኋላም ይቀጥላል::

ሕይወት ደግሞ ከብዙ ጥያቄዎችና ኃላፊነቶች ጋር የተያያዘች ናት:: ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖራቸው ኅብረት፣ ከቤተ ክርስቲያንና ከአማኞች ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት፣ ከማሕበረሰቡና ከቤተሰቦቻቸው ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት፣ ሕይወትን የመምራት ኃላፊነትና ልጆችን ወልደው ከሆነ ልጆችን የማሳደግ ኃላፊነት

እንዴት መያዝ እንዳለበት በአግባቡ ሊያስቡና ትክክለኛ በሆነ ግንዛቤ አቋም ሊይዙ ይገባል፡፡ ካሉበት አስቸጋሪ ቀውስ የተነሳ ብቻቸውን እነዚህን ጥያቄዎች በአግባቡ የማየቱ፣ የመመለሱና ውሳኔና የሕይወትን ኃላፊነት የመምራቱ ጉዳይ ላይ አቅም ላይኖራቸው ይችላል፡፡ ስለዚህ አብሯቸው በመጓዝ አቅጣጫ በማስያዝ፣ በመገሰጽ፣ በማበረታታት፣ በማስተማር፣ በጸሎት በመደገፍ ከትናንቱ ጉዳት ማገገም እንዲችሉና የቀድሞውን የሕይወት ውድቀት በንስሃ አስተካክለው ለቀጣይ ሕይወታቸው ትክክለኛ ምርጫና ውሳኔ እንዲያደርጉ ለመርዳት ሌሎች ወገኖችም ጉዳዩን በመረዳት ከእነዚህ ሰዎች ጋር አብረው መቆማቸው እጅግ በጣም አስፈላጊ አገልግሎት ነው።

## 2. የልጆችን ቀጣይ ሕይወት በተረጋጋ ሁኔታ ለመምራትና ለማሳደግ

የፍች ቀውስ በባለትዳሮች መካከል ሲፈጠር ከሚያስከትለው ክፉ ውጤት አንዱ የቤተሰብ መፍረስ ነው። ባልና ሚስቶች ሲፋቱ ልጆችን በጋራ ሁነው ከማሳደግም ይፋታሉ። በወላጆች የተፈጠረው አለመግባባትና ግጭት ብሎም የፍች ቀውስ ልጆችን በመንፈሳዊ፣ በስነ ልቦናዊ፣ በማሕበራዊና በስሜታዊ ቀውስ ውስጥ እንዲወደቁ ያስገድዳቸዋል፡፡ ይህ ቀውስ በትምህርታቸው፣ በእድገታቸው፣ በጤንነታቸውና በማሕበራዊ ግንኙነታቸው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያስከትልባቸዋል፡፡ ቀውሱ የሚያሳድርባቸው አሉታዊ ተጽዕኖም ወቅታዊ ብቻ ሳይሆን ሕይወት ዘመናዊ አፍራሽ ውጤት ስለሚያስከትል እንዲሁ በቀላሉ የሚታይና የሚታለፍ አይደለም። ወላጆች እያለፉበት ባለው ቀውስ ተጽዕኖ ምክንያት ሳያውቁትና ሳያስተውሉት ገና መድረሻቸው ያልታወቀውን የልጆቻቸውን የወደፊት ሕይወት እያፈረሱት ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ በልጆች ላይ የሚፈጥረውን ከፍተኛ የሆነ ሁለንተናዊ ቀውስ ግምት ውስጥ በማስገባት ልጆችን በመርዳት ሁለንተናዊ የሆነ መረጋጋት ሊያገኙ የሚችሉበትን መንገድና እርዳታ ማመቻቸት አስፈላጊ ነው።

ከፈራረሰ ቤተሰብ የወጡ ልጆችን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እግዚአብሔርን በመውደድና በመፍራት ማምለክ እንዲችሉ፣ በስነ ልቦና ጠንካራ፣ ድፍረትና የታደሰ አእምሮ ያላቸው እንዲሆኑ፣ የተረጋጋና የሰከነ ስሜት እንዲኖራቸው የወላጆች ከፍች በኋላ አዲስ ሕይወትን የመጀመርና የመለማመድ ሂደት ጉዳይ በግዴለሽነት የሚታይ መሆን የለበትም፡፡ በክርስቶስ ላይ የተመሠረተ ማንነት እንዲኖራቸውና ራሳቸውን መቀበል የሚችሉና ስለራሳቸው ትክክለኛ የሆነ ግንዛቤ ያላቸው ግለሰብና ዜጋ እንዲሆኑ የመርዳት አገልግሎት ጊዜ የሚሰጠውና በቸልተኝነት የሚታለፍ አይደለም፡፡ ይህ ጉዳይ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች፣ መጋቢዎች፣ አማካሪዎችና አስተማሪዎች ልናተኩርበት የሚገባ አንገብጋቢ የሆነ የዘመኑ የቤተሰብ፣ የቤተ ክርስቲያንና የሕብረተሰቡ ተግዳሮት ነው።

የነገውን የልጆች ሁለንተናዊ ሕይወት ማለትም ክርስትናቸውን፣ አገልግሎታቸውን፣ ተሰጥዖአቸውን፣ እምቅ ችሎታውን፣ ክህሎታቸውንና ማሕበራዊ





ግንኙነታቸውን ለመቅረጽ መሠራት ያለበት በዛሬው ቀውስ አፍራሽ ተጽዕኖ ከመጥፋታቸው በፊት ነው፡፡ ለራሳቸው፣ ለቤተሰባቸው፣ ለቤተ ክርስቲያን፣ ለማሕበረሰባቸውና ለአገር የሚጠቅሙበትን ምቹ ሁኔታ ከወዲሁ በማሰብ ከፍተኛ የሆነ ጥረት ማድረግና ትውልድን ማትረፍ ጥሪያችን፣ ኃላፊነታችን፣ ግዴታችንና ከሚሰጠን ውስጣዊ እርካታ በተጨማሪ ከተጠያቂነት በማምለጥ ባለብዙ ሕብር ሽልማቶችን በዚህ ዓለምና በዘላለማዊው የእግዚአብሔር መንግስት ውስጥም የሚያስገኝልን ነው።

## 3. በዙሪያ ላሉ ወዳጆችና የቤተ ክርስቲያን ምዕመናን

የፍች ቀውስ መፈጠር በባለትዳሮችና በቤተሰባቸው ላይ ብቻ ሳይሆን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሌሎች ግለሰቦች፣ ቤተሰቦች፣ በቤተ ክርስቲያንና በማሕበረሰቡ ላይም የሚፈጥረው አሉታዊ ተጽዕኖ በቀላል የሚታይና ችላ ሊባል የማይገባው ጉዳይ ነው። ሌሎች በቅርብ የስጋ ዝምድናና በክርስቲያንነታቸው በፍች ውስጥ እያለፉ ላሉ ጥንዶች ቤተሰብ የሆኑ ወዳጆች፣ ቤተሰቦች፣ ቤተ ዘመድና ጎረቤቶች ሁሉ በሚፈጠረው መንፈሳዊ፣ ስነ ልቦናዊ፣ ስሜታዊና ማሕበራዊ ቀውስ ተጽዕኖ ይጎዳሉ፡፡ የሚፈጠረውን ቀውስ ድንበር ስፋትና፣ ጥልቀት መቀነስ እንዲቻል ነፃ የሆኑና የተረጋጉ ሁኔታዎች እንዲኖሩ የማስተማር፣ የመምከር፣ የማስጠንቀቅና የማበረታታት እገዛ ማድረግ አስፈላጊ ነው። እንደ እግዚአብሔር ቃል፣ በጽድቅና በመንፈስ የታደሰ አእምሮ እንዲኖራቸው ሁሉንም ወገኖች ማለትም በፍች ውስጥ እያለፉ ያሉትንና በፍች ሂደት ላይ ባሉ ባለትዳሮች የፍች ሂደት ቀውስ ተጠቂ የሆኑ ሌሎች ሰዎችን ማስተማር፣ መምከርና ትክክለኛውን የሕይወት መንገድ ማሳየት ሊመጣባቸው የሚችለውን አሉታዊ ተጽዕኖ በፍጥነት፣ በብስለት፣ ተቆርቋሪ በሆነ ልብ እና በመልካም አቀራረብ ለመቆጣጠር ይረዳል።

## III. በፍች ሂደት እያለፉ ያሉትን ወደ ፊት መጓዝ እንዲችሉ የማገዝ አገልግሎት

ፍች በእግዚአብሔር፣ በጥንዶች፣ በቤተሰብ፣ በቤተ ክርስቲያን፣ በሕብረተሰቡና በአገር ደረጃ የሚጠላና የማይደገፍ ልምምድ ነው። ከማንም በላይ በሂደቱ ያለፉ ጥንዶች፣ ቤተሰቦችና የቅርብ ወዳጆች ፍች በሚያመጣውና በሚፈጥረው የተለያየ የሕይወት ቀውስ የመጠቃታቸው ሁኔታ ቀላል አለመሆኑ የማይታበል ሐቅ ነው። በፍች ሂደት ውስጥ የሚያልፉ ወገኖችን ለመርዳት በቤተ ክርስቲያን ዘንድ ያለው አገልግሎትና እርዳታ አነስተኛ መሆኑ በፍች ሂደት የሚያልፉት ወገኖች ከተፈጠረባቸው የተለያየ ቀውስ በፍጥነት በማገገም ወደ ፊት መራመድና ማሰብ እንዳይችሉ ሊያባብስባቸው ይችላል።

ቤተ ክርስቲያን ፍችን የማትቀበልና ጥንዶችን የማፋታት ሳይሆን የማጋባት ኃላፊነት የምትወጣ ተቋም ናት። ፍች ግን በጥንዶች በራሳቸው ምክንያትና መንገድ

በመንግሥታዊና በማሕበራዊ ተቋማት አማካኝነት ይፈጸማል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ቤተ ክርስቲያን እኔ ፍች እንዲከናወን አላደረግሁም ፍችንም አልፈቅድም ስለዚህ በራሳቸውና በሕጋዊ መንገድ የተፋቱ ወገኖችን ልቀበልና ላስተናግድ አልችልም የሚል አቋም መያዝ አይኖርባትም፡፡ እነዚህን ፍች በሚባል በሽታ የታመሙና የቆሳሰሉ ወገኖች የመርዳትና ቀውሱና ውጤቱ እንዲቀንስ የሚያደርግ ሕክምና እንዲያገኙ ማገልገል አለባት፡፡ በፍች ሂደት ውስጥ ያሉ ወገኖችን የምትረዳበት መንገድና ምቹ ሁኔታዎችም ሊኖሯትና ልትፈጥር ይገባል። ይህ ዓይነቱ ጥረት በፍች ውስጥ ያለፉ ሰዎችን የመርዳት አገልግሎት ብቻ ሳሆን ተመሳሳይ ቀውስ በሌሎች ጥንዶች ሕይወትም እንዳይከሰት የመከላከል አገልግሎት ነው፡፡

በእርግጥ በአብዛኛው በኢትዮጵያዊያን አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ የተለመደው ችግሩ ከመከሰቱ በፊት አስቀድሞ ከመከላከልና ለሎችንም ወገኖች ከችግሩና ከሚያስከትለው አሉታዊ ተጽዕኖ ከመጠበቅ ይልቅ ችግሩ ከተባባሰና መጨረሻ ደረጃ ላይ ከደረሰ በኋላ እሳት የማጠፋት መንተፋተፍ ነው፡፡ ችግሩ በቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አማካሪዎች ዘንድ የሚታወቀውም ሌሎች ሰዎች ስለጉዳዩ ብዙ ከሰሙና ቀውሱ ሊስተካከል ከሚችልበት ደረጃ ካለፈ በኋላ ነው፡፡ በችግር ውስጥ ያሉ ሰዎችም ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመጡት ችግሩ በምክር አገልግሎት ሊስተካከል በማይችልበትና ከፍተኛ ነውጥ ባለበት ወቅት ነው፡፡ በዚህ ደረጃ ብዙዎቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለማስታረቅ ግር ግር ሲፈጥሩ ይታያሉ። ነገር ግን ከግር ግር ባለፈ መልኩ ምንም ማድረግ አይችሉም፡፡ ስለዚህ ፍችው አይቀሬ ጉዳይ ሆኗል ማለት ነው፡፡ ፍች ሲፈጸም ከስተቱ በእግዚአብሔር ዘንድም የተጠላ ነውና ፍችን ልንጠላው ይገባል፡፡ ነገር ግን ፍችን መጥላትና በፍች ሂደት የሚያልፉ ሰዎችን መጥላት የተለያዩ ጉዳዮች መሆናቸው በቤተ ክርስቲያን ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

ቤተ ክርስቲያን እንደ እግዚአብሔር ቃል በጽድቅ መንገድና የማንም ወገንተኛ ባለመሆን እነዚህን ችግር ውስጥ ያሉ ሰዎች የምትረዳበት ልብ፣ እውቀት፣ ስልጠናና ልምድ ሊኖራት ይገባል። በፍች ሂደት የሚያልፉ ወገኖችን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለመርዳት ሊደረጉ የሚገባቸውን የመፍትሔ አሳቦች ከዚህ ቀጥለን ለማየት እንሞክራለን።

## 1. መረዳት፡- በፍች ምክንያት የሚፈጠሩ የተለያዩ የሕይወት ሂደት ደረጃዎችን መረዳት

እንደ እግዚአብሔር ሰው፣ እንደ አገልጋይና እንደ አማካሪ በፍች ሂደት የሚያልፉ ወገኖችን በመርዳት ሂደት በቅድሚያ ሊታወቁ የሚገባቸውን ጉዳዮች መለየት ተገቢ ነው። በፍች ሂደት የሚያልፉ ወገኖች ላይ የሚፈጠሩ የተለያዩ የሕይወት ሂደት ደረጃዎች እንዳሉ መረዳት ደረጃ በደረጃ በፍች ቀውስ የሚያልፉ ጥንዶችንና ቤተሰቦችን





ለመርዳት ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው። ከዚህ በታች በፍች ሂደት የሚፈጠሩ የተለያዩ የሕይወት ሂደት ደርጃዎችን እንመለከታለን፡-

### 1) የነውጥና ያለመረጋጋት ወቅት

የመጀመሪያው ደረጃ ከባለትዳርነት ወደ ፈትነትና ብቻቸውን የልጆች አሳዳጊ ወደሚሆኑበት የተለየ ሚና የሚገቡበት ሂደት ነው። በዚህ ወቅት በፍች ሂደት በሚያልፉ ወገኖች ላይ የሚፈጠረው ሁኔታ የመናወጥና ያለመረጋጋት ሁኔታ ነው። በዚህ ያለመረጋጋት ደረጃ የተለያዩ ስሜቶች ሊፈራረቁባቸው ይችላሉ። በዚህ የነውጥ ደረጃ ላይ በፍች ሂደት የሚያልፉ ሰዎች የተፈጠረውን ያለማመን፣ በተፈጠረው የመሸማቀቅ፣ ብቸኝነት፣ ተቀባይነት የማጣት ስሜት፣ የተለያዩ ፍርሃቶችና በተፈጠረው ክስተት የመቆጣትና ከፍተኛ የሆነ ንዴት ውስጥ መግባት እንደሚያጋጥማቸው መረዳት አስፈላጊ ነው፡፡ የምናደርገው ድጋፍ እነዚህን የተለያዩ ስሜቶች እንዲያወጡ፣ እንዲተነፍሱና እንዲያንጸባርቁ እድል በመስጠት መታገስን ይጠይቃል። ለቀጣይ ሕይወት መሻሻል በትክክለኛ መንገድ ትክክለኛ ምርጫና ውሳኔ ማድረግ እንዲችሉ በብዙ ትዕግስት ማረጋጋትና ወደ ሚቀጥለው ደረጃ እንዲሸጋገሩ ማበረታታት አስፈላጊ ነው።

### 2) የሽግግር ወቅት

በፍች ሂደት እያለፉ ያሉ ወገኖች የተፈጠረባቸውን ያለመረጋጋት ስሜት መቆጣጠር የሚችሉበትን እርዳታ ካገኙ በኋላ ሌሎችን ነገሮች ማሰብና እርምጃ መወሰድ የሚጀምሩበት ወቅት የሽግግር ሂደት ይባላል። በዚህ ደረጃ ላይ ከተፈጠረባቸው የፍች ቀውስ መረጋጋት በመጀመር ስለፍች ሂደት አሉታዊ የሆኑ አስተሳሰቦችን ብቻ መቀበል ያቆሙና በምትኩ አዎንታዊ የሆኑ አስተሳሰቦችን ማሰብና መቀበል ይጀምራሉ። ይህ ወቅት ፍች በእነርሱ ስህተት ብቻ ሊከናወን የማይችል መሆኑን መረዳት፣ የእግዚአብሔርን ፍቅር መቀበልና መለማመድ የሚጀምሩበት ወቅት እንደሆነም መገንዘብ ይገባል።

በዚህ የሽግግር ወቅት ቀድሞ የነበራቸውን የትዳር ግንኙነት አሉታዊና አዎንታዊ ገጽታዎችን ማንጸባረቅ በመጀመር በወቅቱ የተፈጠሩ የግል ኃጢአቶቻቸውን፣ ራስ ወዳድ የሆኑባቸውን ጉዳዮችና የሠሯቸውን ስህተቶች በሚገባ በማሰብ ተጸጽተው ንስሃ የመግባት አቋም ይይዛሉ፡፡ ለጥፋቶቻቸው ኃላፊነትን መውሰድ የሚጀምሩበት እንዲሁም መብታቸውን በመተው ከተቻለ ለእርቅ የሚዘጋጁበት ያለዚያም ባይታረቁም እንኳን ይቅርታ ማድረግን መለማመድ የሚጀምሩበት ወቅት ነው። ከንስሃና ከይቅርታ ቀጥሎ ያለትዳር አጋር በፈትነት እንዲሁም ለብቻቸው ልጅ አሳዳጊዎች በመሆን ኑሮን በማስተካከል ሕይወትን ለመጀመር ጥረት የሚያደርጉበት የሽግግር ወቅት ነው።

**3) የማገገሚያ (የተሃድሶ) ወቅት**

ከሽግግር ወቅት ቀጥሎ ከፍች ቀውስ የሚያገግሙበት ወቅት ነው። ይህ የማገገሚያ ወቅት በመረጋጋት ወደ ተሻለ ሁኔታ መሸጋገር የጀመሩ የፍች ሰለባዎች እግዚአብሔር ሁኔታዎችን ሁሉ መቆጣጠር የሚችልና በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ላለ ሰው ግድ የሚለው አምላክ እንደሆነ መረዳት የሚጀምሩበት ጊዜ ነው። በዚህ ወቅት እግዚአብሔር ሕይወታቸውንና ባሕርያቸውን በመሥራትና በመቅረጽ ሂደት ላይ እንዳለ፣ በራሳቸው ምንም ማድረግ የማይችሉበት ነገር ግን በእነርሱ በሚኖረው በክርስቶስ ብቻ ሕይወታቸው ሊታነጽ የሚችል እንደሆነ፣ ሕይወት በመመለስና በመታደስ ተስፋ የተሞላች እንደሆነች በመረዳት ተስፋ የሚሰንቁበት ደረጃ ላይ ይደርሳሉ፡፡

የእግዚአብሔርን ምህረት፣ ፍቅርና ተቀባይነት ለሌሎች ሰዎች ለማሳየት አስቀድመው በዚህ አስከፊ ቀውስ ውስጥ ከማለፋቸው እንደተማሩና ሌሎችም እንዳይጎዱ የመርዳት ኃላፊነት እንዳለባቸው የሚያስቡበትና ማመን የሚጀምሩበት ወቅት ነው፡፡ አገልጋዮች እነዚህ ሰዎች የሉበትን ሁኔታ በመገንዘብ ካሉበት ከፍች ቀውስ ማገገም እንዲችሉ ደረጃ በደረጃ፣ በእርጋታና በትዕግስት አብረዋቸው በመጓዝ ማበረታታትና መደገፍ እንደሚያስፈልግ በመረዳት ከጎናቸው መቆም ይጠበቅብናል።

## 2. መርዳት፡- ከፍች ሂደት አገግመው ወደ ፊት መራመድ እንዲችሉ መርዳት

**1) መቅረብ፡- በፍርድ መንፈስ ሳይሆን በፍቅር ልብ መቅረብ**

በጊዜው ከተፈጠሩባቸው የተለያዩ ስሜቶችና ሁኔታዎች በማገገም ስለቀጣይ ሕይወታቸው በአግባቡ በማሰብ ትክክለኛ አሳብ፣ ምርጫና ውሳኔ ላይ እንዲደርሱና እርምጃ እንዲወስዱ ሁኔታቸውን ከመረዳት ባለፈ የተለያዩ እርዳታዎችና አገልግሎቶች በማቅረብና በመስጠት እገዛ ማድረግ አስፈላጊ ነው። እውነተኛና ፈጣን የሆነ አምላካዊ ፈውስ እንዲመጣላቸው፡- በእግዚአብሔር ፊት እውነተኛ ፍላጎታቸውንና ስሜታቸውን ይዘው መቅረብ እንዲችሉ በሚያደርግ አቀራረብ እንደገና ዕድል መስጠት፣ በእውነተኛ ጸጸትና ንስሃ በእግዚአብሔር ፊት በመቅረብ ፈውስ እንዲቀበሉ ሳይፈርዱ በፍቅር ማበረታታት አስፈላጊ ነው። በዚህ ወቅት ልዩ ጥንቃቄ ሊደረግ የሚገባው ሊበረታታ የማይገባውን እንዳናበረታታና ፍችን እንደ ጽድቅ አድርገው እንዲያስቡ እንዳናደርጋቸው ነው።

**2) መስጠት፡- እግዚአብሔር በቃሉ እንዲናገራቸው ዕድል መስጠት**

ሕይወት ሰጭና ለዋጭ በሆነው በእግዚአብሔር ቃል እውነት በመመሥረት ለሕይወት ለውጥ ሙሉ ፈቃደኝነት እንዲኖራቸው እግዚአብሔር በቃሉ እንዲናገራቸውና እንዲመከራቸው መርዳት ተገቢ ነው። በተፈጠረው የፍች ቀውስ ውስጥ ሕያው በሆነ የእግዚአብሔር ቃል ራሳቸውን በማየት ወደ ትክክለኛ ሐዘንና ጸጸት





የሚመለስ ልብ እንዲኖራቸውና መጽናናት እንዲችሉ መርዳት ያስፈልጋል። ፍች ከፈጠረባቸው የሕይወት ቀውስና ምሬት በመውጣትና ቀጣይ የሕይወት ጎዳናቸው እንደ እግዚአብሔር ቃል፣ በጽድቅና በእግዚአብሔር ቃል መሠረት እንጂ በችግሮች ምሬት ተገፋፍተው ሌላ የተሳሳተ ምርጫና ውሳኔ እንዳያደርጉ በማረጋጋት፣ በማበረታታትና በማስጠንቀቅ መደገፍ ራሳቸውን በትክክለኛው መስመር መምራት እንዲችሉ ያግዛቸዋል። በእግዚአብሔር ማንነት ላይ ሙሉ በሙሉ በመደገፍ ቀጣይ ሕይወታቸውን እንዲመሩ አቅጣጫ የማሳየት አገልግሎት ሊሰጣቸውም ይገባል። እንዲህ ዓይነቱን መሠረት የመጣልና አቅጣጫ የማሳየት አገልግሎት መስጠት በፍች ሂደት እያለፉ ያሉ ወገኖች የደስታቸውን መሠረት በራሱ በእግዚአብሔር ላይ በማድረግ በሌላው የሕይወት ገጽታም ላይ የተረጋጋና መደሰት የሚችል ሕይወት እንዲኖራቸው በእግዚአብሔር ቃል ተስፋ የማስነቅ እርዳታ መስጠት በጣም ጠቃሚ ነው።

**3) መመሥረት፡- በክርስቶስ ባለ አዲስ ሕይወት ላይ መሠረትና ትኩረት ማድረግ እንዲችሉ ማገዝ**

ከፍጥረት ጀምሮ ለዛሬውና ለነገው ሕይወት ቀጣይነት ለምድራዊም ሆነ ለሰማያዊው ሕይወት መሠረቱ እግዚአብሔር ራሱ ነው። በፍች ሂደት የሚያልፉ ወገኖች ከነበራቸው የትዳር ሕይወት ቀውስ ወደ ሌላ የሕይወት ገጽታ የተሸጋገሩ በመሆናቸው በዚህ ወቅት በክርስቶስ ያላቸውን ሕይወት፣ ማንነት፣ ተስፋና እምነት ያሉበት ሁኔታ እንዳያጨልምባቸው የሕይወታቸውን ትኩረት ማስተካከል አለባቸው፡፡ ከሰይጣን አሳብ ጋር ተባባሪ ሆነው ተስፋ በመቁረጥና ራሳቸውን በማስጨነቅ የሚያገኙት ምንም መፍትሔ የለም፡፡ ይልቁንም በክርስቶስ ማንነት ላይ እንዲመሠረቱ፣ እንዲበረቱና እንዲቀረጹ የማገዝን ኃላፊነት በአግባቡ መወጣት አስፈላጊነቱ ከፍተኛ ነው።

በክርስቶስ ላይ የተመሠረተ ማንነት ሲኖራቸው በክርስቶስ ሙሉ እንደሆኑ ይሰማቸዋል፡፡ ፍጹም የሆነው ደስታም ከክርስቶስ ጋ የሚፈልቅ እንጂ ከውጭ ከሁኔታዎች የሚመጣ እንዳልሆነ እንዲረዱና እንዲለማመዱ ያግዛቸዋል። በክርስቶስ ማንነት ላይ የተመሠረተ ሕይወት ያለው ሰው ዓላማው እግዚአብሔርን ለማክበርና ለማስደሰት ነው፡፡ ለዚህ ዓላማ ብርቱ ፍላጎትና ትጋት ያለው ክርስቶስ ይቅር ብሎ እንደተቀበላቸው መረዳታቸው ደግሞ ይቅርታ የማድረግና ይቅርታን የመለማመድ ዕድልና አቅም እንዲኖራቸው አስተዋይና ጠቢብ መሆን እንዲችሉ ያዘጋጃቸዋል፡፡

**4) መርዳት፡- የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ዕቅድና ዓላማ እንዲገነዘቡ መርዳት**

የፍች ቀውስ ከሚፈጥራቸው አሉታዊ ተጽዕኖዎች አንዱ ሰዎች በእግዚአብሔር ላይ ያላቸው አመለካከትና እምነት ተለዋዋጭና የተዛባ እንዲሆን ማድረጉ ነው፡፡ በፍች ውስጥ ያለፉ ባለትዳሮች በሕይወታቸው ላይ ያለውን የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ዕቅድና ፍቅርም ባጋጠማቸው ችግር ምክንያት መርሳት፣ መጣልና ግራ መጋባት ይጀምራሉ። በዚህ ወቅት የእግዚአብሔርን ተስፋና ቃል ኪዳን ማሰብ እንዲችሉ በቃሉ

ማስተማርና መምከር ይገባል። የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ቃል ኪዳን በማሰብ የእግዚአብሔር ምህረትና የጸጋው አቅርቦት ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ የተቻላቸውን ሁሉ በማድረግ የእግዚአብሔርን ዓላማ እንዲገነዘቡ መርዳት አስፈላጊ ነው።

**5) መነሳሳት፡- አገልጋዮችና አማካሪዎች በፍች ቀውስ ውስጥ ላለፉ ሰዎች ልዩ ትኩረትና ጥንቃቄ ለማድረግ መነሳሳት**

በፍች ቀውስ የሚያልፉ ወገኖች በአገልጋዮችና በአማካሪዎች ለመረዳትና እገዛ ለመቀበል ፈቃደኛ መሆን አለባቸው፡፡ አገልጋዮችም ችግር ውስጥ ያሉትን ሰዎች ለመርዳት መነሳሳት ያስፈልጋቸዋል። ይህን ሲያደርጉ ግን ድጋፍ ሰጭዎቹ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው፡፡ ሌሎችን በመርዳት ሂደት ላይ ያሉ አገልጋዮች በተመሳሳይ ችግር ውስጥ እንዳይወድቁ ራሳቸውን መጠበቅን መርሳት የለባቸውም። በፍች ችግር እያለፉ ያሉ ወገኖችን የመደገፉን አገልግሎት የሚያከናውኑ አገልጋዮች በትዳራቸው ምሳሌነት ያላቸው መሆንና ጥንካሬን በማሳየት የምክር አገልግሎትን መስጠታቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊና ጠቃሚ ነው። የራስን የግል ልምምድ መሠረት በማድረግ ብቻ የምክር እርዳታ ለመስጠት ጥረት ከማድረግ ይልቅ የእግዚአብሔር ቃል ስለጋብቻና ስለፍች የሚናገረውን መሠረት በማድርግ ድጋፍ ለማድረግ መነሳሳታቸውም መልካም ነው።

በፍች ሂደት እያለፉ ያሉ ወገኖችን የእግዚአብሔርን ቃልና የቤተ ክርስቲያንን ውሳኔ በማሳወቅም እንደሚገባ ሳያገግሙ እና ተገቢ ባልሆነ መንገድ ከሌላ ሰው ጋር ግንኙነት እንዳይጀምሩ ማበረታታት እንዲሁም ለይቅርታና ለእርቅ እንዲዘጋጁ በእግዚአብሔር ቃል ማሳሰብ የመርዳቱ ሂደት አካል መሆን አለበት፡፡ ትክክለኛ ፈውስ ሳያገኙ ለችግራቸው ማስታገሻ ብለው በጥድፊያ ወደ ሌላ የትዳር ግንኙነት የመግባት እርምጃ እዳይወስዱ በመምከር ከሌላ ስህተትና ከከፋ ውሳኔ መታደግም አስፈላጊ ነው።

የፍች ቀውስ የፈጠረባቸውን የተለያየ መጥፎ ስሜት በውስጣቸው አምቀው ይዘው በቁጣ፣ በምሬትና በተሳሳተ ፍርድ ውስጥ እንዳይሆኑ ይልቁንም ስሜታቸውን እንዲገልጹና ለመጥፎ ስሜታቸው መፍትሔ ለማፈላለግ እንዲቻል ነፃ ሁነው እንዲቀርቡ ማበረታታት እንዲሁም የምክር አገልግሎት መስጠት አስፈላጊ ነው። ነገር ግን በአማካሪው ወይም እርዳታ በሚያደርገው ሰው ላይ ጥገኛ እንዳይሆኑ በመጠንቀቅ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ በእግዚአብሔር እውነተኛ ፍቅርና ምህረት ላይ ሙሉ በሙሉ እንዲደገፉ ማሳሰብና ወደ እግዚአብሔር እንዲቀርቡ መደገፍ ያስፈልጋል። ይህን ሁሉ እርዳታና የምክር አገልግሎት በመስጠት ወደ መፍትሔ የመድረሱ ጉዳይ ቅጽበታዊ አይደለም፡፡ ስለዚህ ከፍች ቀውስ የመውጣቱ ሂደት በፍጥነት መፍትሔ ያገኛል ብሎ ማሰብን በመቀነስ በችግሩ ውስጥ ባሉ ሰዎች ላይ ሌላ ችግርና መረጋጋት የሌለበት ተለያየ ስሜት ሲፈጠር ለመርዳት መነሳሳት አስፈላጊ ነው።





## 3. መዘርጋት፡- ከሌላ ወገን የወዳጅነትና የፍቅር እርዳታ እንዲያገኙ የግንኙነት መስመሮችን መዘርጋት

በፍች ቀውስ ውስጥ ያሉ ሰዎች ከሌላ ወገን የወዳጅነትና የፍቅር እርዳታ ሊያገኙ ይገባል የምንለው በመጀመሪያ የሰው ልጅ ሁሉ ፍቅርን መስጠትና ፍቅርን መቀበል የሚፈልግ ፍጡር እንደሆነ በመገንዘብ የፍቅር እንክብካቤ ሊያገኙ የሚችሉበትን ሁኔታ የማመቻቸትን አስፈላጊነት ለመጠቆም ነው። በፍች ሂደት የሚያልፉ ሰዎች ተቀባይነት፣ ፍቅርና እንክብካቤ የሚያሻቸው በመሆኑ ከቤተሰብ፣ ከወዳጅና ከቤተ ክርስቲያን የፍቅር እርዳታ ሊያገኙ ይገባል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ሊያገለግሉና ሊረዱ የሚችሉ ቡድኖችን በቤተ ክርስቲያን በማቋቋም ፍቅርን ገንቢ በሆኑ ቃላት፣ አብሮ የተመረጠ ጊዜን በማሳለፍ፣ የተለያዩ ስጦታዎች አቅም በፈቀደ መጠን በስጦታ መልክ በመለገስ፣ አብሮ በመጸለይና እነርሱን በማገልገል ፍቅርን መግለጽ አስፈላጊ ነው።

ፍችንና ዳግም ጋብቻን ቤተ ክርስቲያን ባታበረታታና እንዲለመድ የማድረግን አቋም ባታራምድም በፍች ሂደት ያለፉ ወገኖችን የፍች ምክንያት ግን እንደ እግዚአብሔር ቃል መመርመር አለባት፡፡ ፍችው በዝሙት ምክንያት ወይም ያላመነ የትዳር አካል ትዳሩን ትቶ በመሄዱ ምክንያት ብቻ የተፈጸመ መሆኑን እና አለመሆኑን በእግዚአብሔር ቃል መሠረት መመዘን ያስፈልጋል /**ማቴ 19፡ 3-9፣ 1ኛቆሮ 7፡ 10-13**/።

በእነዚህ ምክንያቶች ፍች የፈጸሙ ወገኖች የሰሩት ኃጢአት ባይኖርም በተለያዩ የቀውስ ሂደቶች ውስጥ ማለፋቸው ግን አይቀሬ ነው፡፡ ስለዚህ በሌላ ምክንያት ፍች እንደፈጸሙ ሰዎች በፈጸሙት ፍች ምክንያት የመውቀስና የመገሰጽ እርምጃ ቤተ ክርስቲያን ባትወስድባቸውም ከገቡበት ሁለንተናዊ ቀውስና ሕመም እንዲያገግሙ ግን ሁለንተናዊ ድጋፍ ልታደርግላቸው ይገባል፡፡ በእነዚህ ነገሮች ምክንያት ፍች በሚፈጸምበት ጊዜም ቢሆን የመጀመሪያ እርምጃ ሊሆን የሚገባው ፍች እግዚአብሔር ከጥንቱ ለሰው ልጆች ያቀደው የሕይወት መስመር አለመሆኑን በመጥቀስ የልብ ጥንካሬያቸውን አስተካክለው ይቅርታ ማድረግ ከተቻለም መታረቅና ከትዳር ጓደኛቸው ጋር አብረው መኖር እንዲችሉ ጥረት የማድረግ ሂደት ነው፡፡

በፍች ሂደት ያለፉ ወገኖች ወደ ሌላ የትዳር ግንኙነት ለመግባት ሲያስቡ ቤተ ክርስቲያን ጉዳዩን እንደ እግዚአብሔር ቃል ሁሉም ምዕመናን በሚተዳደሩበት የቤተ ክርስቲያን ደንብና ስርዓት እንዲሁም የሚኖሩበትን አገር ሕግ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በጥንቃቄ በመመልከት ልትረዳቸው ይገባታል። ቤተ ክርስቲያን መበረታታት የሌለበትን ባለማበረታታት እንዲሁም መርዳት ባለባት ጉዳይ እንደ እግዚአብሔር ቃል ሚዛናዊነትን በመጠበቅ የጽድቅ አገልግሎት መስጠት ይኖርባታል።

በፍች ሂደት የሚያልፉ ወገኖችም ሌላ የትዳር ግንኙነት ለመጀመር መፍጠንን ሊያቆሙ ይገባል። መጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ ከተናገራቸው ምክንያቶች ውጭ በሆነ ምክንያት ፍች የፈጸሙ ጥንዶች የፈረሰውን ትዳራቸውን እንደገና በይቅርታና በእርቅ

ለመግንባት እንጅ ከሌላ ሰው ጋር ሌላ ትዳር ለመመሥረት መፈለግና መሞከር የለባቸውም፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ይህን አየስተምርምና!! ከተፈጠረ ጉዳት ለማምለጥ እንደገና ለሌላ የከፋ ችግር አልፈው እንዳይሰጡ በሰከነ አዕምሮ እንደ እግዚአብሔር ቃል ሊያስቡ፣ ስሜታዊ ሳይሆኑ ውሳኔ ሊወስኑና ለቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አገልጋዮች በመታዘዝ ሕይወታቸውን ሊመሩም ይገባል፡፡ ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርህ ነውና!!





## ለጥንዶች በግላቸውና በቡድን ለማጥናት የሚረዷቸው የውይይት ጥያቄዎች

## የምዕራፍ ሃያ ሶስት (23)

## የውይይት ጥያቄዎች

1. ከፍች ሂደት በኋላ አዲስ ቀጣይ ኑሮ መጀመር የሚለውን አሳብ እንዴት ትረዱታላችሁ?
2. ከፍች ሂደት በኋላ አዲስ ቀጣይ የሆነ ኑሮን መለማመድ ነውን? አስፈላጊ ከሆነ አስፈላጊነቱን
3. የሚያስረዱ ምክንያቶችን በመዘርዘር፣ አስፈላጊ ካልሆነ ደግሞ ለምን አስፈላጊ እንዳልሆነ ምክንያቶችን በማቅረብ በስፋት ተወያዩ።
4. ከፍች ሂደት በኋላ አዲስ ቀጣይ የሆነ ኑሮ መለማመድ እንዲችሉ የማገዝ አገልግሎት መስጠት የሚፈልገው ልዩ ጥንቃቄ ምንድን ነው?
5. በፍች ሂደት ያለፉ ወገኖችን በመርዳት ሂደት ያሉትን የተለያዩ የሕይወት ሂደቶችና ደረጃዎችን በመጥቀስ በእያንዳዳቸው ላይ በስፋት ተወያዩ።
6. በፍች ሂደት ያለፉ ወገኖች ከፍች ቀውስ አገግመው ወደ ፊት መራመድ እንዲችሉ ቤተ ክርስቲያን ምን ልታደርግ ይገባታል? ደግሞስ እንዴት ባለ መልኩ በመቅረብ አገልግሎት መስጠት ይገባል ትላላችሁ?
7. በፍች ሂደት ያለፉ ወገኖች ቢገጥሟችሁ ምን ማድረግ አለብን ትላላችሁ? ከዚህ ምዕራፍ የተረዳችሁትና ተግባራዊ እርምጃ ልትወስዱበት የሚገባው ነገር ምንድን ነው?

# ማጠቃለያ

## *ግጭትን በመፍታት ጤናማ የትዳር ግንኙነት እንዲኖር ጥንዶች ሊከተሏቸውና ሊለማመዷቸው የሚገቡ አሰርቱ መርሆዎች*

1. **መጀመር፡-**ማንኛውንም ሁኔታ እግዚአብሔርን ከመፍራት፣ ከማስቀደምና ከማክበር መጀመር፣
2. **መወሰን፡-** ማንኛውንም የትዳር ውሳኔ ከመወሰን በፊት የእግዚአብሔርን አሳብ በመረዳት መወሰን እንዲቻል በጸሎትና በቃሉ በኩል ወደ እግዚአብሔር መቅረብን በቋሚነት መለማመድ፣
3. **መመለስ፡-** በአለመግባባትና በግጭት ወቅት ወደ ኋላ በመመለስ የጋብቻ ቃል ኪዳንንና ያለፉትን የፍቅር ጊዜያቶች ማሰብ፣
4. **መረዳት፡-** ላለመግባባትና ለግጭት ከሚዳርጉ ችግሮች ይልቅ የትዳር አጋር እንደሚበልጥ በመረዳት ትኩረት ማድረግ፣
5. **መመካከር፡-** ግጭትን በጋራ ለመፍታት በመቀመጥ ወቅት ለመከራከር ሳይሆን ለመመካከር ራስን ማዘጋጀት፣
6. **መቀበል፡-** ስህተትንና ጥፋትን አምኖ በመቀበል፣ ኃላፊነት መውሰድን፣ ይቅርታ መጠየቅንና መቀበልን የዕለት ልምምድ ማድረግ፣
7. **መመዘን፡-** ነገሮችን ለትዳርና ለቤተሰብ ከሚሰጡት ጥቅምና ሊፈጥሩት ከሚችሉት አሉታዊ ተጽዕኖ አንጻር በእግዚአብሔር ቃል ዘወትር መመዘን፣
8. **መማር፡-** በየጊዜው በግጭቶች በመመረር ሳይሆን በመማር ወደሚቀጥለው የሕይወት ጉዞ መሸጋገር፣
9. **መገንዘብ፡-** ትዳርና ቤተሰብ ከሌሎች ማሕበራዊ ግንኙነቶች ሁሉ በፊትና በላይ ከፍተኛ የሆነ ትኩረት የሚያሻው ተቋም መሆኑን መገንዘብ እንዲሁም:
10. **መፈለግ፡-** የሌሎች ሰዎች እርዳታ በሚያስፈልግበት ወቅት ከትክክለኛ ሰዎች በትክክለኛ ጊዜ ትክክለኛ የሆነ እርዳታ ለማግኘት ጥረት ማድረግ ብልህነት መሆኑን ሁልጊዜ ማስታወስ!!





# ዋቢ መጽሐፍት


1. Addis Ababa Bible Collage (ABC). Marriage Course Class Lecture: Addis Ababa, Ethiopia 2002.
2. Africa communitties Public health Coalitaion. Flyer about Depression. Los Angeles, CA 2013.
3. Arno, Richard G. Temperament Theory: Published by National Christian Counselour Assosation (NCCA) Sarasota, Fl 1994.
4. Bob Burns and Tom Whiteman. The fresh start divorce recovery. Published by Thomas Nelson Inc Nashvil, Tennessee, 1992.
5. California Courts the jugdical branch of California Responding to Divorce or Separation divorce or Separation selfhelp, http://www.courts.ca.gov/1034.htm Accsesed Oct.10, 2014.
6. Chapman, Gary. Marriage Works helping couples God's way, publishing light university: Forest, Virginia, 2011.
7. Clinton, Tim & Trent, John. The Quick-Reference Guide to Marriage and Family Counseling, Baker books, a division of baker publishing Group: Grand Rapids, Michigan, 2009.
8. Clinton, Tim & Hawkins, Ron. The Popular Encyclopedia of Christian Counseling, Harvest House Publishers: Eugene, Oregon, 2011.
9. Clinton, Tim & Laaser, Mark. The Quick-Reference Guide to sexuality and relationship counseling Baker books, a division of baker publishing Group: Grand Rapids, Michigan, 2010.
10. Clinton, Tim. The Bible for Hope, Caring for people God's way. Thomas Nelson: Nashvil, Tennessee, 2001.
11. David M. Ephraim. The Five Levels of Communications http://www.touchoffaith.org/family_ministry/communication/five_levels. Htm: accessed Feb.12, 2014.
12. Donald C. Stamps. The Full life study Bible New International Version. Zondervan Publishing House: Grand Rapids, Micigan 1991.
13. Dr. Tedla Woldegiorgis, Mental health Training handout. African communities Health Coltation 2013.
14. Focus on The Family, The first Five Years of Marriage: Tyndale House publishing Inc Carol stream: Illinois, 2006.

15. http://www.focusonthefamily.com/parenting/effective-biblical-discipline/approaches-to discipline/approaches-to-discipline-ageappropriate-discipline Visited 12/30/2014.
16. Focus on the family: Taken from *Effective Parenting in a Defective World* published by Tyndale House Publishers, Inc. Copyright © 2006 by Chip Ingram. Visited 12/30/2014.
17. Gary & Barbara Rosberg with Ginger Kolbabathe. The 5 sex needs of men and women Tyndale House publishing Inc Carol stream: Illinois, 2006
18. Gregory A. Kuhlman. Marriage facts. Stages of marriage: http://www.stayhitched.com/stages.htm accessed March 25, 2014.
19. Hunt, June. Counseling Through your Bible Handbook. Harvest house publisher: Eugene, Oregon 2008.
20. Jason Howerton, The Difference Between Men and Women's Brains Revealed? http://www.theblaze.com/stories/2013/12/02/the-difference-between-men-and-womens-brains-revealed Dec. 2, 2013 accessed March. 26, 2014.
21. Jason Howerton, The Difference Between Men and Women's Brains Revealed? Dec.2, 2013 accessed March. 26, 2014
22. Joseph warren kniskern when the vow breaks: B & H Publishing group: Nashville, Tennessee, Revised and updated 2008.
23. ከበደ በከሬ, የትዳር ግጭት መፍቻ ስልቶች : መካነ ኢየሱስ የምስራች ድምፅ ኅትመት መገናኛ ዘዴ ክፍል፡ አዲስ አበባ, ኢትዮጵያ 1999 ዓ.ም
24. Mack, A. Wayne. Strengthen your Marriage: P & R Publishing: Phillipsburg, New Jeresy 1999.
25. Senait Fisseha MD, Associate Professor, Obstetrics & Gynecology EBS Helen Show June, 28. 2013.
26. Steve Grissom and Kathy Leonard. Divorce care. Thomas Nelson Inc: Nashville, Tennessee 2005.
27. Wright, H Norman, Crises Counseling. Regal books: Ventura, California, 1993.
28. Wright, H Norman, Marital Counseling. Harper & Row Publisher: San Francisco, California, 1983.
29. Wright, H Norman. Communication key to your marriage. Regal books: Ventura, California, 2000.







30. http://www.samfunnskunnskap.የልጅነት ግዜ፣ የልጆች ህግና የልጆች መብት ጥበቃ accsesed Feb.06, 2014.
31. *my.cbn.com/.../display.php?topicid* Biblical Models of Functional and Dysfunctional Families Accsesed Apiril 23, 2014.
32. www.faiththerapy.org/answer-by-topic-disfunctional and healthy familes Accssed Apiril 13, 2014.
33. Women and Global Human Rights. http://www2.webster.edu/~woolflm/fgm.htmlFemaleGenitalMutilation accesed 05/20/2014
34. ከዶ/ር ዓብይ ዓይናለም Medina/መዲና June 2012 volume II No. 4 ሰኔ 2004.
35. የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር. የአማረኛ መጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት. አዲስ አበባ በባናዊ ማተሚያ ቤት ታተመ 1992 ዓ.ም
36. የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል. አማረኛ መዝገበ ቃላት፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡ አዲስ አበባ 1993 ዓ.ም
37. የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሕግ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ አዲስ አበባ, ኢትዮጵያ 1992 ዓ.ም.
38. http://ethiopia.thebeehive.org/content/205/2483 ፖስትፓርተም ዲፕሬሽን Accsesed Oct,11,2014.
39. ዶ/ር ብርሃኑ ሰንደቀ የጽንስና የማሕጸን ሕክምና ስፔሻሊስት. ኢትዮጵያ ብሮድ ካስቲንግ ኮርፖሬሽን (EBC)ጤናዎ በቤትዎ "ቅድመ እና ድህረ ወሊድ ክትትል ዙሪያ የቀረበ ውይይት" ነሐሴ 03 / 2006 ዓ.ም Acceseed Oct.10.2014.
40. በኤፌድሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የጸደቀ. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሳያዊ ሪፐብሊክ ብሔራዊ የሰብዓዊ መብት የድርጊት መርሃ- ግብር 2005-2007 አዲስ አበባ 2005 ዓ.ም http://www.abyssinialaw.com/ Accsesed Oct.11, 2014.
41. ከሶስት ከተለያዩ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ጋብቻ አማካሪ በቃል በመጠየቅ የተገኘ መረጃ, ግንቦት 2014.
42. የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር. መጽሐፍ ቅዱስ የቀድሞው ትርጉም በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ አዲስ አበባ, ኢትዮጵያ 1962 ዓ.ም

## ስለ ጸሐፊው

ከጌታ ለተቀበሉት የአገልግሎት ጥሪ ምላሽ በመስጠት እ.እ.አ 1993 ዓ.ም በጎንደር ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን ሙሉ ጊዜያቸውን በመስጠት አገልግሎት የጀመሩና ከዚያም ለተወሰኑ አመታት በሙሉ ጊዜ አገልጋይነት ከዚያም የቤተ ክርስቲያኗ መጋቢ በመሆን አገልግለዋል። በዚህ የአገልግሎት ወቅታቸው በተለያዩ ወረዳ ከተማ በቤተ ክርስቲያኗ ሥር የነበሩ ኅብረቶችን ተዘዋውሮ በማገልገል፣ የጎንደር አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት በምክትልና በዋና ሰብሳቢነት በመምራት፣ የሰሜን ምዕራብ ቀጠና ሙሉ ወንጌል አማኞች አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የቦርድ አባል፣ በተለያዩ ቦታዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት ተጋባዥ አስተማሪ በመሆንና በተለያዩ ጌታ በከፈተላቸው በሮች ሁሉ በመስበክ፣ በማስተማር፣ በማሰልጠንና በማማከር አገልግሎት ሰጥተዋል።

ፓስተር ዶ/ር ሙላቱ በላይነህ ለትምህርት ካላቸው ስፍራና ናፍቆት የተነሳ እ.እ.አ በ1998 ከኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል መጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ በዲፕሎማ፣ በ2002 ከአዲስ አበባ መጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ ቢ.ቲ የመጀመሪያ ዲግሪ፣ ከአገር ቤት በመውጣት በ2008 ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማስተርስ ኦፍ ዲቭኒቲ (M.DIV) በ2010 ዶክትሬት ዲግሪያቸውን (D.MIN) ዶክትሬት ኦፍ ሚኒስትሪ ጋብቻና ቤተሰብ ላይ በማተኮር) የተማሩ ሲሆን ከዚያም በመቀጠል ላይሰንሰድ ክሊኒካል ፓስቶራል ካውንስለር መሆን የሚችሉበትን የትምህርት ዕድል በማግኘትና ( LCPC) በመሆን በማማከርና አገልግሎት በመስጠትና  በሀበሻ አብያተ ክርስቲያናት የማማከር አገልግሎት እንደሚገባ ሥራ ላይ እንዲውል መጽሐፍ ቅዱሳዊ፣ ክሊኒካል፣ ክርስቲያን ስነ ልቦናና ተግባራዊ በሆነ መንገድ በማስተማር፣ በማሰልጠንና በማማከር እየተንቀሳቀሱ  ይገኛሉ።

ከአሁን በፊት " ***የአግልግሎት ተግዳሮቶችና መፍትሔዎቻቸው*** " በሚል ርዕስ ለአንባቢያን ያበረከቱ ሲሆን አሁን ደግሞ " የግጭት መንስኤዎችና መፍትሔዎቻቸው በጋብቻ ውስጥ !" በሚል **ቅጽ-**፤ " **በመጀመሪያዎቹ አስርተ ዓመታት የጋብቻ ዘመናት ላይ ሊፈጠሩ የሚችሉ ግጭቶች፣ የግጭት መንስኤዎችና መፍትሔዎቻቸው!**" በሚል ንዑስ ርዕስ ለአንባቢ ይዘው ቀርበዋል። እግዚአብሔር ቢፈቅድና ብንኖር ደግሞ " **የወጣቱ ትውልድ ዕድሎችና ፈተናዎች!**" በሚል ርዕስ የወጣቶችን የተለያዩ ዕድሎችና የሚገጥማቸውን የተለያዩ የዘመኑ ተግዳሮቶች፣ ለፈተና ተጋላጭ ሊያደርጋቸው የሚችለውን በመግለጥ የሚሞግት መጽሐፍ ነው። መጽሐፉ በወጣቶች በተለያዩ ሱስና የተበላሸ ስነ ምግባር መኖር በራሳቸው በወጣቶች፣ በቤተሰብ፣ በቤተ ክርስቲያን፣ በሕብረተሰቡና በአገር ደረጃ ሊያመጣ ያለውን ከፉ ተጽዕኖ በግልጥና በዝርዝር በማስቀመጥ ይመክራል። በዚህ ወጣቱን ትውልድ ለማትረፍ ወጣቶችን፣ ወላጆችን፣ ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችን፣ መንፈሳዊ፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን የሚነካ፣ የሚያስተምር፣ አቅጣጫ የሚያሳይና ለወጣቱ ትውልድ መልካም





ሕይወትና ስነ ምግባር መኖር እንዴት በጋራ መረባረብና መሥራት እንዳለብን የሚጠቁም መጽሐፍ ነው።

ኑሯቸውን በሰሜን አሜሪካ በካሊፎርኒያ ግዛት በሎስ አንጀለስ ከተማ ያደረጉ ፓስተር ዶ/ር ሙላቱ ባለትዳርና የሁለት ወንድ ልጅ አባት ናቸው። ይህን መጽሐፍ ለአንባቢ ማቅረብ ብቻ ሳይሆን የትዳር ዘመናቸው በዚሁ የጋብቻ ዘመን ከመሆኑ የተነሳ እንደ ማንኛውም ባለትዳር ተጠቃሚ፣ በኑሮ እየተፈተኑና እየተለማመዱት የሚሄዱት እንደሆነ ይገልጻሉ። ዶ/ር ሙላቱ በላይነህ በኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ኅብረት ቤተ ክርስቲያን ሎስ አንጀለስ አባልና በዚች ቤተ ክርስቲያን በመስበክ፣ በማስተማር፣ የቤተሰብና የማማከር አገልግሎት ዘርፍ ከሌሎች ጋር በሆን በማገልገል ይገኛሉ። ዶ/ር ሙላቱ ካላቸው ሸክም አንጻር ወደ አገር ቤት በመመላለስ በመስበክ፣ በማስተማር፣ አገልጋዮችን በማስተማር፣ በማሰልጠንና በተለያዩ ነገሮች በመደገፍና በማገልገል ይገኛሉ።

## ደስተኛና ጤነኛ የሆነ የትዳርና የቤተሰብ ግንኙነት ለሁላችን ይሁን !!

ጥያቄና አስተያየት ቢኖርዎ በሚከተለው አድራሻ ይጻፉልን

ናታን የጋብቻና የቤተሰብ የማማከርና የማሰልጠን አገልግሎት
Nathan Marriage and Family Counseling and Training Ministry
Email:-pmulatu@yahoo.com or nmfcml@gmail.com
Phone:-323-898-6200